# የመደመር መንግሥት

ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር)

CamScanner

# መግቢያ

“የኢትዮጵያውያንን ሕይወት መለወጥ!" የሚለው ሐሳብ ለዘመናት በተፈራረቁ መንግሥታትና ትውልዶች ዘንድ እንደ መፈክር የሚነሣ ሐሳብ ነው። ነገር ግን በዘመናት ውስጥ ያደረግናቸው ሙከራዎች ብዙም ፈቀቅ አላደረጉንም። የሕይወት ለውጥ እንደ ሕልም ርቆን እንደ ጉም የማይጨበጥ ውጥን ሆኖብን ቆይቷል። ይልቁንም በአንዳንድ ውሳኔዎቻችን ምክንያት ውስብስብ ለሆኑ ሥጋቶች ተጋልጠንና ችግሮችን ተጋፍጠን ኖረናል። ለመበልጸግ የሚያስችለን ዕምቅ ዐቅም እንደተሸፈነ፤ ሳንጠቀምበት፤ እዚህ ደርሰናል። የሕዝብን ሐሴትና ደኅንነት ለማረጋገጥ የሚያስችል የዕድገትና የሥልጣኔ ደረጃ ላይ መገኘት ከፍላጎትነት አልፎ ወደ እውነታነት ሳይቀየር ዘመናትን አስቆጥሯል።

ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የሀገርነት ታሪክ ያላት ሀገር ናት። ነገር ግን የሕዝብን ተድላና ምቾት ማረጋገጥ ትልቁ ፈተናዋ ሆኖ ለዘመናት ዘልቋል። ሀገራችንን ለመለወጥና የከፍታ ጉዞ ለማስጀመር የተሞከሩ በርካታ ጥረቶች ባክነው ቀርተዋል። በእነዚህ የባከኑ ጊዜያት ችግሮች በጊዜያቸው ባለመፈታታቸው ተወሳስበዋል። ዕድሎችና አጋጣሚዎች በጊዜያቸው ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው መክነዋል። ይህም በችግርና በድህነት አዙሪት ውስጥ እንድንቆይ አደረገን። ዛሬ ዓለም ከደረሰበት መድረስ እንዳንችል አሠረን። ነገም ዓለም ሊጨብጠው ከሚንደረደረው ለመድረስ እንዳንችል ዐቅማችንን እያመነመነ፤ ከዛሬና ከነገ ወደ ኋላ እንድንቀር አድርጎናል። ዛሬ ላይ በሁለት ግዙፍ የቤት ሥራዎች አጣብቂኝ ውስጥ ነን። ትናንት ባለመታረማቸው ሥር እየሰደዱ የመጡ ፈተናዎቻችን የፈጠሩብን ዕዳ በአንድ በኩል፤ ለነገ ትውልድ ያለብን ኃላፊነት ደግሞ በሌላ በኩል ቆመዋል።

የኢትዮጵያ ችግሮች መነሻቸው መልከ ብዙ፤ ጥልቀታቸውም ከዘመን ዘመንና ከቦታ ቦታ የተለያዩ ናቸው። ይሁንና ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ዋነኞች ሆነው ሊጠቀሱ ይችላሉ። አንደኛው ችግሮችን ለመቅረፍ የተመረጡ አብዛኞቹ መንገዶች ውሱንነት የነበረባቸው መሆናቸው ነው። መንገዶቹ በአብዛኛው መፍትሔን ሳይሆን የበለጠ ችግርን እየወለዱ ሀገራችንን አረንቋ ውስጥ የሚከቱ ሆነዋል። ሁለተኛው ከሄድንበት መንገድ ውሱንነትም ባሻገር፣ አደግን ባልን ጊዜ የተጓዝነው ጉዞ የዔሊ ጉዞ መሆኑ ነው። በዚህም የተነሣ የፈጠርነው መሻሻልና ዕሴት ካለብን ችግርና ሥጋት ጋር አይመጣጠንም። የተጓዝነው መንገድ መድረስ ከሚጠበቅብን ምዕራፍ በእጅጉ የራቀና አዝጋሚ ነው።

ኢትዮጵያ አብዛኛው የሕዝብ ክፍላቸው ወጣት ከሆኑና ከፍተኛ የሕዝብ ዕድገት እያስመዘገቡ የሕዝብ ፍላጎት መመለስ ይጠበቅባታል። ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም አቀፍ ሁኔታ ውስጥ ካሉ ሀገራት አንዷ ናት። በዚህም የተነሣ በየጊዜው እየተለዋወጠና እያደገ የሚመጣውን ዋኝታ ከድህነት መላቀቅና ወደ ዕድገትና ብልጽግና ጉዞ መጓዝም ይገባታል።

ለውጥና ዕድገት ማምጣት ያልቻሉ ሥርዓቶች ይረበሻሉ፤ ይመሰቃቀላሉ። በሂደትም ወደ መበስበስ ያመራሉ። በመረበሽና በመበስበስ ውስጥ ለሚገኙ ሀገራት፣ ከነበሩበት ሁኔታ ለመላቀቅ አዝጋሚው መንገድ አያዋጣቸውም። የኋላውን ሲያስተካክሉ አሁናዊው ይደርስባቸዋል፤ አሁናዊውን ሲያሸንፉ ደግሞ በፊተኞቹ በርቀት ይቀደማሉ። ስለዚህም የሦስቱን ምዕራፍ ችግሮች በአንድ ላይ ፈትተው ለውጥን ለማስመዝገብና ሥርዓታዊ ጥንካሬን ለማምጣት፣ የግድ አዲስ መንገድና የተለየ ፍጥነት ያስፈልጋቸዋል፡

የድህነት ወይም የብልጽግና ደረጃ የሁለት ነገሮች ድምር ውጤት ነው። የመጀመሪያው ሀገራት ምን ያህል ዕምቅ ዐቅሞች አሏቸው? የሚለው ነው። ሁለተኛው ደግሞ እነዚህን ዐቅሞች መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት ዘርግተዋልን? የሚለው ነው። አሁን ላይ በኢኮኖሚ ለምተው፣ በፖለቲካ በስለውና ማኅበራዊ ልማትን አረጋግጠው ከፊት በምንመለከታቸው ሀገራትና ብልጽግናን ለማረጋገጥ ከኋላ በቀሩ ሀገራት መካከል ያለው ልዩነት የዕምቅ ዐቅምና የሥርዓት ግንባታ ጉዳይ ነው።

CamScanner

ዐቅሞች ለማደግና ለመለወጥ ዕድል ይሰጣሉ። ሥርዓቶች ይህንን ዕድል በመጠቀም ችግሮችን ይቀርፋሉ። ተድላን፣ ምቾትንና ሀገራዊ ጥንካሬን ያረጋግጣሉ። ሀገራት በሰርክ ውድድር ውስጥ ናቸው። በአንድ መልኩ በየጊዜው የሚነሡ ሀገራዊ ጥያቄዎችንና ፍላጎቶችን ለመመለስ ይሮጣሉ። በሌላ መልኩ ለነገ የሚተርፍ ወረት ለማስቀመጥ በሚኖር የጊዜ እሽቅድምድም ይዋከባሉ። በዚህም ምክንያት ሀገራት ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥና ጠንክረው ለመውጣት ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀምና ተወዳዳሪነትን ማረጋገጥ አለባቸው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ዓለም ያካሄዳቸው ታላላቅ የኢንዱስትሪ አብዮቶች አምልጠውናል፡ ይህንንም ክፍተት ተጠቅመው ችግሮቻችን ሥር ሰደዱ፤ ፈረጠሙ። መልካም አጋጣሚዎችና ዕድሎች ደግሞ ኮሰመኑ፤ መከኑ። በእነዚህ በባከኑ ጊዜያት ውስጥ ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ተለውጦ በብዙ ርቆን ሄዷል። መድረስ ከሚገባን ቦታ እጅግ ኋላ ቀርተናል። ለዚህ አንዱ ማሳያም፤ ከዐድዋ አስደናቂና አስደማሚ ድል በኋላ፤ ጣልያን ለዐርባ ዓመታት ያህል ተዘጋጅቶና ተሻሽሎ ለበቀል ሲመጣ እኛ ባለንበት ቆመን ጠብቀነዋል። በዐድዋና በማይጨው መካከል ያለው የጊዜ ልዩነት ለጣልያን በብዙ ረገድ መሻሻል ፈጥሮለታል። እኛ ግን ከቀደሙት ዘመናት በተሻለ ለመለወጥ አንጻራዊ የተሻለ የሰላም ዕድል ቢኖረንም ብዙም አልሠራንበትም። በዐድዋ የተዋጋንበትን መሣሪያ እንኳን ለመለወጥ አልተጠቀምንበትም። ከጊዜ ጋር አልተራመድንም፤ ያመጣነው ለውጥም የተንቀራፈፈ ነበር። ይህ መንቀራፈፍና መዘግየት ደግሞ ዋጋ አስከፍሎናል።

መዘገየት ከኋላ አስቀርቶናል። የአንድ ሀገር ቀጣይነትና ጥንካሬ ሊመሠረት የሚችለው በሦስት ዓምዶች ነው። የመጀመሪያው ያሉበትን ጥያቄዎች በጊዜ መመለስ ሲችል ነው። ሁለተኛው ከነባራዊ የዓለም ሁኔታዎችና ለውጦች ጋር ተላምዶና ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት ዐቅም ሲኖረው ነው። በመጨረሻ ደግሞ ቀድሞ ለመገኘት የሚያስችል የተፎካካሪነት ችሎታ ሲኖረው ነው። ይህ ሳይሆን ሲቀርና ጥያቄዎችን ለመመለስ በዘገየንና በተንቀራፈፍን ቁጥር ችግሮች እየተወሳሰቡና እየተደራረቡ ይሄዳሉ። እንዲሁም ወደ ኋላ በቀረን ቁጥር ጫናው እየበረታብን ይሄዳል።

ለዚህም ሀገራችን የገባችበት የድህነት አዙሪት ዋና ማሳያ ነው። ጊዜውን ያገናዘበ መፍትሔ ለመስጠት ባለመቻላችን አንዱ በአንዱ ላይ እየተደራረበ፣ ችግር ችግርን እየወለደ፣ ዛሬ የተጋፈጥነውን ቀውስ ፈጥሯል። እንዲህ ሲሆን ለሀገራት የቤት ሥራው ከባድ ነው። ምላሽ የሚሰጥበት መንገድም ከፊት እንደ ቀደሙት አይደለም። የተለየ ፈጠራንና ፍጥነትን ይጠይቃል።

ፈጠራና ፍጥነት እንዲዳብር ደግሞ ሥርዓታዊ ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል። ምላሽ በመስጠት ሂደት ውስጥ የሁሉንም ተዋንያን ሚና ማሻሻልና በመካከላቸው ያለውን ቅንጅት ማሣለጥ የግድ ይላል። ለዚህ ደግሞ ፍጥነትና ፈጠራ በተሞላበት ጉዞ ተከታታይ ለውጦችን ማስተናገድ ይገባል። ሀገራችን ኢትዮጵያ ቀጣይነቷን ለማረጋገጥ በአንድ በኩል የባከነባትን ጊዜ ለማካካስ የሚያስችል ድርብርብ የቤት ሥራዎችን መሥራት አለባት። በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ ተለዋዋጭ ከሆነው ዓለም ጋር ተላምዳና ተወዳድራ መጓዝ የምትችል መሆን አለባት። በመሆኑም የሚያስፈልገን ለውጥ ብቻ ሳይሆን በፈጠራ የታጀበ ፈጣን ለውጥ ነው። አንደኛ፥ ተደራራቢ የቤት ሥራዎቻችንን መሥራት አለብን። ሁለተኛ፥ የባከነውን ጊዜ ማካካስ ይጠበቅብናል። ሦስተኛ፥ ተለዋዋጭ ከሆነው ዓለም አቀፍ ሁኔታ ጋር መራመድ የግድ ነው። አራተኛ፥ ዐቅሞችን ለመጠቀምና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ፈጣን ለውጥ ያስፈልገናል።

"የመደመር መንግሥት የመፍትሔውን መንገድ ያመላክታል። እስከዛሬ ውሱንነቶች ለማረምና ዘገምተኛውን ጉዞ ለማፍጠን የሚችል ቀመር ሆኖ መጥቷል። ከመደመር ዕሳቤ የሚቀዳው የመደመር መንግሥት ኢትዮጵያዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ዕሳቤ ነው። ሁለንተናዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚቻለው ትብብርን ያስቀደመ ሥርዓት በመዘርጋትና ፖሊሲዎችን ገቢር ነበብ በሆነ መንገድ አውጥቶ በቅንጅት በመተግበር ነው ብሎ ያምናል።

CamScanner

በለውጡ ዓመታት ውጥናችንን ለማሳካት የሄድንበትን መንገድ ቃኝተናል። ክፍተቶችንና ጥንካሬዎችን ለይተናል። ክፍተቶቹን አሻጋሪ በሆነ መልኩ የሚቀርፍ፤ ጥንካሬዎችን በተሻለ ሁኔታ የሚያስቀጥል፤ አዲስ ዕሳቤና አዲስ መንገድን ቀምረናል። መደመር ሀገር ከገባችበት ችግር በማላቀቅ፣ ወደ ትክክለኛው የለውጥ ምሕዋር የሚመራ ዕሳቤ ነው። የመደመር መንግሥት፣ ሀገራዊ ጸጋዎቻችንን በማቀናጀትና በማስተባበር ረገድ ካለው ሚና ባልተናነሰ፤ በፍጥነት የምንጓዝበትንም መንገድ የቀመረ አስተሳሰብ ነው።

የመደመር መንግሥት ነገን የተሻለ ለማድረግ የትናንት፣ የዛሬና የነገ ተደራራቢ ኃላፊነቶቻችንን በአስቸኳይ እንድንወጣ ያደርጋል። እንዲሁም ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም ሁኔታ ውስጥ፣ ጥንካሬያችንን ለማረጋገጥና ከግባችን ለመድረስ እንድንፈጥን ያስችላል። የመደመር መንግሥት ፍጥነትና ፈጠራን መሠረት ያደረገ ዕሳቤ ነው። የዚህ መጽሐፍም ዋነኛ ጭብጥ ይህንን የፍጥነትና የፈጠራ ፍኖት ማብራራት ነው።

ይህ መጽሐፍ የመፍትሔ ፍለጋ ቀጣይ ጥረት ሌላኛው ውልደት ነው። ሀገራችን ካለችበት የግርጌ ደረጃ ተስፈንጥራ ወደ ራስጌ መውጣት የምትችልበትን ሐሳብ የሚያቀብል ነው። በዋናነት የተረከብነውን የተከማቸ ችግር በፈጠራና በፍጥነት ለመፍታት እንድንችል የሚያደርግ የተሻለ ሥርዓት ስለመገንባት ያወሳል። ነገር ግን ይህንን ሥርዓታዊ ለውጥ ማምጣትና የፈጠራና ፍጥነትን ዐቅም ማካበት፤ ፈታኝ ይሆን ይሆናል። ፈታኝ የሚያደርጉት ያለንበት ጎታች የሆነ የፖለቲካ ገበያ እና ተያያዥ ማኅበራዊ ጉዳዮች ናቸው።

ፈጠራና ፍጥነት በሥርዓታት ለውጥ ላይ የተመሠረተ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ገበያ ሥርዓትን የሚያዳክም፣ ችግሮችን የሚያወሳስብና ዐቅሞችን የሚያመክን ኢመደበኛ ፖለቲካ ነው። ስለሆነም ይህ መጽሐፍ የፖለቲካ ገበያን እንዴት መቀየር እንዳለብን ሐሳቦችን ያቀርባል፡ ሀገራችንን ካለችበት ሁኔታ ወደ ብልጽግና ማማ ጫፍ ማሻገር፤ በዘመን አጋጣሚ የዚህ ትውልድ ኃላፊነት ሆኗል። ኃላፊነታችንን በሚገባ በመወጣት፤ ለልጆቻችን የበለጸገች ኢትዮጵያን ለማስረከብ በጋራ እንነሣ፡

መልካም ንባብ።

# ብያኔ

## 1. መደመር

CS CamScanner

የመደመር ፍልስፍና የሀገራችን መሠረታዊ ችግር የአስተሳሰብ ችግር ነው ብሎ ይነሣል። የዕድገት ጠንቅ ከሆኑ ደካማ አስተሳሰቦች የጸዳ አእምሮና ኅሊና መያዝ የብልጽግና መሠረት ነው ብሎ ያምናል። ማኅበራዊ ብልጽግናን ለማምጣት የማኅበረሰቦች የእርስ በርስ መፈላለግና መቀባበል የግድ ነው ይላል። ከታኅታይ መዋቅር (ኢኮኖሚ፣ መሠረተ ልማት፣ ወዘተ) ለውጥ ይልቅ ለላዕላይ መዋቅር (አስተሳሰብ፣ ባህል፣ ወዘተ) ለውጥ ቅድሚያ ይሰጣል።

መደመር የሚከፋፍሉ ዕሳቤዎችን (ዘረኝነትን፣ ጎጠኝነትን በማስወገድ ሰውን በሰውነቱ ከብሩና ነጻነቱ እንዲጠበቅ ማድረግ ነው። ከዜሮ ድምር ጨዋታ ወጥቶ በአንድነትና በአብሮነት መትመም፤ ባለን ላይ ዕሴት መጨመር ነው። ሁላችንም እናስፈልጋለን፤ የሁላችንም አበርክቶ አስፈላጊ ነው ብሎ ማመን ነው። መደመር የአንዱ ብሔረሰብ ከሌላው ጋር እንደ አካል መጋጠም ነው። የአቋም መሰባሰብ ነው።

መደመር ሁሉንም የዜጎች ፍላጎት ሳያበላልጥና ለአንዱ መከበር ሲል ሌላውን ሳይደፈጥጥ ሚዛን ጠብቆ የሚጓዝ ፍልስፍና ነው። በመደመር ፍልስፍና ርዕዮታችንን እውን ለማድረግ የምንከተለው መንገድ አቃፊነትን ነው። ሁሉም ዓይነት ሐሳብ የራሱ አስተዋጽዖ አለው፤ ጠንካራ ጎኑን ወስደን እንጠቀምበታለን። ሁሉም ዜጋ የራሱ አስተዋጽዖና ሐሳብ አለው፣ አቅርበን እናሳትፈዋለን። በውይይት የላቀው፣ በክርክር የተሻለው ይወሰዳል። የሀገራችን ሕዝቦች ዕሴቶች ተደምረው ሀገራዊ ዕሴቶች እንዲሆኑ፤ የሀገራችን ሕዝቦች ታሪኮች ተገናዝበው፣ ተጋጥመውና ተሟልተው የሀገራችን ታሪክ እንዲሆኑ፤ በአንድ አካባቢ የሚታወቁ የሀገራችን ጀግኖች ወሰን ተሻግረው የሁሉም ሕዝብ ጀግኖች እንዲሆኑ፤ በውይይት፣ በመግባባት፣ በጥናትና በትርክት ጎልተው የሚወጡ፤ ሁላችንንም የሚያስተባብሩ ሀገራዊ ትእምርቶች እንዲኖሩ የሚያስችል ነው፤ መደመር።

መደመር መደፍጠጥን አይቀበልም። ሕዝብን በአንድ የሐሳብ ቅርጫት ውስጥ መክተትን ፈጽሞ አይቀበልም። በብዙ ነገር ወደ ኋላ ስለቀረን ብዙ ዓይነት ሐሳብ ያስፈልገናል ብሎ ያምናል። በተመሳሳይ ጫፍ የረገጠና የሀገሪቱን ህልውና የሚፈታተን ማንኛውም የመከፋፈል አዝማሚያ በጠንካራ የሕግ የበላይነትና በተቋማት ብርታት ወደ መሥመር እንዲገባ መደረግ አለበት ይላል። ከላይ የጠቀስነውን የህልውና ፍላጎት የምናሳካው ሥርዓትን በሚገባ የሚያውቅ ሕዝብና ሀገር ስንፈጥር፤ ይህም ሥርዓት የሚያውቅ ሕዝብ የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክት እንደየአመጣጡ ስናቅፈው ነው።

መደመር የህልውና ጥያቄዎቻችን በገበያው ጡንቻ ወይም ደግሞ በመንግሥት ጉድለት ብቻ የሚመካኝም አይደለም። ከገበያ ውጭ በኢኮኖሚው ላይ የሚሳተፈው የሲቪል ማኅበረሰቡም ብቻውን ሊፈታው የሚችል ችግር አይደለም። ጤናማው አካሄድ ጡንቻ የሚፈቱ አይደሉም ብሎ ያምናል። ችግራችን በገበያ ጉድለት ወይም በመንግሥት በመቀራረብ፣ በሚፈጥሩት ፍትጊያና መተቃቀፍ የሚገኘው ውኃ ልክ ወይም ሚዛን ነው። በአጠቃላይ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ሚና የሚጫወቱ አካላት በመሳሳብና የመንግሥት ሚናም ይህን ውኃ ልክ ለማስጠበቅ፤ በአንድ በኩል እንደ አንድ ባለ ድርሻ ሚናውን መጫወት፤ በሌላ በኩል ፍትጊያው ወደ መበጠስ ወይም ወደ ጭፍለቃ እንዳይሄድ መጠበቅ ነው። ይህ መንገድ ጎራ ይዞ እንደ መትመም ቀላል አይደለም። ነባሩ የርዕዮተ ዓለሞች አዝማሚያ እጅግ ምናባዊ በሆነ ተምኔት የተጠመደ ነው። መደመር ግን ከጥናትና ከነባራዊ ሁኔታው መንጭቶ፣ በዚህ ተለዋዋጭና ሊተነበይ በሚያስቸግረው ዓለም ውስጥ በንቃት የሚቆም ነው። ስለዚህም በአንድ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ነቁጥ ላይ የምትወሰድ እያንዳንዷ ርምጃ በጠቅላላ ሥርዓቱ ላይ ያላትን ተጽዕኖ በመመዘንና ሚዛኑን እንዳታዛባ በመጠንቀቅ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

ሚዛን አለመጠበቅና የአንዱን ጡንቻ ብቻ ማዳበር በዓለም ታሪክ ውስጥ ሀገራትን ከጥግ ጥግ ሲያላጋቸውና ሲያደነባብራቸው አይተናል። በአንዱ በኩል ሚዛን ስንጥል በሌላ በኩል ያለው ለጊዜው የተሸነፈ ቢመስልም በውስብስቡ ሥርዓት ውስጥ አድፍጦ ኃይል ያጠራቅማል፤ ከዚያም ጊዜና ሁኔታ የገጠመው ዕለት በድንገት ተነሥቶ፤ በተራው ሌላውን

CamScanner

ጨፍልቆ ሚዛኑን ይቆጣጠራል። ስለዚህም በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ሁሉንም ማቀፍና ሚዛን ማስጠበቅ የመደመር አንዱ የሐሳብ ምሰሶ ነው።

ውኃ ልኩ ወይም ሚዛኑ ከተፈጠረ ዕድገቱን ምንም የሚያውከው መንገዳገድ አይኖርም። በሰው ልጆች የፍላጎት ነዳጅ ብቻ ተፈትልኮ ይመነደጋል። ሚዛንን ሳይጠብቁ መመንደግ አይቻልም። በመንገዳገድ ውስጥ የሚኖር መንደርደር መሮጥ አይደለም፤ የሆነ ቦታ ላይ ይጥለናል። ተግተን እንዳንሠራና ከኋላ ቀርነትና ከህልውና አደጋ አዙሪት እንዳንላቀቅ ያደረገን የመበልጸግ ፍላጎትና ጥረት ማጣት አይደለም። ሚዛን ያልጠበቀ እና ፈጠራና ፍጥነት የሌለው ጉዞ መጓዛችን እንጂ። ስለዚህም መደመር በሁሉም መንገድ አቃፊና ውኃ ልክን የሚፈጥር ፍልስፍና ነው።

ይህ አስተሳሰብ ብዝኃ ሕይወትን እንደማስጠበቅ ያለ በነገሮች መካከል ያለን ውስብስብ የተደጋጋፊነትና የተቀናቃኝነት መስተጋብር ታሳቢ የሚያደርግ ነው። መንገዱም የንቃትና የተግባር መንገድ ነው። አንዴ ሥርዓትን ተክሎ የማሸለብ ልማድን የሚተካ የንቃት ፍልስፍና ነው።

በአጠቃላይ፣ መደመር ሁሉንም የህልውና ፍላጎቶች በሚዛን የሚያስጠብቅ ነው። በፖለቲካዊ ኢኮኖሚው ውስጥ ሚና ያላቸው አካላት ለሚፈጥሩት ጉድለት፡ የተዛባ የጊዜ ዕይታችን ነዳጅ ሲጨምርለት፤ እነዚህን የህልውና ፍላጎቶች ለመጠበቅ አስቸጋሪ ይሆናል። ሕልማችንም ሚናችንም በጊዜ ዕይታችንና በጊዜ ምጠናችን ላይ የተመሠረተ ነው። የመጣንበትን፣ ያለንበትንና የምንሄድበትን መጥነን በመመልከት ኃያልና የማትበገር፣ በዚህም ህልውናዋን በአስተማማኝ ሁኔታ ጠብታ የምትዘልቅ ኢትዮጵያን እንፈጥራለን'። መደመር ስንል በላዕላይ መዋቅር ለውጥ ላይ የሚያተኩር፤ የዐቅም፣ የዕሴት፣ የጸጋ፣ የዕድል፣ የሀብት፣ ወዘተ መሰባሰብን የሚያመጣ፤ በሁሉም የፖለቲካ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና ዲፕሎማሲያዊ የሀገር ጉዞዎች ሚዛን ጠብቆ የሚጓዝ፣ ሁሉንም የሚያስተባብሩ ሀገራዊ ትእምርቶች እንዲኖሩ የሚሠራ፣ አቅፎ በሚዛን መጓዝን እንጂ መደፍጠጥን የማይቀበል፣ የሀገሪቱን ህልውና የሚፈታተን ማንኛውም የመከፋፈል አዝማሚያ በጠንካራ የሕግ የበላይነትና በተቋማት ብርታት ወደ መሥመር እንዲገባ የሚሠራ፣ በአጠቃላይ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ሚና የሚጫወቱ አካላት በአንድ በኩል በመሳሳብና በመቀራረብ - በሌላ በኩል በሚፈጥሩት ፍትጊያና መተቃቀፍ መካከል የሚገኘው ውኃ ልክ(ወርቃማው አማካይ) ወይም ሚዛን ነው ብሎ የሚያምን፤ የጊዜ ዕይታው የመጣንበትን፣ ያለንበትንና የምንሄድበትን አጣጥሞ የሚመለከት፤ ፍልስፍና ነው።

## 2. መንግሥት (State)

በዚህ መጽሐፍ አገባብ መንግሥት (State) ስንል "በሕግ የሚሠራ በአንድ በታወቀ አካባቢ ውስጥ በሚገኝ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ፣ የመጨረሻ የሆነ ሥልጣንና ሉዓላዊነት ያለው፣ ሕግ የሚያወጣ፣ ሕግ የሚያስከብር፣ ዳኝነት የሚሰጥ፣ ጸጥታና ደኅንነት የሚያስጠብቅ፣ ከሌላ ሉዓላዊ ግዛት ጋር በአቻነት መነጋገር የሚችል፣ ፖለቲካዊ ተቋም ነው። በሥሩም አያሌ ሕጋዊ ቅርንጫፎች ይኖሩታል" ።

መንግሥት እስካሁን የሰው ልጅ ከፈጠራቸው ማኅበራዊ ተቋማት ሁሉ እጅግ ዓለም አቀፋዊ እና ኃያል ተቋም ነው። አሪስቶትል "ሰው በተፈጥሮው ፖለቲካዊ እንስሳ ነው፤ ስለዚህም ፖለቲካዊ ሰብእና አለው። ሰው መሆንና በመንግሥት ውስጥ መኖር የማይለያዩ መንትያዎች ናቸው" - ይል ነበር። እንደ አሪስቶትል ከሆነ መንግሥት ማለት፣ "የቤተሰቦችና የመንደሮች ኅብረት ነው።

ግቡም ፍጹምና ራስን በራስ የሚያስችል ሕይወት መፍጠር ነው። እርሱም ደስተኛ መልካም የሆነ ሕይወት ነው። አስቶትል መንግሥት የሚለውን ሲያስብ የግሪክ የከተማ መንግሥታትን እያሰበ ነው።

CS CamScanner

ውድሮ ዊልሰን ደግሞ "መንግሥት ማለት በአንድ በታወቀ ግዛት ውስጥ በሕግ የተደራጁ ሰዎች ናቸው ። ይላል። ሲጅዊክ መንግሥት የሚለውን ሐሳብ ሲተረጉም "ንግሥት ማለት ፖለቲካዊ የሆነ ማኅበረሰብ ነው። መንግሥት የሰው ልጆች አንድነት ሲሆን፣ ማኅበራዊ አንድነቱም ለአንድ ዕውቅና ለሰጡት የበላይ ሥልጣን ላለው አካል በላቸው. የጋራ ታዛዥነት ነው። ያም የበላይ ሥልጣን ያለው አካል በአንድም በሌላም መንገድ ያለ | ማኅበረሰብ የሚወክል ነው።” ለጋርነር ደግሞ “መንግሥት ማለት በአንድ በታወቀ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ማኅበር፣ ከውጭ ቁጥጥር ነጻ የሆኑ ሰዎች በአብዛኛው የተግባቡበትን አስተዳደር የመሠረተ ተቋም ነው።

ፈላስፋው ሄግል "መንግሥት ማለት በአንድ ማኅበራዊ ዕቅድ ውስጥ፣ የአመክንዮአዊ ህላዊ ወይም የመንፈስ ክሥቱነት ከፍተኛው ደረጃ ነው። የመንግሥት የመጨረሻ ግቡም ነጻነትን ህልው ማድረግ ነው" ይላል። ለሄግል የመንግሥት ዋናዎቹ መርሖች ራስን ማቀብና ፍጹማዊነት ናቸው። ለሄግል “ብሔረ መንግሥት የመጨረሻው አመክንዮአዊ ነገር ነው:: በአንድ ግለሰብ፣ በቡድኖች ወይም በኮርፖሬሽኖች ደረጃ ሊደረስበት የሚችል ከፍተኛ የሆነ የምክንያታዊነት መገለጫ ነው። ለሄግል ሦስቱ የመንግሥት ሥልጣኖች ሕግ አውጪው የአስተዳደር ዘርፉ እና ንጉሣዊነቱ ናቸው። ከሦስቱ ደግሞ ንጉሣዊ ሥልጣን እጅግ ወሳኙ ሥልጣን ነው ይላል። በአሁኑ መንገድ ፕሬዚዳንታዊው ወይም ጠቅላይ ሚኒስትራዊው ሥልጣን ልንለው እንችላለን።

የ9ኛው መክዘ የጀርመን ኢኮኖሚስት፣ ፈላስፋና የሥነ ማኅበረሰብ ሊቅ ማክስ ዌበር፣ መንግሥት የሚለውን ሐሳብ በሁለት መንገድ ይገልጠዋል። የመጀመሪያው “መንግሥት ማለት በአንድ በተወሰነ ግዛት ውስጥ ሥልጣን ያለው ራሱን የቻለ ሕጋዊ የአስተዳደር ተቋም ነው” የሚለው ነው። ሁለተኛው ደግሞ “የጋራ ተግባር እና የማኅበረሰብ ትእምርት ነው" የሚለው ነው። እንደ ማክስ ዌበር ከሆነ መንግሥትን በግቡና በውጤቱ ከመበየን ይልቅ በመሣሪያዎቹ መበየን የተሻለ ነው። አንዱ መሣሪያው ደግሞ ኃይልን በብቸኝነት የመጠቀም መብት ነው። በዚህም የተነሣ “ዘመናዊ መንግሥት ማለት ኃይል በብቸኝነት የመጠቀም ሥልጣኑን በሚገባ ማስፈጸም የሚችል ተቋም ነው።”

የተባበሩት መንግሥታት የ933 የሞንቴቪዶ ስምምነት (Montevideo Convention) መንግሥት ሲል “የተወሰነ ቁጥር ያለው ቋሚ ሕዝብ፣ የታወቀ ቋሚ ግዛት እና ገዥ አስተዳደር (Government) ያለው፤ ከሌሎች ተመሳሳይ አካላት ጋር በእኩልነት ግንኙነት ማድረግ የሚችል” ማለት ነው፤ ይላል።

በአጠቃላይ ስንመለከተው መንግሥት ስንል “ኃይልን በብቸኝነት የመጠቀም መብት ያለው፣ አንድን የተወሰነ አካባቢ እና በዚያ አካባቢ ፖለቲካዊ በሆነ መልኩ የተደራጁ ሕዝቦችን አንድ ለማድረግና ለመምራት የተዋቀረ፣ ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው፣ ራሱን የቻለ ሕጋዊ የአስተዳደር ተቋም ነው።”

**3.** የመደመር መንግሥት

የመደመር መንግሥት በመደመር ፍልስፍና መሠረት የሚሠራ መንግሥት (State) ነው፤ የቃል አገባቡም ልክ “Developmental State - ልማታዊ መንግሥት” እንደሚለው ዓይነት ነው። በላዕላይ መዋቅር ለውጥ ላይ የሚያተኩር፤ የማኅበረሰብ ልዩ ልዩ የጸጋዎች፣ የዕሴቶች፣ የሀብቶች፣ የባህሎች፣ የዐቅሞች ድምር፤ በተናጠል ከምናደርገው በላይ ለብልጽግና እጅግ አስፈላጊ እና አዋጭ ነው ብሎ የሚያምን፤ መሰባሰብ፣ መከማቸት፣ መቀራረብ እና መገናዘብ ለሀብት እና ለወረት ፈጠራ አስፈላጊ ነው ብሎ የሚያስብ፤ በማናቸውም መስተጋብሮች መካከል ሚዛን መጠበቅን (ወርቃማው አማካይን) መርfh የሚያደርግ፤ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመገንባት እንዲቻል ሀገራዊ አሰባሳቢ ትእምርቶች

CS CamScanner

መኖር እንዳለባቸው የሚቀበል፤ የሕግ የበላይነት መከበር ለውጥን እንደሚያጸናው የሚያምን፤ የጊዜ ምልከታው ትናንትን፣ ዛሬንና ነገን የሚያጣጥም መንግሥት ነው።

ይህ መንግሥት በእነዚህ መርሖችና ዕሴቶች ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ሥርዓት፣ የሕግ፣ የአስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የፍትሕ፣ የማኅበራዊ ልማት፣ በአጠቃላይ የሁለንተናዊ ብልጽግና መንገድን የሚከተል መንግሥት ነው።

"ትብብር" - የመደመር መንግሥት የብልጽግና መሣሪያ

በመደመር መንግሥት ዕሳቤ መሠረት፣ በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግሥት ሚና "ትብብርን መሠረት ያደረገ ነው። በዓለም ላይ የበለጠ ጎልተው የወጡት የመንግሥት የኢኮኖሚ ተሳትፎ ዕሳቤዎች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ሚና ሕግ የማውጣት፣ ሕጉን የማስተግበር እና ፍትሐዊ የሆነ ምኅዳር ለሁሉም የኢኮኖሚ ተዋንያን የመፍጠር ሚና ብቻ ነው የሚለው ነው።

ማንኛውም ሰው የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ ሕጋዊ ዋስትና አግኝቶ፣ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሥራት፣ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም መብቱ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ መንግሥት የኢኮኖሚ ተሳትፎውን ለግል ዘርፉ መተው አለበት ብሎ ያስባል። ሁለተኛው ደግሞ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ ወሳኙ ተዋናይ መሆን አለበት የሚለው ነው። ኢኮኖሚውም መንግሥት መር ኢኮኖሚ ሲሆን፣ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አነስተኛ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለቱም ሊሆኑ አይቻላቸውም። በኢኮኖሚው ውስጥ የግሉ ዘርፍ ብቻ ይምራ ካልን ለዚህ በካፒታል፣ በአደረጃጀት እና በፈጠራ ብቁ የሆነ የግል ዘርፍ ገና አላፈራንም። የኢትዮጵያ የግል ዘርፉ ዕድገት ገና ጅምር ላይ ነው። ባለፉት ሥርዓታት በተከተልነው የኢኮኖሚ ሥርዓት የተነሣ በበቂ ሁኔታ ሀብት የሚፈጥር ጠንካራ የግል ዘርፍ አላዳበርንም። አሁን ባለበት ዐቅም እንዲሁም ካለብን ውዝፍ የልማት ቀሪ የቤት ሥራ አኳያ፣ የግል ዘርፉ የመሪነቱን ሚና ብቻውን ሊወጣው አይችልም።

መንግሥት መር የኢኮኖሚ ፖሊሲ ደግሞ ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ተሞክሮ ነበር። ይህ ፖሊሲ፣ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንትን በማስፋፋትና ድኅነትን በመቀነስ አስተዋጽዖ ቢያደርግም፣ ብልጽግናን ለማምጣት ግን ውሱንነት እንዳለው በስፋት ታይቷል። መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ያልተገራ ጣልቃ ገብነት የግል ዘርፉን ያቀጭጫል፤ ሙስናን ያስፋፋል፤ መንግሥትን በትንሹም በትልቁም ነገር ውስጥ እንዲገባ አድርጎ መንግሥታዊ አገልግሎትን ያዳክማል፤ ፈጠራን ይቀንሳል፤ የሰዎችን የሀብት ባለቤትነት ያሳጣል፤ ከፈጣሪነትና ከሀብት አመንጪነት ይልቅ ተቀጣሪነትንና ጠባቂነትን ያበረታታል።

በተጨማሪም ከኢኮኖሚው የሚመነጨው ወረት በአመዛኙ ወደ መንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች እንዲፈስ በማድረግ፣ ከመንግሥት የፕሮጀክት አፈጻጸም ደካማነት ጋር ተዳብሎ፣ ምርታማ ለሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎችና ለግል ዘርፉ የሚሰጠውን ፋይናንስ በማሳነስ፣ ምርታማነት እንዲኮስስ ያደርጋል።

የመደመር መንግሥት የሚከተለው ሞዴል የእነዚህን ሁለት ፖሊሲዎች ችግር የሚፈታውን "የትብብር ሞዴል" ነው። ይህ ሞዴል በኢኮኖሚው ውስጥ የግልና የመንግሥትን ትብብር የሚያጠናክር ሞዴል ነው። ከዚህ አንፃር ገበያን የሚደግፍ መንግሥት እና ሀብት የሚፈጥር የግል ዘርፍ ሲተባበሩ ወደ ብልጽግና ለሚደረገው ሽግግር ከፍተኛ ሚና አላቸው ብሎ ያምናል።

"የትብብር ሞዴል" ማለት የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢውን ሚና ይጫወታል። ይደገፋል፤ ይበረታታል። መንግሥት ደግሞ ኢንተርፕረነር በሆነ ዕሳቤ የግል ዘረፉ በማይደፍራቸው ዘርፎች ይሳተፋል፤ ከግል ዘርፉ ጋር በጋራ

CS CamScanner

ማልማት በሚቻልባቸው ዘርፎች በጋራ ያለማል፤ አዳዲስ ሐሳቦችን በማመንጨት አዳዲስ የኢኮኖሚ ዘርፎችን ይፈጥራል፤ ያዳብራል። በነባር መንግሥታዊ ዐቅሞች ላይ ፈጠራን በማከል፣ ሀገራዊ ሀብትን ያከማቻል።

በዚህ ዕሳቤ ልማት ማለት የብዝኃ ኢኮኖሚ መዋቅርን ለመገንባትና የእያንዳንዱን ዘርፍ የልማት ዐቅም ለማሟጠጥ የሚደረግ የማያቋርጥ ጉዞ ተደርጎ ይታያል። በዚህ ሂደት ውስጥ የዘርፎችን ዕድገት የሚገድቡ ተጨባጭ መሰናክሎችና ሳንካዎች በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ትብብር እየተለዩ፣ በጋራ መፍትሔ ይሰጣቸዋል። ስኬቶች ደግሞ እየበዙና እየተባዙ የሚሄዱበት አዲስ አተያይ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች የልማት ችግሮች ውስብስብ እና ዘርፈ ብዙ ናቸው። የኋላ ቀርነት ክምችታቸውም ብዙና ረዥም ነው። ስለዚህ ብዙና ውስብስብ ችግርን በአንድ አካል ጥረት ብቻ ለመፍታት አይቻልም።

በፉክክር ጎልቶ የሚወጣ ስኬት(Competitive Success) የሚመዘገበው ከተናጠል ዕይታና አካሄድ ወጥቶ፣ ሁሉም የልማት ኃይሎች ማለትም መንግሥት፣ የግሉ ዘርፍ፣ ሲቪክ ተቋማት፣ የእምነት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማት፣ መካነ ትምህርት፣ ወዘተ ተባብረው፣ ተከማችተውና ተቀናጅተው፣ እንዳንዴም ተፎካክረው ለአንድ የምርታማነት ዓላማ ሲሠሩ ነው።

እነዚህን አካላት በተሻለ ሊያስተባብራቸው የሚችለው ደግሞ "የጋራ ሕልም" ነው። ነገን የተሻለ የማድረግ ሕልም። ነገ የማትረፍ፣ የመሻልና የመበልጸግ ሕልም። ይሄ ሕልም መፈጠሩ ብቻ ግን ውጤት አያመጣም። በተዋናዮቹ ዘንድ ሕልሙ መሥረጽና ተመጣጣኝ ግንዛቤ ማግኘት አለበት።

በዚህ ሞዴል መሠረት

የመደመር መንግሥት፦

- የልማት ጉዳይን ቀዳሚ አጀንዳ አድርጎ ይሠራል፤
- በኢንተርፕረነርሺፕ ዕሳቤ የሚመራ የኢኮኖሚ ተዋናይ ዐቅም ለራሱ ይፈጥራል፤ የዳበረና በውድድር የተመሠረተ የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት ይጥራል፣
- በሀገር ወዳድነት ስሜት ይሠራል፤
- ለገበያ ምቹ የሆኑ መደላድሎችን ያዘጋጃል፤
- የልማት ሥራ የትውልድ ቅብብሎሽ ሥራ ነው ብሎ በማመን፣ ወረት ለማስተረፍ ይሠራል.
- የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ አስተዳደር ለማስፈን ይሠራል፤
- የሚፈጥረው የኢኮኖሚና የሲቪል ሰርቪስ ሥርዓት፣ ለአዳዲስ ሐሳቦች፣ ለንግድ ሸቀጦች፣ ለአገልግሎት ንግድ፣ እንዲሁም ለካፒታል ዝውውር ክፍት ነው።

የግሉ ዘርፍ፦

- ኢንተርፕረነርሺፕ ዕሳቤን ያዳብራል፤
- ለውጥውጤ (Dynamic) መንገድን ይከተላል፤
- ገበያን ይፈጥራል፤

CamScanner

ከዚህም በተጨማሪ የመደመር መንግሥት የግል እና የመንግሥትን የኢኮኖሚ ሚናዎች የሚገነዘብበት መንገድ የተለየ ነው። ዕሳቤውን “የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን የሚያከናውነው ማን ነው? " ከሚለው ይልቅ “የኢኮኖሚውን እንቅስቃሴ የሚያከናውነው እንዴት ነው? " በሚለው ላይ ያተኩራል። የመንግሥት/የግል ከሚለው ክፍፍል በማውጣት፣ የሁለቱም ዘርፎች የሥራ አካሄድ እንዴት መከናወን አለበት? በሚለው ላይ ያተኩራል።

ይሄም ማለት አንድን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የግሉ ዘርፍም ያከናውነው መንግሥት፣ ነገር ግን ክንዋኔው በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚመራ አካሄድ አለው ወይ? በንግድ ዕሳቤ አከናውኖታል ወይ? ገበያ ተኮር ነው ወይ? ዕሴት ይጨምራል ወይ? የሚሉት መመዘኛዎች የግድ መሟላት አለባቸው ይላል። ይህን ዕሳቤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የተመሠረተበትን ዐውድ በማብራራት የበለጠ እናፍታታው።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የአዲስ ዕይታ ውጤት ነው። ይህ ዕይታ ሀብትን በሙሉ ገጽታው ለመገንዘብና ተጨማሪ ሀብት እንዲያስገኝ አድርጎ ለመጠቀም የሚያበረታታ ዕይታ ነው።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ሦስት መሠረታዊ ዓላማዎችን አንግቦ የተነሣ ተቋም ነው።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ መንግሥት ስትራቴጂያዊ የኢንቨስትመንት ተቋም ሆኖ ማገልገል ነው። ሁለተኛው ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ የኩባንያ የመልካም አስተዳደር መርሖችን በመከተል፣ ብቃት ያለው አስተዳደርን ተግባራዊ በማድረግ፣ የመንግሥትንና የሕዝብን ሀብት በማሳደግ፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግና ለመጪው ትውልድ የሚሻገር ሀብትን መፍጠር ነው።

ሦስተኛው በጋራ ለመሥራት የሚያበረታታ የኢንቨስትመንት መደላደልን መፍጠር፣ ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት ሀብትን ማቀናጀት፣ እንዲሁም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሀብቶች ላይ ዕሴት በመፍጠር የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንደ ስትራቴጂያዊ መሣሪያ ሆኖ ማገልገል ነው።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እንደ ሉዓላዊ የሀብት ፈንድ (Sovereign Wealth Fund) ሊታይ የሚችል ነው። ይሄውም የብልጽግና ዕቅዳችን መነሻ ነው።

የብልጽግና ግብን ለማሳካት በየዘርፉ የተቀመጡት የልማት ግቦች ከፍተኛ ፋይናንስ ይጠይቃሉ። ይሄንን ፍላጎት ለማሟላት ከታክስ የሚሰበሰብ ገንዘብ በቻ በቂ ሊሆን አይችልም። ከታክስ በተጨማሪ የመንግሥትን ሀብት ውጤታማ በሆነ መልኩ በማስተዳደር፣ የተሻለ ገቢና ትርፍ እንዲያመጣ ማስቻል አስፈላጊ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስመንት ሆልዲንግስ መቋቋም ሀገራዊ ኢንቨስትመንትን ከፍ ከማድረግ ባሻገር፣ ከልማትና ከኢንቨስትመንት አጋሮች ጋር የተሻለ መተማመን ለመፍጠር ያግዛል።

ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ ሀገራት በመንግሥት ባለቤትነት የተያዙ ሪልስቴት፣ መሬት፣ መሠረተ ልማቶች፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች እና የመሳሰሉት ሀብቶች አሏቸው።

የዓለም የገንዘብ ድርጅት (MF) በቅርቡ በ38 ሀገረ መንግሥታት ውስጥ ጥናት አድርጎ ነበር። የእነዚህ ሀገራት አጠቃላይ ሀብታቸው 103 ትሪሊዮን ዶላር ነው። ይህ ደግሞ በአማካይ የእያንዳንዱን ሀገር GDP 216% ወይም ከሁለት እጥፍ በላይ ነው። ይህ የሚያሳየው ጥቅል ሀገራዊ ምርት (GDP- Gross Domestic Product) የሚባለው የተለምዶው የሀብት ልኬት ብቻውን የሀገራትን ሙሉ የሀብት መጠን እንደማያንጸባርቅ ነው።

CS CamScanner

በእጅ ያለ ወርቅ ከድንጋይ ይቆጠራል ይባላል። በእጅ ያለ ሀብት ሳይታወቅ ለአንድ ሀገር የሚያስተዳድሩትን ሀገር የሀብት ልክ በቅጡ የተገነዘቡት ጥቂት መንግሥታት ብቻ ናቸው። ሕዝብ ተገቢ የሆነ የልማት ፕሮግራምም ሆነ የአስተዳደር ዕቅድ መቅረጽ አይቻልም።

ይህ የዕይታ ጥበት ሁለት ዋነኛ ጉዳቶች አሉት። አንዱ ጉዳት መንግሥት ለልማትና ለአስተዳደር የሚበቃ ሀብት የለም ብሎ በማሰብ፣ የሕዝብን ኑሮ ሊለውጡ የሚችሉ ኢንቨስትመንቶችን እንዳይተገብር እጁ ያጥራል፤ የሕዝብ የዕድገት ትልም እውን ሳይሆን ይቀራል፤ የድህነት ቅነሳ ትግል ወደኋላ ይጓተታል።

ሌላኛው የዕይታ ጥበት የሚያስከትለው ጉዳት ወይም ሥጋት ደግሞ፣ መንግሥት ለልማት የሚያስፈልግ ፋይናንስ ሲፈልግ በዕዳና በችሮታ ላይ ብቻ እንዲመረኮዝ ያደርገዋል። ይሄ ደግሞ የልማት ዕድላችንን በሌሎች መልካም ምኞትና ቸርነት ጥገኛ ያደርገዋል። ይሄም የሀገራችንን ሉዓላዊነትና የወደፊት ትውልድን ነጻነት ሥጋት ላይ ይጥላል። የሀገራችን የቅርብ ዓመታት እውነታም ከዚህ አልራቀም።

ያለንበትን እውነታ እንለውጥ፣ ከኢኮኖሚ ቀውስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንገላገል ብለን ስንነሣ፣ አንደኛው ርምጃ ያለንን የሀብት ዕይታ ማስፋት ነው። የመንግሥት የሆኑ ሀብቶች በሙሉ ታውቀው፣ የሀብት ምንጮች ከተለዩ በኋላ፣ የሞያውን ሳይንስ ተከትሎ የሀብት መጠናቸው ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ያስፈልጋል። በባለሞያዎቹ አነጋገር የመንግሥት የሀብት ሚዛን ሰሌዳ (Balance Sheet) በአዲስ መልኩ መቀረጽ አለበት። ይህ ሲሆን መንግሥት ያለውን ዕሴት ወይም ሀብት ከዕዳው (Liability) ጋር አነጻጽሮ የወጪውንና የገቢውን ሂደት ጤናማነትና ዘላቂነት በመረዳት፣ የሕዝብን የኑሮ ደረጃና የልማት የወጪውንና የገቢውን ሂደት ቀጣይነትን ማረጋገጥ ይችላል።

መበደርም ሆነ ዕዳ መሸከም በራሱ ክፋት የለውም። ነገር ግን ይህ ዕዳ ከሀብት ጋር ሚዛን (Balance) ሳይጠብቅ ሲቀር፣ ለቀውስና ለኢኮኖሚ አለመረጋጋት የሚዳርግ ክፍተት ይፈጠራል።

ከዚያም እነዚህ ሀብቶች ሊሠማሩበት የሚገባውን የዘርፍ ገበያና ሚናቸውን መለየት ቀጣዩ ርምጃ ይሆናል። ሀብቶቹን በተገቢው ዘርፍ ገበያ አሠማርቶ ለሀገርና ለሕዝብ ያላቸውን ፋይዳ የሚያረጋግጥ፣ የመንግሥትን የባለቤትነት ሚና የሚያከናውን፣ የሕዝብን መብት ምጣኔያቸው እየጨመረ እንጂ እየተሸረሸረ እንዳይሄዱ ዘብ የሚያስከብርና ሀብቶቹ የሚጠብቅ የኩባንያ አስተዳደር ማበጀት ለዚህ አዲስ ዕይታ ማስፈጸሚያ ቁልፍ መሣሪያ ነው።

በዓለም የገንዘብ ድርጅት (MF) ጥናት መሠረት እነዚህን የመንግሥት የሆኑ ሀብቶችና የሀብት ምንጮች በተገቢው መልኩ ማስተዳደር በየዓመቱ በጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት (GDP) ላይ 5% ጭማሪ ሊያስገኙ ይችላሉ።

የኢትዮጵያ ኢንቨስመንት ሆልዲንግስ የተቋቋመው ይሄንን ሰፊ የሀብት ዕይታ ለመተግበር ነው። የተቋሙ ቅርጽም የሀብት አስተዳደርን ዓለም አቀፍ መልካም ተሞክሮዎች ከሀገራችን ልዩ ሁኔታዎችና የልማት ትልሞች ጋር በማጣጣም ነው።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የሚመራበትና የሚተዳደርበት የሕግ ማሕቀፍ ተቋሙ ራሱም ሆነ በሥሩ ያሉት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተገቢውን ሞያዊ ዲሲፕሊን እንዲላበሱና የውጭ ባለ ሀብቶች በሀገራችን እንዲሠማሩ አመኔታ እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሆኖ ተቋቁሟል።

ይሄም “የመደመር መንግሥት የትብብር ዕሳቤ” አንዱ ማሳያ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ የተተገበረ ነው።

CS CamScanner

ክፍል አንድ የዓባይን

ልጅ ውኃ ጠማው

CamScanner

ምዕራፍ አንድ

## 1. ከኋላ መቅረት

1.1.በጊዜ መቀደም፡ ከዓለም የት ላይ ተላለፍን? ዛሬ ላይ አልደረስንም ዛሬ የሕዝባችንን ጥያቄዎች መመለስ ከሚያስችልና ዓለም አቀፍ ሁኔታው ከሚጠይቀው ደረጃ ላይ አንገኝም። አንዳንድ ሀገራት በኢኮኖሚ ለምተው በፖለቲካ በስለውና ማኅበራዊ ልማትን አረጋግጠው፤ ሀገራዊ ጥንካሬንና አይበገሬነትን ፈጥረዋል። እነዚህ ሀገራት የዛሬ ዘመን ጥያቄዎችን መመለስ የሚያስችል ብቃት ብቻ ሳይሆን ለትውልድ የሚሆን ትሩፋትም ፈጥረዋል። ከዚያም አልፈው ተርፈው የዓለምን የዕድገት ደረጃ ከፊት ሆነው የሚመሩና የሚበይኑ ሆነዋል።

ዓለም አራት የኢንዱስትሪ አብዮቶችን አስተናግዳ፤ አምስተኛውን ለመቀበል እየተሰናዳች ትገኛለች። የሰው ልጅ የመጀመሪያውን በእንፋሎት ኃይል የሚሠራ ማሽን ሠራ። በዚህም በሰው ኃይል ላይ የተመሠረተው የምርት ሂደት ወደ ማሽን ተለወጠ። ከዚያም ተከታታይና ቀጣይነት ያለው ለውጥና ዕድገትን በማሳየት ኤሌክትሪክ እና ማግኔትን ፈጠረ። የኮምፒውተር መተግበሪያዎችን አመጣ። የበይነ መረብ ነገሮች (nternet of Things IoT) አብዮትን አስከተለ። አሁን ደግሞ የሰው ሠራሽ አስተውሎት(Artificial Intelli gence, AI) ዘመን ላይ ደርሷል።

እነዚህ አብዮቶች ዓለም በተለያዩ ለውጦች ውስጥ እንድታልፍ አድርገዋል። ከስልተ ምርት እስከ ጦርነት፣ ከፖለቲካ እስከ ኢኮኖሚ፣ ከጤና እስከ ትምህርት ዓለም በብዙ ተለዋውጣለች። አስገራሚው ነገር ለውጡ ብቻ ሳይሆን፤ የለውጡ ፍጥነትም ጭምር ነው።ፈጣን ክሥተቶችና ተለዋዋጭነት የዚህ ዘመን መለያዎች ናቸው። የዛሬው አዲስ ነገር ነገ ያረጃል።

ከግብርና ወደ መጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት ለመሸጋገር የፈጀው በሺዎች ዓመታት የሚቆጠር ረጅም ዘመን ነበር። ከመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት እስከ ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የፈጀው ጊዜ እጅግ ቀንሶ ከአንድ ምዕተ ዓመት በታች ሆነ። ከሁለተኛው ወደ ሦስተኛው፤ ከሦስተኛው ወደ አራተኛውና ከአራተኛው ወደ አምስተኛው የተሸጋገርንበት ሁኔታ ፈጣንና በዐሠርት ዓመታት የተገደበ ነበር። በዚህ የተነሣ ሁለትና ሦስት አብዮቶችን በአንድ ትውልድ ውስጥ እንድናይ አስችሎናል"።

ከድንጋይ ዘመን እስከ ሰው ሠራሽ አስተውሎት ዘመን ዓለም በብዙ ለውጦችና የዕድገት ደረጃዎች ውስጥ አልፋለች። ከአንዱ አብዮት ወደ ሌላ አብዮት በሚደረገው ሽግግር የሚፈጠረው የማኅበረሰብ ዕድገት ከፍተኛ ነው። ይህ ደግሞ የሚቀጥለውን አብዮት ለማፍጠን ከፍተኛ ዐቅም ነው። ማኅበረሰቡ ከዘመናት በፊት ከነበረበት ኋላ ቀርና የጨለማ ኑሮ፤ በሂደቱ ዘመናዊና በተነጻፃሪም በዕውቀት ብርሃን የሚመላለስ ሆኗል። ምድርን ከማሰስ አልፎ ሕዋን ለመዳሰስ ችሏል።

የሰው ልጅ በቀደመው ዕውቀት ላይ አዳዲስ ዕውቀቶችን እየጨመረ፤ ከዕለት ዕለት የአዳዲስ ፈጠራዎችና ግኝቶች ባለቤት እየሆነ ነው። ትምህርት ቅርጽና ሥርዓት ይዞ፣ አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ እየተደገፈ፣ ለቀጣይ ደግሞ ትከሻውን ድጋፍ አድርጎ፣ ቅጥልጥል እየሠራ፤ ለዓለም የዘመናዊነትን ብርሃን እያፈካና፤ የብርሃን ምንጭ እየሆነ ነው።

ዕውቀት ተደራሽነቷ ሰፍቷል፤ ከወዲያኛው ዓለም ያለው ትምህርት ከሌላኛው ጫፍ በቀላሉ የሚገለጥበትና ብርሃን የሚሆንበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ማኅበረሰብን የመገንባት ሂደት ዘመናዊነትን ተላብሷል። ቀድሞ አንድን መጽሐፍ ለማግኘት የነበረው ድካም ቀርቶ፣ አሁን ግለሰቦች ከአንድ ቤተ መጻሕፍት በላይ በአንድ አነስተኛ ቋት (Hard disk or Flash disk) ይዘው ይዞራሉ። መጽሐፉን ቢፈልጉ በጽfhፍ፣ ቢፈልጉ በድምፅ ማግኘት የሚቻልበት ዕድል በዝቷል።

ነገ ደግሞ የትምህርት መልክ በእጅጉ እንደሚቀየር ይጠበቃል። አሁን ያለው የተለመደ የዲግሪና የሰርተፊኬት አካሄድ ተቀይሮ፤ እንደየተማሪው ፍላጎትና ዓላማ የሚቃኝ ይሆናል። የትምህርት ሚናም ተማሪዎችን ፈጠራን የተካኑ የልዩ ክሂሎት ባለቤቶች ማድረግና ለዓለም ብልጽግና ዋና ተዋንያን እንዲሆኑ ማስቻል ሆኗል።

CamScanner

ዕታት የ ነበረሰቡን ከነበረበት ኋላ ቀር ዓለም አውጥቶ፤ ዘመናዊና የብዙ አሻጋሪ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዕሴቶች ባለቤት እንዲሆን አስችሎታል።

እንደዚህ ዓይነት ሥልጡን ማኅበረሰብ ባለቤት የሆኑና እነዚህን የኢንዱስትሪ አብዮቶች ወደ ሙሉ ሜካናይዜሽን ገብተዋል። ከእርሻ እስከ ጉርሻ ያለው ሂደት በቴክኖሎጂ የታገዘና የሚመሩ ሀገራት፣ እርባቸው ክራ ትከሻ ከተላቀቀ ቆይቷል። በተከታታይ በነበሩ አብዮቶች የሰውን ጣልቃ ገብነት በእጅጉ የቀነስ ሆኗል። በዚህም የማምረቻ ዐቅም መጨመር ብቻ ሳይሆን፤ የምርት ብክነትን መቀነስና ጥራትን በእጅጉ መጨመር ተችሏል።

ከሜካናይዜሽንም አልፎ፤ የእያንዳንዷን የተክል ቅንጣት የጤና፣ የውኃና የንጥረ ነገር ተመጣጣኝነትና ውጤታማነት መከታተል የሚያስችሉ የነገሮች በይነ መረብ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፤ ችግሮች ሳይባባሱ ቶሎ መፍትሔዎችን መስጠት እስከሚችሉበት የምጥን ግብርና (Precision Agriculture) ደረጃ ደርሰዋል ።

በጤናም ረገድ አብዛኛው ሕክምና በግምትና በልምድ ከሚሰጥበት ባህላዊ ሕክምና ከተሻገሩ ሰነበቱ። መድኃኒቶችና ሕክምናዎች በሽታዎች በጥልቀት ተመርምረውና መነሻቸው ታውቆ፣ ችግሮች ከምንጫቸው ወደ ሚታከሙበት ዘመናዊ ሕክምና ተሸጋግረዋል። በዚህም ሰውን በመድኃኒት ከማከም አልፈው፤ ቀደው በሽታዎችን እስከማስወገድ፤ የአንድን ሰው አካል ለሌላ ሰው ነቅሎ በመትከል፤ የብዙዎችን ሕይወት እስከ መታደግ ተደርሷል። ዛሬ ላይ ደግሞ ከንቅለ ተከላ (Implantation) አልፈው፤ የሰውን አካል አትመው (3D Print) ጥቅም ላይ ለማዋል ጫፍ ደርሰዋል።

ከምርትና ከፈጠራም በተጨማሪ ከውጤታማነትም አንጻር በበለጸጉ ሀገራት መንግሥታዊ አስተዳደር ከማናለብኝነትና ከዕብሪት ተላቆ፣ ግልጽ፣ በእጅጉ መልክ የያዘና በሥርዓት የሚመራ ሆኗል፡፡ እያንዳንዱ የሕዝብ አገልግሎት ከየት ተጀምሮ የት እንደሚጠናቀቅ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅ፣ መሟላት የሚገባቸው አስፈላጊ ግብአቶች ምን ምን እንደሆኑ፣ የትኞቹ አማራጮች ምን ዓይነት ውጤት እንዳላቸውና መሰል ጉዳዮች ሁሉ በትክክል የተበየኑ ናቸው። በዚህም የተገልጋዩን ጊዜና ገንዘብ ከመቆጠባቸውም በተጨማሪ፣ ርካታውንም በከፍተኛ ደረጃ ከፍ አድርገውታል። ማኅበረሰቡ የተለያዩ ሐሳቦቹንና ፈጠራዎቹን ወደ ፊት አምጥቶ በጎ ተጽዕኖ ለመፍጠር የተበረታታ ነው። ዛሬ ደግሞ አብዛኛዎቹ የሕዝብ አገልግሎቶች በመሥመር ላይ (Online) የሚሰጡ በመሆኑ፣ ከቤት ሆነው ብዙ የአገልግሎት ሂደቶችን ማጠናቀቅ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ከምርታማነትና ከፈጠራ አንጻር፣ ባለፉት ጥቂት ዐሠርት ዓመታት ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ተለውጣለች። የለውጡ ዘዋሪያንም በከፍተኛ ደረጃ የበላይነትን አግኝተውበታል። ቴክኖሎጂን ለራሳቸውም ሆነ ለዓለም በማስተዋወቅ ጥቅም ላይ አውለዋል። በዚህም በተለምዶና በባህላዊ መንገድ ይከወኑ የነበሩ ነገሮች፣ ዘመናዊና በዕውቀት የሚመሩ እንዲሆኑ አስችለዋል። ከነበሩበት ኋላ ቀርና አዝጋሚ አካሄድም ወደ ዘመናዊ የላቀ አኗኗር ተሻግረዋል። በእጅጉ ተለዋዋጭ ሁኔታን ፈጥረው በዕድገት ማማ ላይ ተቀምጠዋል።

የመገናኛ ቴክኖሎጂም ጋዜጣ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥንን ከመሰሉት መገናኛዎች እየተሻገረ ነው። ከአንድ ማዕከል ከሚመሩ መገናኛ ብዙኃን ወጥቶ የዘመኑ ዲጂታል ዓለም እያንዳንዱን ግለሰብ የመገናኛ ባለቤት አድርጎታል። የግለሰቦች መኖሪያ ቤትም ስቱዲዮ እንዲሆን አስችሏል። ዓለም በመረጃ ከመቼውም በላይ ተሣሥራለች። የተለያዩ መረጃዎችን ከአንዱ የዓለም ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ ማድረስ የጥቂት ደቂቃዎች ሥራ ሆኗል። አዳዲስ ድርጊቶች ያለ ምንም ፈቃድና ክልከላ በግለሰቦች እጅ በቀጥታ እስከ መሠራጨት ደርሰዋል። ከጅምላ ሥርጭት ወጥተው ግለሰቦች እንደየፍላጎታቸው የተቃኙ ዜናዎችን ማግኘት ጀምረዋል።

በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ ዓለም ኢተገማችና በፍጥነት ተለዋዋጭ ሆናለች። ፖለቲካው፣ ኢኮኖሚውና ማኅበራዊ ጉዳዩ ከምናውቀው በፍጥነት እየተቀያየረና ሌላ መልክ እየያዘ መጥቷል። በፖለቲካ ረገድ የእውነትና የሐሰት ልዩነቶችን መበየን እስከሚያዳግት ድረስ መደበላለቅ ተፈጥሯል። ዓለም በየአካባቢውና በየቀጣናው ጠንክረው በወጡ ኃይላት አማካኝነት

CS CamScanner

ከአንድ ዋልታ ወደ ባለ ብዙ ዋልታነት እየተለወጠች ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የበላይ ሆኖ ለመገኘት በሚደረግ ርብርብ ከፍተኛ ውድድርና ፉክክር ተፋፍሟል። ውድድርም በሰላምና በጦርነት መካከል ያለውን የልዩነት መሥመር አደብዝዞታል።

የሀገር ሰላምንና ደኅንነትን ለማስጠበቅም፤ የጦር ኃይሎችን ዐቅም የመገንባቱ ሂደት፣ ከምድር ለምድር ጦርነት አልፏል። ወደ ባሕርና ወደ አየር እንዲሁም ወደ ሀገር አቋራጭ ግዙፍና ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች ከተሸጋገረ ቆይቷል፡ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት የዚህ አንዱ ምስክር ነው። ዓለም የውጊያ ዝግጁነቷ ለሚቀጥለው ዘመን ነው። ጦርነት፣ የጥይት ባሩድ ከተሠራበት ጊዜ ጀምሮ፣ በኒውክሌር አረር በኩል አልፎ ሰው አልባ መሣሪያዎች እስከተመረቱበት ድረስ በተለያዩ አብዮቶች ውስጥ አልፏል። እነዚህ የቴክኖሎጂ አብዮቶች የጦርነትን ፍጥነት እና ዐውድ በእጅጉ ቀይረውታል። ፍጥነት ለተገዳዳሪ የጊዜ ዐቅም ሲያሳጣ ለሌላኛው ኃይል ደግሞ ተጨማሪ ነገሮችን ለማድረግ ዐቅም ይሰጠዋል። የጦርነት ዐውዶችም ከአየር፣ ከምድር፣ ከባሕር በተጨማሪ የሕዋና የሳይበር ምኅዳሩንም እየተጠቀሙ መጥተዋል።

የሀገር ደኅንነትና የመገናኛ ሥርዓቶችም በከፍተኛ ደረጃ ተቆራኝተዋል። ማኅበራዊ መገናኛ በሀገራት ላይ የሚያደርሰው ተጽዕኖም ከፍተኛ ሆኗል። የፈጠራና የሐሰት ወሬዎች ከየትኛውም የዓለም ጫፍ ወደ ሌላኛው ጫፍ በሰከንዶች እስከ ማስተላለፍ ተደርሷል። የዲጂታል ቴክኖሎጂና የማኅበራዊ መገናኛ ዕድገት እውነትን ከሐሰት አምታትቶታል። የጥልቅ ማመሳሰል (Deepfake) ዘመን እውነትና ሐሰት ልዩነቱ ጠፍቶ፤ የትርክት ፉክክር የሀገራትን ፖለቲካ መረጋጋት ነሥቶታል። ቴክኖሎጂና ማኅበራዊ መገናኛ በሀገራት ፖለቲካ ውስጥ ተዋንያኑ ብዙ እንዲሆኑ አድርገዋል። አለመረጋጋትን መፍጠር ለሚፈልጉ ኃይሎች ድንበር ሳይሻገሩና ጦር ሳያዘምቱ የሀገራትን ፖለቲካ እንዲንጡ ዐቅም ሰጥቷቸዋል። ሀገራትን ለማውደምና ለማንበርከክ የሚደረግ ጦርነትም ሕንጻንና ከተማን ከማፍረስ ጭንቅላትን ወደ መስለብና ወደ ማፍረስ ማዕከሉን ቀይሯል። ጥይት ሳይተኩሱና ሕንጻ ሳያወድሙ፣ በማኅበራዊ መገናኛ የሚለቀቁ የሐሰት ወሬዎች፣ ሀገር ወደ ማፍረስ ተሸጋግረዋል።

በአጠቃላይ ሐሳብና ፈጠራ ዋነኛው የኢኮኖሚ ዕሴት ማዕከል ሆነዋል። ትላልቅ በፈጠራ የተካኑ የበለጸጉ ሀገራት የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች የዓለምን ኢኮኖሚ ብዙውን ድርሻ ተቆጣጥረዋል። የዓለም ኢኮኖሚ በእነዚህ ድርጅቶችና ድርጅቶቹ ባሉባቸው ሀገራት ተጽዕኖ ሥር ወድቋል። የዓለም ኢኮኖሚ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተሣሥሯል።

ስለዚህም በአንደኛው የዓለም ጫፍ የሚነሣ ችግር አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ሲንጠው ይታያል። ድንገተኛ ቀውሶችና ሰው ሠራሽ ችግሮች የዓለምን ኢኮኖሚ የዕሴት ሠንሰለት ሲያናጉ እና በመላው ዓለም ላይ ጫናን ሲያሳድሩ ተመልክተናል።

በአንድ አካባቢ የሚፈጠር ቀውስ በዓለም ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ጫና ግዝፈት፣ ቀውሱ የተፈጠረባቸው ሀገራት በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ባላቸው ድርሻ የሚወሰን ነው። በዓለም ገበያ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ባላቸው ሀገራት ላይ የሚደርስ ማንኛውም ለውጥ ተጽዕኖው በመላው ዓለም ይሰማል። ለዚህም ማሳያ የሩሲያና የዩክሬይን ጦርነት በዓለም ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ማየት በቂ ነው።

በዚህ ተለዋዋጭ ከባቢ ውስጥ የሀገራችንን ቁመና ስንመለከት፤ አንደኛ፥ ዓለም ከደረሰበት የለውጥና የዕድገት ደረጃ አንጻር በብዙ ሩቅ ነን። ሁለተኛ፥ በፍጥነት እየተለዋወጠ ባለው ከባቢ ውስጥ የምንሰጠው ምላሽ አዝጋሚ ነው። በሀገራችን ብዙ ምርቶችና አገልግሎቶች የሚመረቱበትና የሚሸጡበት መንገድ በሰው ኃይል ላይ ጥገኛ የሆነና በቴክኖሎጂ ያልታገዘ ነው። ዓለም አምስተኛው አብዮት ላይ ቢደርስም ግብርናችን እንኳንስ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ተሠናስሎና ተቀናጅቶ ውጤት ሊያመጣ ቀርቶ፣ አሁንም ራሱን ችሎ መቆም ተቸግሯል። ገና ከባህላዊ አሠራሮች ያልተላቀቀ፣ ውጤቱም ከሚጠበቀው በእጅጉ አናሳ ነው። እርሻችን ከከብቶች ትከሻና ከሞፈር ቀንበር ላይ አልተላቀቀም። እጅግ ሲበዛም በዝናብ ላይ ጥገኛ ነው። የበለጸገው ዓለም ከብዙ ዓመታት በፊት የተወውን የአመራረት ዘዬ የሚከተል ነው።

CamScanner

የቀደሙት ሥርዓቶች ሁሉ ግብርና የኢኮኖሚያችን ምሰሶና ማገር መሆኑን ያውጁ ነበር። ቢሆንም፣ ምሰሶና ማገር ነው ያልነውን ዘርፍ ከአያቶቻችን ዘመን የአሠራር ሥርዓት ፈቅ አላደረግነውም። ፈቀቅ ለማድረግ የተጓዝነው መንገድም እጅግ ዘገምተኛ ነው። ከእኛ አነስተኛ የግብርና ዐቅም እና የግብርና ልምድ ያነሰ ዘመን ያላቸው ሀገራት፣ ከራሳቸው ተሻግረው የዓለምን ከፍተኛ የምግብ ድርሻ ይሸፍናሉ።

እኛ ግን ግብርናችን ከዘመናዊው አሠራር ጋር እንዲላመድ አላደረግነውም። አዳዲስ ፈጠራዎችን አልጨመርንበትም። የምርት ሂደቱንም ለማሻሻል አልቻልንም። በዚህም የተነሣ የምግብ እጥረት ዛሬም ድረስ ከባድ ፈተናችን ነው። ረሃብ ብርቱ ክንዱን የሚያሳርፍብን ሕዝብ ሆነናል። ቀዳሚና ትኩረት ተሰጠው የተባለው ግብርና በዚህ ደረጃ ወደ ኋላ የቀረ መሆኑ፣ ሌሎቹም ዘርፎች በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ማሳያ ነው።

ከዓለም ፊት አውራሪዎች ተርታ ከነበርንበት የቀደምት ሥልጣኔ ባለቤትነት፤ ዓለም ጭራነት ያሽቆለቆልንበት ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ እጅግ ያሳዝናል። እንደ ዓለም ሰው ሠራሽ አስተውሎትን ለግብርና እያዋለ፤ እኛ ከበሬና ከሞፈር ቀንበር ጋር ቀደምትነታችን ለዓሰም ብዙ ማበርከት ሲገባን፣ ዓለም ከኋላችን ተነሥቶ አልፎን ነጉሩና። እንታገላለን። ዓለም የደረሰበት ለመድረስ ቀርቶ፤ የመጀመሪያዎቹ የኢንዱስትሪ አብዮቶች ጡትን ትሩፋቶች በሴትነት ለመያዝ ወይም አምራች ለመሆን አልበተንም። ዛሬም ተራ የኤሌክትሪክ ቁሶችን መፍጠር ይቅርና፣ በቅጂ እንኳን እያመረትን አይደለም። ከዓለም ጋር በርቀት ተላልፈናል።

የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት በእንግሊዝ ሲጀመር፣ ሀገራችን በባህላዊ እርሻ ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ነበራት። በመሳፍንት አገዛዝ ሥር ነበረች። ወደ ኋላ ላይ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እንደ ሀገር የኢንዱስትሪ አብዮቱን የመቀላቀል አስፈላጊነትን በመረዳት፣ የተለያዩ ጥረቶችን አድርገዋል። ለዚህም ሴባስቶፖል የተሰኘውን መድፍ ለመሥራት የሄዱበት ርቀት ምስክር ነው። ይሁንና እንደ ብዙ የአውሮፓና የምሥራቅ ሀገራት ሁሉ፤ የፊውዳል ሥርዓቱ አቀንቃኞች የንጉሡን የዘመናዊነት ሕልም ሊረዱት አልቻሉም። በዚህም ምክንያት የንጉሡ ሀገር የማዘመንና የማሳደግ ሕልም ሳይሳካ ቀረ። የንጉሡ ሀገር እናልማ፤ እናዘምን፣ ቴክኖሎጂን እንጠቀም፤ እናምርት የሚለው ጥሪ፤ ሀገር እናጥፋ የተባለ ተደርጎ ተተረጎመ፤  ብዙ ዋጋም አስከፈለን። ንጉሡም በዚሁ የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ርዕይና እንቅስቃሴ ምክንያት በተነሣ ጦርነት ተሠዉ።

በመሳፍንቱይተዳደሩ በነበሩት ሌሎች የሀገራችን ክፍሎችም ይህ ነው የሚባል የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ አልነበረም። በዚህ ወቅት የኢንዱስትሪ አብዮቱን የተቀላቀሉ እንደ አሜሪካ፣ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ጃፓን፣ የመሳሰሉ ሀገራት ዛሬ የደረሱበት ላይ መድረስ እየቻልን ወደኋላ መቅረታችን በእጅጉ የሚያስቆጭ ነው።

ከኤሌክትሪክ ግኝትና በጅምላ ከማምረት ጋር ተያይዞ ዓለም ወደ ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ስትሻገር፤ ሀገራችን ለጥቂት ጊዜ በዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ፣ ቀጥሎም በዐፄ ዮሐንስ አራተኛ አስተዳደር ሥር ነበረች። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የጀመሩት ሀገርን አንድ የማድረግ ጉዞ ተጠናክሮ የቀጠለ ቢሆንም፣ ሙሉ ቅርጽ ግን አልያዘም። በዚህ ወቅት የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን፣ በተለይም በውስጥ ከነበረው ሽኩቻ አንጻር፣ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን የመታጠቅ ፉክክሮች ነበሩ። ከዚያ ባለፈ ለምርትና ለሀገር ዝመና የሚሆኑ የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ላይ ብዙም አልተሳተፍንም፤ ኢኮኖሚያችንም ባህላዊ እርሻን ተንተርሶ ቀጥሏል።

ቀጥለው የነገሡት ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ሀገርን አንድ ከማድረጉ ላይ ጥሩ ውጤት ነበራቸው።ቴክኖሎጂን ወደ ሀገር ከማስገባትና ከመጠቀም አንጻርም ከፍተኛ እመርታ የታየበት ዘመን ነበር። ለዚህም ለሀገራችን የመጀመሪያ የሆነውን የባቡር መሠረተ ልማት መዘርጋታቸው፣ ትምህርት ቤቶች እንዲስፋፉ ማድረጋቸው፤ ስልክ፣ ፖስታ፣ መኪና፣ የውኃ ቧንቧና ሌሎች ዘመኑ የሚጠይቃቸውን የዘመናዊነት መገለጫዎች ለሀገራችን ማስተዋወቃቸው ምስክር ነው። ይሁንና ግትር ከሆነው የፊውዳሉ ሥርዓት አቀንቃኞች ከፍተኛ ተቃውሞ ስለገጠማቸው፤ ንጉሡ ከዚህ በላይ ለመጓዝ የተቸገሩ ይመስላል።

CamScanner

በዚህም ዘመን ቢሆን፤ ዓለም በሥልጣኔው ያመረታቸውን ውጤቶች ሸምቶ ከመጠቀም ባለፈ፤ ወደ ማምረት የገባንበት አንድም የቴክኖሎጂ ምርት የለም። በዚህ የተነሣ የኢንዱስትሪ አብዮቱን ትሩፋቶች ተጠቃሚዎች እንጂ፤ የአብዮቱ ተሳታፊዎች አልነበርንም። በዚህ ወቅት የኢንዱስትሪ አብዮቱን ከተቀላቀሉት መካከል ጣልያን፣ ስፔን፣ ብራዚል፣ አርጀንቲና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ሩስያና ሕንድ ይገኙበታል።

ከዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዘመን በኋላ በነበሩ ነገሥታት፣ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር የማስገባት ሂደት ቀጥሏል። የኤሌክትሪክ ኃይል መዘርጋት፣ የአየር መንገድ፣ የአውራ ጎዳናና የንግድ ባንኮች መመሥረት፣ እንዲሁም ሌሎች መሠረተ ልማቶችን የመዘርጋት ሥራዎች ተከናውነዋል። ይሁንና የኢንዱስትሪ አብዮቱን በመቀላቀል ረገድ፤ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሦስት ዐሠርት ዓመታት፣ እዚህ ግባ የሚባል ውጤት አልነበረንም።

ወደ ኋላ ግን የቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የተለያዩ ፋብሪካዎችን ማቋቋም ጀመረ። በሦስቱ የአምስት ዓመታት የልማት ዕቅዶቹ ውስጥ፡ ኢንዱስትሪን አንዱ አካል አድርጎ ተንተነተነ። የፖሊሲ ማሕታቶም ተዘጋጁ። የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብም የተለያዩ ማበረታቻዎች ተቀመጡ። በዚህም የተለያዩ ለሀገር ውስጥ፣ ፍጆታ የሚሆኑ ዕቃዎችን ማምረት የተጀመረ በመሆኑ የኢንዱስትሪ አብዮቶቹን የመተላቀላችን የመጀመሪያ አብዮቱን ከተቀላቀሉ ሀገራት መካከል ቻይናንና ቱርክን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ ሀገራት ርምጃ የተጓዝነው በዚህ ዘመን ነበር ብሎ መውሰድ ይቻላል። በዚህ ዘመን የኢንዱስትሪ ዛሬ ላይ በኢንዱስትሪ ዕድገት ማማ ላይ የሚገኙ መሆኑ ብዙ ትምህርት የሚገንበት ነው።

ይሁንና የኢንዱስትሪ ጉዟችን ብዙም እመርታ ሳያሳይ፤ ዓለም ኮምፒውተርን መሠረት ወደ አደረገው ወደ ሦስተኛው አብዮት ተሸጋገረ። ብዙም ሳይቆይ የንጉሣዊ አገዛዝ ዘመንም አክትሞ በምትኩ የደርግ ሥርዓት ተተካ። የደርግ ሥርዓት የፊውዳሉን አስተሳሰብ በኅብረተሰብአዊነት አስተሳሰብ የመተካት ሂደቶችን ተጓዘ። ለዚህ የሚረዱ ውሳኔዎችንም ወደ ተግባር አውርዷል”። ከሩሲያ ልምድ በመነሣት የኢንዱስትሪ አብዮቱ በደርግ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ እንደሚሣለጥ ተጠብቆ ነበር።

ነገር ግን “ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁ' ሆነ። ይልቁንም በኅብረተሰብአዊነት አስተሳሰብ ምክንያት የግል ባለ ሀብቱ ተዳከመ። በንጉሡ ዘመን የተጀመሩ ጥሩ ጅማሬዎች እንኳን ወደ ኋላ ተመለሱ። በዚህም የተነሣ የኢንዱስትሪ ጉዟችን ከጅምሩ ቁልቁል መውረዱን ተያያዘው።

ይሁንና በዚህም ዘመን ኮምፒውተርን ጨምሮ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ምርቶችን ከመጠቀም አንጻር ዕድገቶች ነበሩ። ተጨማሪ ፋብሪካዎችን በመንግሥት ዕዝ ገንብተናል። ለዚህም የጦር መሣሪያ ማምረቻ ፋብሪካዎቻችን ማሳያዎች ናቸው። ይህ ዘመን ብዙ ሀገራት የኢንዱስትሪ ጉዟቸውን አጠናክረው የቀጠሉበት ዘመን ነው። በተለይም የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት፣ ቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ቬትናም፣ ታይላንድና ሌሎችም የኢንዱስትሪ ዐቅማቸው በተለየ መልኩ ያበበበትና አስገራሚ እመርታ ያሳየበት ዘመን ነው።

አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የነገሮች በይነ መረብን መሠረት ያደረገና የሰው ሠራሽ አስተውሎት ከፍተኛ ሚና የሚጫወትበት አብዮት ነው። ውሂብ (Data) ዋና ማጠንጠኛ የሆነበትና ሰው አልባ ክንዋኔዎች የተንሠራፉበት ዘመን ነው። ይህ ዘመን የዚህ ትውልድ ዘመን ሲሆን፤ ሀገራችን በኢሕአዴግ መንግሥት እየተመራች አገባዳዋለች። በሀገራችን አሁንም እርሻ ዋነኛው የኢኮኖሚ መሠረትና ዋነኛው የጥቅል ሀገራዊ ምርት (GDP) አስተዋጽዖ አድራጊ ሆኖ ቀጥሏል።

የኢሕአዴግ መንግሥት ከደርግ ኅብረተሰብአዊ ሥርዓት ወደ ቅይጥ የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የተሸጋገረ ቢሆንም፣ እርሻ መር የኢኮኖሚ አቅጣጫን የሚከተል ነበር። በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዐሠርት ዓመታት፤ በኢንዱስትሪ ረገድ ብዙም ዕድገት አልታየም። ይልቁንም ከመሠረተ ልማት፣ ከግንባታና ከአገልግሎት አኳያ የተሻሉ ዕድገቶች ታይተዋል።

CS CamScanner

ወደ ኋላም ኃይል የማመንጨት ፕሮጀክቶች በመጀመራቸው ኢንዱስትሪዎችን ለመገንባት መደላድል ተፈጥሯል። በመጨረሻዎቹ ዓመታት ኢሕአዴግ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የኢንዱስትሪ ማስፋፋት አካሄዶችን ሲከተል ነበር። የተለያዩ የኢንዱስትሪ ዞኖችን በማቋቋም ዘርፉን ለማነቃቃትም ሞክሯል። ይህም አሠራር አሁንም በተጠናከረ መልኩ እየተሄደበት ነው። እንዲሁም በሌሎች የኢንዱስትሪ አብዮቶች የተገኙ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም ባለፈ በአምራችነት ደረጃ በዓለም የኢንዱስትሪ ዘርፍ ተዋናዮች ለመሆን ብዙ ሥራ ይጠብቀናል።

አምስተኛው አብዮት ከሰው ሠራሽ አስተውሎትና ከባዮ ቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ እየመ ያለ አብዮት መሆኑ ይታወቃል። ይህ አብዮት ገና በብዥታ ውስጥ ያለና ይህ ነው ተብሎ ያልተበየነ ትልቅ ለውጥ እንደሚያወጣ የሚጠበቅ አብዮት ነው። ሀገራችን ይሄንን አብዮት የምትቀበለው በተደራራቢ የኢንዱስትሪ ተዋናይነት ግዴታ ውስጥ ሆና ነው።

እንደሚታወቀው አንዱ የኢንዱስትሪ አብዮት ሌላኛውን ሙሉ በሙሉ አይተካም። ከተወሰኑ ማሻሻያዎችና ማስተካከያዎች በስተቀር አንዱ አብዮት በቀዳሚው ላይ ተንተርል ይከሠታል። ወይም አንዱ ለአንዱ አስቻይ ሆነው የሚታዩ ናቸው። በመሆኑም ዓለም ለአምስተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት እየተንደረደረ እኛ ገና ቀዳሚዎቹን በቅጡ አላሳካንም፣ በብዙ ወደ ኋላ ቀርተናል።

**1.2.** ያልተፈጠረ ዕሴት፤ የተጓደለ ሐሴት

የኢንዱስትሪ አብዮቶችን ለመቀላቀል አስቻይ ሁኔታዎች ሊሟሉ ይገባል። ከእነዚህ አስቻg ሁኔታዎች ውስጥ ዋነኞቹ መዋቅራዊ ሁኔታ፣ በቂ ወረት፣ በቂ ገበያ፣ የላቀ የሰው ኃይል እና የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ ወሳኝ ሆኖ የሚጠቀሰው የመሪዎች ሚናና የአመራር ቁርጠኝነት ነው።

ከእነዚህ አስቻይ ሁኔታዎች አንጻር የት እንደምንገኝ መመልከት የመጣንበትን መንገድ ለማጤንም ሆነ ያለንበትን ደረጃ ለመገንዘብ ወሳኝ ነው።

አስቻይ ሁኔታዎችን በጥልቀት መተንተን ራሱን ችሎ ጥናትና ምርምር የሚጠይቅ ነው። ጥናቱን በየዘርፉ ላሉ ባለሞያዎች ትተን፣ ለዚህ ርዕሰ ጉዳይ ግብአትነት በተወሰነ ደረጃ ጉዳዮችን ማንሣቱ ግን ተገቢ ነው።

የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት ከፈነዳበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ሦስተኛው አብዮት ድረስ የነበሩትን ወደ ሁለት መቶ ዓመታት፣ ሀገራችን በፊውዳል ሥርዓት ሥር ነበረች። ከጥቂት እንቅስቃሴዎች በስተቀር ሥርዓቱን ለመቀየር የተደረጉ ሙከራዎች እምብዛም ናቸው። የፊውዳል ሥርዓት ደግሞ አንዱ መለያው ለውጥን የሚጠላ ቆሞ ቀርነት ነው ። የላይኛው መደብ አባላት ብዝበዛን ማዕከል ያደረገ ከፍተኛ ተጠቃሚነት ያላቸው በመሆኑ፣ በጢሰኛው ጉልበት መኖርን እንጂ ሠርቶ መለወጥን የሚያበረታታ ሥርዓት አይደለም። በመሆኑም ነገሥታቱ ሀገራቸውን ለመለወጥ የሚያደርጉት ትግል ከፍተኛ ተግዳሮት ይገጥመዋል። የዐፄ ቴዎድሮስን፣ የዐፄ ምኒልክንና በተወሰነ መልኩም ቢሆን የዐፄ ኃይለ ሥላሴን ጥረቶችና የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች የነበራቸውን ተግዳሮታዊ ምላሽ መመልከት" ለዚህ ጥሩ ማስረጃ ይሆናል።

ቀጥሎ ሀገር የተረከበው የደርግ መንግሥትም፣ የኅብረተሰብአዊት ሶቪየት ኅብረትን የኢንዱስትሪ ልማት ሞዴል አርአያ አድርጎ ነበር የተነሣው። ለሶቪየት ኅብረት የሠራው የኅብረተሰብአዊ የኢንዱስትሪ እመርታ፣ ለሀገራችን ግን ሊሠራ አልቻለም። ለምን? የሚለው ጥልቅ ጥናት የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኖ፣ መዋቅሩ በሀገራችን የተተገበረበት ሁኔታ ግን አንዱ ምክንያት ነው። በንጉሡ ዘመን የተጀመረው የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ፣ በዚያው መጠን ያልቀጠለበት አንዱ ምክንያት፣ የኅብረተሰብአዊው ሥርዓት ሀብት የማፍራት ገደብ ስላለው ነው። የኢሕአዴግ መንግሥትም ለኢንዱስትሪ ምቹ እንደሆነ የሚነገርለትን ገበያ መር ኢኮኖሚያዊ መዋቅር በቅይጥ ገበያ መር አካሄድ ተገበረው። ነገር ግን በቀላሉ ወደ ኢንዱስትሪ ልማት መቀላቀል አልተቻለውም ነበር።

CS CamScanner

ከንጉዎቹ ዘመን ጀምሮ በደርግ፣ በኢሕአዴማ ዘመን እና አሁን የኢኮኖሚ ማጥራትና በተግባር ምን ያህል ልዩነት አለው? ምን ያህልስ ተሻሽሏል? የመዋቅሩ ተዋንያንስ ያህል ባሕርያዊ ለውጥ አላቸው? ምን ያህል ለኢንዱስትሪ ምቹ የሆነ የኢኮኖሚ መዋቅር

ባለቤት ሆነናል? ጉልህ ልዩነት አለው ወይ? የሚለው በሚገባ ቢመረመር ጥሩ ነው.. አብዮት ወቅት የነበራት መነሻ ወረት ከእርሻ ትርፍ ምርትና ከቅኝ ግዛት የተገኘ ሀብት ሁለተኛው አስቻይ ሁኔታ በቂ ወረት ወይም ካፒታል መኖር ነው። እንግሊዝ በመጀመሪያው ነበር። በቀጣይ ለነበሩ አብዮቶችም ከቀደሙት አብዮቶች የሚገኙ ተጨማሪ ሀብቶች እንደ መነሻ አገልግለዋል። የአብዛኞቹ የአውሮፓ ሀገራት ታሪክም ተመሳሳይ ነው። ቅኝ ግዛት ያልነበራቸው ሀገራት ደግሞ ከእርሻው የሚገኘው ትርፍ ምርት ዋነኛ መነሻ ወረት ሆኖ አገልግሏቸዋል። በሀገራችን እርሻ በዚህ ደረጃ ውጤት ያለው ባለመሆኑ፤ ትርፍ ምርት አምርቶ ለኢንዱስትሪ ምሥረታ ወረት መሆን አልቻለም።

በመሆኑም በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ኢንዱስትሪያችን ካፒታል ለማሰባሰብ የሞከረው በዋናነት ከውጭ ኢንቨስትመንት ነበር። በውጤቱም የተወሰኑ ባለሀብቶች ፈቃደኛ ሆነ የመጡ ቢሆንም፣ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን ከመመሥረት ይልቅ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ ጥቃቅን የዕለት ተዕለት ቁሶችን በማምረት ላይ አተኩረዋል”።

ኢንዱስትሪው የውጭ ንግድ አካል ሊሆን ባለመቻሉና የውጭ ምንዛሪ የሚያመጣ ባለመሆኑ፣ የመስፋፋት ሁኔታው እጅግ አዝጋሚ ሆነ። ሌላኛው የካፒታል ምንጭ ብድር ሲሆን በዚህም የተወሰኑ መካከለኛ ደረጃ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም ተችሏል።

የደርግ መንግሥትም ይህ ነው የሚባል ወረት ከቀደመው መንግሥት አልተቀበለም፡ የእርሻውም ሁኔታ ያን ያክል እመርታ አላሳየም። ይከተል በነበረው የኅብረተሰብአዊነት ርዕዮተ ዓለም ምክንያትም መንግሥት ብቸኛ የኢንዱስትሪ ምሥረታ ባለቤት ሆነ። የጦር ፋብሪካዎቹን ለመትከል ብድር ዋነኛው የወረት ምንጭ ነበር። ከቀደመው መንግሥት ወረት በማግኘት ረገድ የኢሕአዴግም ታሪክ ከደርግ የተለየ አይደለም።

ይሁንና ኢሕአዴግ አንዳንድ መሠረት ልማቶችን ለመተግበር ሕዝብን ማንቀሳቀስ ችሏል”። የኢንዱስትሪ ዞኖችን ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት አደረገ። ምርቱም በሀገር ውስጥ ገበያ እንዲሸጥ ሳይሆን የውጭ ንግድን ለማሳደግ እንዲውል ሆነ። በዚህም የኢንዱስትሪ ዞኖችን ለማስፋፋት ሞክሯል። ይህም የኢንዱስትሪው ዘርፍ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው ያለው ግብአትነት በመጠኑ እንዲያድግ ረድቶታል።ይሁንና አሁንም ከእርሻና ከማዕድን ግብአት ወስዶ ለኢንዱስትሪ የማዋል ዐቅም ላይ አልደረስንም። በተጨማሪም ንጉሡ የተቸገሩበት የካፒታል እጥረት ደርግንም፣ ኢሕአዴግንም ለውጡንም ፈትኗቸዋል። ለዚህ መፍትሔ ሲባል በተመረጠው መንገድ ምክንያትም ሀገራችን በተለያዩ ዕዳዎች ጫና ሥር ትገኛለች።

በሌላ በኩል ተጨማሪ የሀብት ምንጭ እንዲሆኑ ታስበው በተለያየ ጊዜ በርካታ የልማት ድርጅቶች ተደራጅተዋል። ከእነዚህ የልማት ድርጅቶች መካከል በጥሩ የስኬት ጎዳና ላይ የሚገኙ አሉ። ከእነዚህ ተቋማት የሚገኘው ገቢምበተወሰነመልኩ ሌሎች ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋምና ለመደገፍ ይውላል። ይሁንና የአብዛኞቹ ገቢ ራሳቸውን ከማስፋፋት አልፎ ለሌሎች የመትረፍ ዕድሉ እጅግ አነስተኛ ነው። ኢንዱስትሪን ከማስፋፋት አንጻር አዳዲስ ኢንዱስትሪዎችን ለማቋቋም የሚውልም ትርፍ የላቸውም። እንደውም አንዳንዶቹ በድጎማ የሚኖሩ ነበሩ። በመሆኑም የሀገራችን የኢንዱስትሪ ልማት ጉዞ አማራጭ ካፒታል የማግኘት ፈተና አሁን መልሶ ገጥሞታል።

በኢንዱስትሪያዊነት ጉዟችን ካፒታል የማግኘት አማራጮች ምን ያህል በየዘመናቱ ተሻሽለዋል? እርሻችን ሀገርን ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር የሚጠበቅበትን ሂደት መወጣት ለምን አቃተው? ከብድር አዙሪት መውጣት ያልቻልነው

CS CamScanner

ለምንድን ነው? የልማት ድርጅቶቻችን ሌሎችን በብቃት መደገፍ ለምን ተሳናቸው? በአጠቃላይስ ከዘመን ዘመን ያለን እመርታ ምን ያህል ነው? የሚለውን መገምገምና ቁልፍ ችግሩን ማወቅ ለነገ ጉዟችን ወሳኝ ነው።

በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነትና ተፈላጊነት ያላቸው ምርቶችን ከሀገር ውስጥ ገበያ አልፎ ሦስተኛው አስቻይ ሁኔታ ገበያ ነው። በመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት እንግሊ በውጭ ሀገር ገበያ ላይ መሸጥ ችላ ነበር። በተለይም የቅኝ ግዛቶቿ ለዚህ ዓለም አቀፍ በሌላ በኩል ደግሞ ምርቱ ተመርቶ በእነዚህ ሀገራት ይሸጣል። ጥሬ ዕቃ በነጻ መጓዙ በራሱ ንግድ ዋነኛ ማዕከላት ነበሩ። በአንድ በኩል ጥሬ ዕቃ ከእነዚህ ቅኝ ግዛት ሀገርት ይሆናል፣ የሀብት ምንጭ ቢሆንላቸውም፤ ጥሬ ዕቃውን ወደ ምርትነት ቀይሮ ለገበያ ማቅረቡ ደግሞ ሌላ ከፍተኛ ገቢ ነው። በመሆኑም እንግሊዝ በዓለም አቀፍ ገበያው ከፍተኛ ተዋናይ መሆኗ ለኢንዱስትሪዋ በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት ወሳኝ ነበር"።

በሀገራችን ንግድ ዘለግ ያለ ዕድሜ ያስቆጠረ ዘርፍ ነው። ሀገር አቋራጭ የንግድ ጉድኝ የቅርብ ጊዜ ታሪካችን አይደለም። ይሁንና የውጭ ንግዳችን መሠረቱ ጥሬ ዕቃና መጠነኛ ዕሴት የተጨመረባቸው ምርቶች ናቸው። በመሆኑም በቂ ሀብትን ወደ ሀገራችን በማምጣት ረገድ እዚህ ግባ የሚባል ውጤት አልነበረውም። በዘመናዊ ንግድ ደረጃ የውጭ ንግድ የጀመርነው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ነው። ይሄም ንግድ በጥሬ ዕቃዎችና አነስተኛ ዕሴት በተጨመረባቸው ምርቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር። ውጤቱም ብዙ አመርቂ አልነበረም። የዓለም አቀፉን የገበያ ዕድልም ተጠቅመንበታል የሚያስብል አይደለም።

የደርግ መንግሥት ይሄንኑ የውጭ ንግድ አካሄድ አልቀየረውም። ጥሬ ዕቃዎችንና ጥቂት የእርሻ ምርቶችን በተለየ ትኩረት ለውጭው ገበያ ሲያቀርብ ቆይቷል። በውጭ ንግድ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ማካተት የጀመረው የኢሕአዴግ መንግሥት ነው። በዚህ ወቅትም መጠኑ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ስለዚህ ገበያን ከመፍጠር፣ ከመጠቀምና ከማስፋት አንጻር በዘመናት ውስጥ የፈጠርነው ልዩነት ምን ያህል ነው? ከባህላዊት ኢትዮጵያ እስከ ዘመናዊት፤ ከነገሥታቱ ዘመን እስከ ኅብረተሰብአዊትና ገበያ መር ዘመን፤ የዓለም አቀፍ ገበያ ተሳታፊነታችን ማነቆዎች የትኞቹ ናቸው? በመሠረታዊነት መለወጥ ያልተቻለውስ ለምንድን ነው?

አራተኛው አስቻይ ሁኔታ የላቀ የሰው ኃይል ነው። የኢንዱስትሪ አብዮቶች ሁሉ ከአብዮቱ ጋር የሚሄድ የላቀ የሰው ኃይል ይፈልጋሉ። ይህ የሰው ኃይል በትምህርት እና ሥልጠና ተቋማት ወይም/እና በሥራ ላይ ሥልጠናዎች የሚገኝ የሰው ኃይል ነው። የኢንዱስትሪ አብዮቶችን በማምጣትም ሆነ በማስቀጠል የሠለጠነና የበቃ የሰው ኃይል ሚና እስካሁን አይተኬ ነው። በሰው እጅ ብቻ ከሚሠራበት ዘመን ወደ ማሽን ሲሸጋገር፣ የማሽን ዕውቀትና ክሂሎት ያላቸው ሠራተኞች በብዛት መገኘታቸው የግድ አስፈላጊ ነበር። የትምህርትና የሥልጠና ተቋማትም እነዚህን ተፈላጊ ብቃቶች ወደ ማምረት ገብተዋል።

አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ሮቦቲክስን፣ አውቶሜሽንን እና ዲጂታል ቴክኖሎጂን ይዞ ሲመጣ፣ በእነዚህ ዘርፎች እጅግ የሠለጠነ የሰው ኃይል አስፈልጓል። የሚቀጠረውን የሰው ብዛት ቢቀንሰውም የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል ክሂሎትና ዕውቀት ግን እጅግ ጨምሮታል። ከአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ "ለሥራዎች ራስን ማብቃት" (Employebility) እጅግ አስፈላጊ ችሎታ ሆኗል። ይህም ማለት ለአንድ ሞያ የሚኖር ቴክኒካዊ ክሂሎት ብቻ ሳይሆን፣ ተለዋዋጭ የሆነውን የሥራ አካባቢ በፍጥነት መልመድ፣ በየጊዜው ዕውቀትንና ክሂሎትን በፍጥነት ማሻሻል፣ ራስን ለማስተማር እና አዳዲስ ክሂሎቶችን በየጊዜው ለምዶ ባለ ብዙ ክሂሎቶች መሆን የአንድ ተፈላጊ ባለሞያ መለኪያዎች መሆን ጀምረዋል ማለት ነው።

በሀገራችንም አሁን ዓለም ከደረሰበት የኢንዱስትሪ አብዮት ጋር የሚሄድ የሠለጠነ የሰው ኃይል ማምረት አለብን። ይህ የሠለጠነ የሰው ኃይል በአንድ በኩል አዳዲስ ነገሮችን የሚፈጥር ነው። በሌላ በኩል የተፈጠሩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ዐውቆ፣ ለምዶና ሠልጥኖ መምራት እና ማንቀሳቀስ የሚችል መሆን አለበት።

CS CamScanner

አምስተኛው አስቻይ ሁኔታ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ነው። የኢንዱስትሪ አብዮቶች ሁሉ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ኃይልና የለውጥ መሠረት ፈጠራ ነው። ፈጠራ የተለያዩ ደረጃዎች ቢኖሩትም፣ ከውስብስብነት ደረጃው ይልቅ ወቅታዊ መሆኑ የበለጠ ውጤታማነትንና ለውጥን ያስከትላል። በኢንዱስትሪ አብዮቶች ውስጥ ፈጠራ የኢንዱስትሪ የህልውና ጉዳይ ነው። ፈጠራ የማያቋርጥና አንዱ በአንዱ ላይ እየተንተራሰ የሚቀጣጠል ፍኖት ነው።

ዓለማችን ብዙ የፈጠራ ባለቤቶች አሏት። ከኢንዱስትሪ አብዮቶች ጋር በተያያዘ አብዛኛው ፈጠራ በምዕራቡ ዓለም የበላይነት የተያዘ ነው። አሁን አሁን የምሥራቁ ዓለም በተወ መልኩ እየተከተለ ይገኛል። ይሁንና የቅርብ ጊዜ የፈጠራ ሥራዎችን እንኳን ብንመለከት የምዕራቡ ዓለም በመሪነቱ እንደቀጠለ መሆኑን ማሳያ ናቸው።

ወደ ሀገራችን ስንመለስ፣ የብዙ ምዕተ ዓመታት ታሪክ ባለቤት ብንሆንም፣ በለም . የቴክኖሎጂ ፈጠራ መድረክ ላይ ይህ ነው የሚባል ሚና አልነበረንም። ያም ብቻ ሳይሆን ራሳችን ነባራዊ ሁኔታ በማዛመድና በማላመድ የመጓዝ ተሞክሯችን እዚህ ግባ የሚባል በሌሎች ሀገሮች ልምምድ ውስጥ እንደምናየው፣ የዓለምን የፈጠራ ውጤቶች ያ አይደለም። ለዚህም ከነገሥታቱ ጊዜ አንሥቶ ቴክኖሎጂዎችን ከመጠቀም ባለፈ፣ በሀ ውስጥ ከማምረት አኳያ የተጓዝነው ርቀት ብዙም አለመሆኑ ማሳያ ነው። እስከ አሁንም ሀገራችን በፈጠራ ለዓለም ያበረከተችውና በማምረትም ገቢ የምታገኝበት ልዩ ቴክኖሎጂ | ባለቤት አይደለችም። በምልስ ምሕንድስናም (Reverse Engineering) እንኳን ወደ ምርት የተሸጋገረ የቴክኖሎጂ ውጤትም እምብዛም ነው።

ስለዚህ ሀገራችን በቴክኖሎጂ ፈጠራ ውስጥ ይህ ነው የሚባል ተሳትፎ የሌላት ለምንድን ነው? ይህ የቴክኖሎጂ ባለቤትነት ጉዳይ ከዘመን ዘመን ምን ያህል መሻሻል አለው? በትክክለኛው መንገድ ላይ እየተጓዝን ስለ መምጣታችን ማሳያዎች አሉ ወይ? ወይንስ መንገድ ስተናል? ልጆቻችን ዐቅም ሳያንሳቸው፣ ሀገራቸውን የሚለውጥ ፈጠራ ባለቤት መሆን ለምን ተሳናቸው? የሚለው ሊመረመር ይገባል።

በአጠቃላይ ስናየው፣ ሀገራችን በተጓዘችበት የኢኮኖሚ ሂደት ውስጥ፤ ከመዋቅር ጀምሮ፣ እስከ ወረት፣ ገበያና ቴክኖሎጂ ድረስ፤ ያላት እመርታ እጅግ አነስተኛ ነው። የኢንዱስትሪ አብዮት ለመጀመር መነሻ ፍላጎት ካሳዩት ከዐፄ ቴዎድሮስ ጀምረን በተጓዝነው መንገድ፤ ከኋላ ተነሥተው ከሥልጣኔ ማማ ላይ የደረሱ ሀገሮችን ስንመለከት፣ ብዙ መሠረታዊ ጥያቄዎችን የሚያስነሣ ነው። ብዙ ቁጭትንም ይፈጥራል። በዚህ ረገድ ይህ ትውልድ የተረከባት ሀገር፣ እንደ አባቶቻችን አሁንም በበሬና በገበሬ ትከሻ በሚከወን ኋላ ቀር እርሻ የምትተዳደር ናት። ኢትዮጵያ ዛሬም ግብርናና የተፈጥሮ ሀብት የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሠረቷ የሆነ ሀገር ናት።

ከፊውዳሉ ዘመን ብዙም ባልተለየ ሁኔታ መሬት የሁሉ ነገር ማጠንጠኛ ሆኖ እስከ አሁን ዘልቋል። ግብርናው ከራሱ አልፎ ለኢንዱስትሪ የሚሆን ወረት እንዲያካብት የሚያበቃ ሥራ መሥራት አልተቻለም። በዚህም የተነሣ ሀገራችን በዝቅተኛ ደረጃ ያለው የሙከራ የኢንዱስትሪ ጉዞዋ እንኳን ብድርን የተንተራሰ፣ ባለ ብዙ ዕዳ ሀገር ሆናለች። በዓለም ገበያና በቴክኖሎጂ ፈጠራ ተሳትፎዋም እዚህ ግባ የሚባል ደረጃ የሌላት ሀገር ናት። በጥቅሉም ለሀገር ሙሉ ዕድገት መሠረት ለሆነው የኢንዱስትሪ ልማት መነሻ የሚሆኑ ጉዳዮች፣ በእንጭጭ ደረጃ የሚገኙባትን ሀገር ይህ ትውልድ ተረክቧል።

ግብርናው ባለበት እየረገጠ ነው። የኢንዱስትሪው አለማደግ በድህነትና ኋላ ቀርነት ውስጥ የሚዳክር ማኅበረሰብን ፈጥሯል። የሕዝባችንን መሠረታዊ ፍላጎት እንኳን ማሟላት አልቻልንም። ኋላ የመቅረት አንዱ መገለጫው የሕዝብን ምቾትና ደኅናነት (Welfare) ለማረጋገጥ መሟላት የሚገባቸው ሀብቶች በሚገባ አለመሟላት ነው። እያደገ ከሚመጣው የሕዝብ ፍላጎትና ተለዋዋጭ ከሆነው አካባቢ የተነሣ በየጊዜው የሚፈጠሩ ሥጋቶችንና ችግሮችን፤ ዕድሎችና ዐቅሞችን ተጠቅሞ ለመመከት በብቃት አልተሠራም። የሕዝብን ደኅናነትና ፍላጎት ለማርካት የሚያስችል በቂ ዐቅምና ሀብት

CS CamScanner

ለማዳበርም አልተቻለም። ሥጋትና አደጋ በየጊዜው የሚለዋወጡ ነገሮች ናቸው። በመሆኑም የሕዝብን ደኅናነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሀብቶችና ዐቅሞችም በዚያው ልክ መለዋወጥ ይኖርባቸዋል። የማረጋገጥ ሥራው የማይቋረጥ ዳሰሳ፣ ማሰላሰልና መፍትሔ ማበጀትን ይጠይቃል። ለዚህም ነው ከፍ ያለ የብልጽግና ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገራት በየጊዜው ተጨማሪና አዳዲስ ሀብቶችን

ለማምጣት የሚያስችል ጥረት የሚያደርጉት። በትጋታቸውም በየጊዜው የሚፈጠሩ አዳዲስ ሥጋቶችንና አደጋዎችን ለመመከት የሚያስችል ሀብትና ዐቅም ያፈራሉ።

ኋላ ቀርነት የሚለካው ሀገራት በትጋታቸው በሚያፈሩት ሀብትና ዐቅም፤ ሕዝባቸውንም ከችግርና ከሥጋት በማዳናቸው መጠን ነው። የፈጠርነው ሀብት ካለብን ትግርና ሥጋት አንጻር ሲመዘን የብልጽግናችንን ደረጃ ያሳየናል። ከኋላ የቀሩ ሀገራት የፈጠሩት ሀብት አነስተኛ፣ ያሉባቸው የቤት ሥራዎችም ተደራራቢ፣ የተከማቹና ሥር የሰደዱ ናቸው:: በአንጻሩ ከፊት የቀደሙ ሀገራት ያለባቸው ችግር ካከማቹት ሀብት አንጻር አነስተኛ ነው:: ይህንን የሕዝባቸውን ምቾትና ደኅናነት ከማስጠበቅ አንጻር አንዳንድ ሀገራት | ከዛሬ ተሻግረው የሩቁን ያሰላሉ። ለዚህም ከብዙ ዓመታት በኋላ ሊከሠት የሚችል አደጋና ሥጋትን መመከት የሚያስችል ዐቅምና ሀብት ፈጥረዋል። ለምሳሌ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የኢኮኖሚ መሠረታቸውን ከነዳጅ ጥገኝነት ወደ አገልግሎትና ወደ ሌሎች ዘርፎች በማስፋት፤ ችግርንና ሥጋትን የሚቋቋም ኢኮኖሚ እየገነቡ ነው። ሌሎች ሀገራት ደግሞ ከምድር አልፈው በጠፈር ውስጥ ያለውን ዕምቅ ሀብት ለመጠቀም የሚያስችል ሀብትና ዐቅም እየገነቡ ነው። በአንጻሩ ደግሞ ኋላ የቀሩ ሀገራት የትናንት የቤት ሥራዎቻቸውን በአግባቡ ባለማጠናቀቃቸውና ዛሬ ላይ የሚያስፈልገውንም ሀብት ባለመፍጠራቸው ከጊዜ ኋላ ይዳክራሉ።

ሀገራችን በተፈጥሮ ቁሳዊ ሀብት የበለጸገች እንደ መሆኗ መጠን፣ የብልጽግና መንገዷ የተፈጥሮ ሀብት እጥረት ካለባቸው ሀገራት በተሻለ ሊፋጠንይገባ ነበር። ይሁንና ባሳለፍናቸው ዘመናት በእነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ተመርኩዘን ወደፊት በመጓዝ፣ ለልጅ ልጆቻችን ወረት መተው አልቻልንም። የተገኙትንም አጋጣሚዎች ሁሉ ስናባክን ኖረናል። ዛሬ ጥቂት የማይባለው ሕዝባችን ኑሮው ከድህነት ወለል በታች ነው። በቀን ገቢው መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ሊያሟላ ቀርቶ፣ ቁርስ በልቶ ምሳ ለመድገም ይፈተናል። የሚቀይረው ልብስ ያጥረዋል። የሚኖርበት ቤት ይቸግረዋል።

ከቁሳዊ ሀብቶች በተጨማሪ የማይዳሰሱ ሀብቶች ለሀገር ዕድገት ያላቸው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። አንዳንዶቹ የማይዳሰሱ ሀብቶች ከቁሳዊ ሀብቶችም በላይ ለሀገር ብልጽግና ወሳኝ ዕሴቶች ናቸው። ከእነዚህ ዕሴቶች መካከል አንዱ የዳበረ ሰብአዊ ሀብት ነው። ተመሳሳይ የመልማት ዐቅምና ዕምቅ ሀብት ያላቸው ሀገራት፣ ለሰው ሀብት ልማት በሚሰጡት ትኩረት | ልዩነት ምክንያት፣ የተለያየ የብልጽግና ደረጃ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ብቃት፣ ዕውቀትና ተሰጥዖ ያለው የሰው ሀብት፣ ለብልጽግና መረጋገጥ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ብልጽግና መፍጠር የሚችል፣ ዕውቀትና ተሰጥዖው ከፍ ያለ ሕዝብ ውጤት ነው።

ለዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው ጀርመን ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከፈጠረባት ከፍተኛ መድመት በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ መገንባት የቻለችው አስገራሚ ኢኮኖሚ ነው። ጀርመን ከጦርነቱ በፊት በከፍተኛ ደረጃ የተማረና በክሂሎት የዳበረ የሰው ሀብት ነበራት። ከእዚያ ሁሉ ውድመት በኋላም የሰው ሀብቷን በከፍተኛ ደረጃ መገንባቷን አጠናክራ ቀጠለች። በዚህም ምክንያት በአጭር ጊዜ በዓለም ተወዳዳሪ የሆነ፣ በፈጠራውና በአይበገሬነቱ የሚታወቅ ኢኮኖሚ ለመገንባት ችላለች።

መለስ ብለን ብናየው ወደ ኋላ በቀሩና በበለጸጉ ሀገራት መካከል ዛሬ ለተፈጠረው ከፍተኛ ልዩነት ዋና ምክንያቱ የብልጽግና መሠረት የሆነውን የሠለጠነ የሰው ሀብት የማፍራት ጉዳይ ነው። በዕውቀትና በክሂሎት የዳበረ የሰው ኃይል እንኳን ለብልጽግና ምቹ ሁኔታ ባለበት ሁኔታ ቀርቶ፣ ማንሠራራት ከሚያስቸግርበት ሁኔታም ብልጽግናን ይወልዳል። ሀገራችንን ጨምሮ አብዛኞቹ ብልጽግና የራቃቸው ሀገራት፣ ያላቸው የዳበረ የሰው ሀብት እጅግ አነስተኛ ነው። የማዳበር ሂደቱም ብዙ ፈተናዎች ያሉበትና እጅጉን አዝጋሚ ነው።

CamScanner

በሀገራችን ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረበት ጊዜ የትምህርት ተደራሽነት መጠንና ጥራት በጣም ከመሠረቱ ለመፍታት የሄድነው ርቀትም እዚህ አንሥቶ እስካሁን ድረስ ማሳካት የቻልነው አነስተኛ ነው። ችግሩን ለማጤንና ከሥር ግባ የሚባል አይደለም።

ለብልጽግና መሠረት ነው ለምንለው የሰው ሀብት ልማት የተጋነው ይሄንን ያህል ከሆነ፣ በሌሎች ዘርፎች ያለንን ትጋትና በውጤቱም የሚኖረውን ውጥንቅጥ ከዚሁ መረዳት ይቻላል። ስለዚህ የትምህርት ሥርዓታችን መሻገር ያቃተው መሠረታዊ ተግዳሮቶች የትኞቹ ናቸው? በውጤቱስ ዋነኛ ተጠቂው ማነው? ከመሥራት ይልቅ በአቋራጭ መክበር የሚመርጥ የተማረ የሰው ኃይላችን ምን ያህሉ ነው? በተሳሳተ የሕክምና አሰጣጥ ምክንያት እያጣን ያለነው ዜጋ ምን ያህል ነው? በየጊዜ በፍርድ መጓደል የሚያለቅሱ እናቶችና ዐቅመ ደካሞችስ ስንት ናቸው? በክሂሎትና በጥራት ማነስ እየተጎዳ ያለው መሠረተ ልማታችንና እያጣን ያለነው ሀብት ምን ያህል ነው? አንድ ሰውስ በቀን መሥራትና ማምረት ያለበትን ያህል እየሠራና
እያመረተ ነው ወይ? ምርምርና መፍትሔ የሚፈልጉ ጉዳዮቻችን ናቸው።

በአጠቃላይ፣ አእላፍ ዘመናትን የተሻገርን፣ ብዙ መንግሥታትን ያፈራረቅን፣ የብዙ ታሪክና ባህል ባለቤቶች፣ እንዲሁም ብዙ ተፈጥሯዊ ሀብት ያለን ብንሆንም፤ ድህነትን አሸንፈን ለሕዝባችን ሐሴትን ከማጎናጸፍ አኳያ ብዙ ይቀረናል። መንገዳችንም በብዙ ዕንቅፋቶች ብዙ ርቀት ሲጓዝ አንዳንድ ሀገሮችም ከኋላችን ተነሥተው ከብልጽግና ማማ ላይ ሲደርሱ፣ የተሞላ ነው። አላላውስ ባሉ ዕንቆቅልሾች ውስጥ የምንዳክር ሆነናል። ዓለም በኢንዱስትሪ የእኛ ጉዞ "ባለህበት ርገጥ ሆኗል።

ከትናንት በስቲያም፣ ትናንትም፣ ዛሬም በአንድ ዓይነት ችግር ውስጥ የምንዋልል ሆነናል። የአንደኛው መንግሥት ተግዳሮት ለሌሎቹ ይተላለፋል እንጂ በዚያው ዘመን እልባት አያገኝም። ነገሥታቱ የተቸገሩበትን ደርግም ኢሕአዴግም፣ ዛሬም እኛ እንቸገርበታለን:: በዚህም የተነሣ ይህ ነው የሚባል ሀብት ያላካበትን፣ ሀብትንም ያልፈጠርን፣ ለሕዝባችንም ሐሴት ማጎናጸፍ የተሳነን፣ ልጆቻችን በሰቀቀን እንዲኖሩ የፈረድን ነን። የዕለት ጉርሱን ማሟላት የማይችለውና ከድህነት ወለል በታች የሚኖረው የሕዝባችን ቁጥር አሁንም ብዙ ነው። የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ይገኛል።

### 1.3. የአዙሪት ሰለባ

እርሻን ከማዘመንና ኢንዱስትሪን ከማስፋፋት አኳያ የሀገራችንን ሁኔታ ከላይ በጥቂቱ ተመልክተናል። በዚህም በዘመናት ሁሉ ለሁሉም የኢትዮጵያ መንግሥታት የጋራ ሆነው የተጣቡንን አንዳንድ ችግሮችን ማጤን አስችሎናል። እነዚህ ችግሮች ዋነኛው ውጤታቸው ደግሞ የድህነት አዙሪት ነው። በ"ውኃ ቅዳ ውኃ መልስ" ውስጥ መሽከርከር። ትናንትም፣ ከትናንት በስቲያም፣ ዛሬም እዚያው መርገጥ። ታሪክን ለጥልና ለንትርክ እንጂ ዞሮ ለማየት፣ ለመማር፣ ለመሻሻል አንጠቀምበትም። ታሪካችን ከታሪክነት አልፎ ህያው ሆኖ ዛሬም እኛን ያባላናል። ቀድሞ የመታን ዕንቅፋት ደግሞ ደጋግሞ ይመታናል። በዚህም የተነሣ ከዓለም ብቻ ሳይሆን ከችግሮቻችንም ወደ ኋላ ቀርተናል።

ችግሮቻችንን ቀድመን፣ አስፈላጊውን ዝግጅት አድርገን፣ ተጠናክረን አንጠብቃቸውም። ይልቁንም ውድመት ፈጥረው ጉዳት ካስከተሉ በኋላ እንደርሳለን። ከድቆሳው ሳናገግምና ያለፈውን ችግር ሳንፈታ፣ ሥጋቶቻችን መልሰው መላልሰው በአዙሪት መልክ ይጎበኙናል፡ በዚህ መልኩ በየዘመኑ ሥጋቶች ወደ አረንቋነት አድገው የፈጠሩብን ኪሣራ ቀላል አይደለም።

ተግዳሮቶቹ ደግመው ደጋግመው መምጣታቸውና ሕዝባችንን ችግር ውስጥ መክተታቸው የርግማንያህል ነው።መንግሥትናሌሎች የመፍትሔአካላትም ቀድመው አለመዘጋጀታቸው በርግማኑን ጥልቅነት ያሳያል። ችግሮቻችንን ለመፍታት የምንጓዝበት መንገድም አዙሪቱን የበለጠ የሚያበረታ ነው። አካሄዳችን አዲስ የመፍትሔ ሐሳብ የሚጎድለውና አዝጋሚ በመሆኑ ችግሮቻችን ይበልጥ እየተወሳሰቡ እዚህ ደርሰናል።

CamScanner

አንድ ማሳያ እናንሣ፤ ድርቅ በየጥቂት ዓመታቱ እንደ ሩቅ ዘመድ ይጎበኘናል፡ የቅርብ ጊዜያቱን እንኳ ብንወስድ፣ በአማካይ በየዐሥርና ዐሥራ ሁለት ዓመታት ድርቅ ሰፋ ባለ ደረጃ ጎብኝቶናል። ድርቅ በዓለም ላይ የሚከሠት፣ የአደጉ ያላደጉ ብሎ ሀገራትን የማይለይ የተፈጥሮ ሁነት ነው። የድርቁን ተጽዕኖ ከማሳነስ፣ ብሎም ከማክሰምና ከመቋቋም አንጻር፣ የአደጉ ሀገራት ካላደጉት ብዙ ልዩነት አላቸው። በአደጉ ሀገራት ከፍተኛ ዝግጁነት መኖሩ፣ ድርቅ ከዜናነት ባለፈ ይህ ነው የሚባል ጉዳት ሳያደርስ በቀላሉ የሚከላከሉት ጉዳይ ነው። በእኛና በመሰል ሀገሮች ግን ድርቅ ከተፈጥሯዊ ሁነትነት አልፎ፣ በረሃብ አለንጋ ሕዝባችንን የሚገርፍና የሚያረግፍ አውሬ ነው።

ረሃብ ለእኛ ከፍተኛ የንብረትም ሆነ ሰብአዊ ጉዳት አድርሶ፣ ትልቅ ጠባሳ ጥሎ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን አስከትሎ፣ የሚያልፍ የዘመናት ባላንጣችን ነው። ለዚህም በየዘመናቱ በድርቅ ምክንያት በሚመጣ ረሃብ የተነጠቅነው ወገን፣ ያጣነው ንብረት፣ የተፈጠረው ማኅበራዊ ቀውስና በአጠቃላይ በሀገር ላይ ጥሎ የሚያልፈው ጠባሳና መጥፎ ስም ማሳያ ነው!!

አስገራሚው ነገር በየዘመናቱ ድርቁን ለመከላከልና ሕዝባችንን ከረሃብ ለመታደግ የተጓዝነው ርቀት እዚህ ግባ የማይባል መሆኑ ብቻ አይደለም። የስሕተቶቻችን ተመሳሳይነትም አስገራሚ ነው። ድርቅን መከላከልን ማዕከል ያደረገ ወይም ሕዝብንና እንስሳትን በረሃብ ከመጠቃት የሚታደግ ዘላቂ መፍትሔ አላዋለድንም።

ሩጫዎቻችን ሁሉ ድርቁ ወደ ረሃብነት ተለውጦ ሰው ማለቅ ከጀመረ በኋላ ለመድረስ የሚደረጉ ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ” ዓይነት ናቸው።

ችግር የተማረው ነገር ስላልነበረ ሌላኛው ድርቅና ረሃብ ሲደርስም ተመሳሳይ ዓይነት በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ይህ ረሃብ በተደጋጋሚ መጥቷል። የንጉሡ አስተዳደር ከአንደኛው ሆኖ ንጉሡን ሥልጣናቸውን አሳጥቷቸዋል። ደርግ በ977 በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈትኖ | ርምጃን ሲወስድ ተመልክተናል። የቱ ረሃብም ለአብዮቱ መፈንዳት አንዱ ምክንያት ወድቋል። ለድርቅ የሰጠው መፍትሔ ድርጅን አስታኮ ወደ ሥልጣን የመጣ መንግሥት አይመስልም ነበር። ተመሳሳይ የርብርብ ምላሽ  ብዙ ሕዝብ እንዲያልቅብን አደረገ።

ኢሕአዴግ በዚህ ረገድ በተወሰነ መልኩ የተሻለ የምንለውን ርምጃ የተራመደ ይመስላል። በርግጥ ያለፈው አዙሪት አልለቀው ብሎ በ86ና በ97 የተፈጠሩ የድርቅ ሁኔታዎች አስቀድሞ በመከላከል ረገድ ይህ ነው የሚባል ርምጃ አልወሰደም ነበር። ነገር ግን ቢያንስ | ድርቁ ረሃብ ሆኖ ሕዝባችንን ከመጨረሱ በፊት ደርሶ፣ ሕዝባችንን ለመታደግ ተችሏል።

እንጠይቅ እስኪ፤ ከድርቅ አዙሪት ለመላቀቅ ወይም ችግሩን ለመቀነስ በሀገራችን ሁኔታ ትክክለኛው ሥር ነቀል መፍትሔ ምንድን ነው? መደጋገሙ የማይቀር ተፈጥሯዊ ሁኔታ አድርገን መቀበል ግድ ከሆነም ተጽዕኖውን የምንቀንሰው እንዴት ነው? ከመፈጠሩ በፊት ዝግጁ ሆነን ለመጠበቅ የተቸገርነውስ ለምንድን ነው? ለነገስ በምን መልኩ ዝግጁ መሆን ይጠበቅብናል? የሚሉት መልስ የሚሹ ጥያቄዎች ናቸው። ሌላው የአዙሪት ማሳያ ጦርነት ነው። “የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። የሀገር ውስጥ የእርስ በርስ ጦርነትና ከውጭ ወራሪ ጋር የተደረጉ ጦርነቶች፤ ለልማት ፋታ የነሡን የሠራነውንም መልሰው ሲያፈርሱብን የኖሩ ናቸው። በተለይ በዘመናዊት ኢትዮጵያ ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀምሮ፣ በዘመኑ ጦርነት ያልገጠመ፤ ከተት ያላወጀ መንግሥት የለንም ማለት እንችላለን። እንደው ዋና ዋናዎቹን እንኳን ብንወስድ ከቱርክ፣ ከግብጽ፣ ከደርቡሽ፣ ከእንግሊዝ፣ ከሱዳን፣ ከጣልያን፣ ከሶማልያና ከኤርትራ ጋር ተዋግተናል”።

የቅኝ ገዢዎችን ዕብሪት ለመታገል ያደረግነው ተጋድሎ ለዓለም በተለይም ለወንድም ጥቁር ሕዝብ ትምህርትና አርአያ የሆነ አኩሪ ገድል ነው። ከጎረቤቶቻችን ጋር የሚደረጉ ጦርነቶች ግን ሌላ መፍትሔ ያስፈልጋቸው ነበር። ጎረቤታሞች አብረን የምንዘልቅ ነን። ወዳጅ እንጂ ጎረቤት መምረጥ አይቻልም። ጎረቤትን ወዳጅ አድርጎ ተስማምቶ መኖር ብቸኛው አማራጭ

CamScanner

ነው። በድንበር ያለው ሕዝባችን ከሕዝባቸው ጋር ብዙ የጋራ ነገር አለው። መሰል ጦርነቶችን ለማስቀረት መደረግ የሚገባው ሁሉ ሊደረግና በውይይት ሊፈታ ይገባል።

ከጦርነት ታሪካችን አኳያ መመለስ ያሉብን ጥያቄዎች አሉ። ማሸነፍ መሸነፍ የጦርነት ባሕርይ ቢሆንም፣ ጦርነት የሚያስከትለውን ውድመት አስቀድሞ ከመከላከል አንጻር ምን ያህሉ በድንገት ደረሰብን? ምን ያህሉንስ በድርድር ለመፍታት ሞከርን ሌላ መፍትሔስ የለም ነበር ወይ? ሕዝባችን በጦርነት አዙሪት ውስጥ ልጆቹን እየገበረ፣ ዋና የሥራ አንቀሳቃሽ ወጣቶቿን በጦርነት ያጣች ሀገር የሚደርስባት ስብራትስ በምን ይለካል? ምንስ ያህል ነው? ምርመራ ይፈልጋል።

የውስጥ ፖለቲካችንም የዚሁ አዙሪት ሰለባ ነው። ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ እንኳን ብናየው ሁለት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች በዐሥራ አምስት ዓመታት ውስጥ ተከናውነዋል። ደርግ ሁለት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራዎች፣ ኢሕአዴግ ሁለት ሕዝባዊ ዐመጾች፤ አስተናግደዋል። ይህ እንግዲህ ከ951 እስከ 200 ድረስ ያሉት ስድሳ ዓመታት ብቻ፣ ከስድስት በላይ በሆኑ ዐመጾች የታጀቡ ናቸው።

ሕዝብ ይከፋል፤ በመንግሥት ላይ ያምጻል። መንግሥትን በኃይል ለመቀየር ይሞክራል። እንዲህ ያሉ ዐመጾች ሳይሳኩ ቀርተው መንግሥት ዕድል ሲያገኝ፣ ብዙ ነገር አስተካክሎ የሕዝቡን ጥያቄ በመመለስ ሰላማዊና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ጉዞ ይጓዛል የሚል ዕሳቤ አለ። የሚሆነው ግን በተቃራኒው መሆኑን ቀጣዩ ዐመጽ ይነግረናል። አስገራሚው ነገር ግን በዚህ መንገድ ተሳክቶለት ሥልጣን የያዘው አካልም ዐመጾችን መልሶ ማስተናገዱ ነው።

ፖለቲካቻን በእስራት ውስጥ የሚዳክር ነው። የፖለተካችን አዙሪትስ ምክንያቱ ምንድን ነው? በእነዚህ ሕዝባዊ ዐመጾች መካከል ያለው አንድነትና ልዩነትስ ምንድን ነው? የሚከተሉት ርዕዮተ ዓለም የተለያየ ቢሆንም፣ ፖለቲከኞቻችን ለሕዝባዊ ዐመጽ ያላቸው ምላሽ እንዴት ተመሳሳይ ሆነ? ከመጀመሪያው የሕዝብ ዐመጽ ፖለቲካችን ትምህርት ያልወሰደውስ ለምንድን ነው? ይህም ግምገማና ትምህርት የሚገኝበት መልስ ይፈልጋል።

በአጠቃላይ ችግሮቻችን ሁሉ አንድ ጊዜ ተጋፍጠን አሸንፈን ወይም ተሸንፈን የምንቀብራቸው እንግዳ አልሆኑም። በአዙሪት የምንጠመድባቸው ናቸው። ይልቁንም በየጊዜው እንደ ጥቁር እንግዳ በድንገት የምንቀበላቸው ሰርክ አዲስ አዙሪቶች ናቸው። በትምህርት፣ በጤና፣ በንግድ፣ ወይም በሌሎች ዘርፎችም ብንዘረዝር የአዙሪት አባዜው እንዳለ ነው። ትግሮቻችን እንደ ጆፌ አሞራ እንደ ዞሩን አሉ። ዛሬን ሲሰናበቱን፣ ለከርሞ እንጠብቃቸዋለን።

### 1.4. መዘግየት፣ መንሸራተትና መጥፋት

ችግሮችን ከሥር ነቅሎ ለመጣል አለመንቀሳቀስ፤ በአዙሪት ውስጥ መጠመድ፤ ከችግሩ ጋር የሚኖረው ሕዝብ ታዝቦ ብቻ የሚያልፈው ጉዳይ አይደለም። ለችግሮች የሚሰጡ የማስታገሻ መድኃኒቶች ለጥቂት ጊዜ የሕዝቡንም ቁጣና መከፋት ሊያበርዱ ይችሉ ይሆናል። መንግሥትም ለጊዜው ፋታ ያገኛል። የሕዝቡን መብረድና መንግሥት ያገኘውን ፋታ ተጠቅሞ ግን ወደ ዘላቂ መፍትሔዎች ማምራት ያስፈልጋል። ይህ ባልሆነባቸው የሀገራችን ሁኔታዎች የሕዝብ ዝምታ ጊዜ ጠባቂ ቦምብ ይሆናል። አንድ ቀን በአንዳች ምክንያት ይገነፍላል። በዚህ ዓይነት መንገድ ገንፍሎ የወጣ ሕዝብ ቁጣውን ሲገልጽና መንግሥትን ሲጥል በሀገራችን በተደጋጋሚ ተመልክተናል”።

አንድ ሥርዓት በየጊዜው የሚያድገውን የሕዝብ ፍላጎት ለመመለስ የሚያስችል ውጤታማነትና ቅልጥፍና መፍጠር ካልቻለ፣ ሕዝቡ በሥርዓቱ ላይ ያለው ርካታና መተማመን በየጊዜው እየቀነሰ ይመጣል። ይህ ጉዳይ በጊዜ መፍትሔ ካላገኘና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ከመጣ፤ ሕዝብ ሀገረ መንግሥቱን የፍላጎቱ አስጠባቂ አድርጎ መቁጠሩ ይቀራል። ይሄም የሀገረ መንግሥት ቅቡልነት መላላትን ያመጣል።

CamScanner

የሀገረ መንግሥት ቅቡልነት መላላት ለሀገራት አለመረጋጋትና መዳከም ዋና ምክንያት ነው። የሀገር ጥንካሬና የሥርዓቱም ቀጣይነት የሕዝብን ፍላጎት በማሟላትና ያንን ተከትሎ በሚኖር የሕዝብ ድጋፍ ላይ የተመሠረተ ነው። የሕዝብን ፍላጎት ማሟላት ያልቻሉ ሥርዓቶች፣ የዛሬና የቀጣይ ትውልድን ፍላጎት ማሟላት አይችሉም። ስለዚህ የቅቡልነት ፈተና፣ እሱንም ተከትሎ ግጭትና አለመረጋጋት የሚስተዋልባቸው ናቸው።

ሥርዓት አዎንታዊ ለውጥና ዕድገት አልያም አሉታዊ ለውጥና ድቀት ሊያስተናግድ ይችላል። ሥርዓቶች አዎንታዊ ለውጥ እየፈጠሩና እየጠነከሩ ካልሄዱ፤ አሉታዊ ለውጥ እየተፈጠረባቸው ወደ ሥርዓት መበስበስ ያመራሉ። ለዚህም ዋናው ምክንያት የሕዝብ ፍላጎት የሚለዋወጥ ብቻ ሳይሆን፣ ያለማቋረጥ የሚያድግም ጭምር ስለሆነ ነው። ሥርዓቱ ቻለም አልቻለ፣ ተመቸውም አልተመቸው፣ የትኛውንም ምክንያት በመደርደር የሕዝብን ፍላጎት ሳይመልስ መቅረት አይችልም።

ቀድሞ ነገር ሥርዓቱ ወደ ሥልጣን ሲመጣ፤ የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስ ነው። አንገብጋቢና ጊዜ የማይሰጡ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ ካላገኙ የሥርዓቱ አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ ይገባል። በተለይም ባላደጉ ሀገራት የሕዝቡ ጥያቄዎች ለመኖር አስፈላጊ በምንላቸው መሠረታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በመሆኑ ሳይመለስ ማደር አይችልም። ፋታም አይሰጥም። በመሆኑም አንድ ሥርዓት ወደ ሥልጣን መጣ ወይም ሀገር ተረከበ ማለት ለማያቋርጥ የሕዝብ ፍላጎት ምላሽ መስጠት ጀመረ ማለት ነው። ሥርዓቱ በሌላ እስኪተካ ድረስ የማያቋርጥ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ውስጥ ገባ ማለት ነው።

ይሄንን ግዴታ በማይወጡ ወይም ለመወጣት በሚዘገዩ ሥርዓቶች ላይ ሕዝቡ ቁጣውን ይገልጻል። ሥልጣናቸውንም ለሌሎች አሳልፎ ይሰጣል። የአምባገነኖች ሥርዓት እንኳን ከዚህ ሊያመልጥ አይችልም። ሕዝብ ራሱን ለማዳን ሲል በመንግሥት ላይ መነሣቱ የማይቀር ነው። በዓለማችን በየጊዜው የምናየው የሕዝብ ዐመጽ ምክንያት በአብዛኛው የሕዝብ ምቾት ማነስና የሐሴት መጓደል ነው። ስለዚህ አንድ ሥርዓት ከሕዝቡ በሚያገኘው የእፎይታ ጊዜ ብዙ ነገሮችን ማስተካከልና ማመቻቸት ይገባዋል። ፋታውን ተጠቅሞ ሥርዓቱ ለሕዝቡ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥበትን መንገድ መቀየስ አለበት። ይህንን ካላደረገ መዘግየት፤ መንሸራተትን፤ መንሸራተት ከተባባሰም መጥፋትን ማስከተሉ አይቀሬ ነው።

ኋላ የቀሩ ሀገራት ለብዙ አደጋዎች ተጋላጭ ናቸው። አደጋዎቹ በጊዜውና በአግባቡ መፍትሔ ካላገኙ ሀገራቱን ከፍ ወዳለው ኋላ መቅረት እንዲሁም ወደ መጥፋት ይወስዷቸዋል። እነዚህ ሀገራት ከጊዜ ቀድመው የተገኙ ባለመሆናቸው፣ የመፈናፈኛ ምኅዳርና ትርፍ ጊዜ የላቸውም። ከዚህ በላይ ሲዘገዩ፣ የሚባክነው ዕድልና ጊዜ፣ ተጨማሪ ጫና ያመጣባቸዋል።

ይበልጥ ወደ ኋላ ይጎትታቸዋል፤ ወደ ባሰ አረንቋም ያስገባቸዋል። ወደ መጥፋትም ይወስዳቸዋል።

የሕዝብን ፍላጎት የማሟላት ጉዳይ፣ ፍላጎቱን ከመረዳት ይጀምራል። ለመረዳት ደግሞ መስማት፣ መቅረብና ችግሩን መካፈል ያስፈልጋል። ሥልጣን “የዛፍ ላይ ዕንቅልፍ" መሆኑን መረዳት ይሻል። አገልጋይነት ከብር መሆኑን፤ በተጻራሪው ደግሞ መሾም አድራጊ ፈጣሪነት አለመሆኑን መገንዘብ ይፈልጋል። ሕዝብ የማገልገል ክብር አድርገን መመልከት ጠቃሚ ነው። “ለጭቁኑ ሕዝብ ጥቅም ሲባል ሥልጣን ማለት አስተምሮ ለዚህ ያደረሰንን በጭቁኖች ትግል ሥልጣን ላይ ወጥተናል” ካልን ጥቂት ዓመታት በኋላ፤ ለሥልጣናችን ሲባል ጭቁኖችን ወደ መጨቆን መሻገር የማይለካ ውርደት ነው።

የመደብ ልዩነት ፈጥሮ፣ በራስ ዓለም ዛቢያ ላይ መዞር፣ በሁሉም አቅጣጫዎት እንዳናይ ያደርጋል። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ሕዝብ ትዕግሥቱ ሲያልቅ አሽቀንጥሮ መጣሉ የማይቀር ነው። ሕዝቡን ማገልገልና በሕዝቡ መገልገል ለየቅል ናቸው። የሕዝብ ጥያቄን ለሥልጣን መጠቀምና ሥልጣንን የሕዝብን ጥያቄን ለመመለስ መጠቀም ለየቅል ናቸው። በሕዝብ ስም ምለን ተገዝተን ሥልጣን ከያዝን በኋላ የሕዝቡን ጥያቄ ለመረዳትና ለመመለስ የማንተ ከሆነ፤ ራሳችን በራሳችን ላይ ብቻ ሳይሆን በሀገራችንም ላይ እየተኮስን ነው ማለት ነው።

CamScanner

አንድ ሕዝብ ጥያቄዎቹን መልስ ብሎ በተለያየ መልኩ መናገር ከጀመረ፤ ሥርዓቱ በመንሸራተት ላይ ነው ማለት ነው። ሥርዓቱ ለመጥፋት ጫፍ ላይ ደርሷል ማለት ነው:: ሕዝብ መጀመሪያ ይታገሣል፤ ዕድል ይሰጣል፤ ሁኔታን ገምግሞ ጥያቄውን በሰላማዊ መንገድ ያቀርባል፤ ለመልሱም ጊዜ ይሰጣል፤ አይቶ አይቶ መዘንጋቱን ካረጋገጠ ግን ሥርዓቱን እንደ ጠላቱ ይቆጥራል። ከዚያ ጠላቴ ያለውን ሥርዓት ለማጥፋት ይነሣል። የተነሣን ሕዝብ ደግሞ ማስቀመጥ አይቻልም። የሀገራችንም ሆነ የዓለም ተሞክሮ የሚነግረን ይህንኑ ሐቅ ነው።

በአጠቃላይ ሀገራችን ከብዙ ሀገራት የቀደመና፤ በብዙ መልኩ አርአያ ሊሆን የሚችል ሥልጣኔ ባለቤት ከነበረችበት ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት፤ በእጅጉ ወደ ኋላ ቀርታለች፡ በዘመናት ሀገራችንን ሲያስተዳድሩ የነበሩ አካላት፤ ሀገራዊ ሀብት ከመፍጠር አንጻር ብዙም አልተሳካላቸውም። ለሰርክ መሠረታዊችግሮቻችን ይወስዱ የነበረው መፍትሔም ቀዳሚዎቹ የተሳካ መፍትሔ የሰጡ ይመስል፤ ተመሳሳይና ከፊተኞቻቸው ትምህርት ያልወሰደ አዙሪት ይመስላል። በዚህም ዓለም ወደ አምስተኛው አብዮት ሲሸጋገር፤ ችግሮቻችንን እንደተሸከምን እየተጓዝን ነው። ለዘመናት ሥልጣንን አምኖ ለሰጠን ሕዝብ ምላሻችን ለምን ይህ ሆነ? ድጋፍ ለሆነልን ሕዝብ ደጀን መሆን ለምን አቃተን? ለምን ወደ ኋላ ቀረን?

## ምዕራፍ ሁለት

## 2. የዓባይን ልጅ ለምን ውኃ ጠማው?

ሀገራችን ከዓለም ወደ ኋላ ለመቅረት ምክንያት እንዳይኖራት ተደርጋ የተፈጠረች እስኪመስል ድረስ ብዙ ጸጋን የተቸረች ምድር ናት። ከመሬት እስከ መልከ ብዙ የአየር ሁኔታ ተንበሽብሻለች። ከተፋሰሶች እስከ ከርሰ ምድር ውኃ ተጥለቅልቃለች። ከወርቅ እስከ ታንታለም፣ ከጋዝ እስከ ፖታሽ ታድላለች። ከስትራቴጂያዊ ጂኦፖለቲካዊ አቀማመጥ እስከ ከፍተኛ ተራሮች ተሞልታለች። ከታሪክ እስከ ቅርስ፣ ከኅብረ ብሔራዊነት እስከ ብዝኃ እምነት ተትረፍርፋለች።

ኢትዮጵያ ከስጦታዎች ይህ አጠራት የምትባል አይደለችም። እነዚህን የተፈጥሮ ችሮታዎች ተጠቅመን ማደግ እንዳንችል ብዙ ተግዳሮቶችን በታሪካችን አሳልፈናል። በሆኑ ዘመናት ብቅ ያሉትን የፈጠራ ፍንጮችም፤ ፈጥነን ወደ ዘላቂ ልማት አልቀየርናቸውም። ያለንን ጸጋም አዳዲስ ሀብት ለመፍጠር አልተጠቀምንም። እነዚህ ተግዳሮቶች አንዱ ለአንዱ መነሻ ምክንያት እየሆነ፤ ዛሬ ካለንበት የድህነት ደረጃ ላይ እንገኛለን። የመከራ አዙሪትና የሥልጣኔ ሾተላይ አለብን፡

ሀብቶች ሳይባክኑ በሀገር ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውሉ እያንዳንዱን ሀብት ወደ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለመቀየር መሠረተ ልማት ወሳኝ ነው። በሀገራት የልማት ጉዞ መሠረተ ልማት መገንባት የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠውም ለዚህ ነው።ይሁንና መሠረተ ልማቶችን መገንባት በቀላል ዐቅም የሚተገበር አይደለም። በአነስተኛ ሥራዎች ጀምሮ እያደጉ መሄድ የብዙ ሀገራት ተሞክሮ ነው። ከትንሽ ተነሥቶ ሩቅ የሚያልም ጉዞ ማሳካት፤ ወደ ሚቀጥለው ግዙፍ መሠረተ ልማት ግንባታ ለመሸጋገር ወሳኝ ነው። ማደግ ዳገት የሆነባቸው ሀገራት ተግዳሮት፤ ከእነዚህ አነስተኛ ጉዞዎች መኮላሸት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

ጉዞን ከሚያበላሹ ተግዳሮቶች አንዱ የመልካም ሥርዓት መጓደል ነው። ሀገር የማበልጸግን ጉዞ ማሣለጥ ዓላማው ያደረገ ሥርዓት ያስፈልጋል። ይህ ሥርዓት የተደራጀና ራሱን እያሻሻለ የሚጓዝ መሆንም አለበት። በተቃራኒው በቢሮክራሲ ሠንሰለት የታነቀ እና ሙስና የተንሠራፋበት ሥርዓት፣ የሀገር ዕድገት አሣሪም አክሳሪም ነው። እንዲህ ያለ አሣሪና አክሳሪ ሥርዓት አነስተኛ መሠረተ ልማቶቹን ገና በእንጭጩ ያኮላሻቸዋል። ለልማት መሠረት የሚሆነውን መነሻ ግንባታ ገና ከጅምሩ ያስተጓጉላል። ሀገር ከመምራት ይልቅ የግል ጥቅምና ጊዜያዊ ድሎትን ያስቀድማል። እንዲህ ዓይነት አክሳሪና አሣሪ ሥርዓት ሀገራችንን ጨምሮ የብዙ ሀገራት ተግዳሮት ነው።

ማደግ ዳገት በሆነባቸው ሀገራት፤ ሌላኛው ተግዳሮት ደግሞ እየደመሰሱ መቅዳት ነው:: አነስተኛ መሠረተ ልማቶች ተሠርተው ብዙም አገልግሎት ሳይሰጡ በግጭት፣ በሙስናና ይበላል። ለልማት መዋል የሚችሉ ሀብቶችን ይቀማል።

CamScanner

በጥቅሉ ሀገርን አፍርሶ እንደ አዲስ መደምሰስና መቅዳት። ጦርነት የልማት ጅማሮዎችን ያፈርሳል። ትኩስ የሥራ ኃይላችንን በግዴለሽነት ማፈራረስ። ከዚያ ደግሞ እንደ አዲስ ብዙ ሚልዮኖችን አፍስሶ መጀመር:: ከዜሮ እንድትጀምር ያስገድዳል። ለመጀመር የሚሆነውንም ሀብት አጥፍቶ ስለሚያልፍ፣ ሀገርን ወደ ቀውስና ወደ ልመና ይመራል። ጦርነት ለብዙ ሀገራት ወደ ኋላ መቅረት ዋናው ምክንያት ነው። የሀገራችን አንዱ የሥልጣኔ ሾተላይም ጦርነት ነው።

በአጠቃላይ የሀገራችን ወደ ኋላ መቅረት የተሠናሠሉ ችግሮች ውጤት ነው። የጦርነት፣ የሙስና፣ የግዴለሽነትና የሌሎችም። እነዚህ ችግሮች ሀብቶችን በማባከን በቂ መሠረ ልማት እንዳይኖር ያደርጋሉ። በቂ መሠረተ ልማት ለመገንባት፤ በቂ ሀብት የሚጠይቅ እንደመሆኑ፤ በእጅ የሚገኘውን ሀብት አብቃቅቶ መጠቀም የግድ ነው። ማብቃቃት ደግሞ ከአስቻይ ሥርዓት መኖር ጋር የተያያዘ ነው። የአስቻይ ሥርዓት አለመኖርና የብልሹ አሠራር መንሠራፋት፣ የመልማት ዕድልን ከጅምሩ ያኮላሻል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ጦርነትና ግጭት ያሉት አፍራሽ ክሥተቶች፣ ጅምር መሠረተ ልማቶችንና የመልማት ዐቅሞችን ያወድማሉ። በጅምር ያሉ ዕድገቶችን፣ የመሠረተ ልማት ጅማሮዎችንና አልሚ የሆነውን የሰው ሀብትን ያጠፋሉ። ሀገርን ማንሠራራት ከሚያዳግትበት አዘቅት ውስጥ ከትተው ያልፋሉ።

ስለዚህ በሀገራችን የባከኑ ሀብቶች የትኞቹ ናቸው? በምን ደረጃ ሊያሳድጉን ይችሉ ነበር? የሥርዓቶቻችን መሠረታዊ ችግሮችስ የትኞቹ ናቸው? በየዘመናት ሀገራችንን ያስተዳደሩ መንግሥታት ችግሮቹን ከመለየትና ከመታገል አንጻር ምን ያህል ተጓዙ? አሁንስ ችግሮቹ በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ የመሠረተ ልማት ክፍተታችን ምን ያህል ነው? እስከ አሁን የተሄደበት መንገድ ከምንፈልገው ደረጃ ያደርሰናልን? ወይንስ ሌላ መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል" ጦርነትና ግጭት ለሀገራችን ወደ ኋላ መቅረት በምክንያትነት የሚነሡ ዋና ጉዳዮች ናቸውን? ጦርነትና ግጭት ሀገራችን ላይ ምን ያህል ውድመት አስከተሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥልቀት ማየትን ለተመራማሪዎቹ እንተዋለን። እዚህ ግን በተወሰነ ደረጃ መመልከቱ የድህነታችንን ሥር ለማግኘትም ሆነ መፍትሔ ለማመላከት ወሳኝ በመሆኑ እንዳስሰዋለን።

## 2.1. ትክክለኛውን ጥያቄ አለመጠየቅ

በኢትዮጵያ ዘመናዊ የሥልጣኔ ጉዞ ውስጥ የውጭ ሀገር የልማት ሞዴሎችን(አስተሳሰቦችን ወደ ሀገር ውስጥ አምጥቶ የመተግበር አካሄድ ለዘመናት የቆየና የተሟላ ውጤት ያላስገኘ ነው። ለዚህም እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሰው በልማት ሞዴሎቹና በኢትዮጵያ ነባራዊ ሥሪት መካከል ያለው ከፍተኛ ልዩነት ከግንዛቤ አለመወሰዱ ነው። እንደ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጃፓን፣ ሩሲያና ደቡብ ኮሪያ ያሉ ሀገራትን የልማት ስኬትን ወደ ሀገራችን አምጥቶ ሙሉ ለሙሉ ለመድገም በመመኘት፤ የኢትዮጵያ ልሂቃን በተለያየ ጊዜ ከሀገራችን እውነታዎች ጋር የማይዛመዱ የልማት ሞዴሎችን ሲተገብሩ ቆይተዋል።

እነዚህ የውጭ ሀገር የልማት ሞዴሎች በተፈጠሩባቸዉ ሀገሮች ውጤታማ ቢሆኑም፤ ወደ ሀገራችን መጥተው ሲተገበሩ ግን የኢትዮጵያን ባህል፣ ታሪክ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ግምት ውስጥ ያላስገቡ ነበሩ። ኢትዮጵያ ከብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገራት በተለየ በቅኝ ግዛት ሥር ባለመውደቋ የራሷን የዕድገት ጎዳና በነጻነት እንድትመርጥ ዕድል አስገኝቶላት ነበር። ነገር ግን የኢትዮጵያ ልሂቃን ኢትዮጵያን የሚመስል ሞዴል ከመፍጠር ይልቅ ወታደራዊ ጥንካሬን፣ የተማከለ አስተዳደርንና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ያጣምራሉ ብለው ወዳመኑባቸው የውጭ ሞዴሎች ፊታቸውን ደጋግመው አዙረዋል።

ኢትዮጵያ የውጭ የልማት ሞዴሎችን ወደ መንግሥታዊ ሥርዓቷ ማምጣት የጀመረችው በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ነው። በወቅቱ ንጉሡ ለልማት ሞዴል ፍለጋ ያማተሩት ኢምፔሪያል ወደነበረችው ሩሲያ ነው። ዓላማውም ማዕከላዊና በወታደራዊ ጥንካሬ ላይ የተመሠረተ አንድነት ያለው የማይበገር መንግሥት ለመመሥረት ያለመ

CamScanner

ነበር።ለዚህ የመከላከያ ኃይልን ለማጠናከር የተሠራውን ሴባስቶፖል መድፍ እንደ ጥረት ተምሳሌት መውሰድ ይቻላል። ይህም ከዚያ በኋላ ለነበሩት ገዥዎት በር ከፋች አርአያ በመሆን፣ ወደ ውጭ ሀገራት ሞዴሎች እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል።

ዐፄ ምኒልክ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ የተቀዱ ትምህርት ቤቶችን፣ የጤና ተቋማት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችንና የምዕራባውያንን ዓይነት የአስተዳደር መዋቅሮችን በስፋት (የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ያላማከሉና ተደራሽ ለማድረግ የሥርዓት ድጋፍ ያልነበራቸው ነበሩ:: አስተዋውቀዋል። ነገር ግን እነዚህ የሥርዓት ለውጦች አብዛኛውን በግብርና የሚተዳደረው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በአርአያነት ከተወሰዱት መካከል ጃፓን አንዷ ነበረች። ጃፓን እንደ ሌሎቹ ስኬታማ ሀገራት ሁሉ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተጠቀመችው የማገገሚያ ሞዴል፤ የሀገሪቱን ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ፣ ባህልና ሥነ ልቡና መሠረት ያደረገ ሞዴል ነው። ጃፓን ከጦርነቱ ውድመት በኋላ በከፍተኛ ደረጃ የተቀናጀና የተሃከለ መንግሥታዊ ሥርዓት አምጥታለች። ይሄንንም መሠረት አድርጋ በቴክኖሎጅ በኢንዱስትሪና በመሠረተ ልማት ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት በማፍሰስ፤ በፍጥነት ራሷ ገንብታለች።

ይህ ሞዴል የተለያዩ የጃፓን ነባራዊ ሁኔታዎችን መሠረት ያደረገ ነበር። የጃፓን ባህል በኮንፊሺየስ አስተምህሮ የተገነባ በመሆኑ ማዕከላዊ ሥልጣንን ያከብራል። ለሥራ ከፍተኛ ቦታ ይሰጣል። በሌላ በኩል ደግሞ በጃፓን ከ200 ዓመታት በላይ የዘለ የኢንዱስትሪያዊነት መሠረት አለ። ጃፓኖች እነዚህ ሁለቱን ሀገራዊ ዕሴቶች ወስደው ከአሜሪካ ከተገኘው ሞዴልና ድጋፍ ጋር በማዋሐድ፣ አስደናቂ ስኬት ለማስመዝገብ ችለዋል።

ይህንን ያስተዋሉ የኢትዮጵያ ልሂቃንም በወቅቱ ጃፓን እንዴት ሠለጠነች? ሲሉ ጠየቁ። ኢትዮጵያ ለምን ደኸየች የሚለውን ግን ዘነጉት። ሁለቱን ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሽ የሚሆን ስልት መቀየስ ከፍተኛ የአተያይ ልዩነትን ያመጣል። በጃፓን ስኬቶች በመነሣሣት የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በ923 በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ሕገ መንግሥት ከጃፓን የሜጂ ሕገ መንግሥትን በመቅዳት አወጣ። በወቅቱም የኢትዮጵያ ልሂቃን በጃፓን ፈጣን የማገገሚያ ስልት ተደምመው የወጪ ንግድ ላይ ያተኮሩ አንዱ ስትሪዎችን በማስፋፋት፣ ለሰፋፊ እርሻዎች ትኩረት በመስጠት እና ለመሠረተ ልማት ቅድሚያ በመስጠት ተመሳሳይ ውጤትን ለማግኘት አልመው ነበር።

ሆኖም በወቅቱ እንደ ጃፓን ዘላቂ የኢንዱስትሪ ዐቅም፣ የሠለጠነ የሰው ኃይል፣ ሥራንና ሠራተኛን የሚያከብር የሥራ ባህል፣ ወይም ተመጣጣኝ የፖለቲካና የኢኮኖሚ መረጋጋት ባለመኖሩ በኢትዮጵያ ይህን ሞዴል ማላመድ ከባድ ነበር። ኢትዮጵያ የጃፓንን ውጤት ልትደግም ትችላለች የሚለው ግምት የሀገሪቱን የግብርና ኢኮኖሚ፣ መሠረተ ልማትና ውስብስብ የፖለቲካ ምኅዳር ያላገናዘበ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያን ተግዳሮቶች ሊፈቱ የማይችሉ ፖሊሲዎች እንዲወጡና ተግባራዊ እንዲሆኑ አድርጓል።

ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ቀጥለውም ፊታቸውን ወደ ምዕራባውያን ሞዴሎች በተለይም ወደ ብሪታንያ ንጉሣዊ ሥርዓት ሕገ መንግሥት አዞሩ። በጣልያን ወረራ ወቅት በእንግሊዝ ያሳለፉት አምስት ዓመት ለዚህ አስተዋጽኦ ነበረው። የመጀመሪያውን ሕገ መንግሥት በማሻሻል በ1948 ሕገ መንግሥታዊ ሥልጣንን ያመጣጥናል የተባለ ሌላ ሕገ መንግሥት ወጣ። በተግባር ግን ሥልጣን አሁንም የማዕከላዊው መንግሥት ሆኖ ቀጠለ። በኢኮኖሚውም ረገድ ግብርናውን ለማዘመንና ከዓለም ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ጋር ያለውን ውሕደት ለማሳደግ የአምስት ዓመት የልማት ዕቅዶችን እንዲሁም እንደ አዋሽ ሸለቆ ባለ ሥልጣን ያሉ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን አስተዋውቀዋል።

ሆኖም እነዚህ የተደረጉ ለውጦች በአብዛኛው ምሁራን ቢደገፉም ውጤታማ አልነበሩም. ይህ የሆነበት ምክንያት የተማከለ አስተዳደርና የመሬት ሪፎርምን በመገደብ ማኅበራዊ መሠረታዊ ማ ነበራዊና ኢኮኖሚያዊ እኩልነት ያልፈታና የምዕራባውያንን ሞዴሎች ተዋረድን ያጠናከረ ባለመሆኑ ነው። ይህ በተግባር ላይ የዋለው ሞዴል የኢትዮጵያን የተከተለ በመሆኑ፣ ለሀገሪቷ ተጨማሪ ፈተና ሆኖባት ነበር።

CS CamScanner

በተመሳሳይ የደርግ መንግሥት የማርክሲስት ሌኒኒስት ሞዴልን በመከተል በሶቪየት ኅብረት ተጽዕኖ ሥር ወደቀ። ኅብረተሰብአዊ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን መከተልም ጀመረ:: ለዚህም ማዕከላዊነትን የተከተሉ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን በመተግበር መሬት ላራሹን ዐወጀ። በግብርና የኅብረት ሥራ ማኅበራትን አቋቋመ። የግል የኢኮኖሚ አውታሮችን በመውረስ መንግሥታዊ ኢኮኖሚን አጠናከረ። በመንግሥት የሚተዳደሩ እርሻዎችንና ኢንዱስትሪዎችን ለማሳደግ በማለም ማዕከላዊ ቁጥጥርን መሠረት ያደረገ ሥርዓት ዘረጋ።

ደርግ በግለሰቦች የተያዙ ሰፋፊ ሀብቶችን ክፍፍል በማድረግ የመደብ ልዩነትን ለማስወገ ጥረት አድርጓል። ሆኖም ግን ሂደቱ የኢትዮጵያውያንን ልዩ ልዩ ባህሎች፣ የአካባቢ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና የገጠር ኢኮኖሚውን ከግምት ያላስባ ነበር። በዚያ ላይ በወቅቱ ደርግ የወረሰው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያካበተው ሀብት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: በውጤቱም ሀብትን ከማከፋፈል ይልቅ ድህነትን ወደ ማከፋፈል ያዘነበለ ሆነ። ትላልቅ እርሻዎችን ለመፍጠር ሙከራ አድርጎ የነበረ ቢሆንም የአብዛኛው መተዳደሪያ የሆነውን የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሩን ግብርና የማዘመን ሥራ ባለመሥራቱ ውጤታማ አልሆነም::

ይልቁንም የግብርና ምርት ዋጋ ጣሪያ በመጣልና በአስገዳጅነት አርሶ አደሮች ምርታቸውን ለማኅበራት እንዲሸጡ ማድረጉ ዘርፉን የበለጠ ጎዳው። በአጠቃላይ ደርግ የመረጠው መንገድ ባህላዊ የግብርና ዘዴዎችንና የጋራ መሬት ባለቤትነትን ከሚከተሉ የአካባቢው ማኅበረሰቦች በኩል ተቃውሞ እንዲገጥመው አድርጎታል።

የደርግ መንግሥት ለኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ተግባራቱ በግዳጅ ሀብት ማሰባሰብ ጀመረ። ከአንድ ዕዝ የሚመራው የኢኮኖሚ ሥርዓት በዐቅምና በቴክኖሎጂ ማነስ የተቋማትን እንቅስቃሴ አዳከመው። የግብርና ምርትና ምርታማነት ቀነሰ። በዚህ የተነሣ የምግብ እጥረት ተፈጠረ። ይህም መጠነ ሰፊ ቅሬታ እንዲፈጠር አደረገ።

ሞዴሉ በሶቪየት ኅብረት የተገኘውን ስኬት ለመድገም ያለመ ቢሆንም፤ ኢትዮጵያ እንዲህ ያለውን ሥርዓት ለመደገፍ የሚያስችል ኢንዱስትሪያዊ፣ ማኅበራዊና አስተዳደራዊ ዐቅም አልነበራትም። የአስተዳደር ዘይቤው በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያገለለ በመሆኑ የተጀመሩት ጥረቶች ወደ ኋላ ቀርተው ለረሃብና ለሰፊ የኢኮኖሚ ችግር ብሎም ለአለመረጋጋት ዳርጎናል።

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም ከሶቪየት ኅብረት ታሪካዊ ዐውድ ጋር የተስማማ ነገር ነበረው። መነሻውም የራሳቸውን ችግር በራሳቸው መንገድ ለመፍታት የሠሩት ነው። ይህ ዕሳቤ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም አልተደረገም። ለሌላ ሰው የተሰፋ ልብስን በግድ እንደመልበስ ሆነ። ረዘመ፤ ተንዘረፈፈ፤ አጠረ፤ ተወጣጠረ። ስለዚህ አደናቀፈንና ወደቅን።

ከደርግ ውድቀት በኋላ ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት ችግር መፍታትን ዋና ዓላማው አደረገ። የብሔር ጥያቄን ለመመለስ አዲስ የፌዴራል ሥርዓትን አስተዋውቋል። የብሔሮች ጥያቄ መመለሱ ተገቢና አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንም፣ ሞዴሉ ብሔርን ከአስተዳደራዊ ወሰን ጋር ማገናኘቱ ጽንፍ ብሔርተኝነትን አቀጣጥሏል። የመሬት ውዝግብና ተያያዥ ውጥረቶችንም አስከትሏል። ብሎም ሀገራዊ አንድነትን ሸርሽሯል።

ከልማት ሞዴል አኳያም ኢሕአዴግም በበኩሉ ፊቱን ወደ ሌላ የውጭ ሞዴል አዞረ። በምሥራቅ እስያ ዕሳቤ የልማታዊ መንግሥት" ሞዴልን በሀገራችን ለመተግበር ተንቀሳቅሷል። ይህ ሞዴል ደቡብ ኮሪያንና ቻይናን በመመልከት የተቀመረ ነው። የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ዕድገት በመንግሥት ጣልቃ ገብነት ሊያመጣ ያስባል። የተመረጡ ኢንቨስትመንቶችን በማልማትና መሠረተ ልማትን በማስፋፋት ላይ ያተኮረ ነው። ሆኖም ተግባራዊ የተደረገው ሞዴል ዘላቂ የገንዘብ ድጋፍ አላገኘም። የሠለጠነ የሰው ኃይል እጥረትም ገጥሞታል። በዚህ ሞዴል ውጤታማ የሆኑ ሀገራት የገነቡት ዓይነት አሳላጭና ጠንካራ ሥርዓትና ቢሮክራሲ አልተፈጠረም። በተጨማሪም ውስብስብ የብሔር ተኮር ፍላጎቶች ታላላቅ ፈተናዎች ፈጥረውበታል።

CamScanner

የኢሕአዴግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ከምሥራቅ እስያ ሀገራት የተቀናጀ ብሔራዊ ማንነትና የተረጋጋ መንግሥታዊ ሥርዓት በተለየ መልኩ የኢትዮጵያን ብዝኃነት ያላማከለ ነበር። በዚህ የተነሣ ፖለቲካዊ ውጥረት አስከትሏል ዕድገቱም ዘላቂና ፍትሐዊ አልነበረም። በኋላም የመንግሥትን ሀብት ለፖለቲካና ለወታደራዊ ባለ ሥልጣናት በማዋል ወደ ጥልቅ ሙስና እንዲወርድ አድርጎታል።

እነዚህ ሁለት ሞዴሎችን ማለትም የሩሲያን የ" ብሔራዊ ጥያቄ" አፈታት እና የምሥራቅ እስያን "ልማታዊ መንግሥት" ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ዕድገትን ለማምጣት የተደረጉ ሙከራዎች አልተሳኩም። ውጤቶቹም ወደ ውጭ የማማተርና ትክክለኛውን ጥያቄ ያለማንሣት አዙሪት ማሳያዎች ናቸው።

ትክክለኛውን መልስ ከመፈለግ በፊት ትክክለኛውን ጥያቄ ማንሣት ይቀድማል። የውጭው ሞዴል ከመፈለግ በፊት የሀገር ውስጥን ዐቅምና ድክመት መፈተሽ ይቀድማል። ይህ ቢሆን ኖሮ ከውጭ የሚመጡ የተለያዩ የልማት ሞዴሎችን ከሀገር በቀል ጥንካሬዎች፣ ፍላጎቶችና ዕሴቶች ጋር በማጣጣም ለኢትዮጵያ የሚሆን ስትራቴጂ ማዘጋጀት ይቻል ነበር። "ኢትዮጵያ እንደ ጃፓን ወይም እንደ ቻይና እንዴት ልትለማ ትችላለች? " የሚለውን ጥያቄ በመቀየር፤ ኢትዮጵያ የበለጸገ ማኅበረሰብ ለመገንባት ምን ዓይነት ሀገር በቀል ፖሊሲዎችን መጠቀም ትችላለች? ከውጭስ የትኞቹን ልትቀምር ትችላለች? ማንኛውም ፖሊሲ መለካት ያለበት በሠራበት ሀገር ካመጣው ለውጥ አንጻር ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ሁኔታ አንጻርም መሆን አለበት።

ለኢትዮጵያ የልማት ፍላጎት በልሂቃን የተሰጠው በተደጋጋሚ ወደ ውጭ የማማተር አባዜ ሀገራችንን ከድህነት አዙሪት አላወጣትም። ሀገራዊ የሆነ ሞዴል አመንጭቶ ለመተግበር ከፍተኛ ውሱንነት አለ። ከውጭ ተቀድተው የሚተገበሩ የልማት ሞዴሎች ጠቃሚ ትሩፋቶችን ለሀገራችን ሊሰጡ የሚችሉበት ዕድል አለ። ይሁንና ብዙውን ጊዜ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ የተሠራበትን ንጥረ ነገሮች ችላ ያሉ ናቸው። ሀገር በቀል ያልሆኑ የልማት ሞዴሎችን በጭፍን መተግበር የየአካባቢውን ኢኮኖሚ፣ ወጎችንና ማኅበራዊ አወቃቀሮችን በማወክ የተፈለገው ዕድገት እውን እንዳይሆን ያደርጋል።

አንድን የደጋ እህል ወደ ቆላ ወስዶ ለማብቀል ሁለት ነገሮች ያስፈልጋሉ። እህሉን ለቆላ አካባቢ እንዲሆን አድርጎ ማላመድ፤ ወይም አካባቢውን ወደ ቅዝቃዜ በመቀየር ደጋማ የልማት ሞዴሎችም እንደዚሁ ናቸው። ማድረግ። ከዚህ ውጭ ለም መሬት ላይ ስለዘራነው ብቻ የደጋ እህል ቆላ ላይ አይበቅልም።

ዓለም አቀፋዊ አስተሳሰቦችን ከኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ለማጣጣም ከተፈለገ፣ የልማት ስልቶች ከሕዝቡ ዕሳቤዎች፣ ዕሴቶችና ፍላጎቶች ጋር በተሻለ ሁኔታ ሊስማሙ ይገባል፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ በዋናነት ወደ ሀገር ውስጥ ዕሳቤዎች በመመልከት ላይ ትኩረት መስጠት አለበት። በመሆኑም ሀገር በቀል ጥንካሬዎችን በመለየትና በማስቀደም መሥራት ትውልዶችን የሚደግፉ የጋራ ዕሴቶች ላይ በትኩረት መሥራትን ይጨምራል።

ማለት ነው። በእነዚህ ሀብቶች ላይ የተመሠረተ የልማት ሞዴልን መቀመር፤ ኢትዮጵያ የራሷን ማንነት የሚያንጸባርቅ የዜጎቿን ብልጽግና በማረጋገጥ ጠንካራ መሠረት ያለው፤ መፃዒ ጊዜ እንድትፈጥር ያስችላታል።

ሕዝብን ያማከለ ሞዴል ተግባራዊ በማድረግ መኀዝ፣ ኢትዮጵያውያን የወደፊት ሕይወታቸውን በመልካም ጎኑ እንዲቀርጹ ያስችላል። ይህም በራሳቸው ጉዳይ ግንባር ቀደም ሚና እንዲጫወቱ ስለሚያስችላቸው የዜጎችን ጽናትና ኩራትን ይገነባል። ወደ ውስጥ መመልከትና ትክክለኛውን ጥያቄ መጠየቅ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ብቻ ሳይሆን ሕዝባዊ አንድነትና የመተሳሰብ ስሜት የሚያጎለብት የልማት ሞዴል ይፈጥራል። ይህም የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በእጅጉ ያግዛል።

**2.2.** የባከነ ዕምቅ ዐቅም

CamScanner

ለመበልጸግ የሚያስችል ዕምቅ ዐቅም የሀገራትን ልማት የሚያግዝ ሀብት ለማፍራት መነሻ ወረት ነው። የተፈጥሮ ሀብት፣ መልክአ ምድር፣ የሰው ኃይልና መሰል ጉዳዮች፤ በአጠቃላይ ለመልማት ያላቸው ምቹነትና ሀብት ለመፍጠር ያላቸው ዐቅም ስፋት ወይም ማነስ፤ ሀገራት ከድህነት ለመውጣት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በአንጻራዊነት ቀለል ያለና ረጅም ጊዜን የማይጠይቅ፤ አልያም ተጨማሪ ጥረቶችን የሚጠይቅና ፈታኝ እንዲሆን ያደርጋል። ወደፊት መጓዝ የምንችለው ዐቅሞችና ዕድሎች ከፍተኛውን ውጤት በሚያስገኙበት መንገድ ስንጠቀም በመሆኑ፤ ያሉንን ዕምቅ ዐቅሞች የምንጠቀምበትና ያጋጠሙንን ዕድሎች ወደ ውጤት የምንቀይርበትን መንገድ መቀየስ ትልቁ ጉዳይ ነው። ይሁንና የሀገራችን ኋላ መቅረት፤ ያሉንን ዕምቅ ዐቅሞች አለመጠቀማችንንና የሚያጋጥሙንን ዕድሎች ስናባክን መቆየታችንን የሚያሳይ ነው።

ግብርናን ብንወስድ፣ ከሀገራችን ለም መሬት እያገኘን ያለው ምርት እጅግ አነስተኛ፤ ጥራቱም ዝቅተኛ ነው። በዓለም ላይ እንደ ዩክሬን ያሉ ሀገራት መሬታቸውን በሚገባ በመጠቀማቸው፤ በከፍተኛና ጥራት ባለው ምርት፤ የአውሮፓ “የዳቦ ቅርጫት” የመሆን ስምን አትርፈዋል።

እንደ እሥራኤል በሎት ሀራት ደግሞ፤ ምቹ ባልሆነ ጥቂት የእርሻ መሬት የተትረፈረፈ ጥራቱ ከፍተኛ የሆነ ምርት በማምረት ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች በቅተዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ግን ሰፊ ያልታረሰ መሬትና ከፍተኛ የውኃ ሀብት ያላት ቢሆንም፤ እኳ የውኃ ሀብት በምግብ ራሳችንን ለመቻል ለምናደርገው ጥረት ከፍተኛ አንጡራ ሀብት ነው: እሁን ድረስ ጥቅም ላይ ሃሳቸው ግን ጥቂቱን ብቻ ነው። ያልተጠቀምነው ሰፊ መሬትና ከሐራ በታች ያለው የአፍሪካ ክፍል ከፍተኛ ሊታረስ የሚችል ነገር ግን ያልታረሰ መሬት ነገር ግን ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ ሰፋ ሲልም አፍሪካ፤ በምግብ እጥረት ሕዝቧ ይሰቃል። ባለቤት ነው። ዓለም ካላት ያልታረሰ መሬት ወቅትም ውስጥ ወደ ግማሽ የተጠጋው የአፍሪካ ነው።

ለም መሬት ብቻም ሳይሆን አህጉራችን አፍሪካ የትላልቅ ወንዞችና የበርካታ ሰፋፊ ሐይዳ ባለቤት ናት። ይህ የተትረፈረፈ ጸጋ የግብርና ምርታማነትን ለማረጋገጥ ትልቅ ዕድል ቢሆንም፡ በአህጉር ደረጃ ሊባል በሚችል መልኩ እየባከነ ያለ ከፍተኛ ዕምቅ ዐቅም ነው።

ሀገራችን ካላት አጠቃላይ መሬት ያረሰችው 50% እንኳን አልደረሰም። ኢኮኖሚዋ በግብርና ላይ የተመሠረተ ነው የምንላት ሀገራችን ለእርሻ ያዋለችው መሬት አደጉ ከሚባሉትና ኢኮኖሚያቸውን ካሸጋገሩ እንደ አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ሕንድ ካሉ ሀገራት ምጣኔው በእጅጉ ያነሰ ነው። ሀገራችን ገና ልትጠቀመው የምትችለው ሰፊ መሬት አላት። ከራሷ አልፏ ሌሎች ሀገራትን እየመገቡ ካሉ የውኃ ተፋሰሶች ጋር ተዳምሮ፣ ቆላማ አካባቢዎችንም ጭምር ለማልማትና በአጠቃላይም ከዝናብ ጥገኝነት ለመላቀቅ የሚያስችል ደረት የሚያስነፋ ዕምቅ ዐቅም ባለቤት ነን። ግን አልተጠቀምንበትም።

ማዕድንን በተመለከተም ሀገራችን የብዙ ማዕድናት መገኛ ናት። ዘርፉ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚያችን ያለው ድርሻ ግን ዝቅተኛ ነው። የተፈጥሮ ሀብታቸውን ተጠቅመው ትልቅ ኢኮኖሚ የገነቡ ሀገራት ብዙ ናቸው። ሳዑዲ ዓረቢያ፣ ሩሲያ፣ ኖርዌይና መሰል ሀገራት የነዳጅ ዘይትን በመጠቀም ብልጽግናቸውን ካፋጠኑ ሀገራት መካከል ይገኙበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ነው የሚባል የተፈጥሮ ሀብት ሳይኖራቸው፡ ዕሴት መጨመርን የኢኮኖሚያቸውና የውጭ ንግዳቸው መሥመር ያደረጉ ሀገራትም አሉ። እንደ ጃፓን፣ ደቡብ ኮሪያና ሲንጋፖር ያሉ ሀገራት በዚህ ሥርዓት የተነሣ ከብልጽግና ማማ ላይ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ በብዙ ማዕድናት የታደለች ብትሆንም፤ አብዛኛው የማዕድን ሀብት ገና ወደ ልማት አልተሸጋገረም። እንደ ታንታለም ያሉ የከበሩ ማዕድናት የምርት ጅማሬዎች አሉ። እንደ ወርቅ ባሎት ላይ ደግሞ በተወሰነ ደረጃ ጥሩ እንቅስቃሴ ጀምረናል። ሰፋፊ ሽፋን ያለባቸው እንደ ነዳጅና ፖታሽ ያሉ ሀብቶቻችን ገና ብዙ መሥራት የሚጠበቁብን ናቸው”።

CamScanner

ሀገራችን ለነዳጅ ዘይት ግዢ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ታወጣለች። ለማዳበሪያ ዋነኛው ግብአት የሆነውን ፖታሽን በከፍተኛ ደረጃ ታቅፋ፣ ለማዳበሪያ ቢልዮን ዶላሮች ትከሰክሳለች። የተፈጥሮ ሀብታም፣ የልማት ድኻ መሆናችን ያስቆጫል። ተገድደን ሳይሆን ወደን ፈቅደን ድኻ የሆንን ይመስላል።

ሌላው የሀገራችንን የመልማት ዕምቅ ዐቅም የሚወስነው የኃይል ሀብታችን ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችል ትልቅ ኃይል የማመንጨት ዕምቅ ዐቅም አላት። ከዚህ ዕምቅ ዐቅም ውስጥ ከታዳሽ የኃይል ምንጮች ብቻ ከፍተኛ ኃይል ማመንጨት ትችላለች፤ ይህም ሀገራችንን በዚህ ረገድ ተመራጭ ያደርጋታል። ከዚህም ባለፈ ከነዳጅና ከጋዝ ተጨማሪ ኃይል የማመንጨት ዕድሎች አሏት።

ኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ እመርታ እጅግ አስፈላጊ ነው። በቀጣናችን ትሥሥርን ለመፍጠርም ይህ ኃይል ብልጽግናን ለማረጋገጥ በሀገር ውስጥ ለመፍጠር ለምንሻው ኢንዱስትሪያዊ መሠረት ነው። ከቀጣናው ተሻግሮ እስከ ሰሜን አፍሪካና እስከ አውሮፓ ድረስ የሚደረስ የታዳሽ ኃይልን ማስፋፋት የሚያስችል ነው። ዓለም በቀጣይ የሚያስፈልጋት የኤሌክትሪክ ኃይል መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ነው።

ይህ ቀጣናዊ ኢኮኖሚያዊ ትሥሥር ተግባራዊ መሆን ሲችል፣ ዓለም አቀፍ የተጽዕኖ አድማሳችንን የምናሰፋበት ዕድል ሊፈጥር የሚችል ከፍተኛ ዐቅም ነው።

ቱሪዝም ሌላኛው ያልተጠቀምንበት ዕምቅ ዐቅማችን ነው። ያደጉት ሀገራት ቱሪዝምን ለዕድገትና ለተጽዕኖ ምንጭነትይጠቀሙታል። የሺዎች ዓመታት ታሪክ ባለቤት በሆነችው ሀገራችን ግን ታሪክ የዳቦ ሳይሆን የጠብ ምንጭ ነው። ሀገራችን ዓይን የሚመገበውን አብዝታ ልትሰጥ የምትችል ናት። የተፈጥሮን ውበት፣ የቀደምቶችን ሥልጣኔ እንዲሁም የብሔር ብሔረሰቦች ብዝኃ ባህል የታደለች ሀገር ናት። ከተፈጥሮ አንጻር ሀገራችን የወንዞች፣ የሐይቆች፣ የተራሮች እንዲሁም የዱር እንስሳት ብዙ ሊጎበኙ የሚችሉ የተፈጥሮ ሀብቶች ባለቤት ናት። የተዋቡ መስኮች፣ የአዕዋፍና እንስሳት መናኸሪያ ናት።

ከታሪክ አንጻር የሰውን ልጅ አመጣጥ፣ የሰውን ልጅ ሥልጣኔ፣ የሰውን ልጅ የእምነት ጉዞ፣ የሰውን ልጅ አኗኗር የሚያሳዩ የሺ ዘመናት ቅርሶች ባለቤት ናት። እየሰፋ ከመጣው የዓለምና የአፍሪካ የቱሪዝም ኢኮኖሚ ገቢ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ መቋደስ የሚያስችል ግን እስካሁን የባከነ ዐቅም አለን።

የምንገኘው የዓለም ዋነኛ የንግድ ኮሪደር በሆነው ሥፍራ አካባቢ ነው። የቀይ ባሕር አካባቢ የምሥራቁንና የምዕራቡን ዓለም አገናኝ ወሸመጥ ነው። በመሆኑም የአፍሪካና እስያ መገናኛ ድልድይ ነን። ይህንን ግን ለዕድገታችን አላዋልነውም። እንደ ሲንጋፖር ያሉት ሀገራት አካባቢያቸው የሰጣቸውን ትሩፋት ተጠቅመው በልጽገዋል። አካባቢያቸው የሰጣቸውን ተጽዕኖ የመፍጠር ትሩፋት ለዕድገታቸው ግብአት ያደረጉ ሌሎችም በርካታ ሀገራት አሉ። ሀገራችን በአንጻሩ በአፍሪካ ያላትን ተጽዕኖ ለዕድገቷ ግብዐትነት በሚገባ አልተጠቀመችውም።

ከቁሳዊ ሀብት ባለፈ የሰው ኃይል ለዕድገት ሌላው ወሳኝ ሀብት ነው። እንደ ቻይናና ሕንድ የመሳሰሉ በዓለም ላይ ከፍተኛ ሕዝብ ቁጥር ባለቤት የሆኑ ሀገራት፣ ሕዝባቸውን እንደ ሀብት ተጠቅመውበታል። ይህም ዛሬ ለሚገኙበት ዕድገት አንዱ መሠረታቸው ነው። ሀገራችን በሕዝብ ብዛት በአፍሪካ የሁለተኛነት ደረጃ ይዛ ትገኛለች። ሕዝቧን እንደ ዐቅም ተጠቅማ ከድህነት ግን ልትላቀቅ አልቻለችም።

ለአንድ ሀገር መጥፊያዋም መዳኛዋም ሕዝቧ ነው። ሕዝቧ የነገን ተስፋዋን ያለመልማል ወይም የማዘግየት ሚና ይጫወታል። ሕዝብ ተምሮና ነቅቶ ለአንድ ዓላማ ከተሰለፈ ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ዐቅም ነው። የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት ለዚህ ምስክር ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ አደጉ በሚባሉ ሀገራት እየቀነሰ በመጣው የሠራተኛ ኃይል ምክንያት ኢኮኖሚያቸው ሥጋት ውስጥ እየገባ ነው። ይህም ሕዝብ ለአንድ ሀገር ብልጽግና መሠረት መሆኑን መመልከት ያስችላል።

CamScanner

የለማ የሰው ኃይል ከሀገሩም አልፎ በሌላው ዓለም በመሠማራት ለሀገሩ ብልጽግና ከፍተኛ ጥቂት አስተዋጽዖ ያደርጋል። ለምሳሌ ሕንድ የሰው ኃይሏ ድንበርና ውቅያኖስ ተሻግሮ በሌሎች ሀገራት በመሠማራት ከፍተኛ የሆነ የገቢ ምንጯ ነው"። ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት ከዓለም ጥቂት ሀገራት ተርታ የምትመደብ ናት። ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሕዝቧ ክፍል ወጣት ነው። የሕዝቧ የወጣትነት ትሩፋት ግን ያልተጠቀመችበት ዕምቅ ዐቅሟ ነው። ይህንን ዐቅም መጠቀም ከቻለች ከፍተኛ የመበልጸግ ዕድል እንዳላትም አመላካች ነው።

ሀገራችን የእነዚህ ብቻ ሳይሆን የሌሎችም እዚህ ያልተዘረዘሩ ዕምቅ ዐቅሞች ባለቤት ናት። ዐቅሞቻችንን ተጠቅመን ወደ ብልጽግና መጓዝ ግን አልተቻለንም። የዜጎቻችንን ፍላጎት ማርካት የሚችል ዕሴት አልፈጠርንም። እንዲያውም በጥልቅ ችግር ውስጥ እየማቀቅ የሚያስችሉ፣ በተለያየ መንገድ ልንጠቀማቸው የምንችላቸው ሰፊ ዕምቅ ሀብቶች ባለቤቶች | ነው። ይህ ቀንበር ሊበቃን ይገባል። የቤት ሥራችንን የሚያቀሉ፣ ብልጽግናን ለማረጋገጥ መሆናችንን ዓይናችንን ገልጠን ማየት አለብን። መንገዳችንን ቀይረን ራሳችንንና ሀገራችን በአዲስ መንገድና ትልም መምራት ያስፈልጋል።

በየጊዜው የሚፈጠሩ ተለዋዋጭ የዓለም ሁኔታዎችና በውስጥ የሚፈጠሩ የሰው አጋጣሚዎች ዕድሎችና ሥጋቶችን ይዘው ይመጣሉ። እነዚህን አጋጣሚዎችና ዕድሎች አስልቶና አስቀድሞ ለይቶ በአግባቡ በመጠቀም ሥጋቶችን መቀነስና መቅረፍ ሲቻል ዕድገት ይፈጠራል። በተቃራኒው ግን ዕድሎች ሲባክኑና ሥጋቶች ሲገነግኑ መቆርቆዝ ይፈጠራል፡ ለማደግ የሚያስችሉንና ለመበልጸግ በር የሚከፍቱ ዕድሎችን በአግባቡ አለመጠቀምና | ማባከን የመሻሻልን መግቢያ በር እንደ መዝጋት ነው።

በየጊዜው የሚፈጠሩ ዕድሎችን ከመጠቀም ይልቅ በር በመዝጋታችን፣ ወደፊት መራመድ | አቅቶን ከኋላ ቀርተናል። ብዙ ዕሴት ሊፈጥሩ የሚችሉ ዕድሎችና ዐቅሞች መክነዋል የሚጠቀምባቸው አጥተው አቧራ ለብሰዋል። ዕምቅ ዐቅሞቻችንን አውጥተን ለመጠቀም የሚያስችል የዕይታ፣ የልየታና የፍጥነት ብቃታችን እጅግ አነስተኛ ነው። በዚህ የተ ብልጽግና ሳይሆን ድህነት፣ ተድላ ሳይሆን ችግር መገለጫችን ሆኗል።

**2.3.** የመሠረተ ልማት እጥረት፤

ዕምቅ ዐቅሞቻችንን አውጥተን መጠቀም ካልቻልንባቸው ምክንያቶች ዋነኛው የመሠረተ ልማት አለመደርጀት ነው። መሠረተ ልማት ለአንድ ሀገር የደም ሥር ነው። የመሠረተ ልማት ግንባታ ለምርታማነትና ቀጣይነት ላለው ዕድገት አስቻይ መሆኑም አያጠራጥርም። በተቃራኒው ደግሞ አነስተኛ የመሠረተ ልማት ሽፋን ለድህነትና ለተደራራቢ ችግሮች ምክንያት ይሆናል። መሠረተ ልማትን መገንባት ከፍተኛ ወጪንና ጊዜን የሚጠይቅ ሥራ ነው። ለድኻ ሀገራት የመሠረተ ልማት እጥረት መዋቅራዊ ተግዳሮት ሲሆን ሊሟላ የሚችለውም በረጅም ጊዜ ዕቅድ ነው። በሀገራችን የተለያዩ መሠረት ልማቶች ዕድገት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያሳየው መሻሻል የሚበረታታ ነው። በአጠቃላይ ስናየው ግን በእጅጉ ወደ ኋላ የቀረና ሂደቱም እጅግ አዝጋሚ ነው። ከመጓጓዣ መሠረተ ልማቶች አንዱ የሆነውን የመኪና መንገድ መሠረተ ልማት ብንመለከት በሀገራችን ማስፋፋት የተጀመረው ቀደም ብሎ ነው።

ነገር ግን በሚገባን ፍጥነትና ፈጠራ ስላልሠራን አሁንም ብዙ መሥራት የሚጠበቅብን ዘርፍ ነው። በአዲስ አበባ የመጀመሪያው አስፋልት ከታየበት 1903 የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ዘመን ጀምሮ በተለያዩ መንግሥታት በተለያየ ደረጃ የሚታዩ መንገዶች ተዘርግተዋል። ይሁንና ዕድገቱ እጅግ አዝጋሚ፣ ጥራቱ አናሳ፣ መጠኑም በዋና ከተማ ደረጃ ከሚጠበቀው በእጅጉ ያነሰ ነው። ከዚህ የተነሣ አሁንም በመንገድ እጦት የሚሰቃየው ሕዝባችን ትንሽ የሚባል አይደለም።

ያስከትላል

CS CamScanner

ከሌሎች መሠረተ ልማቶች በተለየ የመንገድ መሠረተ ልማት መላውን ሕዝብ የሚያገለግል ነው። በዚህም ምክንያት የመንገድ ተደራሽ አለመሆን ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ገበሬ ምርቱን ወደ ገበያ ለማድረስ ስለማይችል ድካሙ ዋጋ ያጣል። በገበያ ሸጦ መጠቀም የማይችለውን ምርት በብዛት ለማምረት የሚኖረው ተነሣሽነት ይቀንሳል። በከተማ የሚኖረውም እንደ ልብ ተንቀሳቀሶ ለመሥራት ይቸገራል፤ ብዙ መሥራት ሲችል በመንገድ እጥረት ምክንያት ጥቂቱን ብቻ ከውኖ ይመለሳል።

የመንገድ ተደራሽ አለመሆን ሌሎች እንደ ጤናና ትምህርት ካሉ መሠረተ ልማቶት ተጠቃሚ የመሆን ዕድልንም ይቀንሳል። ማኅበራዊ መስተጋብርንም ያውካል። ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ማምጣትና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብን መገንባት የሚቻለው በሕዝብ መካከል ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊና ቱሪስታዊ እንቅስቃሴና ትሥሥር ሲፈጠር ነው። ለዚህ ደግሞ መንገድ ወሳኝ ነው።

የመንገድ እጥረት ከዝርጋታ ጋር ብቻ የሚያያዝ አይደለም። ከተዘረጋው መንገድ የጥራት ደረጃ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ደረጃውን ጠብቆ ያልተሠራ መንገድ፣ በአንድ በኩል በፍጥነት ይበላሻል። ይህ ደግሞ ለማያቋርጥ ከፍተኛ የጥገና ወጪ ይዳርጋል። በጥና ምክንያት በመዘጋቱም የሚስተጓጎለው አገልግሎት ትንሽ አይደለም። በተለይም መንገድ ለማዳረስ ገና ብዙ ለሚሠራ እንደ እኛ ላለ አዳጊ ሀገር፣ የአንድ መንገድ መዘጋት ትልቅች ያስከትላል።

በሌላ በኩል ደግሞ በተለይም በከተማ የሚገኙ መንገዶች በጣም ጠባብና ጥቂት መኪኖችን ብቻ በትይዩ የሚያስተናግዱ ናቸው። ይህም ከተሞቹን ለከፍተኛ የመኪና መጨናነቅ ዳርጓቸዋል። የእግረኛ አለፍ ሲልም እንደ ሳይክል ላሉ ለሞተር አልባ መጓጓዣዎች ማሣለጫ መንገድ በቅጡ የላቸውም። በመሆኑም የመኪናው መንገድ ሁሉንም እንዲያስተናግድ | ይገደዳል። በአጠቃላይ የሀገራችን ሰፋ ሲልም የአፍሪካ የአስፋልት ንጣፍ ከሌሎች አዲ ሀገራት በእጅጉ ተደራሽነቱ አነስተኛ፣ ጥራቱም ችግር ያለበት ነው። ይህም ከመንገ ልናገኝ የሚገባውን ጥቅም በእጅጉ ቀንሶታል። ከዚያም አልፎ የጥራት ጉድለቱ የመንገድ ደኅንነት ችግር በማስከተሉ ብዙ የሕይወት ዋጋም አስከፍሎናል።

የባቡር መሠረተ ልማትንም ብንመለከት ተመሳሳይ ነው። በሀገራችን የባቡር መሥመር ዝርጋታ ከመኪና መንገድ ዝርጋታ ያልተናነሰ ዕድሜ አለው። ከጅቡቲ አዲስ አበባ የተዘረጋው የባቡር መሥመር፤ ለዘመናት ብቸኛው መሥመር ሆኖ ዘልቋል"።

ባቡር በሌሎች ሀገራት የሚሰጠው የማስተሣሠር ዐቅም ከፍተኛ ነው። የአውሮፓ ዘመናዊ ሥልጣኔና የሕዝብ ለሕዝብ ትሥሥር ከባቡር መሥመር ዝርጋታ ጋር የተገናኘ ነው። በሀገራችንም አንድ ለእናቱ የሆነው ባቡር በከተሞች ምሥረታ፣ ዕድገትና ትሥሥር ላይ ያለውን በጎ ተጽዕኖ ስናስብ በአንድ መቅረቱ በእጅጉ የሚያስቆጭ ነው። ሀገር አቋራጭ የባቡር መሥመሮች ካላቸው ፍጥነትና የማጓጓዝ ዐቅም አንጻር ምርቶችን በተሻለ ከብካቤና ፍጥነት ለተለያዩ ገበያዎች ማድረስ ይችላሉ። በመላው ሀገራችን ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት ሀገራትም ጭምር የሚያገናኙን መሆን ይገባቸው ነበር።

የሀገር ኩራት የሆነው አየር መንገዳችንም ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ ነው። በዓለም ደረጃ ሀገራችንን አስተዋውቋል። በሀገር ውስጥ መሠረተ ልማትን በማዳረስ ብዙ ከተሞችን አገናኝቷል። በመሠረቱ ቀሪ ሥራዎች ቢኖሩም በአየር ትራንስፖርት መሠረተ ልማትም ሆነ በተቋም ግንባታ እንደ አብነት ሊጠቀስ የሚችለው በትውልድ ቅብብሎሽ ጠንካራ ወረትና ሥርዓት የፈጠረው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኢትዮጵያውያን ተቋም መፍጠርና ሥርዓት ማጽናት እንደሚችሉ ማረጋገጫ ምስክር ነው። ይሁንና ከሀገራችን ስፋት፣ ካሉን የከተሞች ብዛትና ከተቋሙ አንጋፋነት አንጻር በሀገር ውስጥ በረራ ብዙ ከተሞችን መዳረሻ ማድረግ በተገባው ነበር። በአጠቃላይ ከመጓጓዣ አንጻር ያለን መሠረተ ልማት በከፍተኛ ደረጃ ወደ ኋላ የቀረ ነው። ገጠርና ከተሞችን በሚገባ አላስተሣሠረም። በትሥሥሩ ሊገኝ የሚችለውን የገበያ ትሩፋትም ልናገኝ አልቻልንም። ይህም የገበሬውንና የከተማውን ነዋሪ ውጤታማነት በእጅጉ ቀንሶታል። በአጠቃላይም በአዝጋሚና ጥራት በጎደለው ክንውን፣ የሀገርን ዕድገት የጎተተ መሠረተ ልማት ባለቤቶች ነን።

CamScanner

ኢኮኖሚና ማኅበረሰብ ሽግግር መነሻ ዐቅማችን ግብርና ነው። ግብርናን ለማግ እ ወደ ኢንዱስትሪ ለሚደረገው ሽግግር ዋና ግብአት መሆን የሚያስችለን ሌላው የ በግብርና ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ባለቤት መሆናችን ይታወቃል። በመሆኑም ከባሕ መሠረተ ልማት፣ የመስኖ መሠረተ ልማት ነው። መስኖ በዓመት ሁለት ከፍ ሲልም ጊዜ ምርት እንድናገኝ የሚያስችለን ነው።

መስኖ በዓለም ላይ ከፍተኛ የሆነ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ካስቻሉ ለ ልማቶች አንዱ ነው። መስኖ ምርት በተረጋጋና በአየር ሁኔታ ላይ ባልተንጠለጠል ሂደት እንዲመረት ያግዛል። ምርትን በከፍተኛ ሁኔታ ይጨምራል።

ሀገራችን አያሌ የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር የውኃ ሀብቶች አሏት። በእነዚህ ህብኝ ምክንያት የመስኖ ልማትን በከፍተኛ ደረጃ ማከናወን የሚያስችል ዐቅም ቢኖራትም ለዘመናት ግን ብዙም ያልሠራንበት ዘርፍ ነው። ያለውም ጥቂት የመስኖ መሠረት ግንባታ በሌሎች የግንባታ ፕሮጀክቶቻችን የሚታዩ የውጤታማነት ችግሮች ተካፋይ ነው። ከዚያም ባለፈ ተገንብቶ ወደ ተግባር ከገባም በኋላ በብዙ የአስተዳደራዊ ችግሮት ቢዝ ውጤታማነቱ እንደሚጠበቀው አልሆነም። እርሻችን "ባለህበት ርገጥ" እንዲሆን አንዱ ዋነኛ ምክንያት የመስኖ መሠረተ ልማት አለመስፋፋት ነው።

ከመሠረተ ልማት መካከል ሌላው ወሳኝ የዕድገት ሞተር ደግሞ ለብዙ አገልግሎቶ መሠረት የሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭ ነው። የኃይል አቅርቦት አለማደግ፤ አብኖር አገልግሎቶቻችንን እየገታ የሀገርን ዕድገት ያንቃል። ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት ትልቅ ዐቅም ያላት ቢሆንም፤ ነገር ግን ዐቅሟን ሳትጠቀም ቀርታለች።

በዚህም በዓለም ላይ ዝቅተኛ የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ካላቸው ሀገራት ጋር ሎሚ ይነሣል"። ሀገራችን ብዙ ወንዞችንና ለኃይል ማመንጨት ምቹ የሆነ ሥነ ምኅዳርን የታደለች ናት። ነገር ግን በቂ ኃይል ማመንጨት ጉዳይ ከውጭም ከውስጥም ባሉ የተለያዩ ተግዳሮቶች ሳይሳካ ለብዙ ዘመናት ዘልቋል። በዓባይ ወንዝ ላይ የኃይል ማመንጫ ለማጋባት የወሰደብን ጊዜ ጥቂት የሚባል አለመሆኑ ለዚህ ምስከር ነው። ከውጭ የተለያዩ ሀገራት ጥቅማችንን ይነካል በሚል በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለሕዳሴ ግድብ ሊገኝ ይችል የነበረ የውጭ ገንዘብ እንዳናገኝ ለማድረግ የሚያደርጉት ሤራ ተሳክቶላቸዋል።

ክብር ችግር ለማይሰብረው ሕዝባችን ይሁንና በተባበረ ክንዱ የዓባይን ግድብ ፕሮጀከት አስጀምሮ አገባድዶታል። ፈተናው ከውጭ ብቻ አልነበረም። ከውስጥም ብዙ ዕንቅፋት ነበር። የሰላም ማጣት፣ የፕሮጀከት አመራር ድክመት፣ ሙስና፣ ወዘተ ሥራውን ለማደናቀፍ ተገዳድረው ነበር። በዚህም የተነሣ ለፕሮጀክቱ ልናወጣው ከሚገባው ወጪ በላይ አውጥተናል። ግድቡ በተያዘለት ጊዜ ተጠናቅቆ ቢሆን ልንጠቀም ከሚገባው አንጻር ከፍተኛ ኪሣራ ደርሶብናል ።

ሌሎቹንም የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ብንመለከት ብዙ ፈተናዎች ተጋፍጠዋል። በውስጥ የፕሮጀክት አፈጻጸም ችግሮች ይናጣሉ። መጠናቀቅ ከሚገባቸው ጊዜ ዘግይተው ይጠናቀቃሉ። በዚህም ላልተገባ ኪሣራ ሀገራችንን ይዳርጋሉ።

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎቻችን የውኃ ናቸው። የውኃን ቀድመን አነሣን እንጂ፣ ሀገራችን ከመሬት ሙቀት፣ ከነፋስ፣ ከፀሐይና ከሌሎችም ዓይነቶች፣ ኃይል የማመንጨት ዐቅም አላት። በተለይም የስምጥ ሸለቆ መሥመርን ይዘው ባሉ የሀገራችን አካባቢዎች፣ ከመሬት ሙቀት ኃይል ማመንጨት እንችላለን። በዚህ ረገድ የተለያዩ የኃይል ምንጮች ባለቤት መሆናችን፤ በተለያዩ ቦታዎች እንደየአስፈላጊነቱ ተመራጩን መንገድ ተጠቅመን ኃይል የማመንጨት አማራጭ ሰጥቶናል።

ዕድላችን ይህን ያህል ሰፊ ቢሆንም ሕዝባችንና ኢንዱስትሪዎቻችን አሁንም በኃይል መሠረተ ልማት ችግር ውስጥ ናቸው። በሀገራችን እንዳለው ኃይል የማመንጨት ዕምቅ ዐቅም ( ኖሮ ከራሳችን አልፈን ለጎረቤት ሀገሮችና ከዚያም በላይ መትረፍ እንችል ነበር። ከላይ ያየናቸውን ጨምሮ ሌሎችም የተለያዩ እክሎች ዘርፉ ማደግ በሚገባው ደረጃ እንዳያድግ የነፋስና

CS CamScanner

የፀሐይም ቢሆን በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ መዋል የሚችል ነው። ሆኖም ውኃና እንቀውታል። ሀገራችንም ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባውን ብዙ ትሩፋቶች አስቀርተውባታል። ነፋስ በተነጻፃሪ የተሻለ ተሠርቶባቸዋል ማለት ይቻላል። በአጠቃላይ ግን ያለንን የታዳሽ ኃይል አለኝታን ያህል ጥቅም ላይ አላዋልንም።

በዚህ የዲጂታል ዘመን የስልክና የበይነ መረብ ዕድገት ለአጠቃለይ ዕድገት ያለው አንድምታ ትልቅ ነው። ሀገራችን በተነጻፃሪ ትኩረት ካደረገችባቸው መሠረተ ልማቶች አንዱ ይህ ዘርፍ ነው። ዓለም በከፍተኛ ደረጃ ወደ ዲጂታይዜሽን ለሚያደርገው ጉዞ የበይነ መረ መሠረት ልማት ወሳኝ ነው። የበይነ መረብ መሠረት ልማት ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ ነው። ሥሉጥ ከተሞችን (Smart Cities) እና መንደሮችን ለመገንባት ያግዛል። የአገልግሎት አሰጣጥን ቅልጥፍናንና ውጤታማነትን ከፍ ያደርጋል። ተደራሽነትንና ሉላዊነትን በከፍተኛ ደረጃ ያሣልጣል።

በሀገራችን የስልክና የኢንተርኔት ተደራሽነት ጥሩ ደረጃ ደርሷል። ይሁንና ወደ ምርታማነትና ወደ ሙሉ ዲጂታይዜሽን ለመጓዝ ሌሎች በዚህ ላይ የሚገነቡ መሠረት ልማቶች ወሳኝ ናቸው። የኢ-መንግሥት(E-Government)፣ የሳይበር ደኅንነት፣ የኢ-ንግድ(E-Com- merce) የሥሉጥ ከተማና መሰል በዚህ ላይ ተመሥርተው የሚገነቡ ተጨማሪ መሠረተ ልማቶች ግንባታ በከፍተኛ ደረጃ መፍጠን ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪም የሕዝባችን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና ዕውቀት በሰፊው ሊሠራበት የሚገባ ነው። በእነዚህና መሰል አነስተኛ ተግዳሮቶች የበይነ መረብ መሠረተ ልማቱ በምርታማነት ላይ ሊያበረክት ከሚችለው አስተዋጽዖ አንጻር ያልተጠቀምንበት ዐቅም ሆኖ ይታያል።

የመጠጥ ውኃና የፍሳሽ መሠረተ ልማት ዓይነቶችን ብንመለከት የምናገኘው ውጤት የሚያወላዳ አይደለም። የተደራሽነት፣ የጥራትና የአገልግሎት መቆራረጥ ችግር ሰቅዞ የያዛቸው ናቸው። ከፍተኛ የውኃ ዐቅም ያለው እንደ እኛ ያለ ሀገር በመጠጥ ውኃ ሊቸገር አይገባውም ነበር።

ከእነዚህ ጠጣር መሠረተ ልማቶች(Hard Infrastructure) በተጨማሪ ሌሎችም በስስ መሠረተ ልማትነት(Soft Infrastructure) የሚታዩ የጤና፣ የትምህርት፣ የአስተዳደር፣ የግንኙነት፣ የሕግና መሰል መሠረተ ልማቶች በተለያዩ የዕድገት ደረጃዎች ላይ ይገኛሉ። እነዚህ መሠረተ ልማቶች ለዕድገት ካላቸው ወሳኝነት አንጻር በከፍተኛ ደረጃ ልንሠራባቸውና ልናሳድጋቸው ይገባል።

በቀጣይ የሰው ሠራሽ አስተውሎትን ጨምሮ እየመጡ ያሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ታሳቢ ማድረግ አለብን። ሰው ሠራሽ አስተውሎት በጠጣርና ስስ መሠረተ ልማቶች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አዎንታዊና አሉታዊ ችግሮች ማጤን የግድ የሚልበት ዘመን ላይ ነን። የእርሱን ጠባይና ዕድገት ከግምት ባስገባ ሁኔታ ተሻጋሪ የሆኑ መሠረተ ልማቶች ባለቤት መሆን አማራጭ የሌለው የዕድገት መንገድ ነው።

ሌላው ዕድገታችንን በሁለንተናዊ መንገድ ያሠረው የወደብ አለመኖር ነው። ወደብ ለኢትዮጵያ የመኖር ወይም ያለመኖር ጉዳይ ሆኗል። በአፍሪካ ቀንድ ትልቁን ኢኮኖሚ እየገነባን ነው። በአፍሪካ ከሚገኙ ታላላቅ ኢኮኖሚዎች አንዱ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ነው። በአፍሪካ ሁለተኛው የሕዝብ ቁጥር የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። አካባቢያችን በወጪ እና ገቢ ንግድ ላይ ጫና የሚያሳድሩ የጸጥታ ችግሮች ያንዣበቡበት ነው። ወደብ ከኢትዮጵያ የጸጥታ እና ደኅንነት እንቅስቃሴዎችም ጋር የተያያዘ ነው።

ኢትዮጵያ በምትነባው ኢኮኖሚ ልክ የሆነ ወደብ ማግኘት አለባት። የአካባቢ ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት ከኢትዮጵያ ጋር መሳ ለመሳ የሚሄድ ባለመሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የሎጅስቲክስ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የብቃት ችግር ሊያጋጥማት ይችላል። ስለዚህም ራስዋ የምታስተዳድረው፤ በሚያድገው ኢኮኖሚዋ ልክ የምታሰፋውና የምታዘምነው የወደብ መሠረተ ልማት ያስፈልጋል። የመደመር መንግሥት እንደ አንድ የኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ሊያሳካቸው ከሚተጋባቸው አንዱ፣ በኢኮኖሚያዊ ዕድገታችን ልክ የሆነ የራሳችን የወደብ መሠረተ ልማት እንዲኖረን ማድረግ ነው።

CamScanner

ሀገራችን ልታሳካ ከምታልመው ብልጽግና አንጻር በርካታ መሠረተ ልማቶችን ልታስፋፋ ይገባል። የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ከፍተኛ ሙዓለ ንዋይ የሚፈልጉ ናቸው። የሙዓለ ንዋይ እጥረት ደግሞ አንዱ የሀገራችን ችግር ነው። በየዘመናቱ ዐቅምን ያገናዘበ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ለመከወን ሙከራዎች ተደርገዋል። ይሁንና እነዚህ አነስተኛ ጅማሮዎች በሚገባ ውጤታማ አልሆኑልንም። ወደሚቀጥለው ደረጃ ለማደግ በቂ ካለመሆናቸው በተጨማሪ በአግባቡ ጥቅም ላይ ባለማዋላችን ከድህነት አዙሪት ልንወጣ አልቻልንም።

በየዘመናቱ ጥቂት ለመራመድ ብንሞክርም ወቅቱንና መጪውን ዘመን ያገናዘበ ጥራት ያለዉ ጥራትን፣ ቅልጥፍናን፣ በጊዜ መጠናቀቅን፣ ዘመናዊነትንና ባለቤትነትን የተመለከተ ተ መሠረተ ልማት መገንባት ባለመቻላችን፣ ለዚህ ዘመን በዕዳነት ተላልፏል። የተገነቡት አለባቸው። ይህም ብዙ ጥያቄዎችን ያስነሣል። ሀገራችን በዘመናዊ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረች ቢሆንም፣ እንዴት በዚህ ደረጃ የልማት መሠረቶችን ማ ተሳናት? ከዘመን ዘመን ያለው መሻሻልስ አመርቂ ያልሆነው ለምንድን ነው? ተመሳ በሆነ የጥራትና የአስተዳደር ችግር መልሰን መላልሰን የምንቸገረው ለምንድን ነው የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ተገቢ ነው።

## 2.4. ሥርዓታዊና መዋቅራዊ ፈተናዎች

የአንድ ሀገር ከፍታንና ዝቅታን ሁለት ነገሮች ይበይናሉ። የመጀመሪያው ሀገሪቱ ያላት ዐቅም ነው። ሁለተኛው ደግሞይህንን ዐቅም የሕዝብን ሐሴት ወደሚያረጋግጥ ዕሴት መ የሚያስችል ሥርዓት አለ ወይ? የሚለው ነው። በመሆኑም ዕምቅ ዐቅሞችን ውጤታ በሆነ መንገድና በቅልጥፍና መጠቀም የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር ያስፈልጋል።

ሥርዓት ስንል ቀዳሚው ነገር ዕምቅ ዐቅሞችን አሰባጥሮ ዘመን ተሻጋሪ በሆነ መለ መጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ነው። ደርዝ ያለው፣ ግብአትና ውጤት፣ ግብረ መል ምላሽ ያለው፤ እንዲሁም እየተማረና እያደገ የሚመጣ ተላማጅ (Adaptive) የአባ ሚናና መስተጋብር ድምር ውጤት ነው። የዳበረ ሥርዓት ወደ ዕድገት፣ ወደ ሙላት፣ በ መረጋጋትና ወደ ተገማች ውጤት ያመራል። በአንጻሩ ያልዳበረ ሥርዓት በተቃራኒው ረብሻ፣ ወደ ትንሽነት፣ ወደ አለመቀናጀትና ወደ ኢ-ተገማች ውጤት ያመራል።

የመደመር ዕሳቤ ሥርዓታዊ ዕይታ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሥርዓ የተሣሠሩና ተመጋጋቢ፣ ተለዋዋጭና አዳጊ መሆናቸውን ያስረዳል። በመሆኑም የሀገራ ችግሮች ስንተነትን ከተናጠልና ከአቅላይ ዕይታ ይልቅ ምሉዕ ዕይታን መያዝ ያስፈል የመደመር ዕሳቤ የአስተዳደርና የዕድገት አማራጭ አካሄዶችን ለመንደፍ ከዘመናዊ የሥርዓቶች ንድፈ ሐሳብና ከሳይንስ ዕውቀቶች ይነሣል።

የኅብረተሰብ ችግሮችንና ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ሁሉን አቀፍ፣ በሂደት የሚዳብርና ተጨባጭ ሀገራዊ ሁኔታን ያማከለ የአስተዳደርና የዕድገት አማራጭ አካሄድን መንደፍ እንደሚያስፈልግ ያስረዳል።

ይህ ዕሳቤ የሀገራችንን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት ሥርዓታዊ ምላሽ ሲሰጥ አራት ታሳቢዎችን በማስቀመጥ ነው። የመጀመሪያው፥ ሥርዓቶች የተነጠሉ ሳይሆን እርስ በእርስ የተቆራኙ ስለሆነ ምሉዕ ዕይታ ይፈልጋሉ። እንዲሁም ሥርዓታዊ ችግሮች ውስብስብ በመሆናቸው ከተናጠል አካሄድ ይልቅ የጋራ ጥረትን የሚጠይቁ መሆናቸው ነው።

ሁለተኛው፥ የዳበረ ሥርዓትን ለመፍጠር በሂደት እየተማረ የሚሄድ የማይቋረጥ መሻሻልን ይጠይቃል የሚለው ነው። ይህም ማለት ከወግ አጥባቂ ርዕዮተ ዓለማዊ ቀኖና ይልቅ ገቢር ነበብ አካሄድን ይፈልጋል ማለት ነው። ገቢር ነበብ አካሄድ እውነት የስምምነት ውጤት፤ ዕውቀትም የሚሠራና መፍትሔ የሚያመጣ መሆን እንዳለበት ያስረዳል።

ሦስተኛው፥ የመደመር ዕይታ በመደመር ፍጥነት መንገድና ሥርዓታዊ ዕይታ እመርታዊ ዕድገትና ለውጥ ማምጣት(ክሥቱነት) ይቻላል ብሎ ያምናል። በአንድ ሥርዓት ውስጥ ያሉ አካላት የሚያደርጉት ትንንሽ መናበብ እንዲሁም

CS CamScanner

ተስተጋብሮና ተደምሮ መንቀሳቀስ፣ ባልተጠበቀ ሁኔታ ትልልቅ ባሕርያዊና አዝማሚያዊ መቀየሮችን በመፍጠር(Nonlineari- ty) ግዙፍና እመርታዊ ለውጦችን ሊያስመዘግቡ ይችላሉ። ለዚህም ነው ትብብርን መሠረት ያደረገ የጋራ ጥረት ውጤት፤ ከተደማሪዎች የተናጥል ጥረት መጠን በላይ ነው የሚባለው። አራተኛው፥ ሥርዓቶች ከማዕከል ከሚጫን ቁጥጥር ይልቅ ባልተማከለ ሁኔታ እርስ በእርስ በሚያደርጉት መስተጋብርና ቀጣይነት ያለው ዕድገት አማካኝነት፣ የተረጋጋና የደረጀ ሥርዓት መፍጠር ይችላሉ የሚለው ነው። ለዚህ ነው የመደመር ዕሳቤ ትብብርን መሠረት ያደረገ ያልተማከለ ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚያስፈልግ የሚያስረዳው። በጥቅሉ ትብብርን ማዕከል ያደረገ ተለማጭ ሥርዓት መፍጠር የሀገራትን ዕምቅ ዐቅም ወደ ሚጨበጥ ውጤት ለመቀየር ያለው ሚና ከፍተኛ ነው።

ለአብነት የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት በጥቂት ዓመታት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ለውጥ እንዲያስመዘግቡ ያደረጋቸው ዕምቅ ዐቅማቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በዚያው ቀጣና ያሉ ሌሎች ተመሳሳይ ሀገራት በተቃራኒ ተጉዘዋል። ተመሳሳይ የነዳጅ ሀብት ይዘው ዜጎቻቸው በከፍተኛ ችግር ውስጥ ሀገራትም በመፍረስ ሥጋት ላይ ናቸው። ይህም ዕምቅ ነው። በሀብታቸው ባደጉትና ባላደጉት የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት መካከል ያለው በቅም በጠንካራ ሥርዓት ካልታጀበ፣ ብቻውን ብልጽግናን ሊያመጣ እንደማይችል ማሳያ ነው። በሀብታቸው ባደጉትና ባላደረጉት የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት መካከል ያለው ዋነኛ ልዩነት የዕምቅ ዐቅም መኖር አለመኖር አይደለም። ያላቸውን ዕምቅ ዐቅም ወደ ሀብት የሚቀይር፣ ፍትሐዊና ዘላቂ ውጤት የሚያመጣ ሥርዓት መገንባት ወይም አለመገንባ ነው።

ሥርዓት ሀገራት ለሚያስመዘግቡት ዕድገት እጅግ ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ሌላኛው ምስክሮች የምሥራቅ እስያ ሀገሮች ናቸው። በምሥራቅ እስያ ያሉ ሀገራት ያላቸውን ውሱን ሀብት ተጠቅመው ከኋላ ወደ ፊት ሊስፈነጠሩ የቻሉት በገነቡት ሥርዓት ነው። የእስያ ተአምር የመጣው ራሱን ችሎ እንደ አንድ የልማት አማራጭ ተሞክሮ ተደርጎ በሚወሰድ ሥርዓት አማካኝነት ነው።

ሀገራችን ላለፉት መቶ ዓመታት ሦስት መንግሥታዊ ሥርዓቶችን አስተናግዳለች። ነገር ግን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ምን ያህል ተለውጠዋል? ለውጦ ምን ያህል መሻሻል አስገኙልን? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ አለብን። መልሱን ከድህነት አዙሪት ባለመውጣታችን እናገኘዋለን። ስለዚህ መንግሥታትን ከመቀያየር ባለፈ ሥርዓት እንደገና ከመቅረጽና ከማደስ አንጻር መሠረታዊ ለውጦች ነበሩን ወይ? የንጉሣዊው ሥርዓት በኅብረተሰብአዊሲለወጥ፤ እርሱም በተራው በቅይጥ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሲተካ፤ በሕዝባች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ለውጥ ማምጣት ተችሏልን? ወይም ተስፋዎችስ ነበሩ ወይ በየዘመኑ ሌሎች ተመሳሳይ ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉ ስኬታማ ሀገራትን ልምድ ለመቅሰም መሞከራችን ግልጽ ነው። የእነዚህን ሀገራት ተቋማትንና ፖሊሲዎችን ከመቅዳት ባሻገር ዱካቸውን መከተልና ያስመዘገቡትን የልማት ውጤቶች በሀገራችን መድገም ያልተቻለው ለምንድን ነው? የቀዳነው ፖሊሲ ለእኛ ስኬትን ያላመጣልን ለምንድን ነው? የሀገራችን | የሥርዓት ዕንቆቅልሽ ቋጠሮው የት ላይ ነው? መፍትሔውስ? ምላሽ ይፈልጋሉ።

የፖለቲካዊ ሥርዓቱን ጥቂት ባሕርያት ነጥለን እንመለከት። ንጉሣዊ ሥርዓት “ሰማ አይታረስ፣ ንጉሥ አይከሰስ” በሚል ንጉሥነት በግልጽ አይነኬነት የሆነበት ሥርዓት ነበር | ወደ ኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ስንሸጋገር ይህ ተረት ቀርቷል? ወይንስ “ሰማይ አይታረ ሊቀ መንበር አይከሰስ” ወደሚል ተሸጋገርን? ንጉሡ “ከፈጣሪ የተቀቡ” በሕይወት እስካሉ ድረስም ብቸኛ አስተዳዳሪ ነበሩ። ወደ ሊቀ መንበሩ ስንሻገር ሊቀ መንበሩ ሥልጣን | የሚለቁበት አግባብ በወረቀት ላይ ከመዘርጋቱ ባለፈ በተግባር ሥልጣን ማስለቀቅ ይቻል ነበርን? በኋላም ሥልጣን የለቀቁት በተዘረጋው አግባብ አልነበረም። ለመሆኑ ከንጉሡ ምን ይለያቸዋል?

CamScanner

ደርግ ለጭቁኑ ሕዝብ ጥቅም መጣሁ ብሎ ነበር። ኢሕአዴግም “ለጭቁኑ ሕዝብ ጥቅም በትግል ወደ ሥልጣን መጣሁ አለ። ለመሆኑ ከሊቀ መንበሩ ምን ያህል ልዩነት አገኘች 1 ወይንስ “…ጠቅላይ ሚኒስትር አይከሰስ” ወደሚል ተሸጋገርን? ከወረቀት ባለፈ ለውጡን የምናይበት በተግባር የተመነዘረ እመርታ በፖለቲካው ውስጥ ነበረን ወይ? ደርግ ተፎካካሪ ፓርቲዎችን አሳዶ የሚያጠፋበት አካሄድ ነበረው። ለመሆኑ ኢሕአዴግ ከዚህ ምን ያህል ተሻሽሏል? ንጉሡም ይሁን ደርግ ለሕዝብ ሮሮ “ጆሮ ዳባ ልበስ” ያሉበት አካሄድ ነበረ።

የኢሕአዴግ ዘመን በዚህ ረገድ ምን ያህል ለውጥ ነበረው? ምን ያህል ሕዝብን ለመስማት ዝግጁ ነበር? ሕዝብ በንጉሡ ጊዜ ከነበረው ፖለቲካዊ ተሳትፎና መብት የደርግና የኢሕአዴግ ዘመን ምን ያህል ለውጥ ነበረው? ጭቆና ቀርቶለታል ወይንስ ጨቋኝ ስሙን ቀይሯል? በጥቅሉ አንዱ ሄዶ ሌላው ሲተካ፣ “አይከሰሴነትንና አይተኬነትን” እየቀያየሩ ነው የመጡት። ይህም ለፖለቲካ ሥርዓት ቆሞ ቀርነት መገለጫችን ነው። ለሌሎች ዕድል የማይሰጥ፣ እኔ ብቻ ዐውቅልሃለሁ ባይነትን የተላበሰ፣ ችግሮቹን የማይቀበል፣ የሚቀበላቸው ችግሮች ቢኖሩ እንኳን “አስተካክላለሁ እንጂ ሥልጣን አልለቅም” የሚል፣ ብዙ ዓመታትን ወይም ዕድሜ ልኩን ሥልጣን ላይ መቆየትን የሚያልም የፖለቲካ ጠባይ የሦስቱም መንግሥታት የጋራ ጠባይ ነበር።

ከኢኮኖሚ ሥርዓቱ ባሕርያት አንጻር ደግሞ ብንመለከት ከፖለቲካው ብዙም የተለየ አይደለም፡፡ የንጉሡ ሥርዓት በባላባቶችና በጭሰኞች የሚገለጽ ነው። ኢኮኖሚው ብዙ ድኻ ጭሰኞችንና ጥቂት ሀብታም ባላባቶችን ይዞ ነበር። አብዛኛው ሰው ግን በልቶ ማደር ይቸገር ነበር። እንኳን የንብረት የራሱም ባለቤት ያልነበረ ሚልዮን ሕዝብ ነበረን። ደርግ “መሬት ለአራሹ” ን ሲደነግግ አብዛኛው ጢሰኛ የመሬት ባለቤት መሆኑ መልካም ነበረ። ስሙም ከጢሰኛ ወደ “አርሶ አደር” ተቀየረ። የኑሮ ደረጃው ግን ያንን ያህል ለውጥ አልነበረውም።

ለመሆኑ የአርሶ አደሩ ችግር ጢሰኛ ሆኖ መገበር ብቻ ነበርን? እንዲያማ ቢሆን ኖሮ የመሬት ባለቤት በሆነ ማግሥት የብልጽግና ማማ ላይ ባገኘነው ነበር። ግብርናን ከፖለቲካ መጠቀሚያነት ውጭ ችግሮቹን በዝርዝር ማየትና ተግባራዊ ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣት ያልተቻለው ለምንድን ነው?

ኢሕአዴግ በተራው ከደርግ ድኻ አርሶ አደርና ጥቂት ባለሀብቶችን ተረከበ። ከሃያ ሰባት ዓመታት በኋላ ስንገመግም ከድህነት አዙሪት ያልወጣ ሕዝብ ነው ያገኘነው። አሁንም በልቶ ማደር ልብስ መቀየር የሚቸገር፣ መኖሪያ ቤት የሌለው፣ ድኻና የድኻ ድኻ እየተባለ የሚከፋፈል ሕዝብ ነው ያተረፍነው። በንጉሡ ጊዜ “በአይከሰሴነት” የፈለጉትን “የእኔ ነው” ሲሉ ከነበሩ ባላባት ባለ ሥልጣኖች ወደ ባለሀብት ባለ ሥልጣናት ተሸጋገርን። በባለ ሥልጣንነትና በባለ ሀብትነት መካከል መሥመሩ ጠፋ።

ሕዝብን ማገልገል ራስን ከማበልጸግ ጋር አንድ ሆነው ተገኙ፡፡ ስለዚህ ከንጉሣዊው አገዛዝ እስከ አሁን ዘመን ድረስ የሕዝባችን ኑሮ ለውጡ እዚህ ግባ የማይባል ሆኗል። የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት ለውጥ ሕዝብን ከድህነት ከማውጣትና ከማበልጸግ አንጻር ለውጡ እምብዛም ነው። ሦስቱም መንግሥታት አብዛኛውን ሕዝብ ከእርሻ አላቆ ኢንዱስትሪ መ የሆነ ኢኮኖሚ የመገንባት ሕልም ነበራቸው። ከሦስተኛው መንግሥት የተረከብናት ሆ ግን አሁንም አብዛኛው ዜጋ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ እርሻ ላይ የተንተራሰ ሕይወት ያለው ሕዝብ ነው። መካከለኛ መደብ ማኅበረሰብ የመፍጠር ሕልም፣ ከሕልምነት በዘለለ ወደ ተግባር ሊቀየር አልቻለም።

የማኅበራዊ ሥርዓት ጉድለትንም እንመልከት፤ ለመሆኑ የማኅበረሰብ ባህል፣ እምነትና ወግ ሀብት በማፍራት ረገድ ያበረከተው አዎንታዊና አሉታዊ አስተዋጽዖ ምን ያህል ነው? የገዛ ልማዳችን በየዘመኑ የተለያዩ ፈተናዎችን እየደቀነ

CamScanner

እንዳንበለጽግ ዕንቅፋት የሆነብንስ ለምንድን ነው? ባህል፣ ልማድና እምነት ከሰው ልጅ አእምሮና ስሜት ጋር የተገናኙ ናቸው የማይጨበጡና የማይዳሰሱ ቢሆኑም ሀገር ለመገንባትና ለማፍረስ ግን ትልቅድርሻ አላቸው።

የሰው ልጅ አሉታዊ ባህሎችን ትቶ ገንቢዎቹን አጎልብቶና በእነሱ ላይ አክሎ በአዲስ አመለካከት ምኅዋር ውስጥ ካልገባ፣ የቀደመው ባህል እየጠለፈው አዲሱ አጉል ልማድ እየተጨመረበት መዳከር ልማዱ ይሆናል።

በነገሥታቱ ዘመን ሰውን ባሪያና ጌታ ብለው ሲፈርጁ ሥራን ደግሞ ክብር ያለውና የተና ብለው ከፍለውታል። የዘመኑ ልሂቃንም የሚቃወሙት ሳይሆን በዚያ ሥርዓት ውስ ቦታቸውን ማመቻቸትና ለክፍፍሉ ሐሳብ አፍላቂዎች ሆነዋል። በሽመና ሥራ የተሠማሩት "ቁጢት በጣሽ" ተባሉ።

የብረታ ብረት ባለሞያዎች "ቀጥቃጭ" የሚል የንቀት ስም ተሰጣቸው። ገበሬው "አፈር ገፊ ተባለ። ነጋዴው "መጫኛ ነካሽ" ተብሎ በመሰደቡ የንግድ ባህል በማኅበረሰብ ውስጥ እንዳይጎለብት አድርጓል።

ከእኛ እኩል የሽክላና የፖርሲሊ ሥራ ባህል የነበራቸው የሩቅ ምሥራቅ ሀገሮች ዛሬ የዓለምን ገበያ አጥለቅልቀውታል። እኛ ከነበርንበትም ወደ ኋላ ሄደናል። አሁንም ድረስ ሥራንና ሠራተኛን የመናቅ ባህል ምን ያህል ተሻሽሏል፣ እንደ ደቡብ ኮሪያ ያሉ የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት የማኅበረሰቡን ባህል በመቀየር ረገድ የተሳካ አብዮት በማካሄዳቸው ዛሬ በዕድገት ጣሪያ ላይ ይገኛሉ።

ሌላኛው የማኅበራዊ ሥርዓታችን መታወቂያ ለጦርነትና ለጦረኝነት የምንሰጠውን ቦታ ለሥራና ለሠራተኛነት አለመስጠታችን ነው። ለጦርነትና ለጦረኝነት ያለን ቦታ ለሀገሩ ሕይወቱን የማይሰስት ሕዝብ ፈጥሮልናል። የሀገርን ዳር ድንበር አስጠብቆልናል። ነገር ግን ለሥራና ለሠራተኝነት የምንሰጠውን ክብርና ቦታ አነስተኛ አድርጎብናል። ለሀገር ለመሠዋት የምንሰጠውን ዋጋ ያህል፤ ለሀገር ለመኖር የሚገባውን ዋጋ እንዳንሰጥ አድርጎናል። ሁሉንም ነገር በኃይል የማድረግ ባህልን አምጥቶብናል።

ለጦርና ለጦረኝነት ከልክ ያለፈ ዋጋ ስለምንሰጥ፣ በደም መሥዋዕትነት ብቻ የቆመች፣ ህልውናዋ በየጊዜው የሚፈተን ሀገር ፈጥረናል። ይህ የጦረኝነት ባህል አዎንታዊ አስተዋጽዖው፤ በተለይም የሀገርን ሉዓላዊነት ከማስጠበቅ አንጻር ከፍተኛ ቢሆንም፤ አሉታዊ ተጽዕኖንም ፈጥሯል። ሀገር ህልውናዋ የሚቆመው በደምም በላብም ነውና።

ስለዚህም ለደምም ለላብም እኩል ቦታ መስጠት ይገባን ነበር። እኛ ግን ለላብ ተገቢውንቦታ ባለመስጠታችን ህልውናችንን ያልተሟላና በየጊዜው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አድርጎታል።

"ከእንሥራ" ይልቅ "ለእንዝመት" የሚሰጠው ቦታ የመሪዎችን ጉዞ አዛብቶታል። መሪዎች የሥልጣን ማቆያ መንገዳቸውን ከላብ ከሚገኝ ዕሴት ይልቅ፤ ከደም ወደሚገኝ መሥዋዕትነት ቀይሮታል። መሣሪያ ያነገተ ከባላባት ተጠግቶ፤ ሳይሠራ መብላትን ከጌታው ይማራል። ከጌታው ቢጣላ ሸፍቶ እየዘረፈ መብላት ክብር እንጂ ውርደት አይሆንበትም። ይህ ባህል ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ይፈታተነናል። ሐሳቦቻችን አሁንም እንደታጠቁ ናቸው. ለመሆኑ ልዩነቶችን በመነጋገር የሚፈታ ማኅበረሰብ መፍጠር ለምን ተሳነን? ለሁሉም ነገር መፍትሔውን ጦርና ጦረኝነት አድርገን የምንቀጥለውስ እስከመቼ ነው? ኢትዮጵያውያን ይመልሱት ዘንድ ግድ ይላል።

በአሁን ዘመን ለሚገጥሙ ፈተናዎች ምላሽ ከመስጠታችን በፊት፣ ከቀድሞው ዘመን የተላለፈ ፈርጅና ደርዝ ከሌለው ችግር ጋር እንጋፈጣለን። ትግላችን የአሁኑ ዘመን ከፈጠረው ችግር ጋር ብቻ አይደለም። በዘመናት ከተከመረና ከተወሳሰበ ችግር ጋር ጭምር እንጂ። እርሱም ቢበቃን ጥሩ ነበር። ነባሩ ችግር ከወለደው የዛሬ ችግርም እንጋፈጣለን። እንዲሁም ነገ ቀድሞ ከሚጠብቀን ችግርና ፈተና ጋርም እንታገላለን።

CamScanner

በአጠቃላይ ባለፉት መቶ ዓመታት የተለያዩ መንግሥታትን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሥርዓቶች በጉድለት አስተናግደናል። በዚህ የተነሣ ዕምቅ ዐቅሞቻችንን አውጥተን በመጠቀም ወደ ብልጽግና ለምናደርገው ጉዞ ከአጋዥነት ይልቅ የዕንቅፋትነት ሚና ነበራቸው። ስለዚህም ዛሬ የሆንነውን ለመሆን ተገደናል። የሀገራችንም ኋላ የመቅረት መንሥኤው የኢኮኖሚያዊ፣ የፖለቲካዊና የማኅበራዊ ሥርዓቱ ጉድለትድምር ውጤት ነው። የሚፈጠሩ ሥርዓታዊ ክፍተቶች ከኢኮኖሚ ሥርዓቱ ክፍተት በተጨማሪ በማኅበራዊና በፖለቲካዊ ሥርዓቶች ላይ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል። ዘመንና አስተዳደር በተፈራረቁ ቁጥር ለውጦች በአንጻራዊነት ታይተው ይሆናል። እነዚህ ለውጦች ግን ከመሠረታዊ ችግሮቻችን ሳያወጡን በለውጥ ስም የተቀባቡ አያሌ ጊዜያት ባክነዋል።

እነዚህ የአንድ ሥርዓት ሦስት ክፍሎች (ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥሪቶች)፣ ከፍተኛ የሆነ ተመጋጋቢነት ያላቸው ናቸው። የአንዱ ክፍተት የሌላውን ሊቀሰቅስ ወይም ሊያባብስ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ በተለያየ የመንግሥት ርዕዮተ ዓለምና በተለያየ የብልጽግና ደረጃ የተለያየ ተጽዕኖ አላቸው። በገበያ መር ኢኮኖሚ ውስጥ የኢኮኖሚ ሥርዓት ወሳኝ ሚና አለው። ብዙዎቹ ችግሮች የሚመነጩትም፣ መፍትሔ የሚያገኙትም በኢኮኖሚው ሥርዓት የበላይነት የተነሣ ነው። እንደዚህ ባሉ ሀገራት የባለሀብቱ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው። ፖለቲካዊም ሆነ ማኅበራዊ ሥሪቱ በተጽዕኖ ክልላቸው ሥር ነው። ገንዘብ አድራጊ ፈጣሪ የሆነበት፣ ገንዘብ ሥልጣንንም ባህልንም መግዛት የሚችልበት የተጽዕኖ ደረጃን ተላብሷል።

በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበረሰባዊነት የተጫነው የቅይጥ ኢኮኖሚ ርዕዮተ ዓለም በሚከተሉ አንዳንድ ሀገራት፤ ማኅበራዊ ሥርዓቱ በማኅበረሰቡ ተጽዕኖ ሥር ነው። እንዲህ ዓይነት ሕዝብ መር የሆነ ሥርዓት መገንባት፣ የብዙዎቹ ሀገራት የፍላጎት ጥግ ነው። ሕዝብ መር ሥርዓት በብዙ ዓመታት የሥልጣኔ ሂደት የሚደረስበት ስኬት ነው።

በአዳጊ ሀገራት በተለይም ወደ ኋላ በቀሩ ሀገራት ከኢኮኖሚያዊውም ሆነ ከማኅበራዊው ሥርዓት ይልቅ የፖለቲካው ኃይል የገነነ ነው። እንዲህ ባሉ ሀገራት ደግሞ ፖለቲካው ኢኮኖሚውን ይዞ እንደፈለገው ያስኬደዋል። ማኅበረሰቡም በፖለቲካውና በኢኮኖሚው ተጠፍሮ በፍርሃት እንዲኖር ይገደዳል።

አፍሪካ ውስጥ ለሚፈጠር ድህነት ዋነኛው ምክንያት ከፖለቲካው ሥርዓት ጉድለት ጋር የተያያዘ ነው። ፖለቲካዊ ክፍተቶች ፈጣን፣ ፍትሐዊና ዘላቂ ልማት እንዳይረጋገጥ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ተጽዕኖ አላቸው።

በሀገራችንም ብልጽግናን ለማረጋገጥ በሚደረግ ጥረት ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሽግግርን ማምጣት ያልተቻለው፤ ፖለቲካዊ ሽግግርን ማምጣት ባለመቻሉ ነው። ሀብት የመፍጠርና በፍትሐዊነት የማከፋፈልን ግብ ለማሳካት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች የፈጠሩት ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም። ለፖለቲካ ህልውና የሚደረገው ትግል ብልጽግና ትክክለኛውን ቦታ እንዳያገኝ አድርጓል።

ያሳለፍናቸው አስተዳደሮችም ከውስጥና ከውጭ በሚያጋጥማቸው የህልውና ምክንያት ማኅበረሰቡን አስተባብረው ወደ ግንባር እንጂ ወደ ማሳው ለውጥና በማሻሻያ አልታገዙም። በዚህም ምክንያት ቀጣይነታቸውና ውጤታማነታቸው | በሰላሙ ጊዜም ቢሆን ኢኮኖሚያዊ ለውጥን ለማምጣት የተደረጉ ጥረቶች በፖለቲካ ጥያቄ ውስጥ ሲገባ ተስተውሏል። በቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማምጣት የተደረጉ ጥረቶች የባላባቱን ሥርዓት በሚቀይር ማሻሻያ ባለመታገዛቸው በውጤታማነታቸው ላይ የሚያዳልጥ ውኃ ተቸልሷል።

የደርግ ዘመን የኅብረተሰብአዊው ርዕዮተ ዓለም አስተሳሰብ የበላይነትን የተጎናጸፈ ጊዜ እንደነበር ይታወሳል። የግል ባለ ሀብቱን አስተባብሮ ኢኮኖሚውን ከመገንባት ይል የተለያዩ ገደቦችን መጣል ዋና ሥራ ነበር። ባለሀብትነት ስግብግብነት እስኪመስል ድረስ የተወገዘ ተግባር ሆነ። የአብዮታዊነትና የኅብረተሰብአዊነት መለኪያው መቆራፈድና መቆራመድ መሰለ። በመንግሥት ውሱን ሀብትና የማስፈጸም ዐቅም ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ኢኮኖሚ ለመገንባት ተሞከረ። ይሄም ኢኮኖሚውን አሥሮ ሀገራችንን ለከባድ ቀውስ አመቻችቶ ሰጠ።

CS CamScanner

የፖለቲካ ሥልጣን ኃይል ከፍተኛ መሆን ለአምባገነናዊ ሥርዓት ምቹ መደላድለ ይፈጥራል። ባለ ሥልጣንነትን አድራጊ ፈጣሪ ያደርጋል። የኢኮኖሚውና የማኅበራዊው ሥርዓቶች ኃይል በባለ ሥልጣኑ እጅ ይወድቃል። “ባለ ሀብትነት ለባለ ሥልጣን ታማ መሆን ነው” የሚል ትርጓሜን ይይዛል። ማኅበረሰብ ደግሞ በሁለቱ ኃይላት ቅንጅት የሚፈጠር የጭቆና ቀንበርን ተሸካሚ ይሆናል። ሕዝብን ሊያገለግሉ የተመሠረቱ ተቋማት ሕዝብን የሚያንገላቱ ይሆናሉ። ተቋማዊነት ቦታ ያጣል። መዋቅርና መመሪያዎች የይስሙላ ይሆናሉ። ግልጽነትና ተጠያቂነት ዘራቸው አይገኝም። ለውጥን መላመድና ከቴክኖሎጂ ጋር አብሮ መሄድ የማይታሰብ ይሆናል።

በሀገራችን ተቋማትን የመገንባት ጉዳይ በየጊዜው የሚነሣ እንደሆነ እሙን ነው፡ ነው የሚባል ርምጃ ግን ገና አልተራመደም። ሀገራችን በድህነት ውስጥ እንድታልፍ የከፈተው የተቋማት ደካማ መሆን ነው። የበቁ ተቋማት ሊላበሷቸው የሚገቡ ባሕርያት | ብሎም ሽክሙ እንዲበዛባት ካደረጉ መንሥኤዎች ግንባር ቀደሙና ለሌሎች መፈጠር በር በተቋሞቻችን ላይ እምብዛም አይታዩም። ሥራዎቻቸውን በሕግና በሥርዓት ከመሥራት ይልቅ በዘፈቀደ ይከውናሉ። ወጥነትና መስከን አይታይባቸውም። ይህ አካሄዳቸውም ግልጽና የሚያስጠይቅ ሆኖ አልተደነገገም። ወይም ድንጋጌዎች ከባለ ሥልጣኑ በታች ተደርገው ይታያሉ። በዚህም የተነሣ ተሿሚ ማለት ሕዝቡን የሚያንገላታ፤ ተገልጋይ ማለትም አገልግሎትን እንደ ችሮታ ከተሿሚ ጠባቂ ሆነ። ይህ ዓይነት ግንኙነት ሕዝብ በተቋማት ላይ ያለውን እምነት ሸረሸረው። ከትክክለኛ አሠራር ይልቅ በጉቦና በትውውቅ አገልግሎትን ማግኘትን ልማድ አደረገው።

ጠንካራ ባልሆኑ ተቋማት አውታር የቆመ ሀገረ መንግሥት፣ ሥርዓታዊ ችግሮችና መዋቅራዊ ፈተናዎች ይበዙበታል። በተቋሙ ተልዕኮና ገቢር እንዲሁም በልሂቃንና በሕዝብ መካከል ያለው ግንኙነት ተቃርኗዊ አቅጣጫ ይይዛል። በኃይልና በፍላጎት በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሳብ ተቋም፣ ሥርዓትና መዋቅሮቹ ብልጽግናን ከማረጋገጥ ይልቅ ድህነትን ያመርታሉ።

የበቃ ተቋም የሚፈጠረው የሚታወቅ አሠራር፣ የሚጠየቅ አካል፣ የማያልቅ ተደማሪ ኃይልና ሥርዓታዊ ተመጋጋቢነት ሲኖር ነው። የበቃ ተቋም የገነባ ሀገር ግብን በቅልጥፍና፣ በጥራትና በፈጠራ በመከወን፣ ሥርዓታዊ ቅልጥፍናን ያረጋግጣል። ሥርዓታዊ ቅልጥፍናን በማረጋገጥና በማጽናት ደግሞ መዋቅራዊ ኃይልን ይዘረጋል።

የተጋፈጠውንም ሆነ የሚመጣውን ፈተና በመፍታት ለትውልድ ዕሴት ለመፍጠር አንድነት ያለው ኃይልና ብዙ ከዋኝ እጆች ያስፈልጉናል። በአደጋ ጊዜም አንድም ሺም ሆነው ይመክታሉ፤ ያጠቃሉ። እንዲህ በሚገነባ ሥርዓታዊና መዋቅራዊ ኃይል ሀገራት ህልውናቸውን ያረጋግጣሉ። ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና በመንገዱ ይጸናል። ተድላና ፍሥሐ የሞላበት ማኅበረሰብ ይፈጠራል። ጦር ሰብቆ የሚበግራቸው፣ መጽውቶ የሚማርካቸው አይኖርም። የተፈጥሮን ገደብ ጥሰው፣ የድንቁርናን ጨለማ ገልጠው፣ በኃይል ላይ ኃይልን ያበዛሉ።

## 2.5. ጦርነትና ግጭት

ጦርነት አውዳሚ ነው። ሀገራችን በጦርነት ያተረፈችባቸው ጊዜያት ቢኖሩም፣ ያልከሰረችበትና ያልወደመችበት ጊዜ ግን አልነበረም። ጦርነት ከድህነት ጋር ቀጥተኛ ዝምድና እንዳለው ጦርነት በዘመኗ ሁሉ ያልተለያት ሀገራችን በድህነት አዙሪት ውስጥ መሆኗ ዋና ምስክር ነው። ኢኮኖሚን የሚያወድሙ የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢኖሩም፣ የጦርነት መልክ ግን ይለያል። ጦርነት ገና መምጣቱ ሳይታወቅ የሀገርን ኢኮኖሚ ይበላል። ለመምጣት ዳርዳርታው ሲታይ ደግሞ ዝግጅቱ ኢኮኖሚን ይበላል። ሲመጣ ደግሞ ከፍተኛ ኪሳራ አስከትሎ ኢኮኖሚን ለሦስተኛ ጊዜ ይበላል። አልፎ ሲሄድም በአዘቅት ውስጥ ጥሎ ስለሚያልፍ መልሶ ግንባታውና ሰቆቃው ኢኮኖሚን ለአራተኛ ጊዜ ይበላል። ጦርነት የብልጽግና ባላንጣ ነው።

የጦርነት ሥጋትን ለመከላከል አስቀድሞ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ነገር ነው። የመ ዐቅም ግን በአንድ ጀምበር የሚገነባ አይደለም። ባለንበት ዓለም ውስጥ የሀገር መ መገንባት ሌላ አማራጭ የሌለው ተግባር ነው። መከላከያ ሠራዊት መገንባት

CS CamScanner

ደግሞ እጅ ተወዳዳሪነትን እያካበቱ የመሄድ ተግባር ነው። ዓለም ከደረሰበት የውትድርና ትጥቅ ደረጃ ከፍተኛ መዓለ ንዋይ የሚፈልግ ሀገራዊ ተልዕኮ ነው። በየጊዜው ወታደራዊ ዘመናት መድረስ ያስፈልጋል።

በተለይም ሥጋቶቻችንን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ጦርነትን የሚያስቀር የትጥቅና የሠራት ዝግጅት ማድረግ ለነገ የሚባል አይደለም። ጦርነት ገና ግም ሳይል፣ በሥጋት ብቻ ዓለም ብዙ ሀብቷን እንድትገብርለት አድርጓል። ጦርነት ድምፁ ሳይሰማ ብዙ የሚዘርፍ ኃያል ነው። በሌሎች ልማቶች ላይ መዋል የሚችል ሀብትን ሲወስድ ቅር አይለውም።

የሀገራችን ታሪክ ከጦርነት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ በሰላሙም ጊዜ የመከላከያ ሠራዊት ግንባታዋን አጠናክራ የመቀጠል ግዴታ ውስጥ ገብታለች። በየዘመናቱ ያሉ መንግሥታት የመከላከያ ኃይላችንን ለመገንባት ከፍተኛ ሀብት መድበዋል። የኢትዮጵያ የውትድርና ታሪክ ከ30oo ዓመታት በላይ ያልፈዋል። በዚያ ዘመን የነበረው ሁለት ዓይነት ወታደር ነው። የተወሰኑ ወታደሮች ርስትና የንጉሡን ስጦታ እያገኙ በንጉሡና በመኳንንቱ ሥር ይታዘዛሉ። አብዛኛው ወታደር ግን ሲጠራ ብቻ የሚሰባሰብ የገበሬ ጦር ነበር። አደረጃጀቱም ማዕከላዊ አልነበረም። በንጉሡም በመኳንንቱም የሚታዘዝ ጦር ነበረ። ይህም አልፎ አልፎ በማዕከላዊ መንግሥትና በአካባቢ ገዥዎች መካከል ለሚነሣ የእርስ በርስ ጦርነት አንዱ መነሻ ነው። ዘመነ መሳፍንት እንዲፈጠር ያደረገው ዋነኛው መነሻ በየመሳፍንቱ የሚታዘዝ ጦር ስለነበረ ነው። ያ ጦር ዐቅሙ እየፈረጠመ ሲሄድ ማዕከላዊ መንግሥቱን መግዳር ጀመረ።

በመካከለኛው ዘመን የገበሬ ጦር ማደራጀት ተጀመረ። በንጉሡ መሬት ላይ በሰላሙ ጊዜ ያርሳል፤ ከግብር እና ከሌሎች ግዴታዎች ነጻ ነው። በምትኩ ወታደራዊ አገልግሎት ይሰጣል። በ5ኛው መክዘ አካባቢ በንጉሡ ዙሪያ የሚቀመጡ ዕዞች መደራጀት ጀመሩ። እነዚህ አነስተኛ ዕዞች ዋናው ሥራቸው ቤተ መንግሥቱን መጠበቅና በንጉሡ እየተላኩ ግዳጅ መፈጸም ነው ::

በዚህ ዘመን አራት ዓይነት ሠራዊት ነበረ። እነዚህም በንጉሡ የሚታዘዙ ዕዞች፤ በጦር የአበጋዞች የሚታዘዙ ዕዞች፣ ጠረፍ ጠባቂ ልዩ ወታደሮችና መደበኛ ያልሆኑ ወታደሮች - ናቸው። ጠቅላላው ወታደር ሠራዊት" ወይም "ጭራ በሚል ስያሜ ይታወቃል። የሠራዊቱ አከፋፈል በሚመሩት አመራሮች የሚወሰን ነበር። ስያሜውም ተልዕኳቸውን የያዙትን መሣሪያ፣ የሠፈሩበትን አካባቢ የሚመለከት ነበር። እነዚህ ወታደሮች በሰላም ጊዜ ከርስታቸው ጥቅም የሚያገኙ ሲሆን በጦርነት ጊዜ ደግሞ ከሚመዘበረው አካባቢ ይጠቀማሉ።

በዐፄ ቴዎድሮስ ዘመን የጦር መሣሪያዎች ከነገሥታትና ከባላባት የጦር መሣሪያነት ወደ ሀገር ሀብትነት መጡ። ሠራዊቱም ከግለሰብ አዳሪነት ወደ ሀገር አገልጋይነት ተቀየረ። ንጉሡ አሥራት የተባለ ግብር እንዲሰባሰብ በማድረግ የሚሰበሰበው ገንዘብ ለሠራዊት ደመወዝና ቀለብ እንዲውል አደረጉ። በዚህ የተነሣ በማዕከላዊ መንግሥት ሥር የሚያድረው ወታደር እየበዛ መጣ።

የኢትዮጵያ መሪዎች ከቀድሞ ጀምሮ ሠራዊቱን ለማዘመን በዘመን የደረሱበትን ሲያደርጉ ነበር። ከግብር ነጻ ማድረግ፣ ርስት መስጠት፣ ከውጭ አሠልጣኞች አስመጥቶ ማስልጠን ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎችን ማስመጣት፤ በሀገር ውስጥ የጦር መሣሪያዎችን ለማምረት ጥረት ማድረግ ዋና ዋና የጦር ማዘመኛ መንገዶቻቸው ነበሩ።

የመከላከያ ሠራዊታችን መከላከያ ሚኒስቴር ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ እያደገና እየተሻሻለ መጣ። በዘመኑ ሁሉ ሀገሩን አስከብሮ ለሌሎች ሀገራትም የሰላም ዘብነት ተርፏል። ዛሬም ላይ ለሌሎች ሀገራዊ ግዳጆች ራሱን እያዘጋጀ በዘላቂ የለውጥ መዘውር ውስጥ ይገኛል። ሠርክ ዝግጁነት የመከላከያችን መለያ ነው።

ይሁንና ይህ ከ ዝግጁነት፣ የጦርነት ድምፅ ሳይሰማ እንኳን በየዘመኑ ከፍተኛ ሀብትን ለመከላከያ ሠራዊት ግንባታ እንድናውል አድርጎናል ::

CamScanner

የጦርነት ድምፅ ሲያስገመግም ደግሞ የዝግጅቱ መጠን ሌላ መልክ ይይዛል። ሰመት በተረጋጋ መልኩ ይካሄድ የነበረው ዝግጅት፣ ጦርነት ሲያስገመግም በተለየ ውጥረ ይታጀባል። ከፍተኛ ሀብትን በማንቀሳቀስ የአየር፣ የየብስ፣ የባሕር፣ የሕዋና የሳይበር ልምምዶችን ማድረግ ግዴታ ይሆናል። ጦረኞችን፣ የጦር አመራሮችን፣ የጦር መሣሪያዎችን አጋዦችን ሁሉ ዝግጁ የማድረግ ሥራ ይሠራል። ይህም ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅና በጦርነቱ ወቅት ከሚወጣው ባልተናነሰ ወጪ የሚጠይቅ ነው። ፋብሪካዎች ከመደበኛ ሥራቸው በተጓዳኝ በተለየ አስቸኳይነት ጦርነቱን ታሳቢ ያደረገ ምርት ያመርታሉ።

ጦርነት ገና ሳይጀመር ይሄንን ሁሉ ሀብት ካስወጣ በኋላ እንኳን በቀር አዋጪ ነው። ምክንያቱም በዝግጅት ጊዜ ሀብታችንን ሰ በላ የቆየው ጦርነት፤ ሠራዊታችንን፣ ሕሰባችንን ለልማት ተብለው የተገነቡ መሠረተ ልማቶቻችንን ሁሉ መብላት ይጀምራል። ይባስ ብሎ ደግሞ ወጣትና አልሚ የምንለውን ኃይል ይነጥቀናል። ዐቅመ ደካሞች፣ ሕፃናትና ሴቶች ቀያቸውን ትተው ይሰደዳሉ። ከተሞች የጦርነት አውድማ በመሆናቸው ፈራርሰው እንደ አዲስ ለመሠራት እንኳን በማይመች ሁኔታ ይደቅቃሉ። ገበሬው ማረስ ይቸገራል። የዘራውንም መንከባከብም ማጨድም አይችልም። ተሳክቶለት ቢሰበሰብ እንኳን ለጦርነት የሚውል ይሆናል።

በዘመናት ሁሉ ለዚህ ጊዜ የተገነባው የመከላከያ ኃይልም ያለውን ሁሉ አውጥቶ ይዋጋል። መሣሪያዎቹ ይወድማሉ። ትጥቅ ነውና በተለየ በጀትም ቢሆን እንደገና ይገዛል። “ሁሉ ነገር ወደ ጦር ግንባር” ማለት ይመጣል። ያለን አሳጥቶ፣ ሀገራችንን እንደ ሰደድ እሳት በልቶ፡ አንዳንድ ጊዜም ሀገርን አፍርሶ፣ ይደመደማል።

ጦርና የጦር ድምፅ አይሰማ ይሆናል እንጂ ጦርነት በዚህ አያበቃም። ድኅረ ጦርነት ተጽዕኖው ይቀጥላል። የወደሙ መሠረተ ልማቶችን መልሶ ከመገንባት አንሥቶ በርካታ ተደፍነው የማያልቁ ቀዳዳዎች ተግተልትለው ይመጣሉ። በርግጥ በሶሪያ፣ በሊቢያ በቅርቡ ደግሞ በዩክሬን፤ የነበረውን የጦርነት አፍራሽነት ስንመለከት፤ ጦርነት መሠረተ ልማትን ያወድማል የሚለው ገላጭ አይሆንም፤ ይልቁንም መሠረተ ልማትንም፣ ልማትንም፣ የመልማት ዐቅምንም፤ በአጠቃላይ "ሀገርን ያወድማል የሚለው የተሻለ ነው። መልሶ ለመሥራት የሚያስችለው ሀብትም በጦርነቱ ተበልቷል። ቀላል የማይባል ሕዝብ በስደትና በተረጂነት ውስጥ ይገባል። ልጆቹን ለጦርነት ገብሮ በኀዘን ውስጥ ይኖራል። የሠራዊት አባላት በአስከፊ እልቂት ውስጥ እንደማለፋቸው ጓዶቻቸውን ያጣሉ።

አንዳንዶች አካል ጉዳተኛ ይሆናሉ። በዚህም በከባድ ኀዘንና ጭንቀት ውስጥ ይገባሉ። በአጠቃላይ ትኩረታችንን ጦርነት ላይ አድርገን ቸል ያልነው ችግር ሁሉ ስንጋፈጠው፣ ልብ ሰባሪና ዐቅም የሚያሳጣ ነው። ከጦርነት ማገገም ከባድ መሪዎች የሚፈትን ሥራ ነው።

ሀገራችን ከጦርነት ያረፈችበት የመንግሥት ዘመን ነበር ማለት ይቸግራል። ሠርዓ ከመሆን ባለፈ በጦርነት ዝግጅት ከፍተኛ መዓለ ንዋይ ማፍሰስ ሳይገደድ ያለፈ መን የለንም። ያለፉትን መቶ ዓመታት እንኳን ብንወስድ የዐፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከውስጥና ከውጭ ኃይሎች ጋር ተዋግቷል"።

ደርግ በበኩሉ ሥልጣን በያዘ ማግሥት የውስጥም የውጭም ውጊያ ገጥሞታል። ደርግ ዘመኑን ሙሉ ከውስጥ የብሔር ተዋጊ ኃይሎች ጋር ሲዋጋ ነው የጨረሰው።

በመጨረሻም በእነዚሁ ኃይሎች ጥምረት ነው የወደቀው። ኢሕአዴግም በመጀመሪያው ወህት ዓመታት ከኤርትራ ጋር ተዋግቷል። ይህ የጦርነት ፍጥጫ እንዳለ ሆኖ፣ ከሶማሊያ ተገንጣይና አሸባሪ ኃይሎች ለምሳሌ አልሸባብ ጋር ሌላ ጦርነት አድርጓል።

CamScanner

ታሪካችን ሁሉ ከልማት ይልቅ በጦርነትና በግጭት የታጀበ ነው፣ የጦርነትን ወሬ ሳንሰማ ባለንበት ዘመንም የለም። የውጭ ጦርነት ቢጠፋ የውስጥ ግጭት ይመጣል። የውስጥ ግጭት ቢጠፋ መፈንቅለ መንግሥት ይሞከራል። መፈንቅለ መንግሥት በጠፋ የፖለቲካ አመራሩ እርስ በርሱ ይባላል። ይህ ሁሉ ቢጠፋ ጥያቄዬ ይሰማ' የሚሉ ሰላማዊ ዐመጾች ይከሠታሉ።

እነዚህ ከውስጥና ከውጭ የገጠመን ግጭትና ጦርነቶች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮቻችንን አወሳስበውታል። በድህነት ላይ ጦርነት ማለት በብሔር ላይ ቆረቆር ነው። የቅድመ ጦርነት፣ የጊዜ ጦርነትና የድኅረ ጦርነት አፍራሽ ክንዶች ሥነ ልቡናዊ መታወክን በማኅበረሰብ ውስጥ ያራባሉ። በጦርነት ውስጥ ደጋግሞ ያለፈ ማኅበረሰብ መስተጋብራዊ ግንኙነቱ በጥርጣሬ፣ በፍርሃትና ባለመተማመን የተሞላ ይሆናል። በጦርነት አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጉዳት የደረሰበትና ከሰብአዊ ልማት የጎደለ ማኅበረሰብ ደግሞ በድርብርብ ችግር ይመታል። በጦርነት ዐቅሙ የተበላ መንግሥታዊ ሥርዓትም፣ መሠረታዊ የሰው ልጅ ፍላጎቶችን ለማሟላት ፈተና ውስጥ ይወድቃል። ለዚህ ጥሩ ማሳያም እኛው ነን።

በእንደዚህ ዓይነት የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ያለ ሥርዓት የሥራ ዕድል መፍጠር ይሳነዋል። ሀገራችንም ጊዜዋ እየተበላ አብረዋት የተነሡ በጊዜ ውስጥ ተራምደው ቀድመዋታል። ከጊዜ ኋላ ቀርታ አመሻሽ ላይ በድርብርብ ችግር ተጠላልፋ መውጣትና መራመድ ፈተና ሆኖባታል። በጦርነት ግጭት መሰነጣጠቅ የጀመረው ሀገራዊ መሠረት በአካል፣ በሥነ ልቦናና በማኅበራዊ ቀውስ ቀዳዳው በዝቷል። የኢኮኖሚ ድቀት ያነተበው ሀገረ መንግሥት ተፈጥሯል። በመዳከሙ የተነሣም በዕዳ ወጥመድ ተይዞ ወዶገብ ገባሪ ይሆናል።

በድኅረ ዘመናዊነት ደግሞ ብድር፣ ርዳታና ሽብር ማስገበሪያ መሣሪያ ሆነው መጥተዋል:: አበዳሪዎች መንጠቋቸውን ከዓሣው ጉሮሮ ሰክተው የዓሣውን በሕይወት የመኖር ዕጣ ፈንታ በእጃቸው አድርገውታል። የመኖር ዕጣ ፈንታው ከእጁ የወጣ “ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ” ይሆናል። አንዳንዶች ይባስ ብለው ብድርን ለልማት ሳይሆን ሥልጣናት መምነሸነሻ ያውሉታል። ይህም በዕዳ ተጠልፈው እንዲወድቁ ያደርጋቸዋል:: በዕዳ መጠለፉ ደግሞ በህልውና ፈተናና በድህነት አዙሪት ውስጥ ያከርማቸዋል።

እንግዲህ ከዕድገት ማማ ላይ ለመገኘት ብዙ ዕድል የነበራት ሀገራችን ዕምቅ ዐቅሞቹ አውጥታ ለመጠቀም አልቻለችም። በዚህም የተነሣ በድህነት አዙሪት ውስጥ ዘመኗን አሳልፋለች። ዕምቅ ዐቅምን መጠቀም ከብዙ ነገሮች ጋር ይያያዛል። ዋነኛው አንኳር ጉዳይ መሠረተ ልማትን ከመገንባት፣ በሚገባ ከማስተዳደርና ከማስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው. ሀገራችን ሰፋፊ መሠረተ ልማቶችን ለመገንባት የሚሆን በቂ ወረት ስለሌላት በቅያዎ ተከተል አንዱን ለሌላው ግብአት እያደረገች ለመሥራት ሞክራ ነበር። ይህ ጥረት ማ ዘመናዊ በሆነና የራሳችንን ሁኔታ ከግንዛቤ ባስገባ ሥርዓትና መዋቅር አልታገዘም። ይህም ለተደራራቢ ችግሮች አጋልጦናል።

ከዚህ አልፎ የተገነባውን ጥቂት መሠረተ ልማት ደግሞ ጦርነትና ግጭት ብል እንደነካው ልብስ መልሶ ይበላዋል። በመሆኑም ከዜሮ መጀመር የሁሉም የኢትዮጵያ መንግሥታት ዕጣ ፈንታ ሆኗል። ይህ ሁኔታም ኢትዮጵያ ከድህነቷ ለሚያተርፉ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ምቹ እንድትሆን አድርጓታል። በውጤቱም ሀገራችን የሀብታም ድኻ፤ ሕዝባችንም በሀብት ላይ ቆሞ በድህነት እየኖረ ነው።

CamScanner

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. መሻገሪያ መንገድ

ሀገራችን ከድህነት የምትወጣበት ሁነኛ ሥርዓት በአግባቡ አልተዘረጋም። አስፈላጊው መሠረተ ልማትም በበቂ ሁኔታ ካለመገንባቱም በላይ ዕምቅ ዐቅሞቻችንን መጠቀም አልቻልንም። _ እየተንፏቀቅንም ቢሆን የገነባናቸውን አነስተኛ መሠረተ ልማቶች ጦርነት እያወደመ እንደ አዲስ ሲያስጀምረን ቆይቷል። እነዚህ ሁሉ ተደምረው ወደ ኋላ ለመቅረታችንና በድህነት አዙሪት ውስጥ ለመዋኘታችን ዋነኞቹ ምክንያቶች እንደሆኑ በመጠኑ ተመልክተናል። ታዲያ የመሻገሪያው መንገድ የትኛው ነው? ምን ዓይነት ሥርዓት መገንባት ይገባናል? የብልጽግና ጉዟችንስ በምን መርሕ መመራት ይኖርበታል? የሚሉትን ለማየት እንሞክራለን።

ብልጽግና የተከታታይ ጥረቶችና ለውጦች ውጤት ነው። ከማደግ ወደ ኋላ የቀሩ ሀገራት መንግሥታትና መሪዎች ቀድመው እንደ በለጸጉት ሀገራት ልማትን ማሳካት ቀላል የቤት ሥራ አይሆንላቸውም። የበለጸጉ ሀገራት አሁን ላሉበት ደረጃ የመድረሳቸው ምሥጢር በየትውልዱና በየዘመኑ የተከማቸ ወረት መኖሩ ነው። ይህም ወረት አንዱ በአንዱ ላይ እየተጨመረ መጥቷል። እነዚህ ከፍተኛ ወረት ያከማቹ ሀገራት በየጊዜው የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቋቋምና ተወዳዳሪ ሆነው ለመገኘት የተሻለ ዕድል አላቸው።

በተነጻጻሪ ደግሞ አዳጊ ሀገራት ብዙ ሥራ አለባቸው። ትናንት ያልተሠሩ ውዝፍ ሥራዎችን ማቃለል አንዱ ሥራቸው ነው። የዛሬን ሥራዎች መሥራትና ለነገው ትውልድ መደላድል መፍጠር ሌላው ጊዜ የማይሰጥ ግዳጃቸው ነው። የበለጸጉት ሀገራት በተገነባ መሠረት ወደ ላይ ይገነባሉ። አዳጊ ሀገራት ግን መሠረት የሚጣልበትን ቦታ ገና በመፈለግ ላይ ናቸው። ዛሬ እንደ አዲስ መሠረት መጣል አለባቸው። በጣሉት መሠረት ላይም በፍጥነት የመገንባት ተደራራቢ ሥራዎች አሉባቸው።

የመደመር ዕሳቤ ይሄንን ውዝፍ ሥራ ለማቃለል የሚያስችል ወረት በሌለበት ሁኔታ የምናደርገው የተናጠል መፍጨርጨር ትርጉም የለውም ብሎ ያምናል። ይልቁንስ ይህ የተከማቸ የቤት ሥራ መቃለል የሚችለው መጀመሪያ ለብልጽግና የሚሆነንን መነሻ ወረት ከተበተነበት ማሰባሰብ፤ ከዚያም አልፈን በተከታታይ ወረት መፍጠር ስንችል፤ እንዲሁም ወረትን በወረት ላይ በማከል የወረት ክምችት ስናካብት ነው። ቀጥሎም ዐቅሞቻችንን ስናከማችና ስናጠናክር ነው ይላል።

ይህን ግን እስካሁን ሳናደርግ ቆይተናል፤ የተናጠል ሩጫ ላይ ከርመናል። በዚህም ምክንያት አሁን ካለንበት የብልጽግና ደረጃ አንጻር የምንጓዘው ርቀት ረጅም፤ የምንወጣው አቀበትም አድካሚ ነው። ያሉብንን ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች መፍታት ለነገ ልንለው የማንችለው ከፊታችን የተደቀነ ሥራ ነው። ከዘገየንበት በፍጥነት ለመውጣት መፍጨርጨር ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው። ከቀደሙት ላይ ለመድረስ መገሥገሥ ትንፋሽ የሚያሳጥር አቀበት ነው።

የመዘግየት ጣጣን ለማቃለል ወረት ማሰባሰብ ብቻውን በቂ አይደለም። በመደመር መጽሐፍ እንደተጠቀሰው ይህን የመዘግየት ጣጣ የሚያቃልል አቋራጭ መንገድ ያስፈልጋል። ይህ አቋራጭ መንገድ የባከነውን ጊዜያችንን የሚያካክስ መሆን አለበት።መንገዱ ከቀደሙ እንድንደርስና እንድናልፋቸው ሊያደርገን ይገባል። ከጉስቁልና በአጭር ጊዜ የሚያላቅቀ መሆን አለበት። የበለጸገችና ገናና ኢትዮጵያን በጥቂት ዓመታት ውስጥ እውን ለማድረግ የሚያስችለን መንገድ መሆንም ይጠበቅበታል።

ምዕራባውያን ለብልጽግና ሁለትና ሦስት መቶ ዓመታት ወስዶባቸው ነበር። ዘግይተው የበለጸጉት የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት ግን ይሄንን አሳጥረው በሁለትና ሦስት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ ደርሰውበታል። እኛ ደግሞ የእነርሱን ተአምር አሻሽለን መፍጠን ይኖርብናል።

CS CamScanner

ኋላ ከቀረንበት ወደ ፊት በመሻገር፣ ከችግር አዙሪት መላቀቅና ተወዳዳሪ ሆነን መውጣት የምንችለው በመደመር መንግሥት የዕድገት ምሕዋር ውስጥ ስንገባ ነው። ምክንያቱም ካለብን ችግርና ካለንበት የብልጽግና ደረጃ አንጻር በተለመደው መንገድ በመጓዝ የተሰየ ውጤት ልናመጣ አንችልም። በተለመደው መንገድ ከችግራችን መላቀቅና ተወዳዳሪ ሆኖ መውጣት የሚታሰብ አይደለም። መሻሻል ሊኖረን ቢችል እንኳን ከአደጉት ሀገራት ተርታ ልንሰለፍ የምንችልበትን ዐቅምና ብቃት አንታጠቅም። በመሆኑም ካለንበት ደረጃ በቶሎ መንጭቆ ሊያወጣንና ሊያስፈነጥረን የሚችል፤ የዓለምን አሁናዊ የተለዋዋጭነት ሁኔታ የሚመጥን፤ እመርታዊ ለውጥ ማምጣት አለብን።

ከተራራ ጫፍ ወደ ላይ የሚዘልና ከተራራው እግር ሥር ወደ ላይ የሚዘሉ ሰዎች ሊደርሱ የሚችሉት ከፍታ አንድ አይደለም። ከተራራው እግር ሥር የሚዘለው ሰው ከተራራ ጫ ላይ ከሚዘለው ጋር መስተካከል የሚችለው ወይም መበለጥ የሚችለው የሚያስፈነጥረውን ነገር ከተጠቀመ ብቻ ነው። የእኛም የዕድገት ሞዴል መሆን ያለበት ይኸው ነው።

በመደመር መንግሥት አመራር ተስፈንጥረን ከቀደሙን ጋር ካልተስተካከልን ወይም ካልቀደምን በቀር፣ በአደጉት ሀገራት ላይ ጥገኛ እንሆናለን። ይህ ደግሞ የፈለጉትን አድራጊ፣ ያሉትን ፈጻሚ ሆነን እንድንቀር ያደርገናል። ሉዓላዊነታችን ቦታ ያጣል። የአባቶቻችን መሥዋዕትነት መና ይቀራል። ተመልሰን በችግሮቻችን አዙሪት ውስጥ እንቀረቀራለን።

ስለዚህ ያለንበትን ደረጃ በሚመጥንና የባከነውን ጊዜ ሊያካክስ በሚችል መልኩ እመርታዊ ለውጥና ዕድገት ማስመዝገብ የግድ ብቻ ሳይሆን ህልውናዊ ነው።

ብልጽግና ሁለንተናዊና ከፍ ያለ ርዕይ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ከታች የሚጀምሩ ሀገራት ድህነትን መቀነስ ወይም ማጥፋት ከሚል ርዕይ ተሻግረው፣ ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚል ዕቅድ ያስፈልጋቸዋል። ለመሆኑ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት የብልጽግናን ግብ በአጭር ጊዜ ማሳካት ይቻላቸዋልን? ከተቻለስ እንዴት? ብልጽግና እንደ ርዕይ፣ መደመርን እንደ መንገድ

| ስንበይን ብዙዎች የሚያነሡት ጥያቄ ይህ ነው።

የመደመር ዕሳቤ ሃልዮታዊ መሠረት የሥርዓት ንድፈ ሐሳብ ነው። የዚህ ንድፈ ሐሳብ ዋነኛ መርሕ የአንድ ሥርዓት ተዋንያን ለጋራ ዓላማ በትብብርና በቅንጅት መሥራት እመርታዊ ለውጥን እንደሚያስመዘግብ ያስረዳል። እንደ ኢትዮጵያ ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓታዊ ችግር ያለባቸው ሀገራት ማድረግ የሚችሉት አንድ ብልሐት፤ ትንንሽ መናበቦችንና የጋራ ዓላማ ያላቸው የተባበሩ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ሲሆን፤ ይሄም ባልተጠበቀ ሁኔታ ትልልቅ ባሕርያዊና የአዝማሚያ መቀየሮችን ይፈጥርላቸዋል፤እመርታዊ ለውጦችንም እንዲያስመዘግቡ ያደርጋቸዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓለም የኢኮኖሚና ፖለቲካ ጨዋታ ውስጥ ጠንካራ ተወዳዳሪ ሆና መውጣት አለባት የሚል መሻትና ቆራጥነት አለን። ይሄንን ለማሳካት ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ መንገዷ በፈጠራ የታጀበ መንገድ ሊሆን ይገባል። ጥረታችን ከፍተኛ ሁለንተናዊ ሽግግርን ለማምጣት ነው። ለዚህ ደግሞ በእያንዳንዱ ዘርፍ የምናመጣው የችግር መፍትሔ እንደየአስፈላጊነቱ የተለያዩ ፈጠራዎች የታከሉበት መሆን ግዴታው ነው። አዳዲስ መፍትሔዎችን መተለም፣ ያሉንን በተለየ ሁኔታ ለማሻሻል መሞከር፣ ያልተለመዱ አካሄዶችን ለመተግበር ፈቃደኛ መሆን ይኖርብናል።

በሌላ በኩል ለእያንዳንዱ ችግራችን አዳዲስ አሠራሮችን ብንቀይስም፣ ጉዟችን ፍጥነት ከሌለው፣ በዚህ ፈጣን የዲጂታል ዘመን ዋጋ የለውም። በመሆኑም ለእመርታዊ ዕድገት መሳካት ሁለተኛው አስፈላጊ ጉዳይ ፍጥነት ነው።

የዓለም የፈጠራ ፍጥነት እጅግ ከፍተኛ ሆኗል። ጥንት በክፍለ ዘመናት የሚለወጡ ነገሮ፡ ዛሬ በቀናት ይቀየራሉ። በመሆኑም ከእኛ ሁኔታ ጋር የሚስማሙ የፈጠራ መፍትሔም ማምጣት ይገባናል። ማምጣት ብቻም ሳይሆን በፍጥነት በሀገር ደረጃ መተግበር አለባቸው ይሄም በአንድ በኩል ወደ ሌሎች የመፍትሔ ፈጠራዎች ለመሸጋገር ዕድል ይሰጠናል። በሌላ በኩል ደግሞ በፍጥነት በመተግበር የሀብት አጠቃቀማችንን ውጤታማነት ለማሳደግና ለሌሎች ፈጠራዎች ወረት ለማካበት ያስችለናል።

CS CamScanner

ሦስተኛው ወሳኝ ጉዳይ ደግሞ በተለመደው መንገድ በፈጠራና በፍጥነት መጓዝ ብቻ ሳይሆን የእርፍጅ ትሩፋትን መጠቀም አለብን የሚለው ነው። ለዚህ ደግሞ የዝላይ ስትራቴጂን መከተል በመኪና የሄደውን በሮኬት ተተኩሶ ለመብለጥ ያስችለናል። ያደጉት ሀገራት በዕድገት ታሪካቸው ያለፉባቸውን መንገዶች ሁሉ መከተል አይገባንም። እንደ አስፈላጊነቱ መዘለል ያለባቸውን ደረጃዎች መዝለል እንችላለን። በቀድሞ ዘመን ሰዎች መጀመሪያ የገመድ ስልክ ነበራቸው። ከዚያ በኋላ ተንቀሳቃሽ ስልኮች መጡ። የዛሬው ትውልድ ከተንቀሳቃሽ ስልክ ይጀምራል እንጂ ከባለ ገመድ ስልክ አይነሣም።

እኛም ዛሬ ዓለም ከደረሰበት ደረጃ መጀመር በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ ሆነን ለመውጣት አማራጭ የማይገኝለት መንገድ ነው። ዓለም ወደ ተሻለ ተሻግሮ የጣለውንም ሆነ በመጣል ሂደት ላይ የሚገኙ ቴክኖሎጂዎችን እንደ አማራጭ እያዩ መቀጠል፤ የቢቸግር መፍትሔ እንጂ ተወዳዳሪ አያደርገንም።

በአጠቃላይ በዓለም ተወዳዳሪ ሆነን ለመገኘት ልንከተለው የሚገባው መንገድ “ፈጠራና ፍጥነት” ነው። ፈጠራ ያለ ፍጥነት መሻሻል እንጂ መላቅ አያመጣም። ፍጥነት ያለ ፈጠራ ነካ ነካ እንጂ ጥራት አያመጣም። ጉዟችን በከፍተኛ ፈጠራ መታጀብ ይገባዋል። የፈጠራ ውጤቶቹንም በፍጥነት ወደ ሥራ የሚያስገባ መሆን አለበት። እንደየአስፈላጊነቱም በመሐል ላይ ያሉ ደረጃዎችን በዝላይ ማለፍ አለብን።

## 3.1. መደመራዊ የፈጠራ መንገድ

የሰው ልጆች ከነበሩበት የዕድገትና የሥልጣኔ ደረጃ ወደላቀው እንዲሸጋገሩ ያደረጋቸው ለሥልጣኔዎቹ መነሻ የሰው ልጆችን ሕይወት በእጅጉ የቀየሩ ፈጠራዎች የተጀመሩባቸው ፈጠራ ነው። ቀዳሚ የሰው ልጆች ሥልጣኔ የበቀሉባቸውን ቦታዎች ብንመለከት ቀደምት ቦታዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። በቀድመ ታሪክ ዘመን የሰውን ልጅ ሕይወት ከለወጡት ፈጠራዎች ግንባር ቀደሙ ድንጋይን የመጠቀም ቴክኖሎጂ ነው። ከዚያ በሪት እንጨትን፣ አጥንትንና ሌሎችን ለመጠቀም ሞክሮ ነበር።

የድንጋይ ቴክኖሎጂ ቀዳሚ ነው የሚያስብለው ጥንታዊው ሰው ድንጋይን መርጦ፣ ለተወሰነ አገልግሎት እንዲውል በማሰብ፣ ቅርጽ ሰጥቶ መጠቀም የጀመረበት በመሆኑ ነው። በዚህ ቴክኖሎጂ ሂደት የመምረጥ፣ የማስተካከልና የተወሰነ ቅርጽ የመስጠት ሥራ ተሠርቷል። በኋላም ከስለት ድንጋዮች ራስን ለመጠበቅ አንዱን ጫፍ በቆዳ መጠቅለል ወይም እንጨት ማስገባት ተጀመረ። ይሄም ለጦር መሣሪያ ዕድገት መሠረት ጣለ።

ሌላው ለሌሎችም መሠረት የጣለው ትልቁ ፈጠራ ኃይልን የመለየትና የመጠቀም ፈጠራ ነው። ይሄም እሳትን መፍጠርና መጠቀም፣ ብሎም እሳትን ለማቆየት የሚያስችለው ፈጠራ መገኘት ነው። የእሳት መገኘት የእጅ መሣሪያዎች እንዲፈበረኩ መንገድ ጠርጓል። ብረትና ሌሎች ማዕድናትን ለማውጣት፣ ለማቅለጥ፣ ቅርጽ ለመስጠት ዕድል ሰጥቷል። ያም የሰውን ልጅ የግብርና ሥራ ምግብን ከመልቀም ምግብን በሰፊው ወደ ማምረት አሸጋግሮታል።

የድንጋይና የብረት ቴክኖሎጂዎች መቀናጀት የሰው ልጅን የግንባታ ጥበብ ፈጠሩት። በጭቃ፣ በሣር፣ በእንጨትና በድንጋይ ክምር ብቻ ይሠራ የነበረውን ግንባታ ወደ ተጠረበ ድንጋይ፣ እርስ በርሱ በአንዳች ነገር ወደሚገናኝ ግንባታ፣ የሥነ ሕንጻ ንድፍ ወዳላቸው ታላላቅ ሕንጻዎች አሳደገው። በቤተ እምነቶች፣ በመቃብሮችና በአብያተ መንግሥታት የተጀመረው የግንባታ ጥበብ፣ ቀስ በቀስ ወደ መደበኛው ሕዝብ ወረደ። ይሄም ለከተሞች መስፋፋት በር ከፈተ።

አሁንም ቢሆን በዕድገትና በሥልጣኔ ከፊት ቀድመው የምናገኛቸው ሀገራት መፍጠር፣ ፈጠራን ማላመድና መጠቀም የቻሉ ሀገራት ናቸው። በመሆኑም ከድህነት መውጫውና ከኋላ ቀርነት መላቀቂያው ዋነኛ መሣሪያ ፈጠራ ነው።

እያንዳንዱ የኢንዱስትሪ አብዮት ለመከሠት የተለያዩ አስቻይ ምክንያቶች ቢኖሩም፣ የፈጠራ ድርሻ ግን አይተኬና የጎላ ነው። በግዙፍ ኩባንያዎችም ሆነ በአደጉት ሀገራት መካከል የሚደረገው ውድድር፣ በዋናነት በየዘርፉ ያለ የፈጠራ ውድድር ነው። የልዩ ፈጠራ ባለቤት ከመሆን የልዩ ኢኮኖሚ ባለቤት እስከመሆን ድረስ ፈጠራና ዕድገት በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው"።

CS CamScanner

ምርታማነትን ለማረጋገጥና ሀብት ለመፍጠር የሚመረተውን ምርትና የሚመረትበት መንገድ መለወጥ ያስፈልጋል። ፈጠራ የተወሳሰቡ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችልና አዲ ውጤትን የሚፈጥር አዲስ ምልከታና አካሄድ ነው። በሀገር ደረጃ ስናየው ደግሞ ፈጠራ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታን በማሻሻል፣ ሁለንተናዊ የጋራ ብልጽግና ለማረጋገጥ፣ ለሚያጋጥሙ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠትና የሕዝብ አገልግሎቶች ለማቀላጠፍ አዳዲስ ሐሳቦችን የማፍለቅና የመተግበር ዐቅምን የሚያካትት ነው።

ፈጠራ ዕድሎችን በመለየትና አዳዲስ ጽንሰ ሐሳቦችን በማመንጨት ይጀምራል። እነዚህ ሐሳቦች በመገምገም በተሻለ መልኩ ማዳበርና ወደ ተጨባጭ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች መቀየር ሁለተኛው ምዕራፍ ነው። ፈጠራውን ወደ ሥራ ማስገባት፣ ማስፋትና ፈጠራው ለብዙ ተጠቃሚ እንዲደርስ ማሠራጨት ደግሞ ቀጣዩ ሂደት ነው።

በጥቅሉ አዳዲስ ሐሳቦችን የማፍለቅና በተለየ መንገድ የማሰብ ችሎታ፣ ሐሳቦችን ወ እውነታ የመቀየር ሂደትና ብቃት፣ አዳዲስ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን ወደ ገበያ ማምጣት፣ እንዲሁም ሌሎች የፈጠራ ሥራዎችን በማኅበረሰብ ውስጥ እንዲስፋፉ ወይም እንዲሠርጹ ማድረግ መገለጫዎቹ ናቸው። ፈጠራ ችግሮቻችንን ለመፍታት የተሻለውን መንገድ የሚፈጥር፣ እንዲሁም ዐቅሞቻችንን በመገንዘብና በመረዳት ከፍ ያለ ውጤት በሚያመጡበት መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል ነው። ይሄም ከፍተኛ መሻሻልንና ልዩነትን በመፍጠር ባጠረ ጊዜ ውስጥ የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስና ተወዳዳሪ ሆነን ለመቅረብ ያስችለናል።

ፈጠራ የተለያዩ መልኮች አሉት። አንዳንዶቹ ፈጠራዎች አዳዲስ ምርቶችንና አገልግሎቶችን መፍጠር ወይም ማሻሻል ናቸው። በብዙዎቻችን ዘንድ ፈጠራ ስንል ወደ ምናባችን የሚመጣው ይህ ዓይነቱ ፈጠራ ነው። ዓለምን አሁን የምናየውን መልክ የሰጣት የምርት ፈጠራ ነው። በየኢንዱስትሪ አብዮቶቹ የተገኙ የተለያዩ መሠረታዊ ፈጠራዎችና እነዚያ ተንተርሰው የሚሠሩ ማሻሻያዎች በዚህ የሚመደቡ ናቸው። ተጽዕኗቸውም እጅግ ከፍተኛ ነው።

ዛሬ ከአንዱ የዓለም ጫፍ ወደ ሌላኛው ለመጓዝ ከአንድና ከሁለት ቀናት በላይ አይፈጅም። ከአውሮፕላን መምጣት በፊት ይህ አይታሰብም ነበር። የበይነ መረብ ፈጠራ ደግሞ ዓለምን በእጅጉ አስተሣሥሯል።

ሌላኛው የፈጠራ ዓይነት የሂደትና የአደረጃጀት(Process and Organization) ፈጠራ ነው። አንድን ሥራ የምንሠራበትን የአሠራር ሂደት ወደ ተሻለ አሠራር በመቀየር የሚገለጽ የፈጠራ ነው። በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ከሆኑት መካከል የሄነሪ ፎርድ የብዛት አመራረት ዘዴ አንዱ ነው።

የሥራ ሞዴል(Business Model) ፈጠራ ደግሞ ሌላኛው የፈጠራ ዓይነት ነው። ከዚህ ኔትፍሊክስ ነው። ፊልምን ከሲዲና ከዲቪዲ አውጥቶ በክላውድ ላይ በማጋራት የፊልም አኳያ እንደ ጥሩ ምሳሌ የሚጠቀሰው የፊልም ኢንዱስትሪውን በአቅርቦት በኩል የቀየረው ኢንዱስትሪውን ቀይሮታል።

በፈጠራ የታጀበ መንገድ ብዙ ትሩፋቶች አሉት። የመጀመሪያው ትሩፋት ከአዳዲስ ምርቶችና አገልግሎቶች መፈጠር ጋር ተያይዞ አዳዲስ ገበያዎችንና ኢንዱስትሪዎችን ማስገኘቱ ነው። የሞባይል መፈጠር የሞባይል ተጠቃሚዎችን ገበያ ፈጥሯል። ይህ ብቻ ግን አይደለም። የሞባይል ፋብሪካና ከሞባይል ጋር ተያይዘው የመጡ ምርቶችን የሚያመርቱና ወደ ገበያ የሚያቀርቡ ብዙ የኢንዱስትሪ ተዋንያንን አስገኝቷል። ያደጉት ሀገራት በብዙ ሂደት የደረሱበትን ቴክኖሎጂ በሀገር ውስጥ በማምረት፤ ገበያንና ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፤ ሀገራችንን ጨምሮ ብዙ አዳጊ ሀገራት እየተከተሉት ያለው አካሄድ ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚታየው ሌላኛው የፈጠራ ትሩፋት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ ነው። ለፈጠራ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ የፈጠራ ውጤቶችን የሚያስተዋውቅ ማኅበረሰብ፣ ኢንቨስተሮችን መሳቡ የማይቀር ነው። በዚህም ፈጠራን የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታን በመፍጠርና የፈጠራ ዐቅምን በማሳደግ፣ ተጨማሪ ሀብትን የማንቀሳቀስ ዕድል ያስገኛል።

CS CamScanner

ሌላኛው የፈጠራ ትሩፋት ውጤታማነት ነው። ፈጠራ ውጤታማነትን በእጅጉ ያሻሽላል በጥቂት ሀብት ብዙ ምርቶችን እንድናመርትና ብዙ አገልግሎቶችን እንድንሰጥ ያስችላል በተለይም እንደኛ ብዙ ወረት ያላካበቱ ሀገራት፣ በዘመናት የተከመረን ሥራ ለማቃለል ሳይሆን ግዴታቸው ነው። ከዚሁ ጋር የተቆራኘው ሌላኛው ትሩፋት ደግሞ ተወዳዳሪነት ማሳደግ ነው። ፈጠራ ነገሮችን በተሻለ መንገድ የመሥራት ዕድል የሚሰጥ እንደመሆ ውጤታማነትን በማሳደግና አዳዲስ ዕሴቶችን በምርትና በአገልግሎቶች ላይ በመጨመር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመውጣት በእጅጉ ያግዛል። በመሆኑም መደመራዊ የፈጠራ መንገድን መከተል እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት የዕድገታቸው ቁልፍ መንገድ ነው።

አዳዲስ የሚጨመሩ ሥራዎችን ለማቀላጠፍ ውጤታማነታቸውን በፈጠራ ማገዝ ምርጫ የፈጠራን መንገድ የሚከተል ሀገር ለፈጠራ በሚሰጠው ትኩረት ይገለጣል። ግልጽ የ የፈጠራ ግብና መዳረሻ ይበይናል። በእያንዳንዱ ዘርፍ ሊኖሩ ስለሚገባቸው የፈጠራ አካሄዶች የተሟላ ስትራቴጂ ይቀርጻል። ፈጠራ እንዲበረታታ ለምርምርና ለሥርጸት አስፈላጊውን በጀት ይመድባል። የአዳዲስ ሐሳቦች ባለቤት የሆኑ ጀማሪዎችን ይደግፋል። ሥርዓት ትምህርቱ ለፈጠራ ምቹ በሆነ መንገድ እንዲቀረጽ ያደርጋል። የተለያዩ የክሂሎት ማሳደጊያ ሥልጠናዎችን ይሰጣል። ፈጠራ በትብብር ውስጥ የምታብብ እንደመሆኗ ትብብሮችን ያስፋፋል። ይሄንን ሁሉ ደግሞ በየጊዜው እየገመገመ ማስተካከያዎችን ይወስዳል።

የመደመር ዕሳቤ እንደሚያስረዳው በሀገር ደረጃ ፈጠራ እንዲዳብር በኢኮኖሚ ተዋንያን መካከል ያለው መስተጋብር፣ ትብብርና ቅንጅት ጠንካራ መሆን አለበት። ይሄም ትብብር በተለይ በመንግሥት፣ በግል ድርጅቶችና በመካነ ትምህርት መካከል የሚኖር ነው፡ ይህ የሥርዓት መስተጋብር የኢኮኖሚ መዋቅሮች፣ ፖሊሲዎችና ተቋማት እንዲሠናሠ በማድረግ፣ ዘላቂነት ያለውን ፈጠራና ልማት ለማረጋገጥ ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል።

ሀገራችን ሰፋ ሲልም አፍሪካ፣ በዓለም የፈጠራ መዝገብ ላይ ቦታ የላቸውም። አፍሪ የጥሬ ዕቃ አቅራቢ እንጂ የምርትና አገልግሎት ፈጣሪ አይደለችም። የፈጠራ ውጤቶች የሚራገፉባት እንጂ የፈጠራ ባለቤት አልሆነችም። ችግር ወደ ፈጠራ የሚመራ ቢሆን የአፍሪካ ችግር የመራት ግን ወደ ፈጠራ ሳይሆን ያደጉት ሀገራትን "እጅ ወደ ማየት" ነው ፈጠራን አለማስፋፋት ኢኮኖሚን እንደ ማነቅ ነው።

ፈጠራን ችላ ማለት፤ ውጤታማነትን፣ ተወዳዳሪነትን፣ ብሎም ኢንቨስትመንትን ማጣት ነው። አፍሪካ በፈጠራ የታጀበ የመደመር መንግሥት መንገድን መከተል ካልቻለች፣ በዓለም ተወዳዳሪ ሆና መውጣት ይቅርና የተከማቹ ችግሮቿን መፍታት አይቻላትም። ችግሮቻችንን ለማቃለል ከተለመደው አካሄድ ወጥተን፣ ያሉንን አማራጮች መተንተን አለብን። በፈጠራ የታጀቡ መፍትሔዎችን ማምጣትና በፍጥነት መተግበር ግዴታችን ነው።

### 3.2. መደመራዊ የፍጥነት መንገድ

ከኋላ ወደፊት ለመምጣት መፍጠር ብቻ ሳይሆን መፍጠንም የግድ ይላል። አትሌቶች የሚያደርጉት ይሄንኑ ነው። ወደ ሩጫው ሜዳ ሲገቡ ፍጥነትንና ፈጠራን ይዘው ነው። ትንፋሽ እንዴት እንደሚቆጥቡ፣ እንዴት ከነፋሱ ጋር መታገል እንዳለባቸው፣ እያንዳንዱን ሜትር/ኪሎ ሜትር እንዴትና በስንት ደቂቃ መሮጥ እንዳለባቸው፣ የትኛው ርቀት ላይ አፈትልከው መውጣት እንዳለባቸው የሚወስኑት በፈጠራ ችሎታቸው ነው። ይህ ሁሉ ሆኖ ደግሞ ከሌሎቹ የተሻለ የመፍጠን ዐቅምና ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል። ፈጣን ሯጮች በፈጠራ ችግር፤ ፈጣሪ ሯጮችም በፍጥነት ችግር ሲሸነፉ አይተናል።

ኋላ የቀሩ ሀገራት ካሉባቸው ተደራራቢ ችግሮች በተጨማሪ፣ በሚፈጠሩ አዳዲስ ችግሮች እንዳይዋጡ፣ ከችግራቸው ለመውጣት የሚያስችል ፍጥነት ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ሀገራት ተጨማሪ ችግሮችን ለመቋቋም የፈጠሩት ዐቅም አነስተኛ ነው። ስለዚህ ከዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ በፍጥነት መውጣት የማይችሉ ከሆነ አደጋው የከፋ ነው።

CamScanner

እመርታዊ ለውጥ ልናመጣ የምንችለው በፈጠራ መንገድ በፍጥነት ከተጓዝን ብቻ ነው። ችግሮቻችንን ለመሻገርና ዐቅሞቻችንን በአግባቡ ለመጠቀም አዳዲስ ምልከታዎች፤ ከፍ ያለ ምናብ፤ እንዲሁም ሐሳቦችን በቶሎ ተግባራዊ የማድረግ ችሎታ ያስፈልገናል። ከዚህም በተጨማሪ አንዱን እርከን በፍጥነት ጨርሶ ወደ ቀጣዩ እርከን መሻገር ያስፈልጋል።

የተለዋዋጭነት ፍጥነቱ ከፍተኛ በሆነበት ከባቢ ውስጥ፣ ዕድሎችን በፍጥነት መጠቀምና ችግሮችን መገዳደር ካልቻልን፣ ዕድሎችና ዐቅሞች በጊዜ ውስጥ ቦታ እያጡና እየመከኑ ሊሄዱ ይችላሉ። ለምሳሌ ሀገራችን ከፍተኛ የወጣትና የአዳጊ ልጆች ቁጥር አላት። ይሄንን የሕዝብ ቁጥር በአግባቡ መጠቀም ከቻለች፣ ከፍተኛ የሆነ የሥነ ሕዝብ ትሩፋትና የኢኮኖሚ በረከቶችን ይዞላት ይመጣል። ነገር ግን ይሄንን የሰው ኃይል በፍጥነት መጠቀም ካልተቻለ፣ የሚማርበትና የሚሠራበት ዕድሜ እያለፈ ይመጣና ለሀገራችን ተጨማሪ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሸክም ይሆናል። ስለዚህም ፍጥነት ማለት ዕድሎችና ዐቅሞች ሳይባክኑ በጊዜው መጠቀም ነው። በጊዜ ሂደት የተከማቸውን ሥራ ማቃለል ብቻ ሳይሆን በእጃችን ላይ ያሉ ዕድሎችና ዐቅሞች እንዳይባክኑ ማድረግ ነው። ብሎም ወደ ተጨማሪ ችግርነት እንዳይለወጡ የሚያግዝ መላ መፍጠር ነው።

ፍጥነት ብዙ ነገሮችን በውስጡ ይዟል። ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣ ሥራዎችን አላስፈላ መጓተቶች ሳይገጥሟቸዉ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ በቅልጥፍና ማከናወን፣ እንዲሁ ደረጃዎችን በጠበቀና ጥራትን ማዕከል ባደረገ መልኩ መፈጸምን ያካትታል። የዚህ ሁሉ ማሠሪያ ግን የምንደርስበትን ጫፍ በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጠን ማወቅ ነው።

ፍጥነታችንን ለመጨመር በመጀመሪያ መከናወን የሚገባቸውን ሥራዎች በሚገባ መለየት ማቀድና ቅደም ተከተል ማውጣት ያስፈልጋል። በዚህ ሂደት ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ሥራዎች በደንብ መለየት አለባቸው። በአጭር ጊዜ አመርቂ ውጤቶችን በማሳካት ግባችን የምናደርገውን ጉዞ የሚያሣልጡ ተግባራት ላይ ትኩረት ማድረግ ሌላኛው አስፈላጊ ነገር ነው። እንዲሁም የተለዩትን ሥራዎች ቅደም ተከተል የመበየን ሥራ በየጊዜው እንዲከለስና እንዲሻሻል ማድረግ ወሳኝ ነው።

ፍጥነትን እውን ለማድረግ ሌሎችም አስፈላጊ ነገሮች አሉ። ቅደም ተከተልን ጠብቆ በተ ሁኔታ ዕቅድን መተግበር አንዱ ነው። ጥንቅቅ ያለ የጊዜ አጠቃቀምንና አስተዳደር ማስፈ . ደግሞ ሌላኛው ነው። ሥራዎች የሚያስፈልጋቸውን የጊዜ መጠንና የማይጣስ የማጠናቀቂ የጊዜ መሥመር ማስቀመጥ ደግሞ ፈጣን የውሳኔ ፍሰት እንዲኖር ያግዛል።

ፍጥነት የሚጨመርበት ሌላኛው መላ ደግሞ ተግባራዊ ተጣጣፊነትና ሰርክ መሻሻል ነው: ሥራዎችን በቶሎ ሊከናወኑ ወደሚችሉ አነስተኛ ተግባራት መከፋፈል ችግሮች ሳይፈጡ አስቀድሞግብረመልስ ለማግኘትያግዛል።ይሄም ሥራዎችን ከመታነቅ(deadlock) ያድና እንዲሁም ቶሎ ቶሎ ውጤቶችን ለመገምገም ዕድል ይሰጣል። ተግዳሮቶችን ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን፣ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ቀድሞ ለማከናወንና ፈጠራ የታከለባቸው አካሄዶችን ለመከተል ያግዛል። ለዚህም የጠራ የግንኙነት፣ የክትትል፣ የድጋፍና የግምገ መሥመር ማበጀት ሥራን በጥሩ ሁኔታ በማሣለጥ ፍጥነትን ይጨምራል።

ሥራዎች በተለያዩ ደረጃ ያሉ ኃላፊዎችን ውሳኔዎች በመጠበቅ ከተስተጓጎሉ ፍጥነት ይጎተታል። ለዚህም በየደረጃው ያሉ ሠራተኞች ውሳኔዎችን እንዲወስኑ መወከል ሌላኛው በመለየት፣ ለሥራው ባለ ሙሉ ሥልጣን አድርጎ መወከል ተገቢ ነው። በዚህም ለሥራው ፍጥነት መጨመሪያ መላ ነው። ኃላፊነትን ተቀብለው ማስኬድ የሚችሉ ባለ ድርሻዎችን የባለቤትነት ስሜትን መፍጠር ይቻላል። በመሳሳት ውስጥም ቢሆን ኃላፊነት መውሰድን እንዲለማመዱ ያስችላቸዋል። ውሳኔ በመጠበቅ ለሚስተጓጎል ሥራ ጥሩ መፍትሔ፣ በየደረጃው አመራሮችን ለማፍራትም መለማመጃ ቦታ ይሆናል።

ትጋትን የተላበሰ ጠንካራ የሥራ ባህል ሌላኛው ፍጥነትን የምንጨምርበት መሣሪያ ነው። በእጃችን ያለው ሥራ ከተለምዷዊ የሥራ ባህል ወጣ ብሎ፤ የኋላውን ለማካካስ በሚያስችለን ደረጃ መንቀሳቀስን የሚጠይቅ ነው። የሥራ ሰዓትን በተለያዩ ምክንያቶች ከማቃጠል ወጥተን፤ ሰዓትን አክብሮ ሥራን በአግባቡ ከመፈጸምም ተሻግረን፤ ትርፍ ሰዓት መሥራትን ባህላችን ማድረግ ይጠበቅብናል። ከዚህም ባሻገር በመልካም ትብብርና ኅብር የሚከወን ሥራ፣ የሥራ ከባቢን ሰላም ይጠብቃል።

CS CamScanner

ከፍጥነትም ሆነ ከጥራት አንጻር ከፍተኛ ውጤት ያስገኛል። ከግል ትጋት በተጨማሪም ከሌሎች ሠራተኞች ጋር ከፉክክር ይልቅ የትብብር መንፈስ መፍጠርና ለጋራ ስኬት መጣጣር ሥራን የተሟላና ውጤታማ ያደርገዋል።

እነዚህን ፍጥነት መጨመሪያ አካሄዶች ስንከተል ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባን ጥራት እንዳይዘነጋ ነው። ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎችን በፍጥነት የማጠናቀቅ ጉዞ ጥራት ዋነኛ መለያው መሆን አለበት። ሀገር እንገነባለን እያልን በማይረባ የጥራት ደረጃ ሥራዎችን መከወን "አለባብሰው ቢያርሱ፣ በአረም ይመለሱ" ይሆናል። በቶሎ ተንዶ ወደ ድህነት በማውረድ አዙሪት ውስጥ የሚከት በሽታ ነው። በመሆኑም ግልጽ የሆነ የጥራት ደረጃ ማስቀመጥና ተሳታፊዎች በሙሉ በተገቢው መንገድ እንዲረዱት ማድረግ የመጀመሪያ ተግባር ነው። ይሁንና ወደ ተግባር ሲወረድ ደረጃን ጠብቆ መሥራት የራሱ የሆኑ ተግዳሮቶች አሉት። በመሆኑም ጥራት ተጓድሎ እንዳይገኝ በየጊዜው ማረጋገጥን ይፈልጋል።

በአጠቃላይ እመርታዊ ዕድገት ለማምጣት መፍጠርና መፍጠን ወሳኝ መላዎች ናቸው:: በዚህ ዘመን ከብልጽግና ወደ ኋላ የቀሩ ሀገራት በዕድገት ጎዳና ላይ የተሳካ ጉዞ ለማድረግ ሁለት ነገሮች ይጠብቋቸዋል። በየዘርፉ አዳዲስ ነገሮችን መፍጠርና ቀድመው የተፈጠሩ ነገሮችን ለሀገር ዐውድ እንደሚመች አድርጎ የማላመድ ፍጥነት። ይሁንና ፈጠራው በፍጥነት ወደ መሬት እየወረደና ተጽዕኖ እየፈጠረ መሄድ አለበት። ያ ካልሆነ ፈጠራው ከአምሳለ ምርትነት(Prototype) አያልፍም። በሂደትም ይከስማል። በዚህ ምክንያት ለሀገር ዕድገት ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽዖ ውኃ ይበላዋል።

በመሆኑም የተለያዩ ፈጠራዎችን እንዲከናወኑ የምንለፋውን ያህል፣ ፈጠራው በፍጥነት ወደ ተግባር ተለውጦ የሕዝብ የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ በጎ ተጽዕኖ እንዲኖረው ለማድረግ እንዲችል መፍጠን አለብን። ይህም ፈጠራው በተግባራዊ ሙከራ ተፈትኖ እየተሻሻለና እየጠራ እንዲሄድ ከማስቻሉም በላይ፣ ተጽዕኖው ሰፊና ዘላቂ እንዲሆን ዕድል ይሰጣል።

### 3.3. መደመራዊ የዝላይ መንገድ

በዓለም ገበያ ውስጥ አዳዲስ ፍላጎቶች እየተፈጠሩ ነው። ይህንን ተከትሎ የረቀቁ ቴክኖሎጂዎች በመምጣታቸው የመረጃ ኅብረተሰብ ተፈጥሯል። ይህ ደግሞ የዓለም ገበያ በአዳዲስ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች እንዲወጠር አድርጎታል። ስለሆነም በገበያው ላይ ተፈላጊ የሆኑ የዘመኑ ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ መቻል በብልጽግና ጉዟችን ላይ ፈጣን ስኬትን ያመጣልናል። በመሆኑም ግብርና፣ ኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎቻችንን በቴክኖሎጂ ከማዘመን ባሻገር በራሱም የዕድገት ምንጭ የሆነውን የዘመኑን የዕውቀት ኢኮኖሚ መቀላቀል የግድ ነው።

የሀገራት ዕድገት በአንድ ጀንበር የሚጨበጥ አይደለም። አውሮፓውያኑ አሁን ያሉበት ዕውቀትን መሠረት ያደረገ የዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ መቶ ዓመታትንና ውጣ ውረዶችን አሳልፈዋል። በመጀመሪያ በእርሻ ላይ የተመሠረተው ኢኮኖሚያቸው ቀስ በቀስ ወደ ኢንዱስትሪ አደገ። በሂደትም ወደ ዘመናዊ አገልግሎት ዘርፎችና ዕውቀት መር ኢኮኖሚ ሽግግር አደረገ። በዚሁ አንጻር ኅብረተሰቡም ከአራሽ ኅብረተሰብ ወደ ኢንዱስትሪያዊ ኅብረተሰብ ተሻገረ። ከዚያም ወደ መረጃ ኅብረተሰብ አደገ። ይህ ሂደት በውስጡ ብ ንዑስ ደረጃዎች ያሉትና ዘመናትን የፈጀ አዝጋሚ ጉዞ ነበር።

ያደጉት ሀገራትን "ዱካ የመከተል መንገድ በርግጥ በደንብ የሚታወቅ አካሄድ ነው። ግልጽና የታወቀ ፍኖት አለው። እንዲሁም አደጋውና ዕድሉ ተለይቶይታወቃል። በተግባርም የተፈተነ አሠራር ነው። ይህ አካሄድ በተገቢው ዐውድ ከተተገበረ አስተማማኝነት ቢኖረውም፣ በዚህ መንገድ አዳጊ ሀገራት ሊጓዙ የሚችሉት ርቀት የአዳጊነት ክፍታን ለመርገጥ የሚያበቃውን ያህል ብቻ ነው።

ጉዟቸው የአዳጊ ሀገራትን ተርታ ጥሰው በመውጣት ካደጉት ሀገራት ተርታ መሰለፍን አያመጣላቸውም። ምክንያቱም በዓለም ገበያ ላይ የሚወዳደሩት በተመሳሳይ ስልት የበርካታ ዓመታት ልምድ ካላቸውና በስልቱ ተጠቅመው ከበለጸጉት

CamScanner

ሀገራት ጋር ነው። ይሄም ብቻ ሳይሆን፣ አዳጊ ሀገራት የሚወዳደሩት ያደጉት ሀገራት ለራሳቸው ብዙ ምቹ ሁኔታ በፈጠሩበት ዐውድ ውስጥ ነው። እነርሱ ቀድመው የያዙትን መሣሪያ ይዞ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪና አሸናፊ ሆኖ መውጣት ያስቸግራል።

አፍሪካም ከጥሬ ዕቃ አቅራቢነት በጊዜ ሂደት ወደ አምራች ኢንዱስትሪው ለመግባት እየሞከረች ነው። ወደ ከባድ ኢንዱስትሪዎች የመሸጋገር ጅምር ሙከራዎችም አሉ። ይህ ዓይነት የደረጃ በደረጃ ጉዞ አውሮፓውያን ለዘመናት ተጉዘው እዚህ የደረሱበት መንገድ መሆኑ ይታወቃል። ይሁንና ይህ ዓይነቱ አዝጋሚ ሂደት አሁን ባለው የዓለም ሥርዓት ውስጥ በድህነት አዙሪት ውስጥ እንድትዳክርና የሌሎች ሀገራት ምርት ማራገፊያ እንድትሆን እንጂ ጠንካራ ተፎካካሪ እንድትሆን አያደርጋትም። የዘገዩ ሀገራት ይሄን መንገድ እንከተል ቢሉ፣ ምናልባትም ከእነዚያ የበለጡ ዘመናትን በድህነትና በጉስቁልና ለመቆየት በራስ ላይ መፍረድ ይሆናል።

በመሆኑም ከዕድገት የዘገዩ ሀገራት ዋና ጥያቄ፤ ይሄንን ዘመናትን የወሰደ የደረጃ በደረጃ ዕድገት፣በአጭር ጊዜ ውስጥ በአቋራጭ መቀዳጀት የሚቻለው እንዴት ነው? የሚለው ነው። በጥቂት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ ከርሃብና ከልመና ተላቅቀው ወደ ብልጽግና የገሠገሡ ሀገራት ታሪክ የሚነግረን ነገር ቢኖር፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ብልጽግና ለማምራት የሚቻልባቸው፣ ተሞክረው አዋጭ የሆኑ፤ ወይም አዳዲስ አቋራጭ የዝላይ መንገዶች መኖራቸውን ነው።

በመሆኑም ካደጉት ሀገራት ጎራ ለመቀላቀል የመደመር መንግሥት ሦስት ስልቶችን ይጠቀማል። የመፍጠርና የመፍጠን መንገዶች ሁለቱ ናቸው። ዐውዱ በሚፈቅደው ሁኔታ ደግሞ የዝላይ መንገድን መከተል ወሳኝ ነው ይላል። አንደኛው የዝላይ ስልት በተለምዶ ያሉ “ደረጃዎችን መዝለል” ነው። ወይም የዕድገት መሰላሉን ደረጃ በደረጃ ለመውጣት መሞከርን ትቶ፣ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በቀጥታ የመቀላቀል ስልት ነው።

ነገ ከነገ ወዲያ እንደርስበታለን ብለው የሚያስቡትን ወይም ደረጃዬ አይደለም ብለው የሚገምቱትን የዘመኑን ቴክኖሎጂ በቀጥታ ለመቀላቀል የሚያስችላቸውን መንገድ መወሰን ነው።

ደረጃዎችን የመዝለል አካሄድ በዋናነት ዓለም የደረሰበትን ከፍተኛ ቴክኖሎጂ በመታጠቅ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የመሆንና አሸንፎ የመውጣትን ዓላማ ያነገበ ነው። ገበያውን አስቀድመው ከተቀላቀሉ አካላት ጋር የሚኖረውን ፉክክር ለማሸነፍ አንድም እነርሱ ከያዙት መሣሪያ በእጅጉ የተሻለ መሣሪያ መታጠቅ ያስፈልጋል። እርሱም የተሻለ ውጤታማነትን ያመጣል። ሌላም ደግሞ በአዳጊ ሀገራት አነስተኛ ክፍያ የሚከፈለው በቂ ሠራተኛ እንደልብ መገኘቱ ዋና ማበረታቻ ነው።

ይህ የዝላይ ስልት ወደ ኋላ የቀሩት ሀገራት ከበለጸጉት ሀገራት ቴክኖሎጂን በመማር ከራሳቸው ጋር የማዛመድ ስልት ነው። የቻይና ኩባንያዎች በዚህ ረገድ በውጤታማነታቸው ይጠቀሳሉ። ሆኖም የውጤታቸው ምንጭ ሠርክ በመማር ብቻ ሳይሆን ቴክኖሎጂዎችን ካሸጋገሩ በኋላ የራሳቸውን ፈጠራ ይዘው በመምጣታቸው ጭምር ነው። እንዲህ ያሉ ኩባንያዎች በዓለም ገበያ ውስጥ ጠንካራ ተፎካካሪ ለመሆን ችለዋል።

በዚህ ስልት ውጤታማ ለመሆን ሁለት ወሳኝ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ዘመናዊ መሣሪያን የመግዛት ዐቅም ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቴክኖሎጂውን ለመላመድና በቀጣይም በጥገናና በድጋፍ አገልግሎቱ ሳይቋረጥ ለማስቀጠል የዕውቀት ሽግግር የማድረግ ዐቅም ነው። የበለጸጉት ሀገራት በዘመኑ ቴክኖሎጂ ረገድ ያላቸውን ልምድና ዕውቀት በምሥጢር ይጠብቃሉ። ለፈጠራ ባለቤትነት ሕጋዊ ጥበቃ ያደርጋሉ። በዚህ ሁኔታ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ብዙ ርቀት ይጓዛሉ። ይሄም የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማድረግ ትልቅ ተግዳሮት ነው። ሆኖም ተግዳሮቶቹን ተቋቁሞ ቴክኖሎጂ የመግዛት ብቻ ሳይሆን የመጠቀም ዐቅም ከተፈጠረ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር አድርጎ የበለጸጉት ሀገራት የደረሱበትን የቴክኖሎጂ ምርት ማምረት ከተቻለ፣ በዓለም ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ መሆን ይቻላል።

CamScanner

ሁለተኛው ደግሞ፡ "አዲስ መሥመር መፍጠር" የሚባለው ነው። ቴክኖሎጂ በፈቀደው መጠን ለሥራዎች የራስን አዲስ መንገድ ፈጥሮ በዕድገት የቀደሙ ሀገራት ከሚሠሩበት በተለየ መንገድ፣ በአዲስ አሠራር ሥራን ማከናወን ነው። አዲስ መሥመር የመፍጠር አካሄድ የቀደሙት መጠቀም ያልጀመሩትን ከፍተኛ ውጤታማነት ያለው አዲስ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ተወዳዳሪና አሸናፊ ሆኖ መውጣትን ያለመ አካሄድ ነው። ይህ አዲስ መንገድን የመከተል የዝላይ ስትራቴጂ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራትንና የፈጠራ ባለሞያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ የሚስብ ምቹ ሁኔታ መፍጠርን ይጠይቃል።

የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችንና የፈጠራ ባለሞያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ የሚደረግ ጥረት ትላልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን ስለሚስብ የቴክኖሎጂ ዕድገቱን ያፋጥነዋል። ይህ መነሻ ቢሆንም ዘላቂና አስተማማኝ የቴክኖሎጂ ኢንቨስትመንት እንዲኖር በሀገር ውስጥ የፈጠራ ባለሞያዎችንና ክሂሎት ያላቸውን ዜጎች ማፍራት ያስፈልጋል። ይሄኛው የዝላይ ስትራቴጂ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ሳይሆን በሰው ሀብት ላይ የተመሠረተ ነው። በመሆኑም ዘላቂነት ያለውና የሁነኛ ልማት ማረጋገጫ ነው።

አዲስ መሥመር መፍጠር የሚቻለው በአዲስ ቴክኖሎጂ ነው። ስለዚህም ከፍተኛ የምርምርና የፈጠራ ዐቅም ይጠይቃል። ከዚያም አልፎ ቴክኖሎጂውን ለማስቀጠል ከፍተኛ የዕውቀት ሽግግር ያስፈልጋል። በተጨማሪም ከፍተኛ ወጪ የሚኖረው መሆኑና ቴክኖሎጂዎቹ አዲስ መሆናቸውን ተከትሎ የገበያም ሆነ የምርት ሁኔታው በቀላሉ አይተነበይም። ይህም በባለ ሀብቶች ዘንድ ሥጋት ይፈጥራል። ነገሩ አስተውሎትንና ድፍረትን ቢጠይቅም፣ በአጭር ጊዜ ብዙ ገንዘብ ቢያስወጣም የረጅም ጊዜ ትልቅ ስኬትን የሚያቀዳጅ ፈታኝ የዝላይ ስልት ያደርገዋል።

ተሳክቶ አዲስ መሥመር ለዓለም ማስተዋወቅ ከተቻለ ዋናውን ገበያ በቁጥጥር ሥር የማዋል ትሩፋትን ያጎናጽፋል። ይህ ደግሞ በራሱ ከቀደሙት ሀገራት የተሻለ ርምጃ ለመራመድ ዕድል ይሰጣል። ምክንያቱም የበለጸጉ ሀገራት ኩባንያዎች ሙዓለ ንዋያቸውን በሌሎች ቀደም ባሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ ስላፈሰሱ በቀላሉ ሙዓለ ንዋያቸውን አፍርሰው ወደ አዲሱ ዘርፍ ለመቀላቀል ድፍረትና ጊዜ ያጥራቸዋል።

ስለዚህ ጠንካራ ተወዳዳሪ የመሆን ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው። በአንጻሩ የዘገዩ ሀገራት ጀማሪ ኩባንያዎች በቀላሉ አዲሱን ቴክኖሎጂ በመቀላቀል ሙዓለ ንዋያቸውን ማፍሰስ የሚችሉበት ዕድል አላቸው።

ይሄንን የዝላይ ስትራቴጂ ዋነኛ ፈተና አልፈው የዘገዩ ሀገራት ባለሀብቶች በእዚህ ዘርፍ ውስጥ በድፍረትና በአስተውሎት እንዲሳተፉ ለማድረግ ሥራይፈልጋል። ሀገረ መንግሥታት የባለ ሀብቶቹን ሥጋት የሚጋሩበትና ባለ ሀብቶቹን የሚያበረታቱበት ሁኔታ መፍጠር አለባቸው። ባለሀብቶችን ካልተፈለገ ኪሣራና አደጋ ለመጠበቅ የሚያስችል የተላሚነት ያስፈልጋል። ቀድሞ መንገድ የመጥረግ ስልት፣ የጥናትና ምርምር ሥራዎች፣ ማበረታቻዎ እንዲሁም አስፈላጊ የኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ሀገረ መንግሥታቱ በእዚህ ዘርፍ ለግሉ ዘርፍ አርአያ መሆን የሚያስችላቸው የቢዝለ ፈጠራ ውስጥ መግባት ይገባቸዋል።

የዘገዩ ሀገራት ባለ ሀብቶች፣ የበለጸጉ ሀገራትን ትላልቅ ኩባንያዎች ጉልበት ተቋቁመው ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን የሀገረ መንግሥታቱን ድጋፍና ጉልበት ይሻሉ። የትላልቆቹን ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ጉልበት ለመቋቋም የተሻለ ዕድልና ዐቅም ያላቸው ሀገረ መንግሥታቱ ናቸው። ስለሆነም የግል ባለሀብቱን እንደ ታናሽ ወንድም እየተከባከቡ የማሳደግና መንገድ የመጥረግ ሚናን ለመወጣት ሀገረ መንግሥታቱ ከግል ባለሀብቱ ጋር መሳ ለመሳ የሚሠሩበት አቅጣጫን መከተል አስፈላጊ ነው።

በአጠቃላይ የዝላይ ስልት በአንድ በኩል በሁሉም የኢኮኖሚ ዕድገት ጉዟችን ውስጥ ልናካትተው የምንችለው ስልት ነው። ከምርትና ከአገልግሎት ጋር ተያይዞ የምናመርተውን ምርትና የአመራረት ዘዴን ደረጃ በደረጃ ማሻሻልን አይጠይቅም።

CamScanner

ከዚያ ይልቅ ጉልሕ ልዩነት የሚያመጡ የፈጠራ ሐሳቦችን በመተግበር ተስፈንጥረን ከፍተኛ ምርት የምናመርትበትን መንገድ መተለም ይኖርብናል፡፡

አገልግሎት አሰጣጣችንም በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች የተደገፈና ለዜጎች ውጤታማነት አስቻይ ሚናን የሚጫወት መሆን አለበት። እንዲሁም የደንበኛ ርካታን የሚያጎናጽፍና ከጥራትም ሆነ ከውጤታማነት አንጻር አሁን ካለበት በከፍተኛ ደረጃ የዘለለ አገልግሎት መሆን ይኖርበታል። በየዘርፉ ያሉ የኢኮኖሚ ጥረቶችና ሂደቶች የደረጃ በደረጃ ዕድገት መሻሻሎችን መከተል የለባቸውም። የዝላይ ትሩፋቶችን የሚጠቀሙ እንጂ።

በሌላ በኩል ደግሞ የዝላይ ስልት ከኢኮኖሚውም ባለፈ በፖለቲካውና በማኅበራዊ ሥራዎች ውስጥም ጥቅም ላይ ከዋለ ከፍተኛ ለውጥን ያመጣል፡፡ አውሮፓውያኑ በፖለቲካ ታሪካቸው አሁን ያሉበትን የተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት ብዙ ዓመታትን፣ ብዙ ደም አፋሳሽ ሂደቶችን፣ ብዙ ውጣ ውረዶችን አሳልፈዋል። የዘገዩ ሀገራት በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት የሚገጥማቸው ዋና ፈተናም አውሮፓውያኑ ለዘመናት ያለፉባቸውን ውጣ ውረዶች ማለፍ ሳይጠበቅባቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት የተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መገንባት ይችላሉ የሚለው ጉዳይ ነው።

ዓለም አሁን ካለበት ነባራዊ ሁኔታ የአውሮፓውያኑን የዘመናት የደረጃ በደረጃ ጉዞ ተከትሎ የተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመፍጠር ከሞከረ፣ በርካታ ዓመታትን ይወስድበታል። በመካከልም የሀገር ህልውናን አደጋ ላይ ይጥላል። ስለዚህም በአጭር ጊዜ ውስጥ የተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት የፖለቲካ የዝላይ ስትራቴጅ ያስፈልጋል። በተለያዩ የዝላይ ስትራቴጂዎች በመጠቀም በጥቂት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የገነቡና ያጸኑ ሀገራት ተሞክሮ እንደሚነግረን፣ ዴሞክራሲን ለመገንባት እንደ አውሮፓውያኑ የግድ በመቶ የሚቆጠሩ ዓመታትን ማሳለፍ አያስፈልግም።

ዴሞክራሲያዊ ሀገርን በፍጥነት ለመገንባት ምቹ ሁኔታን ከሚፈጥሩ ወሳኝ ነገሮች ዋነኞቹ ጠንካራ ቁርጠኛ አመራርና የነቁ የሲቪል ማኅበራት ናቸው፡፡ አንዱ ሌላውን እያጠናከረ ሀገር በተሳካ ሁኔታ ወደ ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ሞዴል እንድትሸጋገር ያግዛሉ፡ ለዴሞክራሲያዊት ሀገር ግንባታ የጠራ ርዕይና አቅጣጫ በማስቀመጥ፤ ዜጎች በፖለቲካው ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ የሚያበረታታ ጠንካራ አመራር ወሳኝ ነው።

ታማኝነትንና ተጠያቂነትን የሚያሳዩ መሪዎች መተማመንን በመገንባት፣ ዴሞክራሲያዊ ሕጋዊነት እንዲሰፍን ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። አስፈላጊ የሆኑ የሕግና ተቋማዊ ማሕቀፎችን በመዘርጋት፣ እኩልነትን ለማጎልበትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ይተጋሉ። በአጠቃላይም ለለውጥ ሂደት ቅድሚያ የሚሰጡ ጠንካራ አመራሮች፣ ዴሞክራሲያዊ ዕሴቶች የሚጎለብቱበትን ሁኔታ የመፍጠር ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡

ዴሞክራሲ በመንግሥት አካላት ብቻ የሚሠራ ሥራ አይደለም። የማኅበረሰቡን የነቃ ተሳትፎ አብዝቶ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፡፡ ንቁ ማኅበራት ዴሞክራሲያዊ ዕሴቶችን ያስተዋውቃሉ፡፡ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የመንግሥትን ተግባራት ይከታተላሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም መንግሥታዊ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ወሳኝ የማመሳከሪያነት (Crosscheking) ሚናን ይጫወታሉ። መንግሥት ብቻውን ሊጓዝ የሚችለውን የዴሞክራሲ ማሻሻያ መንገድ፣ በንቁ ማኅበራት ሲደገፍ፣ ከመሻሻል ባለፈ የዘለለ ዴሞክራሲያዊ ምኅዳር ባለቤት የሆነች ሀገር ለመገንባት ይቻላል፡፡

በዘመኑ ያሉ ቴክኖሎጂዎችንና የምርምር ውጤቶችን በፖለቲካውና በማኅበራዊው ዘርፍ ከዘመኑ የረቀቁ ቴክኖሎጂዎች አንዱና ዋናው የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነው:: በሚገባ በመተግበር፣ ካደጉት ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ መታገል ያስፈልጋል። ለምሳለ ዘርፎች የሚፈልጉትን ፍጥነት ለማምጣት ያስችላል። ካሉበት ዘልለው ከአደጉት ሀገራት ይህ ቴክኖሎጂ ኢኮኖሚያዊ ከሆኑ ጉዳዮች ባለፈ፣ የዘገዩ ሀገራት በፖለቲካና በማኅበራዊ ተርታ ለመሰለፍም ከምንም በላይ ጥቅም ላይ መዋል ይችላል። መልካም አስተዳደር ለማስፈን ይረዳል። ብቁና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ያገለግላል። ግልጽነትን

CamScanner

ተጠያቂነትን ለማስፈን እጅግ ጠቃሚ ቴክኖሎጂ ነው። በዚህ ቴክኖሎጂ ምክንያ ለዓመታት የተዝረከረኩ ሥራዎች በቀናት ይሸከፋሉ። ወራት የሚፈጁ ሥራዎች ደቂቃዎች ብቻ ይወስዳሉ።

በዚህ ቴክኖሎጂ ዘርፍ ብቁና በቂ የሰው ኃይል ለመፍጠር ባለመቻላችን በፖለቲካ በኢኮኖሚ፣ እንዲሁም በማኅበራዊ ክዋኔዎቻችን ላይ መዘግየትና የጥራት ችግር እንዲገጥሙ አድርጓል። ስለሆነም አቋራጭ የፍጥነት መንገድን ለመፍጠር የዝላይ ስልትን መከተ ያስፈልጋል ስንል በአንድ በኩል በቀጥታ በቴክኖሎጂው ላይ የምናደርገውን ኢኮኖሚያዊ ኢንቨስትመንት ይመለከታል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዘርፉ የምናደርገው ዕድገት ሌሎች ዘርፎቻችንን በማሻሻል እንዲሁም የአስተዳደር ሥርዓታችንን በመቀየር ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። ዘርፉን በማልማት ከምናገኘው ገቢ ባሻገር ዘርፉ ሌሎች ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎቻችንን በእጅጉ ቀልጣፋና ውጤታማ ያደርጋቸዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዘላቂ ልማትንና በቀላሉ በፈተናዎች የማይናወጥ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ለዘመኑ የማይመጥነውን የደረጃ በደረጃ ዕድገት ስትራቴጂን ለመከተል አልመረጠችም፡ ከዚያ ይልቅ በቴክኖሎጂ ላይ ያተኮረና በብዝኃ ዘርፍ የልማት ዕሳቤ ላይ የተመሠረተ የዝላይ ስትራቴጂን መከተል አስፈልጓታል። የዝላይ ስትራቴጂ በተወሰኑ ዘርፎች ብቻ ሳይሆ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካውና በማኅበራዊ ዘርፎች ሁሉ ልንከተለው የሚገባ የዕድገት ስልትና መርሕ ነው። በአጠቃላይ ዕድገታችንን ከዚህ ስልት ተጠቃሚና በመርfክ የሚመራ አድርጎ መቅረጽ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያውያን ሦስት ችግሮች ከፊታችን አሉ። እነዚህን የሚፈታ ስልት ያስፈልገናል የመጀመሪያው ለዘመናት ሲንከባለል የመጣው ችግር ነው። ሁለተኛው ያለንበት ዘመን የፈጠረው ችግር ነው። ሦስተኛው ደግሞ ወደፊት የምንጋፈጠውችግር ነው። የሚያስፈልገን | ከእነዚህ ተደጋጋፊ ችግሮች የምንወጣበትን ብቻ አይደለም። ነገ ከዓለም ተወዳዳሪ የምንሆንበትን ዐቅም ለመገንባት የሚያዋጣን ስልት ጭምር እንጂ። ከተደራራቢ ችግሮች መውጣትና ከዓለም ተወዳዳሪ መሆን የህልውና ጉዳይ ከሆነበት ዘመን ላይ ደርሰናል።

መፍጠር፣ መፍጠንና መዝለል ችግሮቻችንን ለመጋፈጥና ለመፍታት ወሳኝ መንገዶች ናቸው። በየዘርፉ ብዙ ፈጠራዎችን በማፍራት እነዚህን የፈጠራ ውጤቶች ደግሞ በፍጥነት ወደ ሥራ ማስገባት አለብን። እንደአስፈላጊነቱ ደግሞ የዝላይ ስልቶችን በመከተል የሀገራችንን ብልጽግና ማረጋገጥ የዚህ ትውልድ ዋናው የቤት ሥራ ነው። በመሆኑም የምንከተለው መንግሥታዊ ሥርዓትና መዋቅር ለፈጠራ ምቹ የሆነ ከባቢን መገንባት የሚያስትል መሆን አለበት። ሥራዎችን በፍጥነት የሚከውንና የዝላይ አጋጣሚዎችን የሚፈጥር፤ ሲገኙም የሚጠቀም መሆንም ይገባዋል።

CS CamScanner

# ምዕራፍ አራት

## 4. ሥርዓታዊ ፍጥነት

በዘመናዊ ማኅበረሰብ ፖለቲካና ኢኮኖሚ የሚለያዩ ጉዳዮች አይደሉም። አንዱ በሌላው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው እንጂ። አንዱን ከሌላው ነጣጥሎ ማየት እስከማይቻል ድረስ የተሣሠሩ ናቸው። ፖለቲካን ከኢኮኖሚ ነጥሎ ወይም ኢኮኖሚን ከፖለቲካ ነጥሎ የሚሰጥ መፍትሔ፤ የማኅበረሰቡን የብልጽግናም ይሁን የፍትሕ ጥያቄ በምሉዕነት ሊመልስ አይችልም። ምክንያቱም ሁለቱም የአንዱ ማኅበረሰብ ጉዳዮች ናቸው። ሁለቱም ኅብረተሰቡ ለተሻለ ኑሮ፣ ለብልጽግናውና ለፍትሕ የሚደራጅባቸው የተለያዩ አደረጃጀቶች ናቸው።

የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት መምረጥ የአንድን ሀገር ልዩ ሁኔታ በጥንቃቄ ማጤንን ይጠይቃል። እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ማጣጣምይሻል። ሀገራት ታሪካዊ ሁኔታዎችን ባህላዊ ዕሴቶችን፣ ነባራዊ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ጉዳዮችን፤ እንዲሁም ቀጣይ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግቦችን በመገምገም፤ ከልማትና ከማኅበራዊ ደኅናነት ፍላጎቶቻቸው ጋ የሚስማማ የሥርዓት ምርጫ ያደርጋሉ።

የአንድን ሀገር ታሪካዊና ባህላዊ ዳራ መረዳት፤ ተገቢውን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓትን ለመምረጥ ወሳኝ ነው። ዜጎች በአዲሱ ሥርዓት ላይ የሚኖራቸውን ተስፋና ቅቡልነት የሚወስኑትን ማኅበረሰባዊ ዕሴቶችና ወጎች ማወቅ ይገባል። እንዲሁም የቀድሞ አስተዳደራዊ ተሞክሮዎችን በሚገባ መመርመር ያስፈልጋል። አዲስ ሥርዓት መዘርጋትም ይሁን ያለውን ማስቀጠል፤ ወይም በተለየ በማዋሐድ ቀመር የሚገኝ ሌላ ሥርዓት መዘርጋት፤ የማኅበረሰቡን ታሪክ፣ ባህልና ዕሴት በሚገባ መርምሮ መነሣት ይኖርበታል።

ለሚገነባው ሥርዓት ውጤታማነት ሀገራዊ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ያሉበትን ሁኔታ በሚገባ መገምገም አስፈላጊ ነው። ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ከማስመዝገብ ወይም ማኅበራዊ የኢኮኖሚ ፍትሐዊነትን ከማረጋገጥ አንጻር ግባቸውን በግልጽ ማስቀመጥም ተገቢ ነው። ይሄም የትኛውን ሥርዓት እንደሚመርጡ ያመላክታል። ምክንያቱም አንዳንድ ሥርዓቶች ፈጠራንና ፍጥነትን ያበረታታሉ። አንዳንዶች ደግሞ በፍትሐዊነትና በአካታችነት ላይ የበለጠ ትኩረት ያደርጋሉ።

ሁለት ተመመሳሳይ የመበልጸግ ዕድል ያላቸው ሀገራት እንዴት በተለያየ የብልጽግና ደረጃ ላይ ሊገኙ ይችላሉ? እንዴትስ የተሻለ የመበልጸግ ዕድልና ዐቅም ያላቸው ሀገራት ያነሰ የመበልጸግ ዐቅምና ዕድል ካላቸው ሀገራት በታች ሊገኙ ይችላሉ? የአንድ ሀገር ዕድገት በምትመርጠው የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት ይወሰናል።

በቀዝቃዛው ጦርነት የምሥራቁ ጎራ መሪ ከነበሩት ተመሳሳይ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፍልስፍና ከሚከተሉ ሀገራት መካከል ቻይና አስደናቂ የኢኮኖሚ ለውጥን አምጥታለች። ለዚህ ሚሊዮኖችን ከድህነት ያወጣ የቻይና አስደማሚ ለውጥ መነሻው በፖለቲካ ኢኮኖሚ አካሄዳቸው ላይ የፈጠሩት ማሻሻያ ነው። የዴንግ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችን ተከትለው በመጡ የሥርዓት ለውጦች በከፍተኛ ድህነት ውስጥ የምትገኘው ሀገር፤ በአራት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ ከዓለም ቀዳሚ ኢኮኖሚዎች ተርታ ተሰልፋለች ።

በሀገራት መካከል ፈጣን፣ ፍትሐዊና ዘላቂ ልማት የማረጋገጥ ግብን በማሳካት የሚኖር ልዩነት፤ በዋናነት ከመልማት ዕድልና ዐቅም ባለፈ፤ በተዋንያን ሚናና መስተጋብር ልዩነት ምክንያት ይከሠታል። እሱም የመንገድ መረጣና የጉዞ ፍጥነት ልዩነት በመፍጠር ተቀራራቢ የመበልጸግ ዐቅምና ዕድል ያላቸው ሀገራት የተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ እንዲገኙ ሊያደርግ ይችላል።

የኢኮኖሚ ተዋንያን ሚናና መስተጋብር ምን መሆን አለበት? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ብልጽግናን ለማረጋገጥ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ጉዳዩ የተለያዩ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ክርክሮች ዋነኛ አጀንዳም ነው። እነዚህ ክርክሮች በአብዛኛው

CamScanner

ከመንግሥትና ከግል ዘርፍ የገበያ ድርሻ አንጻር የሚነሡ ናቸው። መንግሥት ብልጽግናን በማረጋገጥ ረገድ ምን ዓይነት ሚና ሊኖረው ይገባል? የሚለው ዋነኛ ማጠንጠኛቸው ነው።

በፍጥነት ከድህነት የመውጣት ግብን ለማሳካት፤ ለፍትሐዊነትና ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ ዕድገት የተሻለው መንገድ የቱ ነው? በሚለው ዙሪያ የገበያ መር ኢኮኖሚና የ ኢኮኖሚ ዋነኛ አማራጮች ሆነው ቀርበዋል። አብዛኞቹ ሀገራት ሁለቱንም ቀይጠው እንደ ዐውዳቸው አስተካክለው ሥራ ላይ ያውላሉ።

ይሁንና ከዕድገት ኋላ የቀረን ሀገራት የቱ ያዋጣናል? ከታሪካችን፣ ከባህላችንና ከሌሎች ተጨባጭ ሁኔታዎች አንጻር መታየት አለበት። ካለንበት ሁኔታና ካሉን ተደራራቢ ችግሮች እንዲሁም ልንደርስበት ከምንፈልገው የብልጽግና ደረጃ አንጻርም መፈተሽ አለበት: ከእነዚህ አንጻር በሰፊው የምናውቃቸውና በሀገራችንም በተለያየ ጊዜ የተተገበሩ መንግሥት መር፣ ገበያ መር ወይም ቅይጥ የሚሉ አማራጮች አዋጭ ናቸውን? እነዚህ ሥርዓ በምንፈልገው ደረጃ ቅንጅትን ይፈጥሩልናልን? ሙሉ ዐቅማችንንስ አውጥተን ለመሥራት ያስችሉናልን? ወይንስ ሌሎች አማራጮችን መፈለግ አለብን?

**4.1.** ገበያ መር ኢኮኖሚ - ገበያዊ ፍጥነት

ገበያ መር ኢኮኖሚ የግል ባለ ንብረትነትን ያማከለ፤ ባለ ሀብቶችና የግል ድርጅቶች ሀብትንና ንብረትን የሚቆጣጠሩበት ሥርዓት ነው። የገበያ ዋጋ በፍላጎትና አቅርቦት ሕግ ይመራል። ገበያ ለመሳብ ሲባል በሚፈጠረው ውድድር ገበያው የሸማቾችን ፍላጎት መሠረት አድርጎ ያቀርባል። በዚህም በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ሚዛኑን እየጠበቀ የሚጓዝበት የኢኮኖሚ አካሄድ ነው።

የግል ዘርፉ ዋና ዓላማ ትርፍ ማግኘት ነው። ባለ ሀብቱ ጥቅሙን እያየ፤ ሥጋቶችን እያሰላ ኢንቨስት ያደርጋል። በዚህም ፈጠራ ይበረታታል። አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎቶች ወደ ገበያው ይመጣሉ። ከሀገር ውስጥ አልፎም፤ ገበያው ለውጭ ባለ ሀብቶች ክፍት ስለሆ በዓለም አቀፍ ደረጃ የገበያ ዕድሎችንና ኢንቨስትመንቶችን ለማግኘት ያስችላል። በ መር ኢኮኖሚ ውስጥ የመንግሥት ተሳትፎ በእጅጉ አነስተኛ ነው። በዋናነት ሕጎች በማውጣትና በማስፈጸም ላይ ያተኮረ ሚና አለው።

ገበያ መር ኢኮኖሚ ከውስጥ አሠራሩ የሚመነጩ ብዙ ትሩፋቶች አሉት። ገበያው ሸማቾችንና አቅራቢዎችን በቀጥታ ያገናኛል። በአቅራቢዎች መካከል የሚኖረው ከፍተኛ ትርፍ የማግኘት ውድድር ደግሞ ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም እንዲሰፍን ያግዛል። ይህ · ቴክኖሎጂዎች እንዲጎለብቱ እንዲሁም የምርትና አገልግሎት ጥራት እንዲሻሻል ያደርጋል። ለፈጠራ በር ይከፍታል። የተለያዩ የፈጠራ ውጤቶች ወደ ገበያው ሲመጡ ደግሞ፤ ሸማቾች በሚፈልጉት ዓይነትና መጠን ለመግዛት በቂ አማራጮች ይኖሯቸዋል። በዚህም የኢንቨስትመንት መጠን ይጨምራል። የኢኮኖሚው ዕድገትም ይህንን ተንተርሶ ፈጣን ይሆናል።

በተጨማሪም በገበያ መር አካሄድ ባለ ሀብቱ አዳዲስ ነገሮችን ያስተዋውቃል። ይህንን መሠረት አድርጎም የተሻለ ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት ያደርጋል። ትጋትም ይጨምራል። በዚህም የተነሣ የገበያ መር ሥርዓት፤ ለውጥን እንደ መልካም አጋጣሚ የሚያይና በቶሎ ተላምዶ ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚችል ሥርዓት ነው።

ይሁንና ሥርዓቱ ብዙ ደካማ ጎኖችም አሉት። በተለይም ሀብት በጥቂቶች ቁጥጥር ውስጥ በመሆኑ ከፍተኛ የሀብት ድልድል መዛባትን ያስከትላል። አብዛኛውን የበይ ተመልካች ያደርጋል። ያም ለማኅበረሰባዊ አለመረጋጋቶችና ለብጥብጦች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ትርፍ የማጋበስ አመለካከት ሲሰፍን ደግሞ፣ እንደ ትምህርትና ጤና ያሉ የሕዝብ መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ በቂ ኢንቨስትመንትም ትኩረትም አይኖርም። የአካባቢ ክብካቤ ቦታ ያጣል። በዚህም ምክንያት

CS CamScanner

ከባቢ እየተበላሸና እየነተበ ይሄዳል። ሠራተኞችም ያለመጠን ጉልበታቸው ይበዘበዛል። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ተደማምረው ሥርዓቱ ተመልሶ ወደ ኪሣራ የሚያመራበትን መንገድ ይጠርጋሉ። በዚህም መነሻነት ሥርዓቱ በየጊዜው የከፍታና የውድቀት ዑደት ያስተናግዳል።

ሀገራት ከመሠረታዊ የገበያ መር ኢኮኖሚ አካሄድ በመነሣት በሥርዓቱ ላይ የየራሳቸውን ዐውድ ያገናዘበ ማስተካከያዎችን እያከሉ ተግብረዋል። ትግበራውም ሥርዓቱ የተለያዩ መልኮች እንዲኖሩት አድርጎታል። የልዩነቱ ማጠንጠኛ የመንግሥት ተሳትፎ መጠን ምን ያህል ነው? የሚለው ነው።

አንዳንዶቹ ጥቂት የመንግሥትን ተሳትፎ ብቻ ይፈቅዳሉ። በዚህም የገበያው ክንድ ከፍተኛ ይሆንና በሂደት ውድድሩ ቀርቶ ወደ ብቸኛ ሠሪ ፈጣሪነት (Monopoly) ያመራሉ ፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት በተሻለ ሁኔታ መሳተፍ አለበት የሚሉም አሉ። መንግሥ የማኅበረሰቡን ደኅናነት ለማስጠበቅ መሥራት አለበት የሚል ሐሳብ አላቸው። ለእርሶ ከግሉ ዘርፍ አስፈላጊውን ግብር መሰብሰብ አለበት። የተሰበሰበውን ግብርም ለማበረር በሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶችና ጥቅማ ጥቅሞች ላይ ማዋል ይገባዋል።

ከዚያም አለፍ ሲል ደግሞ እንደ አስፈላጊነቱ ቀጥተኛ ታሳታፊና አቅራቢ ሆኖ በገበያ መሳተፍና ሚዛን መጠበቅ አለበት ይላሉ።

ያላደጉ ሀገራት ገበያ መር የኢኮኖሚ አካሄድን ሲከተሉ፤ ሥርዓቱ ባደጉት ሀገራት የያዘው መልከ ይዞ ሊተገበር እንደማይችል ግልጽ ነው። የመጀመሪያው ምክንያት ገበያ መር አካሄድ ለመደገፍና እንዲያብብ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች መኖራቸው ነው፡ ባላደጉ ሀገራት እንደ መጓጓዣ፣ መገናኛ፣ ኃይል ያሉ መሠረተ ልማቶች ገና አልተሟሉም፡ የሕግና የመንግሥት አሠራር በበቂ ሁኔታ አይገኙም። የተለያዩ ንግዶችን ለማስጀመር የሚሆን በቂ ገንዘብ ወይም መነሻ ወረት አይኖርም። ብድር ለማግኘትም ችግር ነው:: እንዲሁም የሥርዓቱ ዋነኛ ሞተር የሆነው ብቁ የሰው ኃይል እንደ ልብ አይኖርም።

በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ሙስናና የባህል ተጽዕኖ፣ የውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንት እንዳይበረታታ ጫና ይኖራቸዋል። በእነዚህ የተነሣም ገበያ መር ኢኮኖሚ በምዕራቡ ሀገራት አሁን እየተተገበረ ባለበት አግባብ ባላደጉ ሀገራት ሊጎለብት አይችልም፡

የገበያ መር ኢኮኖሚ በዓለም ላይ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነትን አግኝቶ በተለያዩ መልኮች | ተግባር ላይ የዋለ የኢኮኖሚ አካሄድ መሆኑ አሌ አይባልም። የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በእጅጉ በመቀነስና የግል ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ እንዲጎለብት በማገዝ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በዚህም ገበያው በራሱ ሚዛኑን ጠብቆ እንዲጓዝ አስችሏል።

ይሁንና በአሁኑ ጊዜ በብዙ ባደጉ ሀገራት ጭምር ሳይቀር ላጋጠሙ ዘርፈ ብዙ ተግዳሮቶች ገበያው የሚጠበቅበትን መፍትሔ መስጠት ባለመቻሉ፤ በፖለቲካ ኢኮኖሚ አካሄዱ ከማኅበረሰቡ ጥቅም ጋር ተያይዞ የሚያስከትለው ጉዳት ከግምት እየገባ ነው። ርዕዮተ ዓለም ወገንተኝነት ምክንያት በግልጽ ባይሉትም መልሰው እየፈተሹት ይገኛሉ። ከኅረተሰብአዊነትም የተለያዩ ዕሴቶችን እየተዋሰ ነው።

በተለይም በአፍሪካና መሰል ድኻ ሀገሮች መንግሥት የማይተካ ከፍተኛ ሚና አለው። የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ያለው የዕድገት ደረጃና ዐቅምም አነስተኛ ነው። በዚህም የተነሣ ዝቅተኛ የመንግሥት ተሳትፎ ያለበትን ገበያ መር አካሄድ፣ በቀጥታ ለመተግበር አስቸጋሪ አድርጎታል።

CS CamScanner

እንደሚታወቀው በሀገራችን የግል ክፍለ ኢኮኖሚውን የማሳደግ ሥራ በጥቂቱ የተጀመረው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ነው። ከዚያው ዘመን ጀምሮ በየዘመናቱ የተለያዩ ተግዳሮቶችን አልፏል። በዚህ ውስጥም በተወሰነ መልኩ ዕድገት እያሳየና እየጎለበተ መጥቷል። ዛሬም ብዙ ተግዳሮቶችን ተቋቁመን፤ ገበያ መር አካሄድን በተወሰነ መልኩ እየተለማመድን እንገኛለን።

### 4.2. ኅብረተሰብአዊ መንግሥት - መንግሥታዊ ፍጥነት

ኅብረተሰብአዊነት ፍትሐዊ የሀብትና የንብረት ድልድልን መሠረት አድርጎ የሚነሣ ሥርዓተ መንግሥት ነው። መንግሥት ስልተ ምርቱን፣ ማምረቻውን፣ የምርት ሂደቱንና ምርቱን የሚቆጣጠርበት የኢኮኖሚ ሥርዓት ነው ማለት ይቻላል። ለሕዝቡ ማኅበራዊ ደኅናነት (Social Welfare) ቅድሚያ ይሰጣል።መሠረታዊ ነገሮች እንዲሟሉለትም ይሠራል። እንደ ትምህርት፣ ጤናና የቤት ባለቤትነት በፍትሐዊነት መዳረሱን ያረጋግጣል።

ኅብረተሰብአዊነት ከግል ጥቅም ይልቅ የማኅበረሰቡን ፍላጎት ያስቀድማል። ፍትሐዊና ሁሉን አቀፍ ኅብረተሰብ ለመገንባትም ይጥራል። ገበያ መር አካሄድ ፈጣን ዕድገትንና ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን አያረጋግጥም ብሎ ኅብረተሰብአዊነት ያምናል። ስለዚህም የኃላፊነት ስሜት የሚሰማው መንግሥት ይሄንን በማረጋገጡ ረገድ የመሪነት ሚና መጫወት ይገባዋል ይላል።

በመሆኑም መንግሥት የልማት ዕቅዶችንና ግቦችን ያስቀምጣል። እነዚህንም ለማስፈጸም ብቁ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ዐቅም ባለው ጠንካራ መንግሥት መመሥረት ላይ ያተኩራል።

ሥርዓቱ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ግቦችን ያቆራኘ ሥርዓት ነው። የመንግሥት ትልቁ ኃላፊነት ጥቂቶችን ማበልጸግ ሳይሆን በሂደትም በውጤትም የተስተካከለና ፍትሐዊ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚውን ይቆጣጠራል። ማኅበረሰብን ትኩረት ባደረገ አካሄድ፤ ማኅበራዊ ፍትሕና ዕድገት ማምጣት እንደሆነ ያምናል። በዚህም መሠረት መንግሥት በከፍተኛ የገቢ አለመመጣጠንን ለማስተካከል ይሞክራል።

በዚህም የሚገለሉና የሚቸገሩ የማኅበረሰቡ ክፍሎችን ጨምሮ፤ በአጠቃላይ በአካታች ቀርጾ በመተግበር መሠረታዊ ነገሮች መሟላታቸውን ያረጋግጣል። ድህነትን ለመቀነስና የጋ የአኗኗር ጥራት እንዲሻሻል ያስችላል ብሎ ያምናል። የተለያዩ ማኅበረሰባዊ ፕሮግራሞችን ግቦች የበለጠ ትኩረት እንዲያገኙ ይሠራል። በእነዚህም ማኅበራዊ ሕይወትንና አብሮነትን በማበረታታት፤ የኅብረተሰብአዊ ትሥሥርን በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር፤ ይበይናል።

በኅብረተሰብአዊ ሥርዓት ውስጥ መንግሥት የተማከለ አካሄድን የሚከተል መሆኑን አይተናል። በዚህም ምክንያት ውድድር በሥርዓቱ ውስጥ ቦታ የለውም። ሥራዎችም በመንግሥት ክትትልና ቁጥጥር ይተገበራሉ። ቁጥጥር በባሕርይው የግለሰቦች ተነሣሽነትን ይጎዳል። የሥራ ፈጠራ መንፈስን ያዳክማል። ፈጠራን ያቀጭጫል። እንዲሁም ዝቅተኛ ውጤታማነትን ያስከትላል።

ከዚህ በተጨማሪ በኅብረተሰብአዊነት ሥርዓት የተሻለ የምርት አፈጻጸምን የሚሸልም፣ በገበያ የሚመራ ማበረታቻዎች ስለሌሉት ዝቅተኛ ምርታማነትን ያስከትላል። ተያይዞም የኢኮኖሚ ዕድገትን በማቀጨጭ፣ የመንግሥት አገልግሎቶችን በዘላቂነት በጥራት የማስኬዱን ሥራ ፈታኝ ያደርገዋል።

ኅብረተሰብአዊነት የተለያዩ መልኮች አሉት። በአብዛኛው የልዩነቶቹ ማጠንጠኛ የመንግሥትንና የግሉ ዘርፍን ሚና ማዕከል ያደረገ ነው። በአንደኛው መልክ፤ መንግሥት | ከፍተኛውን የኢኮኖሚውንና የፖለቲካውን ኃይል ይቆጣጠራል። በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ የግሉ ባለሀብት እንዲሳተፍ ይፈቅዳል። ይህ አካሄድ ማኅበራዊ ባለቤትነት ጠብቆ ቅልጥፍናን ለማበረታታት ሲል፣ በኅብረተሰብአዊነት ማሕቀፍ ውስጥ አንዳንድ የገበያ ዘዴዎችን ያካትታል።

CamScanner

ሁለተኛው መልኩ መንግሥት የማኅበረሰቡን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር በአንዳንድ የኢኮኖሚ ጉዳዮች በቀጥታ ይሳተፋል። የኢኮኖሚውን መሪ ተዋናይነት ግን ሙሉ በሙሉ ለግል ዘርፉ ይሰጣል ። ይህ አካሄድ የገበያ ውድድርን ይጠብቃል። ፍትሐዊነትና አካታችነትን ለማጎልበት በኅብረተሰብአዊነት ማሕቀፍ ውስጥ የእኩልነትና የአብሮነት ዘዴዎችን ያካትታል።

ድኻ ሀገራት ኅብረተሰብአዊነትን በቀጥታ ለመተግበር ከሚቸገሩባቸው ምክንያቶች አንዱ የተቋማት የማስፈጸምና የማስተዳደር ዐቅም አነስተኛ መሆን ነው። ከፍተኛ የባለ ሞያዎች እጥረት፣ ሀብት በውጤታማነት ሥራ ላይ አለመዋልና ሙስና የድኻ ሀገራት መገለጫዎች ናቸው። ያደጉት ሀገራት በአብዛኛው ገበያ መር አካሄድን የሚከተሉ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ድኻ ሀገራት ኅብረተሰብአዊነትን ለመተግበር የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ፤ ብድርን ጨምሮ፤ እንዳያገኙ በተለያየ መንገድ ከፍተኛ ጫና ያደርጋሉ።

በአጠቃላይ ኅብረተሰብአዊነት ፍትሐዊነትና አካታችነትን ማዕከል አድርጎ የሚንቀሳቀስ ሥርዓት ነው። ይሁንና ጠንካራ የገበያ ሥርዓትን ያላካተተ ኅብረተሰብአዊነት የተለያዩ የውጤታማነት ችግሮችን ይፈጥራል። መንግሥት ብቻውን በገበያ ሥርዓት አማካኝነት ሊሣለጡ የሚችሉ የምርት እና የሀብት ፍትሐዊ ክፍፍልን በውጤታማነት ሊያሳካ አይችልም። ከዚህ የተነሣ እመርታዊ ዕድገት ለማምጣት የግል ዘርፉን ማሳደግ የግድ መሆኑ ታይቷል። ለዚህም ዋነኞቹ የሥርዓቱ አራማጆች ገበያ መርነትን በስፋት እያካተቱ፤ የኅብረተሰብአዊነትን መልክ ሲቀይሩት ተመልክተናል።

በሀገራችንም ለሁለት ዐሠርት ዓመታት ያህል ኅብረተሰብአዊነትን ተከትለናል። የተከተልነው ኅብረተሰብአዊነት አማራጭ የገበያ ሥርዓትን በአግባቡ ያላካተተ ነበር። ይሄም በሌሎች ሀገራት ተሞክሮ እምብዛም ውጤታማ ያልሆነ ነው። ሥርዓቱ እንደ ጦርነት ባሉ ችግሮች ተወጥሮ በልማት ላይ ማተኮር አለመቻሉ ተደምሮበት፤ ከማኅበራዊ፣ ከፖለቲካዊና ከኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች አንጻር ከዕድገት ይልቅ ውድቀት ያስተናገድንበት ወቅት ነበር ማለት ይቻላል።

### 4.3.የመደመር መንግሥት - ሥርዓታዊ ፍጥነት

የሀገራችንን ጨምሮ የብዙ ሀገራት ተሞክሮ የሚያሳየው አንድ እውነታ አለ። ግብያ ወይም ኅብረተሰብአዊነት ብቻ የሚል ጽንፍ እርባና ቢስ መሆኑን ነው። ዋነኞቹ የርዕዮተ ዓለሞቹ አቀንቃኞችም ሳይቀሩ በሃልዮታዊ ክርክሮች ከመጠመድ እየወጡ ነው። ከዚያ ይልቅ ከተግባራዊ ልምድ በመነሣት ወደ መሐል የመምጣት ሂደት ላይ መሆናቸው እየታየ ነው::

ይኸው የሀገራቱ ተሞክሮ እንደሚያሳየው፣በገበያ መር ኢኮኖሚ ውስጥ መንግሥት አነስተኛ ሚና ሳይሆን ቁልፍ ሚናን የሚጫወት ሆኗል። እንደዚሁም በመንግሥት መር ኢኮኖሚ ውስጥ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ወሳኝ ብልጽግናን የማረጋገጥ ድርሻ እየያዘ ነው። ወደ ገበይ መር ያዘነበሉ ምዕራባውያን ሀገራት በፈጠራና በፍጥነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። በሀብት ክፍፍል ፍትሐዊነት ላይ ግን በተነጻጻሪ የተወሰኑ ጥያቄዎች ይነሡባቸዋል። ወደ ኅብረተሰብአዊነት ባዘነበሉት ሀገራት ደግሞ ከአካታችነትና ከፍትሐዊነት አኳያ ጥሩ አፈጻጸም አላቸው። ከፈጠራ መጎልበትና ከፍጥነት ጋር በተያያዘ ግን ውሱንነቶች አሉባቸው።

ምዕራባውያኑ ገበያ መር ሥርዓት ያሉበትን የፍትሐዊነትና የአካታችነት ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችሉ የተለያዩ መላዎችን ከኅብረተሰብአዊነት እየተዋሱና እየተገበሩ ይገኛሉ። ሥርዓቱ ያሉትን የፈጠራና የፍጥነት ትሩፋቶች ደግሞ አጠናክረው ቀጥለዋል። በዚህም መነሻነት ዛሬ ላይ በዕድገት ማማ ላይ ከመቀመጥ አልፈው በዓለም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ለማሳረፍ ችለዋል።

ምሥራቃውያኑም ኅብረተሰብአዊ ሥርዓትን በተመለከተ ተመሳሳይ መንገድ እየተከተሉ ነው። ሥርዓቱ ያሉበትን የፍጥነትና የፈጠራ ችግሮች ለመቅረፍ ከገበያ መር አካሄድ እየተዋሱ ነው። ሥርዓቱ ያሉትን የፍትሐዊነት፣ የአካታችነትና የአብሮነት

CamScanner

ትሩፋቶች ደግሞ አጠናክረው ቀጥለዋል። በዚህ አያያዛቸውም ዛሬ ከምዕራባውያኑ ከመወዳደር አልፈው፡ ከብዙዎቹ ቀድመው ተገኝተዋል።

ፍጥነት መንግሥት ወይም የግል ባለሀብቱ በተናጠል ስለሮጡ የሚሳካ ጉዳይ አይደለም። ሁሉም በጋራ መሮጥና መፍጠን ሲችሉ የሚመጣ ውጤት ነው። ፈጠራም ረዘም ያለ ጊዜና ብዙ ጥረቶችን የሚጠይቅ ሂደት አለው። ሊረጋገጥም ሊሰፋም የሚችለው በጋራ ድምር ጥረት ነው። ዝላይ ደግሞ በሁለቱ ልዩ ጥምረትና ቅንጅት ካልሆነ በተናጠል የሚተገበር አይደለም።

መንግሥትም ሆነ የግሉ ዘርፍ የየራሳቸው ጥንካሬና ጉድለት ያላቸው እንደመሆኑ፤ የገበያ መርም ይሁን የኅብረተሰብአዊነት ሥርዓቶች በየራሳቸው ዐውድ ሌላውን አካተው መሄድ ከቻሉ ብቻ ውጤታማ ይሆናሉ። ይህ አካታችነት የሁለቱንም ትሩፋት ለማጣጣምና የአንዱን ጎዶሎ በሌላው ለመሙላት ወሳኝ ነው። ብዙ ሀገራትም ይሄንኑ የቅይጥ ኢኮኖሚ መንገድ እንደየራሳቸው ዐውድ ተከትለው፤ አመርቂ ዕድገት ማስመዝገብ ብቻም ሳይሆን፤ እንደየዝንባሌያቸውም ውጤት ማግኘት ችለዋል።

ይሁንና ይህ የቅይጥ ኢኮኖሚ አካሄድ፣ በሁለቱም ሥርዓቶች የሚገኙ ትሩፋቶችን ለማግኘት ቢያስችልም የተዋንያን የሚና መሻሻል እምብዛም አይታይበትም። በገበያ መር አካሄድ የፍጥነትና የፈጠራ ሚና ለግሉ ዘርፍ የተተወ በመሆኑ፤ ባለ ሀብቱ ከሸማቾች የሚቀርብለትን ጥያቄ ለመመለስ፣ ወይም መጪውን ጊዜ በደንብ በማጤን ያስፈልጋሉ የሚላቸውን ምርትና አገልግሎቶች ለማምረት ወይም ለማቅረብ ይተጋል። በዚህ ጥረትና ትጋት አዳዲስ ወይም የተሻሻለ ምርትና አገልግሎት በፈጠራ ታግዞ ወደ ገበያው ያመጣል የሚል ዕሳቤ አለው። ከዚህ ውጭ መንግሥት ምርትና አገልግሎቶችን በመፍጠር ቀጥተኛ ሚና ይኖረዋል ብሎ አይወስድም።

በሌላ በኩል ደግሞ ከኅብረተሰብአዊነት ሥርዓት የተገኘውን የፍትሐዊነትና የአካታችነትን ጉዳይ መንግሥት ሥርዓት ዘርግቶ ያስጠብቃል የሚል ዕሳቤ አለው። ከዚህ አልፎ ባለ ሀብቱ ይሄንን ጉዳይ በባለቤትነት ይዞ ውጤታማ ይሆናል የሚል እምነት የለውም። በርግጥ የሀገራትን ተሞክሮ ስንመለከት መንግሥትም ሆነ የግል ባለ ሀብቱ ከሚናቸው አለፍ ብለው ኃላፊነት ለመውሰድ ይሞክራሉ። ማለትም መንግሥት በፈጠራ ሂደት የተወሰነ የአስቻይነት ሚና ይኖረዋል። እንዲሁም ባለ ሀብቶች በፍትሐዊነትና በአካታችነት ዙሪያ በሕግ የተጣለባቸው የተወሰነ ኃላፊነት አለባቸው።

እንደ እኛ ድኻ በሆኑ ሀገራት ግን ነገሩ ለየት ይላል። መንግሥት በአንድ በኩል ከኋላ ቀርነት ጋር ለዘመናት ሲከማቹ በቆዩ በብዙ ችግሮች ይያዛል። በሌላ በኩል ደግሞ ተለዋዋጭ ከሆነው የዓለም ሁኔታ በሚመነጩ ተግዳሮቶች ይወጠራል። የግሉ ባለ ሀብትም ገና በሚገባ ያልዳበረና ነጥሮ ያልወጣ ነው። እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ መንግሥት ፈጠራ ፍጥነት ሥራው አይደለም ማለት አይቻልም። የግል ባለ ሀብቱም አካታችነትና ፍትሐዊ አይመለከተውም ብሎ መደምደም ከባድ ነው።

እንደኛ ብዙ የቤት ሥራ ላለበት ሀገር በትብብር ዕሳቤ የሚመራውን የመደመር መንግሥት መዘርጋት ያስፈልጋል። የመደመር መንግሥት እንደ አንድ ባለ ሀብት የሕዝብን ጥያቄ ለመመለስ ይተጋል። እንዲሁም መጪውን ጊዜ በሚገባ በማጤን የተለያዩ የፈው መፍትሔዎችን በማምጣት ይተገብራል። በዚህም የሕዝብን ጥያቄ በሚገባ ከመመለስ መጪውን ጊዜ ከመዋጀት ባለፈ፣ የግል ዘርፉን በከፍተኛ ሁኔታ ማነቃቃት ይችላል።

የመደመር መንግሥት ዕሳቤ ኢኮኖሚው እንደ ሥርዓት ነባራዊ ተግዳሮቶችን እንዴት መቋቋምና የመጪውን ዘመን ፍላጎቶች እንዴት ማሳካት ይችላል? በሚሉ ጉዳዮች የሚያውጠነጥን ነው። ለችግሮች ምላሽ በመስጠት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚ ብልጽግና ለማስመዝገብ ሁሉም የኢኮኖሚ ተዋንያን የማይተካ ሚና ያላቸው መሆኑ ዕውቅና ይሰጣል።

የመደመር መንግሥት ተናጠላዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምልከታ፤ ኢኮኖሚውን በሙሉ ዐቅም | ለማሳደግና ብልጽግናን ለማረጋገጥ እንደማያስችል ያምናል። ይልቁንም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመመለስ፣ ብሎም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት

CamScanner

ለማረጋገጥ የፈጠራና የፍጥነት አስፈላጊነት ላይ ያተኩራል። የመደመር መንግሥት ፈጠራና ፍጥነትን ለማረጋገጥ | በሚያስፈልገው ሥርዓታዊ ምላሽ ላይ ያውጠነጥናል። በአጠቃላይ ሥርዓቱ ከመደር ዕሳቤ ጋር መሳ ለመሳ ሊታይ የሚችል ነው።

በመሆኑም መንግሥት ፍጥነትን ከግል ዘርፉ ከመጠበቅ ይልቅ ከእነሱ ተምሮ ሥራዎች በከፍተኛ ፍጥነት ይከውናል። ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል። የአገልግሎ ዑደትን በሚገባ ይመረምራል። የሚያቀላጥፉ አዳዲስ ሂደቶችን ይነድፋል፤ በቴክኖሎጂ | ይደግፋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል። አገልግሎትን ወደ ተሻለ ደረጃም ያሸጋግራል።

ዛሬ ያለንን ዝቅተኛ የምርታማነት ደረጃ በማሻሻል፣ ዓለም ከደረሰበት የምርታማነት ደረጃ መድረስ አንድ ነገር ነው። ነገር ግን ከዚህም የተስተካካይነት ጥረት አልፎ መጪውን ጊዜ መቻል ጊዜው የሚጠይቀው የመንግሥት ዓይነት ነው ። ይሄን ለማሳካት መንግሥት ታሳቢ አድርጎ መንቀሳቀስ ይገባል። የዕድገት መሥመርንም በዚያው ፍኖት ለመዘርጋት አስፈላጊውን የፈጠራና የፍጥነት ጉዞ መጓዝ ይኖርበታል። ከዚህ የሚገኘው ትሩፋት ለዜጎችም ሆነ ለባለ ሀብቶች ከፍተኛ አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል።

የመደመር መንግሥት መፍጠርና መፍጠንን ገንዘቡ እንዳደረገ ሁሉ፣ ለዝላይ ስልት አስፈላጊ የሆኑ ባሕርያትን መላበስም ይኖርበታል። የዝላይ ስልትን ለመተግበር የሚያስፈልጉ ወሳኝ ነገሮች አሉ። ምርምር፣ መጪውን ጊዜ መተንበይ፣ አሠራሮችንና ውጤቶችን ማጤን እና መሰል ጥልቅ ትንተናዎችን በትጋት መሥራት ተገቢ ነው። ከዚህም ባለፈ፣ ምቹ ፖሊሲያዊ፣ አስተዳደራዊና ሌሎች የሕግ ማሕቀፎችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። እንዲሁም በግሉ ዘርፍ የሚሠሩ ስትራቴጂያዊ ዘርፎች ላይ የሚመጣ የኪሣራ ሥጋት ካለ ተገቢውን ድጋፍና አበረታች ርምጃ ለመውሰድ ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል።

የመደመር መንግሥት ፍትሐዊነትንና አካታችነትን ከማረጋገጥ ያለፈ ተግባር አለው። እንደ ባለ ሀብት ትርፍንና ኪሣራን ማስላት አለበት። የተፈጠሩ ነገሮችን በተገቢው ፍጥነት ወደ መሬት በማውረድ ሐሳቦችና ፈጠራዎች ከሐሳብነት አልፈው በተግባር የሕዝብን ችግር ወደ መፍታት መሸጋገራቸውን ማረጋገጥ አለበት። ለዚህም አንድ ባለ ሀብት ውጤታማ ለመሆን የሚጓዛቸውን የፈጠራና የፍጥነት አካሄዶች የመደመር መንግሥት ገንዘቡ ማድረግ ይኖርበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከመደመር መንግሥት ጋር የሚሠራ ባለ ሀብት እንደ ፍጥነትና ፈጠራ ሁሉ፣ ፍትሐዊነትንና አካታችነትን በሚገባ መገንዘብና መተግበር ይጠበቅበታል። የመጀሙ መንግሥት የግል ዘርፍ የምንለው ከግል ትርፍና ጥቅም የዘለለ ሐሳብና ግብር ያለው ነው ለሀገር ከፍታና ለሕዝብ ጥቅም የሚቆረቆርና የሚሠራ ነው። የባለ ሀብቱ ትርፍ በሕግ ኪሣራ የሚገኝ ከሆነ፣ ሀገር አታተርፍም። ሕዝብን በመበደል የሚመጣ ሀብት፣ መዘዙ ብዙ ነው። በወደፊቷ ኢትዮጵያም ውስጥ ዕድል ፈንታ የለውም።

በመሆኑም የምንገነባው የግል ዘርፍ በፈጠራ የተካነ፣ በፍጥነት ሥራዎችን የሚከው ፍትሐዊነትንና አካታችነትን ገንዘቡ ያደረገ የግል ዘርፍ ነው። የግሉ ዘርፍ ፈጠራንና ፍጥነት ለመንግሥት እንደሚያስተምረው ሁሉ፣ ፍትሐዊነትንና አካታችነትን ደግሞ ከመንግሥት መማር ይጠበቅበታል።

መንግሥትና የግሉ ዘርፍ ከተናጠል ሚናቸው ባለፈ በከፍተኛ ደረጃ መቀናጀትና እኳ ሌላኛውን የሚደግፍበት ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል። ይህ የማገዝና የማስቻል ትብ በሁለቱ አካላት ቅንጅት የሚፈጠር ተጨማሪ የላቀ ዕሴት ለማፍራትም ወሳኝ ነው። ለዚ ደግሞ የጋራ ግብ ከማስቀመጥ ባለፈ ግልጽ፣ አሳታፊና ተጠያቂነት የሰፈነበት አሠራር መዘርጋት ይገባል። እነዚህ ሁሉ የመደመር መንግሥት የቤት ሥራዎች ናቸው።

ሥርዓታዊ ፍጥነት የገበያ ፍጥነትንና የመንግሥት ፍጥነትን በማሻሻልና በማቀናጀት ሁለንተናዊ ፍጥነትን ማረጋገጥ ነው። በሀገራችን መንግሥት ቀርፋፋና ቅልጥፍና የሌለው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተወዳዳሪነት ይጎድለዋል። ነጻ ተቋማት ጠንካራ ቢሮክራሲ አልዳበሩም። ሥራዎች አዝጋሚ በሆነ መንገድና በተለምዶ ይከናወናሉ፡

CS CamScanner

ከውጤት ጋርም የመተሣሠር ክፍተት አለባቸው። እነዚህ ሁሉ በሀገራችን ብልጽ ላለመረጋገጡ ምክንያት ሆነው ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ከዚህ ውስጥ የአንድ ወይም የሁለት ዘርፎችን ሚና በማሻሻል ሥርዓታዊ ፍጥነት ሊሳካ አይችልም። ሁሉም ተዋንያን | ንዑስ ሥርዓቶች የየራሳቸውን ሚና እንዲወጡና እንዲሻሻሉ በመካከላቸው ቅንጅት ትብብር እንዲፈጠር ማድረግ ያስፈልጋል።

በሥርዓት ውስጥ ያሉ ተዋንያን ቁመናቸው ጤናማ ሲሆንና ሚናቸው ፈጠራና ፍጥነትን ማዕከል ያደረገ ሲሆን ብልጽግናን ለማረጋገጥ ያስችላል። ፍጥነት ሊረጋገጥ የሚችለው በሥርዓት ግንባታ ነው። እርስ በርሱ የተጣጣመና የሚግባባ፣ ሂደትን ከውጤት 2 ያስተሣሠረ ሥርዓት የመዘርጋት አጣዳፊነት ግልጽ ነው። በጥቂት የሥርዓት ክፍሎችና ተዋንያን ላይ የተንጠለጠሉ ጎዶሎ ሥርዓቶችን መሥርቶ ሀገራዊ ፍጥነትንና ቀጣይነትን ማለም አዳጋች ነው።

የምንችለውም በሥርዓት ለውጥ ነው። አሁን የሚያስፈልገን ገበያ መር፣ መንግሥት መር ከኋላ የቀረነው በሥርዓት ጉድለት መሆኑ እሙን ነው። ፈጠራና ፍጥነትን ልናረጋግጥ ወይም ቅይጥ ኢኮኖሚ ከሚለው ያለፈ ነገር ነው። መንግሥት ራሱ እንደ አንድ ባለሀብት ተወዳዳሪነትን ታጥቆ መንቀሳቀስ ያስፈልገዋል። ምቹ ሁኔታን ከመፍጠርና በተወሰኑ የግሉ ባለሀብት ሊገባባቸው በማይችሉ ሥራዎች ውስጥ ከመሳተፍ ያለፈ ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል። በፈጠራና በፍጥነት በመሥራትና በዝላይ ስትራቴጂ የተቋማቱን ቅልጥፍናና የመፈጸም ዐቅም ከመሠረቱ መለወጥ ይገባዋል። የግል ዘርፉን ዐቅም በእጅጉ ማሻሻል ለነገ የማይባል ሥራ ነው። ይህ ነው የመደመር መንግሥት ማለት።

የመደመር መንግሥት ሥርዓታዊ ፍጥነትን የሚያረጋግጥ ነው። በመደመር ዕሳቤ ላይ እንደተብራራው የመደመር መንግሥት ጠንካራ የተፈጥሮ ሥርዓት ባሕርያትን የተላበሰ ነው። እንደሚታወቀው የመደመር ዕሳቤ ከተፈጥሮ፣ ከተጨባጭ የኢትዮጵያ ዕሴትና ትውፊት እንዲሁም ከሳይንሳዊ የሥርዓታት ሃልዮቶች ዕውቀትንና ጥበብን አጣምሮ የያዘ አስተሳሰብ ነው::

ይህ የአስተሳሰብ ማሕቀፍ የሀገራችንን ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ሁኔታ ለመረዳት ሥርዓታዊ ትንተና፣ ምሉዕ ዕይታና ፈጣን ችግር ፈች ዐቅምና ስልት እንደሚያጎናጽፍ ያስረዳል። ይህ ዕሳቤና መረዳት ተፈጥሮ የመረጠቻቸውና ውጤታማ የሆኑ ስድስት የሥርዓታዊ ፍጥነት ዓምዶች አሉት። እነዚህ ዓምዶች የመደመር መንግሥት ዕሳቤ ባሕርያትና መገለጫዎች ናቸው።

መዋቅራዊ ተናባቢነትና ሥምረት (Symmetry)፦ ተፈጥሮ በቅልጥፍናና ያለ ብዙ እንከን ራሱን የሚያራምደውና ቀጣይነቱን የሚያረጋግጠው ሥርዓት ባለው መዋቅራዊ መናበብና ሥምረት ውስጥ ስላለ ነው። የፀሐይና የፕላኔቶች የአካሄድ ዑደት፣ የክረምትና የበጋ ፈረቃ፣ የዕጽዋትና እንስሳት ተመጋጋቢነት፣ የቀንና የማታ ክፍፍል ሁሉ ተናባቢነትና ሥምረትን ያሳያል። የመደመር መርሕ በትክክል ተፈጻሚነት ሲያገኝ በዘርፎች፣ በመሪዎች፣ በክልሎች፣ በሞያዎች፣ በመንግሥት ክፍሎች መካከል የተስተካከለ ተናባቢነትና የተግባር ሥምረትን ይፈጥራል። በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን የሚታየውን ግራ መጋባትና መጣረስ፣ አንዱ ለሌላው ያለውን ዕንቅፋትና የመናበብ ችግር በማስወገድ ወደ ሥርዓታዊ ፍጥነት ለመግባት ይህ የመደመር ዓምድ በጥንቃቄ ሊገነባ ይገባል።

ህልውናዊ አብሮነትና ተደጋጋፊነት **(Symbiosis)፦** ሕይወት ከራሳችን እኩል በሌሎች ነዋሪነትና ቀጣይነት ላይ የተመሠረተች ናት። አንድ ዘርፍ ከሌላው ዘርፍ ስኬት ውጪ ውጤቱ አነስተኛ ነው። የአንዱ ክልል ሰላምና ህልውና የሚረጋገጠው የሌሎች ክልሎች ሰላምና ህልውና ሲረጋገጥ ነው። ሁሉም የመንግሥት ክፍሎች በተደጋጋፊነትና በህልውናዊ አብሮነት ካልሠሩ በቀር እንኳን እነርሱ ሀገርም በትክክል ልትቀጥል አትችልም:: አብሮ ማደግ የፈጣን ዕድገት በር ነው። የሌላውን ግብአት መቀበልና ለሌላው በጎ ግብአት ለመሆን ራስን ማዘጋጀትና መስጠት ለጋራ ከፍ ያለ ስኬት መሠረት ነው።

CS CamScanner

ሀገራችን በዚህ የመደመር ስሌትና ሥርዓታዊ ፍጥነት ውስጥ እንድትገባ ካላደረግን ተያይዘን ከማደግ ይልቅ ተጠላልፈን መውደቃችን አይቀርም።

የጋራ ጥረትና የኃይል ብዜት**(Synergy)፡-** በመደመር ዕሳቤ መሠረት ሕይወት ቀጣይነት እንዲኖራትና የኢኮኖሚ ብልጫ እንድታገኝ፣ የኃይል ብዜት በጋራ ጥረት መፈጠር አለበት። ምክንያቱም የጋራ ድምር፣ ውጤቱ ከተደማሪዎቹ የተናጠል ጥረት ውጤት ድምር ብልጫ ስላለው ነው። ከዚህም ባሻገር የተናጠል ጥረት ሊፈጥረው የማይችል አዲስ ነገር የጋራ ጥረት የኃይል ብዜት ሊከሥተው ይችላል።

ለምሳሌ የመኪና ዕቃዎች በመደመር የጥምረት የኃይል ብዜት ስሌት ካልሆነ በተናጠል የመኪናን ሚና ሊጫወቱ አይችሉም። የመኪና መፈጠር ደግሞ በተጓዡ ላይ የሚፈጥረው የፍጥነት ልዩነት በቃላት ከሚገለጸው በላይ ነው። በተናጠል ለተጓዡ ሸክምና የመዘግየት ምክንያት የሆኑት ዕቃዎች በኃይል ብዜት የመደመር ስሌት ተጓዡን ተሸክመው የሚፈተለኩ መኪና የመሆናቸው ምሥጢር ሊገባን ይገባል። አሁናዊ ዕድላችንን ወደ ፍጥነት መቀየር የምንችለው በየዘርፉና በየክልሉ፤ በየመሥሪያ ቤቱና በየመሪው ውስጥ ያለውን ዐቅም በመደመር፣ ኃይላችንን ስናበዛ ብቻ ነው።

ተሣላጭነትና የጥምረት ፍሰት**(Synchrony)፡-** የሚቆጠሩ መኪኖች ወይም የአየር ክልሉን የሞሉት አውሮፕላኖች፣ ፍጥነታቸውም ሆነ መንገድ ላይ የሚፈስሱ በሺህ ደኅንነታቸው ተጠብቆ ካሰቡበት ሊደርሱ የሚችሉት፣ በተሣላጭ የጥምረት ፍሰት ውስጥ ከገቡ ብቻ ነው። ከዚህ የተለየው የተናጠል ፍጥነት መዘጋጋትና መገጫጨት ብሎም መጠፋፋት ነው። የመንገዱ ጥበት ወይም የሌላው መኪና ክፋት ሳይሆን ተናብቦና ተሣልጦ ያለመፍሰስ ውጤት ነው። የተሣለጠና የተጣመረ ፍሰት የስኬታችን ቁልፍ ነው።

ሀገራችን ከጎረቤቶቿና ከሩቅ ወዳጆቿ፣ በሀገር ቤት ያለው ማኅበረሰብ ከዳያስፖራው የራሳቸውን ማንነት ጠብቀው በጋራ በመሣለጥ ሀገራችን ባገኘችው የዕድል አውራ ጎዳና ጋር፣ የግል ዘርፉ ከመንግሥት ጋር፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከገዢው ፓርቲ ጋር ላይ መፍሰስ አለባቸው። ይሄም ለዕድገታችን መተኪያ የሌለው የመደመር ማሳያ ዓምድ ነው።

የዕይታ ስፋትና ልኬት(Synoptic)፡- በጠባብ ዕይታና በእጦት አስተሳሰብ ውስጥ ባለ ትንሽነት ውስጥ ፍጥነትን ማሰብ አስቸጋሪ ነው። ከመሬት ስፋት ይልቅ የአስተሳሰብና የልብ ሰፊነት ለፍጥነት ቁልፍ ናቸው። ፍጥነትን ለማረጋገጥ በመደመር ውስጥ ያለውን ወሰን የለሽ ዕድልና ሰፊ የስኬት አጥናፍ መመልከት ይጠይቃል። ስኬትን በሌላው ውድቀት ውስጥ ከመመልከትና ለብቻ ከመሮጥ አባዜ ተላቅቀን ሜዳው ለሁላችን የሚበቃ መሆኑን በመረዳት፣ ተደጋግፈን ርቀትና ፍጥነት ያለው ሀገራዊ ሩጫ ልንሮጥ ይገባናል። ለብቻቸው በጠባብ ዕይታና በራስ ወዳድነት የሚሮጡ ለጊዜው የፈጠኑ ቢመስሉም ውሎ አድሮ ግን መሐል ላይ መቅረታቸው አይቀርም። በአንድ ጉዳይ ላይ ባልሞከርናቸው መሥመሮችና መንገዶች መሄድም ለምናስበው ይችላል። ልማድ፣ ባህል፣ እምነትና አስተዳደግ እንዲሁም ተቋማዊ የዕይታን ስፋትና ልኬት የሚወስኑና የሚያጠብቡ እንዲሁም ያልተሻገረና የጠበበ ዕይታ መንሥኤ ሊሆኑ ይችላሉ።

የሙጥኝ ከማለት ይልቅ መንገድ ቁልፍ ሊሆን አሠራሮች ካልተፈተሹ፣ ተጓዳኝነትና የሕይወት አንድነት(Syntropy)፡- የምንኖርበት ዓለምና የከበበን ጽንፈ ዓለም በሁለት ኃይሎችና አካሄዶች ውጥረት ውስጥ ይገኛል። አንድም በሕይወት መፈራረስና መዘበራረቅ(Entropy)፣ አንድም በሕይወት ተጓዳኝነትና ገንቢ አንድነት(Syn tropy)። የመደመር ዕሳቤ ደግሞ መፈራረስና መጠፋፋትን ሳይሆን መገንባትንና አብሮነትን፤ ሥርዓት አልበኝነትንና ዝብርቅርቅነትን ሳይሆን ሥርዓታዊ መያያዝን፤ ብሎም ወደ ጋራ ግብ አብሮ መፍሰስንና መገሥገሥን የሚያስተምር ነው።

በቀውስ መሐል ፈውስ፣ በመፈራረስ ውስጥ መታደስ፣ ተበታትኖ በመጥፋት መካከል ተሰባስቦና ተጣምሮ በአዲስ ጉልበት መነሣት የመደመር መንገድ ነው። ሀገራችንም በዚህ የመደመር መንገድ እንድትጓዝና ከገባንበት አፍራሽና በታታኝ አካሄድ

CamScanner

ነጻ እንድትወጣ ያስፈልጋል። ከዚህ ተላቅቃ ወዳለምንላት የብልጽግና ማማ እንድትወጣ ወደ አዎንታዊ ተጓዳኝነትና ብዝኃነትን ወደማይጨፈልቅ አንድነት መሻገር ይገባናል።

CamScanner

# ክፍል ሁለት

## የመደመር መንግሥት

CamScanner

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የመደመር መንግሥት ባሕርያት

የሀገራችንን የድህነት ደረጃና የዓለምን እጅግ ተለዋዋጭ የሆነ ፈጣን ዕድገት ታሳቢ ካደረግን፤ መንግሥት እስከ አሁን ከሚጫወተው በእጅጉ የላቀ ሚና መጫወት እንዳለበ እንገነዘባለን። የላቀ ሚና ብቻ ሳይሆን ሚናውን የሚጫወትበትም መንገድ ከለውጡ በፊት ከተጓዝንበት በእጅጉ የተለየ መሆን እንደሚገባው ግልጽ ነው። ሀገራችን በፍጥነት ወደ ብልጽግናው ማማ እንድትወጣ፣ የሥርዓት ተዋንያን የሚና ሚዛን ማስጠበቂያ መካከለኛ ቦታችንን ማግኘት አለብን፡፡ ለዚህም ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ ለነገ የማይባል ሥራ ነው:: በለውጡ ማግሥትም የመጀመሪያ ሥራችን ይኼው ነበር።

በሀገራችን ገበያ መር ኢኮኖሚ አይሎ የወጣበትና እንደ በለጸጉ የምዕራብ ሀገራት ገ አስተሳሰብና ሥርዓት የሆነበት ሁኔታ የለም። ይልቁንም የግል ክፍለ ኢኮኖሚው ገና በለጋ ዕድሜ ላይ የሚገኝ ራሱን ችሎ ያልቆመ ነው። ባለሀብቱ ብቻውን ፈጣን፣ ፍትሐዊ፣ ዘላቂና በፈጠራ የታጀበ ልማትን ሊያሳካና ሀገራችንን ወደ ብልጽግና ሊያደርሳት አይቻለውም። በመሆኑም የግል ዘርፉ እንደ አጠቃላይ ሀገርን ሊገነቡና በረጅም ጊዜ ሊጠቅሙ ከሚችሉ ሥራዎች ይልቅ፤ የአጭር ጊዜ ትርፍ ማጋበስን እንደ መሥመር የሚያይ ዘርፍ ሆኗል። ለዚህም ከአምራችነት ይልቅ በሌሎች ሀገራት የሚመረቱ ምርቶችን አስመጥቶ ባልተገባ ዋጋ መሸጥን እንደ ዋና ሥራ አድርጎታል።

እንዲሁም እነዚህን ሸቀጦች በዘላቂነት በሀገር ውስጥ የማምረት ፍላጎት አያሳይም። ይህ የገበያ መር አካሄድ አንዱ ተፈጥሯዊ ውሱንነት ነው። በሀገራችን ደግሞ ይሄ ውሱንነት በከፍተኛ ደረጃ የተንሠራፋና ዘርፉን መሥመር ያሳተ አካሄድ ነው።

በሌላ በኩል የግል ዘርፉ እንደ ሀገር ያሉብንን ተደራራቢ ችግሮችና በተለዋዋጭ ዓለም የሚወለዱ አዳዲስ ፈተናዎችን መቋቋም የሚያስችል ዝግጁነት የለውም። በአደጉት ሀገራት የግሉ ዘርፍ ሀገርን ከመገንባትና ለሀገር ደጀን ከመሆን አኳያ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።ለጉዳዩም ከመንግሥት በእጅጉ የላቀ ዝግጁነት አለው፡፡ ለውጦችን አስቀድሞ የሚመለከትና ዝግጁ ሆኖ የሚጠብቅ ዘርፍ ነው። በሀገራችን ያለው ሁኔታ ግን በአጠቃላይ ሲታይ፣ የግል ዘርፉ የሀገርን ተደራራቢ ችግር ከማገዝ አኳያ፣ እዚህ ግባ የሚባል አበርክቶ ወይም ዝግጁነት አይታይበትም። ገበያው ትኩረቱን ትርፍ ላይ የሚያደርግ በመሆኑም በተፈጥሮ፣ በማኅበረሰብ ወይም በሌሎች ላይ ለሚመጣው ጫና ግድ የለውም። በማምጣት ረገድ አሉታዊ ተጽዕኖን የሚፈጥር ነው። ለዚህ ምክንያቱ ብዙ ቢሆንም፣ ይህ ግዴለሽነት የሚፈጥረው ጫና ቀጣይነት ያለው ፍትሐዊ፣ አካታችና ዘላቂ ልማትን እንዲህ ዓይነት ሀገራዊ ተግዳሮቶችን መታገል ግን ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ለመንግሥት የተተወ ነው::

ገበያው በራሱ መሠረተ ልማትን እየገነባ አይሄድም። ስለዚህም ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ችግር ውስጥ ባለንበት ሁኔታ፣ ሊያመጣ የሚችለው ዕድገት በእጅጉ የታነቀና ቀርፋፋ እንደሚሆን፣ ያለን ተሞክሮ በቂ ማሳያ ነው። ገበያው እንዲሣለጥ፣ መሠረተ ልማት እንዲገነባ ከመንግሥት ብቻ መጠበቅ አልነበረበትም። መሠረተ ልማትን እየገነቡ ሀገርን የሚያገለግሉ ትርፋቸውንም በረጅም ጊዜ ለማግኘት የሚያሰሉ የግሉ ዘርፍ ተዋንያን መኖር ነበረባቸው። ነገር ግን በዚህ ከፍተኛ ሀብት በሚጠይቅ አካሄድ ለመጓዝ የሚችሉ ባለ ሀብቶችን ገና አልፈጠርንም። እንዲህ ዓይነት ባለ ሀብቶችን ማፍራትም የረጅም ጊዜ ዕቅድ እንጂ ድንገት መሳካት የሚችል የአንድ ጀምበር ሥራ አይደለም። አሁን ባለንበት ሁኔታም ተግባራዊ መሆን የሚችል አይደለም።

ይሁንና ትርፍን መሠረት ያደረገው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴም ቢሆን ዘርፈ ብዙ ትሩፋቶችን ፈጥሯል። ቀድሞ በደርግ ጊዜ ከነበረው የኢኮኖሚ ፍሰት የተሻለ ዕድገትና እመርታም ታይቷል። ነገር ግን በተቃራኒው ደግሞ የገበያው ኃይል

CamScanner

በጥቂት ባለ ሀብቶች ቁጥጥር ሥር እንዲወድቅ ሆኗል። በዚህም የተነሣ ሀገራዊ ራዕይን ከማሳካት ይልቅ ጥቂት ባለ ሀብቶች የሚዘውሩት ኢኮኖሚ እየሆነ እንዲመጣ አድርጎታል።

ገበያ መሪ ተዋናይ እንዲሆን፣ ነጻ ውድድርን ማሣለጥ የሚችል፣ ከሙስና የጸዳ አሠራር የሚተገብር፣ ግልጽና ተጠያቂነት የሰፈነበት ከባቢ መኖር የግድ ነው። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ገበያው በከፍተኛ ደረጃ በባለ ሥልጣኑ ላይ ይደገፋል። የእነርሱን ይሁንታና መልካም ድጋፍ ይሻል። በዚያም ላይ ይንጠለጠላል። በዚህም የተነሣ የፖለቲካ ገበያ አረም እንዲለመልምና እንዲወርሰን ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ከተወዳዳሪነት ይልቅ ብቸኛ ሠሪ ፈጣሪነትን(o- nopoly) ስለሚያሰፍን ሌሎች ባለ ሀብቶችን ለማፍራት ያስቸግራል።

ሲከፋም ነጻ ባለ ሀብቶችን በጭራሽ ማፍራት የማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ሊከተን ይችላል። ሆኖ በአቋራጭ መበልጸግን የሚተልም ይሆናል። ያልተገባ ትርፍን ማጋበስና ሕዝቡን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚሠራ ባለ ሀብት ሕዝብን ከማገልገል ይልቅ ብቸኛ አቅራቢ መዝረፍም መገለጫው ይሆናል። ይህ ሁኔታ በሚፈጥረው የሕዝብ ምሬት የተነሣ የተረጋጋ ሁኔታ አይኖርም።

ሀገራችን የረጅም ጊዜ የመንግሥት አስተዳደር ልምድ ያላት ብትሆንም፤ አሁን ካለው የዓለም ሁኔታ ጋር ሲተያይ በእጅጉ ኋላ ቀርና አዝጋሚ ሂደትን የሚከተል ነው። በኋላ ቀርነቱ የተነሣ ሀገርን ለማረጋጋትና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ተቸግረናል። መንግሥታዊ አስተዳደሩ ካለንበት ድህነት አውጥቶ ወደ ብልጽግና ጎዳና ለመቀላቀል ተስኖታል። በአንጻሩ ደግሞ የግል ጥቅምና ሙሰኝነት ተስፋፍቷል። ለዚህ ያሳለፍናቸው አብዮቶችና የሕዝብ ምሬት መግለጫ መድረኮች ማሳያ ናቸው።

በሀገራችን ባለፉት ዓመታት መንግሥት መሠረተ ልማትን በማስፋፋት ፍላጎትን የማነቃቃት ሥራ ለመሥራት ሞክሯል። ነገር ግን አቅርቦትን በበቂ ሁኔታ የሚያሳድጉ ሥራዎች አልሠራም። ይህም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና ፈጥሯል። በተጨማሪም በኢኮኖሚያችን ውስጥ መሠረታዊ የሆነ የምርታማነትና የሀብት ፈጠራ ችግር አለ። የምንጓዘው የዚህ ዓይነት ተደራራቢ ችግሮች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ነው።

በአንድ በኩል ተለዋዋጭ በሆነው ነባራዊው የዓለም ሐቅና በሀገራችን ፈተናዎች ውስጥ የሚገኙ ዕድሎችን መጠቀም አለብን። በሌላ በኩል ደግሞ የሚፈጠሩ አዳዲስ ፈተናዎችን መቋቋም ይኖርብናል።ለዚህም በመንግሥትና በገበያው ተገቢና ተሣላጭ ጥምረት ላይ የተመሠረተ ከፍተኛ ጥረት ያስፈልጋል። ያሉብንን መሠረታዊ የምርታማነት ችግሮች ለመቅረፍና የሚፈጠሩ አዳዲስ ፈተናዎችን ለመቋቋም፤ እንዲሁም የሚፈጠሩ ዕድሎችን ለመጠቀም የመንግሥትና የግል ዘርፉ ጥምር ሚና እጅግ አስፈላጊ ነው።

ስለሆነም እነዚህን ግቦች ለማሳካት የሚያስችል አቅጣጫንና ተልዕኮን ነድፎ በታቀደ መልኩ የሚንቀሳቀስ መንግሥት ያስፈልጋል። ይህ ዓይነት በታቀደበት መልኩ የሚንቀሳቀስ መንግሥት በመንግሥትም ሆነ በግል ዘርፍ ተዋንያን በጅምር ደረጃ የሚገኘውን ብቃት በማስተባበር የተሻለ ዐቅም እንዲኖር በማድረግ፣የኢኮኖሚውን አቅጣጫ ፍሰትን ያስተካክላል። ስለዚህ መንግሥትንና ገበያውን አስተባብሮ በአጋርነት መሥራት ምሉዕ ብልጽግናን ለመጎናጸፍ የተሻለው አማራጭ ነው።

በዚህ ዕሳቤ መሠረት የኢኮኖሚውን ጨዋታ መንግሥት ሙሉ በሙሉ ለገበያው አይተወውም። አልያም በራሱ የመምራት ሚና ብቻ አይወጣውም። ወይም ባለ ሀብቱ በማይገባበት ብቻ እየመረጠ የሚሠራበት አይሆንም። የመደመር መንግሥት ከእነዚህ ያለፈ ሚና ሊኖረው ይገባል። የመደመር መንግሥት ሚና አዳዲስ የገበያ ዕድሎችን በሚፈጥር ሂደት አይቆጣጠርም። እንደ ካፒታሊስት መንግሥትም የገበያን ጉድለት በማስተካከል ላይ የፈጠራ ብቃት ላይ የተመሠረተ ነው።

CamScanner

እንደ ኮሙኒስት መንግሥት ሁሉንም ምርትና የምርት ብቻ አይወሰንም። እንደ ልማታዊ መንግሥትም መሠረታዊ መሠረተ ልማቶች ማቅረብ፣ የማበረታቻ ሥርዓት መፍጠርና መስጠት ላይ ብቻ አይጠመድም።

ይልቁንም የመደመር መንግሥት የሀገርን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ይወስናል። ከዚያም አንጻር የሀገርን ሙሉ ዐቅም(መንግሥትን፣መንግሥታዊ ያልሆኑትን፣ የግል ዘርፉንና ማኅበረሰቡን በጋራ ሕልም በማስተባበር ለአንድ ዓላማ እንዲተጉ ያደርጋል። በተመረጡና የረጅም ጊዜ ግብ ባላቸው ዘርፎች ላይ የገበያ ጉድለትን በመሙላትና ማበረታቻ በመስጠት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ አቅርቦትን በማነቃቃትና በማሻሻል ቀጥታ ሚና ይጫወታል። ከዚህም በተጨማሪ ገበያ የመፍጠር ሚናም አለው። ይህ ዓይነት የመንግሥት ሚና የኢኮኖሚውን አጠቃላይ የፍሰት አቅጣጫ ይቀይራል።

የመደመር መንግሥት ዋና ግብ የማይበገር ኢኮኖሚ፣ በታቀደ አግባብ፣ ደረጃ በደረጃ መፍጠር ነው። የማይበገር ኢኮኖሚ የወደፊቱን የሚያሰላ፤ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ተቋቁሞና እንደ መልካም አጋጣሚ ወስዶ ዕድገቱን ማስቀጠል የሚችል ኢኮኖሚ ነው። ተለምዷዊውን የመንግሥት ቁመና ተላብሶ በፍጥነት በሚለዋወጥ ዓለም ውስጥ አይበገሬ ኢኮኖሚ መገንባት የሚታሰብ አይደለም።

በመሆኑም አንድ ሥርዓት ራሱን ከዓለም አቀፋዊ ተለዋዋጭነት ጋር አጣጥሞ፣ ተወዳድሮና አሸንፎ ለመውጣት የሚጠበቁበት ነገሮች አሉ። ቁመናውን መፈተሽ፣ ማስተካከያዎችን ማድረግና ዝግጁ መሆን ወሳኝ ናቸው። ይህ የመደመር መንግሥት ቁመና ዕድሎችን በመጠቀምና ሥጋቶችን በመከላከል ግቦቹን ማሳካት እንዲችል ለማድረግ ቁልፍ ነገር ነው። ኢኮኖሚው የመጪውን ዘመን ፍላጎቶች ማሟላትና ዐቅሞችን በውጤታማነት መጠቀም እንዲችል በመደመር መንግሥት አስተሳሰብ መመራት አለበት።

አንድ ሥርዓት ለማረጋጋጥ ያሰበውን ዓላማ በሚያረጋግጥ መልኩ መደራጀትና መመራት አለበት። ያም ማለት ፈጣን፣ ፍትሐዊ፣ አካታችና ዘላቂ የሆነ ግብን ማረጋገጥ ከመሻት ያለፈ ተግባር መሆን አለበት። ያንን ግብ ለማሳካት የሚያስችል አቅጣጫን ማመላከትና በዚያ መንገድ መጓዝንም ይጠይቃል። መንግሥት ተፈላጊው ውጤት እንዲመጣ በሕግ፣ በፖሊሲ፣ በምናብ(magination)፣ ሙዓለ ንዋይ በማፍሰስ አቅጣጫን ማመላከትና ኢኮኖሚው በዚያ አቅጣጫ እንዲፈስ ማድረግ አለበት።

አዳዲስ ሐሳቦችን፣ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ወደ ገበያ ያመጣል። ማኅበረሰብን ኋላ ቀር የመደመር መንግሥት ለአስተሳሰብ ለውጥ በር ይከፍታል። ፈጠራን በማበረታታት ከሆነ ስልተ ምርት በማላቀቅ፣ ቴክኖሎጂን በመጠቀምና በማበረታታት የዜጎችን አኗኗር በፍጥነት ያሻሽላል። ማኅበራዊ ለውጥን ያፋጥናል። የመፍትሔ ሐሳቦችን በማፍለቅ የሕዝቡን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ይፈታል። ጤናማ ውድድርን በማበረታታትና ውጤታማ ቢዝነሶችን በመፍጠር ሸማቹን ከዋጋ ንረት ይታደጋል። የሳይንስና ቴክኖሎጂ የጥናት፣ የምርምርና ፈጠራ ተቋማት እንዲበለጽጉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ነባር የንግድ ተቋማት ዘርፈ ብዙ ለውጥ እንዲያመጡ ያደርጋል። ለመደመር መንግሥት የተቋማት ግንባታ መሠረት ይጥላል።

የመደመር መንግሥት የባለ ርዕዮች መንገድ ነው። እነዚህ ባለ ርዕዮች ችግር ፈቺ አዳዲስ ሐሳቦችን ያመነጫሉ፤ በመረጃ ላይ ይመሠረታሉ፤ የተሰሉ ሥጋቶችን ይወስዳሉ። መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀምና ሀብትን በማፍሰስ ርዕያቸውን እውን ያደርጋሉ። በዚህ መሠረት ትርፍ ያገኛሉ፤ ለሌሎችም የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ።

የመደመር መንግሥት ባለ ርዕዮች - አዳዲስ ምርቶችን፣ አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎችንና ሥርዓተ ገበያን ይፈጥራሉ። በዚህም አማካኝነት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ፈትተው የዜጎችን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል፣ ለሀገር ልማት ጉልህ አስተዋጽዖ ያበረክታሉ። ይሄንኑ የባለ ርዕዮች ሚና የመደመር መንግሥት ይጋራል። ከመጋራትም በላይ በሂደቱ ባለ ርዕዮች፣

CS CamScanner

ማኅበረሰባዊ ተቋማትና መንግሥት በቅንጅት የሚሠሩበትን አስቻይ ሥርዓት ይፈጥራል፤ ይገነባል። የመደመር መንግሥትን ውጤታማ የሚያደርገውም ይህ ነው።

የመደመር መንግሥት አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎቶችን ከመፍጠር በተጨማሪ ምርታማነትን ለማሻሻል በሚረዱ አሠራሮች ላይ ለውጦችን የሚያመጡ ፈጠራዎችን ያከናውናል። ለምሳሌ ኩታ ገጠም እርሻ፣ ያልለሙ መሬቶችን ማልማትና በዓመት ሁለት ጊዜ ማልማት፣ ከፍተኛ የምርታማነት ክፍተት ባለበት የግብርና ዘርፍ አዳዲስ የማሻሻያ ፈጠራዎችን ማከል ተጠቃሽ ናቸው። አርሶ አደሩን እንደ ግል ክፍለ ኢኮኖሚ ተዋናይ ብንመለከተው በእነዚህ ፈጠራዎች ላይ ቁርጠኝነት ኖሮት የምግብ ዋስትናን አረጋግጣለሁ ብሎ በዓላማ እና በተልዕኮ የመንቀሳቀስ ክፍተት አለበት። መንግሥት ከአርሶ አደሩ ጋር በትብብር በመሥራት መሬት በኩታ ገጠም እንዲታረስና በበጋ ማምረት እንዲቻል አድጓል። ለዚህም ለሜካናይዜሽን እና ለመስኖ ሙዓለ ንዋይ አፍስሷል። ይህም ከፍተኛ የምርታማነት መሻሻል እንዲፈጠር አድርጓል። በዚህም መንግሥት ፍላጎትን በማነቃቃት ከሚኖረው ሚና ባሻገር በአቅርቦት ዘርፉ ቀጥታኛ ለውጥ በሚያመጡ ዘርፎች ላይ ሙዓለ ንዋይ እያፈሰሰ ይገኛል። ውጤት እንዲመጣ በቁርጠኝነት በመትጋት እና ከአርሶ አደሩ ጋር በመተባበር ከፍተኛ ለውጥ ፈጥሯል።

የመደመር መንግሥት ከተለምዷዊው የመንግሥት መገለጫዎች በተጨማሪ ልዩ ባሕርያት አሉት። በየጊዜው ነባራዊ ሁኔታውን ባማከለ መልኩ የሚከሰሱና ተጣጣሚና አስቻይ ሆነው የተቃኙ ስትራቴጂዎችን የያዘና ሩቅ የሚያልም ነው። ከአሁናዊና መጻዒ ሁኔታ በመነሣት ነገሮችን ይመረምራል፤ በጥልቀት ይተነትናል፤ የምናብ ከፍታ አንዱ መገለጫው ነው።

የምናብ ከፍታ ለፈጠራ፣ ለዝግጁነት፣ ለተወዳዳሪነትና ለልማት ተስተካካይነት ምቹ ነው። በዚህ የተነሣ የመደመር መንግሥት በማያቋርጥ ፈጠራ የታጀበ ነው። ሠርክ ዝግጁና ጊዜው የሚጠይቀውን ተወዳዳሪነት የተላበሰም ነው። ፈጠራ ከተወዳዳሪነት ጋር ሲቀናጅ ከሚገኙ ውጤቶች አንዱ ነገሮችን በከፍተኛ ጥራትና በፍጥነት የመከወን ዐቅም ነው። ጊዜው የሚጠይቀውን ዝግጁነት ተላብሶ ለመገኘትም እነዚህን መገለጫዎች ጊዜውን ባማከለ መልኩ ማቀናጀትና ከፍተኛ ተለማጭነትን መላበስ ይጠይቃል። የመደመር መንግሥት ባሕርያትን በተወሰነ መልኩ በሚቀጥሉት ክፍሎች እናያለን።

### 5.1. ምናባዊ ከፍታ

ሀገራዊ የለውጥ ጉዞ የሚጀምረው ከምናብ ነው። ምናብ የዕሳቤ ምንጭ ነው። አሁን ካሉት ችግሮችና ውጥንቅጦች ከፍ ብሎ የማሰብ ፍኖት ነው። አሉታዊና ችግር ተኮር ምልከታን ወደ ዕድልና ዐቅም ተኮር አእምሯዊ ፍኖት መለወጥ ነው። የይድረስ ይድረስና የአጭር ጊዜ አቧራ የማስነሣት አካሄድን ዐሻራ ወደ ማሳረፍና መጪውን ትውልድ ወደ መቅረጽ ማሻገር ነው። ሀገርና ሕዝብን በማሰናሰል፤ የራስን መጪ ዘመን በራስ የመጻፍ ፍኖት ነው።

ምናብ ከተለመደውና ከነባሩ ወጣ ያለን መንገድ ለመፍጠር መሠረት ነው። ሩቅ ግቦች፣ከነባሩና ከተለመደው አካሄድ የራቁ ናቸው። በአብዛኛው ከተለመደው ይልቅ ሐሳባዊ በመሆናቸው በቀላሉ የሚሳኩ አይመስሉም። ሀገርን ወደ ከፍታ ለመምራት የሚደረግ ጉዞ በምናብ የሚጀመር፣ በምርምር የሚበስልና፤ በተግባር የሚፈተን ነው።

መንግሥት ለፈጠራ መነሻ የሆኑ ችግር ፈቺ ሐሳቦችን ለማመንጨት የሚያስችሉ ሥራዎችን በከፍተኛ ደረጃ መሥራት ይጠበቅበታል። እንዲሁም ኢኮኖሚውን ሊያሸጋግሩ የሚችሉ ከፍ ያሉ ምልከታዎችና ምናቦች ሊኖሩት ይገባል። መንግሥት የግል ክፍለ ኢኮኖሚው ማየት ከሚችለው በላይ መመልከት ይገባዋል። በጊዜና በቦታ ያልተገደበ ተሻጋሪ ምልከታ ሊኖረው ግድ ነው። ጊዜ ተሻግሮ የመጪውን ዘመን ተስፋና ሥጋት ማገናዘብ ወሳኙ ነገር ነው።

የሚችል መሆንም አለበት። ብልጽግናን ለማረጋገጥ የምንሻ ከሆነ ከጊዜና ከቦታ መሻገር እንዲሁም አሁን ከሚታየው ሁኔታ ተሻግሮ ሊፈጥረው የሚችለውን ዕሴት ማየት አለብን። ከፍታን በምናብ በመመልከት ዕሴት መፍጠር የሚችሉ ሐሳቦችን ገንዘብ ማድረግ ይገባናል።

CamScanner

ከለውጡ ማግሥት የተጀመረው ሸገርን የማስዋቢያ መርሐ ግብር፣ የኢትዮጵያን የመደመ መንግሥት ምናባዊ ዐቅም ያሳየ ነበር። የመርሐ ግብሩ ራዕይ ሦስት ነገሮችን ይዟል። ሥ ምኅዳራዊ እድሳትን፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂንና ፈጠራ የታከለበት የሀብት ማሰባሰብን። ይህን ለማከናወን የአካሄድ ስልቱ በሦስት ነገሮች ላይ እንዲመሠረት ተደርጓል፡፡ እነዚህም፦ ያለንን በሚገባ ማወቅ፣ ባለን ነገር ላይ ተገቢውን ዕሴት መጨመር፣ ከዚያም ሌላ ሀብት ለመፍጠር ወደ ሚያስችል ነገር መቀየር ናቸው።

ዓላማው አዲስ አበባን ዘመናዊ፣ ጽዱ፣ አረንጓዴና በቴክኖሎጂ የተሣሠረች ከተማ ማድረግ ነው። በመደመር መንግሥት ግንባታ ተምሳሌትነት ሀገራዊ ኩራትንና አንድነትን በሚያበረታታ መልኩ የተከናወነ ታሪካዊ ሥራ ነው። ድፍረት የተሞላባቸው አዳዲስ አሠራሮችን በመተገበር የተወሳሰቡ የከተማ ችግሮችን እንዴት መፍታት እንደሚቻል አሳይቷል። ይህ መርሐ ግብር የቀየረው የአዲስ አበባን ከተማ ገጽታ ብቻ አልነበረም:: ለሀገራችን ከተሞች የወደፊት ዕድገት ተምሳሌትና ማንጸሪያ አዲስ ምናብ ሆኖ ያገለግላል። የፕሮጀክቱ ገፊ ምክንያት ለዓመታት በቸልተኝነት ብክለት ሲደርስባቸው የነበሩት የአዲስ አበባ ወንዞች ናቸው። ጥንት ወንዞች ለአንድ ከተማ መመሥረት ዋነኞቹ ምክንያቶች ነበሩ። በኋላ ደግሞ ለከተሞች የጤናና የውበት ምክንያቶች ሆኑ። የከተሞች ተመራጭነት ቀዳሚ መለኪያዎች ከተሞቹ የውኃ አካላትን የያዙበት መንገድ ነው። ለከተሞች አረንጓዴ መልክም ወሳኞች ናቸው፡፡ በእኛ ሀገር ግን ወንዞች የቆሻሻ መጣያ ሆነዋል፡፡ ካደጉት ሀገሮች በተቃራኒ በእኛ ሀገር በወንዞች ዳርቻ የሚኖሩት ድኾች ናቸው። በየጊዜው በሚፈጠረው ጎርፍና የአፈር መሸርሸር ነዋሪዎች ለአደጋና ለሥጋት ተዳርገዋል፡፡

በዚህ የተነሣ የአዲስ አበባን ወንዞች ለከተማዋ መስጠት ያለባቸውን ዕሴት ወደሚሰጡበት ደረጃ መመለስ ነበረብን። ፕሮጀክቱ በዚህ ምክንያት የተቀረጸ ነው። ፕሮጀክቱ ተፈጥሮን ከከተማ ኑሮ ጋር ከሚያዋሕዱ አረንጓዴ ኮሪደሮች ጋር ይያያዛል። የፕሮጀክቱ አሠራር አያሌ ጠቀሜታዎችን አካትቷል።

ለሥነ ምኅዳር ተስማሚ የሆኑና በዘመናዊ ዲዛይን ከአካባቢው ውበት ጋር የተጣጣሙ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን፣ መዝናኛ ቦታዎችን፣ ንጹሕ አየር የሚሰጡ ቦታዎችን፣ ዘመናዊ የፓርኪንግ ቦታዎችን፣ የባህል ማዕከሎችንና ኢኮሎጂዎችን፣ ሳቢ መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ ያላቸው ፓርኮችንና የመዝናኛ ሥፍራዎችን ያካተተ ነው። እነዚህም የከተማዋን ዘላቂነት የሚያጠናክሩ ናቸው። የእግረኛ መንገዶቹ ለከተማዋ ነዋሪዎችና ለቱሪስቶች የተረጋጋ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ታስበው የተሠሩ ናቸው።

ይሄንን ጥረት የሚያጠናከረው በከተማው ሰሜናዊ ኮረብታ ላይ የሚገኘው የእንጦጦ የተፈጥሮ ፓርክ ልማትና በመሐል አዲስ አበባ የተገነቡት የወንድማማችነትና የአንድነት ፓርኮች ናቸው። አጠቃላይ መርሐ ግብሩ ሥነ ምኅዳራዊ እድሳትን ከባህላዊና ከታሪካዊ ጥበቃ ጋር አዋሕዷል። ይህ ሁሉን አቀፍ አሠራርና አቀራረብ የዘመናችን አንዱ ፈተና የሆነውን የከተማ ውስጥ መጨናነቅን የሚያቃልል ነው። በተጨማሪም ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ እንቅስቃሴን ያበረታታል። የሕዝብ ደኅንነትን ያስጠብቃል። በአጠቃላይ የከተማውን ገጽታ ያሻሽላል።

የመርሐ ግብሩ ምናባዊ ኃይል ነባር ሥፍራን በአዲስ ዕይታ መመልከቱ ብቻ አይደለም። ፈጠራ የታከለበት ሀብት የማሰባሰብ ስትራቴጂ መከተሉም ጭምር ነው። “ገበታ ለሸገር” ሕዝቡ በሀገሩ ልማት እንዲሳተፍ በማድረግ ረገድ የተዋጣለት ነበር። በመንግሥት በጀት ብቻ በመሥራት ሊወስድ የሚችለውን ጊዜና ቢሮክራሲ ቀንሶታል፡፡ ይሄም ለመደመር መንግሥት ሀገረ መንግሥት ግንባታ ትልቅ ማሳያ ነው። ዜጎች፣ የንግድ ድርጅቶችና ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ከሚያደርጉት መዋጮና ከመልሶ ማልማት መሬት የሊዝ ክፍያ ከፍተኛ የሀገር ውስጥ ገንዘብ ለማሰባሰብ ተችሏል።

CamScanner

ይህ የፈጠራ አካሄድ ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆነውን ካፒታል ከማስገኘቱም በላይ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ጥልቅ የሆነ የባለቤትነት ስሜትና የጋራ ኩራት እንዲፈጠር አስችሏል። የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ሀገራዊ መተባበርን አጎልብቷል። ፈጠራዊ አስተዳደርን በመጠቀም ትልቅ ሀብት ማሰባሰብ እንደሚቻል ዘመቻው አሳይቷል።

ኢተገማች በሆነ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ለውጥን መምራት የሚቻለው በምናብ ነው። ምክንያቱም የጠራ ምናብ ከሌለን ለውጥን መምራት ሳይሆን በተፈጠረልን ለውጥ ውስጥ ለመኖር እንገደዳለን። ድንቅ ነገሮችን መፍጠርም ሆነ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት የሚቻለው በነባሩ አካሄድና በአጭር ጊዜ ምልከታ አይደለም። ድንገተኛ አደጋዎችንም መሻገር የሚቻለው በተለምዶና በቀደመው አካሄድ አይደለም። በአዲስና ከፍ ባለ ምናባዊ እልባት ለመስጠትና የሚገጥሙንን አደጋዎች ወደ ዕድል ለመቀየር፤ አዲስ ምልከታና አእምሯዊ ፍኖት ያስፈልጋል። በተለመደው መንገድ እየሄዱ አዲስ ውጤት፣ ሩቅ ሳያስቡ ምልከታ ነው። በመሆኑም ሀገራችንን ወደ አዲስ ከፍታ ለማሸጋገር፣ ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት ጎመን ብቻ እየዘሩ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንደ መሞከር ነው። ሀገራችንን ወደ ከፍታው ለመምራት ተሻጋሪ ምናብ ይጠይቃል፡

የበለጸጉና ዐቅማቸው የፈረጠመ ሀገራት ዓለምን በራሳቸው ምናብ የመቅረጽና የሌሎች ሀገራትን መዳረሻ የመወሰን ፍላጎት አላቸው። ለምሳሌ የምዕራቡ ዓለም ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት በኋላ የራሳቸውን ዕሴቶች የዓለም ዕሴቶች ለማድረግ እየጣሩ ናቸው፡ ሁሉም ሀገራት የእነርሱ የምናብ ውጤቶች እንዲሆኑ ለማድረግ ጥረት አድርገዋል። ይሄም የምዕራቡ ዓለም ዕሴቶች የሆኑትን ዴሞክራሲና ሊብራሊዝም የተላበሰ ሀገር ከእነሱ ፍላጎት በተቃራኒ ሊቆም አይችልም የሚል መነሻ ያለው ነው።

ምሥራቃውያኑም ቢሆኑ የተለየ አካሄድ ተጠቅመው ግንኙነቶቻቸውን ለማዳበርና ተጽዕኗቸውን ለማሳረፍ መሞከራቸው አልቀረም። ስኬታቸውም ቀላል የሚባለ አይደለም። ከፍተኛ ሀብት ያፈሩ ሀገራትም አዲስ መጪ የዓለም ሁኔታን ከራሳቸው ጥቅም አንጻር ለመቅረጽ የሚያስችላቸውን ተጽዕኖ መፍጠሪያ ትላልቅ ዕቅዶችን ነድፈው ይንቀሳቀሳሉ።

ፈጣን ለውጥ ያስመዘገቡ ሀገራት ለውጣቸውን ለማስቀጠልና ወደ ሌላ ደረጃ ለማሻዥ ከደረሱበት ተሻግረው ሌላ ከፍታን ይመለከታሉ። ምክንያቱም ከፍታን መመልከት ያልቻለ ያለውንም ማስጠበቅ አይቻለውም። ባለበት ላይ ተደላድሎ የተቀመጠና ተለዋዋጭ ከሆነው ዓለም ጋር ያልተራመደ ሀገር ጥንካሬውን ማስቀጠል አይቻለውም። ከፍተኛ ዐቅም ቢኖረውም እንኳን መጪውን መላመድ ወይም መፍጠር የሚችል ምናብ የግድ ነው ያ ከሌለ አሁን ያለውን ዐቅም ማስቀጠል ወይም ጥንካሬውን ማዝለቅ አይቻለውም።

ከዚህ ዓይነቱ ተጽዕኖ ለማምለጥ መነጠልን ምርጫቸው ያደረጉ አንዳንድ ሀገራት አሉ። መነጠል በራሱ ግን ሀገርን ወደ ኋላ የሚመልስ ሽርተቴ ነው። ወደኋላ ከመሄድ ወደፊት መውደቅ ይሻላል ይባላል። ወደፊት መውደቅ የተወሰነ መንገድ ወደፊት ያስኬዳልና። በነባራዊ ዓለም ውስጥ መልካም ዕድሎቹን ተጠቅሞ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ዐቅም መፍጠር እንጂ፤ ተነጥሎ መኖር ከጥቅሙ ጉዳቱ የከፋ ነው። ይሁንና የራስን መዳረሻ መወሰን የሚቻለው የጠራ የራስ ምናብ ሲኖር ነው። በሌሎች ምናብ ውስጥ በእኛ ሳይሆን እነርሱ ለእኛ በመረጡልን የመዳረሻ መንገድ ላይ መጓዛችን አይቀሬ ነው።

ማንኛውም መንግሥት ሀገሩን የመለወጥ ርዕይ ከሌለው ለእርሱ ባልተዘጋጀ የሌሎች ሕልም ሥር ይኖራል። ይህ ደግሞ ቅዠት እንጂ እውነት አመልካች ሕልም ሊሆን አይችልም። የለውጥ ጉዟችን ዓላማ ከእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ተላቅቆ በራሳችን ትልምና አእምሯዊ ፍኖት መጓዝ ነው። የራሳችን የሆነን የወደፊት መዳረሻችንን በራሳችን ዓይን መመልከት ነው። ራሳችን እናልማለን፤ ራሳችን እናያለን፤ ራሳችን እንተልማለን፤ ራሳችን እንጓዛለን፤ ከዚያም ራሳችን እንደርሳለን። መድረስ ከምንፈልገው የብልጽግና ማማ ላይ እንድንቀመጥ የሚያደርገን ይህ አካሄድ ነው።

CamScanner

ነገን አሻግሮ የሚመለከት ምናብ አንዱ ትሩፋት፤ ለሰው ልጆች ብቻ የተሰጠው የፈጠራ ጸጋ ነው። የሰው ልጅ ለውጥና ሥልጣኔ የተፈጠሩት በፈጠራ ምክንያት ነው። ፈጠራ ከተቀነበበልን ሳጥን ውጭ ማሰብን፣ ዕውቀቶችን በተለየ መንገድ ማቀናጀትንና አዲስ ነገር ማፍለቅን፤ የማሻሻያ ፈጠራዎችን ጨምሮ አዳዲስ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ማውጣትን ይጠይቃል።

ይህ በሀገር ደረጃ ሲታይ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ለውጥ ለማምጣት የሚችል ዐቅም ያስገኛል። ለሁለንተናዊ ብልጽግናም መሠረት ይሆናል።

የመደመር መንግሥት ፈጠራን የሚያበረታታ እንደመሆኑ አዳዲስና በዓለም ደረጃም ተጽዕኖ ሊኖራቸው የሚችሉ ሐሳቦችን ለማፍለቅ መሠረትን ይጥላል። ያም መሠረት የሀገራችንን የብልጽግና መንገድ ያሣልጣል። ከዚህ አልፎ ዛሬ የበለጸጉት ሀገራት እያደረጉ እንደሚገኘው፣ መጪውን የዓለም ማኅበረሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በራሳችን ዕሴቶች ለመቃኘት ዕድሉን ያስገኛል። ለዚህ መሠረቱ ደግሞ አሻግሮ የማየት ምናባዊ ከፍታ ነው።

### 5.2 የማድረግ ዐቅም

የተቀደሰ ዓላማን መያዝ፣ መልካም ርዕይን መሰነቅ፣ የተመረጡ ዕሴቶችን መላበስ ብቻቸውን ወደ ምንፈልገው የብልጽግና ግብ ሊያደርሱን አይችሉም። ሐሳብ፣ ዕቅድ ዕቅድ ከማዘጋጀት፣ ከማለም፣ አቅጣጫ ከመስጠትና መመሪያዎችን ከማውጣት የዘለለ ነ ፍላጎት ብቻቸውን በቂ አይደሉም። ችግሮችን ከመለየትና የመፍትሔ ሐሳቦችን ከማፍለቅ ይፈልጋል። ይሄውም ተግባዊ ምላሽ ነው። ለማንኛውም ስኬታማ ሥራ የማድረግ ዐቅም ማጎልበት እጅግ አስፈላጊ ነው። ችግሮችን ከመለየትና መፍትሔዎችን ከማመንጨት ባሻገር የመፈጸም ዐቅምን ማጎልበት የነገሮች የመለወጫ ማርሽ ነው።

በሀገራችን ባለፉት ጊዜያት ይስተዋሉ ከነበሩ ችግሮች መካከል የመፈጸምና የማስፈጸምች አንዱና ዋነኛው ነበር። ከነችግራቸውም ቢሆን ተግባራትን ለማከናወን ዕቅዶች ይታቀባ አፈጻጸማቸው ግን በአብዛኛው የተፈለገውን ውጤት ሲያስመዘግብ አልታየም። ለዚ ደግሞ ዋናው ምክንያት የማድረግ ዐቅም ድክመት መኖሩ ነው። በዚህ የውድድር ዓለም ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቆየት በየትኛውም ቦታና ጊዜ የመፈጸም ዐቅምን ማሳደግ ያስፈልጋል። በሀገራችን አንዱ መሠረታዊ የኢኮኖሚ ችግር የመንግሥት አዝጋሚነት ነበር። የመንግሥት ፕሮጀክቶች ከፍተኛ የጥራት ክፍተት ነበረባቸው። ለመጠናቀቅም ረጅም ጊዜን ወስደዋል። ጥቂት ትላልቅ ሐሳቦች ቢፈጠሩም፣ሐሳቦቹን እውን ማድረግ ላይ ከፍተኛ ክፍተት ነበረ፡ በልማታዊ መንግሥት ሙከራ ሂደት ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ሽግግርን ያሣልጣሉ ተብለው | የተነሡ ትላልቅ ሐሳቦች ነበሩን። ቢሆንም መንግሥት ወደ መሬት በማውረድ ረገድ ከነበረበት ክፍተት የተነሣ ሀገርን ለከፍተኛ የሀብትና የጊዜ ብክነት ዳርገዋል። እንደ ሕጻ› ግድብ፣ የስኳር ፋብሪካዎች፣ የመስኖ ፕሮጀክቶች ኢኮኖሚያዊ ሽግግርን ያረጋግጣ ተብለው ተጀምረው ነበር። ነገር ግን አዝጋሚና ደካማ በሆነ አፈጻጸም ምክንያት እውን መሆን አቅቷቸው ሀገርን እንደ ነቀዝ በልተዋል።

የሕዳሴ ግድብ በሐሳብ ደረጃ የትውልድ ጥያቄና ምኞት ነበር። ሕዝቡ ከመቀነቱና ከኪሱ በ እያወጣ የተረባረበውም ለዚህ የዘመናት ጥያቄው መልስ ያገኘ መስሎት ነበር። የፖለቲካ ልዩነት ሳይገድበው እንደ ሀገራዊ ፕሮጀክት ተቀብሎት ሕዝቡ የዕለት ጉርሱን የዓመት ልብሱን ለግሦ ነበር። ነገር ግን ሦስት ፈተናዎች ገጠሙት።

መጀመሪያው የፕሮጀክት አመራር ችግር ነው። የሕዳሴ ግድብ - ታላቅ፣ ሀገራዊና አያ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ያሉበት መሆኑ ይታወቃል። የፕሮጀክት አመራሩ ግን እንደ አንድ ተራ ፕሮጀክት እንኳን አልተመራም። ሁለተኛው ከሙስና ጋር መያያዙ ነው። ፕሮጀክትነቱ ይልቅ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ጥቅም በመፈለግ ዐቅም ለሌላቸው አካላት ሥራዎቹ ተሰጡ። ያም የማይፈለግ ውጤት አመጣ። ሦስተኛው ወቅትን በጊዜ አለመጠቀም ነው። በሕዳሴው ግድብ ላይ የመጡ ዓለም አቀፍ

CS CamScanner

ፖለቲካዊ ሚናዎችን ለማለፍ የሚያስችሉ ዓለም አቀፍ ዕድሎች ተገኝተው ነበር። ነገር ግን ዘመኑን የሚዋጅ አመራር በማጣቱ እድሎች ያለ ጥቅም አለፉ።

አዳሴ ግድብ በነበረበት የአፈጻጸም ብቃት ድክመት የተነሣ ሀገራችንን ለተጨማሪ ወጪና የውጭ ጫና ዳርጓታል። ከሕዳሴ ግድብ በተጨማሪ በመንግሥት የመፈጸም ዐቅም ክፍተት ምክንያት በከፍተኛ የውጪ ብድር የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ሀብት ማፍራት ሳይጀምሩ የመክፈያ ጊዜያቸው ደርሷል። በዚህም ምክንያት ሀገራችን ለከፍተኛ የብድር ጫና ልትዳረግ ችላለች።

የመደመር መንግሥት ነገሮችን በፍጥነትና በጥራት አከናውኖ ማጠናቀቅ አንዱ ባሕርይው ነው። ተወዳዳሪ ሆኖ ለመውጣት በአንድ በኩል በሀገር ደረጃ ያሉብንን ክፍተቶች መለየትና ስክፍተቶቹ ዙሪያ ከፍተኛ የዐቅም ግንባታ ሥራ መሥራት ይኖርብናል። በዚህም አዳዲስና ችግር ፈቺ የሆኑ ሐሳቦችን ለማፍለቅ፣ ለማጎልበትና ወደ ተግባር ለማስገባት ዐቅም እናገኛለን። በሌላ በኩል ደግሞ አዳዲስ ችግር ፈቺ ሐሳቦችን ይዞ መቅረብ ብቻ ሳይሆን ሐሳቦቹን በፍጥነት ወደ መሬት ማውረድም ያስፈልጋል። በፍጥነት መተግበር የሀብትና የጊዜ ውጤታማነትን ይጨምራል። ሰፊ ሀብትን ለማካበትም ዕድል ይገኛል።

በአንድ ጊዜ ብዙ ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን ለማልማት የሚጋረጥብንን የፋይናንስ ውሱንነት ፕሮጀክቶችን በፍጥነት በቅደም ተከተል በማጠናቀቅና ወደ ሌሎች ፕሮጀክቶች በመሻገር ማቃለል ይቻላል። ይህ ዓይነት የጊዜ ቅልጥፍና መንግሥት በከፍተኛ የፋይናንስ ውሱንነት ውስጥ ቢሆንም እንኳን በጥቂት ዓመታት ውስጥ ብዙ ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን እውን ማድረግ እንዲችል ዐቅም ይሆነዋል።

በሀገራችን አንዱ የማድረግ ዐቅም ማሳያ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ነው። የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በዓለም በስፋት እየተስተዋለ ካለው የአየር ንብረት ግብዝነት(Gre enwashing) ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መንገድ ከንግግር ተግባርን ያስቀደመ መርሐ ግብር ነው።

ዓላማው የደን ሽፋንን ማሳደግና የደን መጨፍጨፍ፣ የመሬት መራቆትና የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን መፍታት የሆነው የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር የአካል መራቆትና የአየር ንብረት ለውጥ ተግዳሮቶችን ተጨባጭ በሆኑ ተግባራት ለመፍታት መጠነ ሰፊና የላቀ ውጤት የተመዘገበበት ተግባራዊ ጥረት ነው።

እንዲህ ያለው ትልቅ ፐሮጀከት በፌዴራል፣ በክልልና በአካባቢ ደረጃ ልዩ የሆነ የሆነ ቁርጠኝነትንና ቅንጅትን ይፈልጋል። ይህ የአመራር ጥበብና ቅንጅት የተለያዩ ማኅበረሰቦች ትምህርት ቤቶችን፣ የንግድ ተቋማትንና ዓለም አቀፍ አጋሮችን ያሳተፈ አካታች መርሐ ግብር ነው። የአረንጓዴ ወሻራ ፕሮግራም የጋራ የኃላፊነት ስሜትን በማጎልበት፣ ተነ ከዛፍ ተከላ በላይ ሆኖ ወደ ሀገራዊ ንቅናቄ አድጓል። የተለያዩ ቡድኖች ለጋራ ዓላማ ተባብረው እንዲሠሩ አስችሏል።

የማስፈጸም ሂደቱ ዛፍ በመትከል ላይ ብቻ ያተኮረ አልነበረም። ሁሉንም ማኅበረ ያሳተፈ ነበር። አካሄዱም ሊለካ የሚችል ከባቢያዊ ጥቅም የሚያስገኝ እንቅስቃሴ መፍ ነበር። የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ስኬት ሀገራዊ ኩራትና ጽናት እንዲጎለብት አስችሏል። አጣዳፊ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ተግዳሮቶችን ለመፍታት በመደመር ስሌት ጠገ የአፈጻጸም ጥበብ ያለውን ዐቅምም አሳይቷል።

የመደመር መንግሥት ከፍ ባለ ምናብ አዳዲስና ቀድሞ ልምድ ባላካበተባቸው ዘርፎች ላይ የሚሠራ እንደመሆኑ፤ ይሄንን ለማድረግ ደግሞ ለትግበራ ድፍረት ያለው፣ በቶሎ የሚሚ በፍጥነት የሚያድግ መሆን አለበት። ተቋማዊ ፍጥነትን ለማሳደግም ተቋማቱን በ የሰው ኃይል፣ በተሣለጠ የአሠራር ሥርዓትና በዘመኑ ቴክኖሎጂ ይገነባል። ብቁ የሰው ኃይል የሁሉም ማሣለጫ ነው። ያም ማለት ቴክኖሎጂን በቀላሉ የሚረዳና ወደ ተግ የሚያወርድ የሠለጠነ ኃይል ነው። በየዘርፉና በየደረጃው ያለንን የሰው ኃይል በሚገ ልክ ማብቃት የብልጽግናን መሠረት የመገንባት ያህል ነው። ለዚህ ደግሞ በትምህርት

CS CamScanner

ዘርፍ ወሳኝ ለውጥ ማድረግ ዋናውና ዘላቂው መፍትሔ ነው። በመደበኛ የትምህርት ውስጥና ከዚያ ውጭ ያለውን ሕዝባችንን ብቃት የምናሳድግበት የተለያዩ መንገዶቹ መከተል አስፈላጊ ነው።

የመደመር መንግሥት ከውስብስብ ቢሮክራሲ ተላቅቀው የመደመር ለውጥ የሚያመጡ ተቋማት ውቅር ነው። በመሆኑም ተቋማት ከተለመደው "የሥራ ሂደት መር" " አካሄድ መላቀቅ ይጠይቃቸዋል። ዓላማቸውንም ተልዕኳቸውን በማሳካት : ላይ : አድርገው መንቀሳቀስ ይገባቸዋል። አደረጃጀታቸውንም ለሚያገለግሉት ሕዝብ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያስገኙ ወደሚረዳቸው አደረጃጀት ማሸጋገር አለባቸው። ለመደመር መንግሥት ሕዝቡን ማገልገል ከቢሮክራሲው በላይ ነው። ስለዚህም አገልጋዮች ውጤትን አስቀድሞ ማየትና በዚያው መሠረትም የሚንቀሳቀሱበት መልክ ሊኖራቸው ይገባል።

አንድን ተቋም በራሱ ልዩ የሚያደርገው የሚሰጠው ተልዕኮ ነው። ይህ ተልዕኮ በተፈለገው ጊዜ፣ ሀብትና ጥራት ሲሳካ፤ ለሌሎች ተቋማት ተልዕኮዎች መነሻም፣ መንደርደሪያም፣ መሙያም የመሆን ሚና አለው። አንድ ተቋም ተልዕኮውን በተፈለገው ደረጃ ሲከውን ሌሎቹንም ተቋማት ተልዕኳቸውን እንዲወጡ የሚያስችል እገዛ ያደርጋል። በተገቢው ሁኔታ ሳይወጣ ሲቀር ደግሞ፣ ሌሎች ተቋማትን ዐቅም ሊያሳጣ ይችላል። ስለዚህም ተቋማት በተልዕኳቸው መሠረት መደራጀትና ተልዕኮን ማሳካት የሚያስችል ቁመና መገንባት ይጠበቅባቸዋል።

ተልዕኮን የሚያሳካ ቁመና መገንባት ውጤት ተኮር ከመሆን ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ውጤት ተኮር መሆን ሀብቶችን በግብአትና በሂደት ላይ ብቻ አፍስሶ ውጤቱን ለመቀበል ከመጠበቅ ያለፈ ነው። ከዚያ ይልቅ ውጤቱ ላይ ትኩረት አድርጎ ከተለመደው ሂደትና ግብአት ላይ ከማተኮር በላይ የሆኑ የፈጠራ መፍትሔዎችን መማተርን ይጠይቃል። ውጤቱን በሚያምር መልኩ መተግበርን እንደ መርሕ ይከተላል። "ግብአት አጣሁ፣ በጀት አጣሁ፣ የሰው ኃይል አጣሁ፣ አቅጣጫ አጣሁ፣ ድጋፍ አጣሁ" ብሎ እጅ አጣጥፎ መቀመጥ የመደመር መንግሥት ተቋማት ባሕርይ አይደለም። ወይም "ሂደቱ ይህን ያህል ጊዜ መውሰዱ ግድ ነው" እያሉ ጊዜን ሲያባክኑ መኖር የመደመር መንግሥት መገለጫ አይደለም።

የመደመር መንግሥት ተቋም፣ የተሰጠውን ተልዕኮ በሚገባ አጥርቶ ይገነዘባል፤ ያለውን ሀብት ሠፍሮ ቆጥሮ ያውቃል፤ ዕድሎቹንና ፈተናዎቹን ይመዝናል፤ ማንንም ሳይጠበቅ ተልዕኮውን ለመፈጸም የሚስችሉትን ሀብቶች ያሰባስባል፤ ይቆጥባል፤ አዳዲስ የሥራ ስልቶችን ያዘጋጃል፤ ይተገብራል፤ የታቀደውን ውጤት ለማምጣት ማናቸውንም መሥዋዕትነት ይከፍላል፤ በመጨረሻም ሪፖርቱ ውጤቱ ይሆናል።

የመደመር መንግሥት ማጠንጠኛ የሕዝብን ፍላጎት ማሟላት ነው። ሕዝቡን ማገልገል ደግሞ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው። የሁሉ ነገሮች መነሻና መድረሻም ሕዝብ ነው። ዕሴት የማይጨምር ቢሮክራሲን ለመጠበቅ ሲባል፣ ሕዝብ የሚንገላታበት ላይ ለተለያዩ ሁኔታዎች የሚጋለጥበት ምክንያት አይኖርም። ሕዝቡን ለማገልገል የሠራነው ቢሮክራሲ፤ ሕዝቡን የሚያንገላታ ከሆነ፣ ከመነሻው ግቡን ስቷል ማለት ነው።

ፍራንሲስ ቤከን "አንዳንድ ጊዜ መድኃኒቱ ከበሽታው ይብሳል" ይል ነበር። አንድ መድኃኒት የሚፈጠረው ሕመምተኛውን ከበሽታው የተሻለ ጤናና ዕረፍት ለመስጠት ነው። መድኃኒቱ በሽተኛውን ከበሽታው በላይ የሚጎዳው ከሆነ ግን መድኃኒት አይደለም። ቢሮክራሲዎ ሕዝቡን ከችግሩ በላይ የሚጎዳው ከሆነ ሕመም እንጂ መድኃኒት አይሆንም። በ20ኛ መክዘ መጀመሪያ የተነሣው የሕክምና ሊቅ ዊልያም ኦዚየርም "መድኃኒት የሚወስድ ሰው ሁለት ጊዜ መትረፍ አለበት። አንድም ከበሽታው፣ አንድም ከመድኃኒቱ ጉዳት" በማለት የተናገረው ለቢሮክራሲም የሚሠራ ነው። ማንኛውም የመደመር መንግሥት ቢሮክራሲ ሕዝቡን ከገጠመው ችግርም፣ ራሱ ቢሮክራሲው ከሚያመጣበት ችግርም የሚታደግ መሆን አለበት።

በየተቋማቱ ያሉ የመንግሥት ሠራተኞች ሕዝቡን ከቢሮክራሲው በላይ የሚመለከቱ እንዲሆኑ ይጠበቃል። አገልጋይነትን የተላበሱ መሆን አለባቸው። በመልካም ሥነ ምግባር የታነጹና ከዚህ ውጭ ያለውን ለመታገል የቆረጡ መሆን

CamScanner

ይኖርባቸዋል። ለሕዝብ ቅድሚያ የማይሰጥ አመራርም ሆነ ሠራተኛ የመደመር መንግሥት ወገን አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ግለሰብም ሆነ ይህንን አይቶ እንዳላየ በማለፍ የማይታገል ሰው በመደመር መንግሥት ውስጥ ዕድል ፈንታ የለውም።

በሌላ በኩል ደግሞ ከሰው ኃይል ብቃት በተጓዳኝ፣ የአሠራር ሥርዓት ደረጃውን የጠበቀ መሆን ወሳኝ ነው። የተሣለጠ የአሠራር ሥርዓት የሌለው ተቋም የብልጽግና ማነቆ ነው ለሌሎች ተደራራቢ ችግሮችም መንሥኤ ነው። በዚህ ተደራራቢ ችግር የመጀመሪያው ተጠቂ ጊዜ ነው። ባልተሣለጠ አሠራር ምክንያት የሚባክነው ጊዜ እጅግ የሚያሳዝን ነው።

በሀገራችን በደቂቃዎች ሊከወኑ የሚገባቸው ሥራዎች በሰዓታትና በቀናት ሲከፋም ሳምንታትን እንዲወስዱ ይደረጋሉ፡፡ ያም አብዛኛውን በሥራው ምክንያት የሚወሰድ ጊዜ ሳይሆን፣ ሥራን የመፈጸም ብቃት ባለመኖሩ የሚጠፋ ጊዜ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ቀርፋፋነት በድህነታችን እሳት ላይ ነዳጅ የሚጨምር ነው። የጥራት ማነስ፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ሙስናና ሌሎችንም ብልሹ አሠራሮች የሚወልዳቸው የቢሮክራሲ መንቀራፈፍና ጥራት ማነስ ነው። አሠራሮች ደረጃቸውን እንዲጠበቁ በማድረግና በቴክኖሎጂ በማሣለጥ፣ ተጽዕኖዎችን መቀነስ የመደመር መንግሥት አንዱ የዐቅም ግንባታ ትኩረት ነው።

የቴክኖሎጂ ዐቅምን ማሳደግ አሠራርን ከማዘመንና የሰው ኃይላችንን ውጤታማነት በከፍተኛ ደረጃ ከማሳደግ ያለፈ ጠቀሜታ አለው፡፡ አሁን ካለንበት ሁኔታ ይልቅ፣ መጪው ጊዜ ከቴክኖሎጂ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። ዓለም የሚታጠቀውን ቴክኖሎጂ መታጠቅ ካልቻልን፣ ተወዳዳሪ መሆን አንችልም። መታጠቅ ብቻም አይበቃም። ባለቤት ለመሆን ካልቻልን በእጅ አዙር የቴክኖሎጂ ባለቤቶቹ ቅኝ ተገዢ እንሆናለን፡፡ በመሆኑም የመደመር መንግሥት ቴክኖሎጂን መጠቀም ብቻ ሳይሆን ባለቤት ለመሆን አልሞ የሚሠራ ነው።

ሀገራችን በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ወደ ዲጂታል ሥርዓት ሽግግር ማድረግ ይጠበቅባታል። ይህ የሽግግር ጉዞ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማትን ከማጠናከርና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከመዘርጋት መጀመር አለበት። ከዚያም የተቋማትን የውስጥ የአሠራር ሂደቶቻቸውን በቴክኖሎጂ ማዘመን ያስፈልጋል፡፡ አገልግሎቶቻቸውን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ታግዘው በኦንላይን እንዲሰጡ ማብቃት አለብን፡፡ ከዚያም ባለፈ ከሌሎች ተቋማት ጋር በቴክኖሎጂ መቀናጀታቸው ወሳኝ ነው። ተገልጋዮች ካሉበት ሆነው ብዙ ጉዳዮችን እንዲያስፈጽሙ እስከማድረግ መጓዝም ይገባናል።

ጉዞው በዚህ የሚያበቃም አይደለም። ወደ ኋላም ተመልሶ በቀደሙ ተቋሞቻችን ተፈጥረው በሰነድ፣ በምስልና ድምፅ መልክ የተከማቹ ዕውቀቶችን ወደ ዲጂታል መመለስንም ያካትታል፡፡ እርሱም ነባር ዕውቀትን ለማሰባሰብ፣ በቀላሉ ለማከማቸትና በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ እጅግ ምቹ ነው።

በአጠቃላይ የመደመር መንግሥት ለተወዳዳሪነት ቅድሚያ ይሰጣል። . ተወዳዳሪነትበየደረጃው በልኩ ይገነባል። በዚህም ተግባራዊ ፍጥነትን የሚያሳካ ሥርዓት ውስጥ የሰው ኃይል ዐቅም፣ የአሠራር ዘመናዊነትና የቴክኖሎጂ ቦታ፣ ፈጠራና ሌሎች ደግሞ የተወዳዳሪነት ትሩፋቶች ይሆናሉ። እነዚህን ወሳኝ ማሣለጫዎቹ ናቸው። የሥራ ጥራት፣ መልካም አስተዳደር፣ ትርፍ ፍጥነት ስንተገብራቸው ሥርዓታዊ ፍጥነትን ያመጣሉ። ፕሮጀክቶችን በታቀደላቸው ጊዜ ማጠናቀቅ፣ ሀብትን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል፣ የምንተልመው በአጭር ጊዜ ለማሳካት ያስችለናል።

### 5.3. ተለማጭነትና ተላማጅነት

የመደመር መንግሥት ዘላቂነቱን የሚያጸናው በተላማጅ(Adaptive) ባሕር ተላማጅነት አንድ ሥርዓት ግትር(Static) መሆን የለበትም ይላል። በጊዜ ሂደት በሚዋጅ መልኩ የሥርዓቱ መዋቅር መለዋወጥ ለውጤታማነቱ ወሳኝ መሆኑን በዚህ ተለዋዋጭ ሁኔታ ውስጥ ራሱን በማሸጋገር ዘላቂነትን ያስጠብቃ መዋቅር ለውጥ ማለት መጀመሪያ ነባራዊ ሁኔታን ማጤንና የወደፊቱን መመ ቀጥሎ ደግሞ ለተሻለ ውጤታማነት ሲባል የሥርዓቱን አወቃቀር መለወጥ ነው: መጨመር፣ መወገድ

CamScanner

ያለባቸውን ማስወገድ፣ መሻሻል ያለባቸውን ደግሞ በተ ማሻሻል ማለት ነው። የመደመር መንግሥት የሽግግሮችን ውጤታማነት ይመረምራል፤ በተረጋጋ ሁኔታ፤ እንደየአስፈላጊነቱ ሽግግሮችን ደረጃ በደረጃ ያከናውንልናል።

የሀገራችን ኢኮኖሚ በፍጥነት እያደገ ነው። የመንግሥት የትኩረት መስኮች ይለዋወጣሉ። ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የሚቀመጡ የትኩረት መስኮች ሁኔታው ሲቀየር፣ የሚፈልጉት የትኩረት ደረጃም ይለዋወጣል። እነዚህን ነገሮች ማቀድና ሽግግሮችን በሂደት መምራት ከአላስፈላጊ ኪሳራና ውድመት ይታደጋል።

ኢኮኖሚያችን በኋላቀር ግብርና ላይ የተመሠረተ ነው። ይሄንን ወደ ኢንዱስ በዘመናዊ አምራችነት ላይ ወደ ተመሠረተ ኢኮኖሚ የማሸጋገር ሂደቱ የተረጋጋና ሽግግር መሆን አለበት። ለዚህ ደግሞ ለውጡ የራሱ የተላማጅነት ዕቅድና ግለ ሂደት ይፈልጋል። እንደዚህ ዓይነት ሽግግሮች፣ ብዙ ዘርፎችን ይነካሉ። በመን ከሌላው ጋር ቅደም ተከተሉን ጠብቆ የተሠናሰለና ተመጋጋቢ ሆኖ መታቀድ አለበት።

የተለያዩ ፈጠራዎችንና ሰፋፊ ኢንቨስትመንቶችንም ይፈልጋል። ስለዚህም ዕቅዱ እነዚህን ፫ አቀናጅቶ፣ ለተሻለ ውጤታማነት የሚያሰልፍ መሆን ይኖርበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የመደመር መንግሥት የውስጥ የኢኮኖሚ ሽግግርን በታቀደ መልኩ የሚመራ ብቻ ሳይሆን ከባቢያዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታን ይተነትናል። ራሱን ለመለወጥና ከእነዚህ ሁኔታዎች ጋር ራሱን ለማላመድ አስቀድሞ ይዘጋጃል። ዓለም ከአንዱ የኢኮኖሚ አብዮት ወለ ሌው እየዘለለ ከተለምዷዊው አሰራር ወጥቶ ወደ ዲጂታል ተሸጋግሯል። ከዚያም አልፎ አልፎ እንደ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ዓይነት ጨዋታ ቀያሪ ዐቅም ያላቸው ቴክኖሎጂዎችን እየታጠቀ ነው።

ከዚያም አልፎ እንደ ሰው ሠራሽ አስተውሎት ዓይነት ጨዋታ ቀያሪ ዐቅም ያላቸው ይሄንን ለውጥ በቶሎ የተላመዱ ሀገራትን ዛሬ የበለጸጉ ብለን እንጠራቸዋለን። ምክንያቱም ለውጥ የሚላመዱትን ያከብራል፤ የማይላመዱትን ደግሞ ይሰብራል። የነገው የበለጸጉ ሀገራት ዝርዝር ማለት፣ የሚቀጥሉትን አብዮቶች መላመድ የቻሉና ራሳቸውን በለውጡ ውስጥ ያሸጋገሩ ሀገራት ዝርዝር ነው።

የመደመር መንግሥት ሌላው ባሕርይ ድንገተኛ ችግሮችን የሚያስተናግድበት ተለማጭነት Flexibility) የተላበሰ መንግሥት መሆኑ ነው። ለድንገተኛ ችግሮች በቀላሉ የሚንበረከክ መንግሥት አይደለም። እንደ ኮሮና ያሉ ዓለም አቀፋዊ ወይም በሀገር ደረጃ የሚነሡ ከፍተኛ ችግሮች በኢኮኖሚው ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ አስልቶ ይተነትናል። ከዚያም ተገቢውን ዓይነት አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ይወስናል። የኢኮኖሚ ዕድገቱንም ያስቀጥላል።ከዚያም በላይ ተግዳሮቶቹን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የኢኮኖሚ ዕድገቱን ያፋጥናል።

በአጠቃላይ የመደመር መንግሥት ለውጥን ተላማጅና ለሁኔታዎች ተለማጭ የሆነ መንግሥት ነው። በትንታኔ ላይ ተመሥርቶ፤ ኢኮኖሚያችንን የሚያሻሽሉ የሚጠቅም፤ ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚያስከብር፤ ሀገራችን ወደ ብልጽግና ማማ ለመውጣት የምታደርገውን ጉዞ የሚደግፍ፤ ወቅቱንና ሁኔታውን የሚመጥን ውሳኔ ከመወሰን ባሻገር የውሳኔዎቹን ተግባራዊነት ይከታተላል። ውጤቱንም ይገመግማል።

### 5.4. ቅንጅት

አጠቃላይ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሥርዓቱ በአንድ ላይ መቆምና ከላይ እስከታችና በነ ሲችል የጊዜና የሀብት ብክነት ይቀንሳል። እንዲሁም ቅልጥፍናን ከሀብት ሊ በመደመር ከፍ ያለ ውጤትን ለማምጣት ያስችላል። ፈጠራና ፍጥነት ሊቀ በኢኮኖሚ ውስጥ የተሣለጠ ቅንጅት ሲኖር ነው። በሥርዓት ውስጥ የመማር ነገ ተግባብቶ የመሥራት ባህል ሲኖር፤ ፈጠራና ፍጥነት የሥርዓቱ መገለጫ ይሆናል።

CS CamScanner

በዓለም ላይ ትላልቅ ፈጠራዎች በውጤታማነት ወደ ምርት የተለወጠ ለፈጠራና ለመደመር በሰጠው ትኩረትና ለእነዚህ ምርቶች ጥናትና ምሮ የተ ድጋፍ ነው። የመደመር መንግሥት አጋርነት ዋና ዓላማ ሦስት ነው። የመጀመ ቅሪ ዘርፍ ማፍራት ትላልቅ ኩባንያዎችን ነው። ሁለተኛው፥ ሀገራቸውን የሚጠ ማብቃት ነው። ሦስተኛው፥ እነዚህ ትላልቅ ኩባንያዎች ከሀገር ውስጥ ግር ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል ነው።

የበለጸገው ዓለም ቀድሞ ያፈራቸው ኩባንያዎች ዛሬ ለሀገር ኩራት ለኢኮኖሚውም ደጀኖች ናቸው። ሀገራችን በዚህ ደረጃ የሚጠራ አንድ የላትም። በዚህ ረገድ የአጭርም ይሁን የረጅም ጊዜ ዕቅድ ነድፎ የግል ዘርፉን የማልማት ጅማሮ እንኳን አልታየም።

የግሉን ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ አድርጎ ለማብቃት በምንሠራ የተ ሁሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ወሳኝ ነው። ዐቅማቸው ሲጎለብትም ሥራ ይገ በሙሉ ለግሉ ዘርፍ በመስጠት ማሠራት አለብን። ካልሆነ ደግሞ በከፊል ትምህርት እንዲቀስሙበት ማድረግ አንዱ ስልት ነው። በዚህ ዓይነት ስልት በሀገራቸው ላይ በመለማመድ ዐቅማቸውን እንዲያጎለብቱ መፍቀድ አለብን።

ይህ በየደረጃው ሲከወን፣ ከትናንሾቹ የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ጀምሮ ግዙፍ ኩባንያዎች በሀገራቸው ከፍተኛ አበርክቶ ይኖራቸዋል። ከዚህም ባሻገር በተግባር እየተፈተሹ ይነጥራሉ። ቀጣይ ሥራዎችንም ወስደው በልህቀት የሚፈጽሙበትን ዐቅም ያዳብራሉ። በዚህም ከሀገራቸው አልፈው ለአህጉራቸውና ለዓለም የላቀ ነገር ማበርከት የሚችሉ፣ የሀገር ኩራትና ደጀን ሆነው ይወጣሉ።

የመደመር መንግሥት ትኩረት የሚያደርገው በግሉና በመንግሥት ስልታዊ ትብብር ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚን ለመገንባት ነው። ይህ ትብብር የጥገኝነት ጉዞ አይደለም። ይልቁንም በአብሮነትና በተደጋጋፊነት ላይ የተመሠረተ፤ ወደ ተመሳሳይ ዓላማና ግብ የሚያመራ ሊሆን ይገባል።

በመሆኑም መንግሥት ባልለሙ ዘርፎች ላይ ቀዳሚ ኢንቨስተር ሆኖ ሊያለማ ይችላል። ነገር ግን የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚም ተከታይ መሆንና አብሮ ለማልማት መቻል አለበት። መንግሥትም በሥራው የግሉን ዘርፍ ማሳተፍና ማንቀሳቀስም አለበት። ጠንካራ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ መንግሥት ቀልጣፋና ውጤታማ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ይፈጥራል። ለመንግሥት ውጤታማነትም ውጤታማ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ አስፈላጊ ነው። ከዚህም በተጨማሪ፣ የተሻሻለው የመንግሥት ሚናና የተነቃቃው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ቅንጅት ደግሞ፣ ይበልጥ ቅልጥፍናንና ውጤታማነትን በማሻሻል ምርታማነት እንዲረጋገጥ ያደርጋል።

የመደመር መንግሥት በአንድ ዘርፍ ላይ ለዘላለም ተቸንክሮ የሚቆይ አይደለም። ዋና ግቡ በሂደት የግል ባለሀብቱን በማጠናከርና በማሳተፍ ሙሉ ለሙሉ እንዲቆጣጠር ማድረግ ነው። አንዱን ዘርፍ ሲያሳካ ሌሎች አዳዲስ ዘርፎችን ለማልማት ጥረት ያደርጋል። በኢኮኖሚ ውስጥ ፈጣን ለውጥን ማምጣት የሚቻለው በሥርዓቱ ተዋንያን መካከል በሚኖር ህልውናዊ አብሮነትና መደጋገፍ ነው። የመደመር መንግሥት በኢኮኖሚ ተዋንያን መካከል ከፍተኛ ቅንጅትን የሚፈጥር እንደ መሆኑ፤ ጥረቶችን ያስተባብራል፤ የሚኖራቸውን የተጽዕኖ አድማስ ያሰፋል፤ ያገዝፋል። የተለያዩ የልማት ተዋንያን በተበታተነ መልኩ በተናጠል በሚሠሩት የልማት ሥራ፤ የሚያመጡት ውጤት አነስተኛ ነው። ቅንጅታዊ አሠራርን በመዘርጋት እነዚህን የተበታተኑ ዐቅሞች መሰብሰብ እጅግ ጠቃሚ ነው። የተሰባሰቡት ዐቅሞችም በሀገር ደረጃ ጉልህ የሆኑ ተጽዕኖዎችን እንዲፈጥሩ ማስቻል ይገባል። ይሄም ጊዜንና ሀብትን ከመቆጠቡም ባለፈ፣ የሕዝቡን ተጠቃሚነት የማስፋትና የማጽናት ሚና ይኖረዋል።

CamScanner

በዚህም ከመደመር መንግሥት ባሕርያት መካከል ሁለቱን ወደ ተግባር እናወርዳለን። የተበጣጠሱ የመሠረተ ልማትና የልማት ሥራዎች፣ ምርምሮችና ዐቅሞችን በመደመር መርሕ ማቀናጀትና ማስተማር አንዱ ነው። በተናጠል ሊያመጡ ከሚችሉት ከፍተኛ ውጤትም በላይ በቅንጅት እጅግ ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ ማስቻል ደግሞ ሌላው ነው።

የቅንጅት ጉድለት ውጤትን ያኮስሳል። ውጤታማነትንም ይቀንሳል። አንዳንድ ጊዜ'ውን ቅዳ ውኃ መልስ" ዓይነት ይሆናል። አንዱ የሠራውን አንዱ ያፈርሳል። ያ ደግሞ የኪስ አዙሪት ያስከትላል። አንዱ ተቋም የሚሠራውን ሌላኛው አስቀድሞ በጋራ በማቀድ ከመፈጸም ይልቅ የተሠራውን የሚያፈርስ ከሆነ፣ እንደ ሀገር ኪሳራው ትልቅ ነው.. በሁሉም ዘርፎች በአሳዛኝ ሁኔታ የቅንጅት ክፍተት በከፍተኛ ደረጃ የተንሠራፋ ችግር ነው። በመሆኑም የመደመር መንግሥት ሥራዎችን ሲያቅድም ሆነ ሲተገብር ቅንጅታዊ አሠራርን ተከትሎ ስለሆነ ከኪሣራ አዙሪት እንድንወጣ ያደርጋል።

ሌላኛው የትምህርት ተቋማት ከተለያዩ ዘርፎች ጋር የሚኖራቸው ቅንጅት ነው። የትምህርት ተቋማት የየኢንዱስትሪዎቹን ችግር በቅርበት ተረድተው ችግር ፈቺ ሐሳቦችን እንዲያፈልቁ ማስቻል ያስፈልጋል። አንዱ ጋር ያለ ገንዘብ ሌላው ጋር ካለ ፈጠራ እንዲቀናጅ ያደርጋሉ። አንዱ ጋር ያለ ጥንካሬ ሌላው ጋር ካለ ጥንካሬ ጋር በማቀናጀት በጋራ ከፍ ያለ ውጤት ይፈጥራሉ። ይህ ዓይነት የመንግሥትና የግል ትብብር ትላልቅ የመንግሥት ፕሮጀክቶች ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆኑ ያደርጋል። አነስተኛ የግል ድርጅቶች ደግሞ ከፍ ወዳ ትላልቅ ድርጅቶች እንዲያድጉ ያደርጋቸዋል።

የመደመር መንግሥት ጥናትና ምርምርን በመደገፍ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን ከግሉ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ያለማል። ለመንግሥት ብቻ በተፈቀዱ ዘርፎች ላይ የግል ባለ ሀብቶች እንዲሠማሩ ይፈቅዳል፤ ያበረታታል። እንዲሁም በመንግሥት ብቻ ተይዘው የነበሩ ድርጅቶችን በሂደት በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ወደ ግሉ ያዞራል። የግሉ ዘርፍ እንዲነቃቃና ትልቅ ሚና እንዲጫወት አስቻይ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

በአጠቃላይ የመደመር መንግሥት አንዱ ባሕርይ በገበያ ውስጥ ከግሉ ክፍለ ኢኮኖሚና ሌሎች የልማት አጋሮች ጋር በቅንጅት በመሥራት፤ የአገልግሎት ጥራትና ቅልጥፍናን ማረጋገጡና ሥጋቶችንም መጋራቱ ነው። በዚህም ለዘላቂ ልማትና ለጋራ ብልጽግና ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

### 5.5. ክፍተትን መሙላት

ሀብት ለመፍጠርና ምርታማነትን ለማሳደግ የምርት ግብአቶችን ወደ ላቀ ምርትና አገልግሎት መቀየር ያስፈልጋል። የምርት ግብአቶች በዋናነት መሬት፣ የሰው ኃይል፣ ካፒታልና ነገረ ምርት(Total Factor Productivity) ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ምርታማነትን ለማረጋገጥ ዕምቅ ዐቅም ናቸው። ነገረ ምርት ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ሌሎች ዕምቅ ዐቅሞችን በማሰባጠር ወደ ውጤትነት የመቀየሪያ መንገድ ነው። የሰው ልጆች ሥልጣኔና ዕድገትም የተመሠረተው በዋናነት ባላቸው ዐቅም አይደለም። እነዚህን ዕምቅ ዐቅሞች ወደ ዕሴትነት በመቀየር ላይ ባላቸው ክሂሎት ነው።

ነገረ ምርት ዕምቅ ዐቅሞችን በፈጠራና በፍጥነት፣ ከፍ ያለ ውጤት ሊሰጡበት በሚችሉበት መንገድ መጠቀም ነው። ሌሎች የምርት ግብአቶች የተገደቡ ናቸው። ነገረ ምርት ግን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ሀብት ለመፍጠር የሚያስችል ያልተገደበ ዐቅም ነው። አዳዲስ ምርቶችንና አገልግሎቶችን በመፍጠር፤ እንዲሁም ምርት የሚመረትበትን አዲስ መንገድ በማስተዋወቅ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ሀብት ለመፍጠር ያስችላል። የነገረ ምርት መሠረተ ሐሳብ ደግሞ በየጊዜው የሚያድግና ያልተገደበ ነው። በዚህም የተነሣ በየጊዜው አዳዲስ ሀብቶችን ይፈጥራል።

ሀገራችን ከፍተኛ የሰው ኃይል፣ መሬትና ሌሎች እንጡራ ሀብት፤ እንዲሁም አነስተኛም ቢሆን በዘመናት የተፈጠረ ወረት አላት። የኢኮኖሚያችንም ትልቁ ክፍተት እነዚህን ዐቅሞች በሚፈለገው ደረጃ ወደ ዕሴት መቀየር አለመቻል ነው። እነዚህን

CamScanner

ዕምቅ ዐቅሞች ተጠቅሞ ወደ ውጤት መቀየር የሚያስችል የመደመር ዐቅማችን አናሳ ስለሆነ የሀብት ፈጠራ ደረጃችን ደካማ ነው፡፡

ሀብት መፍጠርና ምርታማነትን ማረጋገጥ በዋናነት ለግል ዘርፉ የተተወ ክልል ነው፡ ቢሆንም የግል ዘርፋችን እምብዛም ያልዳበረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በፈጠራ የታጀበ ምርትና አገልግሎት የመስጠት ሁኔታችን በእጅጉ አናሳ ነው፡፡ ይህ የፈጠራ ዐቅም እያደገ ካልመጣ፤ በተለመደው አሠራርና ምርት ብቻ እዚህ ግባ የሚባል ዕድገት እንደማናስመዘግብ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ክፍተት ከመሙላት አኳያ የመጀመሪያው የመደመር መንግሥት እገዛ የግል ዘርፉን በማብቃት የተለያዩ ፈጠራዎችን እንዲያወጣ ማስቻል ነው፡፡ ለዚህም የግል ዘርፉ ያሉበትን ችግሮች መለየት፣ ተቋማቱን ማገዝ፣ ሥነ ምኅዳሩንም ለፈጠራ ምቹ አድርጎ መቅረጽ፣ እንደየሁኔታውም ሥጋቶችን መጋራት፤ አስፈላጊ ናቸው፡፡

ለዚህም በሀገር ደረጃ ጀማሪ ድርጅቶችን(Startups) በተለያየ መልኩ የሚያግዝ ተቋም አቋቁመናል፤ አሠራር ዘርግተናል፡፡ የጀማሪ ድርጅቶችን የማበረታቻ መንገድ ሐሳቡን ከውጭ በማምጣት ከሀገራችን ሁኔታ ጋር እንዲስማማ አድርገናል፡፡ ተቋሙ ለሁሉም ተደራሽ፣ ምቹና ቀላል የሚሆንበትን መንገድ ቀርጸናል፡፡ በተለያዩ ደረጃዎች አስፈላጊውን አስተዳደራዊና የገንዘብ እገዛዎች አድርገናል፡፡ በዚህ የተነሣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ግዙፍ ድርጅት መሆን የሚችሉ የፈጠራ ሐሳቦችን አበረታትተናል፡፡

በዚህ የጀማሪ ድርጅቶች ማበረታቻ ፕሮግራም የወጣቶቻችንን የፈጠራ ዐቅም በባለሞያዎች የምክር አገልግሎት እናዳብራለን፡፡ ወደ ገበያ እንዳይወጡ የያዛቸውን ማነቆ ለመፍታት እንጥራለን፡፡ ሊመጡ ያሉ ሥጋቶችን እንጋራለን፡፡አዳዲስ የፈጠራ ሐሳቦች ወደ ምርትና አገልግሎትነት እንዲለወጡ እገዛ እናደርጋለን፡፡

በአንድ በኩል ገና ያልዳበረውን የግሉን ዘርፍ ዐቅም ማጠናከር የግድ መሆኑን አይተናል፡፡ በሌላ በኩል ግን ይሄንን ክፍተት የሚሞላ የመደመር መንግሥት አስፈላጊ ነው፡፡ የመደመር መንግሥት ችግሮችን ወደ ዕድል እንዲሁም የመበልጸግ ዐቅሞችንና ዕድሎችን ወደ ውጤት ይቀይራል፡፡ አዳዲስ ሐሳቦች አሉት፡፡ ሐሳቦቹን ለመተግበር የተጠና ሥጋትን ይቀበላል፡፡ ቅንጅትን ወይም ትብብርንም ይፈጥራል፡፡ አዳዲስ ምርቶችን ለማምረትና ምርቶች የሚመረቱበትን መንገድ ለመለወጥ የሚረዱ ፈጠራዎችን ያወጣል፡፡ በአዳዲስ የመልማት ዕድሎች ላይም ኢንቨስት ያደርጋል፡፡ ይሄንን በማድረግም ሀብት ለመፍጠር የሚያስችል በር የሚከፍት መንግሥት ነው፡፡

ባላደጉ ሀገራት የሚመረቱ ምርቶች በብዛት፣ በዓይነትና በጥራት ጉድለት አለባቸው እንዲሁም የሚመረቱበት መንገድ ውስብስብነት የለውም፡፡ በዚህም በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ተወዳዳሪነታቸው ደካማ ነው፡፡ በመሆኑም ተወዳዳሪነታቸውን ለማሻሻል የሚያመርቱትን በብዛትም ይሁን በዓይነት መጨመር አንዱ መፍትሔ ነው፡፡ እንዲሁም የሚመረትበትን መንገድ ማሻሻል ሌላው አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ይሄንንም ለማድረግ አዳዲስ ምርቶችን የሚያወጣና ምርት የሚመረትበትን መንገድ ለማሻሻል የሚያስችል ፈጠራ ያስፈልጋል፡፡

በሀገራችን መሬት በበጋ ጦሙን ሲያድር ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ ግብርናችን ወቅት ተኮር የማምረቻ መሣሪያውም፣ መሬቱም፣ አምራቹም ሥራ ይፈታሉ፡፡ የክረምቱም እርሻ ቢሆን ነው፡፡ ምርት የሚመረተው በዓመት አንድ ጊዜ፣ ዝናብ ሲጥል ብቻ ነው፡፡ ቀሪውን ጊዜ የሚሠራው በተናጠል ስለሆነ ለሀብት ብክነት ያጋልጠዋል፡፡እያንዳንዱን ገበሬ ለብክነትና ለውጤት ማጣት ይዳረጋል፡፡

የበጋ መስኖ እርሻ የመደመር መንግሥት የለውጥ ሐሳብ ነው፡፡ ሦስት ነገሮችን ይለውጣል፡፡ የአስተራረስ ባህልን፣ የውኃ አጠቃቀም ባህልንና የገበያ ባህልን፡፡ የአስተራረስ ባህል በበጋ ተቀምጦ የሚያሳልፈውን የአርሶ አደር ባህል ቀይሮታል፡፡ በዓመት በትንሹ ሁለት ጊዜ እንዲያመርት አስችሎታል፡፡ ሰፋ ያሉ መሬቶችን የማረስ ዕድል ስለሚያገኝም ቴክኖሎጂን ለመጠቀም አስችሎታል፡፡

CamScanner

ከዚህ በፊት አርሶ አደሩ በአብዛኛው የሚጠቀመው የዝናብ ውኃን ነው። የመስኖ ውኃን የመጠቀምና የማምረት ባህል እንዲስፋፋ ተደርጓል። በዚህም የተነሣ በአካባቢ ስለሚፈሰው ውኃ ያለው አመለካከት እየተቀየረ ነው። ከአካባቢ ውኃዎች ጋር በፈጠረው የጥቅም ግንኙነት የተነሣ የአካባቢ ጥበቃ ባህሉም እያደገ መጥቶ ድርቅ ወደ ረሃብ የሚቀየርበትን ዕጣ ፈንታ እየቀየረው ይገኛል።

ሦስተኛው የገበያ ባህል ነው። አርሶ አደሩ አንድ ጊዜ የመኸር እርሻን ያመርታል። በዚህም የተነሣ አብዛኛው ገበያው ከጥር እስከ መጋቢት ነው። ከዚያ ውጭ ያለው ወቅት የእህል ዋጋ የሚወደድበት ነበር። አርሶ አደሩ ሁለትና ሦስት ጊዜ ማምረት ሲጀምር ግን ይህን የገበያ ቀኖናዊነት ይቀይረዋል። ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ በርካሽ ዋጋ እህል የሚቀርብበት የገበያ ወቅት ይፈጠራል። መሬትን በበጋም በክረምትም የማልማት ከፍተኛ ዘመቻ በማድረጋችን ዛሬ በመላው ሀገራችን ዘመቻው ፍሬ አፍርቷል። ዓመታዊ የምርት መጠናችንንም በእጅጉ አሳድጎታል።

በአጠቃላይ መንግሥት የፈጠራ ክፍተትን የሚሞላ ነው።ይሄንን የሚሞላው በአንድ በኩል የግል ዘርፉን በማብቃትና ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር፣ በሚያደርገው እገዛ ነው። በዚህ እገዛ የግል ዘርፉ በፈጠራ ልቆና ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲወጣ ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት ራሱ የተለያዩ ችግር ፈቺ ፈጠራዎችን ስለሚያወጣ ነው። በእነዚህ ፈጠራዎች የማኅበረሰቡን ሕይወት ፈቀቅ የሚያደርጉ ውጤቶችን ለማግኘት ይተጋል።

አንዳንድ የግብርና ሥራዎች ለማገዝ ከሚኖር መተጋገዝ ውጭ በጋራ ማምረትና በጋራ መጠቀም የተለመደ አይደለም። እንኳን ሌላው ዘመዳሞችና ቤተሰቦች እንኳን በተበጣጠሰ የበሬ ግንባር መሬታቸው በየግላቸው እንጂ በጋራ አያርሱም።

## 5.6. ገበያ የሚፈጥር ንቁ ኢንቨስተር

የመደመር መንግሥት "የመጨረሻ አማራጭ ኢንቨስተር" ብቻ አይደለም። "የመጨረሻ ባልሆነባቸው ዘርፎች የሚሠማራ ነው። ወይም ደግሞ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስት ለማድረግ አማራጭ ኢንቨስተር" የገበያ ጉድለት ባለባቸውና የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በገበያው ጉድለት ምክንያት የሚፈጠሩ የአቅርቦት ክፍተቶችን መድፈን ነው። የግሉ ክፍለ ፈቃደኛ ባልሆነባቸው ዘርፎች ላይ ሙዓለ ንዋይ የሚያፈስ ነው። በዋናነት ትኩረቱ ላያደርግ ይችላል። የመጨረሻ አማራጭ ኢንቨስተር መንግሥት፣ በዚህ ምክንያት ሊፈጠር ኢኮኖሚ በአንዳንድ ዘርፎች ላይ (እንደ ትምህርት፣ ጤና የመሳሰሉት) በበቂ ኢንቨስት የሚችልን የአቅርቦት ክፍተት መሙላትን ታሳቢ ያደረገ ነው።

ይለያል። ነገሮችን አስቀድሞ ይመለከታል። በአዳዲስና ባልተዳሰሱ የመልማት ዕድሎች በተቃራኒው ንቁ ወይም ቀዳሚ ወይም የመጀመሪያ አማራጭ ኢንቨስተር መንግሥት፣ከዚህ ላይ በታቀደበት መልኩ ኢንቨስት ያደርጋል። በዚህም አማካኝነት ኢኮኖሚያዊ ሽግግርን ለማምጣት ይተልማል። የመደመር መንግሥት በሦስት ነገሮች የመጀመሪያ አማራጭ ኢንቨስተር ነው። ሀ) መዋቅራዊ ሽግግርን ለማምጣት በሚያስችሉ፣ 2) ውጤታማነታቸው ባልተረጋገጠ እና 3) ከፍተኛ ሥጋት ባለባቸው አዳዲስ ዘርፎች።

የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እንደዚህ ዓይነት የረጅም ጊዜ ምልከታ ባላቸው፣ ውጤታማነታቸው ባልተረጋገጠና ከፍተኛ ሥጋት ባለባቸው ዘርፎች ላይ የመሠማራት ፍላጎትና ዐቅም ላይኖረው ይችላል። በመሆኑም መንግሥት ቀዳሚውን ሥጋት ተቀብሎ ኢንቨስት ያደርጋል። ከዚያም የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍበት በር ይከፍታል። በዚህም ኢኮኖሚያዊ ሽግግርን ለመፍጠር በተልዕኮ ይንቀሳቀሳል።

የመንግሥት ኢንቨስትመንቶች አቅጣጫን የማሳየት፣ የማስቀየርና ሽግግርን የመፍጠር ተልዕኮ አላቸው። ስለሆነም ባልተዳሰሱ አዲስ ዘርፎች ላይ የሚደረጉ ናቸው። የረጅም ጊዜ ግብን ያነግባሉ። የኢኮኖሚውን ፍሰት አቅጣጫ ያመላክታሉ። ይህንንም መሠረት አድርገው ሽግግርን የሚፈጥር ከፍ ያለ ለውጥ የሚያመጡ መሆን አለባቸው። በመሆኑም

CS CamScanner

የመደመር መንግሥት የኢኮኖሚውን ፍሰት አቅጣጫ የሚያመለክት ወይም የሚቀይር ቀዳሚ ኢንቨስትመንት ያከናውናል። ይህ ቀዳሚ ኢንቨስትመንት በአዳዲስ ሐሳቦች ላይና ባልለሙ ዘርፎች ላይ የሚደረግ ነው። ስለሆነም መላውን ኢኮኖሚ አቅጣጫ በማስያዝ ረገድ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

እነዚህ የንግሥት ቀዳሚ ኢንስትመንቶች የአዲስ ዕይታና ከፍ ያለ ምናብ ውልደ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ለማምጣት እንዲህ ዓይነት ትላልቅና አዲስ ዕይታ ያላቸው ናቸው። ሀብት የሚፈጥሩ ከመሆን ባሻገር አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ይቀርጻሉ፣ ይቀይራሉ። ኢንስስትመንቶች ወሳኞች ናቸው። ኢንቨስትመንቶች ባልተዳሰስና ሽማማርን በሚፈጥሩ እንዲሁም የረጅም ጊዜ ግብና ምልከታ ባላቸው ዘርፎች ላይ ይከናወናሉ። እስኪ የመጀመር መንግሥት ኢንቨስትመንቶች ለአንድ ሀገር ፈጣን ዕድገት ወሳኙን መሠረት የሚጥሉና ትልቅ አስተዋጽዖ ያላቸው ናቸው። መንግሥት ይሄንን አይተካ ሚና በብቃት መወጣት ሲችልና ከሌሎች ተዋንያን ጋር ውጤታማ መስተጋብር ሲፈጥር፤ ሥርዓታዊ ፍጥነት፣ አለፍ ሲልም ከፍታን ያረጋግጣል"።

የዳበረ የግል ዘርፍ ባለበት ሁኔታ የመንግሥት ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ እጅግ ወሳኝነት አለው። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ጠንካራ የግል ባለ ሀብቶች ባሉባቸው ሀገራት ጭምር መንግሥት እጅግ ወሳኝ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እንዲመጣ ሚና ይጫወታል። በመሆኑም በመንግሥት ሚና ዙሪያ የሚኖረው ክርክር ባለፉት ዓመታት እንደነበረው “የኢኮኖሚው ዋነኛ የዕድገት አንቀሳቃሽ የነበረው የመንግሥት ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም?' የሚል አይደለም። የመንግሥት ኢንቨስትመንት ምን ላይ መሆን አለበት? የከዚህ ቀደሙ ጉድለቱስ ምን ነበር? የሚል ነው። መንግሥት በሀገራችን ኢኮኖሚ ውስጥ ከየትኞቹም ተዋንያን በላይ የተሻለ ልምድና ዐቅም አለው። የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ገና በአነስተኛ ደረጃ ባለበት ሁኔታ ይህ የመንግሥት ልምድና ዐቅም የምናስበውን ፈጣን ለውጥና ሽግግር ለማረጋገጥ ትልቅ ወረት ነው።

ለዘመናት አብረውን የኖሩ ዐቅሞቻችንን ተጠቅመን፤ ሀብትን ለመፍጠርና ውስጥ የኢትዮጵያውያንን ተድላና ምቾት ለማረጋገጥ፣ የመደመር መንግሥት በሥርዓት ሊዳብር ይገባል። ዕሴትን ለመፍጠርና በፍጥነት የብልጽግና ክምችታችንን እንድናሳድግ የመደመር መንግሥት ትልቅ ሚና አለው። የመደመር መንግሥት በአዳዲስ ፈጠራዎች ላይ ያተኩራል። በፍጥነት ያስባል። ያሰበውንም በተግባር ላይ ያውላል። የጀመረውን ይጨርሳል። አዲስ ምልከታና ዕይታ፣ ፈጠራና የረጅም ጊዜ ግብ የመደመር መንግሥት በቶሎ የኢንቨስትመንት ባሕርያት ናቸው። በሥራው ሁሉ ተወዳዳሪ መንግሥት ነው።

ለምሳሌ የእንጦጦ ተራራና ጫካ ለዘመናት ነበሩ። እነዚያን ጫካዎች ቅጠል የሚለቅሙ .

ያሰበው የለም። ታዋቂው አሜሪካዊ የኮምፒውተር ሳይንቲስት አላን ካይ እንዳለው፣ “ስለ ከዚያ ውጭ በዋና ከተማ አጠገብ እንደሚገኝ ተራራና ጫካ አድርጎ በኢንቨስትመንት ዓይን ነገ ለመተንበይ የተሻለው መንገድ ነገን ራሱን መፍጠር ነው”። እንጦጦ ነገን የፈጠርንበት ቦታ ነው።

የእንጦጦ ፓርክ ልማት በአራት መንገዶች የተካሄደ ነው። የመጀመሪያው፥ ነባር ዐቅምን ማወቅ ነው። የእንጦጦ ተራራ ነበረ። በውስጡ ያሉት የውኃ አካላትም ሲፈሱ ነበሩ:: ቢያንስ የአዲስ አበባ ከተማ ከተቆረቆረችበት ዘመን አንሥቶ ይህ ሀብት ለመንግሥት ቅርብ ነበረ። ሁለተኛው፥ በነባሩ ዐቅም ላይ ዕሴት መጨመር ነው። በደን በተሞላው የእንጦጦ ተራራ ላይ ከዚህ በፊት ያልነበረ የመንገድ፣ የቴሌና የመብራት መሠረተ ልማቶች፣ የንግድ ተቋማት፣ የመዝናኛ ቦታዎች፣ የሥዕል ጋለሪ፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች፣ ወዘተ. ተገነቡ። እንጦጦንም ከእንጨት መልቀሚያ ደንነት ወደ መዝናኛና ወደ ሕዝብ መገናኛ ሥፍራ ቀየረው። የሀብት ማፍሪያ ማዕከልም አደረገው።

ሦስተኛው፥ የግሉንና የመንግሥትን ትብብር መፍጠር ነው። እንጦጦን ያለሙት መንግሥት እና የግሉ ዘርፍ በመቀናጀት ነው። መንግሥት በመሠረተ ልማት ተሠማርቷል። የግሉ ዘርፍ ደግሞ በንግድ ሥራዎች ተሠማርቶ ሀብት አፍርቷል።

CamScanner

አራተኛው፥ የአካባቢ ጥበቃን የአካባቢ ልማትን ማስተሣሠር ነው። በአካባቢው የሚከናወነው ልማት የእንጦጦን አረንጓዴ ሥፍራ ከመጠበቅ ጋር የተሣሠረ ነው። ባሕር ዛፍን በሀገር በቀል ዛፎች ቀስ በቀስ ለመተካትም እየተሠራ ይገኛል። በመንግሥት ቀዳሚ ኢንቨስትመንት የለማው የእንጦጦ ፓርክ፤ ለብዙዎች ሥራ ዕድልና ከፍተኛ ሀብት የፈጠረ የአዲስ ምልከታና ምናብ ውጤት ነው።

የመደመር መንግሥት የኢኮኖሚ ተሳትፎ አንዱ ወሳኝ ግብ ገበያን መፍጠር እንደመሆኑ፣ የመደመር መንግሥት ገበያ መር አካሄድ የሚፈጥራቸውን አሉታዊ ተጽዕኖዎችንም ያርማል። የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንትም ያደርጋል። ከፍተት ባለባቸው ዘርፎች ላይ በመሠማራት በማሻሻል፣ ገበያን ያነቃቃል። ከዚህም በተጨማሪ የሚመረቱ ምርቶችንና የሚመረቱበትን መንገድ ተፈላጊውን ውጤት በሚያመጣ መልኩ ገበያ የመፍጠር ሚናን ይጫወታል።

ሀብት መፍጠር እንዲሁም ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ የሚቻለውም ገበያን መፍጠርና ገበያውን እያሰፉ መሄድ ሲቻል ነው። ገበያው ባልሰፋና ሀብት ባልተፈጠረ ቁጥር የግሉ ዘርፍ ትርፍን የማሳደግ ዓላማ ሀብትን ወደ መቀራመት ያደጋል። ይሄንንም ተከትሎ ገበያው የአካታችነትና የፍትሐዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ ይነሣበታል። ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥም ተግዳሮት በሰፊው ይገጥመዋል።

ገበያ መፍጠር የምርትና የአገልግሎት ፍላጎትና አቅርቦት መፍጠር ነው። ፍላጎትን ተከትሎ ከሚመጣ የአቅርቦት ለውጥ፣ አልያም አቅርቦትን ተከትሎ ከሚኖር የፍላጎት ዕድገት ጋር የሚያያዝ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የአዳዲስ ምርቶችና አዳዲስ ገዢዎች መፈጠርንም ያካትታል። የአንድ ሀገር የገበያ መጠን መስፋትና ዕድገት በሀገሪቱና በሀገሪቱ የንግድ አጋሮች ዘንድ ያሉ አጠቃላይ ፍላጎት(ገዢዎች) እና አጠቃላይ አቅርቦት(ሻጮች፣ የሚያቀርቡት ምርትና አገልግሎት) ዕድገት ወይም መስፋፋት ነው። የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነትም የሚረጋገጠው አዳዲስ ገበያዎችን ለመፍጠር ሲቻል ነው። የኢኮኖሚ ጤናማነትም በዚህ በአቅርቦትና ፍላጎት መጣጣም ላይ የተመሠረተ ነው።

ገበያን መፍጠር በፈጠራ ዐቅምና በፍጥነት ላይ የተመሠረተ ነው። ለዚህም በየጊዜው ተለዋዋጭ በሆነ ከባቢ ውስጥ የሚለዋወጥ ፍላጎትና አቅርቦትን መገንዘብን ይፈልጋል። መተንበይና በፈጠራ ታግዞ አዳዲስ ገበያዎችን መፍጠር ይገባል። ፈጠራና ፍጥነት የምርት ዕድገት በመጨመር ገበያን ለመፍጠር የሚያስችል የተደራሽነትና የተወዳዳሪነት ዐቅምን ያጠናክራል"።

ከሀገራችን መሠረታዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መካከል አንዱ ያልዳበረ ገበያ ነው። ገበያው በዓይነትም ሆነ በብዛት የሚያቀርበው ምርት አናሳ ነው። በሌላ በኩል የመንግሥት መሠረተ ልማትን በማስፋፋትና ሜጋ ፕሮጀክቶችን በመተግበር ፍላጎት እንዲጨምር የማድረግ ጥረት ውጤቱ ከአቅርቦት ዕድገቱ ጋር አልተጣጣመም። በዚህም ምክንያት ከለውጡ በፊት የነበረው በልማታዊ መንግሥት አማካኝነት የሚመዘገብ ዕድገት ቀጣይነቱ ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ነበር።

በመሆኑም የዕድገቱን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ያሉትን ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ጥያቄዎችን መመለስ ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ አቅርቦትን የሚያሳድግና ምርታማነትን የሚያረጋግጡ ሥራዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ተገቢ ነው። በመሆኑም መንግስት ገበያውን በተዋንያን ቁጥርና ተሳትፎ፣ በሚመረት ምርት ዓይነትና ብዛት ማሳደግ የሚያስችል ሚና ሊኖረው ይገባል።

ለምሳሌ በሀገራችን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሁለት ነገሮች የተነሣ የምርት እድገት ጨምሯል። በግብርናው ዘርፍ የታየው የምርት ሂደት ለውጥ አንዱ ነው። እኔ ዐቅሞችን መጠቀማችን ደግሞ ሌላው ነው። ይህ አዲስ መንገድ በአንድ በኩል ሁኔታውን ተከትሎ የደረሰውን የምርት አቅርቦት እጥረት ጫና ለመቋቋም አሉ በኩል የግብርናውን መዘመን ተከትሎ ከማሽን ጥገናና ከተለያዩ የግብርና አቅርቦት ጋር ተያይዞ ተጨማሪ የሥራ ዕድሎች ተፈጥረዋል። ይሄም የተፈጠረ

CS CamScanner

በአጠቃላይ የምርት ሂደት ለውጥ በማምጣት ነው። ሁለተኛው ደግሞ የመዋቅራዊ ለመጠቀም በሚያስችል ፈጠራ ምክንያት ነው።

በአጠቃላይ ገበያው በራሱ ቀጣይነት ያለው ፍትሐዊና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ መንግሥት ገበያውን እነዚህን ግቦች ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ መቅረት አለበት። ይህ የመንግሥት አካሄድ ገበያው ውስጥ ችግር ከተፈጠረ በኋላ የሚያ የገበያ ጉድለትን በመለየት ለመሙላት የሚንቀሳቀስ አይደለም። ለገበያው የሚያስቀምጥና የታለመለትን ግብ ለመምታት በሚያስችል መልኩ የሚቀርጽ ንቁ ኢንቨስተር ነው።

## 5.7. መዋቅራዊ ሽግግርን መምራት

ትናንት ላይ ቆሞ የቀረና በመደመር መንግሥት መዋቅራዊ መሻሻል ያላሳየ ሀገር መሠረታዊ ፍላጎቶችን በሟሟላት አዙሪት የተጠመደና የብልጽግና በር የተቆለፈበት ነው። ዕድገትና ብልጽግናን ቀጣይና ዘላቂ በሆነ መልኩ ለመምራት ውጤታማ መዋቅራዊ ሽግግር ማድረግ ያስፈልጋል።

ይሄንን ለማሳካት የኢኮኖሚውን ዋና መሠረት እንደ ግብርና ካሉ መሠረታዊ ዘርፎት በፍጥነት ወደ ዲጂታል ቴክኖሎጂን ወደሚጠቀም ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ማሽን የኢንዱስትሪ ልማትን ወደሚደግፍ የአገልግሎት ዘርፍ ማሸጋገር ይገባል። በብዝኃ ዘርፍ ዕይታ ማዋቀር ያስፈልጋል። በእያንዳንዱም ዘርፍ መሻሻሎችን፤ ምርታማነተንና ተወዳዳሪነትን ማምጣት ተገቢ ነው። እንዲሁም በዓለም አቀፍ ንግድ ውስጥ በቴክኖሎጂና በዘመናዊነት ተኮር ዘርፎች ላይ ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል።

ከዚህም በተጨማሪ የአመራረት ሂደትና የግብአት አጠቃቀም ላይም ፈጠራ ላይ ያተኮሩ መሠረታዊ ለውጦችን ማምጣት ይጠይቃል። ይህንን ዓይነት መዋቅራዊ ሽግግርን በውጤታማነት ለመምራት ፈጠራና ፍጥነትን ማዕከል ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይሄንንም በተጠናና በታቀደ መልኩ ለመምራት የመንግሥት ሚና እጅግ አስፈላጊ ነው።

በዘመናዊው ዓለም የሀገራት ኢኮኖሚ ከቀን ወደ ቀን የበለጠ እየተሣሠረና እየተሠናሠለ መጥቷል። ከአዲሱ የዲጂታል አብዮት ጋር ተደምሮ መንግሥት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ሚና እንደገና እንዲፈትሽ የሚያስገድድ ሆኗል። በዚህም መንግሥት አዳዲስ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሥምሪት ዘርፎችን በመፍጠር፣ የሀገርን የምርት ዐቅም የማሳደግና መዋቅራዊ ሽግግርን የመምራት ከፍተኛ ሚና ሊጫወት ይገባል። በዚህም አዳዲስ ምርት ከማስተዋወቅ ጀምሮ እስከ ምርምርና ፈጠራ ሂደት ትልቅ ሚና አለው ማለት ነው።

በሀገራችን የግል ዘርፉ እንቅስቃሴ በአብዛኛው ከአምራች ዘርፍ ይልቅ በቶሎ ትርፍ የሚሰጡ ቀላልና ዕሴት የማይጨምሩ ዘርፎች ላይ ያተኮረ ነው። ቀጣይነት ባላቸውና የላቀ ዕድገት ለማምጣት በሚያስችሉ ዘርፎች ላይ በመሳተፍ በዘርፉ ዐቅም አላጎለበተም። ያም በተለይም ያሉንን ዕምቅ ዐቅሞች ለመጠቀም በሚያስችሉ አዳዲስ ዘርፎች ላይ ለመሠማራት አልተዘጋጀም። የተጠና ሥጋትን በተገቢው መንገድ የማስተናገድ የረጅም ጊዜ ምልከታ የለውም። ባልተለመደና ውጤታማነቱ ባልተረጋገጠ ዘርፍ ላይ ለመሠማራት አይደፍርም። በመሆኑም፣ የግል ዘርፉ መዋቅራዊ ሽግግርን በሚያሣልጡ ዘርፎች ላይ እንዲሠማራ ማበረታታትና መደገፍ አንዱ የመደመር መንግሥት ተግባር ነው። ለዚህም ሥጋትን ከመጋራት ጀምሮ በተለያዩ ማሕቀፎች ለማገዝ በትኩረት መሠራት አለበት።

በመደመር መንግሥት ዕሳቤ፣ መንግሥት ንቁ ኢንቨስተር በመሆን በራሱ ስሌት ዘለቄታዊ አትራፊነታቸውን ተመልክቶ የሚሠማራባቸው ክንዋኔዎችመኖራቸው ግልጽ ነው። እነዚህን ክንዋኔዎች የግል ዘርፉ በሂደት ባለቤት እንዲሆን ማንቃትና ማብቃት ይጠበቅበታል።

ሀገራችን ከግብርና መር ኢኮኖሚ በፈጠራና በፍጥነት ወደ ዕውቀት ኢኮኖሚ ሽግግር ለማድረግ እየሠራች ነው። እርሱም በየደረጃው የራሱ የሆነ የሽግግር ስልት ያስፈልገዋል። ይህንን ሽግግር በቀዳሚነት የመመርመር፣ የመተንበይ፣ የማቀድና

CS CamScanner

የመተግበር የባለቤትነት ተዋንያን ሥራ የመደመር መንግሥት ሚና ነው። በተጨማሪም የግል ዘርፉና የሌሎች ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ አስፈላጊ ነው። እነዚህን አስተባብሮ ሽግግርን መምራት፣ በየጊዜው የሁኔታ ግምገማ በማድረግ የሽግግር ስልትን መከለስና አስፈላጊውን ማስተካከያ ማድረግ፣ የመደመር መንግሥት ሚና ይሆናል።

በአጠቃላይ በኢኮኖሚ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት መንግሥት የሚጠበቁበት ተግባራት አሉ። የምርት ስብጥርንና ብዝኃነትን ማሳደግ፤ የተመረጡና በጥናት ላይ የተመሠረቱ እንቅስቃሴዎችን በፖሊሲና በአሠራር መምራት፣ እንዲሁም ባልተለመዱ ዘርፎች ቀድሞ ገብቶ ኢንቨስት ማድረግ ናቸው።

የመደመር መንግሥት ቀጣይነት ባለው ሁኔታ አዳዲስ የመበልጸግ ዐቅሞችንና ዕድሎችን ለመጠቀም የሚያስችል ሰፊ የኢንዱስትሪያዊ ፖሊሲን ይከተላል። በመንግሥት የሚመራ ሰፊ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ ሀገራት ያላቸውን የመበልጸግ ዕምቅ ዐቅምና በየዘርፉ ያሉ የመልማት ዕድሎችን ለመጠቀም ያስችላል። በሌላ በኩል ደግሞ በተለዋዋጭ ዓለም የሚፈጠሩ የመበልጸግ ዕድሎችን ለመጠቀምና የሚፈጠሩ ጫናዎችን ለመቋቋም እገዛ ያደርጋል። ይህ አካሄድ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ የመልማት ዕድሎችና ዐቅሞችን በመመልከትና ኢንቨስት በማድረግ የሀብት ምንጭን የሚያሰፋና ቀጣይነት ያለውን ዕድገት የሚፈጥር ነው። ከዚህም በላይ ፈጣን መዋቅራዊ ሽግግርን ለማምጣት የሚያስችልና ኢኮኖሚያዊ አይበገሬነትን የሚፈጥር ነው።

እንዲህ ዓይነት ብዝኃ ዘርፍ ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ተራ በተራ ዘርፎችን በማልማት ከሚደረግ አዝጋሚ መዋቅራዊ ሽግግርና የዕድገት ሂደት ይለያል። ፈጣን የኢኮኖሚ ለውጥ በማምጣት በአጠረ ጊዜ ከኋላ ቀርነት ለመውጣት ያስችላል።

ከኋላ ቀር ኢኮኖሚ ወደ ዕውቀት መር ኢኮኖሚ ሽግግር ለማድረግ ዐቅም ይሰጣል። ከዚህም በተጨማሪ ሰፊ የሀብት ምንጭ በመፍጠር በአጠረ ጊዜ ብዙ ሕዝብን ከድህነት ለማውጣት ያስችላል። ሰፊ የሀብት መሠረት ያለው ኢኮኖሚ ጥንካሬው ከፍ ያለ ነው። አማራጭ የሀብት ምንጮች ስላሉት የሚፈጠሩ አደጋዎችንና ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም ይችላል።

በሀገራችን ኮሮና ከተከሠተበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ዓመታት የተፈጠሩ የኢኮኖሚ ጫናዎችን ተቋቁመን ዕድገት እንድናስመዘግብ የተለያዩ ዘርፎች አስተዋጽዖ አድርገዋል። ለምሳሌ በአንዱ ዓመት የማዕድን ዘርፍ ዕድገት ተቀዛቅዞ ነበር። በሌላኛው ዓመት ደግሞ የአገልግሎት ዘርፍ ዕድገት ተዳከመ። በሌላኛውም ዓመት ሌሎች ዘርፎች የመቀዛቀዝ ዕጣ ገጥሟቸው ነበር። በዚህ ጊዜ የግብርናው ዘርፍ ለኢኮኖሚ ዕድገታችን ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል። ይሄም የሚደርሱ ጫናዎችን በአማራጭ የዕድገት ምንጮች አማካኝነት ለመቋቋም የሚያስችል ስልት ነው። ሲጠቃለል ሰፊ የኢንዱስትሪያዊ ፖሊሲ ኢኮኖሚያዊ ሽግግርን ያፋጥናል። ሰፊ የሀብት ምንጭ በመፍጠር ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ይፈጥራል። ከዚህም ባሻገር የኢኮኖሚ ተጋላጭነትን በመቀነስ አይበገሬነትን ለመፍጠር ያስችላል።

## 5.8. አደጋን የሚቋቋም አይበገሬ ኢኮኖሚ መገንባት

አንዱና ዋነኛው የመንግሥት ሚና በአደጋ ጊዜም ይሁን በማንኛውም ወቅት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥበቃና ደኅንነት ማረጋገጥ ነው። የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ለውጭ ውድድር መከፈትና ከዓለም ጋር ያለው መስተጋብር መጨመር አለበት። ተዘግቶ የሚያድግ ኢኮኖሚ የለም። ከዚህ ጋር ግን ተያይዞ የሚመጣ ፈተና አለ። በተለይ በድኻው የማኅበረሰብ ክፍል ላይ የሚደርስ አደጋና የሥጋት ተጋላጭነት ይፈጠራል። ይሄንን ለመቀነስና ለመቋቋም የመንግሥት ሚና ከፍ እንዲል ይጠበቃል። በሌላ በኩል ደግሞ የተፈጥሮም ይሁን ሰው ሠራሽ አደጋዎች ሲያጋጥሙ መቋቋምና በፍጥነት ማገገም የሚችል ኢኮኖሚ መገንባት ወሳኝ ነው:

CS CamScanner

የማይበገር (Resilient) ኢኮኖሚ መገንባት ብዙ ዓምዶች አሉት። አደጋን አስቀድሞ አይቶ ማስወገድ ወይም መከላከል አንዱ ነው። አደጋው ከመጣም አደጋውን ተቋቁሞ ማሳለፍ ሌላው ነው። አደጋው ጉዳት ካደረሰም በቶሎ ለማገገም የሚችል ኢኮኖሚን መገንባት ደግሞ ሌላው የማይበገር ኢኮኖሚ ጠባይ ነው።

የመደመር መንግሥት ኢኮኖሚውን የሚፈትኑ አደጋዎችን ማስጠም የሚችል ነው። ተለዋዋጭ ነገሮችን ይላመዳል፣ እንዲሁም ከአደጋ ቶሎ የሚያገግም ኢኮኖሚ መገንባት ትልቁ ትኩረቱና መገለጫው ነው።

የዘርፍ ብዝኃነትና ፈጠራ ኢኮኖሚው ለተለዋዋጭ ሁኔታዎች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚችልበትን ከባቢ ያጎለብታሉ። የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባትም መሠረት ይጥላሉ። የዘርፍ ብዝኃነት መኖር ኢኮኖሚው በየትኛውም ዘርፍ ላይ ያለውን ጥገኝነት ይቀንስለታል።

ከዘርፍ ተኮር የኢኮኖሚ ተግዳሮቶችና ውድቀቶች ጋር ተያይዘው የሚመጡ አደጋዎች በኢኮኖሚው ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ ለመቀነስ ይረዳል።

ፈጠራ ደግሞ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የንግድ ሞዴሎችን መላመድን በአዳጊ ገበያዎች (Emerging Markets) ውስጥ የዕድገት ዕድሎችን ይፈጥራል። ከ የማይበገር ኢኮኖሚን ከመገንባት አንጻር ችግሮችን የመቋቋም ዐቅምን በመጨመር ሚና ይጫወታል።

በሌላ በኩል ደግሞ የመሠረተ ልማት መስፋፋት ሥራ ያለመስተጓጎል እ ከሚጫወተው ወሳኝ የዕለት ተዕለት ሚና የሚበልጥ ሚናም አለው። በአደጋ ጊዜ አ በፍጥነት ማገገም እንዲችል ያስችለዋል። በዚህም የተነሣ የመደመር መንግሥት ከሚሰጣቸው ልማቶች ዋነኛው ነው። መሠረተ ልማት ሲባል ቁሳዊ መሠረተ ልምዓ ስስ መሠረተ ልማቶችን የሚያካትት ነው። ከስስ መሠረተ ልማቶች አንዱ የመን ልማት በተለዋዋጭ ሁኔታዎች ውስጥ በፍጥነት መላመድ እንድንችል ዐቅም ይ አስተዳደርን ግልጽና ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ አድርጎ መገንባት ነው። ይህ ስስ ማኅበረሰቡን በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ያሳትፋል። ማኅበራዊ ትሥሥርን ያ የጋራ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ያስችላል። አገልጋይ የመንግሥት አስተዳደር የመደመር መንግሥት አንዱ መገለጫ ነው።

የመደመር መንግሥት በከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጣሪ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ከመሠ በላይ ሚናው ያልፋል። የግል ዘርፉን ማብቃትና የማይበገር ኢኮኖሚ የመገንባት ዋነኛ ተዋንያን እንዲሆኑ ማስቻልም ይጠበቅበታል። እንደዚያም ሲባል የግል ዘርፉ ብ ዋነኛ ባለቤት ከመሆን በዘለለ የማይበገር ኢኮኖሚ ከመገንባት አንጻር ለውጥን በግ ረገድም ከፍተኛ ሚና መጫወት አለበት ማለት ነው።

የገበያ መዋዠቅን የሚቋቋሙ አካሄዶችን መተግበርም ይጠበቅበታል። ቴክኖሎጂዎችን በመታጠቅ ምርታማነታቸውን ማሳደግ አለባቸው ተ ሁኔታዎች ፈጣን ምላሽ የመስጠት ዐቅማቸውን ማዳበርም ይጠበቅባቸዋል። በተ ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን ከማገዝ አንጻር በማኅበራዊ ድጋፍ ሥራዎች ላይ ያስፈልጋቸዋል።

ማኅበረሰቡም የማይበገር ኢኮኖሚ ለመገንባት ከፍተኛ ሚና አለው። የትብብርና ባህልን በማጎልበት ትልቅ በጎ ተጽዕኖ ማሳረፍ ይችላል። ግለሰቦች እንደ ግለሰብ ካ አስተዋጽዖ በተጨማሪ፤ ቡድኖችን በመቀላቀል ትልቅ ዐቅም መፍጠር ይቻላ ቡድኖች ደግሞ ወደ ማኅበረሰብነት (Community) ማደግ ይችላሉ። በዚህም በተናጠል ሊያሳድሩት ከሚችሉት በጎ ተጽዕኖ በተሻለ ደረጃ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችል ጠንካራ ኅብረት መፍጠር ይችላሉ።

ጠንካራ ኅብረት ኅብረተሰቡ በተሣለጠ የመረጃ ፍሰት በመንግሥት ውሳኔዎች ላይ በንቃት እንዲሳተፍ ያደርገዋል። ይህ በጎ ተጽዕኖ መንግሥት ለኢኮኖሚው መረጋጋት አስፈላጊ በችግር ወቅትም እንዲህ ዓይነቱ ጠንካራ ኅብረት ብዙ እገዛ ሊያደርግ ይችላል። በመሆኑም የሆኑ ውሳኔዎች ሲወስን፤ ማኅበረሰቡን ታሳቢ አድርጎ እንዲወሰን ያደርገዋል። በአደጋና የመደመር

CS CamScanner

መንግሥት አንዱ መገለጫ ጠንካራ ማኅበረሰባዊ ኅብረቶች በየአካባቢው እንዲመሠረቱ ማድረግ ነው። እነዚህ ኅብረቶች በሚያደርጉት ዘላቂ ተሳትፎ፣ መንግሥትን እንዲያግዙና የማይበገር ኢኮኖሚ በመገንባት ረገድ ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል ነው።

የማይበገር ኢኮኖሚን የመገንባት ጉዳይ የመደመር መንግሥት የአንበሳ ድርሻውን ወስዶ የሚሠራበት ጉዳይ ቢሆንም፤ የመንግሥት ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የሌሎችን ተሳትፎም የሚፈልግ ነው። ማኅበረሰቡ፣ የግል ዘርፉና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ጭምር መሳተፍ አለባቸው። የመደመር መንግሥት የራሱን ድርሻ ከመወጣት ባለፈ ሌሎቹን አካላት ለማብቃት ይሠራል። በመካከላቸው የሚኖረውን ቅንጅት ያሣልጣል። ምቹ ሁኔታን በመፍጠርም የማይበገር ኢኮኖሚ እንዲገነባ ያደርጋል።

በአጠቃላይ የመደመር መንግሥት ሀገራችን ካለችበት ኋላ ቀርነት ለማላቀቅ ወሳኝ መፍትሔ ሆኖ ቀርቧል። የመደመር መንግሥት አርቆ የሚያይ ልዩ ምናብ ያለው፣ ከፍተኛ የመፈጸም ዐቅም የተላበሰ፣ የዓለምን ተለዋዋጭነት ለማስተናገድ በእጅጉ ተላማጅ የሆነ ነው። የመደመር መንግሥት በእነዚህ መርሖች እየተመራ፣ ግቡን የግል ዘርፉን በማሳደግ ላይ ያደርጋል። ለዚህም በቅንጅት ይሠራል፤ ንቁ ኢንቨስተር ሆኖ አዳዲስ ገበያን ይፈጥራል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ለውጥን መዋቅራዊ በማድረግ ሽግግሩን ይመራል። እነዚህን ሁሉ በማከናወን የሀገር ኢኮኖሚ የማይበገር እንዲሆን የማጽናት ዐቅም የተላበሰ መንግሥት ነው።

## **5.9.** መሠረታዊ ችግሮችን በድፍረት መፍታት

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መዋቅራዊና አሁናዊ ችግሮች ነበሩበት። በዕዳ ጫና የኅበጠ፤ የውጭ ምንዛሬ እጥረት የገጠመው፤ ባልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች የተሣሠረ፤ የውጭ _ኢንቨስትመንትንና የውጭ ካፒታልን በሚገባ ለመቀበል ያልተዘጋጀ፣ የኢኮኖሚ ሂደት ነበረው። ይሄንን ለመፍታት የመደመር መንግሥት የተጠናና ደፋር ውሳኔ ወስኗል። ይሄም የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ነው።

### 5.9.1 የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ሪፎርም ርምጃዎችና አንድምታው

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፈጣንና ቀጣይ ዕድገት ካስመዘገቡና እያስመዘገቡ ከሚገኙ አዳጊ የዓለም ሀገራት አንዱ ነው። በተለይም ከ2010 እስከ 2016 በነበሩት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ በዓመት 7.3 በመቶ እድገት አሳይቷል። ይሄም በተመሳሳይ ወቅት በአዳጊ ሀገራት ከነበረው አማካይ እድገት በእጥፍ ይበልጣል። በ2016 በጀት ዓመት ኢኮኖሚው በ8.1 በመቶ ያደገ ሲሆን፣ በ2017 ደግሞ ዕድገቱ ወደ 34 በመን በአዳጊ ሀገራት ከነበረው አማካይ ዕድገት በእጥፍ ይበልጣል። በ26 ተገምቷል። ይሄም ኢኮኖሚው በርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ተግዳሮቶች በረት ሰፊ፣ ዘርፈ ብዙ፣ ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለውና ሥጋቶችን የመቋቋም ዐቅሙም የመጣ መሆኑን አመላካች ነው።

ለዚህ ስኬት የብልጽግና መንግሥት የተከተለውና እየተከተለ ያለው የተጠና ኢኮኖሚ ፖሊሲና የሀገሪቱንና የዓለምን ተጨባጭ ሁኔታዎች አገናዝቦ የ በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራሞች የበኩላቸውን አስተዋጽዖ አበርክተዋል።

### **5.9.2.** ከለውጡ በፊት የነበረው የኢኮኖሚ ሁኔታ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት 15 ዓመታት ቀጣይነት ያለውና ፈጣን ዕድገት .. በመንግሥት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ተቋማት ጭምር የተመሰከ ነው። ይሁን እንጂ፣ እስካለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት ድረስ መንግሥት : የነበረው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በ"ልማታዊ መንግሥት" አስተሳሰብ የተቃኘና ለ ዕድገት እምብዛም ትኩረት የማይሰጥ ነበረ። ይሄውም

CamScanner

የመንግሥትን ጣና " አዋጭነታቸው በሚገባ ባልተመረመሩ ሜጋ ፕሮጀክቶች ላይ ያተኮረ፤ የማስፈጀ ሳይጤን በሚካሄዱ የመሠረተ ልማት የኢንቨስትመንት ሞዴሎች ላይ የተመረኮዘ ነው።

እነዚህ የመሠረተ ልማት ኢንቨስትመንቶች ከሚጠይቁት መጠነ ሰፊ ውስጣዊ የ የገንዘብ ሀብት እንዲሁም ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ከተሰጠው አናሳ ትኩረት የተነሳ ኢኮኖሚው እየተቀዛቀዘና ማክሮ ኢኮኖሚያዊ መዛባቱ እየተባበሰ መጣ በ በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለው ልዩነት አደገ፡ በተለይ መንግሥት ይከተል . ልል የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲዎች የተነሣ የዋጋ ግሽበት ጨመረ።የበጀት ጉድለት የውጭ ዕዳ ጫና በዛ። የውጭ ክፍያ ሚዛን ጉድለት ተባባሰ። የውጭ ቀጥታ ፊ ተቀዛቀዘ። የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችት ተመናመነ። በጥቅሉ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት እየጨመረ መጣ።

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ለግሉ ዘርፍ ዕድገት በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ የግሉ ዘርፍ ለኢኮኖሚው የሚያደርገው አስተዋጽዖ እየተዳከመ፣ ሥራ አጥነት እያደገ፣ የሀብት ድልድል እየተዛባ፣ የገቢ አለመመጣጠን እየጨመረ ሄደ። ልል ከሆኑ የገንዘብና የፊስካል ፖሊሲዎች በተጓዳኝ፣ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓቱ ላለፉት አምስት ዐሠርት ዓመታት ለውጥ ሳይደረግበት የቆየና በጥብቅ አስተዳደራዊ ማሕቀፎች የተጠረነፈ ነበር። ይሄም ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ፍሰትና ግኝት መቀዛቀዝ፣ ለጥቁር ገበያ መስፋፋትና ለንግድ ሚዛን መዛባት የራሱን ተጽዕኖ አሳድሯል።

### 5.9.3. የኢኮኖሚ ሪፎርም አስፈላጊነት

በመሆኑም፣ በ2010 የተካሄደውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ ከላይ የተጠቀሱ በሀገሪቱ ውስጥ ሥር እየሰደዱ የመጡ ውስብስብ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋቶችን ለመቅረፍና መዋቅራዊ፣ ሕጋዊና ተቋማዊ መሰናክሎችን ለማስወገድ፣ እንዲሁም እየተዳከመ የመጣውን የማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማስቀጠል፣ መንግሥት መሠረታዊ ለውጥ የሚያመጣ የሪፎርም ፕሮግራም መቅረጽና መተግበር ወቅቱ የሚጠይቀው ግዴታ ሆነ። ከዚህም የተነሣ መንግሥት በ201 የመጀመሪያውን፣ በ2016 ደግሞ ሁለተኛውን ዙር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም ነድፎ ወደ ሥራ ገብቷል።

### 5.9.4. የኢትዮጵያ የሪፎርም ርምጃዎችና የተገኙ ውጤቶች

የኢትዮጵያ መንግሥት ከንጉሡ ጊዜ አንሥቶ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ የኢኮኖሚ ዕቅዶችን በማውጣት ሥራ ላይ ማዋሉ ይታወቃል። ለምሳሌ፣ ሁለት ዙር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራሞች ከመካሄዳቸው በፊት ሁለት ዙር የሦስት ዓመታት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች ተግባራዊ ሆነዋል። እነዚህም ዕቅዶች በተለያዩ ርእዮተ ዓለማዊ ዕሳቤዎችና የኢኮኖሚ ሞዴሎች የተቃኙ ነበሩ። በአብዛኞቹ አዎንታዊ ውጤቶች የተመዘገቡባቸውና ኢኮኖሚው ለሁለት ዐሠርት ዓመታት በአማካይ 10 በመቶ ያህል ዕድገት ያሳየባቸው ነበሩ።

ይሁን እንጂ፣ ዕቅዶቹ እያደር በኢኮኖሚ አወቃቀርና አደረጃጀት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ዐቅም አልነበራቸውም። በመሆኑም፣ በሂደት የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ግለት እየቀነሰ፣ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ መዛባት እየተባባሰ፣ ሄደ። ይሄንኑ ሂደት ሊቀለብስ የሚችል አዲስ ዕቅድ የመንደፍ አስፈላጊነትም እየጎላ መጣ።

ሀ) የመጀመሪያው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርምና ውጤቱ

በ2010 የተከሠተውን የመንግሥት አመራር ለውጥ ተከትሎ የሀገሪቱን የዕድገት ደረጃና ተጨባጭ የኢኮኖሚ አደረጃጀት እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም በ2011 ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ ገባ።

CamScanner

የዚህ ዕቅድ መሠረታዊ ዓላማ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ መረጋጋትን ለማስፈን፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማረጋገጥ፣ ምርትና ምርታማነትን ለማዳበር፣ የሥራ ለማስፋፋት፣ በኢኮኖሚ ውስጥ የግሉንና የመንግሥትን ሚናዎች የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጮችን ለማስፋትና ምቹ የኢንቨስትመንት ከባቢ ለመጥፎ በጥቅሉ፣ ዕቅዱ ሁለንተናዊ፣ መዋቅራዊና ዘርፋዊ ገጽታዎች ያሉት ነበር።

የመጀመሪያው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም በርካታ አስገኝቷል። የሪፎርም ፕሮግራሙ በኮቪድ ወረርሽኝ፣ በድርቅና በፖለቲካ አለም እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተከሠቱ የሰላም መደፍረሶች ተግዳሮቶች ቢገጥሙትም፣ ኢኮኖሚው ከ2010 እስከ 2015 ባሉ አምስት በአማካይ በ7 በመቶ ያህል ዕድገት አሳይቷል። በዚህም ሀገራችን ፈጣን ዕድገት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያስቀመጣቸውን ዘላቂ የልማት ግቦች የማነ ካላቸው ሀገራት ተርታ መሰለፍ ችላለች። በምሥራቅ አፍሪካ አንደኛ ደረጃ ያለው ኢኮኖሚ ገንባታለች።

የፋይናንስ ዘርፉን በተመለከተ በሁለንተናዊ መልኩ ዕድገት አሳይቷል። የፋይናን በቁጥርም፣ በቅርንጫፎች ብዛትም፣ በሚሰበስቡት ተቀማጭ ሂሳብም ሆነ በዐ/ ዕድገት አሳይተዋል። እንዲሁም በሚሰጡት ብድር፣ በሚሰበስቡት የብድር በካፒታላቸው፣ በሚያገኙት የተጣራ ትርፍ፣ በከፈቷቸው የሂሳብ አካውንቶችና ብዛት ያስመዘገቡት ዕድገት ከፍተኛ ሆኗል። ከዚህም ባሻገር በማናቸውም መመዘኛ ጤናማና ተወዳዳሪ መሆናቸው ተረጋግጧል።

የመጀመሪያው ምዕራፍ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም ስኬቶች የተመዘገቡበት ቢሆንም፣ በርካታ ተግዳሮቶችም አጋጥመውት ነበር። ከእነዚህም ተግዳሮቶ ለን በሀገር ውስጥ የሰሜኑ ጦርነትና በተለያዩ አካባቢዎች ይካሄዱ የነበሩ ግጭቶ ንብረት ለውጥ ተጠቃሽ ናቸው። ከዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ደግሞ የኮቪድ የሩስያና የዩክሬን ጦርነት፣ የመካከለኛው እስያ አለመረጋጋት፣ የዓለም የሱ : ከዚ_ አለመረጋጋትና ሌሎች ተጽዕኖ አድርገዋል። ከእነዚህም በተጨማሪ በኢኮኖ ኣዎ የሚታዩ መዋቅራዊ፣ ሕጋዊና ተቋማዊ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚረዳ የሪፎ ጤና መዘግየት ሌላው ፈተና ነበር።

ለ/ የሁለተኛው ምዕራፍ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርምና የሚጠበቁ ውጤቶች

ኢኮኖሚው ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመቅረፍና የኢኮኖሚውን ቀጣይ ዕድገት እንዲሁም የሕዝቡን ብልጽግና ለማረጋገጥ፣ ከ2016 እስከ 2018 የሚቆይ ሁለተኛው ምዕራፍ የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ፕሮግራም ጸድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል።

ይህ ሁለተኛው ዙር የሪፎርም ፕሮግራም ቀደም ሲል ያልተጠናቀቁ የሪፎርም አጀንዳዎችን ለማስፈጸም የሚረዳ ነው። በዚህ ረገድ አፋጣኝ ምላሽ የሚያሻቸው ጉዳዮች ተለይተዋል። እነርሱም፣ የዋጋ መረጋጋትን ማስፈንና የውጭ ኢኮኖሚ ኢሚዛናዊነትን (የውጭ ምንዛሪ እጥረትን፣ ዝቅተኛ ዓለም አቀፍ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ ክምችትንና የውጭ ዕዳ ናን) ማስተካከል ሲሆኑ፣ የመካከለኛው ጊዜ ትኩረት ደግሞ በኢኮኖሚው ውስጥ የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ ናቸው።

ከዚህ አኳያ የሪፎርም ፕሮግራሙ በአራት ዐበይት ምሰሶዎች ላይ የቆመ ነው። እነዚህም

ምሰሶዎች:-

1. የማክሮ ኢኮኖሚ መረጋጋትና ዕድገት ማስፈንና ዘመናዊና ጤናማ የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ማሕቀፍ መዘርጋት፤
2. ፈጠራንና ንግድን የሚያበረታታ ምቹ ከባቢ በመፍጠር ተወዳዳሪነትን የሚያሳድግ የኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፍ ማሻሻያ ማድረግ፤
3. ምርትና ምርታማነት የመጨመር ዐቅምን መገንባት፣ እና
4. ጥራት ያለው አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስችል የመንግሥትን ዐቅም መገንባት ናቸው።

CamScanner

በጥቅሉ፣ ሁለተኛው ምዕራፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም በርካታ ፋይዳዎች አሉት። የማሻሻያ ፕሮግራሙ በዋናነት በግሉ ዘርፍ የሚመራ ሁሉን አቀፍና አሳታፊ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያስገኝ፤ የሥራ ዕድል ፈጠራን የሚያበረታታ፤ የዋጋ ግሽበትን ወደ ነጠላ አሐዝ የሚያወርድ፤ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደርን የሚያሻሽል፤ የፋይናንስ ዘርፍ ጤናማነት፣ ዕድገትና ተወዳዳሪነትን የሚያጠናክር፤ የመንግሥት ኢንቨስትመንት ውጤታማነትን የሚያሻሽል፤ የመንግሥት ገቢን የመሰብሰብ ዐቅም የሚያጠናክርና ለንግድና ለኢንቨስትመንት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር፤ ምርትና ምርታማነትን የሚያዳብር፣ በጥቅሉ አካታችና የማይበገር፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ኢኮኖሚ የመገንባት ዓላማ ያነገበ ነው።

ከዚህ አኳያ፣ ሁለተኛው ዙር ሀገር በቀል የሪፎርም ፕሮግራም ከተጀመረ ወዲህ በርካታ አዎንታዊ ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል። የፋይናንስ ዘርፉ እንቅስቃሴና ዕድገት፣ _ ጤናማነት እንዲሁም የፋይናንስ አካታችነት በመልካም ሁኔታ ላይ ይገኛል።

ሐ) የገንዘብ ፖሊሲ ማሕቀፍ ማሻሻያ ርምጃዎችና ውጤቱ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የገንዘብ ፖሊሲውን ማሕቀፍ ለማዘመንና ተግባራዊ ለማድረግ ባወጣው ዕቅድ መሠረት ከሐምሌ 2016 ጀምሮ በወለድ ተመን ላይ ወደተመሠረተ የገንዘብ ፖሊሲ ማሕተፍ ተሸጋግሯል። በዚህ ማሕቀፍ መሠረት ባንኩ የገንዘብና የክሬዲት ሁኔታዎችን ለመወሰን የወሰድ ተመኑን በየጊዜው እንደ አስፈላጊነቱ ከፍ ወይም ዝቅ የሚያደርግ ይሆናል። ባንኩ የወለድ ተመኑን ከፍ የሚያደርገው ጥብቅ የገንዘብ ፖሊሲ እየተገበረ መሆኑን ለማመልከትና የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር ወይም ልል የገንዘብ አቅርቦት ሁኔታ መኖሩን ለማረጋገጥ ነው።

በአንጻሩ፣ የዋጋ ንረት ዝቅተኛ ሲሆን ወይም ሲቀንስ፣ እንዲሁም ጠንከር ያለ የገንዘብና የክሬዲት ዕድገት እንዲኖር የሚገፋፉ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ሲኖሩ የወለድ ተመኑን ዝቅ ያደርጋል ማለት ነው።

ከዚህ አኳያ ባንኩ የፖሊሲ የወለድ ተመኑን ለመጀመሪያ ጊዜ 15 በመቶ እንዲሆን አድርጓል:: ይህ የፖሊሲ ተመን ባሁኑ ወቅት የሚታዩ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ማለትም፣ እየረገበ ያለውን የዋጋ ንረት፣ ዝቅተኛ የመሠረታዊ ገንዘብ ዕድገትና ካለፉት ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ደረጃ እያሽቆለቆለ የመጣውን የባንክ ብድር ዕድገት ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው::

የፖሊሲ ተመኑ ባሁኑ ጊዜ ባንኮች እርስ በርስ ለሚበዳደሩት ብድር ከሚከፍሉት የወሰድ ተመን ጋር የተቀራረበ፣ ነገር ግን፣ ባንኮች ለደንበኞቻቸው በሚሰጧቸው የብድር ዓይነቶች ላይ ከሚያስከፍሉት ወለድ ያነሰ ነው። ይሁን እንጂ፣ ይህ የፖሊሲ ተመን ባንኮች በውድድር ላይ ተመሥርተው ለደንበኞቻቸው በሚሰጡት ብድር ላይ የሚያስከፍሉትን የወለድ መጠን በራሳቸው እንዳይወስኑ የሚከለክል አይደለም። እንደዚሁም አዲሱ የገንዘብ ፖሊሲ ማሕቀፍ ባሁኑ ጊዜ ባንኮች በቁጠባ ተቀማጭ ገንዘብ ላይ በሚከፍሉት 7 በመቶ ወለድ ላይ ለውጥ አላደረገም።

በአዲሱ የገንዘብ ፖሊሲ ማሕቀፍ መሠረት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየሁለት ሳምንት ጨረታ ማካሄድ ጀምሯል። የዚህ ጨረታ ዓላማ እንደሁኔታው ከፋይናንስ ሥርዓቱ ውስጥ ገንዘብ ለመሰብሰብ ወይም ገንዘብ ለመጨመር ነው። ብሔራዊ ባንኩ በባንክ ሥርዓት ውስጥ ያላግባብ የተከማቸ የገንዘብ መጠን አለ ብሎ ሲገምት፣ ትርፉን ገንዘብ ከባንኮች ለመሰብሰብ የሚያስችል ጨረታ ያከናውናል፤ ለሰበሰበው ገንዘብም ለባንኮች 15 በመቶ ዓመታዊ ወለድ ይከፍላል። በአንጻሩ፣ በባንክ ሥርዓት ውስጥ የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥም ብሔራዊ ባንክ 15 በመቶ ዓመታዊ ወለድ በማስከፈል ለባንኮች ተጨማሪ ገንዘብ በጨረታ ይሰጣል።

CamScanner

በጥቅሉ፣ በየሁለት ሳምንቱ የሚካሄድ ቋሚ የሰነዶች ግብይት ጨረታ መኖሩ ባንኮች ያላቸውን የገንዘብ መጠን ለመቆጣጠር የተሻለ አማራጭ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በባንክ ሥርዓት ውስጥ የሚያጋጥመውን ጊዜያዊ ወይም ወቅታዊ የገንዘብ እጥረት ወይም ትርፍ ተቀማጭ ገንዘብ ለመቆጣጠር ይረዳል።

ከአዲሱ የገንዘብ ፖሊሲ ማሕቀፍ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአንድ ቀን _የብድር አገልግሎት(Overnight Lending Facility) እና የአንድ ቀን የተቀማጭ ገንዘብ _ አገልግሎት(Overnight Deposit Facility) እንዲሁም አስቸኳይ የብድር አገልግሎት _ Emergency Loan Assistance) መስጠት ጀምሯል። እነዚህ የአንድ ቀን የብድር ወይም የተቀማጭ አገልግሎቶች ባንኮች በተቀማጭ ገንዘብ፣ በብድር፣ በውጭ ምንዛሪ ወይም በሌላ ምክንያት የሚገጥሟቸውን ያልተጠበቁ ክስተቶች ለማስተካከልና ያላቸውን የገንዘብ ሀብት በተሻለ ሁኔታ ለማስተዳደር የሚጠቅሙ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንኮች እርስ በርስ የሚበዳደሩበትን ሁነኛ የገንዘብ ገበያ ለማካሄድ የሚያስችል የኤሌክትሮኒክ መድረክ አዘጋጅቷል። የዚህ ገበያ መመሥረት ትርፍ ገንዘብ ያላቸው ባንኮች የገንዘብ እጥረት ላጋጠማቸው ባንኮች ማበደር የሚችሉበትን ሁኔታ ይፈጥራል። በመሆኑም፣ ባንኮች ያለ ብሔራዊ ባንክ ጣልቃ ገብነት የገንዘብ እጥረትን ወይም ትርፍ ገንዘብን በዚያው በባንክ ሥርዓት ውስጥ ለማከናወንና በባንክ ሥርዓት ውስጥ ቀልጣፋ፣ ግልጽና አስተማማኝ የገንዘብ አስተዳደር እንዲኖር ዕድል ይሰጣል።

ከዚህ ሌላ፣ በአዲሱ የብሔራዊ ባንክ ዐዋጅ መሠረት የገንዘብ ፖሊሲና የፋይናንስ መረጋጋት ኮሚቴዎችን ማቋቋም የተጀመረ ሲሆን፣ የገንዘብ ፖሊሲ ኮሚቴው በቅርቡ የመጀመሪያውን ስብሰባ በማካሄድ አጠቃላይ የማክሮ ኢኮኖሚና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በማገናዘብ መወሰድ ስላለባቸው የገንዘብ ፖሊሲ ርምጃዎች ምክረ ሐሳብ አቅርቧል።

መ) የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያና ውጤቱ

ሪፎርም ከተካሄደባቸው መስኮች አንዱ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓትን ሥር ነቀል በሆነ መልኩ መለወጥ ነው። ለብዙ ዐሠርት ዓመታት ሲሠራበት የነበረውና ለማክሮ ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት አንዱ ምክንያት ሆኖ የቆየው የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ከሐምሌ ወር 2016 ጀምሮ በገበያ ሥርዓት እንዲመራ ተደርጓል። ይህ ማሻሻያ ኢትዮጵያን ተወዳዳሪ ወደሆነና በገበያ ላይ ወደተመሠረተ የውጭ ምንዛሪ ሥርዓት እንደሚያሸጋግራትና _በኢኮኖሚ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ተንሠራፍቶ የቆየውን የማክሮ ኢኮኖሚ አለመረጋጋትና መዛባት እንደሚያሻሽል ይገመታል። ይህ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ማሻሻያ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሐ ግብር ላይ የተመሠረተና በቀጣይ ወራት ሥራ ላይ ከሚውሉ ሰፊ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች መካከል አንዱ ሲሆን፣ ዋና ግቡ ያለው፣ መሠረተ ሰፊና ሁሉን አሳታፊ የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩን ለማረጋገጥ ይሆናል።

የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ሥርዓት ወደ ገበያ መር ሥርዓት መሸጋገሩ በርካታ ጥሩ ያስገኛል። ለምሳሌ፦

1. የውጭ ምንዛሪ ገቢ በሚያስገኙ ዘርፎች የተሠማሩ ነጋዴዎችን፣ ገበሬዎችና ሀብቶችን ያበረታታል።
2. የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ሀብት በሀገር ውስጥ እንዲቀር ያደርጋል።
3. ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለሚያመርቱ ተኪ ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ያደርጋል።
4. የግሉን ዘርፍ ለመደገፍ የወጡ ሌሎች በርካታ የፖሊሲ ርምጃዎትን ያጠናክል
5. ሀገሪቱ ለውስጥና ለውጭ ኢንቨስተሮች ሳቢና ማራኪ እንድትሆን ያደርጋል

CamScanner

6. በአሁኑ ዐውድ ኢመደበኛነትንና ሕገ ወጥነትን የሚያበረታቱ በርካታ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለመለወጥ ይረዳል።

በጥቅሉ፣ የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው ሥር የሰደደ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቅረፍ፣ ንግድ ተወዳዳሪነትን ለማጎልበት፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለመሳብና የግሉ ዕድገትና አስተዋጽዖ ለማጠናከር የተወሰዱ ሌሎች በርካታ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ ለው ለመደገፍ ያገለግላል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው ቀደም ሲል እንደነበረው የ ምንዛሪ ወደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስተላለፍ ግዴታን ያስቀራል። ከዚህ " የተከለከሉ አንዳንድ ሸቀጦች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ ይፈቅዳል። ባንክ ያልሆኑ የ ምንዛሪ ቢሮዎች እንዲቋቋሙ ፈቃድ ይሰጣል። የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦችን የሚ አስተዳደራዊ ደንቦችን ያሻሽላል። በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች ድ እንደሁኔታው የውጭ ምንዛሪ ሂሳቦችን እንዲከፍቱ ዕድል ይሰጣል። የግሉ ዘርፍ.. ብድር ላይ በሚከፍለው የወለድ መጠን ላይ የተቀመጠውን ገደብ ያነሣል።

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያን ለውጭ ኢንቨስተሮች ክፍት ያደርጋል። በልዩ የኢኮኖሚ ውስጥ ለተሠማሩ ኩባንያዎች ልዩ የውጭ ምንዛሪ መብት ይሰጣል። መንገደኞች በሚይዙት የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ገንዘብ ላይ የተቀመጠውን ገደብ ያላላል።

እነዚህ ሁሉ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያዎች ሲጠቃለሉ፣ ቀጣዩን የኢትዮ የዕድገት ደረጃና ከቀረው የዓለም ሀገራት ጋር ያላትን እያደገ የመጣውን ትሥሥር ለማጠናከር የሚረዱ ናቸው።

ማሻሻያውን ተከትሎ በነበሩት ስድስት ወራት ብቻ በጥቁር ገበያና በባንኮች መካከል ባለው የውጭ ምንዛሪ ተመን መካከል ያለው ልዩነት በከፍተኛ ደረጃ ቀንሷል። የውጭ ምንዛሪ ሐዋላና ከወጪ ንግድ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢም መሻሻል

አሳይቷል። የገቢ ንግድ ውጪ ግን በ4 በመቶ ቀንሷል። ይህም አዝማሚያ ከሪፎርሙ አንጻር የሚጠበቅ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

በአንጻሩ፣ ከውጭ ምንዛሪ ማሻሻያው የተነሣ ቀደም ሲል በመደበኛ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሲሸመቱ የነበሩ የገቢ ሸቀጦች ዋጋ ከፍ ሊል፣ በጊዜያዊነትም የዋጋ ንረት ሊባባስና የመንግሥት የውጭ ዕዳ ክፍያ ወጪ ሊጨምር እንደሚችል ታሳቢ

የተደረገ ቢሆንም፣ " በብር ረገድ የውጭ ዕዳ ክፍያ ከመናሩ በስተቀር የዋጋ ግሽበት የመውደቅ እንጂ የመጨመር አዝማሚያ

አልታየበትም። ይልቁንም የዋጋ ግሽበት ሰኔ ወር 2016 ከነበረበት 19.9 በመቶ በታኅሣሥ ወር 2017 ወደ 17 በመቶ፣ በጥር

ወር 2017 ደግሞ ወደ 15.5 በመቶ ቀንሷል።

ይሄም ባለፉት አምስት ዓመታት ከታየው የዋጋ ግሽበት ዝቅተኛው ሆኖ ተመዝግቧል። ይህም የሆነው በከፊል የምርትና የአገልግሎቶች አቅርቦት በመሻሻሉ፣ መንግሥት ጥብቅ የግንዘብና የፊስካል ፖሊሲ መከተሉን በመቀጠሉና ከማክሮ

ሪፎርሙ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የፋይናንስ ድጋፍ በማሰባሰብ በመቻሉ በውጭ ምንዛሪ ተመን ለውጥ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ለጊዜውም ቢሆን ሊረግብ ችሏል። በለውጡም ምክንያት ከውጭ የሚመጡ አንዳንድ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ የማምረት እንቅስቃሴ ጨምሯል።

በተለይ የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙን ዋና ዋና ዓላማዎችና ግቦች ለማስፈጸም ማለትም የውጭ ምንዛሪ መዛባትን ለማስተካከልና የክፍያ ሚዛንን ለማሻሻል፣ የገንዘብ ፖሊሲ ማሕቀፉን በማዘመን የዋጋ ንረትን ለመቀነስ፣ የውጭ ዕዳ ጫና ለማርገብና የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ፣ የፋይናንስ ዘርፉን ተወዳዳሪነትና ጤናማነት ለማጠናከርና የፋይናንስ አካታችነትን ለማዳበር እንዲሁም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል ዘላቂ፣ አካታችና የማይበገር የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት የሚረዳ የገንዘብ ድጋፍ ከዓለም የገንዘብ ድርጅትና ከዓለም ባንክ እንዲሁም ከሌሎች የልማት አጋሮችና

CS CamScanner

አበዳሪ ድርጅቶች _ ለማሰባሰብ ዕድል ይሰጣል። በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራሙ መሠረት በፕሮግራም | ዘመኑ ቢያንስ 10.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ከልማት አጋሮች የሚገኝ ይሆናል።

የፋይናንስ ዘርፉን ለማረጋጋት በተወሰዱ ርምጃዎች፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የራሱን _ አቀፍ መርሖችና መመዘኛዎችን የተከተሉ የቁጥጥርና የክትትል መመሪያዎችን ተግባራዊ ዋጅና የባንክ ሥራ ዐዋጅን በፓርላማ ከማጸደቅ ባሻገር ዘርፉን የሚመለከቱ ዓለም የማድረግ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ካፒታል የማሳደግና ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጋር የነበረውን የተከማቸ የብድር ዕዳ ወደ መንግሥት የዕዳ ሰነድ በመቀየር እንዲሁም ባንክ በተገኘ የፋይናንስ ድጋፍ የፋይናንስ አቋሙን የማጠናከር ሥራዎች ተሰርተዋል።

የፊስካል ፖሊሲ ማሻሻያን በተመለከተ የመንግሥት ገቢን ማሳደግ፣ የመንግሥት የድጎማ ሥርዓትን ውጤታማ ማድረግ፣ በጡረታ ፈንድ ሥርዓቶች ማሻሻያዎችን ማካሄድ፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ውጤታማና ተወዳዳሪ የመንግሥትን የብድር አስተዳደር ውጤታማነትና ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ የመንግሥት ተጋላጭነት ወደ መካከለኛ ደረጃ ማውረድ፣ የልማት ፋይናንስ አማራጮችን የማሻሻያ ፕሮግራሙ ግቦች ናቸው። ከዚህ አኳያ፣ በመንግሥት በኩል የተቀናጀ እየተደረገ ሲሆን፣ አመርቂ ውጤቶች መታየት ጀምረዋል። የመንግሥት የ ሽግሽግ ለማግኘት የሚደረገው ድርድር ወደ መጨረሻው ምዕራፍ ተሸጋግሯል።

ሠ) የኢኮኖሚ ሪፎርም ማሻሻያ እንድምታዎችና ለብልጽግና ያለው ፋይዳ

ሀገራችን በማካሄድ ላይ ያለችው የማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርም ሁሉን አቀፍ፣ ዘርፈ አካታች ነው። በአግባቡ ከተተገበረ መሠረታዊና ዘላቂ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጥቅም ያስገኛል። ይሄም እውን የሚሆነው በአንዴ ሳይሆን በሂደት ነው። የማክሮኢ ማሻሻያው በኢኮኖሚው ውስጥ የሚታየውን ማክሮ ኢኮኖሚያዊ መዛባት ለማለ የሕዝቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል፣ የኢኮኖሚውን ቀጣይ ዕድገት ለማረጋገጥ፣ ሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት በተሻለ መልኩ እንድትጠቀም ለማድረግ፣ ከዓለም ኢኮኖሚ ግንኙነትና ተወዳዳሪነት ለማጎልበት፣የሥራ ዕድልን ለማስፋት፣ ቁጠባና ኢንቨስት ለማበረታታት፣ በጥቅሉ ሁሉም ዜጋ ተጠቃሚ የሚሆንበትን የብልጽግና ትሩፋትሎ የሚኖረው ፋይዳ የጎላ ነው።

ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተነሣ በሚቀጥሉት ዓመታት የኢኮኖሚው ዕድገት ተ ይቀጥላል፤ ምርትና ምርታማነት ያድጋል፤ የዋጋ ግሽበት ወደ ነጠላ አሐዝ ይ የመንግሥት ገቢን የማሳደግና ለልማት የሚውል ሀብት በዋናነት ከሀገር

ውስጥም የማሰባሰብ ዐቅም ይጎለብታል፤ የወጪ ንግድ ይስፋፋል፣ የውጭ ሐዋላ ፍሰትዕ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ይጨምራል፤ የሥራ ዕድል ይ ከኢኮኖሚው ዕድገት፣ ከብሔራዊ ባንክ የቁጥጥርና የሱፐርቪዥን ዐቅም እንዲሁም ከቴክኖሎጂ መስፋፋትና ከውጭ ባንኮች የመግባት ዕድል ጋር ተያይዞ ዘርፉ ጤናማነት፣ ዕድገትና ተወዳዳሪነት ይጠናከራል። በጥቅሉ፣ ሀገሪቱ በአካባቢ ከሰሐራ በታች ካሉ ግዙፍ ኢኮኖሚዎች መካከል በቀዳሚነት እንደምትቆም ይጠበቃል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው ፋይዳው የጎላ እንደሚሆን ከላይ የተገለጸ ቢሆንም፣ አንዳንድ አሉታዊ ጫናዎችን እንደሚያስከትል ታሳቢ ተደርጓል። በመሆኑም፣ መንግሥት በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና ለማርገብ የሚረዱ በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ ያለውን ድጎማ በጊዜያዊነት ለመቀጠል፣ የመንግሥት ሠራተኞችን ደሞዝ ለማሻሻልና በከተማም ሆነ በገጠር የሴፍቲኔት መርሐ ግብርን አጠናክሮ ለማስኬድ በገባው ቃል መሠረት በየደረጃው ተፈጻሚ በማድረግ ላይ ይገኛል።

CS CamScanner

ከዚህ ሌላ፣ ጊዜያዊ ወጪዎችንና የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያ የሚያስከትላቸውን ጫናዎች ለመቀነስ የሚረዳ 14 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ትልቅ የገንዘብ ድጋፍ ከውጭ አጋሮች እንደሚገኝ ቃል ተገብቷል። ይህ ዓለም አቀፍ አጋሮች በሚቀጥሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ ለመስጠት ያቀዱት ትልቁ የተቀናጀ የገንዘብ ርዳታ ነው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም የዋጋና የውጭ ኢኮኖሚ የማረጋጋት፣ የፋይናንስ ዘርፍ የጤናማነትና ዕድገት የማረጋገጥ ቁልፍ ሚናዎቹን ለመወጣት የሚያስችል በቂ ዝግጅት _ አድርጎ ወደ ሥራ ብቷል። በተለይም፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ንረትን የሚያረግብባቸውን አዳዲስ የገንዘብ ፖሊሲ መሣሪያዎች ሥራ ላይ ማዋል ጀምሯል። የገንዘብ ሚኒስቴር በበኩሉ ጠንካራ የገቢ መሠረት ለመጣልና የዋጋ ንረትን የሚያባብሱ ለምሳሌ፣ ከብሔራዊ ባንክ ቀጥታ ብድር መውሰድን የመሳሰሉ) የመበደሪያ ስልቶችን ሳይጠቀም የመንግሥት ወጪን ለማሳደግ የሚያስችሉ ርምጃዎችን እየተገበረ ይገኛል።

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. የተሻገረ ገጠር

### 6.1. አዲሱ ዘመን፡ ለገጠር ዕድሎች

ከገጠር ሕይወት ጋር በከፍተኛ ደረጃ የተቆራኘው ግብርና፣ በዓለም ላይ ባለፉት ጥቂት ዐሠርት ዓመታት ከፍተኛ ውጤታማነትና አጠቃላይ ዕድገት ካመጡ ዘርፎች አንዱ ነው። ያለንበት ዘመን ለገጠር ብዙ ዕድሎችን የያዘ ዘመን ነው። የበለጸገው ዓለም በእጅና ጉልበት ከሚከናወን ግብርና ተላቅቆ፣ በትላልቅ ማሽነሪዎችና ዘመናዊ በብዙ ዓይነት ማሽነሪዎች እንዲታያለንበት ጀብ አድርጓል። ስለዚህም ማረስ፣ መዝራት፣ የ ወደሚዘወር እርሻ ከተሸጋገረ ቆየት ብሏል። የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት መሰብሰብና ማጓጓዝ ሁሉ በእነዚህ ማሽኖች መከናወን ጀመረ። በቴክኖሎጂው ውጤታማነታቸው በከፍተኛ ሁኔታ አደገ። የተትረፈረፈ ምርትም ማምረት ተቻለ።

ሁለተኛው አብዮት በተራው ማዳበሪያዎችንና ፀረ ተባዮችን አስተዋወቀ። ይሄም ለዘመናት በመታረሳቸው የነጠፉ መሬቶች ነፍስ ዘርተው እንደገና ወደ ምርታማነት እንዲገቡ አስቻለ። በተባዮች ይወድም የነበረው ማሳም በፀረ ተባዮች መዳን ቻለ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ምርታማነት በጉልህ እያደገ መጣ። በዚህ ዘመን በተለይም ከመጓጓዣ ዘርፍ ዕድገት ጋር ተያይዞ ረዣዥም የባቡር መሥመሮች አውራ ጎዳናዎች ተዘርግተዋል። እነርሱም የእርሻ ግብአቶችንም ሆነ ምርትን በቀላሉ ከቦታ ቦታ ለማጓጓዝ አስችለዋል። የእነርሱ አስተዋፅኦም ለተትረፈረፈ ምርታማነት የተሳለጠ አቅርቦት ከፍተኛ አስቻይ ሁኔታ ፈጥሯል።

በቀደሙ አብዮቶች ከተገኙ ቴክኖሎጂዎች የማያቋርጥ መሻሻል በተጨማሪ የተከሠቱ አብዮቶች የግብርናን የውጤታማነት ደረጃ በእጅጉ ጨምረውታል፡ አብዮት ኮምፒውተርንና መተግበሪያዎችን ስላስተዋወቀ የሀብት አጠቃቀም አስተዳደርን

በከፍተኛ ደረጃ አሳድጎታል። በውሂብ የሚመራ(Data Driven ግብርናን ከማስተዋወቁም በላይ የተለያዩ የግብርና

ንግዶች (Agribusine እንዲፈጠሩ አግዟል። ይሄም ግብርና ከሌሎች ዘርፎች ጋር ያለውን ትሥሥር ደረጃ አሳድጎታል። የሰው ሠራሽ አስተውሎት አብዮት ሮቦቶችንና ባዮቴ አስተዋውቋል። ይህን መሠረት አድርጎ የግብር አሰባሰብ፣ አሁን ካለበት ውጤ በእጅጉ እንደሚያድግ ይጠበቃል። ጅማሬዎቹም ታይተዋል። ዛሬ ላይ ባደጉት ሀገራት ግብርና ብዙ

CamScanner

ቴክኖሎጂዎችን አስተሣሥሮ የሚጠቀም ነው። ውሂብን መሠረት አድርጎ፣ በከፍተኛ ክትትል በሚከወን ተግባር የሚመራ ዘርፍ ነው።

የበለጸገው ዓለም አንዱን ሲጥል ሌላውን ሲያነሣ፣ በብዙ ውጣ ውረድ እዚህ ደርሷል። በዚህ ሂደት ውጤታማነታቸው በተግባር የተፈተኑ፣ ዋጋቸውም ከቀድሞ የተሻለ፣ ብዙ የቴክኖሎጂ አማራጮችን ለገበያው አቅርቧል። ከቴክኖሎጂው ፈጣን ዕድገት በተጨማሪም የግብርና ምርምሮችና ሞዴሎች ከንድፈ ሐሳብ ባለፈ በተሞክሮ ዳብረውና በየጊዜውም ተሻሽለው ለመላው ዓለም ትሩፋት ሆነው ተጋርተዋል።

አፍሪካ የት ናት? ኢትዮጵያችንስ? በሀገራችን ዘመናዊ እርሻ ገና አልተወለደም፤ ወይም በጨቅላ ዕድሜ ላይ ይገኛል። እርሻችን ከሰዎችና ከእንስሳት ጉልበት ገና አልተላቀቀም። ዛሬም የበለጸገው ዓለም ከመቶ ዓመታት በላይ የተወውን የአመራረት ዘዴ ተከታዮች ነን። መንገዳችን እጅግ አድካሚ ነው። ውጤታማነታችን ዝቅተኛ ነው። ምርቱም የቤተሰብና የአካባቢን ፍላጎት ከማሟላት አያልፍም። ከዚያም በላይ ወቅትን ጠብቀን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የምናርስ ነን። ማዳበሪያና የፀረ ተባይ ማጥፊያ እንኳን እንደልብ አናገኝም። በዚህ ሁሉ ለፋት የተመረተችውን ጥቂት ምርት እንኳን

ለማጓጓዝ የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማታችን አነስተኛ ነው። ገና ሕዝባችንን ከምግብ ድጋፍ ማላቀቅ ያልቻለ ግብርና ባለቤቶች ነን፡

ግብርናን ማሸጋገር ገጠርን የማሻገር መሠረት ነው። ግብርናችን ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ምርታማነት ወጥቶ ለሀገር ለወገን የሚደርስ መሆን አለበት። አለፍ ሲልም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ተላብሶ የውጭ ንግዳችን ዋና ተዋናይ እንዲሆን ማስቻል አለብን። ገጠርን የማሻገር ዋነኛ መላ ይህ ነው።

በመሆኑም ግብርናችን በከፍተኛ ሚካናይዜሽን የሚታገዝ፤ የግብዓት አቅርቦቱ የተሟላና የዘመኑን ቴክኖሎጂዎች የታጠቀ መሆን አለበት።

በዚህ ረገድ ከፖሊሲ ማሻሻያዎች ጀምሮ እስከ ጥቃቅን ተግባራት ድረስ በተናበበ በፍጥነት በታጀበ መልኩ መከናወን አለባቸው። ግብርናችንን ከኢንዱስትሪ ልማት ማሠናሰልም አለብን። ይህ የኋልዮሽና የፊትዮሽ ትሥሥር ሲሠምር ለምርታማነትን ሚና ይጫወታል። ኢንዱስትሪው ከግብርና ግብአት የሚያገኝና የሚወጣ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ለግብርናው የተለያዩ ማሽነሪዎችን በ ግብአት እንዲሆን ይጠበቃል። በዚህ ረገድ የግብርና ሜካናይዜሽንን ማሽነሪዎችንና እንደ ማዳበሪያና ፀረ ተባይ ያሉ ግብአቶችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎችን በስፋት ማፍራት ይኖርብናል።

በግብርና ልማት የአዝርዕት ሰብልን፣ የቅባት እህሎችን፣ የጥራጥሬን፣ የአትክልትና ኢ የሥራ ሥር ምርትን በማሳደግ፤ ከጓዳ ወደ ገበያ ማሻገርን ግብ አድርገን እ በተጨማሪም የግብርና ኢንዱስትሪ ትሥሥር መፍጠርን ለማሳካት በስፋት እንገኛለን። ለማሳያ ያህል የኢትዮጵያ አግሮ ኢኮሎጂ በርካታ ጥራጥሬና የቅባት በዓይነት በዓይነት የማብቀል ታላቅ ጸጋ አለው። የጥራጥሬ ሰብልና የቅባት እህሎት ማሳደግ፣ የውጭ ምንዛሪን በማሳደግና ለኢንዱስትሪ መስፋፋት ግብአት ዐቅም አላቸው። በጥራጥሬና በቅባት እህሎች ምርታማነትን በማሻሻልና ቁ ተሳትፎን በማሳደግ፤ ምርቱን በገበያ ተወዳዳሪ ለማድረግ ይሠራል።

የቅባት እህሎችን ለማምረትና ከዘይት ፋብሪካዎች ጋር ለማስተሣሠር እየሠራን የውጭ ምንዛሪን ወጪ ከማዳን ባለፈ፣ የምርት ዕድገትና ቀጣይነትን እናረጋ ም የሥራ ዕድልም እንፈጥርበታለን። ከዚህም አልፎ ከፍ ያለ ዕሴት የታከለ በማምረት፣

የውጭ ምንዛሪ ለማምጣት ያስችለናል"።

የሀገራችን የምርትና ምርታማነት ዕድገት በቦታና በጊዜ የተገደበ ሆኗል፡ ከ ሁኔታ በመሠረተ ልማት አውታርና በመረጃ ውሱንነት የተነሣ ገበያውም ሥሉ እንዳይሆን ሆኗል። ይህም አምራቾች ተገቢ የሆነ ዋጋ እንዳያገኙ ያደረገ ሲሆን ገበያ

CamScanner

ምክንያት በአምራችና በሻጭ መካካል ያሉ አገናኞች ከፍተኛ ያልተገባ በ ያላቸው መሆኑ፤ ምርት ትክክለኛ ዋጋውን እንዳያገኝ አድርጎታል።

አዲሱ የዲጂታል ዘመን የቦታና የጊዜን ገደብ ለመሻገር፣ ፈጠራን በማምረቻና በአስቻይ በኖቬሽንና በቴክኖሎጂ የአምራቾችን ዐቅምና የጊዜ አጠቃቀምን አልቆ ትርፍ አምራች አድርጓቸዋል። በግብርናና ኢንዱስትሪ ዘርፍ የምርታማነት ገደቦችን የሚያሻግሩ ዐቅሞችን በፈጠራ አጎልብቶ በአዳዲስ ዕድሎች አስተሣሥሯቸዋል። በዚህም ፈጣን መዋቅራዊ | ሽግግርን ለማስቻል ክሡት ዕድል ሆኗል።

ድሉን ባለን ዐቅም አለመጠቀም ለአዲሱ ዘመን ዕድል ባዳ ያደርገናል። ከዚህም ባሻገር ወደ ቀደመው ዘመን ወደኋላ ያንሸራትተናል። በአንድ በኩል በአዲሱ ዘመን ውድድር ውስጥ፣ በሌላ በኩል በቀደመው ዘመን የቦታና የጊዜ ገደብ ውስጥ ሆኖ ትርፍ አምርቶ መሸጋገርና መወዳደር አይታሰብም። ለመሸጋገር፣ በቀደመው ዘመን ላይ የቆመውን የማኅበራዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት ወደ አዲሱ ዘመን ዕሳቤና ዕድል ማንቀሳቀስ ያሻል።

አዲሱ ዘመን ነባሮቹን ከማላቅ ባሻገር አዳዲስ ዕድሎችን ይዞ ከፊታችን አለ። ከመጻዒዎቹ እድሎች ድርሻ እንዲኖረን የዕይታ ለውጥ ማድረግ የግድ ነው። ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት መላመድና ጥቅም ላይ ማዋል ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው። ይህም ዳቦ ከማስገኘት ባሻገር ለቀ ደረጃ የኢኮኖሚያዊ መዋቅር ሽግግርን ያፋጥናል። ከመጪው ጊዜ ጋርም እኩል ተራማጅ ያደርገናል።

አዲሱ ዘመን ለግለሰቦች፣ ለነጋዴዎች፣ ለኅብረተሰቡና ለመንግሥት ብዙና አስደሳች የመበልጸጊያ ዕድሎችን ይዟል። የዲጂታል ዘመን ከግለሰብ እስከ ኅብረተሰብ ብሎም በተቋማት እስከ መንግሥታዊ ሥርዓት፣ ለማደግ፣ ለመላቅና ለፈጠራ አዲስ ምቹ አስቻይ ምኅዳር ነው።

ይሄንን አጓጊና ባለ ብዙ ዕድል ምኅዳር ተጠቅሞ ለማደግና ለመላቅ ተግዳሮት ከሆኑ ምክንያቶች መካከል አንዱ በቀደመው ዘመን ወረት አለመፍጠራችን ነው። በቀደመው ዘመን ሰፊውን ግብርና አንቀሳቅሰን፣ ጀማሪ ኢንዱስትሪዎችን ተክለን፣ ያገኘነው ወረት የመስፈንጠሪያ ዐቅም የሚሆነን አይደለም። ይባስ ብሎ የሠለጠነው ዓለም የወረት ክምችት መገኛ አድራሻውን ከቀድሞ ዘመን በተለየ ወደ ዲጂታል ዓለም አዛውሮታል።

በአጠቃላይ እንደ ሀገር ያለንበትን ተጨባጭ ሁኔታ ስንፈትሽ የምናገኛቸው ሐቆች አሉ። __ በቀደመ ዕሳቤ ተጉዘን ከድህነት መውጣት አልቻልንም። የወረት ቋታችን የነጠፈ በመሆኑ _ የነባሮቹን ዐቅም ለማጎልበት ሆነ እያደገ ያለውን ሀገራዊ ፍላጎት ለመመለስ አይበቃንም።

በተመሳሳይ የተቀናጀ የገጠር ልማት አስተሳሰብ የልማት ሥራዎች የማኅበረሰብ ፍላጎትን መሠረት ያደረጉና በተሳትፎ ላይ ተመሥርተው መቀረጽ እንዳለባቸዉ ያስገነዝባል። ለዚህም አጠቃላይ የገጠር ሽግግርን የሚመሩና የሚያስፈጽሙ አስተዳደራዊ መመሪያዎች ወያም ፖሊሲዎች ቀርጾ መንቀሳቀስ ወሳኝ ነው።

በጥቅሉ ስናየው ዘመኑ ብዙ ተግዳሮቶችንና ዕድሎችን ይህ በፊታችን ተዘርግቷል። የብልጽግና ጉዟችንን ለማደናቀፍ በየደረጃው ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች ቢከታተሉም፤ እንደ ሀገር ለመቀጠል ከማሸነፍ ውጪ አማራጭ የለንም። ይልቁንም ዘመኑ ያመጣልንን ዕድሎች በሚገባ ተጠቅመን ገጠሩን ማሻገር ይገባል። ሀገራችንንም ወደ ሚገባት የብልጽግና ማማ እንድትወጣ ቀን ከሌሊት መትጋት የግድ ነው። ከዚህ ትውልድ የሚጠበቀው የአባቶቻችን አደራም ይህ ነው::

**6.2.** የመደመር መንግሥት በገጠር

CamScanner

ገጠሩን ማሻገር ራሱን በቻለ የሽግግር ዕቅድ መመራት ይገባዋል። በኢትዮጵያም የገጠር ሽግግሩን በሚያሣልጥ ፖሊሲ እየተመራ ነው። በዚህም መሠረት ገጠሩን የማሻገር ትልም የግብርና ሽግግርን መሠረት አድርጎ ይነሣል። ከዚያም ሌሎች ዘርፎችን የማሳደግና _ የማኅበረሰቡ የኢኮኖሚ ፍሰት ከግብርና ባለፈ በእነዚህ ዘርፎችም ላይ እንዲደገፍ ማስቻል አንዱ ግቡ ነው። ገጠሩ የተሻሉና የተሣለጡ መሠረተ ልማቶች ባለቤትና የተለያዩ አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆን ያስችለዋል።

ይሄም ተበታትኖ ከመኖር ይልቅ በተረጋጉና በጸዱ አነስተኛ ዘመናዊ የገጠር ከተሞች እንዲኖር፣ በሂደትም ወደ ሙሉ ከተሜነት እንዲሸጋገር ያበቃዋል። ለዚህ አዲስ የአኗኗር ዘይቤ እንዲጎለብት ተደርጎ ገጠሩ መሠራት ይኖርበታል። ሽግግሩ መላውን የገጠር ማኅበረሰብ ያካተተና ሙሉ ተጠቃሚነታቸውን ማዕከል ያደረገ ሊሆን ይገባል። ሽግግሩ ፈጣንና በፈጠራ የተሞላ መሆን ይጠበቅበታል። የተሻገረ የገጠር ሕይወት ለኢንዱስትሪ እና ለአገልግሎት ምርቶች ገበያን ይፈጥራል።

ከአንድና ሁለት ዐሠርት ዓመታት በኋላ የምንደርስበትን የግብርና ደረጃ ርዕይና ትልም መቅረጽ ያስፈልጋል። ቀዳሚው ርምጃ ግብርናችንን ካለበት ኋላ ቀርነት ማላቀቅ ነው። ዛሬ የምናያቸውን ቴክኖሎጂዎች ከመጠቀም አልፎ፣ በየጊዜው በዓለም ላይ የሚፈጠሩና በራሳችን ዐቅም የምንፈጥራቸውን ቴክኖሎጂዎች መተግበር ይኖርበታል። የቴክኖሎጂ ባለቤት ሆኖ እየተመራመረና በፈጠራ እያጎለበተ መጓዝ ያስፈልገዋል። በዚህ መልኩ በመጓዝ በዓለም ተወዳዳሪ ሆኖ መቀጠል የሚያስችለው ቁመና ላይ እንዲገኝ ያግዘዋል።

በዚህም አማካነት እንደ ዛሬው በብዙኃኑ ጉልበት የሚታረስ መሬትና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ምርታማነት ያለው አይሆንም። በዘመኑ ቴክኖሎጂ እየታገዘ፣ በጥቂት የሰው ኃይል ከፍተኛ በዚህም አማካኝነት እንደ ዛሬው በብዙኃኑ ጉልበት የሚታረስ መሬትና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ በመዋቅራዊ ሽግግር ሂደት ካፒታልን ለማሰባሰብ በምናደርገው ጥረት ውስጥ የውጭ ምርት ያስገኛል። የገበሬውን ፍላጎት ከማሟላትና የሀገር ውስጥ ፍጆታን ከመሸፈን ያልፋል። መልኩ እየተመራ ይሄዳል። ሽግግሩ ለሰው ልጅ ምቹ ተደርገው የተገነቡ፣ መሠረተ ልማት ንግድ ወሳኝ ተዋናይም ይሆናል። ግብርናው ብቻም ሳይሆን የገጠር ሽግግሩም በተሠናሰለ የተሟላላቸው፣ ትናንሽ የገጠር ከተሞች እንዲፈጠሩ ያስችለናል።

ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችለውን ዐቅም ማላበስ አለብን። ይህ ደግሞ የተሻገረ ገጠርን መገንባት የተሻገረ ግብርናን የሚጠይቅ ነው። ስለዚህም ግብርናችንን ይጠይቃል። ግብርናን በፍጥነት ማሸጋገር ዘርፉን በብዙ ወሳኝና አሻጋሪ ፈጠራዎች አሁን ካለበት እጅግ ኋላ ቀር ደረጃ ወደ ዘመናዊ የግብርና ደረጃ በፍጥነት ማሸጋገርን ማነቃቃት ነው። ግብርናችንን በሜካናይዜሽን የሚመራ፣ ግብአቶቹን ያለመቆራረጥ የሚያገኝ፣ ውጤታማነቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ የሚያሣልጥ፣ የወደፊቱን ቴክኖሎጂ ባለቤት ለመሆን በምርምር የሚደገፍ ማድረግ ነው።

በአጠቃላይ ግብርናችን በከፍተኛ ትኩረት ዘመናዊነትን እንዲላበስ መሥራት የግድ ነው:: የተሻገረ ግብርና ገጠሩን ለማሻገር መሠረት ነው ብለናል። ቢሆንም ግን የገጠሩን ሽግግር ለማፋጠን ሊሟሉ የሚገባቸው ሌሎች መሥፈርቶችም አሉ። እነዚህን ከወዲሁ በቅንጅት መምራት፣ የገጠሩ ሽግግር ከግብርናው ሽግግር ጎን ለጎን መከናወን እንዲችል ዕድል ይሰጣል።

የግብርና ሽግግርም ሆነ አጠቃላይ የገጠር ሽግግር በመንግሥት ዐቅም ብቻ የሚሳካ አይደለም። የግል ዘርፉን ከፍተኛ ተሳትፎና የሌሎች የልማት አጋሮችን ቅንጅት ይጠይቃል። መንግሥት ቀዳሚ ኢንቨስተር ሆኖ መሥራት በሚገቡት ሁኔታዎች ሁሉ በከፍተኛ ፈጠራና ፍጥነት ታጅቦ ሚናውን ይወጣል። ለዚህም ባለፉት ጥቂት ዓመታት የታዩት ግብርናውን የማሻገር የፈጠራና የፍጥነት መንገዶች ምስክር ናቸው። በቀጣይም ከልማት አጋሮች ጋር በተለየ ትኩረትና ቅንጅት ሽግግሩን ለማሳካት የሚታትር ይሆናል። የግል ዘርፉም አሁን ካለው የተሳታፊነት ደረጃ በላይ ግብርናውን የማሻገር ከፍ ሲልም ገጠሩን የማሻገር ትልምን ለማሳካት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል። ይሄንን በመገንዘብ በሙሉ ዐቅምና በተባበረ ክንድ የሽግግሩ አካል እንዲሆን ይጠበቃል።

CamScanner

የተረጋጋና የጸና የገጠር ሽግግር ግንባታ የማይበገር ግብርናን(Resilient Agriculture) መገንባትን ይጠይቃል። ይህም ማለት ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና አካባቢያዊ ተግዳሮቶችን የሚቋቋም ግብርና ማለት ነው። ግብርናችን የሀገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን በቶሎ የሚላመድ፣ እንደ የአስፈላጊነቱም ተለማጭ መሆን ይኖርበታል። ለዚህም ግብርናውን በምርምር ላይ እንዲመሠረት ማድረግ ወሳኝ ነው። በዚህ ዐቅም አማካኝነት አካባቢያዊ፣ ሀገራዊም ሆነ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን የመገንዘብ፣ የመተንተንና የመተንበይ ዐቅም ማዳበር ይገባዋል። ነገሮችን አስቀድሞ በመተንበይ፣ ዝግጁ ሆኖ መጠባበቅን መለማመድ አለበት።

በአጠቃላይ፣ የተሻገረ ገጠር የመፍጠር ትልም መሠረት የሆነውን ግብርናችንን አሁን ተቸንክሮ ከሚገኝበት እጅግ ኋላ ቀር የሆነ የአሠራር ቅርቃር በማውጣት፤ እጅግ ዘመናዊ፣ ብዙዎችን ወደሚያካትትና ለሌሎች ዘርፎች መስፋፋትና ማደግ መሠረት ወደሚሆን ደረጃ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ወደ ሆነ፣ በጽኑ መሠረት ላይ ወደተገነባ፣ ለችግሮች ወደማይበገር፣ ድረስ ይጠበቅብናል። ይሄን ማድረግ ደግሞ የመደመር መንግሥትና የዚህ ትውልድ የቤት ሥራ ነው።

በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ይሄንን እናሳካዋለን። ግብርናችን የራሱ መልክና ዕላፊ ያለው ይሆናል። መንገዱም ወዴት እንደሆነ በምናብ ከምናየው ከእኛ አልፎ ለሌሎችም በግልጽ ይታያል። በቀጣይ ጥቂት ዓመታት ዓለም የሚመሰክርለት የግብርና ሽግግር ባለቤቶች እንሆናለን። ለዚህም ሽግግሩን እየሠራንበት ያለው መንገድ፣ በጥቂቱም የታዩ ለውጦችና ያጡት ጉልህ የምርታማነት ውጤት ምስክሮች ናቸው።

### 6.2.1. የግብርና ፍጥነት በተሻገረ ምናብ፣ በተደመረ ጥረት

ሀገራችን ኢትዮጵያን አፍሪካዊት የብልጽግና ተምሳሌት የማድረግ ሕልም የሚጨበጥ ሕልም ነው። ይህ ከፍተኛውን የሀገሪቱን የሕዝብ ቁጥርና የመሬት ስፋት የሚሸፍነውን የገጠሩን ሕዝብ ማሸጋገርን በዋናነት ይመለከታል። የገጠሩን የኢኮኖሚ ዐቅም በፍጥነትና በፈጠራ ማንቀሳቀስን ይሻል። አርሶና አርብቶ አደሩን ማዕከል ያደረገ ልማት ለሀገራዊ ሁለንተናዊ ብልጽግና ሰፊ መሠረት ይሆናል። ተጠባቂውን ፈተና በድል በመውጣት ፈጣንና ቀጣይነት ያለው አጠቃላይ የምርት ዕድገት ለማረጋገጥ፤ የግብርናው ዘርፍ ከወዲሁ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በፈጠራ ሊመራ ይገባዋል።

የግብርና መሸጋገሪያ ርካብ መራመጃው ብዙ ነው። ምርትን በመጠን፤ በዓይነትና በጥራት ማምረት፣ ብሎም የገበያ ትሥሥር መፍጠር፤ አካባቢንና ሥነ ምህዳርን በዕምቅ ዐቅምነት መጠቀም፤ ጊዜን ከምርት ወቅትና ከመድረስ አንጻር መረዳት፣ በምርምርና በቴክኖሎጂ የማምረት ዐቅምን በብዙ እጥፍ ማሳደግ የርካቡ መሸጋገሪያዎች ናቸው።

የግብርና ሽግግራችን የሚሠምረው ያልተጠቀምንበትን ጊዜ፣ ቦታና የገበያ እድል በውጤታማነት ስንጠቀምና በቴክኖሎጂና በፈጠራ ስንታገዝ ነው። ጊዜ፣ ቦታና ሰው መስተጋብራዊ ጥምረት መፍጠር አለባቸው። እነርሱ ደግሞ በምርምር፣ በቴክኖሎጅ በሜካናይዜሽንና በፈጠራ ሲታገዙ ለውጡን ያፈጥኑታል።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በጀመርነው የለውጥ እንቅስቃሴ አያሌ ልምዶችን ቀስመናል። የስንዴ ስኬታችንን በሌሎች የቅባትና የጥራጥሬ እህሎች፣ በአትክልትና በፍራፍሬ፣ በሻይ ቅጠልና በሩዝ ላይ ለመድገም የሚያስችል ልምድና ሥነ ዘዴ ቀስመናል። የግብርንና ዘርፍ የሥራ በመፍጠርና በማስተሣሠር የአርሶና የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለመቀየር እንሠራለን። ከዚህ ፈጠራ ማዕከል ለማድረግ ምርትን በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት እናሳድጋለን። ገበያ በተጨማሪ ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽዖውን እናሳድጋለን። በአጭር ጊዜም ከሌሎች ዘርፎች ጋር በሚኖረው ውጤታማ ትሥሥርና በብዝኃ ዘርፎች አቅጣጫትን ከሚኖረን ስኬት ጋር ተደምሮ፤ የታችኛው መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ እንሰለፋለን።

CamScanner

ሀገራችን ካሉባት ተግዳሮቶች መካከል አንዱ የቦታ አጠቃቀም ነው። ለእርሻ ምቹ መሬት አለን። ነገር ግን እስከ አሁን ያረስነው መሬት መታረስ ከሚችለው አነስተኛውን ነው። ያቺው እርሻችን ደግሞ በተሸነሸነ የገበሬ መሬት ላይ የምትከናወን ናት።

ከፍተኛ የቆላ መሬት ባለቤቶች ነን። ለከተማ ግብርና የሚሆን ምቹ ሥፍራ አለን። ይሁንና እርሻችን ወቅትን የሚጠብቅ፣ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚከናወን፣ ዝናብን ጠባቂ ነው:: መሬታችንን፣ ጊዜያችንንና ጉልበታችንን ሁሉ እናባክነዋለን። በዚህ ምክንያት ዕምቅ የግብርና ሀብት እያለን በረሃብና በድህነት ስንማቅቅ ኖረናል።

ላለፉት ሁለት ዐሠርት ዓመታት የሠራነው የግብርና ልማት በአነስተኛ የገበሬ ማሳ ላይ ያተኮረ ነው። ይህ የግብርና ልማት በተጠቀማቸው የግብርና ግብአቶች ትርፍ ማምረት ባያስችለንም ቢያንስ ግን የቤተሰብ የነፍስ ወከፍ ገቢን በማሳደግ መልካም ለውጥ አሳይቷል፡ አሁን የሚያስፈልገን፣ ግብርናው ከቤተሰብ ፍላጎት ተሸጋግሮ የገበያና የኢንዱስትሪውን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ትርፍ እንዲያመርት ማድረግ ነው። ለዚህ ደግሞ በአነስተኛ ይዞታና ደረጃ በሚከናወን ግብርና ላይ ብቻ መቆም አያራምድም፤ አያሻግርምም።

የግብርናው ሽግግር እንዲፋጠን ከፈለግን፣ በተግዳሮቶች መረታት የለበትም ካልን፡ ኢትዮጵያ መስክ መልማት የሚችልን አንድ ስንዝር መሬት ሳታስቀር ለማልማት መቻል አለባት። ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከደጋ እስከ ቆላ ከአነስተኛ ማሳ እስከ ታላላቅ እርሻዎች ባለን ሰፊ ምኅዳር ልክ ማልማት አለብን። ይህንንም በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ልናሳካው ይገባል። ያን ጊዜ ምርት በመጠን፤ በዓይነትና በጥራት ያድጋል።

የመደመር መንግሥት ስለ እርሻ መሬት ያለው አመለካከት ከቀደሙት ይለያል። የተለመደውን ለእርሻ የተመደበ መሬት ከማረስ ያልፋል። አንድም መሬት ጦም አታድርም በሚል መርሕ የሚመራ ነው።

የመጀመሪያው መሬትን ጦም ያለማሳደር ርምጃ ደግሞ በወሰንነት ያጠርናቸውን የባለቤትነት መለያ መሥመሮችን መናድ ነው። ይህ የእርሻ ወሰንን የመናድ ተግባር፤በድምሩ ለእርሻ | ዝግጁ የሆነ ከፍተኛ መሬት ያስገኝልናል። በዚህ ምክንያት መሥመሮቹን አፍርሰን ኩታ በጠም አደረግናቸው። የሀገራችን የአስተራረስ ዘዴ አንዱ ፈተና የተበጣጠሱ እርሻዎች ሲሆኑ፣ እነዚህ እርሻዎች ከሥነ ምኅዳሩ ጋር የሚሄድ አንድ ዓይነት ምርት ለማምረት አያስችሉም፤ ለቴክኖሎጂ አጠቃቀም ምቹ አይደሉም፤ ለማዳበሪያና ፀረ ተባይ አጠቃቀም አይመቹም። በመካከል ለወሰን የሚተወው የመሬት ብክነትን አስወግደን፣ ጥቅም ላይ እንዲውል አድርገነዋል። በዚህም ኩታ ገጠም አስተራረስ መሬቱን ከማስፋቱም በላይ፣ ግብርና ግብአቶችና ቴክኖሎጂዎች በጋራና ሀብት ቆጣቢ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አግዟል።

የኩታ ገጠም እርሻ ታሪካዊ ፈተና ነበረበት። በደርግ ጊዜ በገበሬ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በኩል አስገዳጅ ተደርገው የተፈጸሙ አንዳንድ ጥፋቶች በገበሬው ትውስታ ውስጥ አሉ። ይሁንና ይሄንን ችግር ለመፍታት እንዲቻል አርሶ አደሮች የመሬት ይዞታቸውን ሳያጡ በፍቃደኝነት በኩታ ገጠም ተባብረው እንዲያለሙ ተደርጓል። በዚህ አካሄድ፣ ማኅበረሰቡን ማሳመንና ማበረታታት፣ የተቀበሉ አርሶ አደሮችን በባለሞያና በቴክኖሎጂ ማገዝ፣ እንዲሁም ሌሎች አርሶ አደሮች ከቀደሙት እንዲማሩ ማድረግ፣ የሚሉ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል።

ሁለተኛው መሬትን ጦም ያለማሳደር ጥረት የሚገለጠው "ጊዜን ተጠቅሞ ቦታን ማስፋት በሚለው መርሕ ነው። የዚህ መርሕ የተግባር መገለጫው በዓመት አንድ ጊዜ ሲታረስ የነበረን መሬት ደጋግሞ በማረስ ነው። ይህ ስልት ሦስት ጥቅሞች አስገኝቷል።

CS CamScanner

ከክረምት ውጭ ይባክን የነበረውን መሬት ዓመቱን ሙሉ ለእርሻ እንዲውል አድርጓል። ገበሬው ተጨማሪ ምግብና ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኝ አድርጓል፤ የገበሬው ዓመታዊ ጊዜ በአብዛኛው ለምርት እንዲውል በማድረግ የሰው ኃይል ምርታማነትን አሳድጓል። በበጋ ግብርና ልማት ልምምድ አማካኝነት የጊዜ ምልከታችን በመቀየር የምርት ለውጥ በሀገራችን በዓመት ውስጥ መሬት ሳያመርት የሚያርፍበት ጊዜ ከፍተኛ ከነበረበት፣ አምጥተናል። በዚህም በዐሥር ዓመቱ የልማት ዕቅድ የያዝነውን ዋና ዋና የምግብ ፍጆታዎችን በሀገር ውስጥ በማምረትና ከውጭ የሚገባውን በመተካት ተስፋ ሰጪ ውጤቶች አስመዝግበናል።

በስንዴ ምርት ሀገራዊ ፍጆታን ለማሟላት የተቀረፀውን ርዕይ በፍጥነት ለማሳካት በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲመረት አድርገናል። በዚህ ጥረትም ከዓመታዊ ፍጆታችን በላይ አምርተን ስንዴን ወደ ገበያ ምርትነት(Cash Crop) ለመቀየር በቅተናል"።

ሦስተኛው መሬትን ጦም ያለማሳደር ጥረት ደግሞ ዐቅም መደመር ነው። በየቦታው ተበጣጥሰው የሚገኙ መሬቶች እንደየዐቅማቸው ማበርከት ቢችሉ፣ በድምሩ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል ከሚል የሚነሣ ነው። ከዚህ አኳያ የከተማ መሬቶች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። እነዚህን መሬቶች በጓሮ አትክልት፣ ዐቀባዊ እርሻን በማስፋፋት፣ የአትክልትና የፍራፍሬ እርሻዎችን በማልማት፣ ለሀገራዊ ምርት ዕድገት ትልቅ ድርሻ እንዳለው ተገንዝበን በተግባር መትጋት ይገባል።

ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በከተማ ግብርና የጊዜና ቦታ የዕይታ ለውጥ መጥቷል። በተግባር ሠርቶ በማሳየትና በማበረታታት አዲስ የከተማ ግብርና ልማድ እየተፈጠረ ነው። ዛሬ ዛሬ ጓሮን ጦም ማሳደርና የተቋማትን መሬት ለጢሻ መተው እየተነወረ ነው። ለምን? ብሎ የሚጠይቅ ከተሜም እየበዛ ነው። የከተማ ግብርናን ባህል በማድረግና የማምረቻ ግብአቶችን በማቅረብ የከተማ ግብርና ልማት እየተጠናከረ ይገኛል። ይህም ለሀገራዊ ጥቅል ምርት ካለው አስተዋጽዖ ባሻገር የተመጣጠነ የሥነ ምግብ አቅርቦት በከተማ ለማሳደግ ይረዳል። ጤናው የተጠበቀ ማኅበረሰብ በመገንባትም ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል።

መሬትን ጦም ያለማሳደር አራተኛው ጥረት የቆላ ግብርና ነው። የኢትዮጵያን ግብርና ምርት የመቀየር ትልቅ ዐቅም ያለው ቆላማ ቦታ ለዘመናት ትኩረት አጥቶ መኖሩን ከመረዳት የሚሣ ነው። በርግጥ የኢትዮጵያን የቆላማ አካባቢ ለማልማት የግብርና ቴክኖሎጂና የመሠረተ እንጃ በአነስተኛ ወጪ መልማት የሚችሉ ቆላማ አካባቢዎች አሉ። በቆላ አካባቢ የሰብል ጥት ግንባታ ይፈልጋል። ይሄ ደግሞ ከፍተኛ ካፒታል እንደሚይት ይታወቃል። ይሁኑ ልጅን ማምረት ማለማመድና በልማት ሂደት በሚፈጠር የካፒታል ዐቅም የቆላ ግብርናን ስፋት ይገባል።

ካለብን የምርትና የምግብ እጥረት፣ እንዲሁም ከሚያስገኘው ቀጣይነት ያለው የምርት ሓድነት አንጻር፣ የቆላማ አካባቢ ኢንቨስትመንትን በካፒታል መደገፍ ተገቢ ነው። በቆላማ አካባቢ አነስተኛና ታላላቅ መስኖዎችን በመገንባትና ያልለሙ ቦታዎችን በማልማት፡ ምርትን በመጠን፣ በዓይነትና በጥራት እናሳድጋለን። የዐሥር ዓመት የልማት ዕቅዳችን ከማለቁ አስቀድሞ የአነስተኛና የታላላቅ መስኖ የማጎልበት የሀገሪቱ ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል። የቆላማ ግብርና ልማት የኢትዮጵያን ግብርና ሽግግር በማቅናት ትልቅ ዐቅም ይሆነናል።

አምስተኛው መሬትን ጦም ያለማሳደር ጥረት ያልታረሱ ልዩ መሬቶችን የማካተት መርሕ ነው። ይሄውም ለእርሻ ምቹ ሆነው  ሳለ በተለያዩ ምክንያቶች ያልታረሱ መሬቶችን፣ በተለየ ትኩረት ወደ እርሻ የማስገባት ጥረት ነው። በዚህ መንገድ የግል ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ እናሳትፋለን። በዚያም አማካኝነት ትላልቅ ኢንቨስትመንቶችንና ሜካናይዝድ እርሻዎችን እንፈጥራለን። ባለፉት ጥቂት ዓመታት መሰል ኢንቨስትመንቶች በከፍተኛ ደረጃ ጨምረዋል። እነዚህ ምቹ የእርሻ መሬቶች የግብርና ዕድገታችንን ለማፋጠን ዋና ማስፈንጠሪያ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው። ከዚህ አንጻር በተለየ ትኩረት ልማት እየተከናወነባቸው ይገኛሉ።

CamScanner

በሌላ በኩል በግብርና ልማት ውስጥ የሰው ልጅ በጊዜና በቦታ አጠቃቀም እመርታዊ ለውጥ በፍጥነት እንዲያገኝ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚፈልጉ ጉዳዮች አሉ። እነርሱም ማሽነሪዎችና ግብአቶች ናቸው። በሰውና በእንስሳት ጉልበትና በማሽነሪ መካከል ያለው የሰዓት አጠቃቀምና የቦታ ሽፋን በፍጥነት ብቻ ሳይሆን በጥራትም ይለያያል። የምርት አቅርቦት ፍላጎት ዕድገትን ለማሟላት እንደ ቀደመው በእንስሳት አርሶ ወቅቶ፤ በሰው ጉልበት ጎልጉሎና አርሞ የሚሟላ አይደለም።

በተለምዷዊው የእርሻ አሠራር በሀገራችን በቅድመና ድኅረ ምርት፣ ከፍተኛ የእህል ብክነት መንገድ የሚፈጠር ነው። በዘመናዊ ማሽነሪዎች ባለመታገዛችን የተነሣ በየዓመቱ ሚልዮኖችን አለ። ብክነቱ በእርሻ ዝግጅታችን፣ በቡቃያ ክብካቤ፣ በፍሬ አሰባሰብና በምናከማችበት የሚቻለው በዋናነት የግብርና ማሽነሪዎችን በግዥና በቴክኖሎጂ ልማት በማብዛት ነው። ሊመግብ የሚችል እህል ሳይመረት ይቀራል። ተመርቶም ይባክናል። ችግሩን መቅረፍ እንዲሁም የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት የምርት ብክነቱን መቀነስና ምርታማነትን ማሳደግ ሲቻል ነው። እርሱም የአርሶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት ያስችላል።

በመደመር መንግሥት የእርሻ ሜካናይዜሽን የሽግግሩ መሠረትና የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው። ስለዚህም ዘመናዊ የእርሻ ማሽነሪዎችን ወደ እርሻችን ማምጣትና ገበሬውን ማስታጠቅ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው። ለዚህም ገበሬው በቁጠባና በብድር መልክ በተደራጀ ሁኔታ ትራክተሮችን የሚያገኝበት መንገድ እየተተገበረ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ከውጭ በሚገቡ ማሽነሪዎች ሜካናይዜሽንን ማሳካት በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጫናው ከባድ እንደሚሆን ይታወቃል። ለዚህም መፍትሔ እንዲሆን የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ዘመናዊ የእርሻ ማሽነሪዎችን እንዲገጣጥሙ፣ በሂደትም ወደ ማምረት እንዲገቡ፣ በተለየ ትኩረት እየተሠራ ይገኛል።

ሌሎች የግብርና ግብአቶችን በተመለከተም አዳዲስ የፈጠራ መፍትሔዎች ያስፈልጉናል። በሀገር ውስጥ ማግኘት የምንችላቸውን የግብአት ምርቶች ቅድሚያ እንሰጣለን። ከውጭ ማስገባት ያለብንን ደግሞ በሂደት እንተካለን። ማዳበሪያ የእርሻችን ወሳኝ ግብአት መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ረገድ የሚፈጠሩ የጊዜ መዛባቶች ኪሣራቸው እጅግ ከባድ ነው። በመሆኑም የማዳበሪያ ፋብሪካዎችን በከፍተኛ ደረጃ በማስፋፋት ከእኛ አልፎ ለሌሎች መሰል ሀገራትም ማዳበሪያ የምናቀርብበትን ዐቅም መገንባት ያስፈልጋል።

በመደመር መንግሥት የገጠር ልማታችን በአርሶና አርብቶ አደሩ ምርታማነት ላይ ብቻ የሚያተኩር አይደለም። አዳዲስ ገበያዎችን በመፍጠር የአርሶና የአርብቶ አደሩን ገቢ በማሳደግ ዙሪያ ይቃኛል። የገጠር ልማት የግብርና ምርታማነትን በማሳደግ የገበያ ትሥሥር እያጎለበተ መሄድና በገጠር የሥራ ፈጠራን ማስፋት አለበት።

የገጠር፣ የገጠር ከተማና የከተማ ለከተማ ትሥሥሮችን ማጠናከር ይኖርብናል። በዚህም የአምራቹንና የሸማቹን የጋራ ተጠቃሚነት ማሳደግ ይገባል። በዚህ ረገድ ዋነኛ ተግዳሮት የመሠረተ ልማት እጥረት ነው። የመስኖ፣ የመጓጓዣ፣ የኃይልና የዲጂታል መሠረተ ልማቶች የተለየ ትኩረት የሚፈልጉ ናቸው።

ሰንጉሡም፣ በደርግም፣ በኢሕአዴግም ከዝናብ ጥገኝነት ለመላቀቅ ተደጋጋሚ ዕቅዶችና ሙከራዎች ነበሩ። እዚህ ግባ የሚባል ስኬት ግን አላስገኙም። የመስኖ ልማት የግብርና ሽግግር የደም ሥር ነው። ሀገራችንም ለመስኖ ልማት ምቹ ናት። የግብርና ምርታችን ከቦታና ከጊዜ ፈተና እንዲሻገር ከፈለግን፣ የውኃ አቅርቦት በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በታላላቅ መስኖዎች መሠረተ ልማት መደገፍ አለበት።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት፣ የመስኖ መሠረተ ልማት በከፍተኛ ትኩረት የሠራንበት ተግባር ነው። በርካታ አነስተኛ፣ መካከለኛና ትላልቅ የመስኖ መሠረት ልማቶችን ገንብተናል። ውጤቱንም የበጋ እርሻን በከፍተኛ ደረጃ በማሣለጥ ተመልክተናል።

CamScanner

በሚቀጥሉት ዓመታትም የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ የውኃ አቅርቦትን በግለሰብና በቡድን ደረጃ ለማድረስ ይሠራል። በዚህ ረገድም የግለሰቦችን ዕይታና ዐቅም ማሳደግና ለግሉ ዘርፍም የተለያዩ ማበረታቻዎችንና ድጋፎችን ማድረግ ይገባል። በመንግሥትና በአጋር አካላት የጋራ ቅንጅት፣ የግብርና ዘርፉ የተለየ ትኩረት እንዲያገኝ ይደረጋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የእርሻ ግብአቶችን ለገበሬው በቶሎ ለማድረስም ሆነ የገበሬውን ምርት ለተጠቃሚዎች ለማከፋፈል ትራንስፖርት ወሳኝ ነገር ነው። የመኪናና የባቡር በተወሰነ ደረጃም የአየር መንገዶች መሠረተ ልማት መስፋፋት ለገጠር መዘመን ሚናቸው ከፍ ያለ ነው። ገጠሩን ከከተማ የሚያስተሣሥሩ ትላልቅ አውራ ጎዳናዎችን እየገነባን ነው። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ የአውራ ጎዳናዎች የማስተሣሠር ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። ይሁንና የሀገራችን የመንገድ ግንባታም በራሱ ረጅም ጊዜ፣ ጉልበትና ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ ሰፊ ሥራ ነው። በቂ መንገድ ባለመኖሩ የተነሣ፣ በበቂ ሁኔታ ሀገራችንን የማስተሣሠር ሂደቱ ፈታኝ፣ ዐቅምንና ጊዜን የሚጠይቅ ተግባር ሆኗል።

በቀጣይ በመንገድ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፈጠራ የታከለባቸው የተለያዩ መፍትሔዎች ያስፈልጉናል። በዚህም ከግል ዘርፉ ጋር በተለየ ቅንጅት መሥራት ይገባናል።

ርቀቶችን ለመሸፈንና ግዙፍ ቁሶችን ለማጓጓዝ ተመራጭ የሆነ መሠረተ ልማት ነው። የባቡር መጓጓዣ አገልግሎት በሌሎች ሀገራት በሰፊው የተለመደና በተለይም ረዣዥም የግብርና ግብአቶችንና ምርቶችን በሰፊው ለማጓጓዝ ዓይነተኛ መንገድ ነው። ሀገራችን ከአውራ ጎዳና ግንባታ ቀድማ የዘረጋቸው የባቡር መሥመርን ነበር። ዕድገቱ ግን በአንድ መሥመር ታቅቦ ቀረ። የባቡር መሥመር ዝርጋታ የመነሻ ወጪው ከፍተኛ ቢሆንም ጥቅሙ ከወጪው በላይ ነው።

ባቡር በአየር ሁኔታ እምብዛም አይስተጓጎልም፤ ፈጣንም ነው። የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስም በተነጻጻሪ የተሻለ በመሆኑ እንደ ሀገር በስፋት ልንጠቀምበት የሚገባ መሠረተ ልማት ነው። በቀጣይ ዓመታት ሀገር አቋራጭ የባቡር መሥመሮችን እንዘረጋለን። ለዚህም በፈጠራ የታጀቡ ዘመናዊ የባቡር መጓጓዣ ባለቤቶች የሚያደርጉንን መፍትሔዎች መከተል ይገባናል።

ዲጂታል ቴክኖሎጂና መሠረተ ልማት የግብርና ምርታማነትን በማሳደግና ሁለንተናዊ የገጠር ልማትን በማፋጠን ያልተነካ ትልቅ ዐቅም አላቸው። በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የግብርና መረጃ አገልግሎት በመስጠት፣ የአየር ትንበያን በመተንተንና መረጃ በማድረስ፣ የገበያ መረጃና ትሥሥርን በመፍጠርና የፋይናንስ አገልግሎትን በማዳረስ ከፍተኛ ዕድገት ያመጣሉ። በዘመኑ ቴክኖሎጂ በመደገፍ የግብርና ምርታማነትና ሽግግርን ያፋጥናሉ፡ የገጠሩን ማኅበረሰብ ሕይወት በመሠረታዊነት ለመለወጥም ያስችላሉ።

የዲጂታል ዘርፉን አስቻይነት በሥርዓትና በተግባር ለመምራት የፖሊሲና የፕሮግራሞች ጥልቀት ተግባራዊ ፍጥነታችንን ይወስነዋል። በመሆኑም ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታን የተረዳ መጪውን ማመላከት የሚችል ፖሊሲና ፕሮግራም ያሻናል። እርሱም ካረፈድንበት ለመነሣት፣ ከቀደሙንም ላይ ለመድረስ የሚያስችል ፍኖተ ካርታ በመሆን ለተግባራዊ ፍጥነት ዐቅም ይሆነናል። በዚህ መረዳት የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዲጂታል ኢኮኖሚን አንዱ የኢኮኖሚ አውታርና አስቻይ በማድረግ ዋነኛ የልማትና የዕድገት ዓምድ አድርጎታል።

በሀገራችን በአሁኑ ወቅት አገልግሎት እየሰጠ የሚገኘው ብቸኛው የባቡር መሥመር የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር ምሥር ነው። በአብዛኛውም ለነት ያገለግላል። ይሁንና ከቅርብ ጊዜያት ጀምሮ መጠነኛ የመንገደኞች ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

የዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ 2025 ለግብርና ዘርፍ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው የዕሴት ሠንሰለት፣ ለብዙኃን ዲጂታል መሠረተ ልማትና ለቱሪዝም ልማት ዐቅም በመሆን ምርትና ገበያን ለማሳደግ አልሞ ወደ ሥራ ገብቷል። የዲጂታል ፖሊሲና

CS CamScanner

ስትራቴጂ ሰነድ ሁሉም የኢኮኖሚ አውታሮች የዲጂታል ጉዳዮችን እንዲያካትቱና ዘርፉ በሀገራዊ ጥቅል ምርት ላይ ያለው አስተዋጽዖ እንዲጎለብት ተግባራዊ ተደርጓል።

ዲጂታል ቴክኖሎጂ የአፈር ባሕርይ የመረጃ ቋት በማደራጀት፣ የአዝርዕት ምርጫንና የግብአት አጠቃቀምን በትክክል የመወሰን ዐቅምን በማሳደግ፤ የሀብት ብክነትን በመቀነስ፣ ምርታማነትን ያሳድጋል። እንዲሁም ብሔራዊ የከርሰ ምድር ውኃ መገኛን በዲጂታል የመረጃ ቋት ለማመላከት መቻል፣ የውኃ መገኛዎችን በመለየት አጠቃቀማችንን ያሳድጋል።

የዲጂታል ቴክኖሎጂን ወደ ሥራ ለማስገባት ወሳኝ ከሆኑ መሠረተ ልማቶች አንዱ የግንኙነት _መሠረተ ልማት ነው። አርብቶና አርሶ አደሩን በትንሽ ወጪ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋር ለማገናኘትም ትልቅ ሚና አለው። በዚህ የተነሣ ሀገራችን ከጫፍ እስከ ጫፍ በግንኙነት መረብ እንድትተሣሠር በከፍተኛ ርብርብ እየሠራን እንገኛለን። የኢትዮ ቴሌኮም ባለ ገመድና ገመድ አልባ መረቦች ሀገራዊ ሽፋን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በእጅጉ ጨምሯል። ጥራትን ከመጨመርና ዋጋን ከመቀነስ አንጻርም ከፍተኛ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። ተደራሽነትን ከመጨመርና ዘርፉን በውድድር በሚገኝ ጥቅም ከማሳደግ አንጻር ለግል ባለሀብቶች ክፍት የማድረግ ሥራዎችን ሠርተናል። በውጤቱም የተሻለ ሀገራዊ ተጠቃሚነት እንደሚኖር ይጠበቃል። በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታትም በዘመናዊ የመገናኛ መረብ ሀገራችን ከጫፍ እስከ ጫፍ የምትገናኝ ይሆናል።

ከግንኙነትመሠረተልማት ባሻገር፣ ለዲጂታል ኢኮኖሚ ወሳኝ ከሆኑት መካከል፣ ኢንተርኔትን ለመጠቀም የሚያስችል ዐቅምን ያገናዘበ ተደራሽ ሞባይል መሰል ቁሶች ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህን ቁሶች፣ የገጠሩ ማኅበረሰብ ሊገዛ በሚችለው ዐቅምና መንገድ ተደራሽ ማድረግ ያስፈልጋል። የአስቻይ ዐቅሞች መሟላት የመረጃ ፍለጋንና ትንተናን ያሳድጋል። የውሂብና የተቋማትን ቅንጅት ይፈጥራል። አውቶሜሽንን ያስፋፋል። እንዲሁም ፈጠራ እንዲያብብ ያደርጋል። የግንኙነት መረብ የተሣለጠበት ሀገር አካታች፣ ውጤታማና በፈጠራ የዳበረ ልማትን ለማረጋገጥ ይችላል።

የግንኙነት መረብ ዲጂታል ቴክኖሎጂዎች መሠረታቸው ኤሌክትሪክ መሆኑ ይታወቃል። ያለ ኃይል አቅርቦት ጥቅም አልባ ናቸው። የኃይል አቅርቦትን ተደራሽ ማድረግ፣ በቴክኖሎጂዎቹ ላይ ነፍስ እንደ መዝራት ነው። በተለይም በጨለማ ውስጥ ለሚኖረው የገጠሩ ማኅበረ መሠረታዊ የመብራትን አቅርቦት ማዳረስ ወሳኝ ነው።

በተለያዩ መልኮች የምናመርተውን ኃይል ለገጠር ከማዳረስ አንጻር ከፍተኛ ክፍተት አለብን። የተለመደውን የኃይል ዋና መሥመር(Power Grid) ዝርጋታ የተከተለ እዩ ለገጠር ትልቅ ወጪን የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም ከዋና መሥመር ውጪ(Off Car አማራጮችን መጠቀም የተሻለ ነው። በእኛም ዘንድ በእነዚህ አማራጮች ላይ በስፋት መፍትሔዎችን ማምጣት ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ የፀሐይ፣ የነፋስ፣ የባዮማስ፣ ወዘተ. እየተሠራባቸው ይገኛል። በዚህ ረገድም ከግሉ ዘርፍ ጋር በመቀናጀት፣ ፈጠራን መሆኑ ያደረጉ ብዙ መፍትሔዎችን ወደ መሬት ማውረድ ያስፈልጋል።

የዘመናዊ ግብርና ባለቤትነታችንና ቀጣይነቱም የሚረጋገጠው በዘርፉ በምናደርገው የዐቅም ግንባታ ሥራዎችና ምርምሮች ላይ ነው። የሀገራችንን የግብርና ምርምርና ቴክኖሎ ደረጃ ማሻሻል፣ ማጠናከርና መለወጥ ይኖርብናል። ይህ ተግባር በጊዜ እንዳንቀደም፣ በ እንዳንወሰን፣ ብሎም የቀጣይ ዘመን ግብርና ምርት ከእጃችን እንዳይወጣ ያስችለናል የምርምርና የፈጠራ ኃይል ሰው ነው። ጊዜና ቦታን በምናብ አሻግሮ ማየት የሚችለው ነው። ዐቅምን ላቅ የሚያደርገውና የሚያፈጥነው ሰው ነው። ሐሳባዊና ቁሳዊ ፈጠራዎች ክሡት ለማድረግ ሰው ታላቅ ኃይል ነው።

ሀገራችን በአንጻራዊነት በግብርና ዘርፍ በርካታ የሰው ኃይል አፍርታለች። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በግብርና ምርምር ማዕከላት የሠለጠኑ ባለሞያዎች አሉን። ብሎ በግብርና ሳይንስ በየመስኩ የሚሠሩ የሠለጠኑ የምርምርና የተግባር ባለሞያዎች ቁ ከሞላ ጎደል በቂ የሚባል ነው። ይሁን እንጂ በግብርና ምርምር ውጤታማነት እንዲሁ በቴክኖሎጂ ፈጠራ

CamScanner

ከፍተኛ ክፍተቶች ይታዩብናል፡፡ የግብርና ምርምር ከቴክኖሎጂ ፈጠ አንጻር በሰብል ላይ የተሠራው ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ቢሆንም፣ የምርምር ውጤቶች ውጤታማነት ግን አነስተኛ ነው፡፡:

የግብርና ምርምር ቴክኖሎጂና ፈጠራ በግብርና ውስጥ በፍጥነት በማስፋፋት ምርት በመጠንና በዓይነት እንዲያድግ ማድረግ ተገቢ ነው። በድኅረ ምርት የሚደርሰውን ብክነትም መቀነስ ይገባል። የዕሴት ሠንሰለትን ማጠናከርና ገበያ መፍጠርም ወሳኝ ነው። በዚህም የገጠሩን ማኅበረሰብ ገቢ መጨመር ይቻላል። ግብርና የብዙኃኑ የኑሮና የኢኮኖሚ ዋስትናና እንቀሳቃሽ ነው። በመሆኑም በሀገሪቱ የግብርና ምርምርንና ልማትን በማጠናከር በየጊዜው አዳዲስ ፈጠራዎችን ማውጣት ከምርቱ ባልተናነሰ አስፈላጊ ነገር ነው። የግብርና ዘርፍ በዕጽዋትና በእንስሳት መስክ የሚደረጉ ምርምሮች፤ ዘመኑ በደረሰበት የምርምር ዕሳቤ ልክ መሆን አለባቸው። በግብርና ጥናትና ምርምር ላይ ኢንቨስትመንቶችን በማስፋፋትና በመደገፍ የዘርፉን መዋቅራዊ ሽግግር እናፈጥናለን።

በዚህ ረገድ የተጀመሩ ሥራዎችን አጠናክረን በፍጥነት በማስኬድ ግብርና በምርምርና በፈጠራ ላይ መሠረቱን እንዲያደርግ እንሠራለን፡፡ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ በሀገራችን ውድ በመቃኘት፣ ለአርሶና አርብቶ አደሩ እንዲመች ሆነው የሚሠሩ ቴክኖሎጂዎች ባለቤት እንሆናለን፡፡

በሚቀጥሉት ዐሠርት ዓመታት የቦታና የጊዜ ምልከታችን ይቀየራል። በምርምርና በቴክኖሎጂ የምርትና የማምረቻ ግብአቶች ይሻሻላሉ። በዚህም የእህል ሰብል ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ስንዴ በብዛት በማምረት ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ተሻግሮ ለጎረቤት ሀገራት ለመላክ ችለናል። የሥነ ምኅዳር ምቹነት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የገበያ ትሥሥር መፍጠር እንደሚቻል አሳይተናል።

በመንግሥት የሚደረጉ ሁለንተናዊ የግብርና ልማት ጥረቶች ተሳክተው ግብርና መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያደርግ የግል ዘርፉ ተሳትፎ በሁሉም መስክ በጉልህ ማደግ አለበት። እንዲሁም የመንግሥትና የግል ትብብርን በስፋት ማጠናከር ይጠይቃል። መንግሥት የሚሠራቸው ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለግል ባለ ሀብቱ ተሳትፎ ማመቻቸት ያለበት ነገሮችም አሉ።

በቀልበስ በ2015 ዓ.ም. 31.3 ሚልዮን ዶላር፣ በ2016: 33.7 ሚልዮን ዶላር እና በ2017 የመጀመሪያዎቹ ወራት ደግሞ 15 ሚልዮን ዶላር ያህል የውጭ ምንዛሪ አስገኝቷል።

በግብርና ዘርፍ የሚሠማሩ ባለ ሀብቶችን ማበረታታት፣ በኢንቨስትመንት የሚያጋጥሙ ሥጋቶችን መጋራት፣ በመንግሥትና በግል ዘርፍ ትብብር ምርምርንና ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ የሚጠበቁበት ናቸው። እነዚህን ማድረግ ከተቻለ ግብርናትን ካሉበት ተግዳሮቶችና ከመጪው ዘመን ፈተናዎች በፍጥነት እንዲወጣ ያስችለዋል።

በመደመር መንግሥት የለውጥ ሂደት የሚያስፈልግ የግብርና ትብብር አለ። ትብብሩም ትብብር ነው። ሁሉም በየመስካቸው የሚያደርጉት ጥረት ሲቀናጅ፣ ሀብትን በውጤታማነት በመጠቀም፣ አጠቃላይ ምርትን ማሳደግ ይቻላል። ዕውቀትና ካፒታልን በግብርናው ዘርፍ መንግሥት ከአርሶና አርብቶ አደሩ ጋር እና መንግሥት ከባለሀብቱ ጋር የሚያደርጉት በማጣመርና ፈጠራን በማበረታታት አጠቃላይ የምርት ዕድገት እንዲፋጠን ያደርጋል። በማላመድና በማሠራጨት ይታገዛል። የግሉ ዘርፍ በእነዚህ ቦታዎች እንዲሠማራ አስቻይ አርሶ አደሩ ያሉበትን ተግዳሮቶች አዳዲስ የአመራረት ስልትና ቴክኖሎጂ በመፍጠር፣ ሁኔታና ዕድሎችን በፖሊሲና በሕግ ብሎም በተግባራዊ ድጋፍ ለማመቻቸት ይሠራል። ይህም ሲሳካ የግሉ ዘርፍ ሰፋፊ የግብርና ልማቶችን ከቀላል ኢንዱስትሪ ጋር እንዲያያዝ ይደረጋል።

በአነስተኛ ይዞታ ለተሠማሩ ከአርሶና አርብቶ አደሮችም የመንግሥት የግብርና ድጋፍ ተጠናክሮ ይቀጥላል። እነዚህም የቴክኖሎጂ፣ የግብአትና የአዳዲስ ፈጠራ ሥነ ዘዴዎችን የማላመድ ድጋፍና ትብብር ናቸው። የሁሉንም ተዋንያን ዕቅም

CamScanner

በፈጠራና በፍጥነት በማቀናጀት፣ ግብርናን የሚያሻግር ዐቅም ይገነባል። ግብርና የሚሻገረው ሁሉን በጊዜና በቦታ መጠቀም ስንችል ነው። በፍጥነት በሚለዋወጠው ዓለም ውስጥ በጊዜ መፍጠን ያሻናል። ጊዜ፣ ቦታ፣ ሰውና ቴክኖሎጂ ዕምቅ ዕድሎቻችን ናቸው። የሥነ ሕዝብ ዕድገትና የአየር ንብረት ለውጥ ደግሞ ከፊታችን ያሉ ፈተናዎች ናቸው።

ኢትዮጵያ በምግብ ምርት ራሷን እንድትችል ታሪክ ቀያሪ ሥራዎችን እየሠራን ነው። ግብርናን በማስፋት፣ ምርምሮችን በመደገፍ፣ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድና ፈጠራዎችን በማበረታታት የፖሊሲና የለውጥ ርምጃዎች በሰፊው እየወሰድን እንገኛለን። የግብርናውን ዘርፍ ከዲጂታል፡ ከምሕንድስና ቴክኖሎጂዎችና ከባዮቴክኖሎጂ ጋር ለማጣጣም እየታገልን ነው። የግብርና ኢንቨስትመንትን ማጎልበት የሠርክ ሥራችን ሆኗል። ለዘላቂ ምርትና ምርታማነት ዕድገት የሚረዱ የተሻሻሉ ግብአቶችንና የሀብት አጠቃቀምን ማሳደግ ከሁሉም ሥራችን የምናስቀድመው ነው። በዚህም የኢትዮጵያን ግብርና በሚቀጥሉት ባሠርት ዓመታት ፈጣን እመርታዊ ለውጥ እናረጋግጣለን።

### 6.2.2. ዘመናዊ የግብርና ምርቶች ንግድን ማስፋፋት

የግብርና ምርታማነት ማደግ ለብዙ ዘርፎች የሚሆን ወረት ይፈጥርልናል። በተለይ ገጠርን ለማሸጋገር የመጀመሪያ ርምጃ ይሆነናል። በገጠር ሽግግር ሂደት ዘመናዊ የግብርና ንግድ የተለየ ትኩረት የሚፈልግ ነው። ምክንያቱም ዘመናዊ የግብርና ንግድ ለግብርና አስፈላጊ የሆኑ ግብአቶችን ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብና የተመረቱ ምርቶችን በፍጥነት ወደ ኢኮኖሚው ሥሉጥ በሆነ አግባብ ለማቅረብ የሚያስችል ነው። ይህ የንግድ ሥርዓት ብዙ ዘርፎችን ባማከለ ሁኔታ መመራት ይኖርበታል።

የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን ከመጀመር እስከ ማስተዳደርና ማስፋፋት ያለውን ሂደት በሙሉ ዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ (Agri-Entrepreneurship) በግብርናው ዘርፍ ውስጥ ያካትታል። ግብርናን ጨምሮ የግብርና ምርቶችን ማቀነባበር፣ ማሸግና ወደ ገበያ ማቅረብ፣ ዘመናዊ የግብርና ግብዓቶችን ማምረትና ማከፋፈል፣ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማዳበርና ማቅረብ፣ እንዲሁም የግብርና ምርቶችን በዲጂታል ቴክኖሎጂ ማርኬቲንግ ማከናወንን ያካትታል። የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ከዚህም በላይ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና ዘላቂነት ያላቸው ስልተ ምርቶችን መጠቀም፣ ምርታማነትን ማሻሻል፣ የምግብ ዋስትናን ማጎልበትና ዕሴት የሚጨምሩ ምርቶችን መፍጠርን ይጨምራል። እነዚህን ተጠቅሞ በኢኮኖሚው ውስጥ ብዙ የሥራ ዕድሎችን መፍጠር፣ የሀገር ውስጥ ገበያዎችን ማበረታታትና የአካባቢ ችግሮችን መፍታት ደግሞ ሌሎች ጥቅሞቹ ናቸው።

ዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ከባህላዊ ግብርና እስከ ባዮቴክኖሎጂ ድረስ የተለያዩ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን ይነካል። ይህም ስኬታማ እንዲሆን በሥራዎቹ ላይ ቅልጥፍናንና ዘላቂነትን ለማሳደግ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና ልምምዶችን በፈጠራ እየታገዘ በፍጥነት ማካተት ይኖርበታል። ሥራዎቹ ምርታማ በሆኑበት ልክ ወደ ኢኮኖሚው ግብአት እንዲሆኑ በተጓዳኝ የሚፈልጉት ድጋፎች፣ መሠረተ ልማቶችና ሥነ ምኅዳር አሉ። የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመሸጥ የሚያስችል የግብይት ሥርዓትና ዐቅም አስፈላጊ ነው። ለዚህም ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የተጣጣሙ ውጤታማ ስልቶችን መዘርጋት ይጠይቃል። ከዚህ ባሻገር አዳዲስ ገበያዎችን ማልማት የግድ ይላል። ይህ ሁሉ ደግሞ ጊዜያዊ የደቦ ሥራ መሆን የለበትም። ለዘላቂነት ጠንከር ያለ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። በተጨማሪም የሀብትንና በአጠቃላይም የሥነ ምኅዳሩን የረጅም ጊዜ አዋጭነት የሚያበረታቱ ለአካባቢው ተስማሚ አሠራሮችን መተግበር የግድ ነው።

የገጠር ሽግግር እንዲፋጠንና ማኅበራዊ ኢኮኖሚ መነሣሣት እንዲኖር ዘመናዊ የግብር ወደ አትራፊ ሥራነት ይቀይረዋል። በግብርና ውስጥ ከግብአት እስከ ገበያ ድረስ ትሥሥር በመፍጠር ሽግግሩን ያፋጥናል። ዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ በአነስተኛ ግብርና ገቢያቸውን እንዲጨምሩ ያስችላል። በገበያ ልምምድ ውስጥ የገበያ ምርቶችን ማምረትና የተሠማሩ

CS CamScanner

አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ለገበያ የሚተርፍ ምርት በማምረት የቤተሰብ የገበያ ባሕርይን የመረዳት ተጨማሪ ልምድና ክሂሎትን ያስገኝላቸዋል። በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን ሥራ አጥ ወጣቶች፣ ንቁና ትርፍ አምራች አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራትና የተለያዩ የገጠር ማኅበራት አደረጃጀቶች በዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ውስጥ ፈር ቀዳጅ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማመቻቸት የመደመር መንግሥት አንዱ ትኩረት ነው።

ዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕረነሮች በስኬታቸው ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ በርካታ ጉልህ ፈተናዎች ያጋጥሟቸዋል። የመጀመሪያው የገበያ ተደራሽነት ነው። እንደሚታወቀው በተወዳዳሪ የአቅርቦት ሠንሰለቶች ውስጥ ስኬታማ ሆኖ ለመቀጠል፣ ከአከፋፋዮች ከቸርቻሪዎች ጋር ትሥሥሮችን መፍጠር አስፈላጊ ነው። በዚያው ልክ ደግሞ አስቸጋ ነው። በተለይም የግብርና ምርቶችን የሚያቀርቡ ነጋዴዎች የምርት መበላሸት ከፍ ኪሣራን ሊያስከትልባቸው ይችላል። ከዚህም ሌላ፣ ለመሬት፣ ለመሣሪያና ለቴክናሉ፤ የሚያስፈልገው መነሻ ወረት በአብዛኛው ከፍተኛ ነው። ገንዘቡን በብድር ወይም በርዶ+ ማግኘት ደግሞ ውስብስብ፣ በውድድር የተሞላና ዋስትና ያስፈልገዋል። በዚህም የተነ የግብርና ኢንተርፕረነሮች ሕልማቸውን በቀላሉ ወደ ተግባር ለመለወጥ ይቸገራሉ፡ ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ የመንግሥት ደንቦችን፣ የምግብ ደኅንነት ደረጃዎች የአካባቢ ሕጎችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል። የቁጥጥሮች መብዛትና መወሳሰብ፣ በተለይ ለጀማሪ የግብርና ኢንተርፕረነሮች ተነሣሽነት እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ።

በመሆኑም፣ እነዚህንና ሌሎችተግዳሮቶችንለመሻገር፣ በዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕረነርሽ ውስጥ ስኬታማ ለመሆን፣ ባለ ርዕዮች አስፈላጊ ክሂሎቶችን መላበስ ይኖርባቸዋል በተለይም በሀገራችን ዘመናዊና መደበኛ የንግድ ሥራ በተደራጀ መልኩ በማኅበረሰቡ ው አልሠረፀም። ስለዚህም ባለ ርዕዮችን በማንቃት ረገድ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ቀርጾ መንቀሳቀስ የግድ ነው። የግብርና ኢንተርፕረነሮች የገበያ አዝማሚያዎች፣ የገንዘብ አስተዳደር፣ ጠንካራና ዘላቂ የንግድ ትሥሥሮችና ውጤታማ የግብይት ስልቶች ላይ ያላቸውን ዐቅሞች ማጎልበት፣ በስኬታቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕርነርሺፕ የዘወትር ተግባር ለማድረግ የንግድ መሠረታዊ ትምህርትን መማርና አስፈላጊውን ጥበብ መላበስ ወሳኝ ነው። ዐውደ ጥናቶች ፣ የበይነ መረብ የመስመር ላይ ትምህርቶችና የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ለዚህ ጠቃሚ ናቸው። እነዚህን ጨምሮ፣ ሥራ ፈጣሪዎች ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ክሂሎቶችን እንዲካኑ ቀጣይነት ያለው ሥልጠናና የዕውቀት መጋራት አካሄዶችን መከተል ያስፈልጋል።

በተጨማሪም የገንዘብ አቅርቦትና የክሂሎት ግንባታ በቅንጅት መካሄድ አለበት። ይሄም የፋይናንሶት፣ በገጠር ቁጠባና ብድር ማኅበራት፣ በንግድና ልማት ባንክ፣ በኢትዮ ቴሌኮም፣ ዘርና በግብርና ልማት፣ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣ በአነስተኛ ማይክሮ በቴክኒክና ሞያ ኮሌጆችና በአጋር አካላት ቅንጅት እንዲሠራ ማድረግ ያስፈልጋል። የሬውን የፋይናንስ ተደራሽነት ለማሳደግ ንግድ ባንኮች ያለ መያዣ የሚሰጡትን ብድር እያደግን ነው። የኢትዮ ቴሌኮምን ማይክሮ የብድር

አቅርቦትን ጅምሩን እያሰፋን መሄድ ✓ አለብን። እነዚህ ለግብርና ኢንተርፕረነሮች ትልቅ ዕድል ይሆናሉ።

ዲጂታል ኢትዮጵያና የኃይል አቅርቦት ልማት በፍጥነት እየተስፋፋ ነው። ይህ ደግሞ | የገጠሩን ማኅበራዊ የኢኮኖሚ ምኅዳሩን ይቀይረዋል። የእርሱ መቀየር ደግሞ ለግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ምቹና አስቻይ ከባቢን በፍጥነት በመፍጠር ላይ ይገኛል። ዲጂታል ኮኖሚን ለመገንባት የሚያስችል መሠረተ ልማትን በማስፋፋት፣ አስቻይ ሥርዓትን በመዘርጋት፣ መተግበሪያዎችን በማበልጸግና አጠቃላይ ትሥሥሮችን በመፍጠር ላይ በስፋት እየሠራን እንገኛለን።

በግብርና የገጠር ልማትን ለማፋጠን እንዲቻል፣ ለዘመናዊ የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች የሚሰጠው ድጋፍና ማበረታቻ በፖሊሲ ተደግፏል። የግብርና ኢንተርፕረነርሺፕ ቴክኖሎጂ ፈጠራ የግብርና ምርታማነትን ከማሳደግ በላይ ነው። አዳዲስ የሥራ ዕድሎችንና ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር፣ ማላመድ፣ ማሠራጨት፣ ብሎም ወደ ውጭ መላክ መጻዒ ትልማችን ነው። አነስተኛና መካከለኛ የሥራ ፈጠራዎችን በማስፋፋት ከተማና በገጠር ያለውን ልዩነት በማቀራረብ

CamScanner

የተስፋ ብርሃን አሳይቶናል። የስልክና 1 የኢንተርኔት መስፋፋት በከተማና በገጠር የገበያ ግንኙነት ለመፍጠር እያስቻለ ነው። የግብርና ምርቶችን፣ ጥበበ ዕድን፣ የአግሮ ኢኮሎጂ ቢዝነስንና የመሳሰሉትን ማስተዋወቅና መሸጥ እየተለመደ መጥቷል።

## 6.3. አረንጓዴ ዐሻራ

ለሰውና ለፍጥረታት አንድና ብቸኛ መኖሪያ የሆነችውን መሬት፤ ሰዎች ፍላጎታቸውን ለማርካት በሄዱት ጥንቃቄ አልባ ጉዞ፣ በበርካታ ለውጦች አስጨንቀዋታል። የአየር ንብረት ለውጥ፣ የብዝኃ ሕይወት መመናመንና የናይትሮጂን ዑደት ምድርን ሰቅዘው ይዘዋታል። በየትኛውም የዓለም ጥግ ያለና በምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚገኝ ሀገር መሬትና አካባቢዋ በጭንቀት ከምትወልደው አደጋና ጥፋት አልዳነም፤ አይድንም። ሁሉን በያለበት የችግሩ ገፈት ቀማሽ ሆኗል።

በተለይ ኢኮኖሚያቸው በግብርና ላይ የተመሠረተ አዳጊ ሀገራት ጉሮሯቸውን እንደተያዙ ያህል ነው። የአዳጊ ሀገራት በምግብ እጥረት መጎዳት በፍጥነት የሚታይ ነገር ነው። ይሁ እንጂ የአየር ንብረትና ተያያዥ ለውጥ በምድር ላይ ላለ ሰውና ፍጥረታት በሙሉ በግልጽ ሥጋት ፈጥሯል፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተለዋዋጭነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተከሠቱ ላሉ ችግሮች ዋነኛ መንሥኤ ነው። ድርቅ፣ የተመጣጠነ ምግብ እጦትና የድህነት መባባስ የዚህ ውጤት መሆናቸውን በአየር ንብረት ላይ የተደረጉ በርካታ ጥናቶች ያመላክታሉ። የአየር ንብረ ለውጥ የምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትን፣ አጠቃቀምንና መረጋጋትን አዛብቷል። ለውጡ በአጠቃላይ በምግብ ዋስትና ጉዳዮች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው።

የአየር ንብረት መዛባት የተለያዩ መፍትሔዎች አሉት። ከሁሉም በላይ ግን በቂ የደን ሽ መኖር ችግሩን ለመቀነስ ሁነኛ መፍትሔ ነው። ይሁንና በተለይም ከእርሻ ማስፋፊ ጋር በተያያዘ የደን ጭፍጨፋ በከፍተኛ ደረጃ በዓለም ላይ የተንሠራፋ ችግር ሆናለ በሀገራችንም ያሳደረውን ከፍተኛ ተጽዕኖ በተለያዩ ዘመናት ተመልክተናል።

የደን መጨፍጨፍ የአየር ንብረት ከማዛባት በተጨማሪ የአፈርን ጥራት በማበላሸትና የውኃ አቅርቦትን በማስተጓጎል በግብርና ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል። ዛፎች የአፈርን ጤና ይጫወታሉ። በተቃራኒ፣ መጨፍጨፋቸው ደግሞ የአፈር ለምነትንና የእርጥበት መጠንን በመጠበቅ፣ የአፈርን መሸርሸር በመከላከልና የውኃን ዑደትን በመቆጣጠር ረገድ ወሳኝ ሚና ይቀንሰዋል። መሬቱን ለእርሻ ለማዋል አስቸጋሪና ምርት የማይሰጥ ይሆናል።

በተጨማሪም የደኖች መጨፍጨፍ የአየር ሙቀት መጨመርን ያስከትላል። እነዚህ የአየር ሁኔታ ለውጦች ደግሞ በተራቸው በሰብል ዕድገትና ምርት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያድራሉ። በአጠቃላይ የግብርና ምርታማነትና የደን ልማት የማይነጣጠሉ ጉዳዮች ሆነዋል። በሀገራችንም የደን በከፍተኛ ደረጃ መመናመን ለግብርናችን ምርታማነት ማጣት ዋነኛው ተግዳሮት ሆኖ ዘልቋል።

ደን በተለያዩ ዘዴዎች የዝናብ መጠንን በመጨመር በአካባቢው የአየር ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል። ዛፎች በዝናብ ዑደት ውስጥ ውኃን በመሳብና ወደ ከባቢ አየር በማስተላለፍ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ። በመተንፈሻ አካላቸው አማካኝነት እርጥበትን ወደ ከባቢ አየር በመልቀቅ ለደመና መፈጠር አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። በዚህም የአካባቢው ዝናብ እንዲጨምር ያግዛሉ።

ይህ ሂደት በአካባቢው ያለውን የርጥበት መጠን ከፍ ያደርገዋል። ለበለጠ ርጥበትና ዝናብ መዝነብም ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። በተጨማሪም የደን ተከላ የአፈርን አወቃቀርና የርጥበት መጠንን ያሻሽላል። ጤናማ አፈር ብዙ ውኃ እንዲይዝ፣ የውኃ ፍሳሽ እንዲቀንስና የከርሰ ምድር ውኃ እንዲጨምር ያደርጋል። ይሄም ከጊዜ ወደ ጊዜ በአካባቢው የሥነ ውኃና የዝናብ ሁኔታ ላይ በጎ ተጽዕኖ ያሳድራል።

CamScanner

ኢትዮጵያ በደን የተሸፈነች ሀገር ነበረች። ከተራሮቿ የሚወርዱት ወንዞችና በዓመት ውስጥ በተመጣጣኝ የምታገኘው ዝናብ ከምቹ መልክዐ ምድራዊ አቀማመጧ ጋር ተደምሮ የደን ሀገር አድርጓት ነበር። በሂደት ግን በሕዝብ ብዛት መጨመር፣ በእርሻ ሥራ መስፋፋት፣ የደኖችን ውጤቶች ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች በመጠቀም እና በመሳሰሉት ምክንያቶች የደን መጠኑ ተመናመነ። በዚህ የተነሣ በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እየደረሰ ያለውን ተጽዕኖ ለመቋቋምና የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ከኮንፈረንስና ከመፈክር ያለፈ ተግባራዊ ምላሽ ይፈልጋል።

ደኖች የውኃ ተፋሰሶችን ንጹሕነት በመጠበቅ፣ የአካባቢ ሥነ ውኃን በመቆጣጠርና ለመስኖ አገልግሎት የሚውል የውኃ አቅርቦትን በማረጋገጥ ለተሻሻለ የውኃ አያያዝ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። ይህ የውኃ መረጋጋት አርሶ አደሩ ዘላቂነት ያለው አሠራር እንዲከተልናምርቶቹን ከአንድ ዓይነትና ከአንድ ወቅት የሰብል ምርት ወደ ብዙ ዓይነትና ብዙ ወቅት እንዲለውጥ ያስችለዋል። የአየር ንብረት ለውጥንና የገበያ መዋዠቅን የሚቋቋምበት ዐቅም ያሳድግለታል። በዚህም ለግብርና ሽግግር የራሱን አስተዋጽዖ ያደርጋል።

በተጨማሪም የደን መልሶ ማልማት ሥራዎች አዳዲስ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ይፈጥራሉ። ለመጥቀስ ያህል የግብርና ጥምር  ደን ልማት፤ የቱሪዝም ልማትና ዘላቂ የጣውላ ምት ተጠቃሚ ያደርጋሉ። ይሄንንም በመፍጠር ለገጠር ሽግግር በጎ አስተዋጽዖ ደንን መልሶ በማልማትና በግብርና መካከል ያለው ትሥሥር የበለጠ ዘላቂነት የግብርና ሥርዓትና የማይበገር የገጠር ኢኮኖሚ እንዲኖር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

በለውጡ ማግሥት የጀመርነው የአረንጓዴ ዐሻራ የደን ልማት ፕሮጀክት ሁለት ዓላማ ነበረው። የመጀመሪያው የደን መመናመንን መዋጋት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ሀገሪቱን የአየር ንብረት መዛባትን ለመቋቋም ያላትን ዐቅም ለማሳደግ ያለመ ነው። ይህ ተነሣሽነት ላለፉት ስድስት ዓመታት በተከታታይ ተካሂዷል። ይቀጥላልም።

በእነዚህ ስድስት ዓመታት ከታቀደው የተከላ መጠን በላይ እየተከልን እንገኛለን። ተነሣሽነቱ ጉልህና ተጨባጭ ለውጥ ያመጣንበት ትልቅ ስኬት ነው። ሕዝባችን ከተ ግዙፍ ስኬቶችን የማስመዝገብ ከፍተኛ ዐቅም እንዳለን አይተንበታል። የደን መመናመን የመሬት መራቆትን፣ የውኃ ማጠርንና የአየር ሁኔታን ከማስተካከል ባለፈ ዘላቂ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ከፍተኛ የሆነ ክንዋኔ ነው።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ዋና ግብ የገጠርና የከተማ አረንጓዴ ልማትን ተግ በማድረግና ለሀገሪቱ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና አስተዋጽዖ ማበርከት በዚህ ዓላማ በመመራት የመጀመሪያው የአራት ዓመት ምዕራፍ በድል ተጠናቅቋል በሁለተኛው ምዕራፍ ውጤታማ የትግበራ ጉዞ ላይ ይገኛል።

ይህ ተነሳሽነት የተራቆተ መሬትን ወደነበረበት ለመመለስ ብዝኃ ሕይወትን ለማሻሻልና በአካባቢያዊ ማኅበረሰቦች መካከል የአካባቢ ጥበቃ ባህልን ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ተጫውል። በመርሐ ግብሩ የሀገር በቀል ዛፍ ዝርያዎችን በመትከል ላይ አጽንዖት ተተናል። ይሄም የሥነ ምኅዳሩን ሚዛን ለመጠበቅና ለአየር ንብረት መዛባት የማይበገር ከባቢን ለመፍጠር አግዟል። በዚህም በተለያዩ የአካባቢ ሁኔታዎች ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ናትን አሳድሯል። የደን ሽፋንን በመጨመር የአየር ንብረት መዛባትን መከላከል፣ ፈርን ጥራት ማሻሻልና የውኃ ዕቅበትን ማገዝ የመጀመሪያ ውጤቶቹ ናቸው። ይህም | የብርና ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጃ ይጨምረዋል። ሥነ ምኅዳሩን መልሶ በማቋቋም ለኃ ሕይወት ማገገም አስተዋጽዖ ያደርጋል። ለውጦችን ለመቋቋምም ዐቅምን ያሳድጋል።

| የኢትዮጵያ አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አንዱ ምሰሶ “ምግብን ከጓሮ” የሚለው ነው። | ለምግብነት የሚውሉ ዛፎችን በመትከል፣ ለምግብ ዋስትና አስተዋጽዖ ያደርጋል። | የአካባቢው ማኅበረሰቦች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ከማስቻል አኳያም ከፍተኛ ■ አበርክቶ አለው። ፍራፍሬና ሌሎችንም ለምግብነት የሚውሉ ፍሬዎችን የሚያፈሩ ዛፎችን | ደን መልሶ

CS CamScanner

ማልማት ጋር ያዋሕዳል። በዚህም የተራቆቱ መሬቶችን መልሶ ማቋቋም ብቻ | ሳይሆን፣ የገጠር ነዋሪዎችን አመጋገብ ሊያሳድጉ የሚችሉ አስፈላጊ የምግብ ምንጮችን ያቀርባል።

እዚህ ለምግብነት የሚውሉ ዛፎች ዘርፈ ብዙ አገልግሎት ይሰጣሉ። ዘላቂ የሆነ የፍራፍሬና ሌሎች አቅርቦትን በማቅረብ አመጋገብን ያሻሽላሉ። እንዲሁም ለአርሶና አርብቶ አደሮች ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ዕድሎችን ይፈጥራሉ። ከዚህም ባሻገር ለምግብነት የሚውሉ ፎችን ማልማት በአየር ንብረት መዛባት ተጽዕኖዎች ሰብሎች በሚጎዱበት ወቅት፣ አማራጭ የምግብ ምንጮችን ለማቅረብ ያግዛል። በአጠቃላይ ይህ አካሄድ የሥነ ምኅዳር ተሐድሶን ከመደገፍ ባለፈ፣ የምግብ ዋስትናንና ኑሮን ያጠናክራል። ማኅበረሰቡ የበለጠ ራሱን እንዲችልና ለምግብ እጥረት ተጋላጭ እንዳይሆን ይረዳል።

በሌላ በኩል ደግሞ ከተጀመረበት ጊዜ አንሥቶ የየአካባቢው ነዋሪዎች በችግኞች ተከላና ከብካቤ ላይ እንዲሠማሩ ሲበረታቱ ነበር። ችግኝ በማፍላት፣ ጉድጓድ በመቆፈር፣ ችግኞችን | በመከባከብ፣ ችግኞችን ከራስ ኪስ ገዝቶ በቤተሰቡና በአካባቢ ደረጃ በመትከል፣ ወዘተ. 1 ሕዝቡ ተሳትፏል። ይህም ዛሬ በመጠኑ የሚታይ የባህል ለውጥን እያመጣ ነው። ትምህርት [ ቤቶች፣ ሕፃናትና ቤተሰቦች ባህል እያደረጉት ነው። ይህም ዛፍ መትከልና መከባከብ 1 የኅብረተሰቡ ባህል ወደ መሆን እያደረገ መሆኑን የሚጠቁም ነው።

.

በአጠቃላይ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብርን ለሀገራችን እንደሚሆን አድርገን በፈጠራና በፍጥነት እየተገበርነው ነው። በለውጡ ዕሳቤ መሠረት ለችግሮቻችን የምንሰጠው መፍትሄ አምስት ማሕቀፎች ያሉት ሲሆን፤ ለአየር ንብረት ለውጥ ችግር በዚሁ መርሕ መሰረት ምላሽ እየሰጠን እንገኛለን።

አንደኛው ሥራው በመርሕ የሚመራ መሆኑ ነው። ያም ማለት ኢትዮጵያን እንደገና በአረንጓዴ ልብስ የማልበስ መርሕ ነው። ጉዳዩ ከኢትዮጵያ ህልውና ጋር ብልጽግናችንን የሚወስን ነው።

ሁለተኛው፥ መርሐ ግብሩን በራሳችን ልንተገብረው የምንችል መሆን አለበት ነው። የግድ ከውጭ ርዳታ፣ ፈንድ እና ትብብር ጋር ማገናኘት የለብንም፤ በኢትዮጵያውያን ዐቅም ሊተገበር የሚችል መሆን አለበት።

ሦስተኛው፥ ለኮሙኒኬሽን ወይም ለኮንፈረንስ ወይም ለሐሳዊ የአካባቢ ጥበቃ ገና የሚሠራ መሆን የለበትም። የምንሠራው ሥራ በሀገራችን ላይ ተጨባጭ ውጤት የሚ መሆን አለበት የሚለው ነው። ለውጡም በአየር ንብረት ሚዛን፣ በምግብ፣ በፈር በወንዞች ፍሰት መስተካከል፣ ወዘተ መታየት አለበት።

አራተኛው፥ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በሚመለከታቸው ተቋማት ታቅዶ ቢን ሕዝቡን በሙሉ ሊያሳትፍ መቻል አለበት የሚለው መርሕ ነው።ተሳትፎውም ማኅበረሰቦችን፣ የማኅበረሰብ ክፍሎችን፣ የእድሜ ደረጃዎችን፣ የእምነት አካባቢም ጾታዎችን፣ ወዘተ. እንዲያካትት ተደርጎ መዘርጋት አለበት። ይህ ደግሞ አምስተኛ መርሕ ለመተግበር ያስችላል።

አምስተኛው፥ የባህል ለውጥ ማምጣትን የሚመለከት ነው። ዛፎችን መትከል፣ መ በተገቢው መንገድ መጠቀም የዘመቻ ሥራ ከመሆን አልፎ የሕዝብ ባህል መሥራት ነው።

አረንጓዴ ዐሻራ በእነዚህ የመፍትሔ መንገዶቻችን የተመራ ነው። መርfh፣ ኢ በሀገር በቀል ዛፎች መልሶ ማልበስ ነው። ይህንንም ራሳችን ችግኞችን በማፍላት እ በማስተባበርና ሀብትን በመቆጠብ ማከናወን ችለናል። የአረንጓዴ ዐሻራን ካቢ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ውጤት የምንለካባቸው መለኪያዎች አሉን። ለእነዚህ መለኪያ ታማኝ በመሆንም በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ በመተግበርና የሚማል በማበጀት መርተነዋል።

### 6.4. የእንስሳት ሀብት፡ የገጠር ሽግግር ምሰሶ

CamScanner

ለማምረት፣ በሥራ ፈጠራና በንግድ ዙሪያ ከፍተኛ አበርክቶ ያለው ዘርፍ ነው። በዓለም ዓለም ላይ ግዙፍ ከሚባሉ ኢንዱስሪዎች መካከል የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ አንዱ ዓይ ዘርፉ፡ በግብርና ኢንዱስትሪ ውስጥ ወሳኝና ግዙፍ ሚና የሚጫወት፤ ምግብ ሊሆን፤ በቢልዮኖች ለሚቆጠሩ ሰዎች የኑሮ መሠረት የሆነ፤ ለብዙዎች ደግሞ ኑሯቸውን ቢና ውስጥ ወደ ግማሽ የሚጠጋው ውጤት ከዚሁ የእንስሳት ሀብት ልማት የሚገኝ የሚደጉም ዘርፍ ነው::

በውስጡ የሥጋ፣ የወተት፣ የዕንቁላልና ሌሎች የእንስሳት ውጤቶችን ይዟል። በቢልዮኖች የሚቆጠሩ ከብቶችና ዶሮዎች፣ በመቶ ሚልዮኖች የሚቆጠሩ በጎችና ፍየሎች፣ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎችን ጨምሮ የብዙ ኢንዱስትሪዎች ዋና ዘዋሪ ዘርፍ ነው። በሌላ ጎኑ ደግሞ ሎች እንስሳትን አካቶ የያዘ ዘርፍ ነው። በመሆኑም የመጓጓዣ፣ የጤናና የምግብ ፉ ከፍተኛ የመሬት መጠንን የሚጠቀም፣ ከፍተኛ የውኃ አቅርቦትን የሚፈልግና ከፍተኛ በካይ ጋዞችን የሚያመነጭ በመሆኑ፣ ከኢኮኖሚም ይሁን ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር ከፍተኛ ተጽዕኖ ያለው ዘርፍ ነው::

ከቅርብ ዓመታትም፤ በዓለማችን ላይ በሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ በገቢ ዕድገትና በአኗኗር ቤ ለውጥ እንዲሁም በምግብ ፍላጎት ለውጥ ምክንያት የእንስሳት ውጤቶች ፍላጎት በፍጥነት እያደገ ነው። በአደጉት ሀገራት የነፍስ ወከፍ የእንስሳት ውጤቶች አመጋገብ ምጣኔ በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት በተነጻጻሪ ከፍተኛና ለረጅም ጊዜ ወጥ ሆኖ የቆየ ነው። በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የእንስሳት ተዋጽዖዎች ፍላጎት እስከ 203o በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያድግ ይጠበቃል።

ይሁንና እስካሁን ባለው ሁኔታ፤ በአዳጊ ሀገራት ዋነኛ የሰውነት ኃይል(Calory) ምንጭ ከእህል የሚገኝ ሲሆን በአደጉ ሀገራት ደግሞ ዋነኛ የሰውነት ኃይል ምንጭ ከእንስሳት ውጤት ይገኛል።

በመሆኑም የዓለም የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ፣ ከዚህ በፊት ያቀረብ ከነበረው ምርት በእጅጉ የበለጠ እንዲያቀርብ ይጠበቅበታል። በተለይም እንደ እኛ በማደግ ሀገራት የእንስሳት ተዋጽዖዎች ለአመጋገብ ሥርዓት የሚያበረክቱት አስተዋጽዖ ሁኔታ ይጨምራል። ከዚህ ከፍተኛ የፍላጎት ጭማሪ የተነሣ፣ ዘርፉ በከፍተና ደረዳ ዕድግ እንደሚኖረውና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ከሚስቡ ዘርፎች መካከል እንደሚሆን ይጠበቃሉ ተዋንያን አሜሪካ፣ ብራዚል፣ ቻይና፣ ሕንድና መሰል ሀገራት ናቸው። አሜሪካ በከፍቶ በዓለም ላይ ከፍተኛ የግብርና ዘርፍና ጠንካራ የውጭ ገበያ ያላቸው ዋነኞቹ የ ቴክኖሎጂ የሚታገዝና በሥጋና በዶሮ ምርት መሪነቱን የያዘ ኢንዱስትሪ ባለቤት ናት ብራዚል ለዘርፉ ከፍተኛ መሬት በመመደብ፣ ውጤታማ የእንስሳት ሀብት ልማት ባለቤት ከፍተኛ የሥጋና የዶሮ ምርትን ለውጭ ገበያ አቅራቢ ናት። ቻይና ደግሞ ዋነኛ የማ አምራችና ተጠቃሚ፣ እንዲሁም በከብት ሥጋና በወተት ውጤቶች ምርትም ትልቅ እያስመዘገበች የምትገኝ ሀገር ናት። ሕንድ በበኩሏ፣ በዓለም ቀዳሚ የከብት ብዛት የወተት ውጤቶችና የጎሽ ሥጋን ለውጭ ገበያ የምታቀርብ ዋነኛ ተዋናይ ናት..

እንደ ብዙዎቹ ዘርፎች ሁሉ ቴክኖሎጂ በዚህም ዘርፍ ከፍተኛ የለውጥና የሽግግር ሚናም እየተጫወተ ይገኛል። በዚህም ውጤታማነትን ይጨምራል፤ የእንስሳቱን ጤናና የ ያስጠብቃል፤ እንዲሁም ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር ከፍተኛ አስተዋጽዖዎችን እ ይገኛል። ከእነዚህ በቀዳሚነት የሚነሣው ምጥን የእንስሳት ሀብት ልማት (Precisin Livestock) ነው።

ቴክኖሎጂው ዓለም አቀፍ አካባቢ ጠቋሚን (GPS) ጨምሮ የተለያዩ አነፍናፊ ድሮኖችን፣ ግዙፍ ውሂብ ስሌትን፣ ሰው ሠራሽ አስተውሎትንና ሌሎች መሰል መሣሪ ይጠቀማል። ቴክኖሎጂው የእንስሳትን የጤና ሁኔታ፣ ባሕርይና ዕድገት መከ የሚያስችል ቴክኖሎጂ ነው።

ስለሆነም አርብቶ አደሮች በሽታን አስቀድመው መለየት እንዲችሉ፤ የተመጠነ መኖ አጠቃቀም እንዲኖራቸውና የተሻለ የማዳቀል ውጤት እንዲያገኙ አስችሏቸዋል። ሌላ በኩል ደግሞ ሮቦትን የተንተራሱ የመኖ ምገባና የወተት እለባ ሥርዓቶች

CamScanner

ጥራትንና ታማነትን እየጨመሩ ናቸው። ከዚህም ባለፈ፣ ተፈላጊውን የሰው ጉልበት ቀንሰው፤ በጥቂት የሰው ኃይል ብዙ ሥራዎችን ለመሥራት አስችለዋል።

በእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የላቀ ልምድ ያላቸው ኔዘርላንድስ፣ አውስትራልያ፣ ዩናይትድ መከተል ዘርፉን አዘምነዋል። ኔዘርላንድስ በከፍተኛ የቴክኖሎጂ እርሻዎች፣ በዘር ነ፣ ዴንማርክና ካናዳ፣ ከባህላዊ ዘዴዎች ባሻገር፣ ሥሉጥና ዘመናዊ አካሄዶችን ያና በምግብ ውጤታማነት ላይ በማተኮር፣ በወተት ምርታማነት ውስጥ ዓለም አቀፍ መሪ ሆናለች። በተለይም በአካባቢ ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ለመቀነስ የምጥን የእንስሳት ሀብት ልማትን በስፋት ትጠቀማለች።

አውስትራልያ ሰፋፊ የግጦሽ መሬቶችን በዘመናዊ የግጦሽ አስተዳደር ዘዴዎች በመጠቀም፣ - ከፍተኛ የሥጋ ምርት አምራችና በዓለም ላይ ካሉ ዋነኛ የሥጋ አቅራቢዎች አንዷ ናት። ከዚህ ሸገር ዘመኑ ያፈራቸውን ድሮኖችና አካባቢ ጠቋሚ ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ የእንስሳት መንጋዎችንና የግጦሽ መሬቶችን በብቃት ከሰው ንክኪ ውጭ በማስተዳደር ላይ ትገኛለች።

አሜሪካ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ በሚታገዝ በእንስሳት ርባታ፣ በዘር ማሻሻያና በምግብ | ማቀነባበሪያ ላይ በማተኮር ከፍተኛ የሥጋና የወተት ምርት ታምርታለች። የእንስሳት ርባታን ውጤታማነት ለመጨመር የዘረመል ምሕንድስናንና ባዮቴክኖሎጂን በስፋት ሥራ ላይ ዋለች ነው። እነዚህ ሀገራት በቴክኖሎጂ፣ በሳይንስና በዘላቂነት ላይ ያተኮሩ የተቀናጁ ልቶችን በመተግበር የእንስሳት ሀብት ልማትን በከፍተኛ ደረጃ በማዘመን፤ ከፍተኛ ምርታማነትን፣ ውጤታማ የእንስሳት ደኅናነትንና የአካባቢ ጥበቃን አስመዝግበዋል።

በአፍሪካ የእንስሳት ሀብት ልማት በመቶ ሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን በገቢና በምግብ ግፋል። የገጠር ኑሮና የኢኮኖሚው የማዕዘን ድንጋይ ነው። አህጉራችን በአርብቶ ሮች ብቻ የሚለማ እንዲሁም ከእርሻ ጋር ተቀላቅሎ የሚሠራ የእንስሳት ሀብት ልማት የቤት ናት። ከብቶች፣ በጎች፣ ፍየሎችና ዶሮዎች በስፋት ይገኙባታል። ልማቱም ለግብርና አጠቃላይ የውስጥ ምርት ጉልህ አስተዋጽዖ አለው።

ይሁንና የአህጉራችን የእንስሳት ሀብት ልማት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ ባህላዊና ምርታማነቱም እጅግ አነስተኛ ነው። ለዚህ የተለያዩ ችግሮች በምንጭነት ይጠቀሳሉ። በቂ ግብአት አለማግኘት፣ የመሠረተ ልማት አለመስፋፋትና የገበያ ተደራሽነት ማነስ ዋነኞቹ ተደርገው ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው።

በሀገራችን የእንስሳት ሀብት በእያንዳንዱ አርብቶና አርሶ አደር ቤት የሚገኝ የባህላችን የሚደገፍበት ሀብትም ነው። የእንስሳት ርባታ ዘርፍ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ትልቅ ሀገራዊና ቀጣናዊ ጠቀሜታ አለው። በገጠር ኑሮና በአጠቃላይ ሀገራዊ ልማት መገለጫ ሀብት ነው። በመላው ሀገራችን የሚገኝ ብቻ ሳይሆን፣ መላው ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

ከሀገራችን አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ውስጥ ወደ አንድ አምስተኛ የሚጠጋውን ከእንስሳት ሀብት ምርት ይገኛል። እንዲሁም ከግብርና አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ውስጥ ግማሽ ያህሉ ያበረክታል። ሀገራችን ከ70 ሚልዮን በላይ የቀንድ ከብቶች እና በዐሥር ሚልዮኖች የሚቆጠሩ በጎች፣ ፍየሎች እና ዶሮዎች አሏት። በእንስሳት ሀብት ብዛት ከአፍሪካ አንደኛ ስትሆን፣ ከዓለም ደግሞ በአምስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች።

በሀገራችን የእንስሳት ርባታ ከምግብነት ያልፋል። ከብቶቹ ለእርሻና ለመጓጓዣ ያገለግላሉ:: ተረፈ ምርታቸው ለፍግነትና በተለያየ መልክ ለማገዶ ይውላል። ዘርፉ ለወጪ ንግድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለው። ሰፊውን የግብርና የሰው ኃይል በመቅጠር በተለያዩ የግብርና ሥነ ምኅዳራዊ ዞኖች ላሉ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደር አደሮች የጀርባ አጥንት ሆኖ ያገለግላል።

CamScanner

ሀገራችን የብዙ ሀይቆችና ወንዞች ባለቤት መሆኗ ይታወቃል፡፡ በእነዚህ የውሃ አካላት የሚገኘው የዓሣ ሀብት ንዑስ ዘርፍም፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና ድህነትን ለመቀነስ ከፍተኛ ዕምቅ ዐቅም አለው፡፡

ይሁንና የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ ገና ከባህላዊው የገበሬው አሠራር አልተላቀቀም፡፡ አልተነካም ማለት ይቻላል፡፡ የሕዝባችን አመጋገብም ካለን የእንስሳት ሀብት አንጻር እዚህ በየአባወራው ቤት የሚገኝ ያልተደራጀ ኢንዱስትሪ ነው፡፡ ካለው ዕምቅ ዐቅም አንጻር ምንም ግባ አይባልም፡፡ የነፍስ ወከፍ የእንስሳት ሀብት ውጤቶች ፍጆታችን እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡

ዘርፉ ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ፤ ውሱን የቴክኖሎጂ ተደራሽነትና ያልዘመነ አሠራር፣ደካማ የእንስሳት ጤና አገልግሎት፣ በቂ ያልሆነ የመኖ አቅርቦት፣ የመሠረተ ልማት እጥረትና ደካማ የገበያ ትሥሥርን የመሳሰሉ ተግዳሮቶች ተጠቂ ሆኗል፡፡ ስለዚህም በኢኮኖሚያችን ውስጥ የሚገባውን ሚና እየተጫወተ አይደለም፡፡

እነዚህን ተግዳሮቶች በመቋቋም፣ ዘርፉን ማዘመንና ማሸጋገር ጠቀሜታው ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ያሳድጋል፡፡ በገጠር ለሚኖሩ ዜጎች የገቢ ምንጭን ለማስፋትና ኑሯቸውን ለማሻሻል ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ከዚህም በላይ፣ ለሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ትርጉም ያለው ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይችላል፡፡

የመደመር መንግሥት የእንስሳት ሀብት ልማት ሽግግርን የሚመለከተው የገጠር ሽግግር _አንዱ ምሰሶ አድርጎ ነው፡፡ በገጠር ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ሥነ ምግባዊ(Nutrition) ትሥሥር ውስጥ የተጋመደው የእንስሳት ሀብት ልማት ሳይለወጥና ሳይሸጋገር፣ የገጠር ሽግግር ስኬታማ አይሆንም፡፡

በሀገራችን የእንስሳት ሀብት በሚልዮን ለሚቆጠሩ የገጠር አባ ወራዎች ቢና ሥራ ብቻ አይደለም፡፡ የሀብት ማከማቻ፣ ችግርን የመቋቋሚያ ደጀንና ለሥነ ምግብ ዋስትና ከፍተኛ ሚና ያለው ነው፡፡ በገጠር በተለይም በአነስተኛ አርብቶና አርሶ አደሮች ዘንድ፣ የእንስሳት ሀብት ቀዳሚው አለያም ብቸኛው ስኬታማ ሀብት ነው፡፡ የዘርፉ መዳከም ሰፊውን የገጠር ሕዝብ ከልማት ዕድገት ውጪ የሚያደርገው ብቻ አይደለም፡፡ በበሬ ለምታርሰው ሀገራችን እርሻውንም እንደ መግደል ነው፡፡

የገጠር ኢኮኖሚያቸውን በተሳካ ሁኔታ ባሸጋገሩ ሀገሮች እንደታየው፣ የእንስሳት ሀብት ልማት ለገጠር ሽግግር ወሳኝ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የእንስሳት ሀብት ልማትን ቅድሚ ስለሆነም ከተለመደው አዝጋሚ ለውጥ በመውጣት፣ ፈጠራንና ፍጥነትን ታሳቢ ያደረ መስጠትና ማዘመን የተሟላ፣ አካታችና ዘላቂነት ላለው የገጠር ሽግግር ዋነኛ ምሰሶ ነው የተለያዩ ተነሣሽነቶችን በመቅረጽ፣ መንቀሳቀስ ተገቢ ነው፡፡

የእንስሳት ሀብት ልማት ሽግግር የመጀመሪያ ዓላማ፣ በመላው ሀገራችን ምርታማነት ተደራሽነትን በማሻሻል፣ በገጠርም ሆነ በከተማ ሕዝባችንን የተመጣጠነ ነገሮች የበለጸጉ እንደ ወተት፣ ሥጋ፣ ዕንቁላልና ማር የመሳሰሉ ምግቦችን ያቀርባል፡፡ በተጠቃሚነትንና በምግብ ራስን መቻልን ማሻሻል ነው፡፡ እንደሚታወቀው ዘርፉ በ አቅርቦቱም ሕዝባችን የተመጣጠነ ምግብ ተጠቃሚ እንዲሆን ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

በመሆኑም የእንስሳት ሀብት በኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለውን ጥልቅ ባህላት ተግባራዊ ውሕደትን ታሳቢ በማድረግ፣ "የሌማት ትሩፋት" የሚለውን ተነሣሽነት ለእን ሀብት ልማት ሽግግር መነሻ አድርገን አስተዋውቀናል፡፡ የሌማት ትሩፋት የእንስሳት ሁሉ ምርቶቻችን የቅንጦት ምርቶች መሆን የለባቸውም ብሎ የሚነሣ ነው፡፡ ሕዝባችን በቀለ እያመረተ በሌማቱ ላይ የሚያገኛቸው መሆን አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ማላቅንና የምግብ ዋስትና ማረጋገጥን አጣምሮ የያዘ ነው፡፡

መርሐ ግብሩ ለአራት ዓመታት የተዘረጋ ነው፡፡ በዚህም ሕዝባችን በጓሮ አነስተኛ የእንስ ርባታ ላይ እንዲሠማራ በማድረግ፣ ዋና ዋና የእንስሳት ተዋጽዖዎችን ማለትም፥ ወተት ዕንቁላልን፣ የዶሮ ሥጋና ማርን ማምረትና መመገብ እንዲችል ለማድረግ

CamScanner

ዓልሞ የተነሣ : በአጠቃላይ የሌማት ትሩፋት፣ ሕዝባችን ከውጭ በሚገቡ ምግቦች ላይ ያለውን ጥ በመቀነስ፣ ራስን መቻልን በማገዝ፣ የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን በመቀነስና የአካባ ኢኮኖሚን በማነቃቃት፣ ለገጠር ሽግግር አንዱ መሠረት ይሆናል።

የሌማት ትሩፋት ከመነሻው ያስመዘገባቸው ውጤቶች አሉ። እነዚህ ውጤቶች፣ የእንስ ሀብት ልማት የገጠር ሽግግር ምሰሶ የመሆን ዐቅሙን ከጅምሩ አሳይተዋል። በ አካባቢዎች የወተት ተዋጽዖዎች በፍጥነት ተስፋፍተዋል፤ የዕንቁላል ምርትና የዶሮ ር በከፍተኛ ሁኔታ አድጓል፤ የማኅበረሰቡ የአመጋገብ ሁኔታ ተሻሽሏል፤ እንዲሁም የሥራ ዕድል ጨምሯል።

አሁን ያገኘናቸውን ድሎች በአብዛኛው አካባቢ በማስፋፋትና በማጽናት፣ በሚቀጥሉ ዓመታት በሀገራችን የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ታሪክ እንዲሆን እንሠራለን። የሽግግርን ከአመጋገብ ሽግግር ጀምረን፣ ሙሉ እናደርገዋለን።

ሁለተኛው የእንስሳት ሀብት ልማት ሽግግር ዓላማ ዘርፉ የአርብቶ አደሩን ኢኮኖሚ ( እንዲያጎለብትና ከመተዳደሪያነት ያለፈ ውጤታማነት እንዲኖረው ማስቻል ነው። ቀርቦት የሚጠበቅ መሆኑን ታሳቢ ያደርጋል። ዓለም ዘርፉን ለማዘመን የተጠቀማቸውን ዘመናዊ መሣሪያዎችና የአሠራር ዘዴዎች ለራሳችን እንደሚሆኑ አድርገን ማላመድን ዋናነት ያከናውናል። እንዲሁም ሀገራችን ዘርፉን ከማልማት አንጻር ያላትን መልካም አሚዎችና ተሞክሮዎች ይጠቀማል። በእነዚህ ስልቶችም፣ ዘርፉ አሁን ካለበት ኋላ ' ቀርነት ወደ ዘመናዊና ሥሉጥ የእንስሳት ሀብት ልማት ልናሸጋግረው የግድ ነው።

ትልቁ የሀገራችን የእንስሳት ሀብት ልማት መሠረት አርብቶና አርሶ አደሩ ነው። በዚህ ደረጃ የሚኖር ምቹነት በአጠቃላይ ኢንዱስትሪው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚኖረው መሆኑን 'ታሳቢ ያደርጋል። ዘመናዊ፣ ዘላቂ፣ አካታችና የማይበገር የእንስሳት ሀብት ልማትን በገበሬው ደረጃ ማሣለጥ ወሳኝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በዘርፉ መሥራት የሚፈልጉ ባለ ሀብቶችን በማበረታታት፣ ሰፋፊና ግዙፍ የእንስሳት ሀብት ልማቶችን በስፋት ማደራጀት ያስፈልጋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ስኬታማ የእንስሳት ሀብት ልማት ያስመዘገቡ ሀገራት፣ አርብቶ አደሮችን ጨምሮ ሁሉንም ባለ ድርሻ አካላት ያሳተፈ አካታች አካሄድን ተከትለዋል። የአርብቶ አደሮችን ባህላዊ ዕውቀት ከዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጋር በማዋሐድ ለአካባቢያቸው ተስማሚ ሆኑ ዘላቂ የእንስሳት ርባታ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርገዋል። የዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም አስፋፍተዋል። ሰፋፊ የእንስሳት ርባታዎችን በብቃት ደግፈዋል። የአርብቶ አደሮችን ምርቶች ወደ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን አሻሽለዋል፡ ምርቶችን ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችሉ አሠራሮችን ዘርግተዋል። የገበያ ተደራሽነትን አስፍተዋል። በእነዚህ መንገዶችም በአጠቃላይ ዘርፉን ለማሳደግ ችለዋል።

ዘርፉ በአጠቃላይ ከሌሎች ዘርፎች ጋር የሚጋራቸው ሀገር አቀፍ መሠረተ ልማቶች እንዳሉ ሆነው፣ ከእንስሳት ሀብት ልማት ጋር የተሣሠሩ መሠረተ ልማቶችንም ይፈልጋል። እነዚህ መሠረተ ልማቶች ቀልጣፋና ዘላቂነት ያለው የእንስሳት ርባታን ለመደገፍ የሚውሉ ቴክኖሎጂያዊ ሥርዓቶችን ይይዛሉ። በዋናነት የእንስሳት ጤና ጥበቃን፣ የማዳቀያ ማዕከላትን፣ የመኖ ማቀነባበሪያዎችን፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓቶችንና _ የመሳሰሉትን የሚያጠቃልሉ ናቸው። ዋና ዓላማቸውም የእንስሳትን ደኅንነት የሚደግፍ አካባቢ መፍጠር፣ ምርታማነትን ማሻሻል፣ ወጪዎችን መቀነስና ዘላቂ የግብርና ልምዶችን ማስፋፋት ናቸው።

ዓለም እነዚህን መሠረተ ልማቶች በመገንባት ሂደት ብዙ ርቀት ተጉዞ ልምድ አካብቷል። ዋናው ጉዳይ ከሀገራዊው ልምድና ተሞክሮ አንጻር በመቃኘትና በማላመድ ወደ ተግባር ማውረድ ነው። በመሆኑም በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ዘመናዊ የምርምርና የማዳቀያ ማዕከላትን በማቋቋም አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣ ከሀገራዊው ዕውቀት ጋር ማላመድና ማዳበር ያስፈልጋል። ይሄም ለሀገር በቀል ዝርያዎች ተመራጭ የሆኑ የማዳቀያ ዘዴዎችን በመጠቀም፣ ዝርያዎቹ እንደተጠበቁ ምርታማነታቸውን ለማሳደግ ያስችላል።

CamScanner

ሌላኛው ትኩረት የመኖ አቅርቦት ነው። የእንስሳት መኖ በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረብ ሲችል ለዚህም በመኖ አዘገጃጀት ረገድ ያለውን ዓለም አቀፍ ልምድ ከሀገራትን ተሞክሮ ጋር ለእንስሳት ተዋጽዖ የተሻለ አቅርቦትም ይሁን ዋጋ ተመጣጣኝነት ትልቅ ሚና ይጫወታል። በማቀናጀት፣ ዘመናዊ የመኖ ማቀነባበሪያዎችን መገንባት ወሳኝ ነው::

ለመኖ ልማት የሚውሉ መሬቶችን በግልጽ በመለየት ለባለ ሀብቶች ምቹ ሁኔታ መፍጠር ወሳኝ ነው። እንዲሁም የግጦሽ መሬት አያያዝና አጠቃቀም፣ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። የመኖ ምርትና አቅርቦት የሀገር ውስጥ ፍጆታን አሟልቶ ወደ ውጭ መላክ እንዲቻል መደገፍ አለብን። እንዲሁም የተሻሻሉ የመኖ ዝርያዎች ማለትም. የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርትና በፋብሪካ የተዘጋጁ መኖዎችን ለገበያ በሚመጥን ደረጃ ማምረት ይኖርብናል። ከዚህም በተጨማሪ የመኖ አቅርቦትና ግብይት በገበያ መርሕ እንዲመራ ማድረግ ያስፈልጋል።

የእንስሳት ሀብትን ከበሽታ ለመከላከል፣ የእንስሳት ሕክምና አገልግሎቶችን ለማሻሻልና ውጤታማ የበሽታ መቆጣጠሪያ ተግባራትን ለማከናወን ሰፋፊ ርምጃዎችን እየወሰድን እንገኛለን። ይሄም የሕክምና አሰጣጥ ሥርዓቶችን ማሻሻልን፣ የበሽታ ክትትልን ማሳደግን እና ተመጣጣኝና ውጤታማ የክትባትና የሕክምና አቅርቦት ማረጋገጥን ያካትታል። በጤና ክትትልና በተለይም በሽታን ቀድሞ ከመለየት አንጻር፣ ምጥን የእንስሳት ሀብት ልማት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። ይሄንንም በፍጥነት ወደ ተግባር ለመቀየር እየሠራን ነው።

በእንስሳት ሀብት ዘርፍ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የፈጠራ ልምዶችን ማስተዋወቅና ሥራ ላይ እንዲውሉ በንቃት መሥራት አስፈላጊ ነው። ይሄም በተለያዩ የእንስሳት ሀብት ልማት ሂደቶች አስቻይ ሆኖ የሚገባ ይሆናል። ለዚህም የተደራጀ የእንስሳት ሀብት ምዝገባና ክትትል ሥርዓትን፣ የገበያ መረጃንና ትንተና አገልግሎቶችን፣ የሥልጠናና ተሞክሮ ልውውጥ ሥርዓቶችን እና ሌሎችንም ሥርዓቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ መዘርጋት ያስፈልጋል።

ሌላኛው ትልቁ ተግዳሮት የፋይናንስ ተደራሽነት ነው። እንደሚታወቀው፣ ለመሻሻልና ለመለወጥ መነሻ የሚሆኑ የብድርና ሌሎች የገንዘብ አማራጮችን ገበሬው በተለያዩ ምክንያቶች በስፋት አያገኝም። በግብርና ዘርፍ የኢንቨስትመንት መመለሻ ጊዜ በአብዛኛው ኢንተርፕረነርሺፕ ሥራዎች የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም አብዛኞቹ ረጅም

ነው። ስለዚህም፣ በተለይም ከእንስሳት ሀብት ልማት ጋር ለተገናኙ የአግሮ- የፋይናንስ ተቋማት ግብርናን ከፍተኛ ሥጋት ያለበት ዘርፍ አድርገው የሚመለከቱ በመሆኑ ነው።

የመሰል ሀገራትን ልምድ በመውሰድ የመንግሥት የፋይናንስ አቅርቦትንና የእንስሳት ሀብትን ለብድር ዋስትና ማዋልን ጨምሮ የተለያዩ አካሄዶችን እየቀመርን እንገኛለን። የእንስሳት ሀብትን ለማሳደግ፣ ለየት ያሉ የፋይናንስ አማራጮችን ተግባራዊ ማድረግ የግድ ነው። በመሆኑም ለአርሶ አደሮች፣ ለአርብቶ አደሮችና በዘርፉ በልማት ላይ ለተሠማሩ አካላትና በዕሴት ሠንሰለቱ ውስጥ ላሉ ሌሎች ተዋንያን፣ የፋይናንስ ተደራሽነትን ለማመቻቸት እየሠራን ነው።

የእንስሳት ሀብትን ምርትና ምርታማነት ከማሻሻል ባሻገር የእንስሳት መሠረታዊ የዕሴት ሠንሰለቶችን ማዕከል ያደረገ የገበያ ትሥሥርን ማጠናከርና ማሻሻል ወሳኝ ነው። ከዚህ አኳያ አርሶና አርብቶ አደሮች ምርቶቻቸውን ለገበያ በቀላሉ እንዲያቀርቡ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን መዘርጋት፣ የገበያ ማዕከሎችንና መጋዘኖችን ማቋቋም፣ እንዲሁም የትራንስፖርትና የመገናኛ አውታሮችን ማሻሻል ያስፈልጋል። ወደ ገበያ የሚሄደው ምርት ላይም ዕሴት መጨመርን ማበረታታትና ማሳደግ ወሳኝ ነው። ስለሆነም አርሶና አርብቶ አደሮች ምርቶቻቸውን አቀነባብረው እንዲያቀርቡ በማድረግ ተጨማሪ ገቢ እንዲያገኙ እያበረታታን ነው።

በተጨማሪም ገበሬው የገበያ ዋጋዎችን፣ የአቅርቦትና የፍላጎት መረጃዎችን እና የገበያ አዝማሚያዎችን በቀላሉ እንዲያገኝ፣ የገበያ መረጃ ሥርዓትን ማሻሻልና ዘመናዊ ሥርዓቶችን መዘርጋት ወሳኝ ነው።

CamScanner

በዕሴት ሠንሰለት ውስጥ ጥራት ያለው ምርት እንዲቀርብና በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ፣ የጥራት ድጋፍና ቁጥጥር ሥርዓትን ማጠናከር ያስፈልጋል። ይሄም የምርት ጥራትን የሚደግፉና የሚቆጣጠሩ ሕጋዊ ማሕቀፎችንና አሠራሮችን ማጠናከር ይሻል። የጥራት ቁጥጥር ቤተ ሙከራዎችን ማቋቋም እና የጥራት ቁጥጥር ባለሞያዎችን ማሠልጠን ይፈልጋል። ባለሞያዎቹም ከቁጥጥር ባለፈ ድጋፍ ማድረግ እንዲችሉ አሠራሮቻችንን ማስተካከልን ያካትታል።

በእንስሳት ሀብት ልማት የተሻሻሉ አሠራሮችን ለማጎልበትና ዘርፉን ለማዘመን፣ የክሎ ልማት ወሳኝ ነው። ከዚህ አንፃር ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ለዘርፉ የሚሰጡ ባለሞያዎች ማፍራት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል። የክሂሎት ልማት በመሠረታዊነት በእንስሳት ሀብት ላይ የቴክኒክ ዕውቀትን፣ የአስተዳደርንና የንግድ ክሂሎቶችን የሚያካትት ነው።

የእንስሳት ሀብት አልሚዎችን፣ የአርብቶና የአርሶ አደሮችን፣ ተያያዥነት ያላቸውን አገልግሎት ሰጪዎችን እና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ዐቅም ማጎልበት ለዘርፉ ዘላቂ ልማት አስፈላጊ ነው። ይሄንን ለማረጋገጥ በየደረጃው ያሉ የከፍተኛና የቴክኒክ የሥልጠና ተቋማትን ማጠናከርና የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ልማት መደገፍ ተገቢ ነው።

ከቴክኒክ ክሂሎቶች በተጨማሪ የእንስሳት ሀብት አልሚዎችን የኢንተርፕረነርሽፕ አስተሳሰብ ማዳበር ለነገ የሚባል አይደለም። ይሄም ተዋንያኑ የገበያ ዕድሎችን እንዲለዩና እንዲጠቀሙባቸው፣ ፈጠራ እንዲያሳዩና ትርፋማ ንግዶችን እንዲገነቡ የሚያግዝ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ገበሬውን በዲጂታል ቁሶችና መተግበሪያዎች አጠቃቀም ዙሪ መሠረታዊ ክሂሎት እንዲያዳብር ማድረግ ይገባል። በራሱ ዐውድ ሥራዎቹን ለማቀላጠፍና ለማሻሻል መጠቀም እንዲችል ማብቃት ያስፈልጋል። እነዚህ ነገሮች ለመጪው የግብርና ሽግግር ዘመን ወሳኝ ናቸው።

የእንስሳት ልማት ዘርፍ በመላው ሀገራችን የሚገኝ አብዛኛው ሕዝብን የሚነካ ዘርፍ በመሆኑ፡ ለአካታችነት ተፈጥሯዊ መሠረት ያለው ነው። ይሁንና እንደ አጠቃላይ ዘርፉ አካታች ሆኖ እንዲዘልቅ የሴቶችን ተሳትፎ የበለጠ መደገፍና ማሳደግ ወሳኝ ነው። በተጨማሪም የቱንም ያህል ዘመናዊ የእንስሳት ሀብት ልማት ብንዘረጋ፣ ዘላቂነቱን ካላረጋገጥን መልሶ ወደ ኋላ መንሸራተቱ አይቀርም። በመሆኑም ዘላቂና የማይበገር አድርገን መገንባት ይኖርብናል። ለዚህም ዓለም አቀፉን ተሞክሮ ወስደን እየሠራን ነው። ልማታችን ከአካባቢያችን ጋር የተስማማ፣ ባህላችንንና ማንነታችንን የሚያጎላ፣ ለአየር ንብረትና ሌሎች ለውጦች የማይበገር አድርገን ለመገንባት እየተንቀሳቀስን እንገኛለን።

በአጠቃላይ የእንስሳት ሀብት ልማት፣ ለገጠር ሽግግር ዋነኛው ምሰሶ እንደመሆኑ፣ የዘርፉ መሻገር ሀገራዊ በጎ ተጽዕኖው እጅግ ከፍተኛ ነው።

# ምዕራፍ ሰባት

## 7. የመደመር መንግሥት፤ በኢንዱስትሪ

ኢንዱስትሪያዊነት(Industrialization) ግብርናን ማዕከል ካደረገና በሰው ጉልበት ላይ ከተደገፈ የኢኮኖሚ መሠረት ወደ ኢንዱስትሪ መርና በማሽኖች ጉልበት ወደሚከወን የአምራችነት ኢኮኖሚ የሚደረገውን ሽግግር የሚወክል ነው። አምራች(Manufacturing) ኢንዱስትሪው ደግሞ ከሀገራት የዕድገት ምሰሶዎች አንዱና ከየትኛውም ዘርፍ ይልቅ ለአጠቃላይ የዕድገት ግሥጋሴያቸው ትልቅ ማሳያ ሆኖ የሚያገለግል ዘርፍ ነው። ዘርፉ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ከፍተኛ

CamScanner

ቁርኝት ያለው ብቻ አይደለም፤ የአምራችነት የዕድገት ደረጃ የሌሎቹንም ደረጃ ይወስናል፤ ያፋፋል፤ ወይም ያቀጭጫል የሚያስብል ነው።

አምራችኢንዱስትሪው ለአንድ ሀገር አጠቃላይ የውስጥ ምርት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል ሲባል በቀጥታ ከሚኖረው አስተዋጽዖ በላይ ነው። በሌሎች ዘርፎች ላይ በሚኖረው ተጽዕኖ የሚያበረክተውም አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። የተሻለ ገቢ ያለው ማኅበረሰብ ለመፍጠር ለሚደረገው ርብርብም ዋነኛው የትኩረት ዘርፍ የአምራች ዘርፍ ነው። አምራች ኢንዱስትሪውን ወደ ከፍታ የማምጣትና የማበልጸግ ጉዳይ፣ ከኢኮኖሚና ከማኅበራዊ ጥቅሙ ባለፈ፣ ደኅንነትንና ሉዓላዊነትን ከማስከበር አንጻርም ሚናው ከፍተኛ ነው። በሌሎች ሀገራት አምራች ኢንዱስትሪ ላይ ጥገኛ ሆኖ፣ ራስን ሳይችሉ፣ ሉዓላዊ ሀገር ነን ማለት ቀልድ ነው።

በዚህ የዲጂታል ዘመን፣ የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ ከሚያስተናግዱ ዘርፎች ዋነኛው ሆኗል። ሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነች አፍሪካ፣ በዚህ ዘርፍ ወደ ኋላ ቀርተዋል። እየመጣ ያለውን ዘመናዊ አምራች ኢንዱስትሪ ለመቀላቀልም በእጅጉ የሚያዳግት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። ያደጉ ሀገራት የቀድሞ የዝግጁነታቸውና የቴክኖሎጂ የበላይነታቸው ለውጡን በፊታውራሪነት እንዲመሩት አስችሏቸዋል። በዚህ መሪነታቸው የተነሣም ለውጡ የበለጠ ዕድገትና ሀብት እንደሚያጎናጽፋቸው ይጠበቃል።

አፍሪካ ግን አሁንም መወዳደሪያ ዐቅሞቹ የምትላቸው ላይ ለውጡ ወደፊት የሚያመጣውን ተጽዕኖ በውል የተረዳች አይመስልም። ዘርፉም ለዓመታት የሚጠበቅበትን ለውጥ ያላሳካ አዳዲስ ዕድሎች በአግባቡ ለመጠቀምና ተወዳዳሪ ሆና ለመውጣት አፍሪካ ስልቶቿን ነገን በዕንቅልፍ ላይ ያለ ይመስላል። በዓለም አቀፍ የአምራች ኢንዱስትሪው ቀድማ ተመልክታ ማሻሻል አለባት።

## 7.1. የነገው አምራች ኢንዱስትሪ

ዓለማችን ተለምዷዊው የኢንዱስትሪና የአምራችነት አካሄድን በተለየ መልኩ በማዘመን ላይ ናት። ዛሬ ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊነትን የተላበሱ፣ ውጤታማነታቸውም አስገራሚ ደረጃ የደረሰበት ዘመን ላይ እንገኛለን። ያለንበት አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን ዲጂታይዜሽን፣ የበይነ መረብ ነገሮችና የሮቦት ቴክኖሎጂ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑበት ዘመን ነው።

የምርት ሂደት ከሰው ጣልቃ ገብነት በተወሰነ መልኩ የተላቀቀበት ዘመን ነው:: የተለያዩ የዋና ምርቱን አካሎች ከማምረት ጀምሮ፣ ገጣጥሞ፣ ጥራቱን አረጋግጦ እና አሽጎ እስከማስረከብ ድረስ፣ በየሂደቱ ማሽኖች ከሰዎች በላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ።

ተንቀሳቃሽ አነፍናፊ የበይነ መረብ መሣሪያዎች በተሠናሰለ መልኩ በየቦታው እየተገጠሙ ነው። እነርሱም የምርት ሂደቱን ፍሰትና ውጤታማነት ይከታተላሉ፤ ያረጋግጣሉ። ከማምረቻ ግቢው እስከ ምርት ክፍሎች፣ አልፎም እስከ ማሽኖች የውስጥ ክፍል ድረስ ይዘልቃሉ። ዘልቀውም የማያቋርጥ መረጃ በማምረት የሂደቱን ውጤታማነትም ሆነ የማሽኖቹን ጤና ከመጠበቅ አንጻር ትክክለኛ ውሳኔና ርምጃ እንዲወሰድ ግብአት ይሰጣሉ።

ሰው ሠራሽ አስተውሎት ከምርት ሂደት ሥርዓት ጋር ተጣምሯል። ከአነፍናፊዎችና ከተለያዩ ዐውዶች የሚመነጩ ሌሎች መረጃዎችን በማስላት፣ የፍላጎት ትንበያን፣ የአቅርቦት ሠንሰለት አስተዳደርን፣ የጥራት ቁጥጥርን፣ የምርት ቅንጅታዊ ዕቅድንና ሌሎች ብዙ ጉዳዮችን በጥራት ይከውናሉ። በሰው እጅ ሲከወኑ ሳምንታትና ወራት የሚወስዱ ጉዳዮች፣ በተሻለ ጥራት በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ይጠናቀቃሉ።

የአሐዛዊ መንታ (Digital Twin) ቴክኖሎጂ አጠቃላይ የማምረቻ ዝርጋታውን፣ ከግብአት ጀምሮ እስከ ፋብሪካው ቅጥር ግቢ ያለውን በመወከል፤ የትክክለኛው ዓለም መንታ ሆኖ ያገለግላል።

CamScanner

ከምርት አዳራሾች እስከ ማሽኖች የውስጥ አካል ድረስ አሐዛዊ አቻ ይፈጥራሉ። በዚህም የማይባክኑበትን መንገድ ይከተላሉ። አስቀድሞ ጥሬ ዕቃዎችን ሳያባክኑ በኮምፒውተር አሠራራቸውንና ቅንጅታቸውን ሁሉ አምሳያቸው አድርጎ በመሥራት፣ ጥሬ ዕቃዎች መምከር (Simulation) እና መከራዎች ከተሳኩ ብቻ ወደ ምርት በማስገባት፣ ብክነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚቀንስ ቴክኖሎጂ ሆኖ ተተግብሯል።

ከዚህ ባለፈ ከአካላዊ የሳይበር ሥርዓቶች (Cyber physical Systems) ጋር በመቀናጀት፣ለክትትል፣ ለማስተካከያ እና ለማሻሻያ ርምጃዎች እየተተገበረ ነው። በዚህም ለሰው ልጅ እጅግ አስቸጋሪና ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳዮችን፣ በአስገራሚ ብቃት እየተወጣ ይገኛል”።

በሌላ በኩል ደግሞ በብዛትና በአንድ ዓይነት ያመርቱ ከነበሩ ግዙፍ ማሽኖች አሠራር በመውጣት፣ ባለ ሦስት አውታር ኅትመት (3D Printing, Additive Manufacturing) የተለያዩ ግብአቶችን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን ለማምረት ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። ምርቶች በቀላሉ እንደ ሥዕል ይታተማሉ። እንደየሁኔታውም ለእያንዳንዱ አስፈላጊ _ማስተካከያዎች ለማድረግ ይቻላል። ከዚያም እንደ ደንበኛው ፍላጎት የተቃኙ ሆነው ይወጣሉ።

በኤሮስፔስ፣ በመኪና እንዲሁም በጤናው ዘርፍ በብዛት እየተተገበረ የሚገኘው ይህ ባለ ሦስት አውታር ኅትመት፣ ቅርጽ ማውጫን መሠረት ያደረገውን ተለምዷዊ አሠራር ከሥር መሠረቱ ይቀይራል ተብሎ ይጠበቃል።

በዚህ ዘመን የፋብሪካዎችንና የማምረት ሂደትን ቀጣይነት ከማረጋገጥ አኳያ፣ ታዳሽ ኃይል መጠቀም፣ ብክነትን መቀነስና፣ አስተማማኝ የግብአት ምንጭ መያዝ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል። እንዲሁም በአረንጓዴ አመራረት (Green Manufacturing) ስልት ምርቶች አገልግሎታቸውን ሲጨርሱ በቀላሉ የሚበተኑ፣ ታድሰው እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ፣ አለያም በቀላሉ ለሌላ ምርት ግብአት የሚሆኑ ተደርገው እየተመረቱ ይገኛሉ።

ፋብሪካዎችን የተሻለ አድርጎ የመቅረጽ ሂደት በዚህ የሚያበቃ አይደለም። በቀጣይ ቅር ትግበራ አሁን ካለበት ከፊል ሽፋን ወደ ሙሉ ስለሚጠጋ በምርት ሂደት ውስጥ የሰው ዓመታት ብዙ ለውጥ የሚታይበት እንደሚሆን ይጠበቃል። የሮቦቶችና የአነፍናፊዎች ተሳትፎ በእጅጉ አነስተኛ ይሆናል። የሰው ሠራሽ አስተውሎትና ማሽኖች ከምርት ሂደት ከጥቂት ሰዎች ጋር ተዋሕደው ግዙፍ ፋብሪካዎችን እንደሚያንቀሳቅሱ ይጠበቃል።

ሰው ሠራሽ አስተውሎት፣ እንደ ሰው ምሁራዊ ሥራዎችን (intellectual tasks) ያማራ ይረዳል። የሰው ሠራሽ ሁለገብ አስተውሎት (Artificial General intelligence, A በራሱ ችግሮቹን እየለየ ያስተካክላል፣ እንዲሁም ይጠግናል።

አዳዲስ ምርቶችን ይነድፋል: እንዲሁም አዳዲስ የአመራረት ስልቶችንና የንግድ አካሄዶችን የሚፈጥር አካል ሆኖ በከፍተኛ ደረጃ ተሳታፊ እንደሚሆን ይገመታል። በዚህም ምርቶችን በብዛትና በአንድ ዓይነት ከማምረት ይልቅ፣ ደንበኞች በሚያቀርቡት ፍላጎትና ንድፍ መሠረት የተቃኙና ግለሰባዊ እንዲሁም በተፈለጉ ጊዜ ብቻ የሚመረቱ ይሆናሉ። በዚህም ውጤታማነት በእጅጉ እንደሚጨምር፣ ብክነት እንደሚቀንስና የደንበኛ ርካታ እንደሚልቅ ይጠበቃል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ የግብአት ዓይነቶች እየተለወጡ መጥተዋል። ከተለመደው የጥሬ ዕቃ የግብአት ፍላጎት ወጥቶ ቅንጣት ቁሶች (Nano materials)፣ ሥሉጥ ቁሶች(Smart Ma terials)፣ እንዲሁም በአፈር ውስጥ የሚበሰብሱ(Biodegradable) ፕላስቲኮች ጥቅም ላይ መዋል ጀምረዋል። በዑደታዊ ኢኮኖሚ(Circular Economy) አማካኝነት ምርቶች ሙሉ በሙሉ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ፣ የሚጠገኑ ወይም ለሌላ ግብአት እንዲሆኑ

CamScanner

ተደርገው እየተነደፉ ነው። ይህ ሁኔታም የአመራረት ሂደትም ሆነ የኢንዱስትሪያዊነት ጉዞ እንደገና እንዲበየን የሚያደርግ ይሆናል።

እንዲሁም ከመሬት ውጭ ያሉ ሀብቶችን የመጠቀምና በሌሎች ፕላኔቶችና ጨረቃዎች ላይ ፋብሪካዎችን መትከል ይጀመራል ተብሎ ይገመታል። አካሄዱም ኢንዱስትሪ አሁን ከምናውቀው ሙሉ በሙሉ የተለየ መልክና ትግበራ እንዲኖረው ያደርግ ይሆናል። ይህንንም መሠረት አድርገው አሁን ያሉ ተዋንያን ሚናቸውን እንደገና የሚፈትሹበትና የሚከልሱበት ዘመን ሩቅ አይደለም።

በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገራት ቀጣይ አመራረትን የመበየን ሥልጣን በእጃቸው ነው ተብሎ ይታመናል። ከጥቅማቸው አንጻር የሚያዋጧቸውን አካሄዶች እያስቀመጡና መንገዱን እያስተካከሉ ይገኛሉ። በዚህም የወደፊቱ አመራረት ሂደት ከቴክኖሎጂ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ፣ ከሰው ጋር በእጅጉ የተፋታ፣ የሀብት አጠቃቀሙም ዑደታዊ ኢኮኖሚን መሠረት ያደረገ ሆኖ ቀርቧል።

እስከ እዚህ ዘመን ድረስ አፍሪካ በኢንዱስትሪ ውስጥ ያሏት የመወዳደሪያ ዐቅሞች የታወቁ ናቸው። ርካሽ የሰው ጉልበት፣ የተትረፈረፈ ጥሬ ዕቃ፣ በማደግ ላይ ያለ ገበያ፣ ያልተነካ ታዳሽ ኃይል፣ እንዲሁም በተወሰነ መልኩም ቢሆን መልከዐ

ምድራዊ አቀማመጧ (በተለይም ለሩቅ ምሥራቅና ለአውሮፓ የባሕር መገናኛ መሆኗ) ነበሩ። ይሁንና የቀጣዩ ትውልድ አምራች ኢንዱስትሪ እነዚህ ነገሮች በተለየ መልኩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራባቸውና ከዚህ በፊት ከሚገኙበት መንገድ በተለየ መንገድ በማግኘት ከፍተኛ ውጤት እያገኘባቸው ነው። ይሄም ለአፍሪካ ትልቅ አጣብቂኝና ፈተና ሆኖ መጥቷል።

ለዚህ አንዱ ማሳያ በከፍተኛ ደረጃ የሮቦቶች ተሳትፎ ያለበት ወይም ሙሉ በሙሉ በሮቦቶች የሚንቀሳቀስ ኢንዱስትሪ እየመጣ መሆኑ ነው። በዚህ ውስጥ ደግሞ ርካሽ የሰው ጉልበት ምን ዓይነት ቦታ ይኖረዋል? ሮቦቶቹ ደከመኝ ሰለቸኝ

ሳይሉ፣ የዕረፍት ቀንና በዓል ሳይሉ 24/7 ይሠራሉ። በጥራትም ሆነ በብዛት ውጤታማነታቸው ከሰው እየበለጠ ነው። ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ሥራዎችን እንኳን በቀላሉ ሊወጧቸው ይችላሉ።

በዚህም የተነሣ ከሰው ድካም አንጻር የተዘረጉ የተለያዩ አሠራሮች፣ በሮቦቶቹ ዐውድ የሚቃኙ ይሆናል። ወጫቸውም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ስለዚህ ብዙ ኢንዱስትሪዎች መንገዳቸውን ወደዚህ እያደረጉ ነው። ይሄንን ሁኔታ ከግምት

በማስገባት፣ አፍሪካ ርካሽ የሰው ጉልበትን እንደመወዳደሪያ መቁጠር ማቆም ያለባት ጊዜ አሁን ነው።

የአፍሪካ ሌላኛው መወዳደሪያ የተትረፈረፈ ጥሬ ሀብት ነበር። የዑደታዊ ኢኮኖሚ ሐሳብና ትግበራ እያየለ መምጣት የጥሬ ዕቃ ገበያ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል። ቁሶችን በተለያየ መልኩ እንደገና ጥቅም ላይ የማዋል ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ነው። እንዲሁም በየትኛውም ቦታ በስፋት ከሚገኙ ቁሶች አዳዲስ የፋብሪካ ግብአቶችን የመሥራት አካሄዶች እየተስፋፉ ነው። ይህም የድንግል ጥሬ ዕቃዎችን ተፈላጊነት በእጅጉ ይቀንሰዋል። አፍሪካ አስቀድማ በገፍ የሸጠችው ጥሬ ዕቃ ደጋግሞ ጥቅም ላይ ከዋለ፣ በእጇ ያለውን እያራከሰው ይመጣል። ሀብቷ ከዚህ በፊት ያስገኝ የነበረውን ገቢ ሊያስገኝ አይችልም። ድንግል ጥሬ ዕቃን በተመለከተም ሕዋን መሠረት ያደረገ አምራችነት፣ ከጨረቃና ከፕላኔቶች

እነዚህን ሀብቶች የሚያገኝበት ጊዜ ምን ያህል ሩቅ ነው?

በአፍሪካ ከተሜነትና መካከለኛ ገቢ ማኅበረሰብ እያደገ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እያደገ ያለው ገበያ አንዱ መወዳደሪያዋ ነው። ይሁንና ይሄንን ገበያ የራሷ የማድረግና በሀገር ውስጥ የተመረቱ ምርቶችን አቅርባ ገበያውን የመቆጣጠር ብዙ ሥራ ይጠብቃታል። ይሄን ሥራ ለማሳካት የተለያዩ ሀገራዊና ቀጣናዊ ትሥሥሮችን መሥርታለች። ቢሆንም ግን በዚህ ረገድ ከአደጉ ሀገራት ዘመናዊና ርካሽ አቅርቦት ጋር ለመወዳደር ዐቅሟ በእጅጉ የተዳከመ ስለሆነ ገበያዋ የበለጸጉ ሀገራት መናኸሪያ ሆኗል።

CamScanner

አፍሪካ ገበያ አላት እንጂ የራሷን ኢኮኖሚ የሚያጠናክር አይደለም። ይልቁንም የሚያዳክምና በሌሎች ሀገራት ጥላ ሥር እንድትኖር የሚያስገድዳት ሁኔታ ውስጥ ናት። የአምራች ዘርፉ ዓለም አቀፋዊ ለውጥ እያስተናገደ ባለበት በዚህ ወቅትና በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታትም ነገሮችን አስተካክላ የራስዋን ገበያ በራስዋ የምትጠቀምበት በቂ ዝግጅት ላይ አትገኝም።

አፍሪካ ታዳሽ ኃይልን በስፋት ለማምረት የሚሆን በተለይም የውኃ፣ የፀሐይ፣ የነፋስ የከርሰ ምድር ሙቀት ኃይል ማመንጫዎችን ለመገንባት የሚያስችል ከፍተኛ ዕምቅ ዐቅም አላት። ነገር ግን እነዚህ ግንባታዎች ከፍተኛ ሙዓለ ንዋይ ስለሚጠይቁ እስከ አሁንም በብዛትና በስፋት አልተሠራባቸውም።

እነዚህ የኃይል ምንጮች በቀጣይ ኢንዱስትሪያዊነትን ለማሳካት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት ታሳቢ ስናደርግ እንደነበረው ዓለም አቀፋዊ ዓውዱ ወይም የውጭ ኢንቨስትመንት ለማምጣት መስሕብ ይሆናሉ ከሚለው አንጻር አይደለም ምክንያቱም ከላይ ካነሣናቸው ሌሎች መለኪያዎች ጋር የተሣሠረ በመሆኑ ብቻውን ለኢንቨስትመንት መስሕብ የመሆን ዕድሉ አነስተኛ ነው። ነገሩ በሀገራቱ ውስጥ ለሚኖር ኢንዱስትሪያዊነት ወሳኝ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው።

ይሁንና ታዳሽ ኃይሎችን ለማልማት ከፍተኛ ወጪ ያወጣ ሀገር፣ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት የሚሆን ተጨማሪ ሀብት ለማግኘት ይቸገራል። በዚህም በእጅጉ የተጎተተ የኢንዱስትሪያዊነት ሂደትን እንደሚጋፈጥ ግልጽ ነው።

የአፍሪካ የመሬት አቀማመጥ ለቢዝነስ ኮሪደር ምቹነትስ ምን ያህል ዘላቂ ጉዳይ ነው? አውሮፓን ከእስያ በባሕር የሚያገናኘው የስዊዝ ካናልና አጠቃላይ የቀይ ባሕር ወሽመጥ፣ በዚህ ዘመን በእጅጉ ወሳኝና የብዙ ሀገራትን ቀልብ የሳበ ጉዳይ ነው። ይሁንና የወደፊቱ አመራረት ሂደት በባለ ሦስት አውታር ኅትመት የታጀበና ቀጣናዊ አነስተኛ ኢንዱስትሪዎችን የሚያቅፍ እንደሚሆን ይጠበቃል።

ይህ ማለት ደግሞ ቻይና ለአውሮፓ የምታቀርባቸውን ምርቶች በአውሮፓ ሀገራት ላይ አነስተኛና ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎችን በመገንባት የምትፈጽመው ይሆናል። አውሮፓም እንዲሁ። በዚህም የኮሪደሩ ብዙ ተጓዦችን የማስተናገድ አሁን ያለው ባተሌነትና ተፈላጊነት በእጅጉ ይቀንሳል።

በአጠቃላይ ስናየው ሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ መላው አፍሪካ፣ ከዚህ በፊት ለኢንዱስተሪያዊነት እንደ መወዳደሪያ ስናያቸው የነበሩ ቁም ነገሮች፣ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ተፈላጊነታቸው በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል። እነዚህን እንደወረዱ ይዞ የኢንዱስትሪያዊነትን ጉዞ ማከናወን የማያዛልቅ ነው።

የበለጸጉት ሀገራት ዐውድ ዛሬ ድንገት መጥቶ ሀገራችንን ያሳጣናል ማለት አይደለም። የዘመናዊነት ጉዳይ አይቀሬ ስለሆነ፣ በተሞክሮም ደረጃ በብዙ የሠለጠኑ ሀገራት እየተተገበረ ስላለ ተጽዕኖው እየነካን ነው። ረጅም በማይባል ጊዜ ውስጥም ሙሉ ተጽዕኖው ይገለጣል። በመሆኑም እየመጣ ያለውን የኢንዱስትሪ ዘመናዊነት ተጽዕኖ በሚገባ ተመልክቶ፣ አዳዲስ መላዎችን መቀየስ ለነገ የማይባል ነው። ዝግጁ ሆኖ ከመጠበቅና በጊዜ ሀብትን በተገቢው ቦታ ከማስቀመጥ አንጻር፤ የቤት ሥራችን ብዙ ነው።

## 7.2. ነገን መገንባት፡ ለኢንዱስትሪያዊነት ዝግጁነት

ቀደም ብለው በተቀመጡ ምዕራፎች እንዳየነው፣ የኢንዱስትሪ ልማት ጥረቶች በኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ተደርገዋል። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ጥረቶች በተለያዩ ተግዳሮቶች የተሞሉ ነበሩ። በሀገራችን በቅድመ ኢንዱስትሪ አብዮት የነበረው

CamScanner

የምርት ግንኙነትና የኢኮኖሚ መሠረት ከሌሎች የዓለም ሀገራት ጋር ተቀራራቢ ነበር። በተለይ ከጥንት ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ከዓለም የሥልጣኔ መሪዎች ጋር የሚወዳደርና በዘመኑ ሥልጡን የሚባል መንግሥት ነበረን። ከዓረቢያ፣ ከሕንድ፣ ከግሪክና ከሮማ ሥርወ መንግሥታት ጋር በንግድ የተሣሠረ፣ የራሱን ገንዘብ የሚያትም፣ በኪነ ሕንጻና በከተማ ግንባታ፣ እንዲሁም በግብርናና በመርከብ ሥራ ከሞላ ጎደል የዘመኑን ቴክኖሎጂ ይጠቀም የነበረ ሥልጣኔ ነበረን።

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ሲጀመር የቀጣይነት ፈተና አለበት። በዚህም የተነሣ ሲወድቅ ሲነሣ ኖሯል። ሁለተኛም ከአክሱም ዘመን በኋላ በመንግሥት ደረጃ ለጥበበ ዕድ የሚሰጠው ቦታ ቀነሰ። ይህ ደግሞ አዳዲስ ፈጠራዎችን እያዳከመ መጣ። በራሱ ሳንቲሞች ሲገበያይ የነበረ ሀገር በአሞሌ ጨው ወደመገበያየት ወረደ። በዝሆን የሚጎተት ሠረገላ የነበረው ሀገር ወደ አጋሰስ መጓጓዣ ወረደ። በድንጋይ ውቅር ቤት ከመሥራት ወደ ሣር ቤት ሄደ። ውኃ የሚቆጥብ መስኖ በድንጋይ ንጣፍ ይሠራ የነበረ ሀገር፣ ወደ ዝናብ ጥበቃ ገባ።

ለአፈንጋጭ ሐሳቦች የሚሰጠው ቦታ ጠባብ መሆንም መፈላሰፍና መራቀቅን፣ መፍጠርንና ሥርዓት ማሻሻልን በእጅጉ ጎድቶታል።

ለዘመናት ይሄው የችግር አዙሪት ቀጥሎ፣ ኢትዮጵያ በ8ኛው ክፍለ ዘመን በውስጣዊ ችግሮች ስትጠመድ፣ በአውሮፓ የኢንዱስትሪ አብዮት ተቀጣጠለ።

በዚህ ሂደት ሀገራችን በኢንዱስትሪ ተስተካካይነት ወደ ኋላ ብትቀርም ለኢንዱስትሪያዊነት መሠረት የሚሆኑ ጥንስሶች በተለያዩ ዘመኖች ተሞክረዋል። በመካከለኛው ዘመን በሙገር አካባቢ የነበረው የጋፋቶች የብረት ኢንዱስትሪ መንደር፤

በወላይታ አካባቢ ተፈጥሮ የነበረው የብረት ኢንዱስትሪ፣ በአንኮበር የነበረው የመሣሪያ ኢንዱስትሪ፣ ከ15ኛው መክዘ ጀምሮ ጥቅም ላይ ውሎ የነበረው ውሃ የሚሰራ ወፍጮ፤ ከጥንቱ የሚጠቀሱ ናቸው።

በዘመናዊት ኢትዮጵያ በዐፄ ቴዎድሮስ የጋፋትን የኢንዱስትሪ መንደር ለመመሥረት እና መድፍ ለማምረት የተደረገው ሙከራ፣ የኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ወደ ኋላ መቅረት የፈጠረው ቁጭት ነው። በዐፄ ምኒልክ ዘመንም የባቡር፣ የስልክ፣ የኤሌክትሪክና የመንገድ ግንባታዎች መጀመር ኢትዮጵያን ከዘመናዊ ቴክኖሎጂና ከኢንዱስትሪ አስተዋውቋታል።

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪያዊነት ጥረት በተደራጀ አግባብ የተጀመረው በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዕቅዶች ተነድፈው ተግባራዊ ተደርገዋል። በዚህ ወቅት የሀገራችን ኢኮኖሚ እጅግ ወደ ዘመነ መንግሥት ነው። በዚህ ወቅት የኢንዱስትሪ ልማትን ለማሳደግ የአምስት ዓመት ኋላ የቀረ ስለነበር የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አነስተኛ ነበረ።ስለዚህም መንግሥት በዋናነት የውጭ ባለሀብቶችን፣ እንዲሁም ከሥርዓቱ ጋር ቁርኝት የነበራቸውን ግለሰቦች በኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ ሆነ። ከዚህ ባሻገር የኢንዱስትሪያዊነት ጥንስ ሊሆኑ የሚችሉ መሠረተ ልማቶች፣ የቴክኒክ ትምህርት ቤቶችና የኢንዱስትሪ ተቋማት ተገንብተዋል።

የደርግ መንግሥት የዕዝ ኢኮኖሚ ሥርዓትን በመከተል ኢንዱስትሪዎችን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር አደረገ። በከባድ ኢንዱስትሪ ልማት ላይ ትኩረት ቢያደርግም ምርታማነታቸው ግን ዝቅተኛ ነበር። የደርግ መንግሥት ኢንዱስትሪን ከማስፋፋት አንጻር ሰፊ ጥረት ቢያደርግም፣ የተከተለው ጫፍ የረገጠ የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለምና የውስጥ ችግሮች የኢንዱስትሪ ልማት ውጥኖቹን አደናቅፈዋል።

የኢሕአዴግ መንግሥት የግሉ ዘርፍ ተሳትፎን ለማበረታታትና የኢንዱስትሪ ልማትን ለማሳደግ ጥረት አድርጓል። የግብርና ልማት መር ኢንዱስትሪያዊነት ስትራቴጂን በመከተል ለግብርና ልማት ቅድሚያ ሰጥቷል። የዕድገትና የማዕዶት ዕቅዶቹ ለኢንዱስትሪያዊነት የተሻለ ትኩረት ሰጥተው ነበር። ነገር ግን የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት አዝጋሚ ስለነበር ኢንዱስትሪው በኮንስትራክሽን ዘርፍ ላይ ጥገኛ ሆነ። መንግሥት ኢንዱስትሪን ለማስፋፋት ሰፋፊ የልማት ፕሮጀክቶችን

CamScanner

ተግባራዊ ያደረገ ቢሆንም፣ የፕሮጀክት አስተዳደር ድክመት፣ የሰው ኃይል እጥረት እና የፖለቲካ ቁርጠኝነት ማጣት የኢንዱስትሪ ልማቱን አደናቅፈውታል።

ዛሬ ሀገራችን በኢንዱስትሪያዊነት በጣም ጥሩ የሚባል ደረጃ ላይ የምትገኝ ባትሆንም፤ ለጉዞው የሚሆኑ ብዙ መደላድሎችን በተለየ ትኩረት በመሥራትና ውጤት በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች። እነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎች ደግሞ በዋናነት የሀገራችንን ዐውድ መሠረት አድርገው የሚሠሩ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ከላይ በጥቂቱ የዳሰስነውን ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በሚገባ ከግምት በማስገባት የተዘጋጁ ናቸው። በተለመደው ቀርፋፋና ፈጠራ አልባ መንገድ የሚተገበሩ

አይደሉም። በመደመራዊ እና ድርመሳዊ ጥ ruptive) መንገድ፣ ትልቅ ለውጥን በሚተልምና በሚያሳካ አኳኋን የሚተግበሩ ናቸው።

በዚህ ረገድ የመጀመሪያው የትኩረት መስክ ለኢንዱስትሪያዊነት ምቹ ሁኔታ መፍጠር እየሠራን ነው። ዝግጁነት ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን የሚይዝ ነው። እያንዳንዱ መደላድል በራሱ ነው። ከዚህ አንጻር አስፈላጊ ርምጃዎችን በመውሰድ እና ዝግጁነታችንን በማጠናከር ላይ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ዘላቂና ውጤታማ የኢንዱስትሪያዊነት ዕድገት ማረጋገጥ የሚቻለው ሁሉም በአንድ ላይ ተቀናጅተው ሲሠሩ ብቻ ነው። በመሆኑም ሥራችን ቅንጅታዊ አንድነት እንዲኖር ማድረግንም የሚጨምር ነው።

ለኢንዱስትሪ አስቻይ ሁኔታዎችን ከመገንባት አንጻር፣ መሠረተ ልማቶቻችንን በሚገባ ማጠናከርና ለመጪው ዘመን የሚሆን የሰው ኃይል መገንባት አለብን። የአገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን ይጠበቅብናል። የጥሬ ዕቃ ዝግጁነት ያስፈልገናል። ከተለያዩ አካላት ጋር የሚያስፈልጉ ትሥሥሮችን ማጠናከር የግድ ነው። እንዲሁም የሕግና የፖሊሲ ዝግጁነት ወሳኝ ነው።

በለውጥ ማግሥት ከሠራናቸው ሥራዎች መካከል አንዱ የአምራች ኢንዱስትሪ ፖሊሲያችንን ማስተካከል ነው።በዚህ ማስተካከያ ኢንዱስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ድርሻ ለማሳደግ ተሞክሯል። በሥራ ላይ በነበረው ስትራቴጂና የፖሊሲ አቅጣጫዎች ያልተፈቱ ክፍተቶችን ለመሙላት ተችሏል። እንዲሁም የዘርፉን የመልማት ዕቅምንና መልካም አጋጣሚዎችን አሟጦ ለመጠቀምና ከዘርፉ ተለዋዋጭ ባሕርያት ጋር የሚመጡ የምርት ሥርዓት ለውጦችን ለማስተናገድ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።

ፖሊሲው የሕዝባችንን የኑሮ ደረጃን በተለየ መልኩ ማሻሻልን ተልዕኮው አድርጓል። ወደ ውጪ የምንልካቸው ምርቶችን በተለየ መልኩ ማሳደግን እና ወደ ውስጥ የምናስገባቸውን ሸቀጦች ደግሞ በሚገባ መተካትን ዋነኛ ግቦቹ አድርጓል። ለዚህ ስኬታማነት የተለዩ የኢኮኖሚ መርሖችን ይከተላል። እነርሱም፥ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ የሚሆኑ አምራቾችን ማፍራት፣ ዕሴት የታከለባቸውንና በዓይነታቸው ብዙ የሆኑ ምርቶችን ማምረት፣ እንዲሁም የውስጥ የአቅርቦት ሠንሰለትን በሚገባ ማጠናከር ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ለውጦችን ለማስተናገድ ዝግጁና እንደየአስፈላጊነቱም በፍጥነት የሚከለስ ፖሊስ ፖሊሲ ይሆናል።

ከአምራች ኢንዱስትሪው ዝግጁነት መገለጫዎች መካከል መሠረተ ልማት ዋነኛው ነው። ቆይታለች። አሁን በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙትን ጨምሮ ከዚህ በፊት የተገነቡት ኢትዮጵያ ለዓመታት በኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶች ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ስታደር የትንራንስፖርትና የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶች፣ የኃይል ማመንጫዎች፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮችና ዞኖች፣ የጉምሩክና ሎጅስቲክስ መሠረተ ልማቶች፣ ሀገራችን ለአምራች ኢንዱስትሪው ዕድገት ያሳካችው ዝግጁነት መገለጫ ተደርገው የሚቀርቡ ናቸው።

የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን ለማስፋፋት ባለፉት ዓመታት ሰፊ ኢንቨስትመንት ለውጥ አሳይቷል። የሕዳሴ የኃይል ማመንጫን ጨምሮ ሌሎች በጅምር ያሉና በሚገባ) ተካሂዷል። ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚቀርበው የኤሌክትሪክ ኃይል

CamScanner

አቅርቦትም ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጡ ያልነበሩ ማመንጫዎችን ወደ መሥመር ለማስገባት ተችሏል። በዚህም ሀገራችን ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚያስፈልጋትን የኃይል አቅርቦት በሚገባ መሸፈን ችለናል።

ካለን ዕምቅ ዐቅም አንጻር ሌሎች ብዙ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶችን የምንቀርጽና የምንተገብር ቢሆንም፣ የኃይል አቅርቦት ግን ጎዶሎ ሆኖ አምራችነትን ከሚጎትቱ ጉዳዮች መካከል መሆኑ አብቅቷል። በሌላ በኩል ግን የኃይል አቅርቦቱን አስተማማኝ ከማድረግና የኃይል መቆራረጥን ከመቅረፍ አኳያ ቀላል የማይባል የማሻሻያ ሥራ ይጠብቀናል።

ሌላው በስፋት የተሠራበት ዘርፍ የመጓጓዣ ዘርፍ ነው። በተለይም ከመንገድ አንጻር ብዙ አዳዲስ መንገዶችን መገንባትና የጥገና ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል። ከተሞቻችንን የሚያገናኙ ዋና ዋና መንገዶችና ለእነዚህም ገባር የሚሆኑ መካከለኛ ከተሞችን የሚያገናኙ መንገዶች እየተገነቡ ናቸው። ከዚያም ሲያልፍ ገበሬው ከመንገድ ብዙ ሳይርቅ ምርቱን በቀላሉ ወደ ገበያ የሚወስድባቸው መንገዶችን በመገንባት ላይ ነን።

ይሁንና የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች ከጥራት፣ ከቅልጥፍና እና ከወጪ አኳያ የአምራች ኢንዱስትሪው በሚፈልገው ደረጃ ላይ ደርሰዋል ማለት አይቻልም። በአጠቃላይ ከትራንስፖርት መሠረተ ልማት አንጻር የበለጠ መስፋፋት፣ ጥሬ ዕቃ ባለባቸው አካባቢዎች ዘንድ ተደራሽ መሆን፣ ሁሉንም የኢንዱስትሪ ዞኖች ማገናኘት፣ ደረቅ ወደቦችን ማስፋፋትና ለባሕር የበለጠ መቅረብ ያስፈልጋል።

ጠንካራ የሎጅስቲክስ ሥርዓት ጥሬ ዕቃና የተመረቱ ምርቶችን ለማጓጓዝ ወሳኝ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ አኳያ ሀገራችን ባለፉት ዓመታት በሎጅስቲክስ ዘርፉ በተሠሩ የሪፎርም ሥራዎች መሻሻሎችን አሳይታለች። ቢሆንም የትራንስፖርት ሁኔታው ቀልጣፋ አለመሆን፣ የምርት አያያዝና ማከማቻ ሥርዓት አለመዘመን ችግር ሆኖ ቆይቷል።

ለኢንዱስትሪ መሠረት በሆኑ ቴክኖሎጂዎች አኳያም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብዙ ነገሮችን ማሳካት ችለናል። በይነ መረብን በመላው ሀገራችን በማዳረስ ዙሪያ ካለን ስኬት በተጨማሪ፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የመረጃ ቋቶችን ገንብተናል። ዘርፉን ለግል ባለሀብቶች ክፍት በማድረጋችን፣ የተለያዩ አገልግሎቶችን ማስተናገድ የሚችሉ የመረጃ ቋቶችን የገነቡና አመርቂ ውጤቶችን እያስመዘገቡ ያሉ ተቋማት ተፈጥረዋል።

ተቋማትን ከማዘመን አንጻርም ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ይገኛል። ለማዘመን የሚውሉ ሶፍትዌሮችን ከማልማት አንጻር የውስጥ ዐቅማችንን በከፍተኛ ደረጃ እየተጠቀምንና በተለየ ትኩረትና ክትትል ከፍተኛ ውጤት እያገኘን ነው።

የሰው ሠራሽ አስተውሎትን ወደ ሥራ ከማስገባት አኳያም፣ ቴክኖሎጂው የሚኖረውን ከፍተኛ ተጽዕኖና ግብአትነት ከግምት ያስገባ እንቅስቃሴ እያደረግን ነው። በዚህም በተለያዩ ተቋማት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የምርምር ውጤቶችን ማፍራት ችለናል። በዚህ ሁሉ ውስጥ ደግሞ የቴክኖሎጂ ደኅንነት ዋነኛ ጉዳይ እንደመሆኑ በሳይበር ደኅንነት ዙሪያ ወሳኝ ዐቅሞችን እየገነባን እንገኛለን።

የዚህ ሁሉ ቅንጅት የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታችን እንዲሠምር እያደረገው ይገኛል። በአጠቃላይም ከቴክኖሎጂ አንጻር ብዙ ርቀት መጓዝ ቢጠበቅብንም፣ በቅርብ ዓመታት ውስጥ የተለምነውን የኢንዱስትሪያዊነት ጉዞ ለመደገፍ የሚችል ዝግጅት አለን ማለት ይቻላል።

በኢንዱስትሪያዊነት ጉዞ ውስጥ፣ ዘመናዊ የአገልግሎት ዘርፍ ወሳኝ ምሰሶ በመሆን የኢንዱስትሪዎችን ስኬት ያረጋግጣል። ይህ ዘርፍ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚያቀርበው ድጋፍ እጅግ ከፍተኛ ነው። ያለው የብስለት ደረጃ የኢንዱስትሪዎችን ተወዳዳሪነት ይወስናል። እንዲሁም የራሱም ብስለት በኢንዱስትሪያዊነት ፍጥነትና ጥራት ይወሰናል።

የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪያዊነት ስኬት፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከግብርና ወደ ዘመናዊ አምራችነት በማሸጋገር ብቻ አይወሰንም። ከዚያም አልፎ ወደ ውስብስብና እጅግ ዘመናዊ ወደ ሆነ የአገልግሎት ዘርፍ ሽግግር በማድረግም ጭምር

CamScanner

ሊረጋገጥ ይገባል። በአሁኑ ጊዜ ዝቅተኛ የዕሴት ጭማሪ በሚያመጡ ተግባራት ላይ ያተኮረውን የአገልግሎት ዘርፍ፣ ከፍተኛ የዕሴት ጭማሪ ወዳለው የቴክኖሎጂ ምጥቀትና ውስብስብነት ማሸጋገር ወሳኝ ነው፡

ከዚህ አንጻር የአገልግሎት ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ የተለያዩ ርምጃዎች ወስደናል። ከብድር አቅርቦት አንጻር የግሉ ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ ተደራሽ እንዲሆን አድርገናል። በሌላ በኩል ደግሞ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በመሥመር ላይ(online) የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች በከፍተኛ ደረጃ ጨምረናል። በዚህ መሠረተ ልማትም በተጨማሪ በመሶብ የአንድ ቦታ አገልግሎት ማዕከል፣ ተገልጋዮች በየተቋማቱ ቢሮ መሄድ ኢንዱስትሪው ተዋንያን ካሉበት ሆነው ብዙ አገልግሎቶችን ለማግኘት ችለዋል። ከዚህም ሳያስፈልጋቸው፣ ብዙ አገልግሎቶችን በአንድ ላይ እንዲያገኙ አድርገናል"።

ይሁንና ዘርፉ እያደገ ቢመጣም፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚሰጠው ድጋፍ አሁነም ዘርፍ ወሳኝ የሆኑ የፋይናንስ፣ የሎጅስቲክስ፣ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ውሱን ነው። የአገልግሎት ዘርፉ ብስለት ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ለአምራች ኢንዱስትሪው የምክር፣ እንዲሁም የጥናትና ምርምር አገልግሎቶች የኢንዱስትሪ ልማትን በሚደግፍ አግባብ ከማቅረብ አንጻር ሰፊ ውሱንነት ይታይበታል። ይህ ዘርፍ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ በከፍተኛ ሁኔታ መሻሻል አለበት።

በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድና በጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ ቴክኖሎጂ ለጠንካራና ዘላቂ ኢንዱስትሪያዊነት መሠረት ነው። ዘመናዊ፣ ተወዳዳሪና አሻጋሪ አምራች ኢንዱስትሪ ልማት፣ በዋናነት ካፒታልና በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደርጋል። ያለ ብቁና በቴክኖሎጂ የሠለጠነ የሰው ኃይል ሁለቱ ግብአቶች የሚፈለገውን ውጤት ሊያመጡ አይችሉም። ለዚህ ደግሞ ማጠንጠኛው ሥልጡን የሰው ኃይል ዝግጁነት ነው።

የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ከሁሉም በላይ በፋብሪካ ምሕንድስናና በዲጂታል ቴክኖሎጂ የበቃ የሰው ኃይል ዝግጁነትን ይጠይቃል። ለዘርፉ የሚደረጉ ሥልጠናዎች ከተግባር ጋር የተያያዙ መሆን አለባቸው። እነርሱም ቴክኖሎጂን የማሸጋገር፣ የማለማመድና የመፍጠር፣ የመተርጎምና የመተግበር ክሂሎት ያለው የሰው ኃይል በማብቃት ላይ ማተኮር ይገባቸዋል።

ቴክኖሎጂ በአምራች ኢንዱስትሪው የነበረውን ምርት ለመተካት ይረዳል። አዲስ ምርት ለማምረት ወይም የነበረውን ለማዘመን ይችላል። በአዲስ የማምረት ሂደት ከፍተኛ ምርታማነት እንዲመዘገብ ያደርጋል። ተለጣጭነትንና የማምረት ሀቅምን በመገንባት የማምረት ወጪን ይቀንሳል። ጥራትና ጊዜን በመቀየር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ የዕሴት ጭማሪ ለማስገኘትና የተወዳደሪነትን ዐቅም ለማጎልበት ያግዛል።

በኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፎች እንዲሁም በቴክኒክና ሞያ ተቋማት በተደረጉ ኢንቨስትመንቶች በርካታ የሠለጠነ የሰው ኃይል መፈጠሩ ይታወቃል። ይሄም በሰው ኃይል በኩል ለአምራች ኢንዱስትሪው ያላትን ዝግጁነት የሚያሳይ ነው። ይሁንና የዛሬና የነገ የኢንዱስትሪ ደረጃን ታሳቢ ስናደርግ በትምህርትና ሥልጠና ታግዞ ለሥራ ዝግጁ የሆነው የሰው ኃይል ቁጥር በኢትዮጵያ ዝቅ ያለ ነው።

ክሂሎት ያለው የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመገኘት የሀገራችን የአምራች ኢንዱስትሪው ማነቆ ሆኖ ቆይቷል። በተለይም በከፍተኛ ትምህርትና በቴክኒክና ሞያ ሥልጠና ተቋማት ትምህርታቸውን ተከታትለው ወደ ሥራ ዓለም የሚገቡ ሠልጣኞች በተግባር የተደገፈ ሥልጠና አግኝተው እየወጡ አይደለም። በዚህ የተነሣ ክሂሎታቸው በተግባር የነጠረ ባለመሆኑ ዘመናዊ ኢንዱስትሪን ለመገንባት በቂ አይደለም።

ከቴክኒካዊ ክሂሎት ባለፈ፣ ዘመኑን የሚመጥን የኢንዱስትሪያዊነት ባህል ወሳኝ ነው። የኢንዱስትሪ መስፋፋትን የሚሻ ማኅበረሰብ _ ቀጣይነት ያለው _ የባሕል ተሐድሶ ያስፈልገዋል። በኢንዱስትሪያዊነት ፋና ወጊ ማኅበረሰቦች አስፈላጊውን ፋይናንስ ቆጥበው፣ ቴክኖሎጂውን ራሳቸው ፈጥረው፣ ጊዜን በአግባቡ ተጠቅመው፣ ዛሬያቸውን የልጆቻቸው ነገ ላይ

CamScanner

አውለው፣ ለዓለም ኢንዱስትሪ እመርታ መሠረት ጥለዋል። ለተሳካ የኢንዱስትሪ ልማት ፈጠራን፣ ትምህርትንና አዳዲስ አሠራሮችን የሚቀበልና ውጤታማ ትግበራን የሚያበረታታ ባህል አስፈላጊ ነው።

እንደ ጃፓን የሜጂ ተሐድሶና እንደ ደቡብ ኮሪያ ፈጣን የኢንዱስትሪ ዕድገት ያሉ ታሪካዊ ምሳሌዎች አንድ ማኅበረሰብ ለትምህርት፣ ለቴክኖሎጂ እና ለኢንተርፕረነርሺፕ በጋራ ያለው ማኅበራዊ ባህልና ቁርጠኝነት ለኢንዱስትሪ ልማት ያለውን ፋይዳ በግልጽ የሚያመለከቱ ተሞክሮዎች ናቸው ።

ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪኳን እንደመነሻ ተጠቅማ በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ አሻጋሪ ለውጥ አላመጣችም። ነገር ግን በጎጆ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ የሚመደብ የእጅ ጥበብ ክሂሎቶች ሰፊ ልምድ ያላት ሀገር ናት። በኢትዮጵያ በተለያዩ ማኅበረሰቦች ሸመና፣ የሸክላ ሥራ፣ የብረትና የቆዳ ሥራዎች፣ የድንጋይ ሥራዎች፣ የጌጣጌጥ ሥራዎች ወዘተ ሀገራዊ ዕውቀቶች አሉ።

ልዩ ልዩ ማኅበረሰቦች በእነዚህ ሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ በኢመደበኛ ሁኔታ ተሠማርተው ዋነኛ የኢኮኖሚ መሠረታቸው አድርገው ይኖራሉ። በእጅ ጥበብ ላይ ያለው ይህ ልምድ የኢንዱስትሪ ልማት ከሚፈልገው ባህል ጋር የሚጣጣም ነው። ከዘመናዊ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ጋር ተሣሥሮ የኢንዱስትሪ ልማትን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልክ መተግበር የሚችል ነው።

በአንጻሩ በኢትዮጵያ አሁንም ቢሆን ኢንዱስትሪያዊነትን የሚፈትኑ ሰፋፊ አሉታዊ ባህላዊ ተጽዕኖዎች አሉ። በጥበበ ዕድ ላይ የተሠማሩ ዜጎችን ማግለል፣ ዕውቀታቸውን በጥናትና በምርምር ያለመደገፍ፣ ለባለ ክሂሎቶቹ ተገቢውን የፖሊሲ፣ የቦታና የካፒታል ድጋፍ ያለማድረግ ክፍተቶች ዙሪያ እየሠራን ነው። ከዚህም ባለፈ በተለያዩ አካባቢዎች ዜጎች ለሥራና ለጊዜ ያላቸው አመለካከት ለኢንዱስትሪ ልማት ምቹ አይደለም።

በኢትዮጵያ የዜጎች የቁጠባና ኢንቨስትመንት ባህል አሁንም ደካማ ነው ማለት ይቻላል። ብዙኃኑ ዜጋ ያለውን ውሱን ሀብት ለአጭር ጊዜ ፍላጎቶች ለማሟላት የመጠቀም ዝንባሌ አለ። እንዲሁም ምርትና ምርታማነት ለሚጨምሩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ሳይሆን እንደ ማኅበረሰብ ዕሴታቸው ከፍ ተብሎ ለሚታዩ ማኅበራዊ ኩነቶች ሀብትን የማዋል አዝማሚያ ይታያል።

በአጠቃላይ በሪፎርሙ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፈተናዎች፣ የማክሮ ኢኮኖሚ ስብራቶች፣ የፖሊሲ መዛነፍና የቢዝነስ አካባቢ ችግሮች መፍትሔ እንዲያገኙ እየተሠራ ነው። በዐሥር ዓመቱ ዕቅድና በሀገር በቀል ሪፎርም ለአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ዕድገት ግልጽ አቅጣጫ ተቀምጧል። ግብርና በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ፣ ማዕድን ለሌሎች ዘርፎች መሠረት እንዲሆን፣ ዲጂታል ኢኮኖሚ እንዲገነባ ትኩረት ተሰጥቷል። የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲጨምር ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሪፎርም ተደርገዋል። ቴሌኮም፣ ባንክ፣ ሎጅስቲክስ፣ ኢነርጂና ሌሎች ዘርፎች ለግል ኢንቨስትመንት ክፍት ሆነዋል። የግል ዘርፍ ተወዳዳሪ እንዲሆን፣ የፕራይቬታይዜሽን ሥራዎች ተከናውነዋል። የትራንስፖርት፣ ተሠርቷል። የፋይናንስና የንግድ ዘርፎች ተከፍተዋል። የነባር ኢንዱስትሪውን ምርታማነት ለመጨመር፣ አዲስ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እና በገቢና በወጪ ምርት ላይ ትኩረት ለማድረግ ተሰርቷል።

በአጠቃላይ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ አትኩረን በመሥራታችን አመርቂ ውጤቶችን ደረጃ ላይ ደርሷል። ነገር ግን አመርቂ አይደለም። ስለዚህም ያሉንን ጠንካራ ጎኖች አጠናክረን መቀጠል አለብን። ክፍተቶቻችንን ደግሞ ለይተን መሙላት

ይጠበቅብናል። አስመዝግበናል። በዚህም የተነሣ የሀገራችን የኢንዱስትሪ ግንባታ ዝግጁነት ደኅና የሚባል . በመሆኑም

CamScanner

በኃይል አቅርቦት፣ በመጓጓዣና በቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶች ግንባታና ዝግጁነት ዙሪያ ያስመዘገብናቸውን ውጤቶች በማስቀጠል፣ ሊመጣ ያለውን የኢንዱስትሪ ዕድገት በሚመጥን መልኩ ማስኬድ ይጠበቅብናል።

በሌላ በኩል ደግሞ በእነዚህ መሠረተ ልማቶችም ይሁን በሌሎች የበለጠ ወደ ኋላ በቀሩ ጉዳዮች ዙሪያ ልዩ የሆነ ትኩረት ልንሰጥ ይገባናል። በዚህም ትኩረት ለኢንዱስትሪ ልማታችን ዕንቅፋቶችን ማስወገድና መደላድል መፍጠር የዚህ ትኩረት መስክ ዋነኛ ግብ ነው። ሁለተኛው የትኩረት መስክ መደላድሎቹን ተንተርሰን የምንገነባውን ኢንዱስትሪ ማዕከል ያደረገ ነው። እርሱም በሚቀጥለው ክፍል ይብራራል።

## 7.3. የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ፡ የመደመር መንግሥት ጎዳና ወደ ብልጽግና

በኢንዱስትሪ ግንባታ ሂደት ስኬታማ ኢንዱስትሪ የገነቡ ሀገራት የየራሳቸውን ዐውድ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የተለያዩ አካሄዶችን ተከትለዋል። ጀርመን፣ ቻይና፣ ሕንድ፣ ብራዚል፣ ደቡብ ኮሪያና ሌሎችም የተከተሉት ኢንዱስትሪያዊነት አንድ ዓይነት አካሄድና መልክ የለውም።

የጀርመን የኢንዱስትሪ ግንባታ መሠረቱ አነስተኛና መካከለኛ የንግድ ተቋማት(Small and Medium Enterprises, SMEs) ናቸው። ሀገሪቱ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የምሕንድስና ውጤቶች ለዓለም የማቅረብ ሞዴልን መርጣ ኢንዱስትሪዋን ገንብታለች። በኋላም አራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት ሐሳብን በማጎልበት፣ ለዓለም ቀድማ ያስተዋወቀች ሆናለች። ሐሳቡ ኢንዱስትሪዋ ባለበት የማይቆምና በቀጣይ የለውጥ ሂደት ውስጥ ቀዳሚ ሚና ለመጫወት ያለመ መሆኑን ማሳያ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ቻይና የወጪ ንግድን ማዕከል ያደረገ መንግሥት መር አካሄድን መርጣለች። መንግሥት ግዙፍ ኩባንያዎችን በተለያየ መልኩ እየፈጠረና ከግል ባለ ሀብቶች ጋር እየተጣመረ አስፈላጊውን ሀብት አንቀሳቅሷል። በዚህም ዛሬ የደረሰችበትን የኢንዱስትሪ ደረጃ አሳይታናለች ።

ደቡብ ኮሪያና ጃፓን የግዙፍ ሀብት ባለቤት ከሆኑ ቤተሰቦች ጋር የተሣሠሩ አካሄዶችን ተከትለዋል። ሕንድ ከተለመደው ግዙፍ ፋብሪካዎችን የመገንባት አካሄድ ወጣ ብላ፣ ዘመኑን የተከተለና ቀጥታ ዲጂታል ኢንዱስትሪን ማዕከል ያደረገ መንገድ ተከትላለች። ሲንጋፖር በበኩሉ አካባቢያዊ ትሩፋቶችን መሠረት ያደረገ አካሄድን ተከትላ ስኬታማ ሆናለች። በመሆኑም፣ እነዚህን ሁሉ ህያው ምስክሮች ይዘን ለሀገራችን የምንመርጠው መንገድ ግልጽ ነው።

የሀገራችን የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግንባታ ጉዞ ከራስዋ ዐውድ የሚነሣ፤ ጠንካራና ደካማ ጎኖቿን የገመገመ ሊሆን ይገባል። ምሳሌ ከሚሆኑ ሀገራትም የምንማረውን እንወስዳለን። ከዚህ በኋላ የሌሎች ሀገራትን ልምድ እንደወረደ የመውሰድን አካሄድ ፈጽሞ አንደግመውም።

የመደመር መንግሥት ኢንዱስትሪያዊነትን የሚረዳው ከኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ባሻገር፣ በዋናነትም ከሉዓላዊነት፣ ራስን ከመቻል፣ ማንም ላይ ካለመደገፍ፣ ከሀገራዊ ክብር ጋር አጣምሮ ነው። በኢንዱስትሪ የመበልጸግ ትልማችንም አምራችነት ለአጠቃላይ የውስጥ ምርታችን የአንበሳውን ድርሻ አበርካች ከመሆንያልፋል። እንደ ሀገር ማሳካት የምንፈልገውን ሁሉ ለመሥራት የሚያስችል የቴክኖሎጂ፣ የሀብት ወይም የዕውቀት ዐቅም ውሱንነቶችን ሙሉ ለሙሉ ለመቅረፍ የሚያስችል ነው።

በዚህ የአምራችነት ዐቅም ግንባታ ሂደት ውስጥ የምንጎናጸፋቸው ነገሮች አሉ። እነዚህም የኢኮኖሚ ምንጭ ብዝኃነት፣ የቴክኖሎጂ ባለቤትነት፣ የኑሮ ደረጃው ከፍ ያለ የዘመነ ከተማ፣ የዳበረ የኢንዱስትሪ ባህል፣ ዓለም አቀፋዊነትና መሰል ብዙ ትሩፋቶች ናቸው። በመሆኑም ኢንዱስትሪያዊነት ሀብት ማንቀሳቀስን ብቻ ማዕከል አድርጎ የሚዘወር አይደለም።

CS CamScanner

በእያንዳንዱ የኢንዱስትሪ ውሳኔ ዘላቂነትንና ራስን መቻልን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ሀገራዊ ፍላጎትን ማስከበርንና ሉዓላዊነትን ሁሉ ባማከለ መልኩ መወሰንና ኢንዱስትሪውም በዚያው መልኩ መገንባት ይኖርበታል።

በመሆኑም የኢንዱስትሪያዊነት አካሄዳችን በዋናነት ዐውዳችንን ያገናዘበ፤ ዛሬ ካለን ወረት ሥቶ፣ የነገን ግዙፍና በዓለም አቀፍ መድረክ ተወዳዳሪ ኢንዱስትሪን በፈጠራና በፍጥነት ግንባትንና ዘላቂነቱን ማስጠበቅን የሚተልም ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ተካካይነትን ለማፋጠን ልትጠቀምባቸው የሚገቡ በርካታ ዕምቅ ዐቅሞች አሏት። የመደመር መንግሥት ከዚህ በፊት ዐቅሞቻችንን ከምንመለከትበትና ከምናለማበት ተለምዷዊ መንገድ መውጣት አለብን ይላል። ዘመኑን በሚመጥንና ለሀገር ከፍተኛ ጥቅም ሎሚያስገኝ መልኩ ማልማትን የዘመናዊ ኢንዱስትሪያዊነት መሠረት አድርጎ ይቆጥራል።

በእውቀት እና ክሂሎት የተገነባ አምራች፣ ዘላቂና ደኅንነቱ የተጠበቀ የሰው ኃይል፣ የዘመኑ  የኢንዱስትሪያዊነት መዘውር ነው። የኢኮኖሚ ተስተካካይነት በሀገራችን የሚረጋገጠው ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር የተዛመደ የሰው ኃይል ሥምሪት ሲኖር ነው። የሕዝብ ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በፍትሐዊ የኢኮኖሚ ልማት ተሳትፎ መረጋገጥ የሚችለው፣ የማኅበረሰብ በቀዳሚነትም ወጣቱ ኃይል በቴክኖሎጂ ዕውቀትና ክሂሎት ሲተጋ ነው።

የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫችን የዘመኑን ቴክኖሎጂ በመታጠቅ ምርታማነትን የሚያረጋግጥ የሰው ኃይል ሥምሪትን መሠረት ያደረገ ነው። ይህ ሥምሪት፣ የሠራተኛን የኅንነት ያስጠብቃል። ለ2ኛው ክፍለ ዘመን የሚመጥን የኑሮ ዘይቤንም ያረጋግጣል። ይህም የኢንዱስትሪ ሥርዓትን በማስፈን ሂደት ውስጥ ብቁ የሰው ኃይል የመፍጠር ፋይዳው ትልቅ ነው።

ሀገራችን ወጣትና ትኩስ ጉልበት ያለው የሰው ኃይል ባለቤት ናት። ይህ ኃይል ከርካሽ ጉልበትነት አልፎ ሥልጡንና የዘመኑን ቴክኖሎጂ የታጠቀ፣ በምርምርና በልማት ከፍተኛ የፈጠራ ዐቅሙን የሚገልጥ፣ በነገው ኢንዱስትሪ ተፈላጊ ኃይል አድርገን ካለማነው፤ በሀገር ውስጥም ይሁን በየትኛውም ኢንዱስትሪ ውስጥ ራሱን ማሳየት ይችላል። በቀላሉ በሮቦቶች የማይተካ፣ ሀገሩን መደገፍ የሚችል ሀብትም ይሆናል።

በሌላ በኩል ደግሞ የተፈጥሮ ሀብታችንን እንደ ጥሬ ዕቃ ለሌሎች ዕሴት ጨማሪዎች _አሳልፈን (በብላሽ) ከሰጠነው ሀገራዊ ኪሣራ ይሆናል። ሀገራዊ ዕሴቶችን ጨምረን፣ __ የኢንዱስትሪ የጥራት ደረጃዎችን አሟልተን፤ በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ ምርት ወይም የምርት ግብአት ካደረግነው ግን የሀገር አለኝታና ድጋፍ ይሆናል። እያደገ ያለው የሀገር ውስጥ ገበያችንም፣ የሌሎች ሀገራት ርካሽ ሸቀጥ ማራገፊያ መሆን የለበትም። ከዚያ ይልቅ ጥራት ያላቸው ሀገራዊ ምርቶችን አቅርበንለት፤ ሀገራዊ ምርቶችን በኩራት የሚጠቀም [ ልናደርገው ይገባል። ከሀገር ውስጥ አልፎ በሌሎች ሀገራት በሚኖረው ቆይታም፣ _ ምርቶቹን የሚያስተዋውቅ አምባሳደር አድርገን መቅረጽ አለብን።

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት መሪነት የሚረጋገጥ ኢንዱስትሪያዊነት ዋና ሀገራዊ ፋይ የማይቀለበስ ዘላቂ ዕድገት ነው። በሰፊው ዐውድ ሲታይ ደግሞ የተሳካ መዋቅራዊ ሽ ማድረግ ነው። የኢትዮጵያ ብልጽግናና የኢንዱስትሪ ተስካካይነት መገለጫው በገቢ ዕድገት ብቻ አይደለም። ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሆነ፣ የዜጎችን የኑሮ ደረጃና አኗኗር ዘይቤ ዘመናዊነት የሚያረጋግጥና የማምረት ዐቅሙ የጎለበተ ዜጋና ኢኮኖሚ ሲፈጠር ነው። ይህንን ለማረጋገጥ ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ ደግሞ ጠንካራ የአምራች ዘርፍን መገንባት ነው።

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተፈጥሯዊ የቴክኖሎጂ ገብነት አለው። ይህንንም ሀገራችን ካ እንዲሁም ዕምቅ ዐቅሞች አሟልቶ መጠቀም መቻል ይኖርብናል። እንደዚያ ከሆነ ይህ ዘርፍ ዝቅተኛ የአምራችነት ደረጃ አንጻር፣ በቀጣይ

CS CamScanner

አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታዎች፣ ዝግጁነት ተከታታይ የሆነ ቀጣይነት ያለው ባለ ሁለት አሐዝ ዕድገት ማስመዝገብ የሚቻልበት ዘርፍ ነው።

የአምራች ዘርፍ ዝቅተኛ ዕሴት ከላቸው ዘርፎች ተነሥቶ የተሻለ ዕሴት ወዳላቸው ዘርፎ በማሸጋገር፣ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ያግዛል። ዘርፉ በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትና የዕሴት ጭማሪ ስላለው፣ ዋነኛ ተዋናይ የሚሆነው ዜጋ ቀጣይነት ያለው የምርትማነት ደረጃው እንዲሻሻል ያደርጋል። በዚህም ገቢው እንዲያድግና ኑሮው እንዲሻሻል ያስችላል። በአምራች ዘርፍ ላይ የሚኖር እመርታ የገጠር መዋቅራዊ የድህነት ሁኔታን በመቀልበስ፣ ምርትና ምርታማነት እንዲሻሻል ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል።

ፈጣንና ዘላቂ የቴክኖሎጂ ዕድገትና ፈጠራ፣ የሀገራችንን ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ብልጽግናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው። ቴክኖሎጂን መለየት፣ መማር፣ መቅዳት፣ እንዲሁም በምርትና በማምረት ሂደት ላይ ጥቅም ላይ ማዋል ባህል መሆን አለበት። የሀገራች የኢኮኖሚ ብልጽግና ተስተካካይነት ብቸኛ ማረጋገጫም ቀጣይነት ያለው የቴክሎሎጂ ደረጃን ማሻሻል ነው። ይህ በዋናነት ሊረጋገጥ የሚችለው ጠንካራ የሆነ የአምራች ዘር መገንባት ሲቻል ነው።

ሉዓላዊነታችንንና ብሔራዊ ጥቅማችንን ከማስጠበቅ አንጻር፣ ኢንዱስትሪያዊነት በየዓ ከሚመረት ምርትና ከሚገኝ ገቢ በላይ ነው። በማምረት ዐቅም የሚወሰኑ የምርት ዓይነ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ከማሟላት በላይ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊና በወታደራ ዐቅሞች የሚገለጹ ተስተካካይነቶችን እንድናረጋግጥ ያስችላል። በየጊዜው በቴክኖሎጂ ደረ እየተሻሻለ የሚሄድ የአምራች ዘርፍና የማምረት ዐቅም በሀገራችን ከወታደራዊ ዐቅም ጀም ሉዓላዊነታችንን የሚያስጠብቅ ጠንካራ የአኮኖሚ ዐቅም እንድንገነባ የሚያስችል ነው።

ሀገራችን በዓለም አቀፍ ተለዋዋጭ የጂኦፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ ብሔራዊ ሉዓላዊነቷን ማረጋገጥ የሚያስችል ወታደራዊ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠር፣ ማምረትና ምርት አቅርቦትና ትሥሥርን ማጠናከር ይኖርባታል።

በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ጉዟችን የውስጥ ዐቅምን አሟጦ መጠቀምንና አስፈላጊ ዐቅሞችን " ወደ ሀገራችን የሚጎርፉ ሸቀጦችን በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት አካሄድ ነው። የብዙ ጥሬ " መገንባትን ማዕከል ያደረገ ነው። በዚህም የመጀመሪያ ጥቅል ግባችን በገቢ ንግድ(mport) ኙ አምራች ብንሆንም፣ እነዚህን ግብአቶች ተጠቅመው የሚሠሩ ምርቶችን መልሰን በውድ ዋጋ ከውጭ ሀገራት የምናስገባ ሀገር ነን። ይሄንን እውነታ ሥርዓት በያዘ መልኩ መቀየር እስካልቻልን ድረስ፣ ዘለቄታዊ ቀጣይነት ያለው ኢንዱስትሪ መገንባት አንችልም። ሁለተኛው ጥቅል ግብ ደግሞ የወጪ ንግድ (Export) ቀጥታ ጥሬ ዕቃን ከመሸጥ አልፎ፣ እሴት የታከለባቸው ምርቶችን ማቅረብን፣ ከዚያም ሲያልፍ ያለቀላቸው ምርቶችን በዓለም ገበያ ተወዳድሮ ለተጠቃሚዎች ማቅረብን ዒላማ ያደረገ ነው።

የውስጥ ገበያን ማዕከል ያደረገ ኢንዱስትሪያዊነት ግቡ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ አምርቶ የሀገርን ገበያ ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር ነው። አርሱም በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ የሚኖረንን ተደጋፊነት የሚቀንስና ራሳችንን እንድንችል ወረዳ ስልት ነው። ስልቱ የሀገር ውስጥ ባለ ሀብቶችን ማገዝን ይጠይቃል። እነዚህ ባለሀብቶች ከቀላል እስከ ከባድ፣ ብሎም እስከ ውስብስብ የሚደርሱ ምርቶችን ማምረት እንዲችሉ ማብቃትን ይሻል። በሚያመርቷቸው ምርቶችም የሀገር ውስጥ ገበያውን በሚገባ ማዳረስ እንዲችሉ ማድረግን ማዕከል ያደርጋል።

በዚህም በተጨማሪ የመደመር መንግሥት እንደየአስፈላጊነቱ ቁልፍ ኢንዱስትሪዎችን ይገነባል። እነዚህም ግዙፍና ወሳኝ የሆኑ፣ በባለ ሀብቱ የማይደፈሩ፣ ለሀገር ብልጽግና ወሳኝነት ያላቸው ናቸው። እነዚህን ምርቶች በመለየትና የተለያዩ ፈጠራዎች በማከል፣ አዳዲስ ምርቶችን ይዞ በገበያው ተሳታፊ ይሆናል።

CamScanner

በዚህ ዓይነቱ አቀራረብ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ከመንግሥት ብዙ ድጋፍ ይታ የገንዘብ ድጎማና ብድር፣ የግብር ቅነሳ፣ እንዲሁም በዋናነት የሀገር ውስጥ ገበያው ምርትን እንዳያስተናግድ ማድረግ፣ በውጭ ምርቶች ላይ የታሪፍ ጭማሪን ጨምሮ የማልማት አካሄድ እንደ ሀገር የማይበገር ኢንዱስትሪ ባለቤት ለመሆን መተኪያ ሊታዩ ርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃሉ። ሆኖም የውስጥ ኢንዱስትሪዎችን ቅድሚያ አቀራረብ ነው።

እንደዚህ ላሉት ኢንዱስትሪዎች አብዛኛውን ግብአት ከሀገር ውስጥ ማቅረብ ከተቻለ በውጭ ሀገራት ላይ የሚኖረን ተደጋፊነት ይቀንሳል። የእነሱ መናወጥ ብዙም የማይን የውጭ ምንዛሪ ብዙም የማያስጨንቀን፣ በተወሰነ መልኩ ራሳችንን በራሳትን እንሆናለን። ራሳችንን ችለን ለመቆምና ሉዓላዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት እጅግ የተሻለው አማራጭ ይህ ነው።

በኢትዮጵያ የዕድገት ጉዞ ውስጥ አነስተኛና መካከለኛ አምራች የንግድ ድርጅቶችን and Medium Enterprises, SMEs) ወሳኝ መነሻ የሚያደርጋቸው ብዙ ምክንያት እ ሀገራዊ የሀብት ዐቅማችን ዝቅተኛ ነው። ያለንበት የቴክኖሎጂ

ሁኔታ አነስተኛ ነው: ብዙ የሠለጠነ የሰው ኃይል የለንም። በአንድ በኩል በሀገር ደረጃ ያለውን ከፍተኛ ፍ ማሟላት አለብን። በሌላ በኩል ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚፈልሰውን የሰው በኢንዱስትሪው ውስጥ ተገቢ ቦታና ዕድል እንዲያገኝ ማድረግ እና የሀገር ውስጥ ገበቶ መሸፈን ይገባናል።

እነዚህ ድርጅቶች የኢኮኖሚ የደም ሥሮች ናቸው። የሀገር ውስጥ ምርትንና ምርታ ያሳድጋሉ። የቴክኖሎጂ ፈጠራን ያበረታታሉ። የተለያዩ አካባቢዎችን ልማትን ያፋጥ የፈጠራ ማዕከላት፣ የሥራ ዕድል ፈጣሪዎችና የኢኮኖሚ ዕድገት ሞተሮች ሆነው ያገለግላሉ።

የሀገራችን አነስተኛና መካከለኛ የአምራች ድርጅቶች በኢንዱስትሪያዊነት እየተጫወቱ ያሉት ሚና አነስተኛ መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን በተለያዩ የኢንዱስ ዘርፎች ውስጥ ተሳትፏቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ለኢኮኖሚው ዕድገት አስተ እያደረጉ ነው። በተለይም የማዕድን ምርትን እያሳደጉ ናቸው። የግብርና ምርት የሆነ ግብአቶች ያቀርባሉ። ከዚህም አልፎ ኢንዱስትሪው የሀገር ውስጥ ግብአትን በ የተለያዩ ምርቶችን በማምረት፣ በሂደት ገቢ ንግድን የሚተካበትና የሀገር ውስጥ ገበያውን የሚቆጣጠርበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

የሀገራችን አነስተኛና መካከለኛ የአምራች ድርጅቶች በምግብ ማቀነባበሪያ፣ በጨርቃ ጨርቅ፣ በቆዳ ውጤቶች፣ በብረታ ብረትና በሌሎችም ዘርፎች ውስጥ በመሳተፍ ለሀገር ውስጥ ገበያ ምርቶችን ያቀርባሉ። ከዚህ በፊት ከውጪ ይገቡ

የነበሩትን የቢራ ብቅል፣ ልብ፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች (ምሰሶ፣ ገመድና ትራንስፎርመር) በሀገር ውስጥ ምርት የመተካት ሥራ ውጤት እያሳየ ይገኛል።

የሀገራችን አነስተኛና መካከለኛ የአምራች ድርጅቶች በሂደት ከፍተኛ ካፒታልና ስለጠነ የሰው ኃይል ወደሚጠይቁ የአምራች ንዑስ ዘርፎች እንዲሸጋገሩ እናደርጋለን። አስተኛና የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ጥራትና የገበያ ድርሻ እያሰፋን ዕውቀት መር ዩ ኢንዱስትሪዎችን እናስፋፋለን። በዚህ መሠረት ከውጭ የምናስገባቸውን የካፒታል ቶች በሀገር ውስጥ የመተካት ሂደት ይጠናከራል። የመጓጓዣ ዕቃዎችን፣ የግንባታ ኀብአቶችን በተለይም ብረታ ብረትንና ሌሎች ትላልቅ የኢንዱስትሪ

CS CamScanner

ምርቶችን በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ይደረጋል። በዚህም አማካኝነት የኢንዱስትሪ ዘረፉ በሀገራዊ ጥቅል ጥርት ቀዳሚ እንዲሆን ይሠራል።

ይሁንና እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ የራሱ ችግሮችም አሉበት። በሀገራችን ያለው የሠለጠነ ሰው ኃይል በቂ አይደለም። እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹ ከሚያገኙት ከለላ ጋር ተያይዞ ተወዳዳሪነታቸው እምብዛም ይሆናል። ይህ ደግሞ የፈጠራ ጉድለትንና ቆሞ ቀርነትን ያስከትላል። በዚህም የኢንዱስትሪያዊነት ጉዟችን እጅግ ቀርፋፋና ፈጠራ አልባ፣ ውጤታማነቱም እጅግ አናሳ ይሆናል። እንዲያ ከሆነ ደግሞ ልናሳካ ያሰብነው ሕልም በአጭር የመቅረት ተግዳሮት ይገጥመዋል።

በቀጣይ ለእነዚህ ድርጅቶች የሚደረጉ ድጋፎች ስንፍናን በማያስከትል መንገድ ተጠናክረው ይቀጥላሉ። የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች እየፈታን ነው። በኢንዱስትሪያዊነት ውስጥ የሚኖራቸው ሚና ጉልህ እንዲሆንም እየሠራን እንገኛለን።

የወጪ ንግድን ወይም የውጭ ሀገር ገበያን ማዕከል ያደረገ አካሄድ ብዙ ነገሮችን ይጠይቃል። በዓለም ገበያ ተወዳድሮ ማሸነፍን ይፈልጋል። የምርትና የአመራረት መመዘኛዎችን ማሟላትን ይጠይቃል። ከፍተኛ የምርት ጥራትና የአመራረት ውጤታማነትን የግድ ይላል። በመሆኑም፣ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውን ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች መጋበዝ ምርቶቻቸውን በሀገራችን እንዲያመርቱ ማበረታታት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ሀገራችንን ከሌሎች ሀገራት መርጠው የሚመጡበት የተለያዩ መወዳደሪያ ዐቅሞችን መለየትና ኩባንያዎቹን ተጠቃሚ ማድረግ ወሳኝ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ ሥራውን ለዘመናት ሲሠሩ የቆዩ፣ ከፍተኛ ልምድ ያላቸውና የተደራጁ ኩባንያዎችን በመጋበዝ የሚሠራ ነው። ስለዚህ የኩባንያዎቹ ልምድ ካለብዙ መንገራገጭ ፈጣን ዕድገትን የሚያጎናጽፍ ነው። በተለይም የሚመጡት ኩባንያዎች የሰው ኃይልን በስፋት የሚጠቀሙ ከሆነ ብዙ የሥራ ዕድል የሚፈጥርና ከፍተኛ የብዙ ውጤት የሚኖረው ይሆናል። ከቴክኖሎጂ ሽግግር አንጻርም ኩባንያው የሀገራችንን ስለሚቀጥር በዘርፉ ጥራት ያላቸው ተግባራዊ ሥልጠናዎችንና ልምዶችም እንዲያ ያስችላል። ዐቅሙ በሀገር ውስጥ ስለሚቀር በቀጣይ በሀገር ልጆች ለሚፈጠር አምራትን መንደርደሪያ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ግዙፍ ኩባንያዎች ባላቸው የትሥሥር የሚያመርቱት ምርት በከፍተኛ ደረጃ የሚሸጥ ነው። ስለዚህም የውጭ ምንዛሬን ለሀገር ውስጥ ከማብዛት አንጻር ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል።

በውጭ ገበያ የሚወዳደሩ አምራቾችን ከማፍራት አንጻር የክላስተር አደረጃጀትን በማጠናከር የአነስተኛና የመካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት እየሠራን እንገኛለን። የግል ዘርፉ ተሳትፎ ለማሳደግና ለወጪ ንግድ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በብዛት፣ በጥራትና በዓይኑ ለመሳብ የሀገር ውስጥ ግብአቶችን ለሚጠቀሙ አምራቾች ድጋፍ እያደረግን እንገኛለን ይህንን አስቻይ ሁኔታ በመጠቀምም ከባድ የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ፣ የኬሚካል የመድኃኒት እንዲሁም ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፈ የሚያስችሉ መደላድሎች እየተፈጠሩ ናቸው።

ኢትዮጵያ በእህል ሰብል፣ በጥራጥሬና ቅባት እህል ምርት እንዲሁም በእንስሳት ሁ ከአፍሪካ በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ሀገራት አንዷ ናት። እነዚህን የግብርና ምርቶች በ ዕቃነት በሚጠቀሙ አምራቾች ላይ መሥራት፣ በቀላሉ በዓለም አቀፍና በሀገር ውስ ከፍተኛ ፍላጎት ባላቸው የግብርና ኢንዱስትሪ ምርቶች ተወዳዳሪ ያደርጉናል። በተለ የሀገራችን ክፍሎች የተቀናጁ የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርኮችን እያለማን እንገኛለን። አሁ ወደ ሥራ ከገቡት እንደ ይርጋለም፣ ቡሬና ቡልቡላ ባሉ ፓርኮች የሚገኘውን ተሞ ማስፋት ይጠበቅብናል። ከእነዚህ በምናገኘው ተሞክሮ በተለያዩ የሀገራችን አነስ መካከለኛ ከተሞች፣ ብዛት ያላቸው ፓርኮች ይገነባሉ።

የውጭ ሀገር ኩባንያዎች ላይ የሚደገፍ አካሄድ ብዙ ተግዳሮቶች እንዳሉት ከታሪካች አይተናል። ነገሩ ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅና ሚዛኑን ጠብቆ እንዲጓዝ ለማድረግ ከፍተኘ ትኩረት የሚሻ ነው።

CamScanner

በመጀመሪያ እነዚህ ኩባንያዎች ለከፍተኛ ትርፍ የሚሮጡና ከሀገራችን ጋር የተለየ ቁርኝት የሌላቸው ናቸው። ስለዚህም ዘላቂነት ብዙም የሚያሳስባቸው አይደሉም። በመሆኑም የሀብት አጠቃቀማቸው በትርፋቸው ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

ስለ አካባቢያዊ ኪሣራ ብዙም አይጨነቅም። በምርት ሂደት የሚፈጠሩ የተለያዩ ብክለቶች አያሳስቧቸውም፤ " ብክለት ለእነርሱ የጋባዡ ሀገር ዕዳ ነው።

የሚጠቀሟቸው የተለያዩ ሀብቶች ዘላቂነትን ታሳቢ ያደረጉ አይደሉም። ርካሽና አዋጭመሆኑ ላይ ሳይሆን ሲነጥፍ ሀገር ለቀን እንወጣለን የሚል ከፍተኛ አሟጣጭነት የተጠናወተው ይጠይቃል። በመሰል አምራቾች ላይ ያለንን ተደጋፊነት በመቀነስ፤ ይልቁንም ሀገር በቀል ነው። በመሆኑም፣ ይህንን አመለካከታቸውን ተረድቶ ሚዛን ያልሳተ አካሄድ መንደፍ አምራቾች በዚህ እንዳይጎዱ መጠበቅ እና በተሻለ ሁኔታ እንዲያድጉ ማመቻቸትና ማገዝ ይገባናል። በዚህ መንገድ ከተጓዝን፣ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ መንገራገጮች፣ ወረርሽኞች ወይም የንግድ ጦርነቶች በሀገራችን ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ መቀነስ እንችላለን።

በአጠቃላይ በሀገራችን ፈጣን ኢንዱስትሪያዊነትን ለማሳካት ባለን ዕምቅ ዐቅሞች ላይ መመሥረት አዋጭ ነው። በተለይም ወጣት የሆነውንና በቀላሉ ዘመናዊነትን ሊላበስ የሚችለውን ሰፊ የሰው ኃይል አሠልጥኖ ማሠማራት የራሳችንን ብልጽግና በራሳችን እጅ ለማምጣት ወሳኝ ነው። እንዲሁም ታዳሽ ሀብትን ጨምሮ በተለያዩ ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብቶቻችን ላይ መመሥረት የሀገሩን በሬ በሀገሩ ሰርዶ ይሆንልናል። እነዚህን ሁለት ነገሮች ይዘን ደግሞ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግ አለብን።

ሆኖም የኢንዱስትሪ ተስተካካይነትን በተደመረ ጥረት ለማሳካት ከዚህ ትይዩ መሠራት ያለባቸው ነገሮችም አሉ። ቀጣይነት ያለው የግዙፍ ኢንዱስትሪ ደረጃችንን ማሻሻል ይገባናል። ለዚህ ደግሞ ቁልፍ ዘመናዊ ኢንዱስትሪዎች ማለትም ውስብስብ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙና ውስብስብ ምርቶችን የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት አለባቸው። በተስፋፉት ኢንዱስትሪዎች የአምራችነት ዐቅማችን ማደግ ይኖርበታል። ይህንን ተከትሎ ደረጃ በደረጃ ከቀላል ምርቶች ሀገራዊ ብልጽግናን ወደሚያረጋግጡ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ምርቶች መሸጋገር አለብን።

ለዚህም ኢትዮጵያ ስታስመዘግብ የቆየችው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የነበረበትን መሠረታዊ | ውጤት የማያመጣ መሆኑንም ተረድተናል። ዕድገቱን ለማስቀጠልና የኢኮኖሚ ስብራቱን | መዋቅራዊ ችግር በአግባቡ ተንትነናል። የመንግሥት ኢንቨስትመንት ብቻውን ዘላቂ | መጠገን የግል አምራች ዘርፍን ማሳደግ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል።

የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የሚገባውን ሚና እንዲጫወትና ዋና አንቀሳቃሽ እንዲሆን ነ በተመረጡ ዘርፎች ላይ ደግሞ የቀዳሚ ኢንቨስተርነት ሚናውን ይወጣል። በዚህ ጊዜ ነው። መንግሥት ደግሞ እመርታዊ ባሕርይ ተላብሶ በአስቻይነት ይሳተፋል። የኢኮኖሚያችን ዕድገት ትሩፋት ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለመጪው ትውልድም የሚሉ እንዲሆን ይደረጋል። ከዚህ አንጻር የሀገራችንን ዕምቅ ሀብቶች በተገቢው አግባብ ለመጠቀ ጥረቶች እየተደረጉ ነው። ይህም የመደመር መንግሥት ለዘላቂ ኢንዱስትሪያዊነት የሰጠውን ትኩረት ያሳያል።

## 7.4. የማይበገር አምራች ኢንዱስትሪ

በዚህ እጅግ ተለዋዋጭና ውስብስብ ዓለም አቀፋዊ ዐውድ ውስጥ፣ የማይበገር አምራ ኢንዱስትሪ መገንባት ማለት፣ በማያቋርጥ ለውጥና ሊተነበይ በማይችል ሁኔታ ው ኢተገማች ነው። ከጥሬ ዕቃ አቅርቦት ሠንሰለት አንጻርም ይሁን ከደንበኛው የተሰጠ . መላመድና ማደግ የሚችል የአምራችነት ሥርዓት ለመገንባት መቻል ማለት ነው። ሁኔታ ፍላጎት ወይም የፍላጎት ማጣት አንጻር በከፍተኛ ደረጃ ተለዋዋጭነት ይበዛበታል። በዚ ሁኔታ ውስጥ ጸንቶ መቆም፣ ሳይታወክ

CamScanner

ማምረት፣ ችግሮቹን ተቋቁሞ መቀጠል የሚ የአምራች ኢንዱስትሪ መገንባት ማለት ነው። አልፎም ወረርሽኝን እና ጦርነትን ለመሰሉ ከባድ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ሳይበገር ለመወጣት መቻል ነው።

የማይበገር ኢንዱስትሪ የመገንባት ጉዳይ ብዙ ነገሮችን የሚመለከት ጉዳይ ነው። ያልተጠ ሁኔታዎችን በፍጥነት ለማስተካከል ያለ ችሎታ የመጀመሪያው ነው። ለተላማጅነት ም የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ሁለተኛው ነው። ምርትንና የምርት ሂደቶችን በ ተለዋዋጭ በሆነ መልኩ መገንባት ሌላው ነው። ይሄንን ታሳቢ ያደረገ የሚመራ የሚተነብይና በፍጥነት መፍጠርና ዕድሎችን ተጠቅሞ ነገሮችን ማስተካከል የሚችል የሰው ኃይል ባለቤት መሆን ደግሞ አንዱ ዋና ነገር ነው። የማይበገር የአምራች ኢንዱስ ሊደግፈው የሚችል ጠንካራ መሠረተ ልማት ይፈልጋል። በቀላሉ ተጣጣፊ የሆነ ፖሊ ይሻል። ያልተቆራረጠ የኃይል አቅርቦት ያስፈልገዋል።

የዲጂታል አገልግሎቶች መረበሽ የለባቸውም። የውኃ፣ የመጓጓዣና የሎጅስቲክስ እንዲሁም መሰል መሠረተ ልማቶች በሚገባና በዘላቂነት እንዲቀርቡለት የሚጠብቅ ነው። በመሆኑም ጠንካራና ዘላቂ መሠረተ ልማት ግንባታ አይበገሬ የአምራች ኢንዱስትሪ ባለቤት ለመሆን ይህ ወረት መሆኑን ዐውቀን እየሠራንበት ነው።

ለአይበገሬ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ሌላው ወሳኝ ነገር የጥሬ ዕቃ ግብአቱ ሳይቆራረጥ ለነገል መቻሉ ነው። ለዚህም ከውጭ ከማስገባት ይልቅ በሀገር ውስጥ ማምረትና ሊፈጠር ከሚችል መንገራገጭ ያድናል። በሀገር ውስጥ መቅረብ ለማይቻሉ ጥሬ ዕቃዎች መረብ እጅግ ችግር ፈቺ ነው። በዓለም አቀፍ የአቅርቦት ሠንሰለት መዛባት ምክንያት አንድ ምንጭ ላይ ከመንጠልጠል ይልቅ ብዙ አማራጮችን መያዝ፣ እንዲሁም ቅርብ ምንጮችን መለየትና መጠቀም ወሳኝ ነው።

አይበገሬ የአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ችግሮችን አስቀድሞ የመተንበይና የመዘጋጀትን ምን ይጠይቃል። የአምራች ኢንዱስትሪው በምርምርና ልማት የሚመራ፣ ከፍተኛ | መፍጠር ዐቅም የታጠቀ፣ ፈጠራዎቹንም በፍጥነት ወደ ተግባር

መቀየር የሚችል መሆን 1 አለበት። ምርምርንና ፈጠራን መሠረት አድርጎ የተለያዩ የግብአት ዓይነቶችን የማመንጨት ሎታ ይጠይቃል። የአመራረት ስልቶችን፣ ነባር ምርቶችንና አዳዲስ የምርት ቅንጅቶችን ጨፍለቅ ይፈልጋል። አዳዲስ ገበያዎችን ማግኘትና መፍጠር የግድ ይላል። አዳዲስ የገበያ መቅረቢያ ስልቶችን ይሻል። እነዚህ ነገሮች ኢንዱስትሪው

ከሚገጥመው የተለዋዋጭ ዓለም -ጽዕኖ ፋታ እንዲያገኝ ያግዛሉ። አዳዲስ ዕድሎችን ተጠቅሞ ወደ ተሻለ ደረጃ እንዲያድግ መንገድ ይከፍታሉ።

“ድር ቢያብር፡ አንበሳ ያሥር” እንዲሉ፣ አይበገሬነት አንድ አካል ለብቻው የሚወጣው ጉዳይ አይደለም። ከብዙዎች ጋር ተደምረን፤ የጋራ ጉዳይ መሆኑን ተግባብተን፤ በመደጋገፍና መተባበር የምንወጣው ጉዳይ ነው። ሀገራትንና ተቋማትን ጨምሮ ከተለያዩ አካላት ጋር ስትራቴጂያዊ ጥምረት መፍጠር አለብን። በኢንዱስትሪው የሚኖሩ ተግዳሮቶችን በጋራ መጋፈጥ ይጠይቀናል። አንዱ ለሌላው ከለላ መሆን የአይበገሬነት ዋናው መገለጫው ነው።

በአፍሪካም ይሁን በሌሎች አኅራባች ሀገራት የተለያዩ የንግድ ቀጣናዎችን ለማቋቋም መሥራት ተገቢ ነው። የቀጣናው ሀገራት የአምራች ኢንዱስትሪን በተለየ መልኩ ለመጋራት፣ ነጥሬ ዕቃ አቅርቦት ሠንሰለትን ለመገንባት፣ የጋራ ምርምርና ልማት ለማከናወን ማበረታታትና ለመደገፍ እንድንችል የጋራ ርዕይና የጋራ ስልት ያስፈልገናል። ገበያን ተግባብተን መሥራት አለብን። ከዚህም ባለፈ መሠረተ ልማቶችን መጋራት ወይም ሌሎች መሰል ጉዳዮችን የጋራ አድርጎ መምራት ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ መጪው የኢንዱስትሪ ዘመን በከፍተኛ ቴክኖሎጂ የታገዘ ዘመን ብክነትን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀነስ ውጤታማነትን ገንዘቡ ማድረግ ይፈልጋል። በእንዲህ ዓይነቱ ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ውስጥ በዘላቂነት መወዳደር የምትችልበት ብዙ ዕምቅ ዐቅሞች አሏት። ነገር ግን ያለንበት የዝግጅት ሁኔታ ዝቅተኛ ነው።

CamScanner

የመደመር መንግሥት ይህንን ሁኔታ ለመቀልበስ እየታገለ ነው። ሀገራችን ተወዳዳሪ ከመውጣትም ባሻገር፣ የማይበገር አምራች ኢንዱስትሪ ለመገንባት የሚያስችላትን ስትራ ቀይሰናል። ለተግባራዊነቱም እየተንቀሳቀስን እንገኛለን። ከዚህ በፊት ያለፉንን የኢንዱስት አብዮቶች ቁጭት የምንወጣበት ሌላ ዕድል ከፊታችን ተዘርግቷል ብለን እናምናለን።ከ ዕድል ተጠቅመን ሀገራችንን ካደጉት ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ የመጀመሪያው ምዕራፍ የዚህ ትውልድ ዕጣ ሆኗል፡

የመጪውን ኢንዱስትሪ ዘመናዊነትና ያለንበትን ሁኔታ ገምግመናል። የሌሎች 1 አካሄድ መርምረናል። ከዚያም ይበጀናል ያልነውን የፈጠራና የፍጥነት መንገድ ይዘን ለተግባራዊነቱ የሁላችንንም የተለየ ጥረትና ልፋት ይጠይቃል። ዘላቂና የማይ አምራች ኢንዱስትሪ የመገንባት ጉዳይ የዚህ ትውልድ ብቻ የቤት ሥራ አይደለም። ቀ ትውልዶችም ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ላይ አተኩረው፣ በፈጠራና በፍጥነት የሚያጠነጥን የተለየ ጥረትንና ትጋትን እንዲያደርጉ የሚጠይቅ፣ የማያቋርጥ ጉዞ ነው።

CamScanner

# ምዕራፍ ስምንት

## 8. የዘመነ ከተማ

### 8.1. የከተማ መልኮችና ውጤታማ መስተጋብር

የሰው ልጅ አሁን በደረሰበት የሥልጣኔ ደረጃ ከተሞች እጅግ ዘምነዋል። ለኑሮ፣ ለምርታማነትና ዕምቅ ዐቅማቸውን ለመጠቀም በሚያስችላቸው መልኩ ተደራጅተዋል። በጋራ ሠልጥኖ ለመኖር ሥርዓትና ኃይል የተደራጀባቸው ተመራጭና ተቀዳሚ ቦታዎች ሆነዋል። ከተሜነት የሰው ልጅ የብልጽግና መዳረሻ ነው ብንል ገሐዳዊውን ዓለም ምስክራችን አድርገን ነው። ከተሞች ለሰው ልጅ አካላዊ፣ አእምሯዊና መንፈሳዊ ጤንነቱ ተጠብቆ አምራችነቱ እንዲያድግ ማኅበራዊ መስተጋብሩን ይፈጥሩለታል።

ድካሙን ቀንሶ ትርፍ ለማምረት የሚያስችሉ የግብአትና የክሂሎት አቅርቦትና ተደጋጋፊነት በከተሞች ይገኛል። እነዚህ ሁሉ የሰውን ልጅ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ መሻቶች ለማሳካት ያስችሉታል። እንዲሁም በተፈጥሮ የተሰጠውን የመመራመርና የመጠየቅ ስጦታ ተጠቅሞ አዳዲስ ፈጠራዎችንና ሐሳቦችን ለማፍለቅ ከተሞች አስቻይ ዐቅም ሆነውታል።

ከተማ ብዝኃ መልክ አለው። ከተማ ማኅበረሰባዊ፣ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እርስ በእርስ ያላቸውን መስተጋብር የሚያቅፍ ነው። እንዲሁም በክልላዊና በዓለም አቀፋዊ ልውጥውጤነቶች (dynamics) ላይ የራሱን ተጽዕኖ የማሳደር ዐቅም አለው። ከተማ የሰው ልጅ ዘመናዊነት መነሻም፤ መገለጫም ነው።

ከማኅበራዊ ዕይታ፥ አንጻር ከተማ ወይም ከተሜነት ሥርዓት ያለው ኅብራዊ አንድነት ነው። ከተለያየ ባህል በተሰባሰቡ ማኅበረሰቦች የበለጸገ የባህል መስተጋብርና ማኅበራዊ ሀብቶች ይጎለብቱበታል። ሁሉም ማኅበረሰብ የራሱን ባህል ይዞ በከተሜነት ባህል አጣጥሞት ይኖራል። ከተሞች የቅይጥ ባህል መፍጠሪያ ማዕከላት ናቸው። ከተሞች ከገጠር ይልቅ

የተለያዩ ማኅበረሰቦች ከሀገር ውስጥና ከውጭ መጥተው የሚኖሩባቸው በመሆናቸው | ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን የመፍጠር ዕድላቸው ሰፊ ነው።

ከተማ ግለሰቦች በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ እንዲሳተፉና አስፈላጊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ያስችላል። የጋራ ልምዶችን ይቀስሙበታል፤ ይተገብሩበታል። የከተማ ማኅበራዊ መዋቅር ከነዋሪዎቹ የተለያየ ባህላዊ ዳራ፣ እምነትና የአኗኗር ዘይቤ ተሰናኝቶ የተሸመነ ነው። ይህም ትብብርን፣ ፈጠራንና የጋራ መግባባትን የሚያበረታታ ተለማጭ ዐውድን ይፈጥራል። ከዚህም በላይ ከተሞች የነዋሪዎቻቸውን ዕሴቶችና ፍላጎቶች የሚያንፀባርቁ የማኅበራዊና የባህላዊ እንቅስቃሴዎች መናኸሪያ

ናቸው::

በከተማ የሚኖር ሕዝብ በመኖሪያ፣ በሥራ ቦታና በመዝናኛ አካባቢዎች ሰፋ ያለና ጊዜ አለው። ይህ ግንኙነቱ በልዩነቶቹ ተስማምቶና ተቻችሎ ሕይወቱን ኅብረቱንና መደጋገፉን ይበልጥ ይፈልገዋል። ችግሮቹን ለመፍታትና ሥራውን ለ ያደርገዋል። ከልዩነቶቹ በበለጠ የማደግ መሻቱን ለማሳካትና ፈተናዎቹን በሚያደርገው ጥረት፣ ትሥሥር፣ ዝምድናና የሐሳብ ተዋሥዖ ይፈጥራል። በዚህ የተነሳ ከነዋሪዎቹ ድምር በላይ የሆነ የከተሜነት ባህልን ይፈጥራል።

የሰው ልጅ በሥርዓት የተዋቀረ ምቹ ቦታን ከተማ አድርጎ ለመቆርቆሩ በርካታ ምክንያቶች ነበሩ። የመጀመሪያው የሰው ልጅ በሕይወት የመኖር ዋስትናውን በህብረቱ ለማረጋገጥ መፈለጉ ነው። ሌላው ከተማ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን በቅርበትና

CamScanner

መንገድ ለማሟላት የሚያስችል በመሆኑ ነው። ከዚህ ባሻገር የማወቅ ፍላጎቱን ለማ ወደ መንፈሳዊ ልዕልና ለመድረስ ከተማ አስቻይ ነገሮችን ስለሚያመቻችለት ነው : የሰው ልጅ ልዩነቶቹን አቻችሎ በጋራ ፍላጎትና በጋራ ጥቅሞች የተነሣ አዲስ የጋራ እሴትና ማንነት እየገነባ ሕይወቱን በበለጠ ምቹ ለማድረግ የሚተጋበት ቦታ ነው።

በአጠቃላይ ከተማ የሰው ልጅ ከብቸኝነት ጉድለት የሚላቀቅበት ሥፍራ ነው:: ጉድ። በኅብረት ይሞላበታል። መሻቱን እውን ያደርግበታል፤ በቀጣይ ጥረት ሐሳባዊ ከተማ ለመገንባት ይተጋበታል። የከተሞች መፈጠርና ዕድገት በሥርዓታት ውስጥ የ ሂደትና ውጤት ዋነኛ ማሳያ ነው። የከተሞች ዕድገት ከብቸኝነት ጉድለት ወደ ክሥተ የሚደረገው የመደመር መስተጋብር አብነት ነው።

ከተሞች የሚፈጠሩት ከብዙ ግለሰባዊና ተናጠላዊ አካላት ውስብስብ መስ ነው። እነዚህም የሰዎች ግንኙነት፣ የንግድ ልውውጦች፣ የመሠረተ ልማትና የ ግንባታዎችን ያካትታል። የመስተጋብሩ አካላት በአንድ አካል ሙሉ በሙሉ ወይም የታቀዱ አይደሉም። ከተሞች ከቀላል የአካባቢ መስተጋብር፣ ከተለያዩ አወል ምግባሮች፣ ባሕርያትና አዝማሚያዎች ይጀምራሉ። በሂደትም ከጊዜ ወደ ጊዜ ባልታ ሁኔታ ወደ ውስብስብ ሥርዓት ራሳቸውን ያደራጃሉ። ለምሳሌ በከተሞች

በ. አሠፋፈርና ሠፈሮች፣ ገበያዎች፣ የንግድ መንደሮች አፈጣጠርና ዕድገት የግለሰቦች ምርጫና የጋራ ተግባር ውጤት መሆኑን መመልከት ይቻላል።

እንደ ኮሪደር ልማት ዓይነት ውሱን ለውጦች ተያያዥነት ያለው ሠንሰለታዊና ግዙፍ ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ። ከተሞች በአግባቡ ከተመሩ ቀጣይነት ላለው ለውጥ ለምሳሌ ለውጫዊና ውስጣዊ ዕድልና ሥጋቶች፣ ለኢኮኖሚ ለውጥና ለቴክኖሎጂ ዕድገት ወቅታዊ ምላሽ እየሰጡና በሂደቱ እየተለወጡ የማያቋርጥ የዕድገት ምሕዋር ውስጥ ይቆያሉ።

በአካባቢያዊ ዕይታ፥ ከተማ የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ከተፈጥሮ ሥርዓቶች ጋር የሚገናኝበትን ውስብስብ ሥነ ምኅዳር ይፈጥራል። ከተሞች በአካባቢያቸው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በሌላም በኩል ከአካባቢያቸው ተጽዕኖ ይደርስባቸዋል።

ስለሆነም በከተሞች ልማትና በአካባቢ ጥበቃ (ከዘላቂነት አኳያ) መካከል ሚዛን መጠበቅ የግድ ይላቸዋል።

በመሆኑም ከተሞች የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች ለመቋቋም የአረንጓዴ መሠረተ ልማትና ቀጣይነትን ታሳቢ ያደረገ ትግበራ ያስፈልጋቸዋል። ይህም የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ ብክለት ዘላቂነትና አረንጓዴነት የከተሞች ግንባታ ሚዛን መጠበቂያ መርሖች እንዲሆኑ አስገድዷል። ውጤታማ የከተማ ዕቅድ የአካባቢ ብክለትና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቀነስ፣ የኃይል ቆጣቢነትን ለመፍጠር፣ የሀብት ጥበቃንና ለሁሉም ነዋሪዎች ጤናማ የመኖሪያ አካባቢዎችን ለማመቻቸት ይተልማል።

በኢኮኖሚ ዕይታ፥ ከተማ የላቀ የዕድገትና የፈጠራ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው። ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪና ለሥራ ፈጣሪነት ማዕከል ይሆናል። የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን የሚያስገኙና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያሣልጡ አገልግሎቶችን ያቀርባል፡ ከተሞች ኢንቨስትመንቶችን፣ ተሰጥዖዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ይስባሉ። በንግድ ተዋንያን መካከል ውድድርንና ትብብርን የሚያበረታቱ ተወዳዳሪና አማራጭ ገበያዎችን ይፈጥራሉ። በተጨማሪም ከተሞች ነዋሪዎች ሁሉ ከኢኮኖሚያዊ ዕድሎች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አካታች ሥርዓት ለመፍጠር ያግዛሉ። እኩልነት እንዲሰፍንና የረጅም ጊዜ ብልጽግናን ያለመ ዘላቂ ልማት እንዲኖር መድረክ ይሆናሉ።

የሰው ልጅ በየምዕራፉ የገጠሙትን ፈተናዎች እየፈታ፣ በርካታ የዕድገት ምዕራፎችን አልፎ፤ በጉዞው የተሻሉ ከተሞችን መሥርቷል። ዛሬ ደግሞ የነገን ምቹ ከተሞች በመሥራት ሂደት ላይ ይገኛል። እንደ የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጥናት ዘገባ፣ በአዲሱ የዲጂታል ዘመን ከተሞች የአብዛኛው ሕዝብ መኖሪያዎች ሆነዋል። ከሁለትና ሦስት ዐሠርት ዓመታት በኋላ የከተማ ነዋሪዎች ብዛት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያድግ ተተንብዮአል።

CamScanner

በዚሁ ጊዜ ከገጠር ወደ ከተማ ከሚፈልሰው ሕዝብ ውስጥ የእስያና የአፍሪካ ሀገራት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ"። ከዚህ የምንረዳው በቀጣይ የሀገራት ከፍተኛ የሙዓለ መፍሰሻና የሀብት መገኛ ከተሞች እንደሚሆኑ ነው።

ለሀገራት ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር መፋጠን ዋና መናኸሪያው ከተሜነት ነው ሀገራት በተለይም አዳጊ ሀገራት የነገ ዕጣ ፋንታቸው በከተሞች ውስጥ ነው። ከተማ ለሀገራዊ ጥቅል ምርት ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው። በአዳጊ ሀገራትም ቢሆን ከተማ ንዋይ ሀገራዊ ጥቅል ምርት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው።

የአሁኑና የመጪው ዘመን የሀብት መገኛ ከተሞች ናቸው። ከተሞችን በፍጥነት ማሳያ ከተሞች ፈጠራን በማጎልበት፣ ተሰጥዖዎችን በመሳብ፣ የተለያየ የንግድ ሥነ ምኅዳር ትልቅ ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሚያደርግ

ዕድሎትን ያመጣ በመደገፍና ለዘላቂ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑትን መሠረተ ልማትና አስተዳደር በማቅረብ . ለኢኮኖሚ ሽግግር ሞተር ይሆናሉ። ከተሞችን የኢኮኖሚ ሽግግር ማዕከል አድርጎ ሙዓ ንዋይን ማፍሰስ የብልጽግናን በሮች ይከፍታል። መክፈትም ብቻ ሳይሆን፣ አካታችና የማይበገር ዕድገት በማረጋገጥ ከዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ሥርዓት ጋር ያስተሣሥራል።

በፖለቲካ ዕይታ፥ ከተሞች በፖለቲካዊ መስተጋብር ውስጥ ወሳኝ ሚና በመጫወት፣ የፖለቲካ ሐሳቦችን በመቅረጽ፣ የሕዝብን ተሳትፎ በማጎልበትና ዴሞክራሲያዊ ዕሴቶችን በማሥ የላቀ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በተለይም የፖለቲካ ዕሳቤዎችና አማራጮች በከተማ ው በትምህርት ተቋማት፣ በፋብሪካዎች፣ በተለያዩ ማኅበራዊ መድረኮች፣ በመገናኛዎች በሌሎች የማኅበረሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በፍጥነት እንዲሠራጩ ያደርጋሉ። በዚ የተነሣም፣ ከተሞች ዜጎች በመንግሥት ሥርዓት ውስጥ የሚኖራቸው ሚና ምን መሆ እንዳለበት በሚደረጉ ውይይቶች ከፍተኛ ተጽዕኖ አላቸው።

የዓለም ታሪክ የሚያሳየውም፣ብዙ የፖለቲካ ለውጦችና አብዮቶች ከከተሞች ውስጥ መነሣታቸውን ነው። በታሪክ ሁሉም ዘመናት፣ ከተሞች የፖለቲካ እንቅስቃሴ የተነሣባቸው ( ከላት እንደሆኑ ታይቷል። ለምሳሌ አቴና በቅድመ ዘመናዊ ዴሞክራሲ የፖለቲካ ሐሳብና አብዮት በፓሪስ ከተማ የሕዝብ ሥልጣንንና የዴሞክራሲ ጥያቄን በማንገብ የተጀመረው አስተሳሰብ ከመቅረጽ አንጻር ወሳኝ ሚና ከነበራቸው ከተሞች አንዷ ናት። በፈረንሳይ / አዮት በሌሎች ሀገራትም

ተስፋፍቷል። በተመሳሳይ በአፍሪካም ዋና ከተሞች የፖለቲካ " ውጥን ያስከተሉ የፖለቲካ ሐሳቦች የመነጩባቸው ናቸው።

ዘመናዊት ኢትዮጵያ ከመመሥረቷ በፊትም የተለያዩ ከተሞች የሐ፣ አክሱም፣ ላሊበላ፣ ወለላህ፣ ኖራ፣ ሐርላ፣ ደብረ ብርሃን፣ ሐረር፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ እና የመሳሰሉት የፖለቲካ ማዕከሎች ነበሩ። በዘመናዊት ኢትዮጵያም አዲስ አበባ በሀገራችን ለተከሠቱ የፖለቲካ ለውጦች የአንበሳውን ድርሻ ስትወጣ ቆይታለች።

ከተማዎች የፖለቲካ ሐሳቦችን የማዘመን፣ የሕዝብ ፍላጎት በውይይት እንዲዳብርና ነጥሮ | እንዲወጣ ለማድረግና የፖለቲካ ሐሳብ ገዢ ሆኖ እንዲወጣ ወሳኝ አስተዋጽዖ አላቸው። ስለዚህም፣ በፖለቲካ ለውጥ ማስነሣትና የዴሞክራሲ ባህሎችንና አሠራሮችን ማበረታታት ሚፈልጉ ሀገሮች፣ ከተማዎችን እንደ ዋነኛ የፖለቲካና የጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል ማድረግ ወሳኝ ይሆናል፡

በአጠቃላይ ከተማ ኅብረተሰባዊ፣ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ያቀናጀ ውስብስብ አካል ነው ማለት ይቻላል። እያንዳንዱ ዕይታም በከተሞች ልማትና ዘላቂነት ላይ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። በማኅበረሰብ ዕይታ ውስጥ ከተሞች የተለያዩ ማኅበረሰቦች ኅብራዊ አንድነት የሚፈጥሩበት ነው። የበለጸጉ ባህላዊ መስተጋብሮችንና ማኅበራዊ ትሥሥሮችን የሚያጎለብቱባቸው ማዕከሎች ናቸው። በአካባቢያዊ ዕይታ ዘላቂነትን፣ ወጥነትንና ለትውልድ መትረፍን ታሳቢ አድርገው መገንባት የሚኖርባቸው ውስብስብ ሥነ ምኅዳሮች ናቸው።

CamScanner

በኢኮኖሚ ዕይታ ደግሞ ከተሞች ለሥራና ለሥራ ፈጣሪነት ሰፊ ዕድሎችን ይሰጣሉ። [ ከፖለቲካ አንጻር ለዘመነ ፖለቲካና ለዳበረ ዴሞክራሲ ውጥን ስኬት ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ሁሉን አቀፍነትንና ፍትሐዊ ዕድገትን ለማምጣትም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እነዚህ | ገጽታዎች አንድ ላይ ሆነው የከተሞችን ገጾች ያሳያሉ። በከተሞች ውስጥ አንዱ በአንዱ ይደገፋል፡፡ አንዱ በሌላው ሙሉ ይሆናል፡፡

8.2. ከየሓ እስከ ሳተላይት ከተማ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የከተሞች ታሪክ ከደኣማት (ዐኛው መክዘ) ቀደም ይላል። የደአማ ዋና ከተማ የሓ ነበረ። በቅርቡ

የተደረጉ የአርኬዎሎጂ ጥናቶች በትግራይ ሽሬ አካባቢ በ አድራሻ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2ኛው መክዘ የተሠራ ከተማ አግኝተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ለከተሞች መመሥረት ምክንያት የሆኑ ሦስት ነገሮች ነበሩ። የመጀመሪያው የፖለቲካ ማዕከል መሆን ነው። ነገሥታቱ፣ ሞቲዎቹ፣ ሡልጣኖቹና ሌሎችም ገዥዎ የሚገዙትን አካባቢ ለማስተዳደር ቤተ መንግሥታቸውን የሚተክሉበት ቦታ ይፈልጋሉ።

በአካባቢው ሌሎች መሳፍንት፣ ወታደራዊ አዛዦች፣ ነጋዴዎች፣ ሠራተኞች፣ የቤተ እምነት አገልጋዮች አብረው ይሠፍራሉ፡፡ እነዚህ ቦታዎች በኋላ ታላላቅ ከተሞች ይሆናሉ።

ሁለተኛው ምክንያት ወታደራዊ ካምፖች ናቸው። አካባቢዎችን ለመጠበቅ የሚሠማ ወታደሮች የሚሠፍሩባቸው ቦታዎች ቀስ በቀስ ወደ ከተማነት ያድጋሉ። የወታደ ቤተሰቦች፣ ለወታደሮቹ ሽቀጣ ሸቀጥ የሚያመጡ ነጋዴዎች፣ የቤተሰቦቹ ሠራተኞች፣ የቤተ እምነት አገልጋዮች በካምፑ ዙሪያ ይሠፍራሉ። ሦስተኛዎቹ በንግድ አመቺነት ነው። ለጥንቱ የሂራራ ንግድም ሆነ ለኋለኛው የባቡርና የመኪና የንግድ እንቅስቃሴ ምቹ የሆኑ ከተዋ በመሥመሮቹ ዳርቻ ይመሠረታሉ። እነዚህ ቦታዎች በዋናነት የታወቀ ገበያ ይኖራቸዋዕ ገበያዎቹ የሚውሉበት ቀን ይታወቃል። አንዳንዶቹ እንዲያውም በእነዚህ የገበያ ቀናት የተሰየሙ ከተሞች ሆነው ቀርተዋል።

የኢትዮጵያ የጥንት ከተሞችን እንዲቀዛቀዙና በኋላም እንዲጠፉ ያደረጓቸው ብ ምክንያቶች አሉ፡፡ መጀመሪያው የቆረቆሯቸው መሪዎች ሲወርዱ ወይም ሲሞቱ ተተኪው መሪ ሌላ ከተማ ይቆረቁርና ነባሩን ይተወዋል፡፡ ጎንደር ከተማ እስክትሆን ድረስ በአካባቢው ከሰባት በላይ ዋና ከተሞች እየተቆረቆሩ ተትተዋል። የሮሐ ከተማ ብቅ በማለቷ አክሱም የጥንት የመንግሥትና የኢኮኖሚ ማዕከልነቷን አጥታለች። በኋላም መንደር ወደመሆን ወርዳ ነበረ።

ሁለተኛው በአካባቢው በሚፈጠር የፖለቲካ ፈተና ምክንያት የመንግሥት መቀመጫ ሲዛወር ነው። የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደርና የአንኮበር ከተሞች ከተማነት የተቀዛቀዘው በዚህ ምክንያት ነበር። ሦስተኛው ጦርነትና የተፈጥሮ አደጋ ነው። በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች በጦርነትና በተፈጥሮ አደጋ የተነሣ ብዙ ከተሞች ከመረሳትም አልፈው ፈርሰው ከምድር በታች ሆነዋል። እነ የሓ፣ ሐርላ፣ የይፋት ሡልጣኔት ከተማ ኖራ፣ በዚህ መልኩ ጠፍተዋል።

በ19ነኛውና 20ኛው መክዘ ዘመናዊ የመንግሥት መዋቅር በየአካባቢዎች ሲጀመር፣ የኢትዮጵያ ከተሞች አመሠራረት አዲስ መልክ ያዘ። የየአካባቢው መዋቅሮች የየራሳቸው የፖለቲካ ማዕከላት የሆኑ ከተሞችን ቆረቆሩ፡፡ መጀመሪያ የግዛት፣ በኋላም የጠቅላይ ግዛት፣ አውራጃና የወረዳ ከተሞች ተፈጠሩ። በኋላም የክፍለ ሀገር፣ የዞንና የክልል አዳዲስ ከተሞች ተመሥርተዋል።

CamScanner

ከመሠረተ ልማት መስፋፋት አንጻር የኢትዮ ጂቡቲ የባቡር መሥመር መዘርጋት በመሥመሩ ' ጥግ አያሌ ከተሞች

እንዲቆረቆሩ አደረገ። ከአዲስ አበባ እስከ ጂቡቲ ድረስ፣ ባቡሩ 20 የጣቢያዎች ነበሩት። እነዚህ ጣቢያዎች ወደ ከተማነት አድገዋል። በተጨማሪም በአውራ ጎዳናዎች መስፋፋት የመንገድ ዳር የንግድ ከተሞች እንዲበራከቱ አደረገ።

ኢትዮጵያ በዓለም ቀደምት ከሚባሉት ሀገሮች ጋር ጥንተ ታሪክ የምትጋራ ሀገር ብትሆንም፣ በከተሞች ዕድገትና በከተማ በነዋሪዎች ቁጥር በቅርብ ከተመሠረቱ ሀገራት አንጻር እንኳን በዝቅተኛ ተርታ የምትገኝ ናት። የዚህ ዋናው ምክንያት እያፈረሱ የመሥራት አባዜያችን ነው። ከተሞቻችንን በዘላቂ ስትራቴጂ አለመምራታችን ሌላኛው ከፍተኛ ተጽዕኖ ካሳደሩ ጉዳዮች አንዱ ነው።

በጥቅሉ ለከተሞች ዕድገት መቀንጨር፣ ምቹ ያልሆነ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚያችን ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። ግብርናው አለመዘመን ለገበያ የሚሆን ትርፍ አምርቶ በንግድ ልውውጥ የከተሞች መስፋፋት እንዳይሣለጥ አድርጓል። ለዘመናት ተግባራዊ የተደረጉ የመሬት ሥሪቶች ከተሜነትና ከተማ ሥሉጥ በሆነ አግባብ እንዳይከናወኑ ፖለቲካዊ ገደብ ሆነዋል። እንዲሁም ለከተማ መመሥረት ምክንያት የሆኑትን የእጅ ሞያንና ንግድን የሚያበረታታ ማኅበረሰብ የለንም። በዚህም የተነሣ የጥበባተ ዕድ ምርትን በማዘመን ለከተሞች ዕድገት የሚገባውን ሚና እንዳይወጣ አድርጓል። ይህም የቴክኖሎጂ ዕድገታችንን ገትቷል። የንግድ ሥርዓቱም ባለመዘመኑ የንግድ ተዋንያኑ የዕለታቸውን ብቻ በማሰብ ሥርዓት ያለው ገበያን አልፈጠሩም።

ለከተሞች ዕድገት መቀንጨር ከፖለቲካዊና ማኅበራዊ ስብራታችን ባልተናነ ልማት መስፋፋት የተጀመረው ጣልያን በኢትዮጵያ በቆየባቸው ዓመታት ነው አውሮፓዊ የሆነ የከተማሥርዓትን አምጥቷል። የከተማ ዕቅድ፣መሠረተ ልማት እና እንቅስቃሴን ተግብሯል። ይሄንን በመከተል በሀገራችን በተለያዩ መንግሥታት መሠረተ ልማት ለማስፋፋት ጥረቶች

ተደርገዋል። ይህ ግን ከተሞቻችን ለነዋሪዎቻቸው . የተጠራቀመ የመሠረተ ልማት ጥያቄ ያለባቸው ናቸው። ከዚህ ባሻገር ያላቸው የኑሮ ሁኔታን በሚያረጋግጥና የከተሞችን ዕድገት በሚደግፍ አግባብ ባለመሆኑ ከተኝ ልማት የቀጣይ ዘመን ተወዳዳሪ ከተማ መሆን የሚያስችላቸው አይደለም።

ዐርበኞች በጣልያን ላይ ድል ተቀዳጅተው የኢትዮጵያ አስተዳደር ዳግም የም የዘመናዊነትና የሥልጣኔ አንገብጋቢነትን ትውልዱ ተረድቶ ነበር። ንጉሡ አስተዳ ለማጽናት የፖለቲካና የንዋይ እጥረት ገጥሟቸው ነበር። በመሆኑም ከመሠርት ወ በላይ የመሠረተ ልማት ግንባታ አለመኖሩ የከተሞችን ዕድገት ወስኖት ቆይቷል። ከ በኋላ የመንገድ፣ የትምህርት ቤት፣ የጤና ተቋማት የመሳሰሉት የመሠረተ ልማት መር የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ ማበብ፣ የኢንዱስትሪ ከተሞች መ የንግድ እንቅስቃሴ መነሣሣት፣ በኢትዮጵያ ከተሞች ታሪክ የመነቃቃት ጊዜ ነበር ማለት ይቻላል።

በዚህ ወቅት ከተሞች እንዲስፋፉና የሕዝብ ቁጥራቸው እንዲጨምር ያደረጉ ም አሉ። በከተሞች፡ የመሠረተ ልማት ግንባታ ማደግ፣ የቴክኖሎጂ መስፋፋት፣ የመሬት መለወጥ፣ የሥራ ዕድሎች በብዛት መገኘትና ሀብት በከተሞች እየተከማቸ መምጣት፡ ከ ወደ ከተማ ለነበረው ፍልሰት ዋነኞቹ ገፊ ምክንያቶች እንደሆኑ ይወሳል። በእነዚህና በተ ምክንያቶች የተነሣ

ከ959-1967 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ከተሞች እንዲቆረቆሩና የነዋሪዎች ቁጥር በሁለትና በሦስት እጥፍ እንዲያድግ ሆኗል።

አብዮቱ መፈንዳቱን ተከትሎ ከገጠር ወደ ከተሞች የሚደረገው ፍልሰት እጅግ በጣም ቀነሰ። ለዚህ አዎንታዊና አሉታዊ ክሥተቶች በገፊነት ይነሣሉ። በአዎንታዊነት የሚነሣው ምክንያት የመሬት ለአራሹ ዐዋጅ መታወጅ ነው። በዚህ ዐዋጅ ጢሰኛው የእርሻ መሬት በማግኘቱ ወደ ከተማ መፍለሱን ቀንሶታል። በአሉታዊነት ከሚነሡት መካከል ደግሞ የመንቀሳቀስ መብት መገደብ፣ ሀብት የማፍራት ገደብ መጣል፣ በከተሞች የሥራ እጥነት መስፋፋት፣ በከተሞች የተከሠተው የመጠለያ

CS CamScanner

እጥረትና በቀይና ነጭ ሽብር የተፈጠረው ማኅበራዊ አለመረጋጋት ይጠቀሳሉ። የኋላ ኋላ ረሃብና ጦርነት በፈጠረው " ውስ ከተሞች በስደተኞች ተጥለቅልቀዋል፡፡ የእነዚህ ውጤቶች የሆኑ በርካታ ማኅበራዊና " ሰብአዊ ቀውሶችንም አሳልፈዋል፡፡

የ1983ዓ.ም የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ በተወሰዱ የፖሊሲ ርምጃዎች፣ የኢትዮጵያ ከተማ ዕድገት ማንሠራራት

የጀመረበት ቢሆንም እስከ ሁለተኛው ዐሠርት ዓመት ድረስ (ፍጥነቱ ቀርፋፋ ነበር። በየአምስት ዓመት የተከፋፈለው የዕድገትና ትራስፎርሜሽን ዕቅድ ከተማ ልማት በሰጠው ትኩረት አበረታች ለውጦች ታይተዋል። ከከተማ ልማት አኳያ የመሬት፣ የቤት ልማት፣ የኮንስትራክሽን፣ የጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ዘርፎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ለእነዚህም ተቋማዊ አደረጃጀቶችና ሕጋዊ ማሕቀፎች ተፈጥረዋል።

ከ2003 ዓ.ም. ጀምሮ ባለፉት ዐሥር ዓመታት አዳዲስ ከተሞች ተመሠረቱ። ነባሮቹም ወደ ጎን ተስፋፉ፡፡ በሁሉም ከተማዎች የሕዝብ ቁጥር ጨመረ። በዚህ ወቅት ከተሜነት በጉልህ ያደገ ሲሆን፤ በከተማ የሚኖረውም ሕዝብ ብዛት ዕድገት ቀጥሏል፡፡ ይሁንና ዛሬም የከተሜነት ደረጃችን ከአፍሪካም፣ ከዓለምም በእጅጉ ያነሰ ነው። ለዚህም በከተሞች መካከል ያለው ያልተመጣጠነ ዕድገት እንዲሁም ያልተቀናጀ የከተማና የገጠር ልማት በመሠረታዊ ችግርነት ይነሣሉ። ያልተመጣጠነና ያልተቀናጀ የከተማ ልማት በርካታ ማኅበራዊ ችግሮችን ከማድረሱ ባልተናነሰ፣ በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ
አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የከተማ ልማት ዘግይቶ በመጀመሩና በፍጥነት ባለማደጉ የተነሣ፣ በአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን አብዛኛው ሕዝባችን በገጠር እንዲኖር ሆኗል። በሌላ በኩል በጥናትና በዕቅድ ባልተመራው የከተማ ዕድገት የተነሣ፣ በከተማ የሚኖረው ነዋሪ በመሠረታዊ አቅርቦቶች እጦት ፈተና ውስጥ ነው።

ከተማን ለነዋሪዎች ምቹ ማድረግ ካለመቻሉ ባሻገር፣ ከተሞችን የንግድ፣ የቱሪዝምና የ ማዕከል የማድረግ ዕድልን አጨናግፎታል፡፡ በከተሞች መሳካት የነበረባቸውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችንም ገትቷል፡፡

ሀገራችንን ጨምሮ በየትኛው ሁኔታ ውስጥ ባለ ሀገር ከፍተኛ ኢኮኖሚ የሚንቀሳቀስ በከተሞች ነው፡፡ ይሁን እንጂ በኛ ሀገር ከተሞችን በዘፈቀደ እያሰፋንና እየመሠረትን የር የኢኮኖሚ ዐቅም ለዘመናት አባክነናል። ከዚህ ብክነት ወጥተን ከተሞች የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር እንዲሆኑ የዕሳቤ ለውጥ ማምጣት አለብን። ስለ ከተማ ያለን ከቀየርንና ከተሞችና ከተሜነት ያሉባቸውን ተጨባጭ ችግሮች በውል ከተረዳን መውጫውን በማመላከት ረገድ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት የከተማ ልማቱን ለመምራት ጥረቶች ቢደረጉም ከተማው ነዋሪውንና ከባቢን አቀናጅቶ ለማልማት መሠረት የሆነው የከተማ ዕቅድ በቂ ትኩ አልተሰጠውም። በዚህ የተነሣ ጋሪው ከፈረሱ እየቀደመ የከተሞች መስፋፋት በዝ ከተሞች ምሥረታ ምስል ተቀርጸዋል። በመሆኑም የከተማ አስተዳደሮች ትግል እ የማጥፋት እየሆነ፣ ነጋ ጠባ መሠረታዊ አገልግሎቶችን በማቅረብ ጥያቄ ውስጥ ወድቀዋል።

በከተማ ሽግግር ለማምጣት ሥርዓታዊችግሮችን መለየትና መፍታት የግድ ነው። የከተፍነ ሽግግር ለማሳካት ቀጣይነት ያለው፣ ለረጅም ዘመን የሚያገለግልና በጥብቅ ዲሲ የሚተገበር የከተማ ዕቅድ ያስፈልጋል፡፡ አብዛኛው የከተማ ክፍሎች

ዕውቅና የላቸውም: በዘመናዊ አስተዳደር ያልተደራጁና የከተማ አገልግሎትና መሠረተ ልማት ያልተዳረሰባችን ናቸው፡፡ እንዲሁም በሕዝብ ብዛት መሥፈርት በአነስተኛ ከተማነት የሚመደቡ በርካ ከተሞች በገጠር አስተዳደር ሥር ይገኛሉ፡፡ አዲስ አበባን ጨምሮ ሌሎች መካከለኛና አነስተኛ ከተሞች በፈጣን ዕድገት ውስጥ ቢሆኑም፣ በበቂ ዕቅድ አለመመራታቸው ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ዳርጓቸዋል።

CS CamScanner

የከተማ መሪ ዕቅድ የከተሞችን ዕድገት ለመምራትና ለመቆጣጠር የሕግ አስገዳጅነት ያ እና በጥብቅ ዲሲፕሊን የሚፈጸም ዕቅድ መሆን አለበት። የከተማን እንቅስቃሴዎች . አጠቃቀም መሥፈርቶችን ባሟላ መልኩ ለማስተዳደርም እጅግ አስፈላጊ ነው። በሀገራች ግን በከተማነት ከተለዩ በሺዎች የሚቆጠሩ ከተማዎች መካከል መሪ ዕቅድ ያላቸው ጥቃቶች ብቻ ናቸው።

ከተሞች በመሪ ዕቅድ ባለመመራታቸው ለአደጋ የተጋለጡ፣ ለነዋሪዎቻቸው የማይመቹ፣ ለከተማ ብክለትና ለዘልማድ መስፋፋት የተዳረጉ ሆነዋል።

ሌላው የከተማ ልማት ችግር በመሬት አጠቃቀምና ግንባታ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ አለመቻላችን ነው። ለዚህ አንዱ ምክንያት የከተማ ቦታን በአግባቡ ለመጠቀምና ተስማሚ ከተማ ለመገንባት የሚያስችል የተሟላ አመላካች መዋቅራዊ ዕቅድ አለመኖሩ ነው። ባትም የከተማ መዋቅራዊ ዕቅዶች በማስፈጸም ዐቅም ማነስ፣ በፖለቲካ ጣልቃ ገብነትና በምልጃ ይጣሳሉ። ገንቢዎችም ሆኑ ሌሎች ተዋንያን ከሕግ በላይ ይሆናሉ። በሀገራችን የከተማና የአካባቢው መሬቶች ዕሴት ሳይጨምሩ በቀላሉ ሀብት መቀራመቻ ሆነዋል። በተዋንያኑና በተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች መካከል ፉክክርና ግጭት ከመፍጠር ባሻገር፣ ለፖለቲካ ገበያ መቀፍቀፊያ ሆኗል።

በፖለቲካ ገበያው የተነሣ ከተሞችን በተዘጋጀ ዕቅድ መምራት ፈተናዎች ይበዙበታል። ይህንን ለመፍታትና መሬትን በቁጠባ ለመጠቀም፤ የመሬትና የመሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሽፋን ማሳደግ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል። እስከ አሁን የደረስንበት ሽፋን

ግን ከምንፈልገው _አንጻር አነስተኛ ነው። በዚህ ረገድ ወደ ኋላ መቅረታችን ለከተማ ልማት ትልቅ ዕንቅፋት ሆኗል።

በዚህ ረገድ ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ ከተሞች የመሬት ሀብታቸውን ሙሉ _በሙሉ ዐውቀው የሚያስተዳድሩበት ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

ገጠሩን ከከተማ አቀናጅቶ ለማልማት በተሟላ ሀገራዊ የከተማ ልማት ማሕቀፍ መምራት ያስፈልጋል። ይህንንም ለማረጋገጥ ገጠሩንና ከተማውን አሠናስሎ ለማልማት የሚያስችል የሀገር፣ የክልልና የከተማ አስተዳደሮችን ዕቅድ መፈተሽ ይገባል፡

በከተማ ዕቅድና አስተዳደር ዙሪያ ከተነሡችግሮች በተጨማሪ፤ ከደረጃ በታች የሆኑ መኖሪያ ቤቶችና ጤና ጎጂ የሆኑ ከባቢዎች የተንሠራፉባቸው ናቸው። መንግሥታዊ አገልግሎታቸው ዝቅተኛ ነው። በተጨማሪም የከተማ ውበትና ማኅበራዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ የሕዝብ መገልገያዎች፣ አረንጓዴ ቦታዎችና መናፈሻዎች የጎደሏቸው

ናቸው3። አብዛኛዎቹ ከተሞች በደካማ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይታወቃሉ። ዓመታዊ ገቢ አሰባሰባቸውም በጣም ዝቅተኛ ነው። በእነዚህ ከተማዎች ውስጥ የሚኖር አብዛኛው ነዋሪ ሕይወቱን የሚመራው በኢመደበኛ የኢኮኖሚ ዘርፍ ተሠማርቶ በሚያገኘው ዝቅተኛ ገቢ ነው።

**8.3.** የመደመር መንግሥት በከተማ፡ የመጪው ዘመን ከተማ

በቀደመ ዕሳቤና ተግባር እየተመሩ በዘፈቀደ ከተማን ማስፋፋት ከባድ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶችን ያስከትላል። በመሆኑም በአዲሱ ዘመን ዕሳቤ ከተሞች ለመኖሪያ ምቹ፣ ለንግድ ማሣለጫ፣ ለፈጠራና ለቢዝነስ መጀመሪያና መጎልበቻ፣ ለቱሪስት ሆነው እንዲቆረቆሩ ማድረግ ያስፈልጋል። እንዲሁም ከአምራች ኢንዱስትሪው የተሣሠሩና ገጠሩን ከከተማው በማቀናጀት የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማፋና አስቻይ እንዲሆኑ ሊሠራ ይገባል። ለዚህም አዲስ አበባና ሌሎች መካከለኛና ነ ከተሞችን የመሠረተ ልማት ችግሮቻቸውን መፍታት ይገባል። ያሉባቸውን የዕቅ የአስተዳደር ፈተናዎች ማቃለል ያስፈልጋል። የመጪውን ጊዜ ተግዳሮቶት ለመፍታት ለመሻገር ደግሞ የላቀ ሐሳብ፣ ፈጠራና ፍጥነት ያለው ሥራ ይጠይቃል።

CamScanner

ሀገራችንን የዘመናዊ ከተሞች ባለቤት የማድረግ ጉዞ በመርሕ መመራት አለበት። ትንንሽ ከተሞችን ማዘመን፣ እንዲሁም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን የታጠቁ አዳዲስ ከተሞች መገንባት ትኩረት ይፈልጋል። በነባር ከተሞቻችን የተዘረጉ ጊዜ ያለፈባቸውም ይሁ ያልተዘረጉ መሠረተ ልማቶች፣ በዘመናዊና የወደፊቱን ታሳቢ ባደረጉ መሠረተ ልማቶ መለወጥ ይኖርባቸዋል። የአዳዲስ ከተሞች ምሥረታ የሚከናወነው ደግሞ እያንዳን የዘመናዊ ከተማ መገለጫዎች ከጅምሩ ታሳቢ ተደርገው ሊሆን ይገባል።

በነባር ከተሞች እድሳትም ሆነ አዳዲሶችን ከመገንባት አኳያ ለአይበገሬነት የቅድሚ ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። የመሠረተ ልማቶች ዝርጋታዎች ወይም ማሻሻያዎች ለአ ንብረት ለውጥ የማይበገሩ ሆነው እንዲታቀዱና ተግባራዊ እንዲደረጉ ማድረግ ተገቢ ነው፡ ይህም የከተማ ደኖችን ጨምሮ እንደየከተማው ጥቅም ላይ የሚውሉ ሌሎች አረንጓ መሠረተ ልማቶችን መዘርጋትን ያካትታል። በተጨማሪም፣ ሁኔታዎችን በቀላሉ ተላማ የሆነ የከተማ አወቃቀር መፍጠር አለብን። ተላማጅ የከተማ አወቃቀር፣ የሕዝብ ስብጥ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ለውጦችን በቀላሉ በከተሞች ለማስተናገድ እንዲቻል ያደር በዚህም ከተሞችም ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እንዲያድጉ ያስችላል።

መገንባት የምንፈልጋቸው የአዲሱ ዘመን ከተሞች አካታችነትን የማዕዘን ድንጋይ ያደረ መሆን አለባቸው። በመጪዎቹ ከተሞች የሕዝብ ሥፍራዎችን ነዋሪዎች በባለቤትነ ስሜት ሊጠቀሙባቸው ይገባል። እነዚህ የሕዝብ ሥፍራዎች ተደራሽነትንና የማኅበረሰ መስተጋብርን ማበረታታት በሚችል መልኩ የሚገነቡ ናቸው። የመኖሪያ፣ የንግ የአረንጓዴ ሥፍራና የመዝናኛ ሥፍራዎችን በጥምር ያካተቱ ሊሆኑ ይገባል። ማኅበራዊ ትሥሥርን የሚያበረታቱ ሠፈሮች እንዲፈጠሩ መደረግ አለበት። ማኅበረሰቡን በእቅድ ሂደት ውስጥ በንቃት በማሳተፍ፣ ነዋሪዎች ፍላጎቶቻቸውንና ምኞቶቻቸውን እንዲገልጹ የሚያስችሉ ሥርዓቶች መዘርጋትና በዚህም ፍትሐዊና አካታች የሆነ ዕድገት እንዲኖር መትጋት ይጠይቃል።

እንቅስቃሴ የከተሞች ሕይወት ነው። አንድ ከተማ የከተማነት ሕይወት እንዲኖራት በከተማዋ ውስጥ የንግድ፣ የባህል፣ የስፖርት፣ የአስተዳደር፣ የዲፕሎማሲ፣ የእምነት፣ ኮንፈረንስ፣ ወዘተ. እንቅስቃሴዎች መኖር አለባቸው። እነዚህ እንቅስቃሴዎች የከተማዋን ግቢ ይጨምሩታል፡ ለከተማዋ ነዋሪዎች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ። ከተማዋን የብዙዎች 'መናኸሪያ እና የኅብረ ብሔራዊ አንድነት መፍጠሪያ ያደርጓታል። የከተማዋን በጎ ገጽታም ያስተዋውቃሉ።

እነዚህን እንቅስቃሴዎች ለማሣለጥ የተለያዩ የመጓጓዣ አማራጮችን በከተሞቻችን መገንባት ያስፈልጋል። ከጤናና ከመዝናኛ ጋር የተሣሠሩትን ብስክሌትን እና የእግር ዞን የሚያስተናግዱ መገልገያዎች እና መሠረተ ልማቶች መኖር አለባቸው። የከተማ የእንቅስቃሴ ሥፍራዎች ንቁ፣ ጤናማ የአኗኗር ዘይቤዎችን የሚደግፉና የማኅበረሰብ ትሥሥሮችን የሚያጠናክሩ ይሆናሉ።

የብዙኃን ትራንስፖርት አማራጮችን በማስፋት በተለይም የአረንጓዴ ትራንስፖርት አማራጮችን (በኤሌክትሪክ

የሚሠሩትን ዓይነት) በከተማ ትራንስፖርት ሥርዓት ውስጥ በማካተት ቀልጣፋና ዘላቂ የመጓጓዣ ዘዴዎች እንዲሆኑ ማስቻል የዘመናዊነት መገለጫ ነው። ይህ አጠቃላይ የከተማ የመጓጓዣ ሥርዓት በግል መኪናዎች ላይ ያለውን ጥገኝነት ይቀንሰዋል። መጓጓዣ ለሁሉም በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆን ያደርገዋል። ማኅበራዊ እኩልነትንም ለማረጋገጥ ያግዛል። ከተሞችን በሁለንተናዊ መንገድ በማልማት፣ የወደፊቱ ከተሞች የበለጸጉና የማይበገሩ እንዲሆኑ መሠረት መጣል ያስፈልጋል።

እንደሚታወቀው ሀገራችን የተለያዩ ምቹ የአየር ጠባይ ያሉባቸው ከተሞች ባለቤት ናት። ከተሞቻችን ከተፈጥሮ አንጻር ይህ ጎደላቸው የሚባል ነገር የለባቸውም። ከተፈጥሮ ጸጋ አንጻር ተመራጭ ሥፍራዎች ናቸው። ይህንን የተፈጥሮ ጸጋ እንደ

CamScanner

ዕድል ተጠቅመን፣ ዘመናዊነትን ለከተሞቻችን በማላበስ በዓለም ደረጃ ተመራጭ የጎብኚዎች መዳረሻ የሚሆኑ ከተሞች ባለቤት መሆን እንችላለን ።

አሁን ያለንበትን ደረጃ ታሳቢ ስናደርግ፣ ከተሞቻችንን እጅግ ዘመናዊ የማድረግ ትልም የጥቂት ዓመታት ጉዞ ብቻ አይሆንም። ከተሞቻችን በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪና ወቅታዊውን የከተማነት መመዘኛ የሚያሟሉ ብቻ መሆን አይበቃቸውም። በቀጣይ ተወዳዳሪ ሆነው ለመቀጠል ዐቅም ያካበቱ ሆነው መገንባትም አለባቸው። ከሁሉ በላይ አካታችና ፍትሐዊ የሆነ ብልጽግናን እውን በማድረግ፣ ከተሞቻችን ለሁሉም ነዋሪዎች ምቹና ተመራጭ እንዲሆኑ መትጋት ያስፈልጋል። ለዚህም የዘመኑን የዲጂታል ዓለም ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች መታጠቅ አለባቸው።

የአዲሱ ዘመን የከተማ ዕቅድ ዝግጅት፣ በዲጂታል ቴክኖሎጂና በግዙፍ የመረጃ ትንተና ላይ የተመሠረተ ሆኗል። የከተሞችን ችግሮች የሚፈታና ዘላቂ ልማትን የሚደግፍ ስትራቴጂያዊ የከተማ ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል።

በተሟላ መረጃ የተዘጋጀ የከተማ ዕቅድ ውጤታማ የመሬትና የሀብት አጠቃቀም ዞ ዙሪያ የሚቀረጹ ፖሊሲዎችና የሚተላለፉ ውሳኔዎች በተሟላ መረጃ ላይ ከተመ ይፈጥራል። ይህ ደግሞ የመሠረተ ልማት ዐቅሞችን ለማሻሻል ያስችላል።

" የከተማውን ቀጣይ የዕድገት ፍላጎት የሚያመላክቱ ይሆናሉ። በበቂ መጠን የተ የተተነተነ መረጃ ያለው ከተማ፣ ሃምሳና መቶ ዓመት አስቀድሞ የከተማውን ንድፍ መንደፍ ይቻለዋ።

ከተሞቻችን ከፍተኛ ፍጥነት ያለው የበይነ መረብና የዲጂታል ትሥሥር ሊኖራቸው : አስተማማኝ የበይነ መረብ አገልግሎት ነዋሪዎችን በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ እንዲ የዲጂታል አገልግሎትና የኢኮሜርስ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። በተዋ በኢመንግሥት በኩል፣ አዳዲስ ዘመናዊ የሕዝብ አገልግሎት ማስተዳደሪያዎች እንዲዳረሱ ያደርጋል። ይህም ሕዝቡ ከአካባቢው መንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት የተሻለ ያደርገዋል።

በዘመናዊ ከተሞች ውስጥ የሀብት አስተዳደርን ለማሻሻል የበይነ መረብ ነገሮች ላይ ይውላሉ። የበይነ መረብ ነገሮች ዘመናዊ የኃይል መሥመሮች ሥርጭትን በ የአቅርቦትና የአገልግሎት ጥራትን ያሳድጋሉ። በመረጃ የተደገፉ ሥርዓቶች አጠቃቀምንና የቆሻሻ አወጋገድን ያሻሽላሉ። ይህም ለተቀላጠፈ የከተማ ኑሮ ይከፍታል።

እነዚህ መረጃ መር ውሳኔዎች፣ የሚዘረጉ መሠረተ ልማቶች እያደገ የሚመጣውን ፍላጎት ማሟላትና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ እንዲችሉ ያደርጋሉ። በመረጃ እርስ የተሣሠሩ መሠረተ ልማቶች፣ የዕለት ተዕለት ኑሮን ያሻሽላሉ። ፈጠራንና ኢኮኖ ዕድገትን ያጎለብታሉ። ከተሞቻችን በዚህ ደረጃ ሲገኙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ ይሆናሉ።

ዘመናዊ የከተሞች ዕቅድ ውብ፣ ጽዱ፣ አረንጓዴና ምቹ ከተሞችን መፍጠር ዓላማው ያደርጋል። ውበታቸው ከተስተካከለ ግንባታ፣ ከግንባታው ጥራት እና ለዓይን ሳቢ ሆኖ ከመሠራቱ የሚመነጭ ነው። ጽዳቱ ደግሞ የከተማውን ንጽሕና ለመጠበቅ ከተፈጠረው ባህል፣ ከቆሻሻ አስተዳደርና አወጋገድ ጋር ይያያዛል። ከተሞች የተወሰነውን ክፍል አረንጓዴ
_በማድረግ የአየር ንብረት ለውጥ ፈተናን መቋቋም አለባቸው።

የከተሞች አካላዊ ገጻቸው መሟላት መሠረታዊ ነገር ቢሆንም፣ የተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ አብሮ ካልዘመነ፣ የከተሞች አጠቃላይ ዕድገት አይሟላም። በመሆኑም አገልግሎት _አሰጣጥን ቀልጣፋ ለማድረግ ከተሞች ይበልጥ ሥሉጥ መሆን ይገባቸዋል። የከተሞች ሥጥነት ውጤታማ የሀብት አጠቃቀም እንዲኖር ያደርጋል። የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቶችን በማሳጠር የከተማውን አሠራር ያቀላጥፋል።

CS CamScanner

በከተሞቻችን እንደ ውኃ፣ መብራት፣ የፍሳሽ መሠረተ ልማት፣ ጤና እና ትምህርት መሠረታዊ ፍላጎቶችን በጥራት ማቅረብ የመደመር መንግሥት አንዱ ግብ ነው። የከተሞች ጸጥታና ደኅንነት ከዕድገታቸው እና ከግባቸው ጋር መመጣጠን አለበት። በተጨማሪም የከተሞች ክፍሎች የንግድ አካባቢ፣ የመሥሪያ አካባቢ እና የመኖሪያ አካባቢ ተብለው ተለይተው መገንባት አለባቸው። ይህም መሠረተ ልማትን፣ አገልግሎትን እና የሕዝብ ፍሰትን ያሣልጣል።

የከተሞች ውስጣዊ ገጽታ በመንግሥት አስተዳደርና በአገልግሎት አሰጣጥ ዘመናዊነት ይታያል። መንግሥታዊ አገልግሎቶችን የሚሰጡ በርካታ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ዘመናዊ ባለመሆኑ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ይፈጠራል። ንግድ በቀላሉ የሚሠራበትና በአገልግሎት አሰጣጥ ዜጎች የሚረኩባት ከተማ የምትፈጠረው ፈጣን አገልግሎት መስጠት ከተቻለ ነው።

በሀገራችን የአገልግሎት አሰጣጥ የማገልገል ባህል የጎደለው ነው። ገና ከባላባታዊ ሥርዓትና ጠባይ አልተላቀቀም። አገልጋይ ባላባት፣ ተገልጋይ ጢሰኛ ነው። በተለይ በከተሞች አገልግሎት ዘመኑ ከደረሰበት ፍጥነት አንጻር የተንቀራፈፈ ነው። ችግሩ የመልካም አስተዳደር ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ አንድምታውም ትልቅ ነው።

ከተሞች የሚሰጡት አገልግሎት በዘመኑ ልክ እንዲሆን የአገልጋይነት ባህልን መገንባትና የአሠራር ሥርዓቶችን ማዘመን ይገባል። በመሆኑም የፌዴራልና የክልል ተቋማት እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ወደ ዲጂታል ሽግግር እያደረጉ ነው።

በከተማ የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን ሥሉጥ ማድረግ ወጪ ቆጣቢ ቀልጣፋ አገልግ ነዋሪዎች እንዲያገኙ ያስችላል። በሥሉጥ ከተሞች ነዋሪዎች ውል ለመስጠትና በአካል መገኘት አይጠበቅባቸውም። የንግድ ሥራ ለመጀመር አብዛኛውን ሂደት በ ለመቅረብ አይገደዱም። የመንግሥት ግዢ ሂደቶች አካላዊ ግንኙነትን በመቀነስ በአካል ሳይገኙ እንዲከናውኑ ያስችላሉ።

ሥሉጥ ከተሞች አገልግሎታቸው ከዚህም በላይ ነው። ዘላቂ የከተማ ልማትን ያረጋግጣሉ አረንጓዴ መሠረተ ልማት ለማስፋፋትይጠቅማሉ። እንዲሁምኃይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎ በመጠቀም የአካባቢና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃን ያሻሽላሉ። ለአየር ንብረት ለውጥ የማይ ከተማን ለመገንባት ሥሉጥ የከተማ መፍትሔዎች ከፍተኛ አስተዋጽዖ አላቸው። ከተሞች ሕይወት እንዲኖራቸውና የሰው ልጅ ሕይወቱንና ሥራውን በረጋ መንፈስ እንዲመራ፣ ለአረንጓዴ ቦታና ለሕዝብ ቦታ ልማቶች ትልቅ ቦታ ይሰጣሉ።

የከተሞች ሥሉጥ መሆን ምቹ የፈጠራ ሥነ ምኅዳር ይፈጥራል። የዲጂታል ፈጠ ያጎለብታል። የመደመር መንግሥት ዕሳቤንያስፋፋል። በቴክኖሎጂ የተደገፉ ኢንዱስትሪዎ ዕድገት ያፋጥናል። በዚህም ዕውቀት መር ኢኮኖሚ መገንባት ያስችላል።

በአጠቃላይ ሥሉጥ ከተሞች በመረጃ የተደገፉ መፍትሔዎችን ይሰጣሉ። በዲ፤ ቴክኖሎጂና በኔትዎርክ በተገናኙ ሥርዓቶች ተጠቅመው የከተማ ልማት ራዕይን ውጤታ ዘላቂና ሁሉን አካታች ያደርጋሉ። የነዋሪዎችን፣ የኩባንያዎችንና የማኅበረሰቡን ፍላጎቶ ግቦች ለማሳካት የሚያስችል ዐቅም ይፈጥራሉ። ሥሉጥ ከተሞች ለቀጣይ ዘመን ዕድሎት ተግዳሮቶች ዝግጁ የሆነ ከተማ ይፈጥራሉ። የዲጂታል ሽግግሩን እውን በማድረ ኢኮኖሚው ከዲጂታል ኢኮኖሚ ወደ ዕውቀት መር ኢኮኖሚ ሽግግር እንዲያደ ያስችላሉ።

ከተሞቻችንን በአዲሱ ዘመን ዕሳቤና ተግባር ማልማትና ፈጣን ዕድገት ማረጋ አለብን።ያሉንን የመሠረተ ልማት ዐቅሞች አሟጥጠን መጠቀምና ኋላ በቀረንባቸው መልማት አለብን። ከተሞቻችን ከዲጂታል ዘመን ዕድል እንዲቋደሱ ከፈለግን በፍጥ ሥሉጥ ማድረግ ይገባል። ለዚህም መሳካት የከተሞች አስተዳደር በመደመር መንግሥት ዕሳቤ መቃኘት አለበት።

CS CamScanner

**8.4.** አዲስ አበባ እንደ ማሳያ

አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን የአፍሪካም ዋና ከተማ፣ ከ5o በላይ ኤምባሲዎች ያባት፣ እንደ አፍሪካ ኅብረትና በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በሚመጥን ደረጃ አላደገችም። ይሄንን ማስተካከልና አዲስ አበባን እንደስሟ አበባና ዓይነት ታላላቅ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ናት። ይሁንና አዲስ አበባ ይሄንን እውነታ የኢትዮጵያ ብልጽግና ማሳያ ከተማ ለማድረግ ብዙ ሥራ እየተሠራ ይገኛል። በዚህም አዲስ አበባን ለከተሞቻችን ምሳሌ የምትሆን ሥሉጥ ከተማ ለማድረግ፣ ችግሮቿን ከሥራቸው ነቅለን በዲጂታል ዘመን ቴክኖሎጂ እየዋጀን፣ እየታደሰችና እንደ አዲስ
እየለማች ትገኛለች።

አዲስ አበባን የማልማት መርሕ ሦስት ዓላማዎች አሉት። እነርሱም የትናንት ውሱንነቶቿን መፍታት፤ ዛሬ ዓለም የደረሰበትን የከተማ ደረጃ ማላበስና ለነገው ትውልድ የምትመች አዳጊ ከተማ ማድረግ ናቸው። አዲስ አበባ ያልተፈቱ የመሠረተ ልማትና የማኅበራዊ አገልግሎት፣ የዘመናዊነትና የተደራሽነት ፈተናዎች አሉባት። ለነዋሪዎቿ ምቹ የመሆንና የአፍሪካ ዋና ከተማነቷን የማሟላት ውሱንነቶች ገጥመዋታል። አዲስ አበባን ለማዘመን፤ እነዚህን ፈተናዎች ማቃለል ያስፈልጋል።

አዲስ አበባ እነዚህን የትናንት ዕዳዎች ከማቃለል በተጨማሪ ዛሬ የሚኖረውን የከተማነት ደረጃ ማሟላትም አለባት። አረንጓዴ ሥፍራዎች፣ የመዝናኛና የስፖርት ቦታዎች፣ ዘመናዊ የጽዳት አስተዳደር፣ የማኅበራዊ ተቋማትና የአገልግሎቶች ተደራሽነት፣ ዘመናዊ የአገልግሎት አሰጣጥ መንገዶች፣ ዘመናዊ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች፣ ወዘተ፣ ያስፈልጓታል። ከእነዚህ በተጨማሪም ለነገው ትውልድ የሚሆኑ አገልግሎቶች፣ መሠረተ ልማቶች፣ አቅርቦቶችና ግንባታዎች ይጠበቁባታል።

በአዲስ አበባ ነዋሪው በፍጥነት እያደገ ነው236። የመኖሪያ ቤትና የመሠረታዊ አገልግሎት አቅርቦት ፍላጎት በዚያው ልክ በማደግ ላይ ይገኛል። እያደገ የመጣውን የከተማ ነዋሪ ፍላጎት በፍጥነትና በጥራት ለመመለስ ባለመቻሏ ለኑሮም ሆነ ለንግድ በሚፈለገው መጠን የማትመች ከተማ አድርጓታል።

በአዲ አበባ በርካታ አስተዳደራዊ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲበረቱ ሆነዋል። የአዲስ አበባ ከተማ ንድፍ ዜጎች እንደልባቸው ተንቀሳቅሰው ማኅበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ለመከወን አይመችም። የከተማዋ የመንገድ አውታሮች ትሥሥር የሌላቸውና ጠባብ በመሆናቸው የተነሣ፣ በቀን ከአንድ ጉዳይ በላይ ተንቀሳቅሶ ለማስፈፀም ያዳግታል።

የአዲስ አበባን የመጓጓዣ መሠረተ ልማት ለማሻሻል መንገድ ማውጣትና ማስፋት የግድ ነው። በዚህ ጊዜ ደግሞ ብዙ ነባር ሠፈሮች እንዲነሡ ይገደዳሉ። ብዙዎቹ በዐብይ እቅድ (Master Plan) መሠረት፣ መሠረተ ልማቶች ተሟልተውላቸው የተገቡ አይደሉም። ብዙዎቹም የመንገዶችን ጠርዝ ታክከው የሚገነቡ ናቸው። ስለዚህም የመንገድ ስራ አስፋልት ጠርዝ
ታክከው ለቆሙ በርካታ ሕንፃዎች መፍረስ መንሥኤ ይሆናል።

አዲስ አበባ ባለባት የንድፍ ችግር ምክንያት በመጓጓዣም ሆነ በእግር ለመንቀሳቀስ የማይመቹ አካባቢዎች ብዙ ናቸው። እንዲሁም እያደገ የመጣው የሕዝብና እንቅስቃሴ በፍጥነት እንዳይሣለጥና ይልቁንም እንዲወሳሰብ እያደረገው ይገኛል። በአጠቃላይ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል። በከተማ ሁለንተናዊ ዕድገትም ላይ ትልቅ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል።

የአዲስ አበባ መንገዶች ሁኔታ፣ የአዲስ አበባን መለያ ጠባብ ጠመዝማዛ መን አስመስለውታል። መንገዶቿ ከመንቀሳቀሻነት በተጨማሪ ቆሻሻ መጣያና ማራ ናቸው፤ የእግረኛ መንገድ ናቸው፤ የመኪና ማቆሚያ ናቸው፤ የድንኳንና ዳስ መ ናቸው።

CS CamScanner

እንዲሁም ወንዞቿ በደረቅና በፈሳሽ ቆሻሻ ተበክለው ጎብኝዎች የሚጠየቅ ሆናለች። በሌላው ዓለም በውኃ አካላት አጠገብ መኖር የሀብት ማሳያ ነው፤ በሆደ ግን በውኃ አካላት አጠገብ መኖር የፍጹም ድኅነት መገለጫ ነው::

በመንገዶችም ሆነ በወንዞች ዳርቻ አረንጓዴ አትክልት አይታዩም። ለአረንጓዴ ተ የተተው ቦታዎች በሕገ ወጥ ግንባታዎች ተሸፍነዋል፤ አልያም የቆሻሻ ማጠራቀሚ ሆነዋል። ከዚህ ቢያልፍ እንኳን አረንጓዴ አልባ ግራጫማ ናቸው። በአጠቃላይ መ መንገዱን ተከትለው የሚገኙ መሠረተ ልማቶች የከተማውን ውበት ከማጥፋትም ከተማዋን ለነዋሪውም ሆነ ለንግድ እንቅስቃሴ የማትመች አድርገዋታል፡

የአዲስ አበባ ችግሮች ከአመሠራረቷ ጋር ይያያዛሉ። ከዚያም በላይ አብዛኞቹ በፍጥነት መስፋት በጀመረችበት ወቅት፣ ከተማዋ በዘመናዊ የከተማ ዕሳቤ ባሉ የተፈጠሩ ችግሮች ናቸው። አብዛኛዎቹ የሀገራችን ከተሞች በዘመናዊ ዕሳቤ ባለመ የሚፈጠረውን ይህንን ችግር በተለያየ መጠንም ቢሆን ከአዲስ አበባ ጋር ይጋሩታል።

የአዲስ አበባ ነባር የከተማዋ ክፍሎች አመሠራረታቸው በቅርብ ከተስፋፉት የከተማዋ ክፍሎች ይለያል። ቤተ መንግሥቱንና መኳንንቱን ተከትለው አገልጋዮች፣ ወታደሮች፣ ነጋዴዎችና አብያተ ክርስቲያናት ከትመዋል። እንዲሁ በተወሰነ ሁኔታ ቦታ እየተመሩ " ወይም እየገዙ የሰፈሩም አሉ። ይሄም ሲሆን በታወቀ ዕቅድና ዕሳቤ አይደለም። ለመንገድ፣ ለማኅበራዊ አገልግሎቶች፣ ለአረንጓዴ ሥፍራዎች፣ ለፍሳሽ ማስወገጃዎች፣ ለመንግሥታዊ አገልግሎቶች፣ ለአደጋ ጊዜ መገልገያዎች የታቀዱ አሠራሮች አልነበሩም። በዚህም የተነሣ የከተማዋ ዕድሜ ሲጨምር እነዚህን አገልግሎቶች ለማሟላት የሚሠሩ ሥራዎች መንደሮችን የሚነኩ ሆኑ።

አዲስ አበባ በ1879 ዓ.ም. ስትቆረቆር ነባር ሠፈሮቿ የተመሠረቱት በእቴጌ ጣይቱ ዕቅድ መሠረት ነው። ይህ “የጣይቱ ዐቢይ ዕቅድ” የሚባለው ዕቅድ ለተለያዩ መኳንንትና መሳፍንት የ አካባቢዎችን በመስጠት ሠፈሮችን መመሥረት ነበር። መኳንንቱንና መሳፍንቱን በመከተል ሌሎች ነዋሪዎች ሠፍረዋል። ይህ ዓይነቱ ሠፈራ በኋላ ለተፈጠረው አስቸጋሪ የመሐል ' ከተማ የአኗኗር ሥርዓት ዋና መነሻ ነው። በእነዚህ ነባር መንደሮች ውስጥ ደረጃቸውን | የጠበቁ መኖሪያ ቤቶች፣ መጸዳጃዎች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ ማኅበራዊ አገልግሎት | መስጫ ማዕከላት፣ የመዝናኛና የስፖርት ቦታዎች አይገኙም።

አዲስ አበባ ከስልሳ ወይም ከሰባ ዓመታት በፊት ጠባብና ከከተማነት ይልቅ ገጠርነት የተጫናት ከተማ ነበረች። ይህ ሁኔታ በመካከለኛው የከተማዋ ክፍል እስከ ቅርብ ዘመን እምብዛም አልተቀየረም። የዛሬም ተጨባጭ ሁኔታ ነው። የከተማችን አብዛኛው ክፍል ኮኮሽ(Slum) አካባቢ ተብሎ ሊጠራ የሚችል ነው። እነዚህ መንደሮች የከተማውን መሠረተ ልማት አውታራት ለማስተካከልና ለመገንባት ገዳቢ ሆነው ቆይተዋል። አዲስ አበባ ካሉባት ችግሮች ተላቅቃ የመጪው ዘመን ከተማ እንድትሆን እነዚህ ችግሮች መቀረፍና በላቀ ደረጃ መሻሻል አለባቸው። አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿና ለቱሪስቶች፣ ለፈጠራና ለኢንተርፕረነርሺፕ እንዲሁም ለንግድና ለግብይት ምቹ የሚያደርጉ ሥራዎች አሁን እየሰፉ ነው።

አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ ለማድረግ የከተማ ዕቅድ ዝግጅት፣ የመሰረተ ልማት እድሳትና ግንባታ፣ የመልሶ ማልማት፣ የወንዝ ዳርቻ ልማትና የሕዝብ መገልገያ ቦታዎች በከፍተኛ ፍጥነትና ጥራት እየለሙ ናቸው። በተቀናጀና በተሠናሰለ የከተማና የመሰረተ ልማት ግንባታ አዲስ አበባ እየፈካችና እየደመቀች እንድትታይ አድርጓታል።

አዲስ አበባን ሕይወት አልባ ካደረጓት ምክንያቶች አንዱ መንገድና በመንገድ ዙሪያ ያሉ ችግሮች ናቸው፡፡ አገና መንገድ ባለመኖሩ አቃቂና ቃሊቲ እንደ ዓይንና ቅንድብ የቅርብ ሩቅ ሆነው ሳይተያዩ ቆይተዋል። መንገድ የሌለው ከተማ እንኳን ሥሉጥ ከተማ ለመሆን የከተማ ደረጃን በቅጡ ለማሟላት አይችልም።

CamScanner

እነዚህን መሠረታዊ መዋቅራዊ የአዲስ አበባን ችግሮች በመፍታት የቀጣይ ዘ እንድትሆን የኮሪደር ልማትን ተግባራዊ ማድረግ በጥሩ እመርታ ላይ ይገኛል። አበባ የኮሪደር ልማት ቢያንስ ሰባት ጥቅሞችን አስገኝቶላታል። የመኪና መንገድ አረንጓዴ ሥፍራዎች፣ የእግረኛና የብስክሌት መንገዶች፣ የነዋሪዎች መገልገያ ሥፍ የመኪና ማቆሚያዎች ግንባታ፣ የንግድ አካባቢዎች ማሻሻያና የመኖሪያ መንደሮች ማሻሻያ።

በአጠቃላይ የኮሪደር ልማቱ እየተመራ ያለው ማስተካከልን፣ ማዘመንን፣ ማሳመርንና ማመቻቸትን ገዥ መርሕ በማድረግ ነው።

ማስተካከል፥ ያልነው ቀድሞ የነበሩትን መንገዶችና ዐደባባዮች፤ የመንገድ ላይ መብራቶችንና የማስታወቂያ ሰሌዳዎች፣ የፍሳሽ ማስወገጃዎች፣ የቴሌ፣ የውኃና የመብራት.. መሥመሮች ማስተካከልን ነው፡

ማዘመን፥ ደግሞ በዚህ ዘመን የሚሠራን ሥራ ከዲጂታል ኢትዮጵያ ርዕይና ዘመኑ ከደረሰበት ክፍሎጂ ጋር ማስተሣሠርን ነው። ለምሳሌ የእሳት አደጋ ቢነሣ ውኃ ለመቅዳት የሚያስችል " መሠረተ ልማት በየአካባቢው በበቂ ሁኔታ አልነበረም። ይሄን በዓለም አቀፍ ደረጃ መሠረት በመንገዶች ላይ ሰርተናል።

ማሣመር፥ በሌላ በኩል የምንሠራቸው ሥራዎች ውበታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። ንጽሕናንና ውበትን በማስተሣሠር ከተማችንን ጽዱና ውብ የሚያደርጉ ሥራዎች ተሠርተዋል። ዛፎችና ሣሮች ተተክለዋል። ዘመናዊ የቆሻሻ ማስወገጃ ሥርዓት ተዘርግቷል። የመንገድ ላይ የአጥር ግንቦችን በማፍረስና ደረጃ በመስጠት ቤቶችና መንገዶች እንዲጣጣሙ ተደርጓል። የተደበላለቀ የነበረው የሕንጻዎች ቀለም የተግባባ እንዲሆን ተደርጓል። ከዓይን ባለፈም የአየር ንብረት ለውጥን በማስተካከል ረገድ ከፍተኛ ድርሻ ያለው አረንጓዴና የቆሻሻ አወጋገድ አስተዳደር ተዘርግቷል። አዲስ አበባ ከግራጫ ጠርዞቿ እንዲሁም ከባዕድ ጠረኗ እየተላቀቀች ነው።

ማመቻቸት፥ ስንል ደግሞ አካባቢን ለነዋሪዎች፣ ለመንገደኞች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ወዘተ. ምቹ ማድረግ ነው። በዚህ ረገድ የመንገድ ላይ ማረፊያዎች ሠርተናል። የእግረኛና የብስክሌት መንገዶችን በዘመናዊ መልኩ ሠርተናል። መንገዶችን ለአካል ጉዳተኞች፣ ሠፈሮችን ደግሞ ለሕፃናት ምቹ አድርገናል። የውኃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የፍሳሽ፣ የቴሌ መሥመሮች ለጥገና ምቹ ተደርገዋል።

ከተሞች ለኑሮና ለሥራ ምቹ እንዲሆኑ በቀላሉ መንቀሳቀስ እንዲሁም በእንቅስቃሴው አእምሮና መንፈሱን የማይጎረብጠው መሆኑ አንድ ነገር ነው። እንዲሁም ዜጎች በተመቸ አካባቢና ቤት ውስጥ ሊኖሩ ይገባል። አዲስ አበባ መቶ ሃምሳ ዓመታትን የተሻገረች ከተማ እንደመሆኗና በአብዛኛው መንደሮቿ እንደ ሌሎቹ ዕድሜ ጠገብ የዓለማችን ከተሞች ዘመን ተሻጋሪነት ስለሚጎድላቸው፣ ለኑሮ የማይመቹ አካባቢዎችና ቤቶች አሏት። በመንግሥትና በማኅበረሰብ ድጋፍ ዐቅመ ደካማ ዜጎች ከእነዚህ ከዘመሙ ቤቶች ወጥተው ወደ ዘመናዊ ቤቶች ገብተዋል።

መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ዜጎች የቤት ባለቤት የሚያደርጉ ሥራዎች በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች ተደግፈው ተጀምረዋል። እነዚህ ፕሮጀክቶች የግል ዘርፍን በማሳተፍ በተመጣጣኝ ዋጋ የቤት ተደራሽነት እንዲያድግ በሥራ ላይ ያሉና የሚቀጥሉ ፕሮጀክቶች ናቸው።

አዲስ አበባ ተጨማሪ ቤት እንደሚያስፈልጋት ሁሉ፣ በመሐል ከተማ ደግሞ ለመኖሪያ የተቆረቆረችው ከአዲስ አበባ መቆርቆር ጋር ተያይዞ ነው። አዲስ አበባ ስትቆረቆር ዋለ የማይመቹ መንደርና ቤቶች አሉ። ከእነዚህ አንዷ ፒያሳ ነበረች። ፒያሳ በከተማ ማዕከል ማዕከላትን መሠረት አድርጋለች። ግቢ፣ አራዳና የቤተ ክርስቲያን ቅጽርን። ግቢ የአራት ኪሎው ቤተ መንግሥት ሲሆን፣ አራዳ ደግሞ ዛሬ ዐድዋ ሙዝየም በተሠራበት ቦታ በዙሪያው የነበረው ገበያ ነው።

CamScanner

አራዳ የገበያ ሥፍራ እንዲሆን ያደረገው በአካባቢው የአራዳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲ መኖር ነው፡፡ ገበያውን ተከትሎ የንግድ ቤቶች ተስፋፉ። በአዲስ አበባ የመጀመሪ ጎዳና የተዘረጋው ከቤተ መንግሥቱ ወደ አራዳ ገበያ ነበረ። በኋላ የ928ቱ የጣልያ ወረራ የከተማዋን መልክ ቀየራት፡፡ አራዳም በጣልያንኛ ፒያሳ ተባለች። ገበያውም ከአራዳ እንዲወጣ ተደርጎ ዛሬ መርካቶ ወደሚባለው ቦታ ተዛወረ፡፡

ፒያሳም በዋናነት የከተማው የጣልያን አስተዳደር መቀመጫ፣ ለውጭ ዜጎች መ የመዝናኛና የገበያ ቦታ እንድትሆን ተደረገ። አራቱ ሲኒማ ቤቶች ለውጭ ሀገር እንዲያገለግሉ ሆነው ተገነቡ 48። መሸታ ቤቶች ተስፋፉባት፡፡ የውጭ ዜጎችን የሚያገለ የእኛ ሰዎችም የወንዙን ዳርቻ ይዘው ሠፈሩ፡፡ ይህም በኋላ ዘመን ከፒያሳ ወርቅ ቤቶች የተፈጠሩትን የድኾች መንደሮች ፈጠረ፡፡

የጣሊያን ወረራ ሲቀለበስም በተለቀቁት ቤቶች የተስፋፉት መጠጥ ቤቶች፣ ሥጋ ቤቶች፣ አልባሳት መሸጫዎች፣ ወርቅ ቤቶችና ቡና ቤቶች ናቸው፡፡

ፒያሳ ዘመናዊነት በየዘመኑ ያረፈበት የከተማው ክፍል ሆኖ ሳለ ከዘመናዊ ከተማ እጅግ የራቀ መንደርና ቤቶች በውስጡ አቅፎ ኖሯል፡፡ በአንድ በኩል በመንገድ ዳር የተገነቡ ዘመናዊ የሚመስሉ ቤቶች አሉ፡፡ በሌላ በኩል ከእነዚህ ቤቶች ጀርባ ኮሽኮሽ መንደሮች ይገኛሉ፡፡ የተጎሳቆለው ፒያሳ የነዋሪውንም የከተማውንም ዕድገት ገትቶት ቆይቷል።

አዲስ አበባን እንደስሟ አበባ የማድረግ የኮሪደር ልማት ሥራ ወሳኝ ማሳያ ፒያሳ ናት። ይህ ፒያሳን የማዘመን ተግባር አምስት ተግባራትን አንድ ላይ እንዲይዝ ተደርጓል። የመጀመሪያው፥ ለነዋሪዎቿ ተስማሚ የመኖሪያ ቦታ መስጠት ነው፤ በፒያሳ በዝቅተኛ ሁኔታ ሲኖሩ ለነበሩ ነዋሪዎች በሦስት አማራጮች የመኖሪያ ቦታ ተሰጥቷቸዋል። በቀበሌና | በመንግሥት ቤቶች ለሚኖሩ ተመጣጣኝ መኖሪያ፣ ለአካባቢው ሁለንተናዊ ልማት ምቹ " ባለመሆናቸው ለተነሡ የግል ባለ ይዞታዎች ተመጣጣኝ መሬትና ካሣ፣ እንዲሁም ለተወሰነ | ጊዜ የቤት ኪራይ የሚሆን ጥሬ ገንዘብ ተሰጥቷል። ለንግድ ባለቤቶች ምትክ የንግድ ቦታ ወይም መሬትና ካሣ ቀርቧል። በዚህም ነዋሪዎቹም ሆኑ ነጋዴዎቹ የተሻለ ቦታ እንዲያገኙ አስችሏቸዋል።

ሁለተኛው፥ የአካባቢውን መሠረተ ልማት ማሻሻል ነው። ፒያሳ የተጨናነቀ አካባቢ ነው። አካባቢው አማራጭ መንገዶች አልነበሩትም፡፡ በኮሪደር ልማቱ ግን መንገዶች ሰፍተዋል፡፡ አራት አዳዲስ ጎዳናዎችም ተገንብተዋል፡፡ አካባቢው የፍሳሽ ማስወገጃ ተሠርቶለታል። ወንዞቹ ወደ መናፈሻነት ተቀይረዋል። በሺ ለሚቆጠሩ መኪኖች የሚሆኑ የመኪና መቆሚያዎች ተሠርተውለታል፡፡ በባለ ጥላ የመኪና መቆሚያና መሣፈሪያ ጣቢያዎች የተነሣ የመንገድ ላይ መጨናነቅ ቀንሷል። ተሳፋሪዎችም ከፀሐይና ከዝናብ ተርፈዋል፡፡

ሦስተኛው፥ በአካባቢው የሚገኙ ቅርሶችን መጠበቅ ነው። በፒያሳ አካባቢ የነበሩ ታሪካዊ ቅርሶች በባለሞያዎች ተጠንተው መጠገንና ለትውልድ መተላፍ ያለባቸው ተጠግነው ወደ ቱሪስት መዳረሻነት ተለውጠዋል፡፡ አንዳንዶቹም ዕሴት ተጨምሮላቸው ዛሬንና ነገን እንዲዋጁ ተደርገዋል። 126 ዓመት ያስቆጠረው፣ “የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር” የቢትወደድ ኃይለ ጊዮርጊስ ቤት፣ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት፣ በኋላም ፍርድ ቤት ሆኖ _ ያገለገለው ቤት ላይ የተደረገው የቅርስ ጥገና ለዚህ ማሳያ ነው።

አራተኛው፥ አካባቢውን ወደ ዘመናዊ የመኖሪያና የንግድ ቦታ የመቀየር ተግባር ነው፡፡ የፒያሳ አብዛኞቹ የንግድ ሥፍራዎች ከፊት የተዋቡ ቢመስሉም ከኋላ ግን አሳዛኝ ገጽታ ነበራቸው፡፡ የፒያሳ ልማት ደረጃቸውን የጠበቁ የንግድ ቤቶች እንዲኖሩ አስችሏል፡፡

CamScanner

የ አምስተኛው፥ አካባቢውን ትእምርታዊ (Land mark) ማድረግ ነው። ፒያሳ የአድዋ ሙዝየምን የመሰሉ ትእምርታዊ ዕሴት ያላቸውን ቦታዎች ጨምራለች። በዚህም የታላላቅ መሪዎች የክብር አበባ ጉንጉን ማስቀመጫ፣ የጉብኝት ቦታና የከተማዋ መለያ ሆናለች::

ዛሬ ነዋሪዎቿ በተሟላ መኖሪያ ቤት ሕይወታቸው ሲቀየር፣ ፒያሳም ጥንታዊ ቅር ከዘመናዊ ከተማ ጋር አዋሕዳ እያበራች ነው። ፒያሳ በነበራት የንግድ እንቅስቃሴ) የተጨመሩት ዘመናዊ ግንባታዎችና መሠረተ ልማቶች በከተማችን አዲስ የንግድና ግብይት ማዕከል እንድትሆን አድርገዋታል።

አዲስ አበባን ሥሉጥ የማድረግ መነሻው አገልግሎት የሚሰጡ የመንግሥት ተቋማትን ማዘመን ነው። በዚህ መሠረት በከተማ አስተዳደሩ ተቋማት አገልግሎታቸውን በማዘመን ከተገልጋይና ከተቋሞቻቸው ጋር የሚያደርጉት ግንኙነት ከፍተኛ ፍጥነት ባለው የኢንተርኔት ግንኙነት ሆኗል።

በከተማው የአገልግሎት ክፍያን እንዲሁም ንግድና ግብይትን በዲጂታል ማከናወን የተለመደ ሆኗል። የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች አስተዳደር ሥሉጥ እየሆኑ የከተማው የትራፊክ እንቅስቃሴ ደኅንነት እንዲሁም የጸጥታ አስተዳደር በዲ ቴክኖሎጂ እየተደገፈ ነው። በከተማው እየተፋጠነ ያለው የዲጂታል ሽግግር ከተ ወደ ሥሉጥ ከተማነት እየመራት ነው። አዲስ አበባ የመሠረተ ልማትና የገጽታ ተቀርፈው ለሥሉጥ ከተማ ልማት ተደላድላለች፡ አዲስ አበባን የፈጠራ፣ የመደመር መንግሥት፣ የንግድ፣ የግብይትና የቱሪዝም ማዕከል ለማድረግ ከመሠረተ ልማቶቿና ገጽታዎቿ ባለፈ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ልማቶች ወደ ሥሉጥ ከተማነት እየወሰዷት ይገኛሉ።

አዲስ አበባ ይሄንን ሁሉ ለውጥ ያመጣችው በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው። እ የሥራ ግንኙነትና ትሥሥር ከተማዋን ደማቅና ሳቢ አድርጓታል። ፈጠራ አካባቢንበ በማየትና በመረዳት ይመጣል። ፍጥነት ቀንና ማታ በመሥራት ይገኛል። የአዲስ መንገዶች፣ የቤት ግንባታዎች፣ የፓርክ ልማቶች፣ የመንግሥት ተቋማት ግንባታዎች በፀሐይ ብርሃን ሌሊት በመብራት ያለማቋረጥ በመሠራቱ የተገኙ ለውጦች ና ጊዜያችንን፣ ዕውቀታችንንና ጉልበታችንን በሙሉ ከሰጠን የማይፈጥንና የማይለወጥ እንደሌለ ያሳያል። ይሄም በሀገራችን መለመድ ያለበት ፈጣንና ትውልድ ተሻጋሪ የሥራ. ነው። በሀገራችን ብልጽግና የሚረጋገጠው ሁሉም ይህንን ባህል ገንዘብ ሲያደርግ ነው።

### 8.5. የከተማ ዕምቅ ዐቅምን መግለጥ

ከተሞችን የዕድገት አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጎ ለመጠቀም የተቀናጀ የከተማ ዕቅድ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ መምራት ያስፈልጋል። በኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ላይ የተቀናጀ የከተማ ዕቅድ መስፋፋትን በማጎልበት፣ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ፣ መሠረተ ልማቶችን በማሻሻል፣ ትልቅ ሚና አለው። በአግባቡ የተተገበረ የከተማ ዕቅድና ስትራቴጂ ዘላቂነት ያለው የከተማ ፈጠራን በማጎልበትና የነዋሪዎችን ሕይወት በማሻሻል ትልቅ ድርሻ አለው። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ምርታማነትን በማሳደግ በጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

በአግባቡ የተነደፈና የተመራ የከተማ ዕቅድ ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊ የሆኑትን የመጓጓዣ አውታሮችና የግንኙነት ሥርዓቶችን በፍጥነትና በጥራት ለማልማት ያስችላል። ይህም ምቹ የንግድ አካባቢዎችን በመፍጠር፣ ኢኮኖሚያዊ ክላስተሮችን _በማስተዋወቅና ለኢንዱስትሪ አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን በማቅረብ፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስትመንቶችን መሳብ ያስችላል።

የመንገዶችን፣ የባቡር ሐዲዶችን፣ የወደቦችንና የአውሮፕላን ማረፊያዎችን ጨምሮ የመጓጓዣ መሠረተ ልማት ዝርጋታ ግንኙነትን ያሳድጋል፤ ንግድን ያሣልጣል። የመጓጓዣ ወጪን በመቀነስ ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነትን ከፍ ያደርጋል። ቀልጣፋ የመጓጓዣ አውታሮች የሎጅስቲክስ፣ የአቅርቦት ሠንሰለት አስተዳደርንና የገበያ ተደራሽነትን በማሻሻል ኢኮኖሚያዊ

CamScanner

ዕድገትንና ተወዳዳሪነትን ያጎለብታሉ። ሁሉን አቀፍ የሕዝብ ማመላለሻ መስፋፋት፣ ተደራሽነትን ይጨምራል። የእንቅስቃሴ መጨናነቅን ይቀንሳል። የትራንዚት ኮሪደሮች ላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ፈጣን ያደርጋል። በዚህም ለጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት አስተዋጽዖ ይኖረዋል።

በሚገባ በተዘጋጀ ዕቅድ የተመራ ከተማ ውጤታማ የመሬት አጠቃቀም አለው። ትክክለኛ የሀብት ድልድልን ያሰፍናል። የመገናኛ ዘዴዎችን ያሻሽላል። የእነዚህ ድምር ምርታማነትን ያሳድጋል። እንዲሁም በከተሞች ውስጥ ለተለያዩ ነገሮች የሚውሉ ቅይጥ መጠቀሚያዎችን ማልማት ንግዶችን በመሳብ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን አነቃቅቶ ለማኅበረሰቡ አዳዲስ ዕድሎች ይከፍታል። በግንባታ፣ በከተማ አገልግሎትና በተዛማጅ ዘርፎች የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር የዜጎችን ገቢ ያሳድጋል። ዘላቂ ልማትን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ዕቅድ፣ ለነዋሪዎች ሕይወት ምቹ የሆነ አካታች መስተጋብርና አረንጓዴ ልማት ይኖረዋል። ይህም በርካታ የሥራ ዘርፎች፣ ችሎታ ያላቸው ግለሰቦችና ተቋማት ወደ ከተማው እንዲሳቡ ያደርጋል።

የተቀናጀ የከተማ ልማት ዕቅድ የኢኮኖሚ ዕድገትን በማንቀሳቀስ ምርታማነትን ያሳድጋል። እንዲሁም ዜጎች ጥራት ያለው ሕይወት እንዲኖራቸው ያስችላል። ከተሞችን በስትራቴጂያዊ ዕቅድ መምራት ቀጣይነት ያለው የከተሞች መስፋፋትንና የመሠረተ ልማት ዝርጋታን ያሳድጋል። ከተሞች ያላቸውን ዕምቅ ዐቅም በማውጣት የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ሞተር እንዲሆኑ ያደርጋል።

በብዙ የዕድገት መመዘኛዎች የሀገራችን ከተሞች ወደኋላ የቀሩ ሲሆኑ፤ ከተሞቹ የተመሩበት ስትራቴጂና የመሠረተ ልማት ግንባታ ውሱንነት የተከማቸ የቤት ሥራ ጥሎብናል። ወደኋላ ከቀረንበት የከተማ ዕድገት በፍጥነት ለመውጣት ሁለት ሥራዎችን አጣምረን በፍጥነት መሥራት አለብን። አንደኛው ዘመናዊ የከተማ መለኪያዎችን ያሟሉ ከተሞችን ማስፋፋትና ገጠሩን ከከተማ ጋር ማስተሣሠር ነው። ሌላው የለሙ ከተሞችንና መሠረተ ልማቶችን ወደ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በፍጥነት ለማሻገር የዘመናዊ ከተማ አሠራሮችን አብሮ መተግበር ነው::

የመሠረተ ልማቶች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ላቅ ያለ እንዲሆን የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ግንባታን ማፋጠንም ያስፈልጋል። በዚህም በአንድ በኩል ኋላ ከቀረንበት መሠረተ ልማት እየወጣን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የተፈጠሩ የመሠረተ ልማት ዐቅሞችን ዘመናዊ ማድረግ አለብን። ይሄን በፍጥነት በማከናወን ከተሞቻችን ፈጥነው የኢኮኖሚው ሞተርና የብልጽግና ማዕከል እንዲሆኑ ማስቻል የቤት ሥራችን ነው።

ኋላ የመቅረት ጣጣን ለመሻገር ፈጠራና ፍጥነትን ዕሴት አድርገን የአርፋጅነት ትሩፋቶችን(latecomers Advantages) መጠቀም አለብን። በዚህም ከተሞችን በአዲሱ ዘመን ዕሳቤና ግብ ማልማት፣ ፈጥኖ ሀብት ለማፍራትና ኢኮኖሚያዊ ሽግግሩን ወደፊት ለመግፋት ዐቅም ይሆናል። በመሆኑም ከተሞችን በተቀናጀ ዕቅድና መሠረተ ልማት እያለሙ ከአዲሱ የዲጂታል ዘመን ጋር መራመድ ፈጥኖ ፍሬ ለማፍራት ያስችላል። የከተሞቻችን ችግር ውሱንነት የመጠን ብቻ አይደለም። የጥራትና የፍጥነት ችግሮችም አሉባቸው።

ፍጥነትና ጥራት በጎደለው የከተማ ዕድገት የተነሣ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድሎች አምልጠውናል። በቀጣይ ከገጠር - ከተማ የሚደረገው ሽግግር የታቀደ መሆን አለበት። አዲስ አበባን ጨምሮ ትልልቅ የክልል ከተሞችን ዕድገት በፍጥነትና በጥራት መምራት አለብን። ሀገራዊ የብልጽግና ግቦቻችንን ለማሳካት የከተሞችን ዐቅም አሟጦ መጠቀምን ይጠይቃል።

የተቀናጀ የከተማ ዕቅድና ስትራቴጂ የለውጥ ሥራ አራት ብሔራዊ ግቦችን ማሳካት አለበት። የመጀመሪያው የበለጸገች ኢትዮጵያን የመገንባት ዓላማ ነው። በዚህም የነፍስ ወከፍ ገቢን ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ገቢ ማድረስና በአጠቃላይ

CS CamScanner

የልማት ትግበራ ውጤት የአፍሪካ ብልጽግና ተምሳሌት ራዕይን የማሳካት ዓላማን የያዘ ነው። በዚህ ረገድ ከተሞች ትልቅ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ የከተሞችን ዐቅም አሟጠን የምንጠቅም ይሆናል።

ሁለተኛው ግብ የሥራ አጥ ቁጥርን የመቀነስ ዓላማ ነው። ይህ ግብ ከገጠር ይልቅ ከተሞች ዘርፈ ብዙ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችል ምኅዳር ያላቸው መሆኑን ታሳቢ ያደርጋል። ይሄንን ዕድል ተጨባጭ አድርገን በበርካታ ዘርፍ በርካታ የሥራ ዕድል መፍጠር አለብን።

ሦስተኛው ግብ የመሠረተ ልማት ግንባታን ማስፋፋት ሲሆን ብዙ የኢንዱ ስትሪ ኮሪደሮችን በማልማት እንዲሁም የብዝኃ ሞዴል ሎጅስቲክስ ልማትን በማስፋፋት የከተሞችን መሠረተ ልማት የማዘመንና የማስፋት ውጥንን ይይዛል። አራተኛው ግብ የአካባቢ ጥበቃ ሥራን ማሳካት ነው። አረንጓዴ ዐሻራ፣ የወንዝ ዳርቻ ልማትና የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማት ለኑሮና ለሥራ ምቹ የሆነ ከተማ በመገንባት፣ በአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ የሚገነባ ይሆናል።

በአጠቃላይ የከተማ ዕቅድና ስትራቴጂን መሠረት ባደረጉ የለውጥ ሥራዎች፣ የመሬት አጠቃቀማችንን በማሻሻል፣ ሁሉም ከተሞች በዕቅድ መመራታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በሀገራችን የከተማን ዕቅድ የማያሟሉ ከተሞች መኖር የለባቸውም። እነዚህን የደቀቁ ከተሞች ለማሻሻል፣ በመልሶ ማልማት ፕሮጀክት አማካኝነት፣ በከተሞቹ ላይ የማዘመን ሥራ መሥራት ይጠይቃል።

በከተሞች ዕድገትና ልማት ፈተና የሆኑ ሁለት ተግዳሮቶች አሉ። እነርሱም፥ የመሬት አቅርቦትና የቤቶች ልማት ናቸው። በመሠረታዊነት ችግሩን ለመፍታት የሊዝ መሬት አቅርቦትን ማሳደግ አንዱ መፍትሔ ነው። እንዲሁም በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ የቤት ልማቶችን በፍጥነትና በጥራት በማልማት በተመጣጣኝ ዋጋና ጥራት የቤት ልማትና ተደራሽነትን ማፋጠን ይገባል።

የከተሞች ዕድገት ከቁልፍ የመሠረተ ልማቶች ዕድገት ጋር ይቆራኛል። በሀገር ደረጃ የቴክኖሎጂ፣ የኃይል፣ የመጓጓዣና የሎጅስቲክስ መሰል ልማቶች በፍጥነትና በጥራት እንዲስፋፉ ከማድረግ ጋር ይቆራኛል። የዚህ መስፋፋት የከተሞችን ዕምቅ ዐቅም በማውጣት የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሞተር እንዲሆኑ ያስችላል።

## 8.6. የከተማ አንቀሳቃሾች፡ የሽግግር መስፈንጠሪያዎች

የከተማው ዕቅድ፣ የከተሞች ማማርና የመሠረተ ልማቶች መሟላት የሚፈለገውን ፈጣን የኢኮኖሚ ሽግግር ለማድረግ ብቻቸውን አይቻላቸውም። ከእነዚህ ግብአቶች በተጨማሪ አምስት መስፈንጠሪያዎች አሉ። ከፈጠራ፣ ኢንዱስትሪና ዲጂታል ኢኮኖሚ በተጨማሪ ኢንተርፕረነርሺፕ ንግድ ናቸው። እነዚህን የከተማ የኢኮኖሚ መስፈንጠሪያዎች የመደመር መንግስት በፖሊሲና በመሠረተ ልማት ሥራዎች መደገፍ አለበት።

መሠረተ ልማት የተሟላበት ከተማ በፈጠራ አብረው ለሚሠሩ ግለሰቦች፣ ኩባንያ ተቋማት ምቹ ምኅዳር ይሆናል። በዚህ ምኅዳር ውስጥ አዳዲስ የሥራ ሐሳቦች በማፍለቅ ሀብት በማሰባሰብ የንግድና የአገልግሎት ድርጅቶችን ለማስጀመርና ታላቅ ለማድረግ ያስችላል። የከተማ ልማት ከተሞችን በማነቃቃት ኢንተርፕረነሮችን ያበዛል። ይህ ደግሞ የፈጠራንና የጀማሪ ንግዶችን ዕድገትና ቀጣይነት በማጎልበት ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

በጥሩ መልኩ የታቀደ ከተማ ለኢንተርፕረነርሺፕ የጀርባ አጥንት የሆኑትን ዕሴቶች ይ የጋራ መሥሪያ፣ ማልሚያ፣ ምርትና አገልግሎት ለገበያ ማቅረቢያ ቦታዎችና የንግድ ት መፍጠሪያ ዕድሎችን ያመቻቻል። አስፈላጊ የመሠረተ ልማት አውታሮችና  ግብ ተደራሽ ሲሆኑ፣ የስታርት አፖችን የማደግ ተስፋ ያለመልማል። እንዲሁም የዕው የሀብት ትብብርን በማሣለጥ ፈጠራን ያጎለብታል። ይሄም ከተሞቻችን ቀስ በቀለ ከተሞች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

CamScanner

ምቹ የኢንተርፕረነርሺፕ ምኅዳር ለመፍጠር ከተሞች በዕቅዳቸው የፈጠራ ማዕከ የምርምር ተቋማትንና የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችን በአንድ አካባቢ ማልማት አለባቮካ በኢንተርፕረነርሺፕ ምኅዳሩ ውስጥ ተመሳሳይነት ያላቸውን ባለ ርዕዮች፣ አ ኢንቨስተሮች እና የጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም የሥልጠና ተቋማትን በአንድ ቦታ ማስ እጅግ ጠቃሚ ነው። ይህ ሲሆን ሐሳብ እንዲጎለብት፣ ፈጠራ እንዲፋጠን በማድረግም አገልግሎትን ለገበያ ፈጥኖ ማድረስ ያስችላል።

የከተሞች ውስጣዊ ገጽታ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን ኢንቨስተሮች ለመሳብና ለማ ያስችላል። በኅብረ ባህል ትዕይንት የደመቁ፣ የብዝኃ ማንነት (ዓይነተ ብዙ ማኅበረሰብ) መገኛና ለኑሮ ምቹ የሆኑ ከተሞች፣ ከፍተኛ ችሎታና ክሂሎት እንዲሁም ሀብት ያላቸውን አካላት ለሥራና ለንግድ ይስባሉ። ከተሞች በዕውቀትና በክሂሎት የጎለበተና ስብጥርነት ያለው
የሰው ኃይል ማግኘት ከቻሉ፣ የሐሳብ ብዝኃነትን በማበረታታት የሥራ ፈጣሪነት መንፈስን ያቀጣጥላሉ።

ብዝኃነት ለከተሞች የዕድገታቸው መሠረት ነው። ጥንታዊ ከተሞች በሥልጣኔ እንዲመጥቁ ያደረጋቸው አንዱ ምክንያት ከአካባቢያቸውና ከሩቅ ሀገሮች ጭምር ልዩ ልዩ ዓይነት _ማኅበረሰቦች፣ ዐዋቂዎች፣ የፈጠራ ሰዎች፣ ፈላስፎች፣ ነጋዴዎች፣ የሃይማኖት አስተማሪዎች፣ የጥበበ ዕድ ባለሞያዎች፣ ወዘተ ወደ ከተሞቹ ለመምጣት በመቻላቸው ነው። በሀገራችንም ይህንን ዕሴት በአክሱምና በላሊበላ፣ በሐረርና በጎንደር፣ በጅማና በቦንጋ፣ በሐርላና በዳሞት፣ በይፋትና በወላይታ፣ የከተሞች ሥልጣኔዎች ውስጥ እናየዋለን።

የከተማ ልማትና የመደመር መንግሥት ምኅዳር ተደጋጋፊነትን በመገንዘብ የከተማ ልማት ንድፍና የልማት ሥራዎች ጀማሪ ቢዝነሶችንና ፈጠራን መደገፍ በሚያስችል መንገድ መቀረጽ አለባቸው። የሚያሠራ የከተማ ዕቅድና የመንግሥት ፖሊሲ፤ የኢንተርፕረነርሺፕ ሥነ ምኅዳር ይፈጥራል። ይህ ሥነ ምኅዳር ደግሞ የማይበገር፣ መሠረተ ሰፊና በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ የሚያድግ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ያስችላል።

በኢትዮጵያ ኢንተርፕረነርሺፕ በፍጥነት በማደግ ላይ ይገኛል። የኢንተርፕረነርሺፕ ሥነ ምኅዳሩ በፖሊሲ ድጋፍ ተሰጥቶት በከተማ የልማት ሥራዎች እንዲካተት ተደርጓል። ይህም ለተዋንያኑ አሣላጭ ድጋፍ ለማድረግ አስችሏል። መንግሥት የግሉን ዘርፍ ጅምር የሥራ ፈጠራ ሐሳቦችን የመደገፍ አካሄድ አጠናክሮ መቀጠል አለበት። በጥቂት ድጋፍ በብዙ ፈተና ውስጥ አልፈው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽዕኖ መፍጠር የቻሉ ኢንተርፕረነሮች በሀገራችን ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል።

በሀገራችን ኢንተርፕረነሮች በከተሞች በዲጂታል ቴክኖሎጂ የተደገፉ አገልግሎቶችንና ግብይቶችን ከማስፋፋት አንጻር አስተዋጽዖ እያደረጉ ይገኛሉ። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ ሀገራዊ ታላላቅ የዲጂታል ፕሮጀክቶችን ወስደው የሚሠሩ ኩባንያዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት እያደጉ ናቸው። ከታላላቅ ድርጅቶች ፕሮጀክቶችን የሚቀበሉ አነስተኛና መካከለኛ ኩባንያዎችም በየጊዜው እያደጉ ናቸው። እንዲሁም በርካታ ወጣቶች በግላቸው በፕሮጀክቶች ሥራዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ። የመሠረተ ልማቶች ዐቅም ማደግና የወጣቶች ክሂሎት መጨመር ታላላቅ ድርጅቶችን ወደ ሀገራችን እንዲያማትሩ አድርጓቸዋል። ጅምሩ አበረታች ቢሆንም ካለን ዐቅም አንጻር ገና አልተነካም።

የወጣቶችን ዐቅም በማጎልበትና የዲጂታል ሽግግሩን በማፋጠን፣ በኢንተርፕረነርሺፕ ያልተነካውን ዐቅም ለመጠቀም መፍጠን ይገባናል። ያልተነካውን ዐቅም ወደ ኢኮኖሚ ለመቀየር የመንግሥትና የግል ዘርፉ ትብብር ከመቼውም ጊዜ በላይ ሊጠናከር ይገባል። በመንግሥት የለሙ የፈጠራ ማልሚያና የገበያ ማፍጠኛ ቦታዎች ለበርካታ ወጣቶች ተመቻችተዋል። በግሉ ዘርፍ እንዲሁ ከፍተኛ የፈጠራ ማዕከላት እየተስፋፉ ይገኛሉ ሁሉም የፈጠራ ማልሚያ ማዕከላት ዘርፈ ብዙ ምርምር የሚያደርጉ ወጣቶችን መያዛቸው ትልቅ ተስፋ ይሰጣል። መንግሥት፣ ሐሳብ የሚለማበትንና የሚልቅበትን ቦታ ከማዘጋጀት በተጨማሪ፣ የገንዘብ ድጋፍ ምንጮችን እያሰፋ ይገኛል።

CamScanner

በሚቀጥሉት ዓመታት በወጣቶች ላይ የምንሠራው መሠረተ ሰፊ ሥራ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሥራ ፈጠራ አመለካከትና ዕውቀትን በትምህርት ሥርዓታቸው ውስጥ አካተው ያስተምራሉ፡፡ ከቀለም ትምህርቱ ጎን ለጎን ተማሪዎች የፈጠራ ሐሳባቸውን የሚያለሙበት ቦታና ግብአት እንዲሁም የሞያ ድጋፍ ተመቻችቷል፡፡ በዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትሥሥርም የተማሪዎችን ተግባራዊ ዕውቀት ማሳደግና በጋራ የምርምር ሥራዎችን በመሥራት አበረታች የኢንተርፕረነርሺፕ ዐውድ እየተፈጠረ ነው፡፡

ልጆች ከልጅነታቸው ጀምሮ ተሰጥዖዋቸውን እንዲፈልጉና እንዲያጎለብቱ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የሥርዓተ ትምህርት ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ የፈጠራ ተነሣሽነት የሚያጎለብት ትምህርትና ግብአት እንዲሁም የውድድር ዐውድ ተፈጥሯል፡፡ ሀገር አቀፍ የተማሪዎች የፈጠራ ውድድርና ሽልማት ዓመታዊ መርሐ ግብሮች እየተዘጋጁ ነው፡፡ እነዚህም ፈጣሪ ትውልድ ለመፍጠር ትልቅ ዐውድ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ከዚህም በላይ የነገዋ ኢትዮጵያ ፈጣሪዎች ማኅጸናት ናቸው፡፡

የከተሞች ልማት ለኢንተርፕረነርሺፕ ምኅዳር ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ሁሉ ኢንዱስትሪዎችን ያስፋፋል፡፡ የከተሞች መለያ የሚሆኑ የላቁ ኢንዱስትሪዎች እንዲፈጠሩ ዕድል ይከፍታል፡፡ በከተሞችና በልማት ኮሪደሮች ቁልፍ የመሠረተ ልማት አውታሮች መስፋፋት፣ ለኢንዱስትሪ ክላስተሮች መመሥረትና ማደግ የጀርባ አጥንት ናቸው ይህም የአቅርቦት ሠንሠለት አስተዳደሩን በማሻሻል በኢንዱስትሪዎች መካከል ትሥሥር ይፈጥራል፡፡

ትሥሥሩ ደግሞ የኢንዱስትሪ ሥራዎችን ቅልጥፍና ያሳድጋል፡፡ በሂደትም በከተሞች ኢንዱስትሪ ስፔሻላይዜሽን ይጎለብታል፡፡ በአግባቡ የታቀደ ከተማ ውጤታማ የሆነ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ስለሚዘረጋ የግብአት ትሥሥርና የመጓጓዣ ሎጅስቲክስን ያሳድጋል፡፡ በዚህም ተመጋጋቢ ንግድና ኢንዱስትሪዎችን በአንድ አካባቢ እንዲለሙ ያስችላል፡፡

ኢንተርፕረነርሺፕ ከተማን ለኑሮ ምቹ ከማድረግ ባሻገር በኢንዱስትሪዎች መካከል ትብብርና ዕውቀት ለመጋራት ያስችላል፡፡ ተወዳዳሪና ፈጣሪ ኢንዱስትሪዎች እንዲበዙ ያደርጋል፡፡ በኢንዱስትሪዎች መካከል ቅርርብን መፍጠር የፈጠራ ምኅዳርን ያሳድጋል፡፡ በተለይም የፈጠራ፣ የምርምርና የቴክኖሎጂ ማዕከላት መጠናከር ከፍተኛ ዕሴት ያላቸው ዕውቀት መር ልዩ ኢንዱስትሪዎች እንዲፈጠሩ በር ይከፍታል፡፡

በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ምኅዳሩ፣ ዘርፍ ተሻጋሪ ትብብርና የሥራ ፈጠራ ንግድ እየፈለሰፈና የቴክኖሎጂ ሽግግር እያካሄደ፣ ለብዝኃ ዘርፍ ኢኮኖሚ መደላድል ይሆናል፡፡ የተቀናጀ የከተማ ልማት፣ ገጠሩና ከተማውን በማስተሣሠር፣ ኢንዱስትሪዎችን በመሳብና በማሰባሰብ፣ በከተማ ንግድ እንዲበለጽግና ፈጠራ እንዲስፋፋ በማድረግ፣ ኢኮኖሚያዊ ተወዳዳሪነትን ያሳድጋል፡፡

የከተማ ልማት በከተሞች ውስጥ ንግድና የንግድ ልውውጥ እንቅስቃሴዎችን በማመቻቸት ከተሞች የኢኮኖሚ፣ ፋይናንስና የገበያ ማዕከል እንዲሆኑ ያስችላል፡ በተቀናጀ የመሠረተ ልማት የተገናኘ ከተማ ለንግድ ፍሰት፣ ለአቅርቦት ሠንሠለትና ለገበያ ትሥሥር ወሳኝ ቦታ ይሆናል፡፡ የተያያዘና የተገናኘ ከተማ ሸማቾችን፣ የንግድ ተቋማትንና ኢንዱስትሪዎችን ፍላጎትን፣ አቅርቦትንና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን መሠረት ያደረገ ማዕከላዊ አገናኝ ከበብ ይፈጥራል፡፡ ይህ ማዕከላዊ ክበብ ሰፊ የንግድና የግብይት ዕድልን ያስገኛል፡፡

ከተማና ከተሜነት ሲያድግ፣ የምርቶችንና የሸቀጦችን ጠቅላላ ፍላጎት በዚያው ልክ ይጨምረዋል፡፡ ይህም ለአምራቾችና ለነጋዴዎች ገበያን በማነቃቃት፣ ውድድር በመፍጠር የምርት መጠንንና ዓይነትን እንዲጨምሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ንግድና የንግድ ልውውጥንም ያሳድጋል፡፡ ንግድና ግብይት የሚያሣልጡ የንግድ ማዕከሎችን በከተማ ዕቅድ ውስጥ ለይቶ ማልማት እነዚህን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያስገኛል፡፡

በከተማ ውስጥ የንግድና የፋይናንስ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት እንዲሁም የንግድ አደራዳሪና አማካሪዎች በአንድ አካባቢ መሰባሰብ፣ አጠቃላይ የንግድ ሂደቱን በሁሉም መስክ ያመቻቻል፡፡ በዚሁ ቦታ የንግድ ትርዒቶች ማሳያ ቦታዎች ማስፋፋት

CamScanner

ምርትን ለማስተዋወቅ፣ ከደንበኞችና ከአጋሮች ጋር ግንኙነት ለመፍጠርና አዳዲስ የቢዝነስ ዕድሎችን ለማመቻቸት ያስችላሉ። ንግድና የገበያ እንቅስቃሴዎችን የሚደግፉ የከተማ ልማት ውጥኖች ከተሞችን የንግድ ማዕከላት በማድረግ የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሞተር ያደርጋቸዋል።

በከተሞች የሚሰሙ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቦታዎች ሁለት ነገር እንዲይዙ ተደርገዋል። የመጀመሪያው ያላቸውን ነባር ሀብት አልቆ በማውጣት ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት እንዲፈጥሩ ማድረግ ነው። በሁለተኛነት ደግሞ ከሚለሙበት ዓላማ ጋር በተጣጣመ መልኩ የንግድና ግብይት ማዕከላት እንዲኖራቸው ተደርጓል። ለምሳሌ የዐድዋ መታሰቢያ በከተማ መካከል የሚገኝ ግዙፍ የሕንፃ ትሥሥር ነው። በአንድ በኩል የኢትዮጵያውያንን ኅብረትና አንድነት ያጎላል። ትናንትን ከዛሬ ጋር በማስተሣሠር ለሕዝብ ኩራት ይሆናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ለዛሬው ትውልድ ተጨማሪ ሀብት የሚፈጥርበት ምቹና ዘመናዊ የንግድ ማዕከሎችን ይዟል። በከተሞች ሰፊው ሕዝብ የዕለት ፍጆታ የሚገበያይባቸው ማዕከላት በየአካባቢው ክረምት ከበጋ እንዲያገለግሉ ሆነው ተገንብተዋል። እነዚህ ማዕከላት ከንግድ ማዕከልነታቸው በተጨማሪ የሕዝብን ትሥሥር ያጠናክራሉ። ለባህል ልውውጥ ያገለግላሉ። የመገናኛ ማዕከላት ይሆናሉ። የወግ፣ የላንቲካና የባህል ዕቃዎችን በማስተዋወቅ የቱሪስት መዳረሻ ይሆናሉ።

በንግድና በግብይቱ ዋና ተዋናይ የሆነው የግሉ ዘርፍ የሚያለማቸው የንግድ ማዕከላት ሪል ስቴቶች፣ በከተማው በከተሞች ዕቅድ መሠረት፣ ለንግድና ለግብይት ተስማሚ ሆነው እንዲሠሩ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

በቅርብ ዘመናት የገጠመን አንዱ የሞራል ስብራት ጀምሮ ያለማጠናቀቅ ስንኩል ባህል ነው። በየአካባቢው የመሠረት ድንጋይ መጣልና መርሳት ልማድ ሆኗል። ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ ማንቀራፈፍ የሥራው ዋና ሂደት ሆኗል። ፕሮጀክቶች ከታቀደላቸው ጊዜ እጅግ መዘግየትና በዚያው ተረስተው መቅረት ዕጣ ፈንታቸው እየሆነ ነበር። የግሉ ዘርፍም ይህ ልማድ ተጋብቶበታል።

የለውጡ መንግሥት አንዱ የቀየረው ባህል ይሄንን ነው። ከማይጀመር የመሠረት ድንጋ መቆጠብ፣ የተጀመሩትን በጊዜያቸውና ከጊዜያቸው ቀድሞ ማጠናቀቅ፣ ባለፉት ዘመናት ተጀምረው የተላለፉልንን ፕሮጀክቶች ደግሞ አስፈላጊውን እርምት ሰጥቶ መጨረስ።

ባለፉት አምስት ዓመታት አዲስ አበባን ጨምሮ በሁሉም ከተሞች ተጀምረው የቆሙ ሕንፃዎች በፍጥነት ተጠናቀው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ከፍተኛ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። አንድ ሕንፃ መሠረት ወጥቶለት አንድና ሁለት ዐሠርት ዓመታትን ሳይጠናቀቅ ማቆየት የተለመደ ነገር ሆኖ ነበር። ይህ የከተማውን ገጽታ ከማጥፋት ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ጫናው ከፍተኛ ነው። ከባንክ ብድር ስምምነት ውጭ ገንዘብ ማሸሻ ሆኗል። በዚያውም ልክ ባልለሙ የከተማው ሕንፃዎች የተነሣ የንግድና የግብይት ቦታ ኪራይ እንዲወደድ አድርጓል። አካሄዱ በኢኮኖሚው ውስጥ የማይንቀሳቀስ ገንዘብ እየፈጠረ ንግድ ለመጀመር ትልቅ ካፒታል እንዲጠይቅ ሲያደርግ ነበር።

አዲስ አበባ ከዚህ ችግር ፈጥና እየወጣች ነው። ተጨማሪ ቦታዎች በመልሶ ማልማትና ጋር ትሥሥር ያላቸውን የፋይናንስ ተቋማትና የመንግሥት ተቋማት ወደ አንድ አካባቢ በኮሪደር ልማት ለንግድና ለግብይት ተስማሚ ተደርገው ለምተዋል። ከንግድና ከግብይት እንዲሰበሰቡ ተደርጓል። የመንግሥትና የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎት በአንድ አካባቢ በፍጥነት

እንዲገኙ መደረጉ የንግድና የግብይት ሥርዓትን ለማቀላጠፍ ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ ይገኛል፡

ሌላው በሀገራችን ንግድና ግብይት ውስጥ ትልቅ ለውጥ እንደሚያመጣ ታምኖ የተጀመረው የካፒታል ገበያ ነው። የካፒታል ገበያ በንግድና በግብይት ሥርዓት ውስጥ መተማመን ይፈጥራል። እያንዳንዷ ብር የማልማት ዐቅም እንዲኖራት ያስችላል። ሰፊው ሕዝብ ባለው ዐቅም ሀብት እንዲያፈራ ሥርዓት ይዘረጋል። በአጠቃላይ የሀገር ውስጥን ሀብት አሟጦ በመጠቀምም

CamScanner

ሆነ ከውጭ ሀብት በመሳብ ንግድና ግብይትን ያስፋፋል። ታላላቅ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ፣ ሐሳብ ያላቸው ሐሳባቸው ወደ መሬት እንዲወርድና ሀብት እንዲያፈሩ ያስችላል። አያሌ ኩባንያዎች እንዲፈጠሩ ምቹ ሁኔታን ያስገኛል።

በሀገራችን የንግድ ሥራን ለመጀመር ሂደቶቹ ብዙና የተወሳሰቡ ናቸው። በእነዚህ ብዙና ውስብስብ ሂደቶች ምክንያት ንግድን ለመጀመር ኢትዮጵያ ምቹ ሳትሆን ቆይታለች። እንዲህ ያለ የአሠራር ችግር ባልተፈታበት ሁኔታ የንግድ ሥራ ዕድገት አይኖርም። በመሆኑም ተሞች የንግድ ሥራ በቀላሉ የሚጀመርባቸውና የሚሠራባቸው እንዲሆኑ በርካታ የሕግና የአሠራር ማሻሻያዎች ተደርገዋል። አገልግሎቱን በሚሰጡ ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሠራር እንዲሻሻል ተደርጓል። እንዲሁም የንግድ ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓትን እንዲከተል ተደርጓል።

በአጠቃላይ ከተሞች የኢኮኖሚና የቢዝነስ ልውውጥ ማዕከል ሲሆኑ፣ ከውስጥም ከውጭም በተለያየ የሥራ መስክ የተሠማሩ ሰዎች መገናኛ ይሆናሉ። ይህም የከተሞችን ዕድገት በማፋጠን ኢኮኖሚውን የማሸጋገር ዐቅማቸውን ያሳድጋል። መንግሥት ከተሞችንና የልማት ኮሪደሮችን በመሠረተ ልማት አውታሮች ከማሳደግ ያለፈ ሥራ እየሠራ ነው። ለፈጠራና ለኢንተርፕረነርሺፕ መጎልበት የፖሊሲና የፋይናንስ ድጋፎችን ያደርጋል። የኢንዱስትሪ ክላስተሮችን በመገንባት ማበረታቻዎችን ይሰጣል። ንግድና ኢንቨስትመንት በቀላሉ የሚሠራበትን ምኅዳር ያመቻቻል፤ ይቆጣጠራል። የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን ያለማል። እንዲሁም የመደመር መንግሥት ሚናን በመጫወት፣ የኢኮኖሚ ሞተሮችን በፍጥነት እየዘወረ የኢኮኖሚ ሽግግርን ያፈጥናል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## 9. ቱሪዝም፡ አዲሱ ምሰሶ

የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ሀገራት በዘመናቸው ሁሉ የሠሩትንና ተፈጥሮ ያደለቻቸውን መልካም ገጽታ በኩራት ለዓለም የሚያስተዋውቁበት፣ ሀገሬ ይሄንን ትመስላለች የሚሉበት መድረክ ነው። ሀገርን በሚያኮራና ለሌሎች ለመጋበዝ በማያሳፍር መልኩ መገንባት፣ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ መሠረቱ ነው።

ቱሪዝም በተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ከፍተኛ የማብዛት ችሎታ አለው። ለአጠቃላይ የውስጥ ምርት ከፍተኛ አበርክቶ ያለውና ያደጉት ሀገራት ከውስጥና ከውጭ ጎብኚዎችና ተጓዦቻቸው ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙበት ኢንዱስትሪ ነው። ቱሪዝም ከነዳጅና ከኬሚካሎች በመቀጠል፣ እንዲሁም ከምግብና ከአውቶሞቲቭ ምርቶች በመቅደም በዓለም ሦስተኛው ተኛ ትልቁ

የውጭ ንግድ (Export) ኢንዱስትሪ ሆኗል።

በተለይም አውሮፓ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ከፍተኛ ዓለም አቀፍ ድርሻ ትወስዳለች። ምሥራቅ እስያ በተከታይነት፣ ሰሜን አሜሪካ በሦስተኛነት ይከተላሉ። አፍሪካ በዚህኛውም ኢንዱስትሪ ውስጥ ይህ ነው የሚባል ድርሻ የላትም።

ቱሪዝም ባለፉት ዐሥር ዓመታት ውስጥ ጉልህ ለውጦችን ያስተናገደ ኢንዱስትሪ ነው። የነፍስ ወከፍ ገቢ መጨመር፣ የቴክኖሎጂ ዕድገትና የተለያዩ መሠረተ ልማቶች ወደ ዘመናዊነት መሸጋገር፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ፣ ለእነዚህ ከፍተኛ ለውጦች በምክንያትነት የሚታዩ ናቸው። የቴክኖሎጂ ዕድገት መጓጓዣን፣ ኢኮኖሚን፣ ጤናንና ሌሎችንም ዘርፎች በከፍተኛ ደረጃ መለወጡ፣ ቱሪዝም በደንብ የተሣለጠ አገልግሎት መስጠት እንዲችልና ጎብኚዎች የተሻለ ልምምድ እንዲኖራቸው አስችሏል። የመሥመር ላይ የጉዞ ኤጀንሲዎች፣ የሞባይል መተግበሪያዎችና በሰው ሠራሽ

CamScanner

አስተውሎት ቴክኖሎጂዎች የጉዞ ዕቅድ የማውጣትና ቦታ የማስያዝ አገልግሎቶች፣ ቅልጥፍናን ከመጨመራቸው በላይ፣ የጎብኚዎቹን ምቾት በመጠበቅ፣ ኢንዱስትሪው እንዲያድግ አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ኢንዱስትሪው በሰው መዝናናት ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ፤ የሰውን ልጅ እንቅስቃሴ የሚገድቡ ጉዳዮች፣ በኢንዱስትሪው ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አሏቸው። ለዚህም ጥሩ ማሳያው የኮቪድ-19 ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ነው። ቱሪዝምን በእጅጉ አንገራግጮ፣ በኢንዱስትሪው ላይ ከፍተኛ ኪሳራ አስከትሎና ጠባሳ ጥሎ አልፏል። ይሁንና በቀውሱ ምክንያት የተፈጠሩ አንዳንድ መልካም አጋጣሚዎችም፣ ኢንዱስትሪውን በዘላቂነት የመቀየርና የማሳደግ ዕምቅ ዐቅማቸውን ከወረርሽኙ በኋላ ባሉ ዓመታት መመልከት ችለናል።

የርቀት ሥራ በኮቪድ ምክንያት ተስፋፍቷል። ሥራን ለመሥራት የግድ በተለምዷዊ የሥራ ቦታዎች መገኘት በአብዛኛው አስፈላጊ አለመሆኑ በተግባር ታየ። በዚህም የትም ሆኖ መሥራት (Digital Nomadism) ተስፋፋ። ይህም በኢንዱስትሪው ላይ ዘላቂ በጎ ተጽዕኖ ካሳረፉ ጉዳዮች አንዱ ነው። ዛሬ ተጓዦች በርቀት ለመሥራት ምቹ ሁኔታዎችን የሚያቀርቡ መዳረሻዎችን ይመርጣሉ።

የነገው የቱሪዝም ኢንዱስትሪን የዕድገትና የድርሻ ሁኔታን ከሚወስኑ ጥቂት ነገሮች መካከል አንዱ ከፍተኛ መጠን ያለው የመካከለኛ ገቢ ማኅበረሰብ በተለይም በሩቅ ምሥራቅና በአፍሪካ መፈጠሩ ነው። ሌላኛው ደግሞ የቴክኖሎጂ የምጥቀትና የተግባራዊነት መጠን ነው። እስከ አሁን በቱሪዝም ውስጥ በጎብኚነትም ይሁን በአስጎብኚነት ከፍተኛውን ድርሻ እየወሰዱ ያሉት የአውሮፓ ሀገራት ናቸው። በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ይህ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ይቀየራል ተብሎ ይጠበቃል። በተለይም የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት ከፍተኛ የጎብኚነት ድርሻን ይወስዳሉ። አፍሪካም ቀላል የማይባል አበርክቶ እንደሚኖራት ይጠበቃል። ይህ ሁኔታ የትም ሆኖ ከመሥራት ጋር ሲጣመር ደግሞ ጉብኝትና ሥራ አንድ ላይ ይመጣሉ። ስለዚህም እየተዘዋወረ የሚሠራ አዲስና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ ይፈጠራል።

በሌላ በኩል ደግሞ ቴክኖሎጂ የዕለት ተዕለት የሰው ልጅ እንቅስቃሴን እየደገፈና እያቀለለ ስለሚሄድ፣ ከጊዜ፣ ከደኅንነት፣ ከጤና፣ ከገንዘብና ከሌሎች ምቾቶች አንጻር ትልቅ በጎ ተጽዕኖ በቱሪዝም ላይ እንደሚፈጥር ይገመታል።

በዚህ በጎ ተጽዕኖ ምክንያትም ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያድግ ይጠበቃል። ቴክኖሎጂ በሌሎች ኢንዱስትሪዎች አልፎ ከሚፈጥረው ምቾት ባለፈ፣ ቀጥታ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ውስጥም ትልቅ በጎ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ለዚህም ምናብን ከእውነታ ጋር አቀናጅተው የሚያቀርቡ ቴክኖሎጂዎች ቀዳሚውን ሚና ይጫወታሉ።

አፍሪካ ሰፊ የባህልና የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖሯትም ለቱሪዝም ዕድገት ምቹ ያልሆኑ በርካ ጉዳዮችም አሉባት። በተለይም ከመሠረተ ልማትና ከጸጥታ ጋር የተያያዙ ዕንቅፋቶች ኢንዱስትሪው እንዳያድግና ያላት ተጠቃሚነት እንዲቀንስ አድርገውታል። እንቅስቃሴ ያላቸው በጣት የሚቆጠሩ ሀገራት ቢኖሩም፤ ከዓለም የቱሪዝም ገበያ አንጻር እነሱም እዚህ ግባ የሚባል ውጤት ያላቸው አይደሉም። ዋናው ጉድለት የመሠረተ ልማት ጉዳይ ነው። መሠረተ ልማቶች በተሟሉባቸው ቦታዎችም ቢሆን ግን ያን ያክል ጎብኚዎች አለማስተናገዳችን ችግሩ ከዚያም የዘለለ እንደሆነ ጠቋሚ ነው። የፖለቲካ አለመረጋጋትና የደህንነት ስጋቶች ሌሎች ምክንያቶች ተደርገው የሚቆጠሩ ናቸው።

መላው አፍሪካ የሰላም እጦት ሰለባ አይደለም። ይልቁንም ብዙ ሀገራት ከሌሎች የዓለም አካባቢዎች የተሻለ ሰላም ባለቤቶች ናቸው። ነገር ግን ያም ቢሆን በኢንዱስትሪው ያላቸው ተሳታፊነት ከእነዚህ ሀገራት አንጻርም አነስተኛ ነው። ዋነኛው የአፍሪካ የቱሪዝም ችግር፣ ኢንዱስትሪውን በሚገባ ካለመረዳትና ሀገርን በመልካም ሁኔታ ገንብቶ ለዓለም ካለማሳየት የሚመነጭ ነው።

CS CamScanner

እንደ አፍሪካ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች የቱሪዝም ዕድገት በውጭ ቀጥኛ ኢንቨስትመንት፣ በገጠር ልማት፣ በንግድ፣ በግብይትና በመሠረተ ልማት ዕድገት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ያደርጋል። ድህነትን በመቀነስ ረገድም ትልቅ ድርሻ ያበረክታል። በመሆኑም በቱሪዝም ላይ መስራት ለአፍሪካ ዕድገት የዕድል በር ነው።

የቱሪዝም ልማት መጓጓዣዎችን፣ የከተማ ኔትዎርክን፣ ሆቴሎችን፣ ሙዚየሞችን፣ የጥበባተ ዕድ ሥራዎችን፣ የንግድ ቦታዎችን፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎችን፣ የባህልና የኩነት ቦታዎችንና ሌሎችንም በከተማና በቱሪዝም መስሕቦች አካባቢ እንዲለሙ ዕድል ይፈጥራል። ይህም ገጠርን ከከተማ የሚያገናኙ መሠረተ ልማቶች እንዲስፋፉ ከማድረግ ጎን ለጎን፣ አዳዲስ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር የገጠር ዕድገት እንዲፋጠን ያስችላል። እንዲህ ባለ ዕሳቤ የሚመራ የቱሪዝም ልማት፤ የፈጠራ ኢንዱስትሪውን በማጎልበት፣ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ትልቅ ድርሻ ያበረክታል።

## 9.1. ተስፋን መትከል፣ አቧራን ማራገፍ፣ ውበትን መግለጥ

ጉብኝት በሀገራችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ አይመስልም። ነገር ግን ዘመናዊ የቱሪዝም ታሪካችን እንደ አብዛኞቹ ኢንዱስትሪዎች የቅርብ ጊዜ ጅማሮ ነው። “የዐሥራ ሦስት ወራት የፀሐይ ብርሃን ጸጋ የሚሉት ፖስተሮች የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያን የማስተዋወቅ ጥረቶችና የዘመናዊ ቱሪዝም ጅማሮ እንደሆኑ ታሪክ ይነግረናል። በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የተጀመረው
የቱሪዝም ሥራ፣ የተለያዩ ተግዳሮቶት ሲገጥሙትም፣ በደርግም በኢሕአዴግም ቀጥሏል።

ይሁንና ቱሪዝም በሀገራችን ሊያገኝ የሚገባውን ያህል ትኩረት የተነፈገው ዘርፍ እንደነበር ውጤቱ ይነግረናል። በታሪክም ሆነ በተፈጥሮ ችሮታ ከእኛ ጋር ሊወዳደሩ የማይችሉ ብዙ ሀገራት፣ ከኢንዱስትሪው ብዙ አትርፈዋል። እኛ ግን ዕንቁዎቻችንን ደብቀን፣ ታሪካችንን አቧራ አልብሰን ለዘመናት ቆይተናል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪክ፣ በባህልና በተፈጥሮ ሀብቶች የታደለችና እነዚህ ተዋሕደው ጊዜ የማይሽረው ኅብረ ቀለም ያለበሷት ናት። ሁሉም ዓይነት የቱሪዝም ሀብቶች የሚገኙባት፣ የቱሪዝምና የኪነ ጥበብ ሙዚየም ናት።

ታሪኳንና ቅርሶቿን ገልጦ ለተመለከተ፣ መልክአ ምድሯን ለቃኘ፣ በማኅጸኗ ያቀፈቻቸውን እንስሳት፣ አዕዋፍና ዕጽዋት ዓይኑን ገልጦ ላሰሰ፣ የሕዝቦቿን ባህል፣ ትውፊት፣ ፍልስፍና፣ በማስተዋል ለመረመረ፤ ኢትዮጵያ የመስሕቦች ማንጸሪያ፣
የልዩነት አጽናፍ ማስረጃ ናት' ከዳሎል እስከ ራስ ዳሽን ያሉ ልዩ ልዩ ዓይነት መልክአ ምድሮች አሏት። በአንድ በኩል ከባሕር ጠለል በታች እጅግ ዝቅተኛውንና ሞቃታማውን ሥፍራ ይዛለች። በሌላ በኩል ደግሞ በበረዶ የተሸፈኑ ተራራማና ብርዳማ ሥፍራዎች አሏት። እነዚህ ሁለቱን በአንድ ጉብኝት ማግኘት የሚቻልባት ሀገር ናት። በዓለም ረዥሙ ወንዝ ዓባይ የሚነሣው ከኢትዮጵያ ነው። የአፍሪካ የውኃ ማማ በሆነችው ሀገራችን፣ ታላቁን የምሥራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆና በውስጡ የያዛቸውን ሐይቆች፣ ዕጽዋት፣ እንስሳትና አዕዋፍ ለመጎብኘት ምቹ ሀገር ናት። ኢትዮጵያ ብዙ ወንዞችና ሐይቆች ያሏትና
የአያሌ የውኃ ውስጥ ሕይወት ናት። መገኛዎች፣ የጥንታዊ ታሪክ ማኅደሮችና ለመዝናኛ መዋል የሚችሉ አካባቢዎች ባለቤት ናት።

ከብዝኃ ሕይወት አኳያም በኢትዮጵያ እጅግ ብዙ ልዩ ልዩ የዕጽዋት ዓይነቶች አሉ። በሀገራችን ብቻ የሚገኙ(ብርቅዬ) ዕጽዋትም ቁጥራቸው ከፍተኛ ነው ። የሀገራችን ከፍተኛ ቦታዎች በዓለም ላይ በመጥፋት ላይ ለሚገኙ የዕጽዋት ዝርያዎች መናኸሪያዎች ናቸው።

ለብዙ ቱሪስቶችና ተመራማሪዎች መስሕብ የሚሆኑ፣ በርካታ የአዕዋፍና የእንስሳት ዝርያዎችም ባለቤት ናት269 27።

እነዚህ ሁሉ ጸጋዎች ለምግብ፣ ለጤና ምርምርና _ ለአገልግሎት ከሚሰጡት ጥቅም ባሻገር፣ የእንስሳትና የአዕዋፍ መመልከቻ ቦታዎችን ካስፋፉን፣ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ግዙፍ ሀብት ናቸው።

CS CamScanner

ከሀገራችን ጥንታዊነት የሚመነጩ በአራቱም ማዕዘናት የሚገኙ ታሪካዊ ቅርሶቻችን ሌሎቹ ወሳኝ የቱሪዝም ዕቅሞቻችን ናቸው። ጥንታውያን የአምልኮ ቦታዎች፣ አብያተ መንግሥታት፣ ጥንታውያን ከተሞች፣ ታሪካዊ ቦታዎች፣ ታሪካዊ የጽfiፍ

ቅርሶች፣ ታሪካዊ የወግ ዕቃዎች፣ እንዲሁም ዘመናዊ ቅርሶች ባለቤት ነን"። የኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛነት በርካታ ፓሌንትሮፖሎጂያዊና አርኬዎሎጂያዊ ቅርሶች እንድንታደል አድርጎናል። የደች አክሱም የአርኬዎሎጂ ጥናት ከተደረገበት እ.አ.አ. ከ1906 ጀምሮ ኢትዮጵያ የአርኬዎሎጂና የፓሌንትሮፖሎጂ ጥናት ውጤት የሆኑ አያሌ ቅርሶች አሏት።

የሀገራችን ብዝኃነት ትሩፋት የሆኑትና ህያው ሙዚየም ያሰኟት ባህላዊ መስሕቦቻችን ልዩ ሀብቶቻችን ናቸው። የየብሔረሰቡን ባህል፣ ወግ፣ ትውፊት፣ አኗኗር የሚሳዩ በርካታ የቱሪስት መስሕቦች አሉን። በየባህሉ በእጅና በአነስተኛ አካባቢያዊ ቴክኖሎጂዎች የሚሠሩ ጌጣ ጌጦችና አልባሳት፣ የጥበባተ ዕድ ሀብቶችም ትልቅ ዕምቅ የቱሪዝም መስሕብ ናቸው።

በዓለም ልዩ ከሚያደርጉን ሀብቶቻችን ውስጥ የምግብ ልማዶችና ባህሎቻችን አንደኛዎቹ ናቸው። ኢትዮጵያ ብዝኃ ማንነት ያለባት ሀገር መሆኗ አንዱ ያስገኘላት ዕሴት በተለያዩ አካባቢዎችና ማኅበረሰቦች የሚዘወተሩ ልዩ ልዩ ዓይነት የምግብ

አማራጮች መኖራቸው ነው። እነዚህ የምግብ አማራጮች በአብዛኛው በተፈጠሯዊ(Organic) አመራረት የብሔረሰቡ የተመረቱ ናቸው። የአትክልት፣ የሥራሥርና የዱር ፍሬዎችን እንደ አማራጭ ለማግኘ ጽያ በየአር የሚቻልባቸው ናቸው። እነዚህን ሀብቶች ማወቅ፣ ማጥናትና ማስተዋወቅ፣ ብሎም በገበያ እንደልብ እንዲገኙ ማድረግ በዓለም ላይ እየተዘወተረ ለመጣው የምግብ ቱሪዝም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ጎብኚዎች ሰፋ ያለ በጀታቸው ለምግብ የሚያውሉ እንደመሆኑ፣ የምግብ ቱሪዝም ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ የሚገኝ ሲሆን ሀገራችን ከዚህ አንጻር ሰፊ ዕምቅ ዕቅም አላት።

ትዕይንታዊ ሀብቶቻችንም ለብዙ ዘመናት ባህላዊና ሃይማኖታዊ በሆነ መንገድ ሲከወኑ ሩ የኢትዮጵያ የቱሪስት መስሕቦች ናቸው። የሕዝቦችን ትውውቅና ትሥሥር ለሚያሳድጉ፣ ባህልንና ቅርስን ለመጠበቅ የሚረዱ እንደ የዘመን መለወጫዎች፤ የጥምቀት፣ የኢሬቻ፥ የአረፋ፤ የአዋ የፈረሰኞች ትርዒት፣ ዓይነቶቹን የያዘ ነው። ከኪነ ጥበባዊ ቅርሶችም አኳያ ሀገራችን የሙዚቃ፣ የሥዕል፣ የቅርጻ ቅርጽ፣ ሀብታም ናት።

ኢትዮጵያ ከዋሻ ላይ ሥዕሎች ጀምሮ እስከ ዘመናዊ ሥዕሎች ድረስ ከ5ሺ ዘመን የበለጠ የሥነ ሥዕል ታሪክ አላት። የተቀመረና በኖታ የተገለጠ ዜማ በማዘጋጀት ከዓለም ቀደምቶቹ ተራ የሚያሰልፋት የቅዱስ ያሬድ ዜማ ባለቤት ናት።

በየብሔረሰቡ ዘንድ ልዩ ልዩ የጭፈራ፣ የዜማ ስልትና የሙዚቃ መሣሪያዎች ይገኛሉ። ኢትዮጵያ በየአርኬዎሎጂው ቦታ ከተገኙት ቅርጻ ቅርጾች አንሥቶ በየብሔረሰቡ እስካሎት የቅርጽ ጥበቦች የተሞላች ናት።

ይሁንና ይህ ሁሉ ሀብት አቧራ ለብሶ፣ ለሀገራችን ይህ ነው የሚባል የገቢ ምንጭ ሳይሆን፣ በከንቱ ዘመናትን አስቆጥሯል። አምላክ ብዙ ተፈጥሯዊ ውበት አላብሶን ሳለ፣ እንደ ተራ ነገር ጥለነው ኖረናል። የቀደምቶቻችን ድካምና ልፋት፣ የብዙ አስገራሚ ታሪክ ባለቤቶች ቢያደርገንም፣ ቅርሶቻችን በየቦታው ወድቀውና በየሀገሩ ተበትነው ቀርተዋል። አቧራቸውን የሚያራግፍ፣ የኔ የሚላቸው ባለቤት አጥተዋል። አንዳንድ ጊዜም ሌሎች በድፍረት ባለቤት ሆነው ሲጠቀሙበት ይታያል።

የድል ታሪኮቻችንንም በተመለከተ ለተወሰኑት በየዓመቱ ከምናደርገው ዝክር ባለፈ፣ ብዙም ቦታ አልሰጠናቸውም። የብዙ ባህሎች መናኸሪያ ብንሆንም፣ እንኳን ለጎብኚዎች ልናደርሰው ይቅርና እኛ እንኳ በቅጡ አናውቃቸውም። በአጠቃላይ ብዙ እያለን፤ ምንም እንደሌለን ሆነን የምንኖር ነን።

## 9.2. ከቱሪዝም ማዕድ ለመጋራት፡ ዝግጁነት

CS CamScanner

ከዓለም የቱሪዝም ማዕድ መጋራት ብዙ ዝግጁነትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ለዚህም የአውሮፓና የምዕራቡ ዓለም በኢንዱስትሪው ላይ ያላቸው የበላይነት፣ እንዲሁም በቅርቡ አስገራሚ ዕድገት ባለቤት የሆኑት የሩቅ ምሥራቅ ሀገራት ወደ ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ፍጥነት መቀላቀላቸው በቂ ማሳያ ነው። ለቱሪዝም ዝግጁ መሆን፣ የጎብኚዎችን ፍላጎት ከመረዳት ጀምሮ መዳረሻ ቦታዎችን ምቹ አድርጎ እስከመገንባት ይደርሳል። መሠረተ ልማቶችን ከመዘርጋት ሥልጡን አገልግሎት እስከመስጠት ይሄዳል። ይህንን በዘላቂነት ማንበር፣ ይህንን ሁሉ የሚያሣልጥ ስትራቴጂ መንደፍንና ሕጋዊ መሠረቶችን መጣልን የሚያጠቃልል ጉዳይ ነው።

መደመር ከምናብ የሚጀምር፣ አሻግሮ ተመልክቶ ተስፋን የሚዘራ፣ ዛሬን ከትንሹ የሚጀምር፣ ዘላቂና የማይነትብ አድርጎ የሚሠራ ፍልስፍና መሆኑ ከታየባቸው ዘርፎች መካከል የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዋነኛው ነው። ትንሿ ዘር ተዘርታ እንዴት ዋርካ አክላ፣ ለብዙዎች መጠለያ፣ ማረፊያና መደገፊያ እንደምትሆን አይተንበታል። ከቤተ መንግሥት የጀመርነው የፓርክ ሥራ ዛሬ በእያንዳንዱ ክልል ተዳርሷል።

በጥቂት ጊዜና በትንሽ ሀብት ከግቢ ማስዋብ የጀመርነው የፓርክ ግንባታ ዛሬ የሰፋፊና እጅግ አስደማሚ ፓርኮች ባለቤት አድርጎናል።

የቱሪዝም መደመራዊ አመራር የተጀመረው ከአራት ኪሎ ነው። ከመቶ ዓመታት በፊት በዳግማዊ ምኒልክ ከተመሠረተው ከአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት። ቤተ መንግሥቱ ሰፊ ይዞታ ያለውና በውስጡ የግብር አዳራሽ፣ ዙፋን ቤት፣ ዙፋን ችሎት፣ ዕንቁላል ቤት የንግሥት ዘውዲቱና የእቴጌ ጣይቱ ቤቶችና ሌሎችንም የያዘ ነው። ይህ ቤተ መንግሥት በኋላ ላይ

በወታደራዊ መንግሥት ጊዜ፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መኖሪያና የጉባኤ አዳራሾች

ተጨምረውለታል። ለውጡ ሲመጣ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤትና አዳራሾቹ የተሻለ አገልግሎት እየሰጡ ነበር።

የተቀረው የግቢ ክፍል ግን በአሮጌ ቆርቆሮ ቤቶች የተሞላ ሲሆን፣ በቅርስ ደረጃ የሚታዩት ነባር ቤቶች አርጅተው በመፍረስ አደጋ ላይ ነበሩ። እነዚህ ከመቶ ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ ሕንጻዎች ተራ የማዕድ ቤት ግልጋሎት እየሰጡ፣ የማብሰያና የመመገቢያ ሥፍራዎች ሆነው ቀርተው ነበር።

በ‹‹ገበታ ሸገር›› የተመራው ተነሣሽነት፣ ከአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ጀምሮ እንጦጦና ወዳጅነት ፓርክን፣ አብርሆት ቤተ መጻሕፍትን፣ የአንድነት ፓርክ የመኪና ማቆሚያን ያዳረሰ ነው። በግል ባለ ሀብቶች፣ በመንግሥትና በባለሞያዎች የጋራ አስደማሚ ጥረት ሥራው ተሳክቷል። ረጅም ዓመታት ሊወስድ የሚችለው ሥራ፣ በመደመር ዕሳቤ በሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቋል። በአራት ኪሎ ቤተ መንግሥት ለሚገኙ ጥንታዊ ሕንጻዎች እድሳትና ጥገና በማድረግ የማንበር ሥራዎች ተሠርተዋል። አዳዲስ አገልግሎቶች ተጨምረዋል።

ከጥንቱ ታሪካችን በተጨማሪ የዛሬዪቱን ኢትዮጵያ መልክ የያዙ የክልሎች እልፍኞች፣ የእንስሳትና የዕጽዋት ማሳያዎችና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ተገንብተዋል። ግቢውንም ለተጠቃሚዎች ምቹ የማድረግ ሥራዎች ተሠርተዋል። እነዚህን

ዕሴቶች በመጨመር ኅብረ ብሔራዊ ትሥሥራችንን በልጆቻችን ኅሊና ለመገንባት እንዲቻል ፖርኩ “አንድነት ፓርክ” ተብሎ ተሰይሟል።

በአዲስ አበባ ካከናወንናቸው ቁልፍ የቱሪዝም ልማቶች አንዱ የመስቀል ዐደባባይ” ቅርስን ማንበርና ማዘመን ነው። የመስቀል ዐደባባይ ፕሮጀክት ታሪክን፣ ተዝናኖትንና ጤናን የማስተሣሠር ፕሮጀክታችን አንዱ መገለጫ ነው። ዐደባባዩ ለሃይማታዊና ባህላዊ ክዋኔ የበለጠ ምቹ ተደርጓል። የዐደባባዩን ደረጃ የማሳደግ፣ የመኪና ማቆሚያ ግንባታ፣ ቦታውን ለአገልግሎት ምቹ የማድረግ ሥራዎች ተሠርተዋል።

CS CamScanner

ዛሬ መስቀል ዐደባባይ የቱሪስት መዳረሻ፣ የሃይማኖትና የሌሎች ባህላዊ ኩነቶች ማከናወኛ፣ የወጣቶች የስፖርት ማዘውተሪያ፣ የአረጋውያን ማረፊያ፣ ሆኗል። የዐደባባዩ ፊተኛው ክፍል ሰፍቶ ለትርዒት ምቹ ተደርጓል።

የዓድዋ ሙዝየምንም ከአዲስ አበባ ልማት ጋር አስተሣሥረን ገንብተናል። ዐድዋ የአፍሪካ ድል ነው። አፍሪካውያን ቅኝ ግዛትን ፈጽሞ እንደማይቀበሉ ያሳዩበት ድል ነው:: ኢትዮጵያውያን ደግሞ የራሳቸውንና የአፍሪካንም ነጻነት ለማስከበር ያላቸውን ቁርጠኝነት ያመለከቱበት ድል ነው። ነገር ግን ለ50 ዓመታት ያህል ይህን ድል የሚመጥን ማዕከል አልነበረውም።

የዐድዋ ሙዝየም መፈጠር በዐድዋ መንፈስ ትውልዱን ለመገንባት፣ የፓን አፍሪካዊነት ስሜት ለትውልዱ ለማስገንዘብ ይረዳል። የትውልድ መገናኛ ማዕከል በመሆንም ያገለግላል። ሀብት በመፍጠርም ለራሱና ለከተማው አስተዋጽዖ ያደርጋል። መሪዎች ኢትዮጵያን ሲጎበኙ የአበባ ጉንጉን የሚያስቀምጡበት ታሪካዊ ሥፍራም ተፈጥሯል። አብረውት የተገነቡት የንግድ ሥፍራዎችም ዘመናዊ የንግድ እንቅስቃሴንና ሥርዓትን የሚያሣልጡ ናቸው።

የዐድዋ ሙዝየም ግንባታ ከአካባቢው ጋር በመሠናኘቱ ዐድዋ ከፍ ብሎ እንዲታይ አድርጎታል። ግንባታው የዐድዋ ዘመቻ በተጀመረበት ከአራዳ ጊዮርጊስ ፊት ለፊት ባለው ሜዳ እንዲሰራና ከነባሩ የዳግማዊ ሚኒሊክ ሐውልት ጋር እንዲናበብ በመደረጉ ታሪክና ቅርስ ተታጥሞ እንዲሄድ አስችሏል።

በመዲናችን አዲስ አበባ በዋናነት ከሚጠቀሱት የጎብኚዎች መስሕቦች መካከል አንዱ በአዲስ መልክ የታደሰው ብሔራዊ ቤተ መንግሥት ነው። በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የኢትዮጵያን ታሪክ የያዙ ቅርሶች፣ የወግ ዕቃዎች፣ የዲፕሎማሲ ማሳያዎች፣ መኪናዎች፣ መዛግብት፣ መጻሕፍት፣ ወዘተ ይገኛሉ። ላለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመት በከፊል የመሪዎች መኖሪያ ከመሆን ባለፈ ለሕዝብ ዝግ ሆኖ ቆይቷል።ቅርሶቹም በተጨናነቁ ቦታዎች፣ በቆርቆሮዎችና በሜዳዎች ተቀምጠው ዘመናትን ገፍተዋል።

በብሔራዊ ቤተ መንግሥት በርካታ ዋና ዋና ሥራዎችን ሠርተናል። የመጀመሪያው፥ ሀብትን ማወቅ ነው። ለግማሽ ክፍለ ዘመን በቤተ መንግሥቱ ተቀምጠውም ሆነ ተጥለው የሚገኙ ሀብቶች ምንድን ናቸው? ለምንስ ሊጠቅሙ ይችላሉ? የሚለው በባለሞያዎች በዝርዝር እንዲታወቅ ተደርጓል።

ሁለተኛው፥ ሀብትን የመለየት ሥራ ነው። ከተገኙት ሀብቶች መካከል በግምጃ ቤት መቀመጥ ያለባቸው፣ ለሙዝየም መቅረብ ያለባቸው፣ ለሙዝየም ባይቀርቡም በየክፍሎቻቸው ተሠድረው መቀመጥ ያለባቸው ሀብቶች ተለይተዋል።

ሦስተኛው፥ መልሶ ግንባታ ነው። የቤተ መንግሥቱ ሕንጻ እንደ ጠላት ገንዘብ ተጥሎ ስለኖረ ብዙ ጉዳት ደርሶበታል። በመሆኑም ታሪካዊነቱን ሳይለቅ ከሦስት ዓመታት በላይ የፈጀ የጥገና ሥራ ተሠርቷል። በተለያዩ የጥገና ሥራዎች እንደታየው ጥቂት ጊዜ ቢቆይ ኖሮ የከፋ አደጋ ይደርስበት ነበር።

አራተኛው፥ ግቢውን የማስተካከል ሥራ ነው። ግቢው እንደሚታሰበው አልነበረም። ብዙው ቦታ በዳዋ የተዋጠ፤ የፍርስራሽና የቆሻሻ መከመሪያ ነበር፡ የአገልግሎት መስጫ ጥንታዊ ቦታዎቹ ዝገው፣ አርጅተውና ከጥቅም ውጭ ሆነው ነበር። ግቢው ሕይወት እንዲዘራበት የተለያዩ ሥራዎች ተሠርተዋል።

አምስተኛው፥ ተጨማሪ አገልግሎቶችን መጨመር ነው። የጎብኝዎች መቀበያ ማዕከላት ተሠርተዋል። የመኪና ማሳያ ትዕይንት ተገንብቷል። በዚህም በቆርቆሮ ቤቶች ውስጥ መስሕቦች . . . የነበሩትን መኪኖች፣ ፉርጎዎችና ሠረገሎች ወደሚገባቸው ሥፍራ ለመውሰድና ለዕይታ ለማብቃት አስችሏል። ታሪካዊ ቦታዎችን ከጤናና ከተዝናኖት ጋር በሚያስተሣሥረው የሥራ መርሐችን መሠረት፣ በግቢው ውስጥ ሆቴሎች፣ ካፍቴሪያዎች፣ ስቲምና ሳውና ቤቶች፣ የሥዕል ማሳያዎች፣ ወዘተ ተገንብተዋል። በግቢው ውስጥ በእግር ለመዝናናት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችም ተፈጥረዋል።

CamScanner

ስድስተኛው፥ የቤተ መንግሥት ሙዝየም ማደራጀት ነው። የሙዝየም ዕቃዎችን በመምረጥና በመሠደር፣ የታሪክ ፈለግ በማዘጋጀት፣ ባለሞያዎችን በማሠልጠንና ቤተ መንግሥቱን ለጎብኝዎች ጉዞ ምቹ በማድረግ ሙዝየሙ ተዘጋጅቷል።

ታሪካዊ ቅርሶችን ከማደስና የቱሪስት መስሕብ ከማድረግ በተጨማሪ በአዲስ አበባ አምስት ዕውቀት ተኮር ማዕከላት ተገንብተዋል። አብርሆት ቤተ መጻሕፍት፣ ሳይንስ ሙዝየም፣ የሀገር በቀል ዕጽዋት ማሳያ፣ የአንድነት ቤተ መዛግብትና የማዕድን ሙዝየም። የሁሉም ዓላማ የዕውቀት ሙዝየሞችን ማስፋፋት ነው። የመጀመሪያው፥ የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ሲሆን፣ ትእምርታዊ በሆነና ጥበብን በሚገልጥ ሕንጻ ውስጥ ይገኛል። አካባቢው የሕዝብ መገናኛና ማረፊያ እንዲሆን ክፍት ተደርጓል። የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ደረጃውን የጠበቀ፣ ወጣቶችን ሊስብ የሚችል፣ ዲጂታል አማራጮችን ያካተተ ማዕከል ነው። የአብርሆት ቤተ መጻሕፍትን አርአያ በማድረግ ተመሳሳይ አብያተ መጻሕፍት በየክልሉ እየተገነቡ ናቸው።

የሳይንስ ሙዝየም ሁለተኛው የዕውቀት ሙዝየም ነው። የተገነባበት ዓላማ የሳይንስ ፈጠራን ለማበረታታት ነው። ሳይንሳዊ ሥራዎች የሚታዩበት፣ የሳይንስ ትርዒቶች የሚቀርቡበት፣ የሳይንስ ፈጣሪዎች የሚገናኙበት፣ ወጣቶችና አዳጊዎች የሳይንስ ሥራዎችን የሚለማመዱበት ማዕከል እጥረት ነበረብን። የሳይንስ ሙዝየም ይህን ያቃልላል።

ሦስተኛው፥ በአንድነት ፓርክ ውስጥ የሚገኘው የዕጽዋት ማሳያ ሥፍራ ነው። ኢትዮጵያ የብዙ ዕጽዋት ዝርያዎች ሀገር ናት። ማዕከሉ በሂደት እነዚህን ዝርያዎች ለማሳየት የተፈጠረ ነው። በተለይም ልጆችና ወጣቶች የሀገራቸውን የተፈጥሮ ሀብት እንዲያውቁ፣ እንዲመራመሩና አዳዲስ ነገሮችን እንዲቀምሙ ዕድል ይፈጥርላቸዋል።

አራተኛው፥ የአንድነት ቤተ መዛግብት ነው። የውጫሌ ውልን ጨምሮ እጅግ ጥንታዊ የሆኑ ሰነዶች ይገኙበታል። ለታሪክ ተመራማሪዎችና በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ምርምር ማድረግ ለሚፈልጉ ሁሉ ከፍተኛ ሀብት የያዘ ነው። እነዚህን ሀብቶች በመለየት፣ ከደረሰባቸው በላይ ጉዳት እንዳያገኛቸው ዘመናዊ በሆነ መልኩ እንዲደራጁ ተደርጓል። ከቤተ መዛግብትነት በተጨማሪ ለጎብኚዎች የሚሆን ዐውደ ርዕይና ለተመራማሪዎች ደግሞ አነስተኛ ቤተ መጻሕፍት ተዘጋጅቶለታል።

አምስተኛው፥ የማዕድን ሙዝየም ነው። የኢትዮጵያን የማዕድናት ሀብት ለማሳየት፣ በየአካባቢው የሚገኙ ማኅበረሰቦች አንጡራ ሀብታቸውን ዐውቀው ለልማት እንዲያውሉ ለማበረታታት፣ ወጣቶችና ልጆች የሀገራቸውን ጸጋ ዐውቀው እንዲያድጉ ለማድረግ የተቋቋመ ነው። በውስጡ በኢትዮጵያ የሚገኙ ማዕድኖችን የሚያሳይ ንድፍ፣ የማዕድኖች ናሙናዎች፣ ማዕድናትን ለማልማት የተደረገውን ጥረት፣ የሚያሳዩ ትዕይንቶች ተካተውበታል።

CS CamScanner

መተሐራ የሚገኘው የቤኑና ሪዞርትና በጅማ ጥንታዊ ቤተ መንግሥት ግቢ የሚሠራው ሆቴል ሌሎቹ ማሳያዎች ናቸው። ታሪክን፣ ተፈጥሮን፣ ማኅበረሰብንና መዝናኛዎችን አቀናጅተውም ተገንብተዋል።

ወንጪ ገጸ ምድሯ እስትንፋስን ቀጥ የሚያደርግ መግነጢሳዊ ኃይል የረበበባት ናት። ውብ የተፈጥሮ ገጽዋ ውለው ቢያድሩባት፣ ደጋግመው ቢመለከቷት የማትሰለች አድርጓታል። እንዲህ ያለ ያማረ ቦታ ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት ቢገኝም፣ ከቦታው ለመድረስ አመቻ የመሠረተ ልማት ባለመኖሩ፣ የቅርብ ሩቅ አድርጓታል። የአካባቢው ማኅበረሰብም ዕድሉን ወደ በረከትነት መመንዘር ሳይችል ቀርቷል።

ገበታ ለሀገር በተራራ የተከበበችውን በኮረብታ የተከፈለችውን ወንጪን ተራራዋን ገምሶላታል። ኮረብታዋን ቆርጦላታል፣ መዳረሻዋን አመቻችቶ፣ ምቹ ውበቷን አገናኝቶ አድምቋታል። ደረጃውን የጠበቀ የመንገድ፣ የመብራትና የቴሌኮም አገልግሎቶች አግኝታለች። የወንጪ ልማት ገጠርን ከከተማ አስተሣሥሯል። የወንጪ ሪዞርት ግንባታ የአካባቢውን ጥንታዊ ታሪክ፣ ውብ መልክአ ምድር፣ ማኅበረሰብና አዲሱን ሪዞርት ያስተሣሠረ ነው።

ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የኃይል፣ የተፈጥሮና የባህል ማማ ነው። ከአዲስ አበባ 450 ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኘው የተቀናጀ የኮይሻ ፕሮጀክት፣ በደቡብ ጋሞ፣ በምዕራብ ጅማ፣ በሰሜን የጎጀብ ተፋሰስ እንዲሁም በምሥራቅ ወላይታን ይጎራበታል። ኮይሻ ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክን፣ ሐላላ ኬላን፣ የጊቤ 3ና የኮይሻ ሰው ሠራሽ የተፈጥሮ ሐይቅን በማስተሣሠር የአካባቢውን ተፈጥሯዊ መስሕብና ባህል ከፍ ያደርገዋል። አካባቢው የተፈጥሮ ኅብር የሚታይበት የተፈጥሮ ሙዝየም ነው። የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ዓላማ ይህንን የተፈጥሮ ዕምቅ ዐቅም አጉልቶና አድምቆ በማውጣት ለኢትዮጵያውያንና ለዓለም ማበርከት ነው።

እንዲሁም በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በጣና ምዕራባዊ ዳርቻ የተዘረጋው የገበታ ለሀገር የጎርጎራ ፕሮጀክት ተፈጥሮንና ታሪክን አሠናሥሎ ለአካባቢው ድምቀትና ሞገስ ሆኗል። ጥንታዊ ታሪክን፣ የጣናን የውኃ ሥፍራ፣ ታሪካዊ ገዳማትን፣ የደንቢያን የግብርና ምርቶች፣ ጎርጎራ እንደ አንድ የቱሪዝም መዳረሻ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ለሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችም የጎንደርንና የባሕርዳርን ከተሞች የሚያስተሣሥር ማዕከል ነው የጎርጎራ ሪዞርት። ማዕከል ሆኗል።

በኮይሻ፣ በሐላላ ኬላ፣ በወንጪና በጎርጎራ የተከናወኑ የልማት ሥራዎች መሠረተ ልማትን ለአካባቢው አድርሰዋል። አዳዲስ ሀብቶችን ከነባር ጸጋዎች ጋር አያይዘዋል። በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ አድርገዋል። ቅርስን ለመጠበቅና ለማስተዋወቅ አስችለዋል። የቱሪስት መዳረሻ ልማትን አስፋፍተዋል። አካባቢውን አስተዋውቀዋል። የገጠር አካባቢዎችን ከከተማ ጋር አስተሣሥረዋል። ይህም የዘመናዊት ኢትዮጵያ ግንባታን የሚያፋጥን፣ ለዘመናዊ ቱሪዝም ኢንዱስትሪም መንደርደሪያ የሚሆን ዐቅም ነው።

በተጨማሪም የቱሪዝም ውድድር ዓለም አቀፍ ጎብኚዎችን ወደ ሀገር ለመሳብ የሚደረግ ግብግብ እንደመሆኑ፣ የምንገነባው መሠረተ ልማት ከተወዳዳሪ ሀገራት አንጻር ሚዛን የምንደፋበት እንዲሆን ይጠበቃል። ከዚህ አኳያ የምንሠራቸው የዲጂታል፣ የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ፣ የውኃና መሰል መሠረተ ልማቶች በተቻለ መጠን ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲከወኑ ለማድረግ ሞክረናል።

በአዲስ አበባ ጀምረን ወደ ክልል ከተሞች ያስፋፋነው የኮሪደር ልማት ከተሞቻችንን ለሕዝባችን ውብና ማራኪ አድርጎ ከማቅረብ በተጨማሪ፣ የጎብኚዎችን ምቾት ለመጠበቅና ርካታቸውን ለመጨመር ያለመ ነው። ለዚህም በአዲስ አበባ የገነባናቸውን የቱሪስት መስሕቦች በኮሪደር ልማቱ ለማስተሣሠር ተሞክሯል። በክልሎችም የሚለሙ ተመሳሳይ ኮሪደሮች፣ በዚሁ መርሕ መሠረት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

CamScanner

ጎብኚዎችን ከማስተናገድና መልሰው መልሰው የሚጎበኙን ደንበኞች አድርጎ ከማስቀረት አንጻር፣ በተለይም የግል የአስጎብኚ ድርጅቶች ከተለምዷዊው መንገድ መውጣት አለባቸው። ዘርፉ የሚጠይቀውን ደረጃ የሚያሟሉ፣ ብዙ ቋንቋ የሚናገሩ፣ ስለሚያስጎበኙት ጉዳይ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸውና ጎቢኚዎችን በሚገባ የሚያስተናግዱ አስጎብኚዎችን ማፍራት ይጠበቅባቸዋል።

ከአስጎብኚዎችም ባለፈ፣ ሆቴሎችና ሬስቶራንቶች ባህላዊ ምግቦቻችንን በሚገባ ለማስተዋወቅ የሚያስችል ሞያና የተለያዩ ሀገራት የምግብ አሠራሮችን በሚገባ ጠንቅቀው የሚያውቁ የምግብ ባለሞያዎችን ማፍራት ይኖርባቸዋል። ጎብኚዎች የባይተዋርነት ስሜት እንዳይኖራቸው እንደቤታቸው እንዲሰማቸው የማድረግ ኃላፊነትም አለባቸው። እነዚህን ለናሙና ያህል አነሣን እንጂ ጎብኚዎችን በሚዘዋወሩበት ቦታ ሁሉ፣ ተገቢውን ክብርና መስተንግዶ ሰጥቶ ማስተናገድ ጨዋነታችንን፣ እንግዳ አክባሪነታችንንና ሥልጣኔያችንን ያሳያል። የሀገራችንን ገጽታ በበጎ ይገነባል። የለፋነው ልፋት ሁሉ መቋጫው

መስተንግዶ እንደመሆኑ፣ ክፍተቶቻችንን ነቅሶ አውጥቶ በተለየ ትኩረት ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

በአጠቃላይ እነዚህን ሁሉ ዝግጅቶች ማድረጋችን፣ እዚህ ግባ የማይባለውን የሀገራችንን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ታሪክና ነባራዊ ሁኔታ ከሥር መሠረቱ እየቀየረው ነው። ሀገራችን ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ጥቅም እንድታገኝ እያስቻለም ነው።

ዕምቅ የጎብኚዎች መስሕብ ዐቅም የሆኑትና እንደ ተራ ነገር አቧራ ለብሰው የተደበቁትን ዕንቁዎቻችንን አቧራቸውን አራግፈንና ውበታቸውን ገልጠን እያሳየን እንገኛለን። በዚህም ለራሳችንም፣ ለጎረቤቶቻችንም እንዲሁም በየትኛውም የዓለም ጫፍ ላሉ ሁሉ ክፍትና ተደራሽ እያደረግናቸው ነው። በአንድ በኩል የመንፈስ ርካታና ደስታን መሸመት አለ። በዚያም ውስጥ የሀገርን ገጽታ መገንባት ይከናወናል። ብሎም የሀገርን ኢኮኖሚ መደገፍ ይቻላል። እነዚህ ዋነኛ ግቦቻችን ናቸው።

## 9.3. ተስፋን ማለምለም፡ የቱሪዝም እመርታ

ቱሪዝም በዓለም አቀፍ መድረክ ትርጉም ያለው ቦታ አለው። የምሥራቅና የምዕራብ ኢኮኖሚ መመጣጠን የቱሪስቱን ብዛትና ዓይነት ጨምሮታል። ለቱሪዝም ያለን ሀገራ ዕምቅ ዐቅማችንም ከፍተኛ ነው። ይህንን በመረዳት በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ውስጥ ከተቀመጡት አምስቱ ዓምዶች መካከል አንዱ እንዲሆን አድርገናል።

ኢንዱስትሪው በሀገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ውስጥ ትልቅ አስተዋጽዖ እንዲኖረው እንፈልጋለን። የመጣውን መልካም ዕድል ወደሚጨበጥ ጥቅም ለመቀየር፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት፣ በፈጠራ እና በተግባራዊ ፍጥነት በርካታ መዳረሻዎችን አልምተናል። በከተማና በገጠር የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎችን አቀናጅተናል። እንዲሁም ነባር የጎብኚ መዳረሻዎችን አሻሽለናል። አዳዲስ መዳረሻዎችንም አልምተናል። እነዚህ ሁሉ በተለየ ትኩረት ከሠራንባቸው የለውጥ ማሳያዎቻችን መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

ሀገራችን ከዚህ በፊት ከነበሯት የጎብኚ መዳረሻዎች ላይ በእነዚህ ጥቂት ዓመታት ብዙ ጨምረናል። መዳረሻዎቹም መላው ሀገራችንን ያካለሉ ናቸው። ከሀገራችን ስፋትና ከሀብት እጥረት አንጻር ያልደረስንባቸውና በዕቅድ ላይ ያሉ ብዙ መዳረሻዎችም በቀጣይ ይገነባሉ።

በእጃችን ላይ ያሉ የጎብኚ መዳረሻዎችን በሚገባ አገልግሎት ላይ ማዋልና ከዚህም ሊገኝ የሚችለውን ሀገራዊ ጥቅም ሁሉ መሰብሰብ ተገቢና በቀጣይ ለምንጓዘው አቅጣጫ ትልቅ ግብአት የሚሆን ነው። ከዚህ አንጻርም ብዙዎቹን በፍጥነት ወደ ሥራ አስገብተናል። ትሩፋቶቹንም እያጣጣምን እንገኛለን።

CS CamScanner

በእነዚህ ጥረቶች ምክንያት ሀገራችንን የሚጎበኙ የውስጥም ይሁን የውጭ ጎብኚዎች ቁጥር በጥሩ ሁኔታ እያደገ ነው። ይሁንና ዘርፉ ከፍተኛ ዕድገት እንዲያስመዘግብ ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል።

ሀገራችን ከቱሪዝም ልታገኛቸው የምትችላቸውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አካባቢያዊ ጥቅሞች ሁሉ ከቀረው ዓለም ጋር ተወዳድራ እንድታገኝ፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጎብኚ ወደ ሀገራችን መሳብ አለብን። ለዚህም የተለያዩ ስልታዊ መላዎችን(Strategies) ነድፈን እየተንቀሳቀስን እንገኛለን።

የመጀመሪያው ግብ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን በከፍተኛ ቁጥር መጨመር ነው። በአሁኑ ወቅት ካሉን ጎብኚዎች በብዙ እጥፍ ለማሳደግ ዐቅደን እየሠራንበት ነው። ከዚህ ጋር የተቆራኘው ሁለተኛው ግባችን ደግሞ ጎብኚዎች በሚኖራቸው ቆይታ እጅግ የሚረኩበትን ከባቢና ሁኔታ መፍጠር ነው። ከመሠረተ ልማትም ይሁን ከሌሎች አስፈላጊ ነገሮች አንጻር፣ የተሟላና የተሳካ ቆይታ እንዲያገኙ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን በየመዳረሻዎቹ ለመፍጠር እየሠራን ነው።

ሦስተኛው ግብ ደግሞ በጎብኚዎች አስደሳች ቆይታ ውስጥ ከጎብኚዎች - ሊገኝ የሚችለውን የገቢ መጠን ማሳደግን ጨምሮ ሌሎች ትሩፋቶችን በላቀ ሁኔታ ማግኘት ነው።

ለዚህ ደግሞ ብዙ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ መልካም አጋጣሚዎች አሉ። የመጀመሪያው የዓለም የቱሪዝም ኢንዱስትሪ በከፍተኛ ደረጃ ያደገ መሆኑና በሚቀጥሉት ጊዜያትም ኢንዱስትሪው በከፍተኛ ደረጃ እያደገ እንደሚመጣ የሚጠበቅ መሆኑ ነው። በተለይም የሩቅ ምሥራቅና የአፍሪካ ሀገራት የመካከለኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ከመበራከት የተነሣ ከእነዚህ ቦታዎች የሚነሡ ጎብኚዎች ቁጥር በእጅጉ እንደሚጨምር ተገምቷል፡

ይህ ሁኔታ ቀድሞ በምዕራባውያን የበላይነት ተይዞ የነበረውን የጎብኚነትም ሆነ የተጎብኚነት ኢንዱስትሪያዊ ሁኔታ በተወሰነ መልኩ ወደ አዳጊ ሀገሮች ያዞረዋል። በአግባቡ ከተጠቀምንበት፣ ከምዕራቡ ከሚመጣው በተጨማሪ የእነዚህ አህጉራት ጎብኚዎችን ገበያ ልንሻማ የምንችልበት ዕድል አለ።

ሌላኛው ዓለም አቀፋዊ መልካም አጋጣሚ፣ ዓለም በተለያዩ አቅጣጫዎች የመኪና መንገዶችን እየገነባ መሆኑ ነው። ከእነዚህም ውስጥ የቻይናው ዓለም አቀፋዊ መሥመር (Belt and Road)፣ እንዲሁም ከግብጽ ካይሮ ተነሥቶ እስከ ደቡብ አፍሪካ ኬፕታውን የሚደርሰው የትራንስ አፍሪካ ጎዳና (Trans-Africa Highway) ይገኙበታል።

ከትራንስ አፍሪካ መንገዶች አንዱ ሀገራችንን አቋርጦ ያልፋል። ከብዙ አልያም በቅርብ ርቀት መያያዝ የሚችል መንገድ ነው። የቻይናው መንገድ እስከ ጅቡቲ ወይም እስከ ኬንያ ይመጣል። ከሌሎች ዘርፎች በተጓዳኝ ሁለቱንም መንገዶች በሚገባ ለቱሪዝም መጠቀም እንችላለን።

ሀገራዊ ጥንካሬዎችንና ዕድሎችን ስንመለከት፣ የለሙና ወደ ሥራ የገቡ ወይም በቅርቡ የሚገቡ በዛ ያሉ መዳረሻዎች አሉን። በየመዳረሻዎቹ በቂ መሠረተ ልማት እየተዘረጋ ነው። እንዲሁም ወደፊት ልናሰማቸው የሚችሉ ብዙ ዕምቅ የቱሪዝም ሀብት ባለቤቶች ነን። በአጠቃላይም ለቱሪዝም ተገቢውን ዕውቅና መስጠታችን በቀዳሚነት የሚነሣ ነው።

ሁለተኛ አፍሪካንና የተቀረውን ዓለም የሚያገናኝ የሰማይ ድልድይ የሆነው አንጋፋው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው። ከአየር መንገዳችን የተነሣ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ በር ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ መግቢያና መውጫ በር ሆናለች። ወደ ኢትዮጵያም ይሁን ወደ አፍሪካ የሚገቡ፣ እንዲሁም ከአፍሪካ ወደ ተቀረው ዓለም የሚጓዙ ቀላል ሚልዮን ተጓዦች በዚህች በር ያልፋሉ። ከእነዚህ መንገደኞች የተወሰኑት፣ ለቀጣይ በረራቸው ከተወሰኑ ሰዓታት እስከ ቀናት በአዲስ አበባ ሊቆዩ ይችላሉ። ይህንን በሚገባ መጠቀም ከቻልን፣ ብዙ ተጓዦች ሀገራችንን እንዲጎበኙ ለማድረግ ዕድሉ አለን።

CamScanner

በአዲስ አበባና በዙሪያዋ እንዲሁም በሌሎችም የክልል ከተሞች በገበታ ፕሮጀክቶች የሠራናቸውና በሌሎች የልማት ሥራዎቻችን እየሠራናቸው የሚገኙ መዳረሻዎች ይህንን ታሳቢ አድርገው የተሠሩ ናቸው። ከአየር መንገድም አንጻር ምቹ፣ ዘመናዊና በቂ የሆነ የአውሮፕላን ማረፊያ ለመፍጠር የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

በመጀመርያውን የቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያን ማስፋትና ማዘመን ነው። የቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ተጨማሪ መንገደኞችን ለማስተናገድና ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለመስጠት እንዲችል ሆኖ እየተስፋፋ ነው።

ሁለተኛው ዘመናዊና ብዙ መንገደኞች ማስተናገድ የሚችል ዓለም አቀፋዊ የአውሮፕላን ማረፊያ መገንባት ነው። ይሄም ከአዲስ አበባ በቅርብ ርቀት በቢሾፍቱ አካባቢ ሥራው ከተጀመረ ነው። እንዲሁም የሌሎች አውሮፕላን ማረፊያዎቻችንን ደረጃ ማሻሻልና ለዓለም አቀፍ በረራ ምቹ ማድረግ በስፋት እየሠራንበት የምንገኘው ጉዳይ ነው።

ሦስተኛው ሀገራዊ ዕድል ደግሞ፡ አዲስ አበባ የዲፕሎማቶች ከተማ መሆኗ ነው። በዚህ _ ዕድሏም የተነሣ የተለያዩ ኩነቶችን ለማስተናገድ ዕድል አላት። በተለያየ ጊዜም ብዙ ፖለቲካዊም ሆነ ማኅበራዊ ኩነቶችን ስታዘጋጅ የቆየች ከተማ ናት። ይሄንን ዕድል በቱሪዝም ቅኝት በሚገባ መጠቀም ከቻልን፣ በኩነት ቱሪዝም ከፍተኛ ተጠቃሚ እንሆናለን። እንዲሁም ከብዜት ውጤቱ ብዙ ጎብኚዎችን ማግኘት እንችላለን።

በመሆኑም እነዚህን ምቹ ሁኔታዎች ጥንካሬዎችና መልካም አጋጣሚዎች በሚገባ በመጠቀም፣ ከሁሉ በላይ ሀገራችንን በከፍተኛ ደረጃ ማስተዋወቅ ይኖርብናል። በመቀጠል ወደ ሀገራችን የሚመጡ ጎብኚዎች በከፍተኛ ርካታ አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻል ይኖርብናል። እንዲሁም ከምንሰጠው አገልግሎት የምናገኘውን ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ አለብን። ለዚህ ደግሞ ከብዙ ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት ወሳኝ ነው።

ሀገራችንን የማስተዋወቅ ጉዳይ ብዙ መልኮችና መንገዶች ኣሉት። እስከ አሁን በነበረን ታሪክ ከምንታወቅባቸው ጉዳዮች አብዛኞቹ ወደ አሉታዊ የሚያደሉ ናቸው። ይሁንና በተወሰነ መልኩም ቢሆን እንደ ኦሎምፒክ ስፖርት ባሉ መድረኮች መልካም ስም የገነባንባቸው መስኮች አሉ። አሉታዊውን መቀየርና በጎውን ደግሞ እያሻሻሉ መቀጠል የዚህ ዘመን የቤት ሥራ ሆኗል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያ ነገር የሚገደው ሁሉ፣ እንደ ግለሰብም ይሁን እንደ ቡድን ወይም እንደ ሀገር፣ ከተማ፣ ድርጅት ወይም ማኅበር፤ ሀገሩን የማስተዋወቅ ኃላፊነት አለበት።

ለዚህም የመጀመሪያው ርምጃ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም በሚገባ እንዲስፋፋና ባህል ሆኖ እንዲወጣ ማስቻል ነው። የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም፤ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ማሳደግ ግዙፍ የብዜት ውጤት አለው። በሀገራችን ለተለያዩ በዓላት

በተለይም ሃይማኖታዊ _በዓላት ወደ ተለያዩ ቦታዎች መዘዋወር የተለመደ ነው። ይህ ደግሞ ለውስጥ ቱሪዝም እንዱ አስቻይ ሁኔታ ነው። ይህንንና ሌሎች መሰል አስቻይ ሁኔታዎችን ተጠቅመን ተጓዦች በየአካባቢው ያሉ የቱሪስት መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ ማስተዋወቅና የተለያዩ ማበረታቻዎችን ማድረግ፣ ሀገርን ማወቅ፣ ማክበርና መውደድን ጨምሮ ውጤቱ ብዙ እጥፍ ነው። ለምንገነባው ህብረ ብሔራዊ አንድነትም መደላድል ይፈጥራል።

መንግሥት በተለየ መልኩ አዋጭ የሆኑ መንገዶችን ለይቶ፣ ለተገቢ ታዳሚዎች አስፈላጊውን የማስተዋወቅ ሥራ እየሠራ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥም የተለያዩ ተነሣሽነቶችን ከመጀመር አንሥቶ፣ የተለያዩ ሀገራዊ፣ ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ኩነቶችን እያዘጋጀን ነው። ወደፊትም ለማዘጋጀት ብዙ ጥረቶችን እያደረግን እንገኛለን። በተናጠል የሚሠሩ ማስታወቂያዎች ብዙ ጥቅም ቢኖራቸውም፣ በቅንጅት ሲሠሩ ደግሞ የበለጠ አመርቂ ውጤት ያመጣሉ። ስለዚህም ከሌሎች ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ብዙ መሥራት ይጠበቃል።

CamScanner

ከማስተዋወቅ ጎን ለጎንም ጎብኚዎች ወደ ሀገራችን እንዲመጡ የሚያበረታቱ ብዙ ምቹ ሁኔታዎች(ቪዛን ጨምሮ) መፍጠር ወሳኝ ነው። ሀገራችንን መጎብኘት ምን ያህል ትልቅ ዋጋ ያለው ጉዳይ መሆኑን ማሳየትና ጎብኚዎች ከሌሎች መዳረሻዎች ይልቅ ሀገራችንን እንዲመርጡ የተቻለንን ያህል መጣር ይኖርብናል።

ሀገራችንን ለማየት ፈቃደኛ ሆነው የሚመጡ ጎብኚዎች፣ ምርጥና የማይረሱት ጉብኝትና ልምምድ እንዲሆንላቸውና በከፍተኛ ርካታ ከሚያስታውሷቸው ጉብኝቶች ቀዳሚው የእኛ እንዲሆን አስበን መሥራት ይጠበቅብናል። ከዚህ አንጻር በመዳረሻዎች የሚኖር መሠረተ ልማት በተለየ ትኩረት የማይቆራረጥ አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል፣ የጸጥታና ደኅንነት ሥጋትን ሙሉ በሙሉ መቅረፍ፣ እንዲሁም ምቹ የመስተንግዶ አገልግሎት መስጠትና ጎብኚዎች የቤተኛነት ስሜት እንዲያድርባቸው ማድረግ ያስፈልጋል። በጉብኝቱ የተሰማቸውን ርካታ መለካትና ማስተካከያዎች ካሉ በፍጥነት ማስተካከል፣ እንዲሁም ጨርሰው ከተመለሱም በኋላ በተለያዩ መንገዶች ግንኙነታችንን ማስቀጠል፤ የወደፊቱን ርካታ ቀድሞ የመሥራት አካል ነው።

ከቱሪዝም የሚገኝ ገቢን ከፍ ማድረግ የዚህ ሁሉ ጥረት ዋነኛ ግብ እንደመሆኑ፣ የተለያዩ አገልግሎቶችን በማቅረብ በመዳረሻዎችና በአጠቃላይ ሂደቱ ልናገኝ የምንችለውን ገቢ ከፍ ለማድረግ መጣር ይኖርብናል። ለዚህ ደግሞ ከግል ዘርፉ ጋር በመጣመርና በመደገፍ በልዩ ፈጠራና ፍጥነት፣ በኢንዱስትሪው ውስጥ ትልቅ ሚና እንዲኖራቸው ማስቻል ወሳኝ ነው።

ቀደም ብለን እንዳየነው ኢትዮጵያ በቱሪዝም ሀብቶች የበለጸገች ሀገር ናት። እያንዳንዱ ረዳ ቢዳሰስ የቱሪዝም ሀብቶች የሌሉት አካባቢ የለም። እነዚህን ወደ ኢኮኖሚያዊ ድቤት ለመቀርየር ዕምቅ ዐቅሞቻችንን ለይቶ ማወቅ፣ በቅንጅት ማልማት፣ ማስተዋወቅና ማህበር አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር ብዙ ዐቅሞችን ከመለየት አንሥቶ፣ ብዙ መዳረሻዎችን በግንባት ረገድ የተሻለ ርቀት ተጉዘናል። ካለን ሀብት አንጻር ግን ብዙ ይቀረናል። የነባቸውን እያስተዋወቅን፣ በእነርሱ

አገልግሎት እየሰጠንና እያነበርን፣ ተገቢውን ገቢ እንነበስባለን። በዚህም አዳዲስ ዐቅሞችን እንለያለን፤ እንገነባለን፣ በሂደቱም የበለጸገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ቱሪዝም ዋነኛው ምሰሶ ሆኖ ይቀጥላል።

# ክፍል ሦስት

## የፖለቲካ ስክነት፤ የኢኮኖሚ ሥምረት

CamScanner

# ምዕራፍ ዐሥር

## 10. የፖለቲካ ስክነት

ከትናንት እስከ ዛሬ የሀገራችን ዘመናዊ የፖለቲካ ጉዞ ስክነት የጎደለውና መግባባት የተሳነው ነው። ይህም ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዋጋ እያስከፈለን ቀጥሏል። መንግሥታት በየዘመናቸው ያቀዱት የዕድገትና የልማት ውጥን እንዳይሳካ ያደረጉ በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም በሀገር ውስጥ የፖለቲካ ስክነትና መግባባት አለመፈጠር ትልቅ ድርሻ አለው።

በአዳጊ ሀገራት የፖለቲካ ስክነት ማጣትና የመግባባት እጦት የመንግሥታትን ትኩረት ከኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ፕሮግራሞች እያናጠበው ይገኛል። እዚህም እዚያም የሚለኮሱ ፖለቲካዊ እሳቶችን በማጥፋት፣ ወርቃማ የለውጥ ጊዜ ይባክናል። ይህም በጊዜ መቀደምን ያመጣል። ከዚያም በላይ ችግሮቹ ሌላ ችግር እንዲወልዱና እንዲባዙ አድርጓል።

### 10.1. ከራስ የተሻገረ የፖለቲካ ዓላማ

ፖለቲካ ለሐሳውያን ባልተገባ መልኩ የግል ፍላጎት ማስፈጸሚያ፣ የሀብትና የጥቅም በር ነው። ለእውነተኞች ግን ከራስ የተሻገረ የጋራ ፍላጎትን ማስፈጸሚያ መንገድ ነው። ፖለቲካ ስለጋራ ጉዳዮች የሚወሰንበት መንገድ ነው። ፖለቲከኛ ደግሞ በጋራ ጉዳይ ላይ ብዙኃኑን የሚመለከትን ነገር ለመወሰንና በውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ዕድል ያገኘ ሰው ነው።

እውነተኛ ፖለቲከኛ ግላዊ ፍላጎትን ከማርካት ባሻገር፣ የጎረቤቱን፣ የአካባቢውን፣ የሀገርንና የዓለምን ደኅንነት ለማረጋገጥና ለውጥ ለማምጣት በግሉና ከሌሎች ጋር ተባብሮ በዓላማ ይንቀሳቀሳል። ፖለቲካ ከራስ ተሻግሮ የጋራ ዓላማን ለማስፈጸም የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። እውነተኛ ፖለቲከኞች ከራሳቸው ስሜትና ፍላጎት ተሻግረው የማኅበረሰቡን ደኅንነትና ምቾት ለማረጋገጥ የሚተጉ ናቸው።

የሰው ልጅ በታሪኩ ሁለት ነገሮችን በግሉ ለማሳካት አልቻለም። የጋራ ደኅንነትንና ፍትሕን። እነዚህ ሁለቱም ከሌላ አካል በሚደርስ በጎ ወይም ክፉ ነገር ተጽዕኖ ሥር የወደቁ ናቸው። በዚህ ምክንያት ሰዎች ለጋራ ደኅንነትና ለፍትሕ ሲሉ በጋራ መሥራትና በጋራ መታገል አስፈለጋቸው። በጋራ ለመሥራት መንግሥትን፣ በጋራ ለመታገል ደግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ተቋማትን መሠረቱ።

ሰዎች መሰባሰብ ያስፈለጋቸው ፖለቲካዊ ግቦች በተናጠል ማሳካት ከሚችሉት በላይ ስለሆኑ ነው። በተናጠል ያለባቸውን የህልውና ክፍተትና ጉድለት በመሙላት፣ የተጠናከረ ህልውና መፍጠርና በተሻለ ሁኔታ ፍላጎቶቻቸውን ማርካት እንዲቻላቸው ነው። ፖለቲካ በተፈጥሮው የሰው ልጆች በጋራ ሲኖሩ በጋራ ጉዳዮቻቸው ላይ ውሳኔ የሚሰጡበት መንገድ

ነው?።

በፖለቲካ ውሳኔ ላይ ከሕዝቡ ጀምሮ የተለያዩ አካላት፣ በተለያየ ደረጃና መልክ ተሳትፎ ያደርጋሉ። መንግሥታዊ ሥልጣን የያዙና ለመያዝ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ተዋንያን የሚሰጡት ውሳኔና የሚያደርጉት እንቅስቃሴ፣ በብዙኃኑ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ነገር ግን ፖለቲከኞች ብቻ ሳይሆኑ መገናኛ ብዙኃን፣ ምሁራን፣ የማኅበረሰብ መሪዎችና የመንግሥታትን ሌሎችም የፖለቲካ ተጽዕኗቸው ግለሰባዊ ሳይሆን ማኅበረሰባዊ ነው። ከዚህ በተጨማሪ እዚህም እዚያ ማኅበራዊ መገናኛ የተለያዩ ግለሰቦች ከራሳቸው ተሻግረው ማኅበረሰባዊ የፖለቲካ ተጽዕኗቸው ከፍ እንዲል አድርጎታል።

በመሆኑም በፖለቲካ የሚሳተፍ እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከራሱ አልፎ በሌሎች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርግ መሆኑን ማወቅ ይገባዋል። የተጽዕኖውን ሁኔታ ዐውቆ በኃላፊነት ስሜት ድርጊቱን መመርመር አለበት። በዋናነትም

CamScanner

ፖለቲከኞች ፖለቲካ ከራስ ተሻግሮ ሰዎች በጋራ ለመኖር የተሰባሰቡባቸውን የጋራ ፍላጎትና ደኅንነት ለማረጋገጥ ሚያ፣ የሀብትና የሞት የምንተጋበት መድረክ መሆን አለበት። የፖለቲካ እንቅስቃሴ በእንቅስቃሴው ውስጥ ከሚሳተፈው ግለሰብ በላይ በብዙኃኑ ላይ ተጽዕኖ አለው። ስለዚህም የፖለቲካ ተሳትፎዎች ከግለሰብ ስሜት፣ ጥቅምና ፍላጎት የተሻገረ መነሻ ሊኖራቸው ይገባል።

ፖለቲካ የማኅበረሰብ ችግሮችን በመፍታት፣ የጋራ ከፍታን ለማረጋገጥ የሚከወን ነው። ከጊዜያዊ ግብና ከሥልጣን ቆይታ በላይ ነው። ዘላቂ ግብና ዓላማን ያነገበ፣ አቧራን በማስነሣት ከሚገኝ ጊዜያዊ ድጋፍ የሚልቅ ነው። ዐሻራን በማኖር የሚፈጠር ዘላቂ ለውጥን የሚተልም ነው። ፖለቲከኞችም ከራሳቸው ተሻግረው የብዙኃኑን ፍላጎት ለማርካት የሚሠሩ መሆን አለባቸው።

ይሁንና በሐቅ ከራስ የተሻገረ ዓላማን ለማሳካት የሚደረጉትም ይሁን ፖለቲካን ለግላዊ ፍላጎት ማሳኪያ የሚጠቀሙት፣ ሽፋናቸው ሕዝባዊ ፍላጎትና ዓላማ ነው። እንዲያውም _ በተገላቢጦሹ በፖለቲካ ውስጥ ግላዊ የሥልጣን ጥምን ለማርካትና የሀብት ፍላጎትን ለመሙላት የሚደረገው ጥረት፣ ሕዝባዊ ዓላማን ካነገበው በላይ ለሕዝብ ተቆርቋሪና የዓላማው አስፈጻሚ መስሎ ይታያል።

ግላዊ ጥቅምና ፍላጎት ከማርካት ባሻገር እውነትንና ሁኔታን ከሀገራዊ ጥቅምና ፍላጎት አንጻር ከመመልከት ይልቅ፤ በስሜትና በእልህ በመመራት የሚደርሰው ጥፋትም ቀላል አይደለም። በልሂቃን ዘንድ የሚታየው የከረረ ቁጣ፣ ስሜትና እልህ ዘርፈ ብዙ ጥፋቶችን ያስከተለ ነው። ስሜትን በመግራትና እልህን በማብረድ ነገሮችን ከፍ ካለው ዓላማ አንጻር አለመመልከት፣ ብዙ ዕድሎች እንዲመክኑና ዘርፈ ብዙ ፈተናዎች ተደራርበው እንዲከመሩ አድርጓል።

ለሀገራችን ችግሮች መፍትሔ ለማምጣት የሚያስቸግሩን፣ እንዲህ ዓይነት ስሜቶችና እልሆች ገነው በመውጣታቸው ነው። እንዲህ ዓይነት ስሜቶችና እልሆች ተመሳሳይ ዓላማና ግብ አንግበናል በሚሉ ሰዎች መካከል እንኳን ተባብሮና ተጋግዞ ለመሥራት አዳጋች እንዲሆን አድርገዋል። በሰላማዊ መንገድ ተወዳድሮ፣ በሐሳብ የበላይነት ተከባብሮና ተቻችሎ ለመገዛት ፈተና ነው። ለችግሮቻችን የጋራ መፍትሔ በማምጣት፣ ከነባራዊ ሁኔታችን ተሻግረን፣ የተረጋጋ ፖለቲካና የተጠናከረ ሀገር ለመፍጠር ደንቃራ ሆኖብናል።

የአደረጃጀትና የመዋቅር ጥያቄዎች፣ ሕጎችና መመሪያዎች፣ ተቋማዊ አሠራሮች ሲወጡ መመዘን ያለባቸው እንደ ሀገር በሚኖራቸው ጥቅምና ጉዳት ነው። ተጽዕኖ ያደርግብናል ብለው የሚያስቡ ግለሰቦች የሚያደርሱት ግለሰባዊ ተጽዕኖ ግን ቀላል አይደለም። ጊዜያዊ የተመቻል አለብን። ሥልጣንን ለማጠናከርና ለማቆየት እንዲሁም የተወሰነ ጥቅምን ለማግኘት ተብለው ሀገራዊ ጥቅምንና ዘላቂ መፍትሔን ሳያማክሉ የሚወሰኑ ውሳኔዎች አሉ። እነዚህ የሚወሰኑ ውሳኔዎች፣ የሚፈጠሩ መዋቅሮችና የሚወጡ ሕጎች ዘላቂ ፈተናና መከራን ፈጥረው ሲያልፉ ቆይተዋል። በዚያው ልክ ጊዜያዊ የሆነ ተጽዕኖን በመሥጋት፣ ሳይመለሱ ተሸፋፍነው በይደር የተተዉ ጉዳዮች በጊዜ ሂደት ጠንክረው ትልቅ ፈተና ሆነው መጥተው ያውቃሉ።

ግላዊ ጥቅምን መሠረት ያደረጉ ፖለቲከኞች፣ እታገልለታለሁ የሚሉት ሕዝብ ፍላጎት ቢሳካም እንኳን፣ እነርሱ ሥልጣን እስካልያዙና ሀብት እስካልተቀራመቱ ድረስ ተሳክቷል ብለው አያምኑም። ሕዝብ በላ የሚሉት እነርሱ ሲበሉ፤ ሕዝብ አጣ

የሚሉት እነርሱ ሲያጡ ነው። እነርሱ የሕዝብ አካል ሳይሆኑ የሕዝብ መለኪያ "ቴርሞ ሜትሮች" ናቸው። ለውጥ በመጣ ቁጥር የተለያዩ የሥልጣን ፍላጎት ያላቸው አካላት ጎራ ለይተው እንዲፋለሙ የሚያደርጋቸው፣ ከጋራ ግብ ይልቅ ግላዊ የጥቅም ግጭቶች ናቸው።

CamScanner

ከስድስት ዓመት በፊት የተከሠተውን ለውጥ ተከትሎ በሀገራችን እስከዛሬ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የዴሞክራሲ ምኅዳር ሰፍቷል። ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በሐሳብ የማሸነፍ ዕድል ተፈጥሯል። አስገራሚው ነገር ይህ አይደለም። ለዘመናት የዴሞክራሲን ጥያቄ እንግበናል የሚሉ ኃይሎች የዘመናት ጥያቄያቸው የሚፈታበት ዕድል ሲመጣ በተቃራኒው ቆሙ። ያገኙትን ዕድል ከማጠናከር፣ ከማሳደግና ከመጠቀም ይልቅ የዕድሉ አምካኝ ሆነው መጡ፡ ዕድሉን ከግላዊ ስሜትና

ከግላዊ ፍላጎት አንጻር ብቻ መዘኑት። ከለውጡ የእኔ የግሌ የአክስዮን ድርሻ ስንት ነው? ብለው ጠየቁ።

ግላዊ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ ትኩረቱ ውጤቱ ላይ ስለሆነ ሂደቱ ስለሚያስከፍለው ዋጋ ግድ አይሰጠውም። ሥልጣን አገኝበታለሁ ብሎ ካሰበ ሂደቱ ሀገርን ቢበትን ግድ የለውም። እታገልለታለሁ የሚለውን ሕዝብ ዋጋ ቢያስከፍልም ቁብ አይሰጠውም። ግላዊ ውጤቱን እንጂ ሂደቱን ከውጤቱ አንጻር አይመዝንም።

ፖለቲካችን ከእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በመራቅ በሚዛንና በምክንያት የነጠረ መሆን አለበት። ፖለቲከኞች ነገሮችን ከራሳቸው ስሜት ሳይሆን ከማኅበረሰብ ጥቅምና ጉዳት አንጻር የሚመዝኑ መሆን አለባቸው። ፖለቲካን ከራስ ፍላጎት ለገዘፈ ዓላማ ማስፈጸሚያ አድርጎ የሚያስብ ሰው፣ ከገዛ ስሜቱ ተላቆ እያንዳንዱ እንቅስቃሴው ሕዝብ ላይ ከሚያመጣው ለውጥና ውጤት አንጻር ለመመዘን መቻል አለበት። ከራስ ስሜት፣ ከጊዜያዊ መፍትሔና ከአንጻራዊ ጥቅም ከፍ እንበል። ከራስ ከተሻገረና ከዘላቂ መፍትሔ አንጻር ችግሮቻችንን እንመልከት። ያኔ መፍትሔው በዚያው ልክ እየቀለለ ይመጣል። ሀገራችንን ወደ ተሻለው ቀላል አይደለም መንገድ ለመምራት ከታሠርንበት የስሜትና የጥቅም አጥር በመውጣት ከፍ ብለን ለመመልከት መቻል አለብን።

## 10.2. ፖለቲካዊ መረጋጋትና መግባባት

በኢትዮጵያ የዘመናዊ መንግሥት ምሥረታን ተከትሎ ባለው ዘመን የፖለቲካ ሥልጣን ቅቡልነት ምንጮች ሦስት ናቸው: መለኮታዊ ኃይል፣ ወታደራዊ ኃይልና ከፊል ሕዝባዊ ቅቡልነት ናቸው። በኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ግንኙነት ቅቡልነት የሚገኘው በኃይል የታገዘ ሥነ ልቡናዊ ፍርሃት በማንገሥ ነበር። ፈጣሪ ለቀባው ንጉሥ አለመገዛትና አለመታዘዝ ኃጢአት በመሆኑ በሥጋም በነፍስም ያስቀጣል። የልዩ ልዩ እምነት አባቶች ንጉሡን ወይም ሞቲውን፣ ወይም አሚሩን ወይም ሡልጣኑን ከመንፈሳዊ ነገር ጋር ያያይዙታል። ይህ ደግሞ በሕዝቡ ላይ ሥነ ልቡናዊና መንፈሳዊ ፍርሃት
ይፈጥራል።

ኃይለ መለኮትን በኃይለ ሰብእ የተካው ወታደራዊ ደርግ ነው። ፖለቲካዊ ቅቡልነቱን አብዮታዊ ርምጃ በመውሰድ ከጠመንጃ ኃይል ለማግኘት ሞክሯል። ደርግን ሁለት ዓይነት ኃይሎች መልሰው ገጥመውታል። በአንድ በኩል በመለኮታዊው ኃይል የጸና ነው የተባለውን ዘውዳዊ ሥርዓት የታገሉ ወጣቶች። በሌላ በከል ደግሞ ንጉሡ ከዙፋን ከወረዱ ፀሐይ ትጨልማለች የተባለው እውነት አለመሆኑን ያየው ማኅበረሰብ።

በ1966 አብዮት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ያደረገው የቅቡልነት ሽግግር ከመንፈሳዊ ወደ ሥጋዊ ነው። ሰማዩን ከመፍራት ምድሩን ወደ መፍራት እንዲሸጋገር ነበር የተፈለገው። ዐመጽ ሰማያዊ የተባለውን ሥልጣን ሲገረሥሠው አይቷል። ስለዚህም ፊቱን ወደ ምድራዊ ለማዞር ወራት አልፈጀበትም። መንፈስና ሥጋን ከማስገዛት በነቢብም በሀልዮም ወደ ማመጽ መጣ። መንግሥታዊም ሆነ ማኅበረሰባዊ የፖለቲካ ሽግግር ከዕሴት ይልቅ የኃይልና የጉልበት ሽግግር አደረገ።

ጥንት መለኮታዊ ሥልጣንን ለምን ብሎ ሳይጠይቅ ይገዛ ነበር። አሁን ደግሞ የኃይል የበላይነቱን ለያዘና ላረጋገጠ ዝም ብሎ ይገዛል። ያ ሥልጣን የተዳከመ ሲመስለው ደግሞ ካደፈጠበት በመውጣት ያምጻል። ይህ የማኅበረሰባችን ዘመናዊ የፖለቲካ ባህል ሆኗል።

CamScanner

ኢሕአዴግ የደርግን የ7 ዓመት ቆይታ በኃይል ጥሎ የሀገረ መንግሥቱን መንበር ሲቆጣጠር ኃይልና ሕግን እየደባለቀ የፖለቲካ ሥልጣን ቅቡልነት ለማግኘት ሠርቷል። ሕወሓት መራሹ ኢሕአዴግ የመራው የሽግግር ጊዜ ፖለቲካዊ መረጋጋትና ስምምነት ከመፍጠር ይልቅ በኃይል የተወጉና የተገፉ ክፍሎችን ፈጥሮ አለፈ። በዚህ ምክንያት ማኅበረሰብ ዳግም ወደ ፍርሃት ዋሻው እንዲገባና እንዲያደፍጥ ተደረገ።

ምርጫ-97 የሕዝብና የመንግሥት ግንኙነት ከኃይል አለመውጣቱ የታየበት ነበር። የሕዝብ ድምፅ በኃይል ሲነጠቅ የፖለቲካ ልሂቁ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሂደትን ከመረዳት ይልቅ ሥርዓቱን በኃይል ገፍቶ ለመጣል ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ከምርጫ - 97 ማግሥት ኢሕአዴግ ቀጭን በትሩን ሲያነሣ የፖለቲካ ልሂቁም ሆነ ማኅበረሰቡ ጎመን በጤና ብሎ እንደ ቀንድ አውጣ ወደ ምሽጉ ተከትቷል።

ከዐሥር ዓመታት ዝምታ በኋላ የተጀመረው የተቃውሞ እንቅስቃሴ በመንግሥት በኩል የኃይል ርምጃ አላጣውም ነበር። የተቃውሞ መንገዱ ግን ሰላማዊ - ሕዝባዊ ዐመጽ ነበር። ይህም በኢሕአዴግ ውስጥ ላሉ የለውጥ ፈላጊዎች ምቹ መንገድን ፈጠረ።በመሆኑም በዐደባባይ ማኅበረሰቡ፣ ከውስጥ ደግሞ የኢሕአዴግ የለውጥ ኃይሎች ባደረጉት ትግል የፖለቲካ ሥልጣን ሰላማዊ በሚባል ደረጃ ሽግግር እንዲያደርግ አስገድዷል። መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም የተደረገው ለውጥ፣ ለጥቂት ወራት የመረጋጋትና የመግባባት ምልክቶች የታዩበት ነበር። ልማደኛው የፖለቲካ ልሂቅ ከጥቂት ወራት ደፈጣ
በኋላ ዳግም ወደለመደው የኃይል ፖለቲካ ተመልሷል።

"ከድጡ ወደ ማጡ" እንደሚባለው በፖለቲካ መረጋጋትና መግባባት ላይ ባለመደረሱ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ተባብሰው ዳግም ለፖለቲካ አለመረጋጋት ይዳርጉናል።

ከዚህ አዙሪት ለመውጣትና ወደ ሚቀጥለው ደረጃ ለመሻገር፣ ፖለቲካዊ ስክነትና መግባባት _ ለአንድ ሀገር ወሳኝ ናቸው። በርካታ አዳጊ ሀገራት በፖሊሲ፣ በፕሮግራምና በፕሮጀክት ዝግጅትና ትንታኔ ረገድ ካደጉት ሀገራት እምብዛም ያልተለየ አረዳድና ዝግጅት አላቸው። ይህንንም ለመተግበር በሰነድ ቀምረው አስቀምጠዋል። ሀገራቱ ያላቸውን ሀብት ፣ አስቻይ በቅሞች፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የለውጥ መዳረሻዎችን የሚያመላክቱ ድንቅ ሰነዶች አሏቸው።

አዳጊ ሀገራትን የሚገጥማቸው ትልቁ ፈተና ዕቅዱን በጊዜ፣ በጥራትና በቅልጥፍና ስለ ማከናወን ያለመቻል ነው። ዛሬ ዛሬ በዕድገት ሞዴል ምርጫ የዓለም ሀገራት ተቀራራቢ ሞዴሎችን ይከተላሉ። የልዩነት መሥመር ሆኖ የሚነሣው ይሄው የመፈጸም ዐቅም ነው። የመፈጸም ዐቅም ዝቅተኛ ለመሆኑ የሚዘረዘሩ ሌሎች ምክንያቶች ቢኖሩም፣ በቀዳሚነት የሚጠቀሰውና ለተከታዮቹ ችግሮች ወላጅ የሆነው፣ የፖለቲካ መረጋጋትና መግባባት ላይ ወሓትና አለመድረስ ነው።

አዳጊ ሀገራትን ከገቡበት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ምስቅልቅል እንዳይወጡ ጠላልፎ የያዛቸው የፖለቲካ አለመረጋጋት ነው። ይህ እውነት ዛሬም ድረስ ቀጥሏል። በወረቀት የቀሩ፣ ተጀምረው ያልተጠናቀቁና የሚያጓጉ የመልማት ዐቅሞች

ተሰነካክለው ይቀራሉ። ይህን በር፡ _ የሚያሰናክለው አንደኛውና ዋነኛው ምክንያት የፖለቲካው አለመስከንና ወደ መግባባት ዳት አለመሸጋገሩ ነው። ኢትዮጵያም የዚህ ፈተና ተጋሪ ናት።

ለአንድ መንግሥትና ማኅበረሰብ ሀገራዊ መረጋጋትና መግባባት የመብረሪያ ሁለት ክንፎች ናቸው። ፖለቲካዊ መረጋጋትና መግባባት ከቀደሙት ዘመናት በበለጠ በፖለቲከኛው፣ በአስተዳደሩ፣ በመገናኛውና በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ አንገብጋቢ

ሆኗል። ይህን ያደረገው _ የመንግሥትና የሕዝብ ግንኙነት ስለተቀየረ ነው። ከመለኮትና ከጠመንጃ የሚገኙ መንግሥታዊ ቅቡልነቶች ከሕዝብ ድምፅ መነጩ። ይህም ፓርቲዎችንና የማኅበረሰብ ፍላጎቶችን አበራከታቸው። የፍላጎቶች ፉክክርና

CS CamScanner

ትግል መረጋጋትንና መግባባትን ተናፋቂ _ እንዲሆን አደረገው። የፍላጎቶች ግጭት ከፍ ብሎ ሥርዓታዊና ማኅበራዊ ንዝረት ይፈጥራል። የሁሉም ርዕሰ ጉዳይ ፖለቲካዊ መረጋጋትና መግባባት እንዲሆን አድርጎታል።

በርግጥ ፖለቲካዊ መረጋጋትና መግባባትን ተናፋቂ ያደረገው ከሚያስከፍለን ኢኮኖሚያዊ፣ _ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዋጋ የተነሣ ብቻ አይደለም። ፖለቲካቸው ከስክነት ወደ መግባባት የተሻገረ ሀገራት ያስመዘገቡትን ብልጽግና በመመልከትም ጭምር ነው።

መረጋጋት በርግጥ በፖለቲካዊ ሥርዓት መረጋገጥ ብቻ የሚገኝ ሳይሆን ማኅበረሰባዊ (ቡድናዊ) መረጋጋትና መግባባትንም ይሻል። በሀገራችን መንግሥታዊ ሥርዓት በሕዝብ ድምፅ መመሥረት ከጀመረበት ሦስት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ፣ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ልምምዳችን ሥርዓታዊም ሆነ ማኅበራዊ ችግሮች አሉበት። የምርጫ ጊዜዎችን ጠብ ሁከትና ግርግርን በዕቅድ ከመያዝ አልፎ፣ በሕዝብ ድምፅ የተመረጠ መንግሥት ፖሊሲና ፕሮግራሙን በነጻነት እንዳያስፈጽም፣ ተቃዋሚዎችና ቡድኖች ፖለቲካዊ መረጋጋት ታዋ ለውጦችን ማድረግ እንዳይፈጠር ይሠራሉ። ለአንድ የምርጫ ዘመን
የተመረጠ መንግሥት ፖለቲካዊ ትኩሳቶችን በማርገብ እንደተዋከበ ለቀጣይ ዘመን ምርጫ ዋዜማ ይደርሳል። የፖለቲካ ካ አለመረጋጋት በሀገሩ ልሂቃንና ቡድኖች፣ የዴሞክራሲ ሥርዓትና ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲፈጠር የሚያስችል ዕውቀትና ጥበብ ስለሚጎድላቸው፣ ፖለቲካዊ ስክነት በሀገሩ እንዳይረብብ አድርጎታል።

በመንግሥት መረጋጋትና በፖለቲካዊ አስተዳደር መረጋጋት መካከል ልዩነት አለ። የፖለቲካ ራና በፍጥነት ምላሽ ካል አስተዳደሩ የአንድን ሀገር አጠቃላይ ሕገ መንግሥታዊ መዋቅር ያመለክታል። የአንድ ውና አደጋ ይዳርጉናል። ሥርዓት መሠረታዊ ሕጎችና ሕገ መንግሥታዊ አካላት በድንገት ሲቀየሩ የሥርዓት ለውጥ ይባላል። ያልረጋ ሥርዓት እያረመና እየገነባ ከሚሄድ ይልቅ፣ እያፈረሰ ችግር መከመር ይቀናዋል። በድንገትና በተደጋጋሚ የሚፈጠር የሥርዓት ለውጥ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትና አለመግባባት እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል።

ኢትዮጵያ በተለይ ከደርግ ሥርዓት ጀምሮ ላለፉት አምስት ዐሠርት ዓመታት ባልረጋ ሥርዓት ውስጥ አልፋለች። የ966ና

የ983 ለውጦች የሥርዓት አለመርጋትን የሚያባብሱ፤ በስብራት ላይ ስንጥቃት ዓይነት ነበሩ። በ200ሩ የረጋ የሥርዓት ለውጥ፣ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትና ልምምድን ለማስቀጠል እንዲቻል በርካታ ጥረቶች ተደርገው ነበር።

ክፉ ልማድ ከሰይጣን ይብሳል ይባላል። ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ሥርዓትን የመለወጥ በጎ ልማዳችን አናሳ ነው። በዚህ የተነሣ

አብዮት ከደማችን ጋር ተዋሕዷል። ይህ ደግሞ ቶሎ ወደ ጽንፍ ይወስደናል። የ2010ሩ ለውጥም ፈተናው ይህ

ነው። “ሕገ መንግሥቱ ይቀደድ እና “ፈጽሞ እንዳይነካ” በሚሉ ቡድኖች መካከል ያለው ዋልታ ረገጥ እንቅስቃሴ፣ ለፖለቲካ አለመረጋጋትና ለፖለቲካ አለመግባባት ዋናው መንሥኤ ሆኖ ይታያል።

የፖለቲካ ሥርዓት መረጋጋት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን በፍጥነት ለመምራት መሠረት ይሆናል። የፖለቲካ መረጋጋትና መግባባት በሀገር ደረጃ መፍጠር የሚቻለው የሚከተሉት ሁለት ነገሮች ሲኖሩ ነው። የመጀመሪያው

የፖለቲካ ሥልጣን _ለሰፊው ማኅበረሰብ ለጋራ ጥቅም እንደሚውል ሲታመን ነው። ሁለተኛው ደግሞ መልካም አስተዳደር ማስፈን ግቡ ያደረገ ሥርዓት ሲኖር ነው። ለዚህም ፈጣን ማኅበረሰባዊና ሥርዓታዊ ለውጦችን ማድረግ ይጠይቃል። እነዚህ ለውጦች በፍጥነት ካልተመሩ የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖችና የማኅበረሰብ ክፍሎች ነጣጣይ አጀንዳ በመፍጠር

ስለሚጠመዱ፣ መንግሥት ፖለ. ፖለቲካዊ መረጋ ንግሥት ፖለም። ይደርሳል። የፖለቲካ አለመረጋጋት በሀገሩ ይንሠራፋል።

CamScanner

ብዝኃ ማንነት ያለው ማኅበረሰብ የተለያየ ፍላጎትና ምልከታ አለው። እነዚህ ፍላጎቶች በታሪክ ሂደት የመጣጣም ዕድል ካላገኙ፣ ሰብአዊና ኢኮኖሚያዊ ጉድለቶችን ፈጥረው፣ የፖለቲካ መግባባትና መረጋጋትን ያወሳስቡታል። እኛም ያለንበትን ነባራዊ ሐቅ ተረድተን በፈጠራና በፍጥነት ምላሽ ካልሰጠናቸው፣ ከፖለቲካ አለመረጋጋትና አለመግባባት ባለፈ ለህልውና አደጋ ይዳርጉናል።

ብዙ የፖለቲካ ሃልዮቶች ብዝኃ ማንነት በበዛበት የተረጋጋ ፖለቲካና የተግባባ ማኅበረሰብ መገንባት አዳጋች እንደሆነ ያትታሉ። ከዚህ በተቃራኒ የሚቆሙ፣ ካለንበት ምድራዊ ሐቅ ተነሥተን፣ የሰው ልጆች የሚጋሯቸውን ራእዮች አስቀድመን፣ ልዩነታቸውን የሚያቻችል ሥርዓት በመዘርጋት፣ የተረጋጋና የተግባባ ማኅበረሰብ መፍጠር ይቻላል የሚሉም አሉ። የዚህ ሐሳብ አቀንቃኞች ብዝኃ ማንነት ባለበት ሀገር፣ ከአብላጫ ድምፅ የዴሞክራሲ ሥርዓት ይልቅ የመግባባት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይሻላል ይላሉ። ይሄም በሀገር ውስጥ የፖለቲካ መረጋጋትና መግባባት ለመፍጠር የሚያስችል ሥርዓት እንደሆነ ያስረዳሉ።

የመግባባት ዴሞክራሲ የሚፈለገውን የፖለቲካ ስክነት እንዳይፈጥር ፈተና የሚሆንበት፣ ዋልታ ረገጥ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው። ዋልታ ረገጥ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በበዛበት የፖለቲካ ምኅዳር የጥምር መንግሥት መመሥረትና የሥልጣን መጋራት መርሖች ቢተገበሩ እንኳን መፍትሔ አያመጡም። ምክንያቱም ዋልታ ረገጥ ቡድኖች ወርቃማውን አማካይ ከመፈለግና

ወደ መግባባት ከመምጣት ይልቅ፣ "እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን" የሚሉና፣ አቻችሎ ለመሄድ የሚቸገሩ መሆናቸው ነው። አንድን ሀገር በጋራ እየመሩ ለመገንባትና ለማበልጸግ፣ እጅግ ሰፊ ልዩነቶችንና አለመግባባቶችን ይዞ መቀጠል፣ የሚፈለገውን ፖለቲካዊ መረጋጋትና ስክነት ከመፍጠር ይልቅ፣ ለሥርዓተ መንግሥት መፍረስ ይዳርጋል።

ብዝኃ ማንነት ባለበት ሀገር የመግባባት ዴሞክራሲ ፖለቲካዊ መረጋጋትና መግባባትን የሚያስገኘው በሁለት ማሕቀፎች ነው። የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች መቻቻልና መተሳሰብ የሚያስቀድሙ ከሆነ፣ እንዲሁም በወንድማማችነት መርሕ የሚመሩ

ከሆነ ነው:: በመሆኑም ብዝኃነት ባለበት ሀገር፣ መንግሥታዊ ሥርዓት ውክልናን በማረጋገጥ ብቻ የፖለቲካ መረጋጋትና መግባባትን አያመጣም፡ ብዝኃ ማንነትን በማሳሳብ ወደ መሐል እንዲመጡ በማድረግ ጭምር እንጂ።

በሀገራችን ባለፉት ዓመታት ሁለት ዓይነት ማንነቶች ለየብቻቸው ተቀንቅነዋል። የመጀመሪያው ሀገራዊ ማንነት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አካባቢያዊ ማንነት ነው። አንዱ አንዱን በመጨፍለቅ የሄድንበት መንገድ፣ ሁሉንም አሸናፊ ሳያደርጋቸው ቀርቷል። አዲሱ የመደመር አካሄድ በብዝኃ ኃይል ኢትዮጵያን ከፍ የሚያደርግ እንዲሆን ተመጣጣኝ ትኩረት ይሰጠዋል። አንዱ ሌላውን ሳይውጠው፣ አንዱ ለሌላኛው ተቃራኒ ሳይሆን፣ በመሳሳብ የተግባባና የተከባበረ መንታ ማንነት መፍጠር

ነው 99። የሁለቱ ኃይሎች መሳሳብ ቢኖርም፣ በሂደት ሁሉን አሸናፊ የሚያደርገው መንገድ ሁሉንም ያሰባስባል። ይህንን በፍጥነት ማድረግ መንግሥታዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበረሰባዊ መረጋጋትንና መግባባትን ያሰፍናል።

በኢትዮጵያ የተጀመረው ሥርዓታዊ ለውጥ አበክሮ እየሠራ ያለው የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች _ሚቻልበትን ምኅዳር

መፍጠር ነው። የ2oo ለውጥን ተከትሎ በሀገር ውስጥ የፖለቲካ ወደ መሐል እንዲመጡ ነው። ወደ መሐል መምጣት ከነልዩነት አብሮ መሥራትና መፎካከር እሥረኞችን ለመፍታት፣ በጫካ የሸመቁ በሐሳብ ትግል እንዲያደርጉ ለመጋበዝ፣ ዘሩ ከሚዘራበት እርሻ እርቀው በሰው ሀገር ተጠልለው የፖለቲካ ዘር የሚዘሩ ሁሉ፣ ተሰባስበው ወደ ሀገራቸው ፖለቲካዊ ሜዳ ገብተው፣ በሕግና በሥርዓት በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ መንገድ ለመክፈት ጥረት የተደረገው በዚሁ የመደመር ዕሳቤ ነው።

ከፖለቲካ ተሳትፎ ባሻገር የ6ኛውን ብሔራዊ ምርጫ ውጤት ተከትሎ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ፌዴራል፣ በክልልና በከተማ መስተዳድር ውስጥ የአስፈጻሚውን ሥልጣን እንዲያገኙ ተደርጓል። በተጨማሪ የብልጽግና ፓርቲ ያልሆኑ ቴክኖክራቶች

CS CamScanner

በአስፈጻሚ ተቋማት ውስጥ የኃላፊነት ድርሻ እንዲኖራቸው ተደርጓል። የዴሞክራሲ ተቋማት ማኅበረሰባዊ ውግንናቸው እንዲዳብር በሰብአዊ መብትና በምርጫ ተቋማት፣ እንዲሁም ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር በተቋቋሙ ኮሚሽኖች ውስጥ፤ በማኅበረሰቡ ዘንድ ተደማጭነት ያላቸውና ሕዝባዊ ውግንናቸው ከፍ ያለ ዜጎች እንዲመሯቸው ዕድል ሰጥቷል።

እንዲህ ያሉ ፈጣን ለውጦች መደረጋቸው በፖለቲካ ምኅዳሩ ስንዴውን ከእብቁ እንድንለይ አስችሏል። ፖለቲካዊ ቅቡልነት ሐሳብ በመሸጥና የሕዝብን ድምፅ በመግዛት የሚገኝ ነው። ይህን የተረዱ እውነት፣ ዕውቀትና ድፍረት ያላቸው ተፎካካሪዎች አብረውን እየሠሩ ነው። በአንድ በኩል ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታና ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች መሻሻል ባላቸው ጊዜ የድርሻቸውን እየተወጡ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ምኅዳሩ በመሳተፍ ለነገ ተመራጭ የሚያደርጋቸውን ሐሳብ እያደራጁ ይገኛሉ።

በተቃራኒው ፖለቲካን በስሜት ግለትና በመጠቀሚያ መሣሪያነት የሚመለከቱ ኃይሎች ሥልጣን በሐሳብ ልዕልና ሳይሆን በክንድ ብርታት ይገኛል" ከሚል ያረጀ አመለካከት መላቀቅ አቅቷቸዋል። ይሄንንም ይዘው፣ በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጫካ ውስጥ አድፍጠዋል። እነዚህ ኃይሎች መንግሥት ለዘላቂ መረጋጋትና መግባባት ሲል፣ "ኑ በጋራ እንሥራ"

ማለቱን የድክመት ምልክት አድርገው ቆጠሩት። በዚህ የተነሣ "ዕድሉ ሳያመልጠን ሥልጣን በኃይል እንያዝ" ወደሚል ሩጫ ውስጥ ከተታቸው።

በኃይል ሥልጣን ለመያዝ ፍላጎት ያላቸው እነዚህ ኃይሎች፣ በሰላማዊ የፖለቲካ ውድድር ውስጥ ገብተው ሐሳባቸውን ለሕዝብ አቅርበው አያውቁም። ሥልጣን በአፈ ሙዝ እንጂ ከሕዝብ ይገኛል የሚል እንጥፍጣፊ እምነት የላቸውም። ዕድል በኢትዮጵያ ላይ ፊቷን ብታዞርና ኢትዮጵያ በእነዚህ ኃይሎች እጅ ብትወድቅ፣ አክራሪ ማንነታዊ ዕይታቸው ራሳቸውንም ለእርስ በእርስ ጦርነት ይዳርጋቸዋል። የእርስ በእርስ ጦርነቱ በአንዱ አሸናፊነት ቢጠናቀቅና ኢትዮጵያ በመዳፋቸው ብትወድቅ፤ ቅቡልነትን ከሕዝብ ድምፅ ሳይሆን በጠመንጃ ድምፅ ለማረጋገጥ የሚሞክሩ ናቸው።

እንዲህ ያለ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ቢኖሩም፣ በአንጻሩ ደግሞ ወደ መሐል በመምጣት አበረታች እንቅስቃሴ የሚያደርጉም እየበዙ ነው። ዛሬ ዛሬ በብሔራዊ ጉዳዮች፣ በትርክት፣ በብዝኃ ማንነትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ከአብዛኞቹ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ከሞተ ጎደል ወደ መቀራረብ ተደርሷል። ያልተስማማንባቸው ነጥቦች አብሮ የማያሠሩ አይደሉም። በሕዝብ ፍላጎት እንዲዳኙ የተተዉ ናቸው።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉ ሰላማዊና ሕጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ዕድል ተፈጥሯል። በጋራ ለመሥራት በመንግሥት በኩል ሆደ ሰፊነት አለ። ይህም ያስፈለገው፣ ሁላችንንም አሸናፊ ስለሚያደርግ ነው። በአካሄድ ብንለያይ እንኳን መድረስ በምንፈልገው ውጤት ላይ እስከተስማማን ድረስ፣ በጋራ የመሥራት ዕድሎችን መፍጠር አንዱ ምክንያት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ሥልጣን የማጋራት ልምምድ እንዲዳብር በማሰብም ነው። እነዚህን የመሰሉ ሂደታዊ ግቦቻችን እንዳሉ ሆነው ታላቁ ግባችን እንደ ሀገር የፖለቲካ መረጋጋትንና መግባባትን መፍጠር ነው። የፖለቲካ መረጋጋትና መግባባት፣ የመደመር መንግሥትን ፈጠራና ፍጥነትን ለማሣለጥ ለዓሣ የሚያስፈልገውን ውኃ ያህል ነው።

## 10.3. ከመረጋጋት ወደ መግባባት በእምነት

የተረጋጋ የፖለቲካ ምኅዳርና የተግባባ ማኅበረሰባዊ ኅብረት የመንግሥት የልማት ሞዴሎች ስኬታማ እንዲሆኑ ያግዛሉ። በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ሀገረ መንግሥቱ መረጋጋትን ሲላበስና በማኅበረሰብ ክፍሎች መካከል መግባባት ሲጎለብት፣ ለመደመር መንግሥት ፈጣን የልማት ዕቅድ መሳካት መሠረት ይጥላል። በአንድ ሀገር የፖለቲካ መረጋጋት ወደ መግባባት

CamScanner

የሚያደርገው ሽግግር፣ ውጤታማ አስተዳደር፣ ማኅበራዊ ዕድገት፣ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ማኅበረሰባዊ ስምምነትን በመፍጠር ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ ያስችላል።

ከፖለቲካዊ መረጋጋት ወደ መግባባት የሚደረግ ሽግግር እምነት ይፈልጋል። በሀገራችን የመንግሥትና ሕዝብ ግንኙነት በተደጋጋሚ መካካድና መሸነጋገል የበዛበት ሆኖ አልፏል። መንግሥትና በሕዝብ፣ በመንግሥትና በፓርቲዎች፤ በፓርቲዎችና በፓርቲዎች መካከል መካካድና መበላላት ልማድ ሆኖ ኖሯል። ከዚህ አልፎም በማንነቶች መካከል አንዱ በአንዱ ላይ እምነት ለማሳደር ይቸገራሉ።

በርግጥ እምነት መጣልና እምነት ማጣት እንዲሁ በአጋጣሚ የተፈጠረ አይደለም። ካለፈ ክና ከነበረው መስተጋብር የሚነሣ ነው። ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ አካላት ባላቸው መስተጋብር ልምድና ተጋላጭነት የተነሣ ስለ አካባቢያቸው ከሚይዙት አረዳድ የሚፈጠር ነው። በእምነት ጉድለት ኪሳራ ውስጥ ያለው ፖለቲካችን፤ ብሔራዊ ችግሮችን ተነጋግሮ መፍታት ዐቅም እንዲያንሰው ሆኗል። ወደ ምስክር ኮሚሽን የሚገቡና የሚወጡ የፖለቲካ ቡድኖች የእምነት ጉድለት ሰቀቀናቸው ያባንናቸዋል።

የእምነት ጉድለት ዛሬ በድንገት የመጣ አይደለም። በረጅም መንግሥታዊና ኅብረተሰባዊ አይደሉም ግንኙነት የተሰበሩ ቃል ኪዳኖች የፈጠሩት ጠባሳ ነው። በሕዝቡ ዘንድ የልማት ዕቅዶችን ከማመን ይልቅ በጥርጣሬ ማየት የተለመደ ሆኗል። ምክንያቱም ቃል ተገብተው የተቀመጡ ሺ የመሠረት ድንጋዮች ከትውልድ ወደ ትውልድ ያለ ተግባር ሲተላለፉ

አይቷልና°። በወረቀት አጊጠው ያልተፈጸሙ ዕቅዶች መደርደሪያዎችን ሲያጨናንቁ ታዝቧልና። በምርጫ ጊዜ የጠገቡ ቃል

ኪዳኖች እንደ ኬክ ሲቆራረሱ ተመልክቷልና። በዚህ ሁሉ ወጀብ ውስጥ፣ “እባብ ያየ በልጥ በረየ” በሚል ማኅበረሰብ፣ በሕዝብና በመንግሥት መካከል ከእምነት ይልቅ ጥርጣሬ ቢነግሥ አይገርምም።

ለረጅም ዘመን በተደጋጋሚ ለእምነት መጓደል ተጋላጭ መሆናችን፣ የልቡና ውቅራችን ከማመን ይልቅ ወደ መጠርጠር ያዘነበለ እንዲሆን አድርጎታል። ያልጠረጠረ ተመነጠረ፣ ጠርጥር ከገንፎም ይገኛል ስንጥር፣ በሚል የኖረ ነው። ይህ ልቡናዊ ውቅር ለውጥ ያስፈልገዋል። ምክንያቱም እምነት በጎ ዕሴት ነውና። በአንድ አካል ላይ እምነት ስንጥል በራሳችን ላይ ያለን ቁጥጥር አሳልፈን ከመስጠት ይጀምራል።

ተጋላጭነታችን በዚያ ወገን በእምነት እንደሚጠበቅ ማመንን ይጨምራል። ሁለቱም ወገኖች ተጋላጭነታቸውን መሥዋዕት አድርገው አንዱ አንዱን በማመን መፍትሔዎችን መተግበር፣ ችግሮችን መፍታትና አንዳቸው ከአንዳቸው እየተማሩ እምነትን የትብብርና የኅብረት ማዕከል ማድረግ መቻል አለባቸው። አንዳችን በአንዳችን ላይ ያለን እምነትና መተማመን ሲዳብር፣ የጋራ ስኬት እናስመዘግባለን። እምነትና መተማመንን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዕሴታችን ስናደርግ፣ ትሥሥር ይጠነክራል፤ ኅብረት ይዳብራል።

እምነት ለትብብርና ለኅብረት የመሠረት ድንጋይ ነው። በአንድ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ውስጥ፣ እምነትን መሠረት ያደረገ ትብብርና ኅብረት ሲጎለብት፣ ታላቅ ሕዝባዊ ኃይል ይፈጠራል። በአዎንታዊ ኃይል የተሞላ ማኅበረሰብ በፈጠራና በፍጥነት ምኅዋር ውስጥ ይገባል። ከነበረበትና ካለበት የድህነት አዘቅት በፍጥነት ለመውጣት ይችላል። በፈጠራ አዲስ ዕይታና አዲስ ግንኙነቶችን በማከል ፍጥነቱን ያሣልጣል።

## 10.4. ራዕይ መጋራት፣ እምነትን ማጽናት

በእምነት ላይ የተመሠረተው ትብብርና ኅብረት ወደ ኃይል ተቀይሮ ወደ ግቡ እንዲደርስ፣ የሚመራበትና የሚጋራው ራዕይ ያስፈልገዋል። አንድ ማኅበረሰብ በጋራ የሚስማማበት ብሎም አስፈላጊውን ዋጋ የሚከፍልለትና የሚጓጓለት ብሔራዊ

ራዕይ ሊኖረው ይገባል። ያለ ራዕይ የሚወጠን ዕቅድና ተግባር “ሥራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል" ዓይነት ነው።

CamScanner

በኮምፓስ የሚመራ መርከብ ከወደቡ እንደሚደርስ፤ በራዕይ የሚመራ ተግባርም ዓለምን ይቀይራል። የራዕይ ኃያልነት፣ ምናብና ተግባር የሠመሩ ዕለት ነው።

የጋራ ራዕይ በትብብር ለሚደረግ ጥረት የልብ ምት ማለት ነው። ትጋትንና ጥብአትን በእያንዳንዱ ተነሳሽነትና ፕሮጀክት ውስጥ ያሠርጻል። እንደ ፋና መንገድ ከመምራቱ በላይ፣ የግለሰቦችን ጉጉት በአንድነት በማስተሣሠር የጋራ ዕሴት እንዲኖረው ያደርጋል። ልዩ ልዩ አካላትን ወደ ጋራ ግብ ይወስዳቸዋል፤ አብዛኞቹ ወሳኝ የሆኑ ሽግግሮች የማይሳኩት በተሳትፎ እጥረትና ግልፀ ሆኖ የተቀመጠ ራዕይ ስለሌላቸው ነው።

ከዓለም እጅግ ፈጣን ተለዋዋጭነት ጋር ለመጓዝ ዘመኑን የዋጀ ራዕይ መሰነቅ ግዴታ ነው። ቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማብቃቱን ተከትሎ የሉላዊ ዓለም ሥርዓት መከሠት፡ የሀገራትን የንግድ ሥርዓት ከመሠረቱ ነቅንቆታል። በየምዕራፉ በፍጥነት እየተለዋወጠ የመጣውን የዓለም ኢኮኖሚ መረዳትና ለጥቅም ማዋል፣ የአዳጊ ሀገራት ወቅታዊ ፈተና ነው። የሀገራት የኃይል ምንጭ ከፖለቲካ ወደ ኢኮኖሚ ተቀይሯል። ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን ማስፈጸም የሚቻለው የኢኮኖሚ ዐቅምን በማፈርጠም ብቻ ነው የሚለው ጎልቶ ወጥቷል።

ይህንን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ተገንዝበን፣ በጋራ ራዕይ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን ለመፍጠር ፀማችንን ማሰባሰብ አለብን።

ውጤታማ ራዕይ የሀገሩን ልዩ ዐቅምና ሀብት የተረዳ ነው። እንዲሁም ሁሉንም ባለ _የማኅበረሰብን ደኅንነት፣ ብልጽግናና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት የሚያረጋግጥ መሆን ድርሻ አካላት ያሳተፈና ያግባባ መሆን አለበት። በመንግሥት የሚቀረጽ ብሔራዊ ራዕይ ይገባዋል። ራዕዩን ብሔራዊ ራዕይ የሚያደርገው መንግሥት፣ የማኅበረሰብ ልዩ ልዩ መሪዎች፣ ማኅበረሰባዊ ተቋማት፣ ምልዐተ ሕዝቡ፣ የንግዱ ማኅበረሰብና ምሁራን ሲጋሩት ነው፡ እነዚህ ኃይሎች ራዕዩን እንዲጋሩትና እንዲጓጉለት እምነት የማሳደርና የተግባቦት ሥራን ይጠይቃል።

በመንግሥትና በሕዝብ መካከል የሚፈጠር እምነት የራዕይን ታማኝነት ያስገኛል። በርግጥ ራዕይ ከእምነት ጉድለት ባሻገር ባሉ ጉዳዮችም ይፈተናል። ብዙ ጊዜ የለውጥና የሽግግር ሂደቶች ፈጥነው ለዜጎች ተጨባጭ ጥቅም አያስገኙም። በዚህ የተነሣ ዜጎች በረጅም ጊዜ ራዕይ ላይ መተማመናቸውና ጉጉታቸው እየቀነሰ ሊመጣ ይችላል።

በሀገራችን መጠራጠርና ከዳር ሆኖ መመልከት የዐዋቂነት መለኪያ ሆኖ ይታያል። አንድ ገበሬ የገጠመው ነገር ለዚህ ሥነ ልቡናችን ጥሩ ማሳያ ነው።

በገጠር ለሚገኝ ቤተሰብ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን ለማገዝ በየቤቱ ምዝገባ ይደረግ ነበር። መዝጋቢዎቹ አንድ ቤት ደረሱ። እንደተለመደው የቤቱን አባ ወራ ጠየቁ። የለም ተባሉ።

የለም ያላቸው ሰው መልሶ፣ "ለምን ፈልጋችሁት ነው? አላቸው። መዝጋቢዎቹም "የምንሞላው ቅጽ አለ" አሉት።

"ችግር የለም እርሱ እስኪመጣ እኔ እነግራችኋለሁ አላቸው።

ስም ተናገረ፤ ስንት ልጆች እንዳሉ ተናገረ፤ የት እንደሚማሩ ተናገረ፤ የቤተሰቡን የገቢ መጠን
ተናገረ።

በመጨረሻ "ለልጆቹ ያዘጋጀነው ደብተር፣ ስክርቢቶና ዩኒፎርም አለ። የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍም ይደረግላቸዋል። መረከብ ያለበት ግን አባ ወራው ነው" አሉት። ያም ሰው "አባ ወራውማ እኔ ነኝ" አላቸው።

"እንዴ የሉም አላሉንም ነበር" አሉት። "መጨረሻው ሳይታወቅማ አሉ አይባልም" አላቸው።

CamScanner

ይህ ነው ሥነ ልቡናችን። መጨረሻው እንዲሠምር አብሮ ከመታገል ይልቅ፤ መጨረሻው እስኪሰምር ዳር ሆኖ በጥርጣሬ መጠበቅ።

ራዕዩን ቢወድደው እንኳን "ይህ ነገር የሚሳካ አይመስለኝም" ብሎ መጠራጠር ጀግንነት ሆኗል። "ያልጠረጠረ ተመነጠረ" ተብሎ ያደገ ነውና። ወይም "ይህ ራዕይ ለፖለቲካ ፍጆታ ልማድ ሆኗል። ከመንግሥታዊ መዋቅር እስከ ኅብረተሰብ መዋቅር ድረስ ባሉ አካላት ይህ አልያም ለአጀንዳ ማስቀየሻ ሊሆን ይችላል" በሚሉ ምክንያቶች አለማመንና አለመተባበር

ችግር አለ። እንዲህ ዓይነት አሉታዊ ልማዶች እንዲሁ አይፈጠሩም። ይልቁንም ከእምነት _ መጓደል የዘመናት ስብራት የሚመነጩ ናቸው። በሀገራችን ከምግብ እጥረት በላይ የመተማመን እጥረት አለ። ሁለቱም ለዘመናት በተፈጠሩ ችግሮች የመጡ ናቸው።

የመተማመን እጥረትን ለማቃለል የአረዳድና የአመለካከት ለውጥ መምጣት አለበት። ለዚህ ደግሞ ፍቱን መድኃኒቱ ተግባራዊ አስተማሪነትን ማስቀደም ነው። አለመተማመን ባህል የሆነው ከተደጋጋሚ ተግባር በመነሣት ነው። መተማመንንም ባህል ማድረግ የሚቻለው በተደጋጋሚ ታምኖ በማሳየት ነው።

ብሔራዊ ራዕይ ከማኅበረሰብ ሕይወት ጋር ያለውን ቁርኝት በሚገባ በማሳየት አረዳድና አመለካከትን ማስተካከል ያስፈልጋል። በመቀጠልም የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር የተግባቦት ሥራ በተከታታይነት መሥራት ቸል የሚባል አይደለም። የተግባቦት ሥራ እምነትን በመገንባት ሕዝብ ለራዕዩ ግብ በኅብረት እንዲሰለፍ ያደርጋል። አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ እምነት ከፈጠረ በትብብርና በኅብረት ከተሰባሰበና ራዕይ ከተጋራ፤ ታላላቅ ድሎችን በፍጥነት ማሳካት ይችላል።

በዋና ዋና ግቦች ላይ መስማማት ብቻውን በቂ አይደለም። ወደ ራእያችን ግብ ለመድረስ ቅድሚያ በምንሰጣቸው ጉዳዮችና በመድረሻ ስልትና ዘዴዎች ላይ ግልጽ መሆንም ያስፈልጋል። እነዚህንም ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ሊጋሯቸው ይገባል። በሩጫ መሙ ላይ መገኘት ብቻ አሸናፊ አያደርግም፤ የአሸናፊነት ራዕይ በድል የሚጠናቀቀው በመሙ ላይ

በሥርዓት(የሩጫውን ሕግ ጠብቆ)፣ በጥበብ (ሌሎቹን ሯጮች፣ አየሩንና ሁኔታዎችን እያዩ) እና በፍጥነት(ከሰዓት ጋር እየተፎካከሩ) በመሮጥ ነው፡

ራእያችን በፖሊሲ፣ በብሔራዊ ዕቅድ፣ በፕሮግራሞችና በፕሮጀክቶች ውስጥ እንዴት እንደሚተገበር፣ የሚያደርገው ሽግግር ልኬታዊ አመላካቾች ምን እንደሆኑ፣ ራዕያችንን ተከትለን ወዴት እየሄድን እንደሆነ፤ የጋራ መረዳት መፍጠር ያስፈልጋል። በሂደቱ ግልጽነትና ተጠያቂነት እየተረጋገጠ መሄድ ማኅበረሰባዊ እምነትን ያሳድጋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ራዕይ ብልጽግናን ማረጋገጥ ነው። ከትናንት ወረት ቆጥረን ዛሬን በትጋትና ጥበብ ሠርተን ለትውልድ የበለጸገ ሀገር የማሻገር ራዕይን ሰንቀናል።ራእያችንን ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲጋሩን እንፈልጋለን። በዚህ ራዕይ ውስጥ የኢትዮጵያዊ ማኅፀን ያፈራው ሁሉ ራሱን ሊመለከትበት ይገባል። እኛ ኢትዮጵያውያን በከፋ ጭቆና፣ በተደጋገመ ገርነት፣ በአሰቃቂ ረሃብ፣ አንገት በሚያስደፋ ስደትና ጉስቁልና ውስጥ አልፈናል። መከራና ችግር እንደደፍ ቢወርድብንም፣ የድህነት ሐሩር እንደሰም አቅልጦ እንደጧፍ ቢያነደንም፣ ላንረታና ሳንበተን በብርታት ዛሬ ላይ ደርሰናል። በፈተና ውስጥ ያበረታን ወረታችን ነው። ዐርበኝነትና መንፈሳዊነት ታላላቅ ወረቶቻችን ናቸው። ዛሬ እነዚህን አንጡራ ወረቶቻችንን ይዘን፣ ጉልበታችንን ያዛለውን ድህነትን አራግፈን፣ ኢትዮጵያን የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ ራዕይ ሰንቀናል።

ይህ ታላቅ ብሔራዊ ራዕይ የጋራ ራዕይ እንዲሆን አምስት ነገሮችን አከናውነናል፡

CamScanner

የመጀመሪያው ራዕያችንን በግልጽ ቋንቋ አስቀምጠናል። “መደመር መንገዳችን ነው፣ ብልጽግና መዳረሻችን ነው” ብለናል። ይሄም በቀላል ቋንቋ ዐቅማችን እንዴት እንደምናሰባስብና ባሰባሰብነው ዐቅም የት እንደምንደርስ ያስረዳል።

ሁለተኛው፥ በተለካና በተመዘነ መንገድ እንዲገለጥ ማድረግ ነው። በ2030 የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት የመሆን ራዕያችን ቀን ተቆርጦለታል። የሀገራችንን ዕምቅ ዐቅም ተጠቅመን በዐሥር ዓመት ውስጥ የመካከለኛ ገቢ ዐቅምን እንፈጥራለን። ለዚህም የኢትዮጵያን ሕዝብ የመበልጸግ መሻት እውን የሚያደርግ ራዕይና የለውጥ ዕቅድ ተነድፏል። የበለጸገ ማኅበረሰብ ለመገንባት የሚያስችሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ የማሻሻያ ሥራዎች ተጀምረዋል።

ሦስተኛው፥ ሕዝቡ ራዕዩን ለመረዳት የሚችልባቸው ልዩ ልዩ መድረኮችንና መንገዶችን ማመቻቸት ነው። በራእያችን ላይ የሚያጠነጥኑ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል። ከፌዴራል እስከ ወረዳ ውይይቶች ተደርገዋል። ከፈጻሚና ከተባባሪ አካላት ጋር ውይይቶች ተካሂደዋል። በየጊዜው በሚኖሩ የፓርቲና የመንግሥት ውይይቶችና ሥልጠናዎችም ራእያችን ዋና ጉዳይ ሆኖ እንዲነሣ ይደረጋል።

አራተኛው፥ ለዚህ ራዕይ ያለንን ጥብዐትና ቆራጥነት በተግባር ማሳየት ነው። ሐሳቦችን በማቀንቀን፣ በራእያችን መሠረት ለሚተገበሩ ሥራዎች የቅድሚያ ተነሣሽነቱን በመውሰድ፣ ፕሮጀክቶችንና ኢኒሼቲቮችን በማስጀመርና በመከታተል፣ ለራእያችን ያለንን ቆራጥነት እያሳየን ነው። ለአንዳንድ ፕሮጀክቶች ሕዝባችንን እናስተባብራለን፤ ለአንዳንድ ፕሮጀክቶች ከውጭ አካላት ገንዘብ እናፈላልጋለን። አንዳንድ ፕሮጀክቶችን መጻሕፍትን ሸጠን እንገነባለን። ይህም ለራእያችን ያለንን ትጋትና ጥብዐት የሚያመለክት ነው። የተጀመሩ ፕሮጀክቶች ከተባለላቸው ጊዜ ቀድመው እንዲጠናቀቁ የምናደርገው በሕዝባትን ላይ የተፈጠረውን ያለማመን ባህል ለመስበር ጭምር ነው።

አምስተኛው፥ በየወቅቱ መገምገምና የደረስንበትንና ያልደረስንበትን በግልጽ መነጋገር ነው። በየመቶ ቀናቱ ከሚደረገው ግምገማ ጀምሮ የአስፈጻሚው አካል ቅርንጫፎች በራእያችን አፈጻጸም ላይ እንዲወያዩ ይደረጋል። በየተወሰኑ ጊዜያት ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በራእያችን አፈጻጸም ላይ እንወያያለን። ከማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በራእያችን አፈጻጸም ላይ ውይይቶች ይደረጋሉ። የፓርቲና የመንግሥት ን እንዲሠምር ከፍተኛ አመራሮች በየተወሰኑ ጊዜያት ወደ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ሄደው የራእያችን ለ ማኅበረሰቡ የአፈጻጸም ይገመግማሉ። በእነዚህ ግምገማዎች መሠረት ጠንካራ ነገሮች እንዲበረታቱ ይደረጋል። ስሕተቶች ይስተካከላሉ። ጥፋቶች ይታረማሉ። ያልታዩ አዳዲስ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ እንዲገቡ ይደረጋሉ።

“ብልጽግና ለኢትዮጵያውያን” ስንል፣ ብልጽግና የሚለውን ሐሳብ በምልዐት መረዳትና ልስጋት ኢትዮጵያ ራዕዩን መጋራት ያስፈልጋል። ብልጽግና በቁሳዊ ሀብት ብቻ የተገደበ አይደለም። ብልጽግና ሁለንተናዊ የሰውን ልጅ ፍላጎት በሚዛን ማሟላት ነው። ከፍ ሲልም የሰውን ሁለንተናዊ ገጽታ የሚመለከት ጥልቅ ዕይታም ነው። ብልጽግና የሰውን ሞራላዊ፣ ስሜታዊ፣ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊና አካላዊ ሥልጣኔን የሚመለከት ነው። ዜጎች የቁስ፣ የስምና የነጻነት ፍላጎቶቻቸውን በቀጣይነት ማሟላት እንዲችሉ ዐቅማቸውን ማሳደግ ነው።

ብልጽግና፣ ቀጣይነትና አስተማማኝነት ያለው የሰው ልጆችን ነጻ የምርጫ አድማስ በማስፋት፣የዜጎችን ደኅንነት ማረጋገጥ ነው። “ሰው ሰው በመሆኑ ብቻ ክብሩና ነጻነቱ ሊከበር ይገባል። በመሆኑም ግለሰባዊ ነጻነትና ቡድናዊ መብቶች የተከበሩባት ሀገር መፍጠር ነው።ማኅበረሰባዊ ደኅንነቱ የተረጋገጠ ማኅበረሰብ መገንባት ነው። ሀገራዊ አንድነቷ የጸና ሀገር እንዲኖረን ማስቻል ነው። ሕዝብን በወንድማማችነት እኅትማማችነት ማስተሣሠር ነው። ኅብረ ብሔራዊ ማንነቷ ከአንድነቷ፣ አንድነቷም ከኅብረ ብሔራዊ ማንነቷ የተግባባላትን ሀገር መገንባት ነው።

CS CamScanner

በኢኮኖሚ መስክ የተረጋጋ ዐቢይ ንዋይ፣ ሚዛን የጠበቀና ቀጣይነቱ የተረጋገጠ የኢኮኖሚ ኢንቨስትመንት የተመቸና ለመዋቅራዊ ሽግግር የሚያስችል የኢኮኖሚ ከባቢ በመፍጠር፣ ዕድገት ለማረጋገጥ፣ ሁሉን አቀፍ የተቀናጀ ሪፎርም መተግበር ተጀምሯል። ቀጣይነት ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ በዓላማ እየሠራን ነው።

ኢኮኖሚው በፍጥነት ዕድገቱ የሚጨምርበት፣ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በሁሉም አካባቢ በጥራት የሚደርሱበት፣ መሠረተ ልማት የሚስፋፋበት፣ መዋቅራዊ ሽግግሩ የሚጠናከርበት፣ ኢኮኖሚው መንገራገጮችን በማለፍ ጥንካሬውን የሚያሳይበት ምዕራፍ ላይ በቅርቡ እንደርሳለን። ኢኮኖሚያችን ለአፍሪካ ተምሳሌት ይሆናል። በዓለም ደረጃ ይወዳደራል። ማኅበረሰባችን ሁለንተናዊ የብልጽግና ዓምዶች የተሟሉለት ማኅበረሰብ ይሆናል። ኢትዮጵያም የደስተኛ ማኅበረሰብ መኖሪያ ሀገር ትሆናለች። ይሄንንም በቅርቡ እውን እናደርጋለን።

ራዕያችን እንዲሠምር የግሉ ዘርፍ፣ ሕዝቡ፣ የሕዝቡ ልዩ ልዩ ነባር ተቋማት፣ ምሁራንና ሲቪል ማህበረሰቡ የተቀናጀ ተሳትፎ ያስፈልጋቸዋል። በመሆኑም ብሔራዊ ራዕይን ብሔራዊ አድርገን በእኔነት መንፈስ ለማስፈጸምና ለመደገፍ ራዕዩን መጋራት ያስፈልጋል። በአስቸጋሪ ጊዜና በድርብርብ ፈተናዎች እያለፍን መሥራት፣ ማድረግና መፈጸም ዕሴታችን ሊሆን ግድ ነው። ያን ጊዜ የኢትዮጵያ ብልጽግና አይቀሬ ይሆናል።

የምንፈልጋት ኢትዮጵያ እንድትፈጠር ወደፊት መመልከትና ራእያችንን መከተል ይገባናል። እጅ በማጣጠፍና በጥርጣሬ በመመልከት የሚገነባ ሀገር የለም። የጋራ ሕልማችንን ተጨባጭ ለማድረግና ይበልጥ በፍጥነት ለመቅረብ፣ ከትናንቱ በበለጠ ጠንክረንና ተባብረን መሥራት ይገባናል። ሁሉም የራሱ ሐሳብ፣ ምኞትና ሕልም አለው። ያ ክፋት የለውም። የሁሉም መሻት፣ ምኞትና ሕልም በትልቁ የኢትዮጵያ ብልጽግና ራዕይ ውስጥ እስካደረ ድረስ።

### 10.5. የመንግሥትና ሕዝብ ግንኙነት በመደመር መንግሥት

ኢትዮጵያ የልማታዊ መንግሥት ሞዴል በመተግበር አንጻራዊ ዕድገት አስመዝግባለች። ይሁን እንጂ በአዳጊ ሀገራት እንደሚሆነው ሁሉ በሀገራችንም የልማት ሞዴሉ ያመጣው ለውጥ እንዳለ ሆኖ፣ ዘላቂነቱ በመንግሥትና በሕዝብ ግንኙነት ባጋጠመው ስብራት የተነሣ ወደፊት መጓዝ አልቻለም። በአንድ ሀገር ልማት ውስጥ የመንግሥትና የማኅበረሰብ ግንኙነት ጤናማ ካልሆነ የልማት ዘላቂነትን ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል።

ልማት የሰዎችን ምልዐተ ፍላጎት በማሟላት ወደ ነጻነት ያደርሳል። ልማት ለነጻነት እንደሚያስፈልገው ሁሉ ነጻነትም ለልማት የግድ አስፈላጊ ነው። የመልማትና የነጻነት ፍላጎቶች እንዲሠምሩ የመንግሥትና የሕዝብ ግንኙነት በመደመር መንገድ መፍሰስ አለበት።

ፈጠራና ፍጥነትን እውን ለማድረግ ነጻነትና ኅብረት የተሰኙ አእምሯዊና ግዝፈታዊ ኃይላት እንደሚያስፈልጉ የመደመር መንግሥት ይረዳል። ነጻነትና ኅብረት ሰዎች በግላቸውና በቡድን በመቀናጀት ለአንድ ሀገር ልማት አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ቁልፍ መሣሪያዎች ናቸው። ነጻነትና ኅብረት እንዲያብቡ የልማት ዕድል፣ የዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች መከበር የግድ ናቸው። ከዚህ በተቃራኒ፣ ነጻነትን የሚያቆሽሹትና ኅብረትን የሚያፈርሱት መድሎ፣ መገለል፣ ዐመጽ፣ ልግመኝነት፣ ብዝበዛ

የመሳሰሉት የፖለቲካ ንግዶች ናቸው:: የመንግሥትና የሕዝብ ግንኙነት በእነዚህ ሁለት ዕይታዎች ውስጥ ሲታይ፣ የአንድን የልማት ሞዴል ተግባራዊ ስኬት ወይም ውድቀት አስቀድሞ ያመላክታል።

ግንኙነቶችን በአጠቃላይ በሦስት ከፍለን ማየት እንችላለን።

አንደኛው፡- አንዱ የሚያገኝበትና ሌላው የሚያጣበት።

ሁለተኛው፡- ሁለቱም የሚያጡበት ሲሆን፣

CS CamScanner

ሦስተኛው ደግሞ ሁለቱም የሚያገኙበት ነው። ከሦስቱምድብ መካከል አንዱ የሚያገኝበት ሌላው የሚያጣበት ሁኔታ በአዳጊ ሀገራት በስፋት ይታያል። ይሄም ፖለቲካዊ አልያም ማኅበራዊ መገለል የሚያመጣው ነው።

በሀገራችን የመንግሥት ሥልጣን ላይ የነበረው ፓርቲ በአፋር፣ በሶማሌ፣ በጋምቤላና በቤኒሻንጉል አድርሶት የነበረው ይሄንን መገለል ነበር። ለመገለሉ የተሰጠው ስያሜ "አጋር" የሚል የፖለቲካ አደረጃጀት ነው። እነዚህ ማኅበረሰቦች በገዥው ፓርቲ በኩል ጠቅላይ ሚኒስትርም ሆነ ፕሬዚዳንት ሆነው ሀገር የመምራት መብት አልነበራቸውም እንደ ማኅበረሰብም በማዕከላዊ መንግሥት ቢሮክራሲ ውስጥ እንዳይሳተፉ የሚያገልና በተግባርም የማያበረታታ ነበር። አንዱ ዕድል ሲያገኝ ሌላው እየተነፈገ የበይ ተመልካች በመሆን የቀጠለው ግንኙነት፣ በልማት ላይ የሚያስከትለው ልዩነት ከፍተኛ ነው።

ሁለተኛው፥ በፖለቲካ ገበያ የሚፈጠር ፖለቲካዊ ኢኮኖሚን ለመቆጣጠር በቡድኖች መካከል የሚደረግ የፖለቲካ ቁማር ነው። ይህ ግንኙነት ሁሉም በመጨረሻ የሚያጣበት ነው። በፖለቲካ ገበያ ብዙ ሀገራት የመፍረስ አደጋ ደርሶባቸዋል። አንዳንዶቹ ከነበሩበት ታላቅ የሥርዓተ መንግሥት ክብር ወርደው ማንም የሚዘውራቸው ሆነዋል። አንዳንዶች የፖለቲካ ገበያው የፈጠረባቸው ቁስል እያመረቀዘ መዳን አልቻሉም። በፖለቲካ ገበያ እናተርፋለን ብለው የገቡ ሁሉ ከራሳቸው ኪሳራ አልፈው ሀገራቸውንም አጥተዋል። በመሆኑም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል የሚኖር ግንኙነትን የሚፈትን የዜሮ ድምር ፖለቲካ የልማት ሞዴሎችን ያሰናክላል።

ሦስተኛው፥ ሁሉም የሚያሸንፍበት የመደመር ኃይል ነው። ሁሉም በኅብረት የድል ዋንጫውን ከተከታታይ ጨዋታና ከ90 ደቂቃ ፍጻሜ በኋላ የሚያሸንፍበት ነው። ሁሉን አሸናፊ የሚያደርገው ነጻነትና ኅብረት በአንድ መሥመር የሚጓዙበት የድል ጥምረት ነው። በዚህ ግንኙነት አንዱ የጎደለውን አንዱ ይሞላል። ሁሉም ያለውን ያዋጣል። በኅብረት ክንድ የከረሙ ዕዳዎች ይናዳሉ። በነጻነት ቀንዲልነት ፈጠራ ይበረክታል። ሁሉም ይተልማል፤ ሁሉም ይደክማል፤ ሁሉም ያሸንፋል።

ኅብረቱ በነጻነት ፋናነት የጋራ ራዕይ ይላበሳሉ። ወደ ራዕዩ ግብ በፈጠራና በፍጥነት ይደርሳሉ። የመንግሥትና ሕዝብ፣ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶች ሁሉ አሸናፊ በሚያደርግ የመደመር ዕሳቤ ሲቃኙ፣ የልማት ሞዴሎች የለሰለሰ መሬት እንዳገኘ ዘር ሥር ሰድደው ያማረ ፍሬን ያፈራሉ።

የመደመር መንግሥት ሞዴል በመደመር ፍልስፍና መሬት ላይ የሚዘራ ዘር ነው። አንድ ዘር በማዳበሪያ፣ በክብካቤና በጥበብ ብዙ ፍሬ እንድታፈራ እንደሚደረገው ሁሉ፣ የልማት አቅዶቻችን በፈጠራና በፍጥነት ታግዘው ብዙ ፍሬዎችን ያፈራሉ።

ይህንን ወደ መሰለ ልህቀት ለመድረስ የሦስቱ አካላት ቅንጅት እጅጉን ያስፈልጋል። የቢሮክራሲ መዋቅር፣ የማኅበረሰብ መዋቅርና የገበያ መዋቅር ግንኙነት ሥርዓታዊ ቅንጅት ሲፈጥሩ ለልማት ግቦች ዓምድ ይሆናሉ። በሕግ የሚመራ ጠንካራ የቢሮክራሲ መዋቅር በተደራሽነትና በማስተባበር የሚታወቅ ተገማች ሥርዓት ለመፍጠር ይረዳል። ይህ ደግሞ = በገዥው ፓርቲ በበኩሉ ፍጥነትን የሚጨምርና ከሌሎች መዋቅሮች ጋር በኅብረት ለመሥራት የሚችል መብት አልነበራቸው ዐቅምን ይፈጥራል። የቢሮክራሲ መዋቅር አንጻራዊ ጥንካሬው የሚሸለመውን እየሸለመ፣ እንዳይሳተፉ የ _የሚቀጣውንም እየቀጣ በመጓዝ ማሽኑ ከሥራ እንዳይቦዝን ለማድረግ መቻሉ ነው።

አንጻራዊ ድክመቱ ግትርነት ወይም ተላማጅ አለመሆኑ ነው። የቢሮክራሲ መዋቅሩ ከግትርነቱ ተላቆ እንዲፍታታና ተላማጅ እንዲሆን በፈጠራና በፍጥነት ውስጥ መግባት አለበት። ፈጠራና ፍጥነት ቢሮክራሲው ያለውን ጥንካሬ ይዞ፣ ችግሩን ፈትቶ፣ የኅብረቱ የግንኙነት አስኳል እንዲሆን ያስችለዋል።

ሁለተኛውና ትልቁ ማኅበረሰባዊ መዋቅር ነው። ማኅበረሰባዊ መዋቅር የጋራ ዕሴት፣ የጋራ ፍላጎትና የጋራ እንቅስቃሴ ባላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚመሠረት ነው። በግንኙነት ውስጥ ያለው ሚና ትልቅ ነው። ይህ ማኅበረሰባዊ መዋቅር

CamScanner

ብዙኃን የሚሳተፉበት በመሆኑ _ በማኅበረሰብ ውስጥ የቆዩ በመሆናቸው ሥራቸውን የሚያከናውኑበት ሂደት ከታች ከፍተኛ ማኅበረሰባዊ ግፊት መፍጠር ይችላል። ማኅበረሰባዊ መዋቅሮች ለረጅም ጊዜ ወደ ላይ ነው። ማኅበረሰባዊ መዋቅሮች በራሳቸው ከፍ ያለ ዐቅም አላቸው። እንዲሁም ከማኅበረሰብ ጋር የተጋመዱ እንደመሆናቸው መዋቅራዊ

ቅንጅቱን ማሣለጥ ይቻላቸዋል:: የልማት ውጥኖች ግባቸውን እንዲመቱ የሚኖራቸው ቅንጅታዊ ድርሻም ትልቅ ነው። የገበያ መዋቅር በዋናነት ዋጋን ተከትለው በፍላጎትና በአቅርቦት የሚመሩ ተዋንያን መድረክ ነው። የዚህ መዋቅር ተዋንያን ግለሰባዊ ርካታን በመፍጠር ነጻነትን ማቀናጀትን ግባቸው ያደርጋሉ። ነጻነት ለገበያ መዋቅሩ የፈጠራ ዐቅምን ያጎለብትለታል። የገበያ መዋቅሩ በግለሰባዊ ግንኙነቶች ላይ የተመሠረተ ቢሆንም መድረኩ በራሱ የሚፈጥረው ሕግ አለ የነጻነት ምኅዳሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የሁለቱ መዋቅሮች ተጽዕኖ ዜሮ ነው ማለት አይቻልም በመሆኑም የገበያ መዋቅሩ ከሁለቱ መዋቅሮች ጋር ያለው ግንኙነት ተሣላጭ መሆን ለገበያው ፈጠራና ፍጥነት ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና አለው፡

እንደሚታወቀው የመደመር መንግሥት ሞዴል ፈጠራን የሚያበረታታ፣ ፈጠራን የሚመራና ገበያን የሚፈጥር ነው። በዚህ የተነሣ ለገበያ መዋቅሩ አዲስ ዕድልን ይፈጥራል። የገበያ መዋቅርን ከሚፈትኑ ተግዳሮቶች አንዱ መዋቅሩ በግለሰቦች እጅ ወድቆ ለግልና ለቡድን እኩይ ዓላማ የማዋል አዝማሚያው ነው። በብዙ ሀገራትም ግለሰቦችና ቡድኖች የቢሮክራሲና የገበያ መዋቅሮችን ተቆጣጥረው ከሀገር ጥቅም ይልቅ የግልና የቡድን ጥቅም ማካበቻ ሆነው ይታያሉ።

እንደሚታወቀው አንድ የልማት ሞዴል ፖለቲካዊ መረጋጋትና መግባባት ሳይኖር በሚፈለገው መጠን የለውጥ ፍጥነትን ማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል። የሦስቱ መዋቅራዊ ግንኙነቶች ስብራት አንዱ ጎማ ተንፍሶ እንደሚጓዝ መኪና ነው። መኪናው ፍጥነቱ አዝጋሚ ይሆናል። የጉዞው ቀጣይነትም አያስተማምንም። የመንግሥትና ሕዝብ እንዲሁም የሕዝብና ሕዝብ ግንኙነት በቢሮክራሲ፣ በማኅበራዊና በገበያ መዋቅሮች ሲቀናጅ፣ ሁለንተናዊ ሀገራዊ ብልጽግናን ለማሳካት አስቻይ መደላድል ይሆናል።

**10.6.** መንግሥትና የንግድ ማኅበራት

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዓለምን ምስቅልቅል ውስጥ ከትቷት ነበር ያለፈው። አንዳንድ ሀገሮች ከዚህ ምስቅልቅል በመውጣት ድህነትን ሰብረው ወደ ብልጽግና ጎዳና ለመገሥገሥ ችለዋል። እነዚህ የትናንት አዳጊ፣ የዛሬ ያደጉ ሀገራት የተለያየ የልማት ሞዴል ተከትለዋል። ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ቢኖር የግሉን ዘርፍ የብልጽግና ማዕከል ማድረጋቸው ነው። ባለ ራእዮችን መደገፋቸውና ማስተዳደራቸው ለዕድገታቸው ፍጥነት አስቻይ ዐቅም ሆኗል። ቢሮክራሲው ሞያን፣ ብቃትንና ተወዳዳሪነትን መሠረት ያደረገና በሕግ የሚመራ አድርገው መንግሥታት ገንብተውታል። የግሉ ዘርፍ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ፣ ሀገራዊ የልማት ዕቅዶች በፍጥነት እንዲሳኩ አስችለዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት አምስት መሠርት ዓመታት የመንግሥት መዋቅር በቤተሰብ፣ ለሥርዓቱ ቅርብ በመሆንና በፓርቲ የተያዘ ነበር። በዚህ የተነሣ በብቃት ላይ የተመሠረተ ተቋም ለመገንባት ነጻነት አልነበረም። በመሆኑም የመንግሥትን የልማት ቢሮክራሲያዊ ቅድና የግሉን ዘርፍ ፍላጎት ለማርካት የሚችል ተቋማዊ ዐቅም አልገባንም። ከዚህ የተነሣ ቡግሉ ዘርፍና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት ገበያው በሚፈልገው ልክ አይደለም።

ባለፉት ሦስት ዐሠርት ዓመታት በሀገራችን አበረታች የግል ዘርፍ ዕድገት መታየቱ አሌ አይባልም። ነገር ግን የግሉን ዘርፍ ፉክክር የሚጎዱ የፓርቲ ኢንዶውመንቶችና ኦሊጋርኬዎች ተፈጠሩ። ለእነዚህም ከገበያ ሕግ በተቃርኖ የሚደረጉ ድጋፎች ስለነበሩ ፉክክሩን ገደሉት። በመንግሥት የፖሊሲ አፈጻጸምም ላይ አሉታዊ አንድምታ አሳደሩ።

የግሉ ዘርፍና መንግሥት በልማት የፖሊሲ ትኩረትና አቅጣጫ ላይ ለሚደረግ ውይይት በጠረጴዛ ዙሪያ ቢሰባሰቡም፣ ወንበሩን የያዙት ግን አንድ ዓይነት ሰዎች ነበሩ። እነዚህ አንድ ዓይነት ሰዎች ከግሉ ዘርፍ ይልቅ ለሥርዓቱ የቀረቡ

CamScanner

በመሆናቸው፣ ሐቀኛ ውይይትና ክርክር አይደረግም። የዚህ መሠረታዊ ዕሳቤ የኢኮኖሚ የበላይነትን በማረጋገጥ፣የፖለቲካ ሥልጣን እናስጠብቃለን ከሚል የመነጨ ርምጃ ነው።

ሥር ነቀል የፖሊሲ ለውጦችና ማሻሻያዎችን ለማከናወን የፖለቲካ ቅቡልነትን ከሰፊው ሕዝብ ማግኘት ይጠይቃል። የሚደረጉ የፖሊሲ ለውጦች ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖራቸው በማድረግ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን እያረጋገጠ የሚሄድ ሥርዓት በድርድርና በመግባባት መፍጠር ይቻላል። ይህም የግሉ ዘርፍ ለልማት ፖሊሲዎች አፈጻጸም የሚኖረውን ሚና በሙሉ ዐቅሙ እንዲያወጣ ያስችላል፡

የመንግሥትና የግሉን ዘርፍ ትሥሥር ለማጠናከር፣ የመንግሥት ፖሊሲና ግቦች ላይ እንዲወያዩና እንዲደራደሩ የሚያስችል ተቋማዊ አሠራርን መዘርጋት ይገባል። ከግሉ ዘርፍ ጋር በሚደረግ ውይይትና መግባባት፣ የመንግሥት የልማት ፖሊሲ አቅጣጫና አፈጻጸም በጋራ ራዕይ ላይ ከተመሠረተ፣ ወደ ልማት ግቦቻችን ለመድረስ የመጀመሪያውን ርምጃ እንደመራመድ ይቆጠራል።

ከዚህ ቀደም መንግሥት የካፒታል ግንኙነቶችን መሠረት አድርጎ ፖሊሲዎችን በማስገደድ የመተግበር አካሄድን ብቸኛ መንገድ አድርጎ ሲጠቀም ቆይቷል። እንዲያም ሆኖ የልማት ፖሊሲዎችንና ዕቅዶችን በማስተግበር ረገድ ያለው ገቢራዊ አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው። ከአፈጻጸም ባሻገር የፖሊሲ አቅጣጫ ልዩነት እንዲከሠትም ምክንያት ሆኗል።

በፍጥነት ያደጉ ሀገራት በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል ያሉ ግንኙነቶች በንግድ ማኅበራት አማካኝነት የሚሣለጡ ናቸው። የንግድ ማኅበራት በሥልጣን ላይ ካለው መንግሥት ጋር የንግዱን ማኅበረሰብ በሚመለከቱ ጉዳዮች በአጋርነት ይሠራሉ። የፖሊሲ ማብራሪያ ላይ በመሳተፍና በመሞገት የነጠረ ፖሊሲ እንዲወጣ ያደርጋሉ። የወጣውንም ፖሊሲ ከኢንቨስትመንት ዕቅዶቻቸው ጋር አጣጥመው ያስፈጽማሉ።

የንግድ ማኅበራት የመንግሥትን ስትራቴጂዎችና ተግባራት ለአባሎቻቸው በማብራራት የማኅበሩንና የመንግሥትን ፍላጎት ያጣጥማሉ። በፖሊሲ አቅጣጫው መሠረት ኢንቨስትመንቶች እንዲከናወኑ ያደርጋሉ። የንግድ ማኅበራቱ የኢንተርፕረነሮችን ፍላጎት ዋጋ በመስጠት፣ የመንግሥት መዋቅሮች ጉዳያቸውን እንዲረዱና የፖሊስ ማስተካከያና ድጋፍ እንዲደረግ ያግባባሉ። ግፊትም ያደርጋሉ።

በአንጻሩ በኢትዮጵያ ያለፉት መንግሥታት ልማድ፣ ከንግድ ማኅበራት ጋር ተቋማዊ ድርድር ከማድረግ ይልቅ በቁጥጥርና በኃይል ላይ ያተኮረ አካሄድ ነበረ። ይህም የንግድ ማኅበራት የግሉን ዘርፍ ጥቅም የመወከል ዐቅም የሌላቸው ሆነው እንዲታዩ አድርጓል። ማኅበራቱ የሥርዓቱ ተላላኪዎች ተደርገው በአባሎቻቸው በመቆጠሩ፣ በአባሎቻቸው ዘንድ ተቀባይነት እንዲያጡ ሆነዋል። በንግድ ማኅበራትና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት የግል ዘርፉን ተሳትፎ ለማረጋገጥ ያለው ሚና ከፍ ያለ ነው።

የንግድ ማኅበራቱና የመንግሥት ግንኙነት በተገቢ መንገድ ባለመመቻቸቱ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤትን ዋልታ ረገጥ ኃይሎች ፖለቲካዊ ሜዳቸው እንዲያደርጉት አሳልፎ ሰጥቶታል። በዚህ የተነሣ የግሉን ዘርፍ ጥቅም በሐቀኝነት የሚወክል በመጥፋቱ፣ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል አገናኝ ድልድይ እንዳይገነባ ተደርጓል። ብሔርን መሠረት ያደረገ የንግድ ማኅበራት አደረጃጀት የንግዱን ማኅበረሰብ ከንግድ መነጽር ዕይታ አውጥቶት በብሔር መነጽር እንዲተያይ አድርጎታል። በመሠረቱ ንግድ እንኳን ብሔር ሀገርም አይበቃው።

የንግድ እንቅስቃሴ ወገን ዘለል ብቻ ሳይሆን ድንበር ዘለልም ነው። ይህንን የንግድን ባሕርይ ከግምት ያላስገባው የንግድ ማኅበራት የብሔር አደረጃጀት፣ በብሔሮች መካከል ውጥረት እንዲፈጠር አድርጓል። በንግዱ ማኅበረሰብ ዘንድም መከፋፈልን ፈጥሯል። የንግድ ማኅበራቱ የአባላቶቻቸውን ጥቅም ማስከበር አለመቻላቸው ብቻ አይደለም። የመንግሥትን የልማት ፖሊሲና ዕቅድ ተረድተውና ተበረታትተው ለመተግበር አልቻሉም። ለግብርና ዘርፍ መንግሥት የፖሊሲና

CamScanner

የፋይናንስ ድጋፍ አድርጓል፡፡ እንዲሁም ለአምራች ዘርፉ ድጋፍና ማበረታቻ ተሰጥቷል፡፡ በተቃራኒ ግን ዕድገት እያስመዘገበ ያለው ብዙም እገዛ ያልተደረገለት የአገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡ ይህም በግሉ ዘርፍና በመንግሥት መካከል መናበብና መግባባት አለመፈጠሩን ያመለክታል፡፡

የመንግሥትንና የንግዱን ማኅበረሰብ ግንኙነት ተቋማዊ ለማድረግ ባለመቻሉ፣ በግሉ ዘርፍና በመንግሥት ባለ ሥልጣናት ግላዊ ግንኙነቶች ላይ ጥገኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ሁኔታን አመቻችቷል፡፡ ይህን መሰል ያልተገባ ግንኙነት ደግሞ የመንግሥት የልማት ዕቅዶች ይህ ደግሞ በግል ዘርፉና በመንግሥት መካከል ያልተገባ ግንኙነት በመፍጠር ለሌብነት ምቹ አፈጻጸምና የግሉ ዘርፍ ዕድገት በሚፈለገው ልክና አቅጣጫ እንዳያመሩ አድርጓቸዋል፡፡

የኢሕአዴግ መንግሥት በየደረጃው ባሉ የግሉ ዘርፎች ተዋናዮች መካከል የፓርቲ አባልነትን የሚያጎለብትበትን አሠራር ዘርግቶ ነበር፡፡ የንግድ ድርጅቶች በመንግሥት ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ በማድረግ ታማኝነታቸውን ለመግዛት ሞክሯል፡፡ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ግብአት በማቅረብ ከኢሕአዴግ ጋር የተሣሠሩ ነበሩ፡፡

በዚህ የተነሣ በመንግሥት የመወዳደሪያ ሜዳቸውን የተነጠቁ የግሉ ዘርፍ ተዋንያን ከዘርፉ ድጋፍ በማጣታቸው የተነሣ ወጡ፡፡ በመንግሥት የሚደገፉት አንዳንድ አካላትም ዘርፉን በብቸኝነት እየተቆጣጠሩት መጡ፡፡ በርካቶቹ የግሉ ዘርፎች መንግሥትን ከሚያስተዳድረው ፓርቲ ወገን ጠባቂና ተከላካይ ከሌላቸው በቀር፣ መከራ ውስጥ ይወድቁ ነበር፡፡ የንግድ ፈቃዶችን ለማደስ፣ አዲስ የሥራ ፈቃድ ለማግኘት ወይም የብድርና የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት መንገዱ እንደ ሲኦል መንገድ አስቸጋሪ ሆኖባቸው ቆይቷል፡፡

እንዲህ ዓይነት መሠረታዊ ስሕተቶችን ለማስተካከል ቆራጥ ውሳኔ ያስፈልግ ነበር፡፡ ንግድ በቀላሉ የሚሠራበትን ሥርዓትና አገልግሎት ፈጥሮ የሀገር ውስጥ ባለ ሀብቶች ባላቸው ችሎታና ካፒታል ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሥርዓት ዘርግተናል፡፡ የግሉ ዘርፍ ከገዥው ፖርቲና ከብሔር ጥገኝነት ተላቆ፣ በባለ ራዕይ ዕሳቤ የሚመራበት መንገድ ተጀምሯል፡፡ የንግድ ማኅበራትና መንግሥት ከፖለቲካ ሥልጣን ሥጋት ተላቅቀው እንዲጓዙ እየተደረገ ነው፡፡ የሁለቱም የጋራ ጉዞ የግሉን ዘርፍ ያካተተ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ዕቅድ ትግበራን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ሁለቱንም ኃይሎች አሸናፊ ያደርጋል፡፡

የመደመር መንግሥት የመንግሥት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊነት ላይ ሳይሆን፣ ምን ዓይነት ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋል? በሚለው ላይ ያተኩራል፡፡ ይህም የሚመለሰው መንግሥትና የግሉ ዘርፍ ባላቸው መስተጋብር ይሆናል፡፡ ብልጽግና የሚረጋገጠው የሁለቱ መስተጋብር እንዲሠምር የፖለቲካ ልሂቃኑ ሚናቸውን በሚገባ መወጣት ሲችሉ ነው፡፡

ቢሮክራሲያዊ ተቋሞቻቸው ደካማ የሆኑ መንግሥታት፣ በብዙ አቅጣጫ በሉዓላዊ ኃይላቸው ላይ ጣልቃ የሚገባባቸው ይበዛል፡፡ በዚህ ሳንካ የተነሣ በኢኮኖሚ ዕድገት የሚሳካላቸው ጥቂቶች ናቸው፡፡ ተቋማዊ ቢሮክራሲያቸው የዳበረና ሉዓላዊ ኃይላቸው አስተማማኝ የሆኑ መንግሥታት ግን የብልጽግና መንገዳቸው የቀና ይሆናል፡፡

የመንግሥትና የማኅበረሰብ መስተጋብራዊ ግንኙነት መጠናከር፤ በፖሊሲ፣ በስትራቴጂ፣ በግብና በአተገባበር ጉዳዮች ላይ የመደራደሪያ ምቹ መድረክ እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል:: ይህም መድረክ የፖለቲካ ልሂቁና የንግዱ ማኅበረሰብ ስለ ብልጽግና ለማውጋት አስቻይ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ግንኙነት ከኢመደበኛነት ይወጣል፡፡ ግንኙነቱ መንግሥት እንደ ተቋም፣ ሕዝብ እንደ ማኅበረሰባዊ መሠረት በመሆን ላይ ይመሠረታል፡፡ ብልጽግናን እውን ለማድረግ የመንግሥት ሉዓላዊ ኃይል መከበር ሆነ አካታችነት ብቻውን ውጤታማ አያደርግም፡፡ ይልቁንም የሁለቱን ኃይሎች መስተጋብር ሚዛን ጠብቆ ማራመድ በልማት መስክ ድል ያቀናጃል፡፡

የዳበረ ቢሮክራሲያዊ ተቋማት ካሏቸው ሀገራት አንዷን ኮሪያን በምሳሌነት እንመለከት:: መንግሥት ከንግድ ኩባንያዎች ጋር ጠንካራ ትሥሥር ፈጥሯል፡፡ በዚህም ኩባንያዎቹ የመንግሥትን ፖሊሲና ዕቅድ ተቀብለው እንዲተገብሩ አስቻይ

CamScanner

ሁኔታዎችን አመቻችቷል። ይህ ግንኙነት የጠቀማቸው የኮሪያ ኩባንያዎች፣ ከዓለም አቀፍ ገበያ ውድድር ተከልለው የቴክኖሎጂ ምርምርና ልህቀትን ሲደግፉ ኖረዋል። በዚህም ተወዳዳሪ ምርቶችን ይዘው ለመውጣት በ1960ዎቹ ያደረጉት ጥረት ተሳክቶላቸዋል። ዛሬ የኮሪያ ኩባንያዎች በቴክኖሎጂ ዘርፍ ከቀዳሚዎቹ ተርታ ተሰልፈዋል።

በቅርብ የሩሲያና የዩክሬን ጦርነትን ተከትሎ የአውሮፓ ሀገራት ለጦር መሣሪያ አቅርቦት ደቡብ ኮሪያን ነበር የመረጡት። የዚህ ዋናው ምክንያት በፍጥነትና በጥራት ለማቅረብ ከአውሮፓና ከሌሎች ያደጉ ሀገራት የተሻለ ዐቅም በመፍጠሯ ነው።

ብራዚል ከኮሪያ ያነሰ፣ ከላደጉ ሀገራት ግን የተሻለ ቢሮክራሲያዊ አደረጃጀት አላት። የቴክኖሎጂ ተቋሞቿ ቢሮክራሲያዊ አደረጃጀት የተሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከቴክኖሎጂ ውጭ ያለው የመንግሥት ቢሮክራሲያዊ አደረጃጀት ግን ግላዊ ግንኙነትን መሠረት ያደረገ ሆኗል። አጠቃላይ የሀገሪቱ ተቋማዊ ቢሮክራሲ ስላልዳበረ፣ የቴክኖሎጂ ፖሊሲ ትግበራ ዘላቂና ቀጣይ እንዳይሆን ፈትኗታል። የፖለቲካ ልሂቁም ከገበያ ተዋንያኑ ጋር ያለው መስተጋብር እንዲሳሳ አድርጓል።

በአጠቃላይ መንግሥትንና ማኅበረሰቡን የሚያስተሣሥር ተቋማዊ ቢሮክራሲ አለመዳበር በብልጽግና ስኬቶች ላይ አሉታዊ አንድምታ እንዳለው የብራዚል ተሞክሮ ያስረዳናል።

ለምሳሌ የአይሲቲ. ኩባንያዎች ሐርድዌርና ሶፍትዌሮችን አምርተው የገበያ ትሥሥር የሚጠብቃቸው የፖለቲካ ልሂቅ ትኩረቱ በሌሎች የፖለቲካ አጀንዳዎች ላይ በመሆኑ ነው። በመፍጠር፣ በዓለም አቀፍ ውድድር ማሸነፍ አልቻሉም። የዚህ ዋናው ምክንያት ደግሞ በዚህ የተነሣ የቴክኖሎጂው ዘርፍ አጋዥ እንዲያጣ አድርጎታል። የብራዚል ሉዓላዊ መንግሥታዊ ኃይል ቢኖረውም፣ በአካታችነት ረገድ ውሱንነት ነበረበት። ይህም መንግሥት ተስፋ ሰጪውን የአይ.ሲ.ቲ. ዘርፍ ተስፋውን አደብዝዞታል።

ሕንድም እንደ ብራዚል የቢሮክራሲ ሥርዓቷ ባይዳብርም፣ የልማት ዕንቅፋታቸው የአንድ ማኅበረሰባዊ አወቃቀር ውስብስብ ነው። ሕንድ በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በክልላዊ አስተዳደር መሥመር የተከፋፈለች ሀገር ናት። በዚህ ሁሉ መካከል ሰፋፊ መሬቶችን የያዙ ልሂቃን ሞልተዋል። በእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ መንግሥት ስለ ኢንዱስትሪ ለውጥ ከማኅበረሰብ ጋር መደራደር ይኖርበታል።

በመሆኑም በመጀመሪያዎቹ የዕድገት ጅማሮ ጊዜያት መንግሥት በአይቲ ቴክኖሎጂ ምርት ላይ በቀጥታ በመሳተፍ ለመግፋት ሞክሯል። ይህም የሆነው መንግሥታዊ ሉዓላዊ ኃይሉን ተጠቅሞ ነው። ይሁን እንጂ በማኅበረሰቡ መከፋፈል የተነሣ የአካታችነት ተግዳሮት ገጥሞታል።

የሕንድና ብራዚል በዚህ ሂደት እንደ ደቡብ ኮሪያ ያለ ዕድገት ባያስመዘግቡም አንጻራዊ ዕድገትን በየፈርጁ አስመዝግበዋል። የብራዚል ዕድገት በሉዓላዊ ኃይል ጉድለት የተነሣ ሲገደብ፣ የሕንድ ዕድገት ደግሞ ከአካታችነት ጉድለት የተነሣ ፍጥነቱ ተይዟል።

በአንድ ሀገረ መንግሥት ሥርዓት ውስጥ ፈጠራና ፍጥነትን ለማረጋገጥ መንግሥታዊ ሉዓላዊ ኃይል አካታችነትን እንደ ደቡብ ኮሪያ ማስፈን አለበት። በአንድ በኩል የመንግሥትን ሉዓላዊ ኃይል ጠብቆ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበረሰብን አካቶ የሚገነባ ሥርዓት ሚዛኑን ጠብቆ መጓዝ ይችላል። በዚህ መሰል ጥምረት የሚመጣን ዕድገት ከፍጥነቱ የሚገታውም ሆነ የሚጎትተው ኃይል አይኖርም።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሀገራት የምትጋራቸው የመንግሥት ጥረቶችና ማኅበረሰባዊ ብዝኃነቶች አሉ። በተለያዩ የመንግሥት ሥርዓቶቻችን፣ የመንግሥትን የቢሮክራሲ ኃይል በመጠቀም አካታችነት የጎደለው ረጅም የአገዛዝ ዘመን አሳልፈናል። ይህም የሀገር ሀብት በሌቦች እንዲመዘበር አድርጓል። የመንግሥት አጠቃላይ ቢሮክራሲ ባለመዳበሩ የመከኑ

CamScanner

የዕድገት ተስፋ ውጥኖች በርካታ ናቸው። ባለፉት ሦስት ዐሠርት ዓመታት የግሉ ዘርፍና የመንግሥት ፖሊሲ ጉዞ በተቃራኒ ስለ ነበረ፣ እንደ ብራዚል በፖለቲካ ልሂቃን መጠለፉ ይጠቀሳል።

ከመንግሥት ቢሮክራሲያዊ ድክመት ባሻገር ሀገራችን እንደ ሕንድ ብዝኃ ማንነት ያለባት ሀገር ናት። ይህ ነባራዊ ሁኔታ በአካታችነት የመንግሥት ፖሊሲና ግብ ላይ ድርድር ለማድረግ ቀላል አይደለም። ሥር ነቀል የልማት ፖሊሲዎችና ትግበራቸው ከብሔር፣ ብልጽግና መንግሥታዊ አካታችነትን ለማስፈን የፖርቲው አደረጃጀት የተሻለ ዕድል ይሰጠዋል። ከሃይማኖት ወይም ከክልላዊ አስተዳደር መሥመር ጋር ተያይዞ ጥያቄዎች ይሡባቸዋል። ለዚህም ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶችን ማንሣት ይቻላል።

አንደኛ፣ ኅብረ ብሔራዊ ፓርቲ መሆኑ ሰፊ ማኅበራዊ መሠረት እንዲኖረው ያደርገዋል። በሚዛን ጠብቆ ለመራመድ አፈጣጠሩ ዕድል ሰጥቶታል። ይሁንና ዕድሉ ከፈተና የጸዳ ነው ሁለተኛ፣ የመሐል ፖለቲካ አራማጁ ዐቅም ይሆነዋል። የመንግሥት ሉዓላዊ አካታችነትን ማለት አይቻልም። ዋልታ ረገጥ ፖለቲካን ያልተሻገረ የፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ ነን። ሁለቱን አጣጥሞ መጓዝ ያለው ፈተና ቀላል አይደለም።

### 10.7. የመደመር መንግሥት፡ የፖለቲካ ምኅዳር

ሀብት ሊፈጠር የሚችለው ምቹ የሆነ የፖለቲካ ምኅዳር ሲኖር ነው። ውጤታማ የሆነ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲሁም ውጤታማ የመንግሥት ሚና እንዲኖር፣ ምቹ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ምኅዳር ያስፈልጋል። ኢኮኖሚው መልክና ሥርዓት ኖሮት እንዲሠራ፣ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚው መልክና ሥርዓት መያዝ ይገባዋል። በጥቂት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ ፈጣን ልማትን ያረጋገጡ ሀገራት እውነታም ይህንን የሚያሳይ ነው። ሀብት ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ መንግሥት በተገቢው ሁኔታ ሚናውን እንዲወጣ፣ ብሎም ጠንካራ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲኖር የፖለቲካዊ ኢኮኖሚው ሁኔታ የተስተካከለ ሊሆን ይገባል። የመደመር መንግሥት ስኬታማነት በእነዚህ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ ነው።

የመጀመሪያው ቁልፍ ጉዳይ ንግድን ለመሥራት የሚያስችል የተረጋጋና ተገማች የፖለቲካ ሁኔታ ያሻል። የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ከሌለ ሀብት መፍጠር አይቻልም። እንዲያውም የተፈጠረ ሀብትን ለብክነትና ለውድመት ይዳረጋል። ያልተረጋጋና ምቹ ያልሆነ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምኅዳር፣ ከፍተኛ የመበልጸግ ዕምቅ ዐቅም ያላቸውን ሀገራት ለጉስቁልናና ለስቃይ ሲዳርግ ተስተውሏል።

በለውጡ አምስት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከነበረው በእጥፍ አድጓል። ያልተረጋጋው የፖለቲካ ሁኔታ ግን በኢኮኖሚው ላይ ከባድ ጫና አሳርፏል። ኢኮኖሚው ምቹ የፖለቲካ ምኅዳር ቢያገኝ ኖሮ ከዚህ የተሻለ ሊያድግ እንደሚችል አያጠራጥርም።

ፖለቲካው ሰፊ ሀብትን ለውድመትና ለብክነት በመዳረግ ተጨማሪ ዕድገት ማስመዝገብ ሚቻልባቸውን ሁኔታዎች ዘግቷል። ከዚህም በተጨማሪ ያልተረጋጋው የፖለቲካ ሁኔታ ያለን ዕምቅ ሀብት (ለምሳሌ ማዕድን) ለጥቂቶች መጠቀሚያ እንዲውል አድርጓል። በተለያዩ ፕሮጀክቶች ላይ የፈጠረው ጫናም ቀላል አይደለም። በአጠቃላይ በኢኮኖሚው ላይ የፈጠረው ጫና ከፍተኛ ነው።

ሁለተኛ፥ የሀገራት የልማት ፍላጎት፣ ተነሣሽነትና ሂደት እንዲሁም የመንግሥታት የትግበራ _ወቅም፣ ሀገራት ባላቸው መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ተቋማት ተጽዕኖ የሚያርፍበት ነው። ተቋማት በሀገር የልማት ፍላጎት፣ በትግበራ፣ በሂደትና በመሰል ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል። ተቋማቱ በብቁ የሰው ኃይል የተሞሉና ከሌብነትና ከብልሹ አሠራር መጽዳታቸው ለመደመር መንግሥት ውጤታማነት ቁልፍ ነው።

CamScanner

ሦስተኛ፥ ልማት እንዲኖርና ቀጣይነቱ እንዲረጋገጥ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች(መሪዎች፣ ኢንቨስተሮችና ሰፊው የኅብረተሰብ ክፍል) ከልማት ተልዕኮና ግብ ጋር ሊተሣሠሩ ይገባቸዋል። ብልጽግናን ማረጋገጥ የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉ። ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችል የጋራ ትልም መፍጠርና ያንን እውን ለማድረግ የሚያስችል የጋራ ተነሣሽነትና ትብብርን ይጠይቃል።

የጋራ ሕልምና የጋራ ተነሣሽነት እንዳይፈጠር በማድረግ የመደመር መንግሥትን ዐቅም የሚያዳክመውና ሀብት እንዳይፈጠር ዕንቅፋት የሚሆነው የፖለቲካ ገበያ ነው። የፖለቲካ ገበያ ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታን ይፈጥራል። ተቋማትን ያደቅቃል። የማኅበረሰብ ትሥሥር እንዲላላ ያደርጋል። ኢፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ያስችላል። ሌሎች አሉታዊ ተጽዕኖዎችንም ያስከትላል። የፖለቲካ ገበያ ለሀገረ መንግሥት ቅቡልነት ክፍተት ምክንያት የሆኑ ልዩነቶችንና ትርክቶችን እንደ አጀንዳ ይጠቀማል። ኢመደበኛና ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ ሥልጣንና ሀብትን ለመቀራመትም ጥረት ያደርጋል።

ይህ የሐሳብ አልባ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሁኔታ ሕጋዊ የሆነ ሥልጣንና ሀብት የማግኛ መንገድን ያዳክማል። በምትኩ ሕገ ወጥ፣ ኢመደበኛና ያልተረጋጋ ሂደት እንዲሠለጥን ያደርጋል። የዚህ ፖለቲካ ተዋንያን አንደኛ ግባቸው በዋናነት ግላዊ ነው። ዓላማቸው ፖለቲካዊና ከፍ ያለ ሀገራዊ ግብ ለማሳካትና ያነገቡትን አማራጭ ሐሳብ ለማስፈጸም አይደለም። ፖለቲካዊ ኃይልን ለግል ጥቅማቸው ማሳኪያ እንደ መጨረሻ ግብ አድርገው የሚጠቀሙ ናቸው።

ሁለተኛ ይህን ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም የሚጠቀሙት መንገድ ኢመደበኛና ሕገ ወጥ ነው። የዘመድ አዝማድ የጥቅም ትሥሥር በመፍጠርና ኃይልን በመጠቀም ሀብትና ሥልጣን ለመቀራመት ጥረት የሚያደርጉ ናቸው። ሦስተኛ የትግል አጀንዳቸው ጽንፈኝነት የተላበሰ፣ ልዩነትን መሠረት ያደረገና ሕዝበኛ ነው።

በእንደዚህ ዓይነት ፖለቲካ ውስጥ የጋራ ግብን መፍጠርና በዚያ ዙሪያ መሰባሰብ አዳጋች ነው። ሁሉም ነገር ለግላዊ ጥቅም ሲባል የሚሸጥ የሚለወጥበት እንጂ፣ የሕዝብ ፍላጎትና ሀገርን የማሻገር ጉዳይ ቦታ የሚሰጠው አይደለም። ይህም ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲፈጠር፣ ተቋማት እንዲደቅቁ፣ የማኅበረሰብ ትሥሥር እንዲላላ፣ ኢፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር በማድረግ ወደ ጉስቁልና የሚያመራ መንገድ ነው።

ይህ ጉዞ ድህነትና ጉስቁልና የሀብት እጦት ብቻ ሳይሆን፣ የሰላምና መረጋጋት አለመኖር፣ ጦርነትና ሌሎች ችግሮችን ጭምር የሚያካትት ነው። በተጨማሪም ደካማ እርስ በእርስ መተማመንና መግባባት፣ የአንድነት እጦት፣ ደካማ የሥራ ባህልና የተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ድምር ውጤት ነው። ብልጽግና በሌላ በኩል የምርታማነት መረጋገጥ፣ አዎንታዊ ሰላም፣ ፍትሕ፣ የሕግ የበላይነት እንዲሁም የመቻቻልና የመግባባት መኖር ነው። ብልጽግናን ለማረጋገጥና መንግሥትም የመፍጠርና የመፍጠን ዐቅም እንዲኖረው፣ የተሻሻለ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሁኔታ ይፈልጋል።

CS CamScanner

# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## 11. ሐሳብ አልባ ፖለቲካ

ሃገራዊ ሀብት ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት አንድ ዋነኛ ፈተና አለበት። እርሱም ሀብትንና ' ሥልጣንን ኢመደበኛና ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ለመቀራመት የሚደረገው ሙከራ ነው። ይሄንን መንገድ "ሐሳብ አልባ ፖለቲካ" እንለዋለን። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ በሀገራችን በለውጥ መመታት ብልጽግናን ለማረጋገጥ ፈተና ሆነው ለቆዩት የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ግጭትና የሀብት ብክነት ተቀዳሚው ምክንያት ይህ ነው። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ በሐሳብ ልዕልና አያምንም። በሠለጠነ መንገድ አይጓዝም። ሀብትንና ሥልጣንን ኢመደበኛ በሆነ መንገድ መቀራመት ብቻ ነው ምኞቱም ግቡም።

ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ምኅዳር መደበኛና ሕጋዊ ፖለቲካዊ የኢኮኖሚ ሥርዓትን ይጠልፋል። ለምዝበራ ምቹ የሆነ ስንኩል ሥርዓት ይዘረጋል። ከዚያም የአንድን ሀገር የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሥርዓት ለመጋራት፣ ለመውረስ አልያም ለመቆጣጠር አልሞ ይሠራል። የሐሳብ አልባ ፖለቲካ ተዋንያን የፖለቲካ ሥልጣንን የሚፈልጉት የኢኮኖሚ ጥማቸውን ለማርካት ሲሉ ነው። ለእነርሱ የፖለቲካ ሥልጣን ሀገርና ሕዝብ የማገልገያ መሣሪያ አይደለም።

ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ትግል ሥርዓትን በመጠምዘዝ ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ ዳፋው ለሀገርና ለሕዝብ ይተርፋል። ትግሉ በሀገራዊ ብልጽግናና በንዑሳን ቡድኖች የግል መሻት መካከል የሚደረግ ነው። በዚህም ምክንያት ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ምኅዳር ብልጽግናን ለማረጋገጥ ዕንቅፋት የሆነ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሁኔታን ይፈጥራል። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ ግቡ ሀብትና ሥልጣንን ኢመደበኛ በሆነ መንገድ መቀራመት ነው። በመሠረቱ የዚህ ዓይነት የፖለቲካ ምኅዳር ዕሴት አይጨምርም። እንዲያውም የማኅበረሰብን ዕድገትና ብልጽግና በማቀጨጭ ሀገረ መንግሥቱን እያመነመነ ወደ ውድቀት እንዲያመራ ያደርገዋል።

ሐሳብ አልባ ፖለቲካ የሥራ ባህልን ያዳክማል። መሞዳሞድንና ማስመሰልን በማበረታታት ፈጠራን እርባና ቢስ ያደርገዋል። የሀብት ማግኛና ማፍሪያ መንገድን በትውውቅና በጥቅም ትሥሥር ብቻ ያደርጋል። በፖለቲካ ኢኮኖሚ ውስጥ የሚሳተፉ የፖለቲካና የንግድ ልሂቃን ፈጠራ በታከለበት መንገድ አዲስ ሀብት ከመፍጠር ይልቅ፣ ያለውን ሀብት ለመቀራመት ይራኮታሉ።

በመሠረቱ መቀራመት ከእጥረት አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው። በዚህ ውስጥ የሚሳተፉ ልሂቃን በፈጣራ ሥራዎች ላይ ለማተኮር የሚያስችል አእምሯዊ ዝግጁነት አይኖራቸውም። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ በገነነበት ምኅዳር ውስጥ ባሉ ሀገራት ተጨማሪ ሀብት አይፈጠርም። ስለዚህም ሕዝብ በድህነት ለመማቀቅ ይገደዳል። ሀገራዊ ዕድገትና ማኅበረሰባዊ ብልጽግና በንዑሳን ቡድኖች ስግብግብነት ይከሸፋል። በአንድ መንግሥት ሥርዓት ውስጥ ሐሳብ አልባ ፖለቲካ ከገነነ፣ የሀገራዊ ብልጽግና መቀጨጭንና የፖለቲካ ገበያ መፍካትን ያመለክታል።

ለሥርዓት ስብራት ቁልፍ መንሥኤዎች የተቋማት ደካማነት፣ የሰላምና የፖለቲካ ግብቡነት መዳከምና ሌሎች የፖለቲካ ሁኔታዎች አለመሟላት ናቸው። እነዚህ ጠንካራ ተቋማት በሌሉበትና የፖለቲካ መተማመንና ግብቡነት እየተዳከመ በመጣበት፣ ኢመደበኛና ልዩነትን መሠረት ያደረጉ የጥቅም ትሥሥሮች እየተጠናከሩ ይመጣሉ። ለጋራ ግብ የሚደረጉ ትብብሮች እየላሉ ለግላዊ ጥቅም የሚደረጉ ሽኩቻዎች እየተጠናከሩ ይመጣሉ፡ ልዩነትን መሠረት ያደረጉ ሥልጣንና ሀብትን መቀራመት የጥቅም ትሥሥሮችና ፉክክሮች ይጠናከራሉ። የፖለቲካ ገበያ ፖለቲካዊ ታማኝነት፣ ኃይልና ሥልጣን በገንዘብ፣ በጥቅም ትሥሥርና በዐመጻ የሚሸጥበት የሚለወጥበት ፖለቲካ ነው።

CamScanner

ጠንካራ ተቋማት የመገንባት ሂደትና ብልጽግናን የማረጋገጥ የመደመር መንግሥት አካሄድ ትልቁን ፈተና እያስተናገደ ያለው ከሐሳብ አልባ ፖለቲካ አካባቢ ነው። ጠንካራ ተቋማት ያልተገነባባት ሀገራችን ሥርዓትን በተመለከተ ሁለት የቤት ሥራዎች አሉባት። የመጀመሪያው በሥርዓት ስብራት ከመናጥ ወጥቶ ስብራቶችን የማቅናት ሥራ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ነባር ዕዳን የሚያሻግር ፈጣን ለውጥ ማምጣት ነው። ነገር ግን፣ በስብራቶቹ ሽንቁር ውስጥ ብቅ ብቅ እያለ ያለው የፖለቲካ ንግድ፣ የብልጽግና ጉዞን እንዳይቀለብሰው፣ ተግቶ መታገልን ይፈልጋል። የፖለቲካ ንግድ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሥልጣንና ሀብት በመቀራመት ሀገረ መንግሥቱን የመቆጣጠር ፍልሚያ ነው።

በአጠቃላይ አንድ ሥርዓት ብቁ የሆኑ ተቋማትን መገንባትና ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናን ማረጋገጥ ሳይችል ሲቀር ወደ ፖለቲካ ገበያ ሊያመራ ይችላል። ይህንን ክፍተት በመጠቀም ሀገረ መንግሥቱን በቁጥጥር ሥር በማዋል የገዛ ፍላጎታቸው ማስፈጸሚያ ያደርጉታል። የአንድ ሀገር የፖለቲካ ሥሪት ብልጽግናን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚናን ይጫወታል። ለብልጽግና አዎንታዊ የሆነ የፖለቲካ ምኅዳር እንዳይፈጠር እያደረገ ያለው ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ንግድ ነው። ብልጽግናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጉዞ ፍጥነትን በመግታት ብሎም በመሳብ ወደ ኋላ ሊያስቀረን የሚጎትተን የሐሳብ አልባ ፖለቲካ መኖር ነው።

በሐሳብ አልባ የፖለቲካ ምኅዳር ፍልሚያው ጥቂቶች ሀብትና ኃይል የሚጠቀልሉበት ይሆናል። መቆሚያ መሠረቱም ተቃርኖና ግጭት ነው። የፖለቲካ - ተዋንያኑን የሚያንቀሳቅሳቸው ኃይል አለመግባባት ነው። በሐሳብ አልባ ፖለቲካ አለመግባባት መርሕነት ይወሰዳል።

የፖለቲካ ገበያ ያለባቸው ሀገራት ሦስት ጠባዮችን ይጋራሉ። ከመደበኛ ሕግና አሠራር ይልቅ ግለሰባዊ የፖለቲካ ዐቅም ይነግሣል፤ ኪራይ ሰብሳቢነት በፖለቲካና በንግድ ልሂቃን ዘንድ _ይንሠራፋል፤ እንዲሁም የሀገር ውስጡ የጥቅም ሠንሰለት ከውጭው የጥቅም ሠንሠለት ጋር ይተሣሠራል። በዚህ የተነሣ የፖለቲካ ገበያ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ በአንድ ሀገር ውስጥ እንዳይፈጠር ያደርጋል። ተቋማት ይዳከማሉ። ማኅበራዊ _ስምምነት ይጠፋል። አክራሪነት ይነግሣል። የፖለቲካ መረጋጋት እንዳይኖርና ሰላም እንዳይሰፍን ይደረጋል። የፖለቲካ ነጋዴ ዐመጽንና ግጭትን እንደ ገበያም እንደ ማዳከሚያም ይጠቀምበታል። እንደ ገበያ በግጭቱ ውስጥ የኮንትሮባንድ ንግድ ያካሂዳል የመሣሪያ ንግድ ያጧጡፋል። የተከለከሉ ነገሮችን ያመላልሳል።

በሌላ በኩል ደግሞ ግጭቶች ሕጋዊ አሠራሮችን ለማስፈን ምቹ ሁኔታን ስለማይፈጥሩ የመንግሥት ቢሮክራሲ ይዳከማል። ሕግ የማስከበርና ቅጣትን የመጣል ዐቅሙ ይቀንሳል። የተዳከመ የመንግሥት ሥርዓት ደግሞ ለፖለቲካ ነጋዴዎች ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። የራሳቸውን የቢሮክራሲ መረብ ይዘረጋሉ፡ ከዚህ ሲብስ የራሳቸውን የታጠቀ ኃይል ያሠማራሉ። ይህንን መረብና ኃይል በመጠቀምም ሕገ ወጥ የጥቅም ትሥሥሮችን በመዘርጋት ሀብትና ሥልጣንን ይቀራመታሉ።

የጥቅም ትሥሥሮቹ የብሔርና ሌሎች የማንነት መሥመሮችን ተጠቅመው የሚፈጠሩ ናቸው። በእነዚህ ትሥሥሮች የመንግሥትን አሠራር የማዳከም፣ ውሳኔዎችን የማስቀልበስና የማዘግየት፣ ዐመጽና fከከት የማስነሣት ተግባራት ይከናወናሉ። ዋነኛው የፖለቲካ አጀንዳ በአክራሪ የፖለቲካ መሥመሮች መካከል የሚፈጠር ልዩነት ነው። ልዩነትን ማጉላትና ማክረር ደግሞ እንደ ኢኮኖሚና ፖለቲካ መጠቀሚያ ይታያል። እነዚህ የልዩነት መሥመሮች ሌላውን በማግለል ፖለቲካዊ ሥልጣንንና ሀብትን ለመቀራመት ይውላሉ።

በአንድ በኩል መንግሥት የመደመር መንግሥት ሆኖ ራሱንም ምልዐተ ሕዝቡንም ለማኅበራዊ ኢኮኖሚ ለውጥ ያነሣሣል። ያልነበረ ሀብት ይፈጥራል፤ አዳዲስ ሐሳቦችንም ያፈልቃል። ምቹ አሠራርና ቅልጥፍና ያሰፍናል።

እያንዳንዱ ዜጋም ሆነ ተቋም ዕሴት ጨማሪ ይሆናል። በተቃራኒው ደግሞ ሐሳብ አልባ ሀብት እንዳይፈጠር መሰናክል ይሆናል። ሀገርን ያጠፋል፤ ትውልድን ያመክናል። ይህ ፖለቲካ የሚፈጥረው የፖለቲካ ንግድ የተፈጠረውን ሀብት እንደ

CS CamScanner

ቅንቅን ይበላል። ተጨማሪ አስተሳሰብ በጥቅሉ ሀገርን ወደ ፖለቲካ ገበያነት የሚቀይር አስተሳሰብ ነው። ይህ ሐሳዊ መንገድ የሁሉም አዳጊ ሀገራት ይልቁንም የሀገራችን አረንቋ ሆኖ ከፊት ለፊታችን ቆሟል።

የፖለቲካ ንግድ አስተሳሰብ ትኩረቱ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ሀብትና የፖለቲካ ኃይልን መቀራመት እንደመሆኑ፤ ፈጠራንና ፍጥነትን ትኩረት ላደረገው ለመደመር መንግሥት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ግንባታ ዋና ደንቃራ ነው። የመደመር መንግሥት ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጠንካራ ተቋማትን በመገንባት፣ ብቃት ባለው አፈጻጸም፣ በትብብር፣ በሥርዓት ግንባታና ከፍ ባለ ሀገራዊ ርዕይ ላይ የተመሠረተ ነው። የሐሳብ አልባ የፖለቲካ ምኅዳር ግን ሕጋዊና ተቋማዊ ባልሆነ የጥቅም ትሥሥር፣ በሸኩቻ፣ በግላዊና ቡድናዊ ፍላጎት ላይ ይመሠረታል። ሀብት ፈጠራ እንዲካብትና ፖለቲካዊ ኢኮኖሚው እንዲረጋጋ፤ ጠንካራ ተቋማት ያሉት እና ፖለቲካዊ ስምምነትና ቁርጠኝነት ያለው ልሂቅ ሊኖር ይገባል።

የፖለቲካ ገበያ ግቡ ሀብትና ሥልጣን መቀራመት በመሆኑ፤ እዚያ ቤት የፖለቲካ ሀብትና ሥልጣን እንደ ሸቀጥ የሚሸጥ የሚለወጥ ነው። መደበኛና ሕጋዊ መሥመርን በመተካት በጥቅምትሥሥር ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ ይዘረጋል። በዚህም ዜጎች አገልግሎት የሚያገኙት ማንነታቸው ታይቶ አልያም በገንዘባቸው ገዝተው እንዲሆን ያደርጋል። በማንነታቸው የጥቅም ትሥሥር ይፈጥራሉ። እንዲሁም በገንዘባቸው ባለ ሥልጣንን በመግዛት የፈለጉትን አገልግሎት ያገኛሉ። ባለ ሥልጣናት ሥልጣን የሚያገኙትም ይሁን የሚያጸኑት አንድም በማንነታቸው በፈጠሩት የጥቅም ትሥሥር ነው። አልያም በገንዘብ አክቲቪስት፣ የብዙኃን መገናኛ፣ ምሁር፣ የተወሰነ ቡድንና ፖለቲካዊ ድጋፍ ገዝተው ነው።

በአጠቃላይ የፖለቲካ ገበያ በጥቅም ትሥሥር ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ ነው። ይህ የጥቅም ትሥሥር የሀብትና የኃይል ምንጭን በመቆጣጠር ያልተገባ ክብርና ዝናን አልመው በሚሠሩ ቡድኖች ይዘወራል። በጥቅሙ ላይ ከሚመጡበት ኃይሎች ራሱን ለማዳን አንድን ማኅበረሰብ ወይም አንድን ማንነት መከለያ ያደርጋል። እንዲህ ዓይነት ፖለቲካ በዋናነት ሦስት ፍላጎታዊ መገለጫዎች አሉት። ያልተገባ ሀብት፣ ያልተገባ ኃይልና ያልተገባ ክብር፡ እነዚህ ሦስት የፍላጎት መነሻዎች እርስ በራሳቸው ይደጋገፋሉ። አንዱ የአንዱን ፍላጎት እንዲያሟላ በማድረግ በተዋንያኑ መካከል ጠቅላይ እንዳይኖር ይሠራል። ይህ የእከከኝ ልከክህ አካሄድ፣ በመንግሥትና በማኅበረሰብ መዋቅሮች ውስጥ ሳይጠፋፉ የተወሰነ ርቀት እንዲጓዙ ያደርጋቸዋል።

በጥቅሉ የሐሳብ አልባ ፖለቲካ ኢኮኖሚው የንዑስ ቡድኖችንና የግለሰቦችን ፍላጎት በማርካት የሚገፋ ነው። የፖለቲካ ኢኮኖሚው ለሐሳብ ቦታ የማይሰጥ በመሆኑ መፍጠርና መፍጠንን አዳጋች ያደርገዋል። ሩጫው የተፈጠረን ሀብት ለመቀራመት ነው። መርfh - ለእኔ፣ ወደኔ፣ ስለ እኔ፣ በእኔ" የሚል ብቻ ነው። የቻለውን አፍሶ የቀረውን አተራምሶ በመውጣት የሚመራ የስግብግብ ፖለቲካ ነው።

ማተራመስና መስገብገብ በመደናበር ውስጥ ያለ ኃይል መገለጫ ነው። የሚደናበር አቅጣጫውን አያውቅም። በመሆኑም ፈጥኖ ከመውጣት ባለበት ዙሪያ ገባውን መማሰን ዕድል ፈንታው ይሆናል። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ፣ አካባቢውን ከማውደም ያለፈ አዲስ ነገር አይፈጥርም።

### 11.1 የጥቅም ትሥሥር ፖለቲካ ሥር መሠረት

የፖለቲካ ገበያ የሚያመለክተው የፖለቲካ ሁኔታዎች በገበያ እንቅስቃሴና በኢኮኖሚ ውስጥ በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ ነው። ይህ ነገር በፖለቲካዊ ግንኙነት፣ በመረጃ ተደራሽነት ወይም የገበያ ውጤቶችን በሚነኩ ደንቦችና ፖሊሲዎች ላይ ተጽዕኖ የማድረግ ችሎታን ጨምሮ የተለያዩ ባሕርይዎች ሊኖሩት ይችላል። ይሁንና የፖለቲካ ገበያ ኢኮኖሚያዊ ውጤቶችን በመቅረጽና ለተለያዩ የገበያ ተሳታፊዎች ጥቅማ ጥቅሞችን ወይም ጉዳቶችን በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና ይጫወታል። እነዚህ ነገሮች ወደ ገበያ ሸቀጥነት የመቀየራቸው እውነታ ከገበያ ኢኮኖሚና ከሐዲስ ሊብራሊዝም ጋር ተያይዞ እየጎለበተ ይመጣል። ያኔ ደግሞ ፖለቲካም በገበያ ሕግ ውስጥ ማለፉ አልቀረም።

CamScanner

ሆኖም ፖለቲካን በግብይት የመምራት ልምድ በታሪክ ውስጥ አዲስ ክሥተት አይደለም። ለምሳሌ በአፍሪካውያን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የፓትሪሞኒያሊዝም እና የሐዲስ ፓትሪሞኒያሊዝም ሥርዓቶች የዘመድ አዝማድና የብሔር ትሥሥርን በመጠቀም ግለሰቦች ፖለቲካዊ ግብይት የሚያካሂዱባቸው ነበሩ።

ሐዲስ ፓትሪሞኒያሊዝም የመንግሥት ግለሰባዊና አምባገነናዊ አገዛዝ የሚገለጽበት የ ሥርዓት ዓይነት ነው። ሥልጣን ከተቋማትና ሕግጋት ይልቅ በግል ግንኙነትና ላይ በማተኮር የሚተገበርበት ነው። ይህ ዓይነቱ የፖለቲካ ሥርዓት ብዙውን ጊዜ ደካማ ተቋማዊ ልማት፣ ዝቅተኛ የዴሞክራሲ ደረጃና የሕግ የበላይነት ውሱንነት ውጤት ነው።

በሌላ በኩል በዓለም አቀፍ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ቅኝ ገዥዎች ሀገራትን በመቀራመትና በቅርምታቸው ዙሪያ ድርድርና ውል በማድረግ የፖለቲካ ግብይት የሚፈጽሙበት “የተጽዕኖ ቀጣና" የሚባል ፈሊጥ ነበራቸው። የተጽዕኖ ቀጣና ማለት አንድ ቅኝ ገዥ ኢመደበኛ በሆነ መልኩ አንድን ቀጣና ወይም ሀገር ያለ ሌላ ቅኝ ገዥ ጣልቃ ገብነት ለማስተዳደር የሚኖረው መብት ማለት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ በአንዱ ቅኝ ገዥ ቀጣና ውስጥ ሌላው ቅኝ ገዥ. እንዳይገባ ልዩ ልዩ ግብይት መሰል ውሎች በሰጥቶ መቀበል መርሕ ይፈራረሙ ነበር:: በአፍሪካ ውስጥ የቅኝ ግዛት ታሪክ የሐዲስ ፓትሪሞኒያሊዝም ሥርዓቶችን ጨምሮ፣ አሁን ያለውን የፖለቲካ ምኅዳር በመቅረጽ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች የተማከለ አገዛዝን ሲጭኑ፣ የአካባቢውን ባህላዊ አመራር በማፈን አዳዲስ አስተዳደራዊ መዋቅሮችን ፈጥረው ነበር። ነገር ግን የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ሥልጣን ለቀው ሲወጡ አፍሪካውያን ከነበሯቸው ደካማ ተቋማት ጋር ተዳምሮ አስተዳደሩ ውጤታማ አይደለም። የደካማ ተቋማት ዳፋ ከቅኝ ግዛት በኋላ ሥልጣናቸውን ለማስጠበቅና ለማስፋት ከሚጥሩ ልሂቃን ጋር ተዳምሮ፣ ለብዙ የአፍሪካ ሀገራት ሐዲስ ፓትሪሞኒያሊዝም እንዲቀጥል አስተዋጽዖ አድርጓል።

ቅኝ ገዥነት በብዙ አዳጊ ሀገሮች ላይ ዘላቂ ተጽዕኖ አሳድሯል። ቅኝ ገዥ ኃይላት በቅኝ ግዛት ሥር ከነበሩት ግዛቶች ሀብትን በማውጣታቸው፣ አፍሪካን ለልማት ማነስና ለድህነት ዳርጓል። በተጨማሪም ቅኝ ገዥዎች ለአካባቢው ሁኔታ የማይስማሙ ሥርዓቶችንና ተቋማትን ይጭኑ ነበር። ይሄም ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፈተናዎችን አስከትሏል። እነዚህ የፖለቲካ ገበያዎችና የቅኝ ግዛት ታሪካዊና ቀጣይ ውጤቶች ለብዙ አዳጊ ሀገራት ዘላቂ ልማት ዋና ዕንቅፋቶች ነበሩ። ሁሉን አቀፍና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስፈን እነዚህን ጉዳዮች መፍታት አስፈላጊ ነው።

አፍሪካውያን በውስጥ ፖለቲካቸው ደጋፊ ለማሰባሰብ የሚያደርጓቸው የፓትሪሞኒያል ግብይቶች ወይም የዘመድ አዝማድ መሰባሰቦች፣ የአፍሪካን ፖለቲካ ተቋማዊ መልክ እንዳይኖረው አድርጎታል። በሌላ በኩል ከውጭ በቅኝ ገዥዎች መካከል በላያቸው ላይ ሲከናወኑ የነበሩ ውሎችም አፍሪካ የፖለቲካ ንግድ መናኸሪያ የሆነችበትን አጋጣሚ የፈጠረ ነበር።

ዘመናዊ ፖለቲካ እየተለመደ መምጣቱን ተከትሎ አፍሪካውያን ተቋማዊ ፖለቲካንና ፓትሪሞኒያሊዝምን የቀላቀለ ሐዲስ ፓትሪሞኒያል ሥርዓት መሠረቱ። የአፍሪካ የነጻ ገበያ ሥርዓት የተጀመረው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ነበር። ይሄውም ብዙ የአፍሪካ ሀገራት በበለጸጉ የአውሮፓና የአሜሪካ ሀገራት የንግድ ልውውጥ ውስጥ መሳተፍ በጀመሩበት ወቅት ነው። ግንኙነቱ እየጎለበተ ሲሄድ በእነርሱና በሌሎች ሀገራት መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ እያደገ በመምጣቱ የተቀናጀ ዓለም አቀፍ ገበያን አስገኝቷል።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ትሥሥር ከተቀረው ዓለም ጋር እየተጠናከረ መጥቷል። በአፍሪካ ውስጥ የንግድ ልውውጥ ለኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ አካል ሆኗል። በሌላ በኩል ደግሞ የቅኝ ግዛት ማብቃትና የቀዝቃዛው ጦርነት መቋጨትን ተከትሎ አሜሪካ የተጽዕኖ ቀጣናዎቿን ወደ አንድ የተጽዕኖ ቀጣና በመሰብሰብ ዓለምን የራሷ የተጽዕኖ ቀጣና አደረገች። በዚህ ሂደት ውስጥ ትልቁን ሚና የሚጫወተው የገበያ ሥርዓትና የሐዲስ ሊብራሊዝም መምጣት ነው።

CamScanner

ሐዲስ ሊብራሊዝም በምርት ዝውውር ብቻ ታጥሮ የነበረውን የዓለም የግብይት ሥርዓት ወደ ምርት ኃይሎች (ማለትም የካፒታል፣ የሰው ኃይልና የመሬት ዝውውር) የቀየረ ሥርዓት ነው። ሐዲስ ሊበራሊዝም የነጻ ገበያን፣ የግል ንብረትንና የግለሰብ ነጻነትን አስፈላጊነት የሚያጎላ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አስተሳሰብ ነው። የፖለቲካ ገበያ የሚያመለክተው የፖለቲካ ኃይልን በመጠቀም የገበያ ውጤቶችን በመቅረጽና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በመቆጣጠር ነው።

በተግባር ሐዲስ ሊበራሊዝም ብዙውን ጊዜ ገበያ ተኮር ፖሊሲዎችን ማስፋፋት፣ እንደ ፕራይቬታይዜሽንንና ሊበራላይዜሽንን የመሳሰሉ ፖሊሲዎችን ማራመድና የመንግሥትን በኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ሚና መቀነስ ያካትታል። አንዳንድ የሐዲስ ሊበራሊዝም ደጋፊዎች እነዚህ ፖሊሲዎች የላቀ ኢኮኖሚያዊ ብቃትን፣ ብልጽግናንና ነጻነትን ያመጣሉ ሲሉ ተቺዎች ደግሞ ተበላላጭነት እንዲጨምር በማድረግ የሀገራትን ማኅበራዊ ጥበቃን እንደሚያዳክም ይከራከራሉ።

በሐዲስ ሊበራሊዝም አካሄድ፣ በሀገረ መንግሥታት የበላይነት ተይዞ የነበረው የሰው ሊመረት ይችላል ማለት ነው። ይህም ማለት በኢኮኖሚ ረገድ ማምረቻውም ሆነ ምርቱ ሀገር የለውም። ሀገሩ ገበያው ነው ማለት ነው። በአደጉ ሀገሮችና በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ኃይልና የካፒታል ዐቅም እንደ ፈለገው በየትኛውም የዓለም ሀገር እየተዘዋወረ ምርት _ አባባል ገበያው ያውቃል" የሚለው ነው። ይህ ሐረግ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት መካካል ያለውን የሐዲስ ሊበራሊዝምና የነጻ ገበያ ፖለቲካ ሥርዓት የሚገልጸው ምሳሌያዊ የሚፈቅድላቸው ነው። መንግሥት በኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው አነስተኛ ተጽዕኖ ሀብትን የሚቀንስበትና የገበያ ኃይሎች የሸቀጦችን፣ የአገልግሎቶችንና የካፒታልን ፍሰት እንዲወስኑ ለመመደብ በጣም ቀልጣፋና ውጤታማ መንገድ ነው የሚለውን እምነት ያሳያል።

ይሄም የሀገረ መንግሥታት የኢኮኖሚ ሚና እየሟሸሸ፣ ሚናቸው የውድድር ሥርዓትንና ሕግን በማስጠበቅ ብቻ እንዲወሰን የሚያደርግ ነው። በአጭሩም የመንግሥታት ሚና እየቀነሰ ግለሰቦች በየትኛውም ሀገር ውስጥ እንደፈለጉ የዓለም ዜጋ ሆነው የሚኖሩበትን ሁኔታ የሚተልም ነው።

ሐዲስ ሊበራሊዝም መንግሥት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ እጅግ አናሳ እንዲሆን የሚያበረታታ የፖለቲካ ኢኮኖሚ አስተሳሰብ ነው። ይህ የምጣኔ ሀብት አካሄድ ባለፉት በርካታ ዐሠርት ዓመታት ውስጥ የዓለምን ኢኮኖሚ በመቅረጽ ላይ ተጽዕኖ ያሳደረ ነው። ይሄም በገበያ ሥርዓቱ ላይም ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል። ሥርዓቱ የመንግሥት ኢንተርፕራይዞችንና አገልግሎቶችን እንደ ጤና ጥበቃ፣ እንደ ትምህርትና መሠረተ ልማት ያሉት ወደ ግል እንዲዛወሩ ያበረታታል።

ይህ ለውጥ የግሉ ዘርፍ በእነዚህ አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ ያለውን ሚና ከፍ አድርጎ የመንግሥት ሚና እንዲቀንስ አድርጓል። ሐዲስ ሊበራሊዝም በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን የመንግሥት ቁጥጥር ይቀንሳል። የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና የካፒታል እንቅስቃሴ ማነቆዎችን ማስወገድን ይጨምራል። ይህም ድርጅቶች ያላቸውን እንደፈለጉ የመንቀሳቀስ ነጻነትን በመጨመር ድንበር ተሻጋሪ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲኖር አመቻችቷል።

ሐዲስ ሊበራሊዝም የሉላዊነት ሂደትን በማንቀሳቀስ የንግድ ዕንቅፋቶችን በማስወገድና ብዙ ዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖችን በማስፋፋት በሀገሮች መካከል ያለው ጥገኝነት እንዲጨምርና ኢኮኖሚ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲዋሐድ አድርጓል። ሥርዓቱ የገበያ ቅልጥፍናና የገበያው ሂደት አብዛኛዎቹን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፍታት ይችላል በሚለው ሐሳብ ላይ ከፍተኛ ተረት ይሰጣል። ይህም ሀብትን ለመደብ ዋጋ ለመወስንና ከቀኖችንና እንስቶችን ማከፋፈል በገበያ ዘዴዎች ላይ የበለጠ ጥገና እንዲሆን አድርጓል። በአጠቃላይ ሓዲስ ሊበራሊዝም ነጻ ገበያን በማስተዋወቅ የመንግሥትን ሚና በመቀስና ሉላዊነትን በማሳደግ የ ሥርዓቱን ቀይሯል።

የሊብራሊዝም መሠረታዊ መነሻ የነገሥታትን ኃይል ቀንሶ ዜጎችን የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነጻነት ማጎናጸፍ ነበር። የሐዲስ ሊበራሊዝም መነሻ ደግሞ ጭራሹኑ የመንግሥታትን ዕቅም በማዳከም ሀገረ መንግሥት የሚባለውን የፖለቲካ መዋቅር ማጥፋትና የሰው ልጆች ነጻነት በድንበር ያልተገደበ እንዲሆን ማድረግ ነው። ይህ የሐዲስ ሊበራሊዝም ሥርዓት ወደ

CamScanner

ፖለቲካው ዓለም ሲቀላቀል ያስከተለው ውጤት ግን እንደሚባለው የሰው ልጆችን ነጻነት ወደ ማስከበር አላመራም። ይልቁንም ድንበር ዘለል ይሆናሉ የተባሉት የሰው ልጆች በትናንሽ ድንበሮች ታጥረዋል። ከዚያም አልፈው እርስ በርሳቸው እንዲሻኮቱና የተረጋጋ ሀገረ መንግሥትና የሲቪክ ፖለቲካ እንዳይኖራቸው እያደረገ ነው።

በአፍሪካ ውስጥ የሐዲስ ሊበራል ፖሊሲ ተጽዕኖዎች የተደባለቁ ናቸው። አንዳንድ ሀገሮች የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገቡ ሲሆን ሌሎች ደግሞ ቀጣይነት ያለው ድህነትና ፍትሐዊነት የጎደለው የሀብት ክፍፍል ተጋርጦባቸዋል። በአንድ በኩል የሐዲስ ሊበራሊዝም ደጋፊዎች በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት የውጭ ኢንቨስትመንት እንዲያድግ የንግድ ልውውጥ እንዲጨምርና የተሻሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲፈጠር በር ከፍቷል ሲሉ ይከራከራሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሐዲስ ሊበራል ፖሊሲ ድህነትን ጨምሯል ብለው የሚከራከሩ አሉ። የእኩልነት መጓደል አስከትሏል ብለው ይወቅሱታል። እንደ ጤና አጠባበቅና እንደ ትምህርት ያሉ የሕዝብ አገልግሎቶች በሐዲስ ሊበራሊዝም ምክንያት ተሸርሽረዋል ይላሉ። ፖሊሲዎቹ የአፍሪካን ሀብትና ሕዝብ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ኮርፖሬሽኖችና የውጭ ባለ ሀብቶች እንዲበዘብዙ አድርጓቸዋል ሲሉም ችግር ፈጣሪነቱን ያስቀምጣሉ።

አሁን ባለው ሁኔታ የሐዲስ ሊበራሎች ፖለቲካዊ ግብይት የፈጠረው ትልቁ አውነታ አዳጊ ሀገራት የሲቪክ ፖለቲካቸው ፈተና ውስጥ እንዲወድቅና በአካባቢያዊ ፖለቲካዊ ሽኩቻዎች እንዲጠመዱ ማድረጉ ነው። በሌላ አነጋገር በሐዲስ ሊበራል ሥርዓት ውስጥ ሁለት ሥርዓቶች እየጠነከሩ መጥተዋል። እነዚህም ዓለም አቀፋዊ ሥርዓቶችና አካባቢያዊ (ማንነታዊ) ሥርዓቶች ናቸው። በሁለቱ መካከል ያለው ሥርዓት ማለትም የሀገረ መንግሥት ሥርዓት ደግሞ ፈተና ውስጥ እየገባ መጥቷል። ሉላዊ ኃይሎች ከአካባቢያዊ ኃይሎች ጋር በመሠናሰል ሀገረ መንግሥታትን የሚያዳክሙበት የገበያ ሥርዓት ተፈጥሯል።

የኃያላኑ የተጽዕኖ ቀጣና ወደ ሐዲስ ሊበራሊዝም ሲያድግና የአዳጊ ሀገራት ፓትሪሞኒያል . ሥርዓት ወደ ሐዲስ ፓትሪሞኒያሊዝም ሲለወጥ፣ በሁለቱ ጋብቻ የፖለቲካ ገበያ ተወለደ። · የአፍሪካ አባታዊ ሥርዓት፣ በአንድ “ታላቅ ሰው” የሚመራ፣ መሪዎች በግል ግንኙነት፣ በታማኝነትና በደንበኛነት ሥልጣን የሚይዙበት ባህላዊ የፖለቲካ ድርጅት ነበር። ይህ ሥርዓት በጥቂት ግለሰቦች እጅ ውስጥ ያለው የሥልጣን ክምችትና ተጽዕኗቸውን ተጠቅመው ሀብትና ሥርጭትን በመቆጣጠር ይገለጻል።

ይሁን እንጂ በድኅረ ቅኝ ግዛት ዘመን ይህ ባህላዊ ሥርዓት ተብሎ ወደሚታወቀው የፖለቲካ የገበያ ሥርዓት ተለወጠ። ይህ ለውጥ በበርካታ ሐዲስ ፓትሪሞኒያል ሥርዓት ምክንያቶች የተመራ ሲሆን ከእነዚህም መካከል አንዱ የመድበለ ፓርቲ ዴሞክራሲን ማስተዋወቅ የሚባለው ነው። የሥልጣን ክፍፍል ማድረግና የአፍሪካ ኢኮኖሚዎችን ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር መቀላቀል የሚሉትንም ይጨምራል።

በሐዲስ ፓትሪሞኒያል ሥርዓት ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን ብዙውን ጊዜ በጥቂት ግለሰቦች የተያዘ ነው። ነገር ግን ከግል ትሥሥርና ታማኝነት ጎን ለጎን በገበያና በአገልግሎት ሂደት ውስጥ በሚኖረው ልውውጥ ላይ ይወሰናል። ይህም ለኢኮኖሚያዊ ጥቅምና ለሀብት ክምችት ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጥና የማኅበራዊና ባህላዊ ደንቦች ተጽዕኖ እንዲቀንስ በተወሰነ መልኩ አድርጓል።

በተለያዩ ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ምክንያት በነበረው ተጽዕኖ፤ የአፍሪካን የአባቶች ሥርዓትን ወደ ሐዲስ ፓትሪሞኒያዊ ሥርዓት የመቀየር ሂደት በአህጉሪቱ አንድ ዓይነት አልነበረም። በአጠቃላይ ግን ሽግግሩ በባህላዊ የኃይል አደረጃጀቶች መሸርሸርና በአዳዲስ ልሂቃን ብቅ ማለት ተመሳሳይ ነው።

CamScanner

እነዚህ አዳዲስ ኃይሎች ሀብትን በመቆጣጠርና በገበያ ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ሥልጣን ያገኙና ያስቀጠሉ ናቸው። የአፍሪካውያን በዘመድ አዝማድ ድጋፍን የማሰባሰብ የቆየ ልማድ፣ ጥንትም የግብይት ባሕርይ ነበረው። ሙሉ ለሙሉ የፖለቲካ ገበያ ሥርዓት እየፈጠረ የመጣው ግን ይህ የቆየ ልማድ ከዓለም አቀፍ የገበያ ሥርዓት ጋር ሲሠናሰል ነው።

በአሁኑ ጊዜ ማንኛውም ዓለም አቀፍ ኃይል በማንኛውም አዳጊ ሀገር ውስጥ ገብቶ፣ ከተለያዩ ማንነታዊ ቡድኖች ጋር የፖለቲካ ንግድ ይፈጽማል። ልክ ማንኛውም ባለሀብት ወይም ሀገር በየትኛውም አዳጊ ሀገር ሄዶ ኢንቨስት እንደሚያደርገውና ሸቀጥ እንደሚገበየው ማለት ነው። በሐዲስ ሊበራልና በፖለቲካ ገበያ ሥርዓት ውስጥ ባደጉ ሀገሮችና በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገልጸው ዘይቤ ብዙውን ጊዜ “ኢኮኖሚያዊ ኢምፔሪያሊዝም” ወይም “ሉላዊ ብዝበዛ - global exploitation” የሚለው ነው። ያደጉ ሀገራት የኢኮኖሚ ዐቅማቸውን ተጠቅመው በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን መቆጣጠርና ሀብታቸውን በማውጣት በዋናነት ራሳቸውን የሚጠቅሙ ፖሊሲዎችን መተግበር እየተጠቀሙ ነው የሚል ነው።

የአውሮፓ ኃያላን ከዚህ ቀደም ሌሎች የዓለም ክፍሎችን በቅኝ ግዛት መያዛቸውና መቆጣጠራቸው ይታወሳል። አሁን ደግሞ በሐዲስ የቅኝ ግዛት መንገድ ያደጉ ሀገራት፣ በአዳጊ ሀገራት ውስጥ ሀብታቸውን በመቆጣጠርና በመበዝበዝ በእጅ አዙር የገበያ ሥርዓቱን በመቆጣጠር የበላይነትን እያስቀጠሉ ናቸው።

ይህም “አዲሱ ኢምፔሪያሊዝም” የሚባለው ዘይቤ ነው።

ይህ ንጽጽር የሚያመለክተው በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ውስጥ ያደጉ ሀገሮች በ19ኛውና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከነበሩት የኢምፔሪያሊዝም ፖሊሲዎች ጋር እንደሚመሳሰል ነው። ያኔ ኃያላን ሀገሮች በሌሎች የዓለም ክፍሎች ላይ ያላቸውን ተጽዕኖና ቁጥጥር ለማስፋፋት ጥረት ሲያደርጉ ነበር። ያሁኑ ነባራዊ ሁኔታም ተመሳሳይ እንደሆነ የሚያስቀምጡ አሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ የምዕራባውያኑ ሀገረ መንግሥታት በተቋማዊ ጥንካሬያቸው መዝለቅ ችለዋል።

የፖለቲካ ገበያን ከፓትሪሞኒያል ሥርዓቶች የሚለዩት የተለያዩ ጉዳዮች አሉ። በዋናነት ሁለት ጉዳዮችን ለይተን ማስቀመጥ ግን እንችላለን። አንደኛው ጉዳይ የፖለቲካ ገበያ በውስጥ ኃይሎች መካከል ብቻ የሚካሄድ ንግድ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ነጻ የገበያ ሥርዓት የሚመራ መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት ማንኛውም ዓለም አቀፍ ኃይል በየትኛውም ሀገር ውስጥ ገብቶ የፖለቲካ ንግድ መነገድ የሚችልበትን ነጻ የገበያ ሥርዓት ያመለክታል።

አንድ ሀገር ልዩ የተጽዕኖ ቀጣና ሳያስፈልገው በሌላ ሀገር ውስጥ ገብቶ የፖለቲካ ንግድ የሚነግድበትና ትርፍ የሚያገኝበትን ዕድል ፈጥሮለታል። በአንድ ሀገር ውስጥ ማንነትን ወይም አካባቢን መሠረት ያደረጉ የፖለቲካ ንግዶች፣ በሀገር ውስጥ ብቻ ታጥረው የሚቀሩ አይደሉም።

የገበያውን ሁኔታ ያጠናና ትርፍ አገኛለሁ ብሎ የሚያስብ ማንኛውም ዓለም አቀፍ ኃይል በገበያው ውስጥ ተሳታፊ ይሆናል። ገንዘቡን፣ መሣሪያውን፣ መገናኛውን ይዞ ገበያውን ይቀላቀላል። ከዚያም የፖለቲካ ትርፉን በቀላሉ ያካብታል። በዚህም መሠረት በአሁኑ ጊዜ የአዳጊ ሀገራት ፖለቲካና የውስጥ ሽኩቻ በራሳቸው የውስጥ ሁኔታ ብቻ የታጠረ አይደለም። ማንኛውም የፖለቲካ ካፒታል ይዞ የመጣ ኃይል በገበያው ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው፡

ሁለተኛው ጉዳይ የፖለቲካ ገበያ ከፓትሪሞኒያል ሥርዓቶች በበለጠ ወደ ፍጹማዊ ንግድነት ያዘነበለ መሆኑ ነው። “ትሻልን ሰድጄ ትብስን አመጣሁ" የሚለው ነው የተፈጠረው:: ሁኔታ ይፈጠራል። በአንጻሩ በፓትሪሞኒያል ሥርዓቶች ፖለቲካዊ ንግድ ቢኖርም የሀገረ መንግሥት ተቋማት የበላይነታቸው እንደተጠበቀ ነበር። በፖለቲካዊ ገበያ ውስጥ ግን በፖለቲካ ገበያ ውስጥ ተቋማት ያላቸው ሚና እየሟሸሸ ሄዶ ከገበያ በታች የሚሆኑበት ገበያው የበላይ፣ ተቋማት የበታች እየሆኑ ይመጣሉ። ይህም ሂደቱ ከሀገረ መንግሥታት ቁጥጥር ውጭ የመሆን አዝማሚያን ያስከትላል።

CamScanner

ሀገረ መንግሥታት ገበያውን መቃኘትና መቆጣጠር ፈጽሞ እየተሳናቸው ይሄዳል። የሀገራትንም ዕጣ ፈንታ ገበያው ብቻ እየወሰነው ይመጣል። የፖለቲካ ገበያ የፖለቲካ ሥልጣንና ተጽዕኖ የሚነግዱበትና የሚከራከሩበት መድረክ ነው። የፖለቲካ ግብይቱ እንደ ፍጹም ገበያ ሊታይ ይችላል። ምክንያቱም የፖለቲካ ሀብቶች ማለትም የሥልጣን ቦታዎች ፖሊሲዎችና ልዩ መብቶች ድልድል የሚወሰኑት፣ አንድ አካል በአንድ ሥርዓት ውስጥ ባለው የፖለቲካ ሥልጣን ክፍፍል ነው።

በሐዲስ ፓትሪሞኒያል የፖለቲካ ገበያ ሥርዓት ውስጥ በማደግ ላይ ባሉ ሀገሮች ፉክክር ብዙውን ጊዜ የሚሽከረከረው በሁለት ነገሮች ላይ ነው። ሀብትን በመቆጣጠርና በማከፋፈል እንዲሁም በሥልጣን አቅርቦትና በውሳኔ አሰጣጥ ላይ። ይህ ውድድር የፖለቲካ ፉክክር፣ የመንግሥት ተቋማትን ለመቆጣጠር የሚደረግ ትግል ወይም መንግሥት የሚያመነጨውን ሀብት ለማግኘት የሚደረግ ሽኩቻ ሊሆን ይችላል።

ውድድሩ ብዙውን ጊዜ የሚቀረፀው በፖለቲካ መሪዎች የግል ፍላጎትና ማበረታቻ ነው:: ይህም የብዙኃኑን ሕዝብ ጥቅም ከማስከበር ይልቅ የራሳቸውን ሥልጣንና ተጽዕኖ ለማስቀጠል ወይም ለመጨመር በሚጥሩ የፖለቲካ መሪዎች ነው። ይህ ደግሞ ሙስናና ሥልጣንን አላግባብ መጠቀምን እንዲሁም የመንግሥት ተጠያቂነትና ግልጽነት እጦትን ያስከትላል።

ይህ ሂደት ትልቅ የፖለቲካ ካፒታል ላላቸው ኃያላንና ላደጉ ሀገራት ገበያውን የመወሰን ድርሻ እየሰጣቸው ይመጣል። በአጭሩ የአዳጊ ሀገራት የፖለቲካ ገበያ ዋጋና የግብይት ሕግ የሚወሰነው ትልቅ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ካፒታል ባላቸው ያደጉ ሀገራት ይሆናል ማለት ነው።

ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ገበያ ሥርዓቱ ውስጥ ትልቅ ሚና ያላቸው ምዕራባውያን፣ በሀገራቸው ውስጥ የሚገነቡት ሥርዓትና በአዳጊ ሀገራት ላይ ለመፍጠር የሚሞክሩት ሥርዓት ፈጽሞ የተቃረነ ነው። በሀገራቸው ተቋማትንና ዘመናዊ ቢሮክራሲን ይገነባሉ። ሀገረ መንግሥቱን ያጠናክራሉ። የሲቪክ ባህልን ያጎለብታሉ። በሐሳብ ውድድር ላይ የተመሠረተ የዴሞክራሲ ሥርዓት ያሰፍናሉ። እነዚህን ሁሉ በግልጽና በዐደባባይ ሲያራምዱ ለአዳጊ ሀገራትም ምክር ቢጤ በመለገስ ጭምር ነው።

ሆኖም በዓለም አቀፍ የፖለቲካ ገበያው ውስጥ ገብተው የሚያራምዱት ነገር ፈጽሞ ከዚህ ተሞክሯቸውና አስተምህሯቸው የተቃረነ ነው። የፖለቲካ ገበያ ተሳትፏቸው የሚያሳየን ቅቡልነት ለመስጠት የሚጣደፉ ናቸው። የተለያዩ የሽኩቻ እንቅስቃሴዎችንና የመከፋፈል ነገር ቢኖር፣ ለማንነታዊ(አካባቢያዊ) እንቅስቃሴዎችና የዐመጻ ድርጊቶች ዕውቅናና አጀንዳዎችን ወደ ትልቅ የፖለቲካ አጀንዳነት ይቀይራሉ። የምርጫ ፉክክርን ችላ ብለው ቅድሚያ በአካባቢያዊ የጎበዝ አለቆች የሥልጣን ክፍፍል ላይ ያተኩራሉ።

በዚህ ሂደትም ዓለም አቀፍ የተጽዕኖ አድማሳቸውን በማስፋት ገበያውን በሞኖፖል መቆጣጠር የሚፈልጉ ናቸው። በማንነት ስም የሚደረጉ የፖለቲካ ገበያው እንቅስቃሴዎች፣ ሀገረ መንግሥታቱን በማዳከም፣ ምዕራባውያኑ በቀጥታ ከየአካባቢው የጎበዝ አለቆች ጋር የመገበያየት ዕድልን ይፈጥርላቸዋል። ይህም የቅኝ ግዛት ታሪክ አሁናዊ ቅጅ ነው።

የአሁኑን ከቀድሞው የሚለየው ዋነኛው ጉዳይ፣ በተወሰኑ አካባቢዎችና ኃይሎች ብቻ ያልታጠረ የተጽዕኖ ቀጣና መኖሩ ነው። ማለትም ማንኛውም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ካፒታል ያለው ኃይል፣ በሌላ ሀገር ሉዓላዊ ድንበር ውስጥ ገብቶ ፖለቲካን የመነገድ ዕድል ማግኘቱ ነው። የእኔ ቀጣና ነው፣ የአንተ ቀጣና ነው የሚል የቅኝ ገዥዎች የእርስ በርስ አከራካሪ ውል ዛሬ የለም፡፡

ሉዓላዊነት የሚባለው የሀገራት ዋነኛ ማገር በዓለም አቀፍ የነጻ ገበያ ሥርዓት ወይም በሐዲስ ሊበራሊዝም አስተምህሮ እየተሰነጣጠቀ ነው። ሀገራት ሁሉም ገብቶ የሚነግድባቸው ነጻ የግብይት መድረኮች ሆነዋል። በኢኮኖሚው የሚደረገው የሸቀጥ ግብይትና በፖለቲካ የሚደረገው የሸቀጥ ግብይት መሳ ለመሳ የሚከወን ሆኗል።

CS CamScanner

ለዚህ የሉዓላዊነት ድንበር መጣስና ሀገራት የፖለቲካ ገበያ እንዲሆኑ ዋነኛ ርዕዮተ ዓለማዊ ምክንያት ተደርጎ የሚጠቀሰው የሰው ልጆች ነጻነትና ዴሞክራሲ ነው፡፡ "መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ" የሆነው አካሄድ በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብት ስም የፖለቲካ ገበያውን ለመቀላቀልና ሉዓላዊነትን ጥሶ ለመግባት ቀላል መንገድ አድርጎታል፡፡ በኢኮኖሚያዊ ማዕቀቦችና በቀጥተኛ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነቶች የፖለቲካ ገበያውን የሚቀላቀሉና በነጻ ገበያ ሕግ ከፍተኛ የፖለቲካ ትርፍ ይዘው የሚወጡ ሀገራት ጥቂት አይደሉም፡፡

ማንነትን መነሻው ያደረገ የፖለቲካ ገበያ፣ ውስብስብ ውጤቶች አሉት፡፡ በርካታ ለመፍረስ በኋላ ብዙ የሰላም ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡ ሁሉም ግን ከማስታገሻ መድኃኒትነት የህ የቀረቡ ወይም የፈረሱ ሀገራት የዚህ ሥርዓት ገፈት ቀማሾች ናቸው፡፡ ሀገራቸውን ካፈረሱ ትርጉም እንደሌላቸው ታራቂዎቹም አስታራቂዎቹም ያውቁታል፡፡ "ወደሽ ከተደፋሉ. ቢረግጡሽ አይክፋሽ" እንደሚባለው ሀገራቸውን ለነጻ ገበያነት አሳልፈው እስከ ሰው ድረስ ማንም በሂደቱ ውስጥ እየገባ በገላጋይነትም ሆነ በደጋፊነት ትርፉን ለማጋበስ ይራኮታል፡፡

ያደጉ ሀገሮች በተለያዩ ምክንያቶች የፖለቲካ ገበያ ሥርዓቱን ተቆጣጥረውታል፡፡ ከእነዚህም መካከል ታሪካዊና ኢኮኖሚያዊ ኃይላቸው፣ ወታደራዊ ኃይላቸው የባህል ተጽዕኗቸው በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ያላቸው ውክልና ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ይህ የበላይነት በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ላይ በርካታ መዘዝ አስከትሏል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ በማድ ላይ ያሉ ሀገራት በኢኮኖሚ ባደጉት ሀገራት ላይ ጥገኛ የመሆናቸው ነገር ነው፡፡ ይህ ጥገኝነት እኩል ያልሆነ የንግድ ግንኙነት ፈጥሯል፡፡ የኢኮኖሚ ዕድገት ውሱንነትንም አስከትሏል፡፡

### 11.2 የሐሳብ አልባ ፖለቲካ መዳረሻ

የሰው ልጅ መንግሥትን የፈጠረውና በውስጡ ለማደር ፍቃዱን የሰጠው ሥርዓቱ የግልና የቡድን መሻቶችን በፍትሐዊነት፣ በቀጣይነትና በተሻለ መንገድ ያረጋግጥልኛል በሚል እምነት የተነሣ ነው፡፡ ዘመናዊ ሥርዓተ መንግሥት ከመፈጠሩም አስቀድሞ ከመካከሉ ጎበዝ መርጦና በንዑሳን ቡድን አደራጅቶ ቡድናዊና ግላዊ መሻቶቹ በሥርዓትና በሕ እንዲመሩ የማድረግ የረጅም ጊዜ ልምምድ አለው፡፡ ከቅድመ ታሪክ እስከ 21ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ መሠረታዊው መሻት ለውጥ ሳያደርግ የሚያስተዳድርበትንና የሚሠራበትን ሥርዓትና ጥበብ እያዘመነና እያሠለጠነ ከዚህ ደርሷል፡፡

በዚህ ሁሉ ዘመን ከበርካታ መሻቶቹ መካከል የመሻቶቹ ዓምድ የሚሆኑት ሀብት መፍጠርና ማስተዳደር፣ ደኅንነቱ የሚጠበቅበትና የሚረጋገጥበት ኃይል ማግኘትና የተሟላ ሰብአዊ ክብርን መጎናጸፍ ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስት መሻቶች ሰብሰብ ተደርገው በቃላት ቢቀመጡ፡ ሀብት፣ ኃይልና ክብር ናቸው፡፡ እነዚህን የሰው ልጅ መሻቶች ለማርካትና ለማስጠበቅ የተመሠረቱ ሥርዓቶች በተለያየ ደረጃ ፈተና ላይ ይገኛሉ፡፡ ባደጉ ሀገራትና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ሦስቱን መሻቶች ለማኅበረሰባቸው በማደላደል ረገድ ያሉበት ደረጃ ይለያያል፡ ሀገራት በዘረጉት ሥርዓት ማኅበረሰባዊና ግለሰባዊ ሀብት የማፍራት መሻትን ለማሟላት ብሔራዊ ሀብት በመፍጠርና የዜጎችን የነፍስ ወከፍ ድርሻ በማሳደግ ረገድ ብዙ ርቀት የሄዱ አሉ፡፡ ነገር ግን በሀገራት መካከልም ሆነ በሀገራት ውስጥ ልዩነቶች አሉ፡፡ መሻቱም ርካታ ፈጠረላቸው ይገኛሉ፡፡ በሥርዓተ ማኅበር ውስጥ ግላዊ ሁብት የመፍጠርና የመጠቀም ሥርዓትና ሕግ ይበልጥ የዳበረበትና ብዙዎች የሚተዳደሩበት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ብሔራዊ ሀብትና ግለሰባዊ ጥረትን ጠቅሎ ለመያዝ የሚደረጉ ቡድናዊ እንቅስቃሴዎች በሀገራዊም ሆነ በዓለማዊ ሥርዓት ውስጥ ይስተዋላሉ፡፡

ሌላኛው የሰው ልጅ መሻት ኃይል ነው፡፡ የሰው ልጅ ኃይል የመሻት ጥንተ ነገር ራሱን በሕይወት ለማኖር ካለው ፍላጎት ይመነጫል፡፡ ሰው ኃይሉ ሰዋዊ ጉልበቱ ብቻ በነበረበት ወቅት ኃይሉ ከዱር አራዊት ያነሰ ነበር፡፡ በመሆኑም ተጋፍጦም ሆነ ሮጦ ማምለጥ ባለመቻሉ ከሽሽት የሚያድነውን ኃይል መሻት ጀመረ፡፡ በርካታ የአርኪዎሎጂ ግኝቶች የሚያሳዩን የሰው ልጅ ኃይል ይሆኑኛል ያላቸውን መሣሪያዎች በማበጃጀት ተጠምዶ እንደነበር ነው፡፡ በሰው ልጅ የመጀመሪያው የኃይል ፍላጎት

CamScanner

በሕይወት ለመቆየት የሚያስችለውን ዐቅም ለመፍጠር ነበር። በሂደት የሰው ልጅ ኃይል የሚያጎናጽፉትን ቁሶችና እሳትን ሲፈጥር የምግብ አማራጩን አሰፋለት። ግዛት የመከለል ዐቅምም አጎናጸፈው።

አካላዊ ድክመቱን በፈጠራ ኃይል ያሟላው የሰው ልጅ በጫካው ገዥነቱን አረጋገጠ። በዚህ ሂደት ኃይል የገዥነት ምንጭ መሆኑን ተረዳ። በመሆኑም ሥርዓተ ማኅበሩን በኃይል ማደራጀትና ከባላጋራ መጠበቅ ጀመረ። ከዚያም በኃይል ፍላጎቱን ለማርካት መንቀሳቀስ ቀጠለ። የሰው ልጅ ኃይልን መጠቀም የጀመረው በአጎራባች ያለው የእርሻ መሬት ይገባኛል ከሚል መሻት ነበር። በኋላ ይህን አጠናክሮ ግዛትና ሃይማኖት ከማስፋፋት እስከ ቅኝ ግዛት አደረሰው። ብሎም ሁለቱን የዓለም ጦርነቶች ያስከተለ የኃይል ግጭት ድረስ አከፋው። በሕይወት ለመቆየት፣ በኋላም ለመስፋፋት፣ በመቀጠልም ሐሳብን ለመጫን ኃይልን ተጠቅሟል። የኃይል መሻቱ በብርቱ የገፋው የሰው ልጅ፤ ከድንጋይ አንሥቶ እስከ ኒዩክሌር ኃይል አድርሶታል።

በርግጥ የሰው ልጅ የኃይል ፍላጎት በርካታ ጥፋቶችን አስከትሏል። የኃይል ፍላጎቱ የሚነሣው በሕይወት ለመኖር ዋስትናዬ ነው ከሚል እምነት ነበር። በመሆኑም የሰው ልጅ አካላዊ፣ ስሜታዊና ማኅበራዊ ደኅንነቱ እንዲረጋገጥለትና እንዲጠበቅለት አብዝቶ ይሻል። የሚታመንበት ኃይል ማጣት የስሜትና የመንፈስ መረበሽ በመፍጠር በዕለት ተዕለት ሕይወቱ መተማመንና ደኅንነት እንዳይሰማው ያደርገዋል። ይሄንን ፍርሃት አሸቀንጥሮ ለመጣል በአንድ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ዜጎችና ቡድኖች ኃይል የመጠቀምና የማስተዳደር ኃላፊነትን ለመንግሥት አሳልፈው ሰጡ። በሀገራትም ደረጃ የኃይል አጠቃቀም የቃል ኪዳን ስምምነቶች ተፈርመዋል። ኃይል በሕግ እንዲተዳደር በርካታ ሕጎች ወጥተዋል።

የሰው ልጅ የኃይል መሻቱ ከጦር መሣሪያ ባሻገር ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሥርዓትን ወደ አሰባሰቦና አሠናስሎ የያዘ በመሆኑ፣ የቡድኖችም ሆነ የግለሰቦች ትኩረት በሥርዓታዊ መቆጣጠርና የኃይሉ ምንጭ ወደ ማድረግ አድጓል። ሥርዓት በርካታ ኃይሎችን በአንድነት ኃይል ላይ ሆኗል። ሀገራት በሀገር ውስጥ ካላቸው ሥርዓታዊ ኃይል በተጨማሪ ሌላ ኃይል በመሻት ከሁለትዮሽ ስምምነት ባለፈም አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና በተለያየ ስም የሚጠሩ ቡድኖችን ይቀላቀላሉ። በአጠቃላይ ከግለሰብ የተነሣው የመኖር መሻት እንደ ማኅበር፣ እንደ ሀገር፣ እንደ አህጉር እያደገ የመኖር ጥያቄንና ደኅንነትን ለማረጋገጥ ከነጠላ ኃይል ወደ ሥርዓታዊ ኃይል ተሸጋግሯል። ውስብስብ በሆነው ሥርዓት ኃይልን ለማስተዳደርና ለጋራ ጥቅም ለማዋል የሚያስችል ሥርዓትና ሕግ ተፈጥሯል።

ሰብአዊ ልኩ ነው። ከሰዎች ክብር ማግኘትንና ለሰዎች መስጠትን ይፈልጋል። ሰብአዊ የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ብቻ፣ ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታና ዕይታ እንዳይነካበት የሚፈልገው ተአማኒነትን ማረጋገጥና ማጽናትን ይሻል። ተፈጥሯዊና ሰብአዊ መብቶች ሳይበላለጡ እንዲከበሩለት ይሻል። የሰው ልጆች የክብር መሻት በሥርዓታዊና በማኅበራዊ መዋቅሮች ይጨፈለቃል። ከላይ የተመለከትናቸው የሀብትና የኃይል መሻት ግብ ክብርን ለማስጠበቅ ነው።

በአጠቃላይ እነዚህ ሦስት ሰብአዊና ሥርዓታዊ መሻቶች እጅግ አስፈላጊ ቢሆኑም ባልተገባ መንገድ እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት የሚኬድበት መንገድ በርካታ ጥፋቶችን ያስከትላል። የኢኮኖሚ፣ የኃይልና የክብር ፍላጎቶችን በግልና በቡድን ባልተገባ መንገድ ለማርካት የሚደረገው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሀገራትን ሥርዓትና ማኅበራዊ መስተጋብር ፈትኗል።

የፖለቲካ ገበያ የሰው ልጅ መሻት የሆኑትን የሀብት፣ የኃይልና የክብር መሻቶች ባልተገባ መልኩ ወይም ከሥርዓተ ማኅበሩ ሕግና ሥርዓት ባፈነገጠ መልኩ በግልና በቡድን ለማርካት የሚደረግ ጥረት ነው። እነዚህን መሻቶች በቡድኑ አልያም በግሉ ለማርካት የሚሄድበት መንገድ የሌሎችን ፍላጎት ይነጥቃል። አልያም ደግሞ ፍላጎታቸውን ታሳቢ አያደርግም። ወይም በሌላ ገጹ ግጭት በመፍጠርም ጭምር ይካሄዳል፡

የፖለቲካ ገበያው እነዚህን የሰው ልጅ ፍላጎቶች መሠረት አድርጎ ቡድናዊ መሻትን እያቀጣጠለ ሥርዓትና ሕግን ለመጣስ ያነሣሣበታል። በዘመናዊ የመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ሀገራት በተለይ አዳጊ ሀገራት የገጠማቸው ፈተና የፖለቲካ ገበያ ነው።

CS CamScanner

የፖለቲካ ገበያ ተዋንያን እነዚህን ሦስት ፍላጎቶች እንዴት በፖለቲካ ገበያው እንደሚሸጧቸውና እንዴት ፍላጎታቸውን እንደሚያረኩ ፍላጎቶቹን ከፋፍለን እንመልከት።

## 11.3 የኢኮኖሚ ፍላጎት

የፖለቲካ ነጋዴዎች ሀብት የማፍራት ተፈጥሯዊ የሰው መሻትን ለራሳቸው ዓላማ ይጠቀሙበታል። ባልተገባና ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ ሀብት ማካበቻና የፖለቲካ ቡድን ማደራጃ ያደርጉታል። ለመከለያነት የመረጡትን የማኅበረሰብ፣ ሰዋዊ ሀብት የማፍራት መሻትን እየቆሰቆሱ፣ የፖለቲካ ገበያ አጋፋሪ ያደርጉታል። የፖለቲካ ገበያ በየትኛውም የፖለቲካ ሥርዓት በተለያየ ደረጃ የሚታይ ነው። ፖለቲካዊ ታማኝነት እንደ ሸቀጥ ለገበያ ቀርቦ በገንዘብ ይገዛል። በግለሰቦች መካከል ትብብርን ለመፍጠር በገንዘብ የሚደረጉ ድርድሮች፣ የፖለቲካ ነጋዴዎች አንድ ገጽታ ናቸው። የዳበረ የፖለቲካ ሥርዓትን በገነቡ ሀገራትም ይሁን ጠንካራ ሥርዓትን ባልፈጠሩ ሀገራት፣ ገንዘብ በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ቀላል የማይባል ጫና አለው።

የፖለቲካ ገበያ ተዋንያን ኢኮኖሚያዊ ፍላጎታቸውን ለማርካት በመንግሥትና በማኅበረሰብ መዋቅር ውስጥ ይሠገሠጋሉ። በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ሆነው በፖለቲካ ገበያው መድረክ በኅቡዕ ከፖለቲካ ነጋዴዎች ጋር የሚመሣጠሩ የመንግሥት ሹማምንት ሁለት ፍላጎቶችን ለማርካት ያስባሉ። አንድም ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶችን ማሳካት ነው። ሌላም የፖለቲካ ሥልጣናቸውን ለማስጠበቅ ከመሻት ይመነጫል።

በመሆኑም በሕግ የተሰጣቸውን ሥልጣንና ኃላፊነት የግልና የቡድን ሀብት ለመፍጠር ያውሉታል። እነዚህ የፖለቲካ ነጋዴዎች ሕጋዊ ሥልጣናቸውን ተጠቅመው መሬትን፣ የወጪና የገቢ ንግድን፣ የተፈጥሮ ሀብትንና የመሳሰሉትን ተቋማዊ በሆነ መንገድ ይዘርፋሉ። መዝረፍ ብቻ ሳይሆን ለቡድኖቻቸው ያከፋፍላሉ። በዚህም የፖለቲካ መሠረታቸውን ለማጠናከር ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን ግላዊ ሀብት ማከማቻ መንገድ ያደርጉታል።

የፖለቲካ ነጋዴዎች በመንግሥት መዋቅር ውስጥ እንዳሉት ሁሉ በማኅበረሰባዊ መዋቅሮች ውስጥም አሉ። በማኅበራዊ መዋቅሮች ውስጥ በመግባትና በመደራጀት ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶቻቸውን ያረካሉ። መዋቅሩንም ለፍላጎታቸው ዘላቂ ማስፈጸሚያ እንዲሆን ይቆጣጠሩታል። ማኅበረሰባዊ መዋቅሮች በአመዛኙ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓታቸው ደካማ ነው። ይህም ለፖለቲካ ነጋዴዎች መስፋፋትና መደራጀት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ተጠያቂነት የሌለበት ሀብት የማካበት ጥማታቸውን ያረኩበታል። ከዚህ ከፍ ባለ ሁኔታ፣ የፖለቲካ ነጋዴዎቹ በጥቅም ትሥሥር የሚፈጥሯቸውን አንጃዎች እንደ ኃይል ይጠቀሙባቸዋል። እነዚህን ኃይሎች በመጠቀም ረዘም ላለ ጊዜ ማኅበራዊ ተቋማትን ተከልለው ሥራቸውን ይሠራሉ።

የሰውን ልጅ ሀብት የማፍራት መሻትን ተገን አድርገው በመንግሥትና በማኅበራዊ መዋቅር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ነጋዴዎች ዓላማ ሁለት ነው። የመጀመሪያው በሕገ ወጥ ጠባቂ ቡድን በማበጀት መከላከል ነው። ክንዳቸው በፈረጠመ ቁጥር ፍላጎታቸው መንገድ ሀብት ማፍራት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሀብት ለማፍራት የሚያስችላቸውን በዚያው ልክ እየሰፋ ይሄዳል።

ተፈጥሮ ከጸጋዋ ያደለቻቸው አንዳንድ ሀገራት፣ በፖለቲካ ገበያ ሸኩቻ የተነሣ የተፈጥሮ ለማስጠበቅና ለማስፋት በነጋ በጠባ ቁጥር ጦርነት አይለያቸውም። ከተፈጥሮ ገጸ ሀብታቸውን ግለሰቦችና ቡድኖች ይቀራመቱታል። እነዚህ ቡድኖች ድርሻቸውን በረከታቸው በተቃራኒው በጦርነት፣ በበሽታና በርሃብ እንዲታወቁ አድርጓቸዋል።

የፖለቲካ ንግድ ግለቱን በሚያቀጣጥሉ የውጭና የውስጥ ኃይሎች ፍላጎት እየተጠላለፈ ሀብታቸው በረከት ሳይሆን ርግማን ሆኖባቸዋል። በፖለቲካ ገበያ የሚሳተፉ ተዋንያን የኢኮኖሚ ፍላጎታቸውን ለማሳካት ከውስጥም ከውጭም ግፊት ያደርጋሉ። በዚህ ግፊ መንግሥታዊ ሥርዓትን ደካማ በማድረግ የኢኮኖሚ ሽሚያና ቅርምትን ያስፋፋሉ።

CamScanner

በአጠቃላይ የፖለቲካ ነጋዴዎች የሕዝብን ሀብት ለግላቸውና ለቡድናቸው ያውሉታል በእንዲህ ዓይነት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ውስጥ ሠርቶ መክበር፣ ፈጥሮ መበልጸግ ላም አለኝ በሰማይ ይሆናል። የተማረው ቦታ ያጣል። አምራች ልፋቱ በመናኛ ይለወጣል። ፈጠራ በአቋራጭ ይቀደማል። ለፍቶ ማግኘት ባላዋቂነት ያስመድባል። መፍጠን ይሰናከላል። ብዙ ድኻዎች ጥቂት ባለ ዕንቁዎችን ከበው ይታያሉ። ዕሴቶች ተንደው ተቋማት ተገርሥሠው ገንዘብ መናገር ይጀምራል። በዚህ ጊዜ የፖለቲካ ገበያው ደርቶ የሀገር ምሰሶ በእቶን እሳት ይበላል። የሀገር ጣሪያም አንድ ቀን መደርመሱ የማይቀር ይሆናል።

## 11.4 የኃይል ፍላጎት

ለኃይል ፍላጎት ገፊው ምክንያት የአንድን ግለሰብ ወይ የአንድን ቡድን ፍላጎት አልያም የአንድን ማኅበረሰብ የጋራ ግብ እውን ለማድረግ ሌሎችን የመቆጣጠርና የማስገደድ ፍላጎት ነው። በምድር ላይ ያለው ፍጥነት ከኃይል ፍላጎት ይመነጫል። የሳይንሳዊ ምርምር፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራው፣ የጦር መሣሪያ ክምችትና ፈጠራ እንዲሁም በጠፈር ላይ ቦታ ለማግኘት የሚደረገው እሽቅድድም ከምርምርና ከማወቅ ፍላጎት ባሻገር ያለው የኃይል ፍላጎት ነው።

የኃይል ፍላጎት ትሥሥሩ በሕይወት ከመኖር ጋር ተዋሕዷል። የኃይል ፍላጎት በግልና በቡድን ማኅደር ውስጥ ይኖራል። የግል የኃይል ፍላጎት ከቡድኑ ጋር ሲሠምር ቡድኑን ይቀላቀላሉ። ይሁንና በቡድን ውስጥ ግላዊ የኃይል ፍላጋ እንደተጠበቀ ይቀጥላል። ቡድኖችና ግለሰቦች እንዳይጠፋፉ ኃይልን የፈለጉበት ዓላማ ያቆያቸዋል።

ኃይል በፖለቲካ ውስጥ ተጽዕኖ መፍጠሪያና ዓላማን ማከናወኛ መሣሪያ በመሆን ያገለግላል። የፖለቲካ ልሂቃን ግብ የኃይል ፍላጎት መሆኑ የሚደበቅ አይደለም። የሰውል ጅ ሥልጣኔ የኃይል ፍላጎትን የሚገራ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት አበጅቷል። የኃይል ፍላጎታችንን በሕግ፣ በሥርዓትና በሞራል ልዕልና እንድናስተናግድ የሚያደርጉ አስገዳጅና ገላጭ ሥርዓቶችን አበጅቷል። ባደጉና ባላደጉ ሀገራት መካከል ያለው የዕድገት ልዩነት መሠረት የኃይልን ፍላጎት መግራት በመቻልና ባለመቻል ነው።

መግራት ማለት ማስተማር፣ መሥመር ማስያዝ፣ ማሠልጠንና ማብቃት ማለት ነው። ይህም በአስተሳሰብና በጠባይ የሚገለጥ ይሆናል። በመሆኑም በአንድ ሀገር የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ የኃይል ፍሰት፣ ፍላጎትና ስበት ስለ ሀገሩ ብዙ ይነግረናል።

በሀገራችን የኃይል ፍሰትና ስበት በኃይል ፍላጎት ሲናጥ ይስተዋላል። የስበት ኃይሉ በርትቶ ሁሉን ጨምድዶና ደፍጥጦ በመያዝ የሚታይበት ጊዜ አለ። በሌላ በኩልም የኃይል ፍላጎቶችን ባለመግራት ምክንያት በተገኘው መንገድ ሁሉ የኃይልን ፍላጎት ለማርካት ግርግር ሲፈጠር ይታያል። ፍሰቱ ያልተስተካከለና ያልተገራ ኃይል አውዳሚ ነው። ፍሰቱና ስበቱ የተዛባን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ገበያ ብለን እንጠራዋለን።

በሕግና በሥርዓት የማይመራ የኃይል ፍላጎት በፖለቲካ ገበያ ውስጥ ይጠነሰሳል። የኃይል ፍላጎታቸውን ለማሳካት የልዩነት ስንጥቃትን እያሰፉ በዳይና ተበዳይ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ፣ አሸናፊና ተሸናፊ፣ ተገፊና ገፊ፣ ባለጊዜና ጊዜ የጣለው በሚሉ የኃይል ውርወራዎች ኃይል ለመያዝ የሚደረጉ ሩጫዎች የፖለቲካ ገበያው ሸቀጦች ናቸው። በፖለቲካ ገበያው የኃይል ፍላጎት ሩጫው የግልና የቡድን የኃይል ፍላጎትን በተዘዋዋሪ መንገድ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ውስጥ ለማርካት መንሰፍሰፍ ነው።

በመንግሥት የተሰጣቸውን ኃይል ለግላቸውና ለቡድናቸው ፍላጎት ማርኪያ ያደርጉታል። የኃይል ፍላጎት በገንዘብ ይመጣል፤ በገንዘብም ይጠበቃል የሚል እምነት አላቸው። በዚህም የተነሣ ሕገ መንግሥትና ሕገ መንግሥታዊነት በፖለቲካ ንግድ ቦታ የላቸውም። በሕግ የተገኘ ሥልጣንና ኃይል በገንዘብ ይጠበቃል፤ በገንዘብ ይሸጣል። ባለ ሀብቶች የኃይል ፍላጎታቸውን ከገበያው እንደ ሸቀጥ ይገዙታል። ኃይልም ሀብትን(ገንዘብን) ይገዛል። በፖለቲካ ገበያው አንዱ የጎደለውን አንዱ እየሞላና እየተገበያዩ ቢቀጥሉም፤ ለረጅም ጊዜ አይዘልቁም።

CS CamScanner

የኃይል ፍላጎት ካልተገራ ሁሉን መጠቅለል ይፈልጋል። ይሄም በፖለቲካ ገበያው ላይ በዚህም የኃይል ሞገዱ ማንን እንደሚያጠፋ መለየት እስኪያዳግት ድረስ ረብሻ ይሆናል። ትርምስ ይፈጥራል። የኃይል ፍሰትና ስበትም ይረበሻል። ትርምሱ ሥርዓትን ይበጠብጣል።

**11.5.** ያልተገባ ክብር

አንዳንድ ጊዜ፣ ተፈጥሯዊው የሰው ልጅ ክብርን የመሻትና የመጎናጸፍ መብት "ሁሉም እንስሳት እኩል ናቸው፤ አንዳንድ እንስሳት ግን የበለጠ እኩል ናቸው" በሚለው የጆርጅ ኦርዌል ሕግ የሚመራይመስላል። ለዚህም ነው ወደ ጥፋት የሚያመራው። በርግጥ ሀብትም ሆነ ኃይል ግባቸው ክብርን ማስጠበቅና ማረጋገጥ ነው። ይሁን እንጂ እንደ እንስሳቱ ተረክ ሁሉም ለኔ ይገባኛል ማለት ዘላቂ ክብር አያቀናጅም። ባልተገባ መንገድ የተገኘ ሀብትና በሕግ የማይገራ ኃይል ክብር አያላብስም።

የፖለቲካ ገበያውን ከሚያቀጣጥሉ ምክንያቶች መካከል የመሪዎች ያልተገባ ክብርና ሀብት ፍለጋ ውስጥ መግባት ነው። ይህ የመሪዎች ያልተገባ ውዳሴና ጥቅምን ፍለጋ የዓላማ መሳትን ይፈጥራል። እንዲሁም ሂደቶችን በማወሳሰብ ቅልጥፍናና ውጤታማነት እንዳይመጣ አዳጋች ያደርጋል። መሪዎች ያልተገባ ክብርና ጭብጨባ ለማግኘት ሲሉ የፓርቲና የመንግሥት ዓላማን ይስታሉ። እንደዚህ ዓይነት አመራሮች ባልተገባ አጀንዳ ይንሳፈፉና ጉዟቸው ወደ ዓላማና ግባቸው አይሆንም። ገንዘብና ጭብጨባ ወዳለበት ይታጠፋሉ።

መንገዶች ሲጠለፉና አቅጣጫ ሲስቱ መፍጠን አዳጋች ይሆናል። በመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ያሉ መሪዎች በፖለቲካ ገበያው ሲጠለፉና አቅጣጫ ሲስቱ ብልጽግናን ማረጋገጥ አዳጋች ይሆናል።

ቅልጥፍናን መጨመርና መፍጠን ያልተቻለበት አንዱ ምክንያት የመሪዎች ያልተገባ ጥቅምና ያልተገባ ክብር ፍለጋ ነው። መሪዎች ያልተገባ ጥቅምን ለማግኘት ሲሉ ሂደቶችን እያወሳሰቡ፣ መሆን የሚገባውን ትተው የማይሆነውን ወደ ማድረግ ይሄዳሉ። የሌብነት ትልቁ ችግር የሕዝብ ሀብትን ለግል ጥቅም ማዋሉ ብቻ ሳይሆን ነገሮችን ማወሳሰቡና ሂደቶችን ማጠላለፉ ነው። ለመስረቅ ሲባል በአነስተኛ ጊዜና በትንሽ ሂደት ሊፈጸም የሚችለው ጉዳይ ሂደቱ ይተበተባል። በማያልቅ ቀጠሮ ይጓተታል። ይህም በከፍተኛ ሁኔታ ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል።

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ዋናው ፍላጎታቸው የራሳቸውን ፍላጎትና ስሜት ማስጠበቅ ስለሆነ በአጭር ዕይታ/ርዕይ ነው የሚመሩት። መሬት ላይ ያሉ ተጨባጭ ችግሮችን ለማየት ስለ ሚያዳግታቸው መፍትሔን ለማምጣት አይችሉም፤ አይፈልጉምም። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ሁኔታ በመሪዎች መካከል የሚኖር የእርስ በእርስ መናበብ የላላ እንዲሆን አድርጓል። አንዱ አንዱን ለማድመጥና በጋራ ለመሥራት ከፍተት ስለሚፈጥር፣ በቅልጥፍናና በውጤት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይፍጥራል። በአጠቃላይም ይህ ተደራራቢ ችግር ሕዝብ ያለአግባብ እንዲንገላታ በማድረግ ምሬት ፈጥሯል።

በአጠቃላይ ያልተገባ ክብርና ሀብት መሻት፤ ለማውደም የሚፈጥን፣ በፈጠራ ሀብት ከማብዛት ይልቅ ያለችውን ተቀራምቶ የሚያሸሽና ባልበላውም ጭሬ ልበትነው በሚል ብሂል የሚመራ ነው።:

**11.6.** የሐሳብ አልባ ፖለቲካ አደጋዎች

በአንድ ሀገር ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ገበያ በፖለቲካ ምኅዳሩ ሲሰፋና በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በማኅበራዊ ተቋማት ውስጥ ሲንሠራፋ ሀገረ መንግሥቱን አደጋ ላይ ይጥለዋል። ሀገረ መንግሥቱን ከማፍረሱ አስቀድሞ የተለያዩ ሂደቶችን ያልፋል። ዋና ዋናዎቹን እንሥተን የሐሳብ አልባ ፖለቲካ ዳፋን እንመልከት። በሂደቱና በውጤቱ በሀገር ህልውናና በብልጽግና ላይ ያለውን አንድምታ ያስረዳልናል።

CamScanner

በሐሳብ አልባ የፖለቲካ ገበያ በምትናጥ ሀገር፣ ተቋማዊ ዐቅም እንዳይፈጠር፤ ያለውም እንዳይጸናና እንዲዳከም ያደርጋል። የተቋማት የማስፈጸምና የመቆጣጠር ዐቅም መዳከም፣ ለሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች እግር መፍታታት ይሆንላቸዋል። ተቋማትን ለግል መሻታቸው ከሕግና ከአሠራር ውጭ እንደተውሳክ ተጣብቀው መጠቀሚያ ያደርጓቸዋል። ተቋማትን ከማዳከሚያ ስልቶቻቸው መካከል ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። የሙስና መረብ መዘርጋት፣ ጉዳይን ከምንዳ ባለፈ በጥቅም የሚተሣሠር አጋር መፍጠሪያ ማድረግና ተቋማትን በቤተ ዘመድ መሙላት ናቸው።

የፖለቲካ ነጋዴዎች በእነዚህ ስልቶች ተቋማትን ለአንድ ቡድን ወይም ለአንድ ግለሰብ ገባሪ ያደርጋሉ። ተቋማዊ አሠራሮችን በመናድና ብቃት የሌለው የሰው ኃይል በመሠግሠግ፣ ተቋማትን ስንኩል ያደርጋሉ። በሂደቱም በተቋም ውስጥ ግልጽነትና ተጠያቂነት ይጠፋል።

በውጤቱም ተቋማቱ ለሕዝብና ለግል ዘርፍ የሚሰጡት አገልግሎት ይወድቃል። የዜጎች የፈጠራ ብርሃን ይጨልማል። የመንግሥት የብልጽግና ፍጥነት ይገታል። ይህ ሁሉ ተደምሮ ሀገረ መንግሥቱን እንዲፍረከረከ ያደርጉታል።

የሐሳብ አልባ ፖለቲካ ግብ ከሕግ በላይ ሆኖ ሀብትና ሥልጣን መቀራመት ነው። የሕግ ተቋማት ደግሞ የፖለቲካ ገበያን የመቆጣጠር ዐቅም አላቸው። የሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች ደግሞ፣ ራሳቸውን ከሥጋት ነጻ አድርገው ለመንቀሳቀስ፣ አስቀድመው የሕግ ተቋማትን በማዳከም እነርሱን ብቻ የሚያገለግሉ እንዲሆኑ ይሠራሉ። የሕግ የበላይነት አስከባሪ ተቋማትን ክንድ ለመጠምዘዝ የተለያዩ ስልቶችን አቅደው ይንቀሳቀሳሉ።

በዋነኝነት የሕግ አስፈጻሚውን አካል ክብር፣ ዝናና ታማኝነቱን የሚፈትን ፕሮፖጋንዳ በሰፊው ያሠራጫሉ። ፕሮፖጋንዳው በማንነትና በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ያነጣጠረ ነው። የሕግ አስፈጻሚዎችን ማሸማቀቅና ጥርጣሬ እንዲገባቸው ማድረግ የመጀመሪያው ማፍታቻ ስልታቸው ነው። ማኅበራዊ መገናኛውን የሕግ አስከባሪውን ጥላሸት ለመቀባት ይጠቀሙበታል። በመቀጠል የሐሳብ አልባ ምርኩዝ የሆኑትን ማንነትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችን በየቦታው ይለኩሳሉ። የሕግ አስከባሪውን ኃይል እንዲከፋፈል አድርገው ተቋማዊ ዐቅሙን ለማዳከም ይሠራሉ። በፈጠሩት ግጭት የሕግ አስከባሪውን አካል ደግመው በፕሮፖጋንዳቸው ሰቅዘው ይይዙታል።

የሐሳብ አልባ የፖለቲካ ነጋዴዎች ወጥመድ በዚህ አያበቃም። ከፍተኛ ገንዘብ መድበው ተቋሙን ለመቆጣጠር ይሠራሉ። በገንዘብ የገዟቸውን ኃይሎች በመጠቀም በተቋሙ ውስጥ ሠርገው ይገባሉ። ሥርገቱ በገንዘብ ኃይል ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን ሰው በማስገባትም ይጠናከራል።እሥርገው ያስገቧቸውን ሰዎች በመጠቀም ቁልፍ የሚሏቸውን የተቋም ሰዎች ለጥቅም ትሥሥር ያጫሉ። እነዚህን በመሳሰሉ ስልቶች የሕግ አስፈጻሚውን አካል እንደ “መስቀል በሬ” በየአቅጣጫው በሚወረወር ገመድ ጠልፈው ይጥሉታል።

በሐሳብ አልባ የፖለቲካ ገበያ ነጋዴዎች በሂደት እየተገዘገዘ የሚሄደው የሕግ አካል፣ ሀገር ከሚያገለግል ይልቅ የእነርሱ ጠባቂ ለማድረግ ይሠራሉ። በውጤቱም በሕግ ተከልለው የሀገርና የሕዝብ ሀብት የሚዘርፉ ኃይሎች ይፈጠራሉ። ሕግና ሥርዓት በተዛነፈበት ደግሞ እኩል የሚያወዳድር ሜዳ አይኖርም። ስለዚህም ራሱ ውድድርም አይኖርም። ውድድር በሌለበት ደግሞ ፈጠራና ፍጥነት ድርሽ አይሉም። ፈጠራና ፍጥነት ድራሻቸው በጠፋበት ሁኔታ የበለጸገ ማኅበረሰብ መገንባት የሕልም እንጀራ ነው።

ተቋማዊ ዐቅም ባለመዳበሩ የተነሣ የመንግሥት ሥልጣን ከሐሳብ ይልቅ በጫካ ትግል ይሆናል ተብሎ ይታመናል። ቀጥሎም በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ለታመም አባ የፖለቲካ ገበያ ኢመደበኛ የሆነ የሥልጣን መወጣጫ ይዞ መምጣቱ ሌላ አደጋ የተቋማት መዳከምና የሐሳብ አልባ ፖለቲካ መስፋፋት መንግሥትነትን በምርጫ መሆኑ ቀርቶ በፖለቲካ ገበያ ነጋዴዎች በድርድርና በሸያጭ የሚገኝ ያደርገዋል። ፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ ተቋማት በፖለቲካ ነጋዴዎች ያጠቃሉ። ይህም

CS CamScanner

የሥርዓት ደካማነትን ያስከትላል። የፖለቲካ ምኅዳሩ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ቡድኖች ሽኩቻ በረታታል። በዋልታ ረ ፖለቲከኞች መሳሳብ የተነሣ ተቋማዊና ማኅበረሰባዊ መከፋፈል ይበረታል። የተቋማቱ ድርሻ እሳት ከማጥፋት ያለፈ ዕቅም አይኖረውም፡ በመሆኑም አካባቢያዊነት እየደነደነ፣ ማኅበረሰባዊ ትሥሥር እየተበጣጠሰ ይሄዳል።

መንግሥታዊ አገልግሎት ከዝቅተኛ ደረጃ በታች ይሆናል። መንግሥት ማኅበራዊ ኃላፊነቱን መውጣት የማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። ማኅበራዊ አገልግሎቶች ያልተሟሉለት ኅበረተሰብ ለአካላዊና ለሥነ ልቡናዊ ሕመም ይዳረጋል። ማኅበራዊ ቀውሱ ሰብአዊ ቀውስ ያስከትላል። በመሆኑም የማደግና የመለወጥ ሕልሙን የተነጠቀ ማኅበረሰብ፤ የሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች መጠቀሚያ ይሆናል። አክራሪነትና መከፋፈሉ በዚያው መጠን ይጨምራል። ዘረፋና ንጥቂያ ሀገሩን ይሞላዋል። "ከሌላው የበለጠ ይገባኛል የሚለው የማጋበስና የመቀራመት ክፉ መንፈስ በነጋ በጠባ በግጭትና በጦርነት ውስጥ ያኖረዋል። ማኅበረሰባዊ ስክነት ይጠፋል። ስክነት በሌለበት ሰላም የለም፤ ሰላም በሌሌበት መፍጠርና መፍጠን አይኖርም። የሐሳብ አልባ ፖለቲካ መጨረሻ ከብልጽግና ይልቅ ጉስቁልና ይሆናል።

የሐሳብ አልባ ፖለቲካ ሌላኛው አደጋ ኢፍትሐዊ ኢኮኖሚና የሀብት ክፍፍል እንዲፈጠር ማስቻሉ ነው። የሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች የመጨረሻው ግባቸው የኢኮኖሚ ምንጮችን በመቆጣጠር ሀብት ማካበት ነው። የፖለቲካ ሥልጣንን የዚህ ግብ ማስፈጸሚያ ስልት ብቻ አድርገው የሚመለከቱ ናቸው። የኢኮኖሚ ምንጮችን በብቸኝነት በመቆጣጠር ኢፍትሐዊነትን ያሰፍናሉ። በሌላው ገጽ ደግሞ የኢኮኖሚ ምንጮችን ለመቆጣጠር በሚያደርጉት ፉክክር ግጭትና ጦርነት ይከፍታሉ። የኢኮኖሚ ምንጮችን ያለተወዳዳሪ በብቸኝነት በመቆጣጠር ኢኮኖሚውን ከውድድር ውጭ ያደርጉታል። ውድድርና ሰላም የራቀው ኢኮኖሚ፣ ለሀገር ዕዳ እንጂ ምንዳ አያተርፍም። ኢፍትሐዊ ቁጥጥሩም ሆነ የመቀራመት ግጭት፣ ኢፍትሐዊ ኢኮኖሚን በመፍጠር ጥቂት ሀብታሞችና ብዙ ድኻዎችን ይፈጥራል።

ኢኮኖሚው ከውድድር ወጥቶ በጥቂት የፖለቲካ ነጋዴ ባለ ሀብቶች እጅ ስለሚገባ መንግሥት የቀረጻቸውን የልማት ፖሊሲዎች ለማስፈጸም አይችልም። የመንግሥት

የልማት ፖሊስ አቅጣጫና በኢፍትሐዊነት የኢኮኖሚ ምንጮችን የተቆጣጠረው ባለ ሀብት አይጣጣሙም። ለምሳሌ መንግሥት ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን የመተካት ፖሊሲ ያራምዳል። በሌላ መልኩ ግን እነዚህ ባለ ሀብቶች በገቢ ሸቀጦች ላይ ያተኩራሉ። ከዚህ ከፍ ሲልም መንግሥት ያለማቸውን የሀገር ሀብቶች ይቀራመቷቸዋል። በመሆኑም እንዲህ ባለ ተቃርኗዊ ጉዞ የመንግሥት የልማት ፍጥነት ጎታችና አሣሪ ገመድ ይገጥመዋል። በሐሳብ አልባ ፖለቲካ የተጠለፈ መንግሥት፣ ሀገራዊ ሀብት ለማልማት የሚያስችል የረጅም ጊዜ ዕቅድ ለማውጣት አዳጋች ይሆንበታል።

ሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች በሀገርና በየአካባቢው የኢኮኖሚ ምንጮችን ለመቆጣጠር በሚያደርጉት ጥረት፣ ሽኩቻና fከከት ይፈጥራሉ። ሕዝቡን ሰላም እያሳጡ ሕዝብ በድህነትና በጉስቁልና እንዲኖር ያደርጉታል። ሀገራዊ ሀብትን ለመቀራመት በሚፈጠር ግጭትና መከፋፈል ዜጎች ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ለመሥራት ይቸገራሉ። በአጠቃላይ ሐሳብ አልባ ፖለቲካ የዜጎችን መዋቅራዊና ግለሰባዊ የመልማት መብት ይነፍጋል።

ሐሳብ አልባ ፖለቲካ ዓለም አቀፍ ግንኙነቷና ተደማጭነቷ የቀነሰ፣ ብሎም ለውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት በሯ ወለል ብሎ የተከፈተች ሀገር ይፈጥራል። "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባሉ፡ እንደሚባለው፡ ሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች ያመጡት አደጋም በውጭና በውስጥ ኃይሎች እየሰፋ ይሄዳል። በሁለትዮሽም ሆነ በብዝኃ ግንኙነት ብሔራዊ ጥቅሞቹን ማስጠበቅ የማይችል ሀገር ይፈጥራል።

"ፀሐይ በምዕራብ ስትገባ በምሥራቅ ትወጣለች" ይባላል። አንድ አካባቢ መሸቶበት ተኝቷል፤ ሌላው አካባቢ ለሥራ እየተነሣ ነው ማለት ነው። በሐሳብ አልባ ፖለቲካ የአንድ ሀገር ዕድገት እግር ተወርች ሲታሠር፣ ሌሎች ሀገራት ኢኮኖሚያዊም ሆነ ጂኦፖለቲካዊ ጥቅማቸውን በፈቀዱት መንገድ ያለ ድርድር ለማስፈጸም ዕቅም ያገኛሉ።

CS CamScanner

ሐሳብ አልባ ፖለቲካ ሉዓላዊነቱንና ብሔራዊ ጥቅሙን ማስጠበቅ የማይችል ሀገር እንዲፈጠር ያደርጋል። በመሆኑም ሀገራዊ መሠረተ ልማቶችን እንዳናለማ ከማድረግ ባሻገር፣ ከሀገር ውስጥ የፖለቲካ ነጋዴዎች ጋር በመመሣጠር ሀገራዊ ሀብት ይመዘበራል። በንዑሳን የፖለቲካ ነጋዴዎችና በውጭ ኃይሎች በሚፈጠር የጥቅም ትሥሥር ግጭቶችና ጦርነቶች ይበረታሉ። የውጭና የውስጥ ተዋንያን በዝተው ሀገራዊ መረጋጋትና ሰላም ማስፈን ሕልም ይሆናል። በመንግሥትነት የሚቀመጥ ኃይል የሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ከማስጠበቅ የውጭ ኃይሎች ወኪል ሆኖ ያገለግላል። በፖለቲካ ገበያው የሚፈጠረው እሽቅድምድምም የበለጠ ታማኝ አገልጋይ ለመሆን ይሆናል።

በአጠቃላይ በአንድ ሀገር የሐሳብ አልባ ፖለቲካ መስፋፋት አደጋው ብዙ ነው። ተቋማዊ ዐቅምን አድቅቆ ማኀበረ ፖለቲካዊ ቀውስ ይፈጥራል። ኢኮኖሚያዊ ኢፍትሐዊነት ያነግሣል። አለመግባባት፣ መከፋፈል፣ አክራሪነት፣ ግጭትና ጦርነት የበዛበት ሀገር ያደርጋል። ይሄም ሀገሪቱን ውስጣዊ መረጋጋትና ሰላም የራቃት ሀገር በማድረግ፣ ለባዕዳን አሳልፎ ይሰጣታል።

## 11.7. የተቋማት ድቀት

ለፖለቲካ ነጋዴ ተቋማት ማለት፣ በገፊ ምክንያቶች ላይ ተራብቶና አድጎ ህልውናውን ማቆያው ናቸው። የፖለቲካ ገበያ ግብ በተቋማት ውስጥ በመስፋፋት ከተቋማት ሕዋሳት ጋር ተመሳስሎ የኢኮኖሚና የኃይል ፍላጎትን ማሳካት ነው። በተቋማት ውስጥ የሚኖሩት የዕድገት ደረጃዎችም ማስተጓጎል፣ ማደናቀፍና መቆጣጠር ናቸው። በየትኛውም ደረጃ ያሉ ተቋማት በተለያየ መጠንና በተለያየ ደረጃ የዚህ ሰለባዎች ናቸው። የዳበሩ ተቋማትን በገነቡ ሀገራት የመንግሥት ፖሊሲዎችን የሚያስተጓጉሉና የሚያደናቅፉ ሥውራን እጆች አሉ። እነዚህ ሥውራን እጆች ባላቸው የገንዘብ ኃይል የሕግ አውጪ አካላትን የመመረጥ ዕጣ ፋንታን ይወስናሉ።

ያደጉ ሀገራት ይህንን የመሰለ ፈተና ባያጣቸውም የገነቧቸው ተቋማት ፈተናው ሀገረ መንግሥቱን እንዳያሠጋው አድርገውታል። በሠለጠነ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የፖለቲካ ሕይወት አገልግሎት፣ ትብብር፣ ሀብትና ኃይል እንደሚፈልግ አይካድም። ነገር ግን ቁጥጥር ይደረግበታል። በዚህም ተገቢና ሕጋዊ ያልሆነው ግብይታዊ ፖለቲካ እንደ ሙስናና ሌብነት ይቆጠራል። እንዲሁም ተጠያቂነት አለበት። በመሆኑም ሕጋዊ ቁጥጥር ስለሚደረግባቸውና ተጠያቂነት ስላለባቸው፣ ያፈጠጡና ዓይን ያወጡ ሳይሆኑ በድብቅና በጥንቃቄ የሚደረጉ ናቸው። ከተቋማዊ ፖለቲካ ጀርባ ወይም በከለላ ይደረጋሉ።

ጠንካራ ተቋም ባልገነቡ አዳጊ ሀገራት ግን የፖለቲካ ገበያው ከኢፍትሐዊነት ማንሠራፋት ተሻግሮ፣ በሀገር ህልውና ላይ አደጋ ይደቅናል። በአዳጊ ሀገራት ተቋማት በፖለቲካ ገበያ፣ በሥርዓትና በዘልማዳዊ አሠራር ይፈተናሉ። ዘልማዳዊ የተቋም አሠራሮች ለፖለቲካ ነጋዴዎች የሚፈጥሩት ምቹ ሁኔታ፣ የፖለቲካ ነጋዴዎቹ ወደ ተቋማት ለመግባት የሚያደርጉትን ትግል ቀላል አድርጎላቸዋል።

የፖለቲካ ንግድን ትርፍ አልባ ለማድረግም፣ መረጋጋትንና ሥርዓትን በመፍጠር፤ በጥቅም ትሥሥር ላይ ከተመሠረተ ፖለቲካዊ ሥርዓት ወደ ተቋማዊ የፖለቲካ ሥርዓት መሸጋገር ያስፈልጋል። ዘመናዊ ሥርዓቶች በዘመድ አዝማድ ከተመሠረተ የጥቅም ትሥሥር ተሸጋግረው ተቋማትን መገንባት የቻሉ ናቸው። የፖለቲካ ገበያ ይሄን ሽግግር ያላደረጉ ሥርዓቶች ገጽታ ነው። ይልቁንም በቤተ ዘመድ የጥቅም ትሥሥር ላይ የተመሠረተው የቀደመው ሥርዓት፣ የነጻ ገበያ ባሕርያትን ተላብሶ የተፈጠረ የፖለቲካ ዓይነት ነው።

ማንኛውም ሥርዓት ወደ መደርጀት መሄድ አለበት። የደረጀ ሥርዓት፣ ተገማች የሆኑ ጠንካራ ተቋማት የተገነቡበት ሥርዓት ነው። ነገር ግን በአፍሪካ ውስጥ ሥርዓቶች መደርጀት አልቻሉም። የአፍሪካ ሀገራት ተቋማትን መገንባት አዳጋች ሆኖባቸዋል። በእነዚህ ሀገራት ውስጥ ፖለቲካ ግለሰባዊ ነው። ሀገራቱ የተንጠለጠሉት በተለያዩ ግለሰቦች እጆች ላይ ነው። ሁኔታውም ኢተገማችና ያልተረጋጋ ነው። መረጋጋትና ሥርዓት ባልሰፈነባቸው በእነዚህ ሀገራት ፖለቲከኞች የሚንቀሳቀሱት በገበያ ሕግ ፖለቲካን ነግደው ነው።

CamScanner

ይህ ዓይነቱ አካሄድ ከቀደሙት የዘመድ አዝማድ የጥቅም ትሥሥር አካሄድ ጋር ይቀራረባል:: ከመቀራረብም አልፎ ከፍተኛ ውድድር የበዛበትና ሙሉ ለሙሉ የገበያን ባሕርይ የተላበሰ የፖለቲካ ዓይነት ነው። ፖለቲከኞች በእንዲህ ዓይነት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የፖለቲካ አገልግሎትን ገዥም ሻጭም ናቸው። አንድ ፖለቲከኛ ታማኝነቱን አከራይቶ በሚያገኘው ጥቅም መልሶ ከሌሎች ፖለቲከኞች ወይም ልሂቃን ጋር የጥቅም ትሥሥር ይፈጥርበታል።

ተቋማት ባልዳበሩባቸው ሀገራት የፖለቲካ ገበያ፣ የሥርዓቱ ዋነኛ ገጽታ ነው። ፖለቲካ የሚሠራው እንዲሁም ፖለቲካዊ ሕይወት የሚወሰነው ግለሰባዊ በሆነ የፖለቲካ ግብይት ነው። በእነዚህ ሥርዓቶች ውስጥ ግብይት ዋና ገጽታ ሲሆን፣ የትብብርና የታማኝነት ዋጋ በአቅርቦትና በፍላጎት ላይ ይመሠረታል። ጠንካራ ተቋማትን ባልገነቡ ሀገራት፣ የፖለቲካ ገበያ ከአብዮታዊ ለውጦች በኋላ፣ ወይም በጦርነት ውስጥ፣ ወይም ከጦርነት በኋላ ሊከሠት ይችላል።

በብዙ የአፍሪካ ሀገራት፣ ተቋማት በሚገባ አለመገንባታቸው ይታወቃል። በተቋማት እጥረትና ድክመት የተነሣ አንዳንድ ሀገራት የሥልጣን ሽኩቻን ተከትሎ ወደ እርስ በእርስ ግጭት ገብተዋል። የፀረ ቅኝ ግዛትን ትግል የመሩ ጠንካራ መሪዎችና ድርጅቶች በነበሩባቸው አንዳንድ ሀገራትም፣ ጠንካራ አምባገነናዊ ኃያላን ተፈጥረዋል። አንዳንዶቹ ወደ ዴሞክራሲያዊ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት የተሸጋገሩ ቢሆንም፣ ፈተናው ቀላል አይደለም።

ከእርስ በእርስ ግጭት በአንሠራሩት ሀገራት ወይም አዲስ በተመሠረቱ ሀገራት ውስጥ፣ በጦርነት ውስጥ የተፈጠሩ የኃይልና የጥቅም ትሥሥሮች አሉ። እነዚህ የጥቅም ትሥሥሮች ከጦርነት በኋላም ቀጥለው የፖለቲካ ገበያ ሥርዓት እንዲስፋፋ በር ከፍተዋል። አምባገነናዊ · ነጻ ተቋማት ባልተገነቡበት ሁኔታ በጠንካራ ሰዎች እጅ ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው። ከሥርዓቶቹ መውደቅ በኋላ የኃይል ክፍተት እንዲፈጠር አድርገዋል። ብሎም፣ ኃይልን የመጠቀም ዐቅም ባላቸው ልዩ ልዩ ተዋንያን መካከል በገንዘብና በብጥብጥ ላይ የተመሠረተ ከፍተኛ የፖለቲካ ድርድርና ውድድር ፈጥረዋል።

በእነዚህ ሀገራት ውስጥ የሀገረ መንግሥት ግንባታው የተጠናከረ አይደለም።

አንደኛ፥ የፖለቲካ ፋይናንስ ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎት ባላቸው ግለሰቦች (ባለ ሀብቶችና ፖለቲከኞች) እጅ የተያዘ ነው።

ሁለተኛ፥ የዐመጽ መሣሪያዎችን በበላይነት የመቆጣጠር መብት (ኃይልን በብቸኝነት የመጠቀም መብት) የተበታተነና አሻሚ ነው።

ሦስተኛ፥ የፖለቲካ አለመግባባቶች በተቋማዊ ሕግና አሠራር የማይፈቱበት (ሕግና ሥርዓቶች ባልተረጋጉና ድንገቴ በሆኑ ክሥተቶች ለተሞላው ፖለቲካ ጥገኛ ናቸው) ባህል አለ።

አራተኛ፥ የዓለም አቀፋዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሥርዓት ዋነኛ ጥገኞች ናቸው።

በእንደዚህ ዓይነት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛ በሆነ የሀብት መቀራመት ላይ የተመሠረተ የጥቅም ፉክክርና ግጭት ይፈጠራል። ይህን ሊቆጣጠርና ሊዳኝ የሚችል ሕግና የተቋማት ቁመና ግን አይኖርም። ሀገረ መንግሥቱ ፖለቲካውን ለማስተዳደር ዐቅሙ የላላ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ኃይልን የመጠቀም ዐቅምን በያዙ የተለያዩ ግለሰቦች ወይም ልሂቃን መካከል ከፍተኛ ፉክክር ይኖራል።

ፖለቲካዊ እንቅስቃሴንና ፖለቲከኞችን ለማስተዳደር የሚችል ተቋማዊ ዐቅም በሌለበት ሁኔታ አንድ ችግር ይፈጠራል። ፖለቲካን ለማካሄድ የሚያስፈልግ ፋይናንስ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ወታደራዊ ፍላጎት ባላቸው የተለያዩ ኃይላት ዘንድ ይያዛል። ይህም ሀገራቱን የአንድ ሰው ጠንካራ አገዛዝ የሰፈነባቸው ሀገሮች ያደርጋቸዋል። አልያም ዴሞክራሲ ያልሰፈነባቸው ሌላ ዓይነት ባሕርይን የተላበሱ ሀገሮች ይሆናሉ። ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ወይም ድርድሮች የተመሠረቱት

CamScanner

በገንዘብና በኃይል ልውውጥ (ግብይት) ላይ ይሆናል። በዚህም የፖለቲካ ገበያ በሀገራቱ በአጠቃላይ ወይም በሀገራት በተወሰኑ ክፍሎች የሰፈነውን አስተዳደራዊ ሥርዓት የሚገልጽ ነው።

ኢኮኖሚውን ወደ ግል ማዞር የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ነጻ ገበያ በማስታከክ፣ ሕጋዊ የሆነ የፖለቲካ ገበያን ለማሣለጥ ከፍተኛ ድርሻን ይወጣል። ይህ ዕሳቤ ጠንካራ ተቋማትን በገነቡ ያስችላል። ጠንካራ ተቋማት በሌላቸው ሀገራት ኢኮኖሚውን ወደ ግል ከማዞር ሀገርን ሀገሮች ላይ ነጻና ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ጤናማ የሆነ ፉክክር ለመፍጠር ወደ ግል ወደ ማዞር የደረሰ ነው። የሀገር ሀብት የነጻ ገበያ ውድድርና ዕድገትን ወደሚፈጥር ሁኔታ ከመቀየር ይልቅ፣ ለሀብት ቅርመታና ሀገርን የግል ንብረት ወደ ማድረግ እንዲዘዋወር ዕድል ክፍቷል።

**11.8.** የተከፋፈለ ፖለቲካዊ ማኅበረሰብ

የፖለቲካ ንግድ ከፍተኛ ደረጃ መድረሱ የሚታወቀው፣ ትጥቅ ያነገቡ ኃይላትና አደረጃጀቶች የንግድና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ ሲጀምሩ ነው። አክራሪነትን መሠረት ያደረጉ እንቅስቃሴዎች ሽኩቻን በመፍጠር በፖለቲከኞች ዘንድ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎትን በኃይል የማስፈጸሚያ መንገድ ናቸው። እነዚህ ኃይላት በፖለቲካ ንግድ ውስጥ ዑቅም እያገኙ ሲሄዱ፣ የውጭ ኃይላት የእነዚህን ኃይላት ፖለቲካዊ ታማኝነት በመግዛት ፍላጎታቸውን ያስፈጽሙባቸዋል።

ባላደጉት ሀገራት የፖለቲካ ንግድ ለደካማ መንግሥት መፈጠር ምክንያት ይሆናል። የፖለቲካ ንግድ ደካማ መንግሥታትን ይፈጥራል። ደካማ መንግሥታት ደግሞ የፖለቲካ ንግድ እንዲስፋፋ ምቹ መደላድል ይሆናሉ። ይሄም በተራው ሀገራትን የድቀት አዙሪት ውስጥ ይከታቸዋል። የድቀት አዙሪት ማለት በሀገራችን የልመና አዙሪት የሚባለው ዓይነት ነው። አንዲት በልመና የምትተዳደር እናት በልመና ላይ እያለች ልጅ ትወልዳለች። ልጅቱ በልመና ካባ ውስጥ ታድጋለች፤ እርሷም በተራዋ በልመና ትሠማራለች፤ እርሷም በጊዜዋ ልጅ ትወልዳለች፤ ልጇም በልመና ይሠማራል/ትሠማራለች። እንዲህ እያለ ትውልድ በልመና አዙሪት ውስጥ ያልፋል። አንድ ችግር ሌላን ችግር እየፈጠረ፣ ያ ችግር ደግሞ መልሶ እርሱን የፈጠረውን ችግር እያባባሰ የሚከሠት የውድቀት አዙሪት ነው። በአጠቃላይ ግን የፖለቲካ ንግድ በየትኛውም ሥርዓት ውስጥ የሀገረ መንግሥትን ጥንካሬ የሚፈትኑ የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል።

የጋራ ግብ መላላት፦ የጋራ ግብ ማለት አንድ ሕዝብ ሁሉም ዓይነት ልዩነቶቹ እንደተጠበቁ ሆነው፣ ነገር ግን በአንድነት የሚኖርበት ምክንያት፣ ኖሮም ሊያሳካው የሚፈልገው የጋራ ዓላማ ነው። በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖር ሕዝብ የጋራ ዕጣ ፈንታ ይኖረዋል። ይህ የጋራ ዕጣ ፈንታ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ባስቀመጠው ግብና በግቡ ዙሪያ ተሰባስቦ ለስኬቱ በሠራው ሥራ ላይ ይንጠለጠላል። በንብረትና በጥንካሬ በጋራ ግብ ዙሪያ የራ ሕዝብ ነገውን የተሻለ ያደርጋል። ከዚህ በተቃራኒ ለጋራ ግብ በጋራ መቆም የተሳነው ደግሞ ዕጣፈንታው የከፋ ይሆናል።

ፖለቲካ በልዩነት ላይ ሲያውጠነጥን ሰው እንደ ሥርዓት የተሰባሰበባቸው የጋራ ግቦች ታ እያጡ ይመጣሉ። የልሂቃኑ እንዲሁም በሕዝቡ ውስጥ የተፈጠረው የፖለቲካ ድባብ ትኩረቱ ተናጠላዊ ፍላጎቶች (ከሀገራዊ ግብ ይልቅ ቡድናዊ ወይም ግለሰባዊ) ይሆናሉ። ይልቁንም አለመግባባት የሚፈጥሩ ተናጠላዊ ፍላጎቶች ክፊት ለፊት ይፈጣሉ። በመሆኑም በተለያዩ ቡድናዊ ፍላጎቶች መካከል ያልተገባ ውድድርና ግጭት ይፈጠራል።

የፖለቲካ ሥርዓት የቆመበት አንደኛው መሠረት በፍላጎቶች መካከል ያለውን ልዩነት በማስታረቅና በማቻቻል ለጋራ ግብ የቆመ የፖለቲካ ማኅበረሰብ መገንባት ነው። የጋራ ግብ ከሁሉም በአጠቃላይ ከፍ ያለ ፍላጎት ነው። ማኅበረሰብን በአንድ አሰባስቦ የሚያስቀምጥ የጋራ ጉዳይ ነው። እነዚህ ግቦች ከቡድኖች በላይና በተናጠል ለማሳካት ከበድ ያሉ አጠቃላይ ፍላጎቶች ናቸው።

CS CamScanner

አግላይ የሆነ የማንነት ፖለቲካ በሰፈነበት ሥርዓት ውስጥ፣ ፖለቲከኞች ራሳቸውን በተናጠል የአንድ ማንነት ተወካይ አድርገው ይቆጥራሉ። ማንም ሳይሰጣቸው የአንድን ወገን ውክልና ነጥቀው ይወስዳሉ። ሥልጣን የሚታየው የአንድ ብሔር፣ የአንድ ሃይማኖት ወይም የሌሎች ማንነቶች ጉዳይ ማስፈጸሚያ ተደርጎ ነው። በመሆኑም ሁሉም እወክለዋለሁ የሚሉትን ሕዝብ ተናጠላዊ ፍላጎት አስጠባቂ አድርገው ራሳቸውን ይሾማሉ። በዚህ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ፣ የጋራ ግብ ቦታ እያጣ ይመጣል። ሁሉም አነስ ሲል ግለሰባዊ ፍላጎቱን፣ ከፍ ሲልም ቡድናዊ ፍላጎቶችን ለመፈጸም የሚሯሯጥ እንጂ፣ ለሀገራዊ ጉዳዮች ቁብ የሚሰጥ አይሆንም። ይልቁንም ሌሎች ፍላጎቶችን ወይም የጋራ ፍላጎትን መሥዋዕት በማድረግ፣ ግለሰባዊና ቡድናዊ ፍላጎትን ለማርካት እሽቅድምድሞች ይበዛሉ።

የማኅበረሰባዊ ትሥሥር መላላትና አለመረጋጋት፡- አንድ የፖለቲካ ሥርዓት የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ውቅር ነው። ጥቁር ነጭ፣ ሀብታም ድኻ፣ ሴት/ወንድ፣ የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች በአንድ ላይ የሚኖሩበት ነው። አንድን ሥርዓት ሥርዓት የሚያደርገው በእነዚህ ማኅበረሰቦች መካከል የሚኖር ትሥሥር ነው። የፖለቲካ ንግድ ልዩነትን በማጉላት፣ ይህንን ማኅበረሰባዊ ትሥሥር ያናጋል።

ማኅበረሰባዊ ትሥሥር በማኅበረሰቡ አባላት መካከል ያለ የግንኙነት ጥንካሬ፣ ትብብርና ወንድማማችነት/ እኅትማማችነት ነው። አንድ የፖለቲካ ሥርዓት ጥንካሬው የሚለካው በተቋማቱ ብቻ አይደለም። በአባላቱ የእርስ በእርስ መስተጋብርም ጭምር ነው። አንዱ የሌላውን ችግር በሚያዳምጥበትና በጋራ በሚቆምበት ልክ የሀገር ጥንካሬ ይለካል። የፖለቲካ ንግድ ትርፍን ለማግኘት ልዩነት ላይ የሚያውጠነጥን በመሆኑ፣ የማኅበረሰቡን የጋራ ዕሴቶችና ግንኙነቶች ይንዳል። በምትኩም ፉክክርና ሽኩቻ እንዲሰፍን ያደርጋል።

በተናጠላዊ የቡድን ፍላጎት ላይ የተንጠለጠለው የፖለቲካ ንግድ፣ ለዘመናት የቆየውንና በሂደት የዳበረውን የማኅበረሰብ የትሥሥር ሥሪትን ከሚሸረሽሩ ጉዳዮች መካከል ነው። በእኛና በእነርሱ፣ በወዳጅና በጠላት፣ በቅርብና በሩቅ ክፍልፋዮች ላይ ይንጠለጠላል። ማንነትን መሠረት ባደረገ የሤራ ትንታኔ ላይ የተመሠረተው ይህ ፖለቲካ፣ በማኅበረሰብ ውስጥ መተማመንን ይሸረሽራል። በማኅበረሰቦች መካከል እንዲሁም በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ያለውን መተማመን ይንዳል። ይሄንንም እያደረገ የሥርዓቱን መረጋጋት ቀጣይነት ጥያቄ ውስጥ ይከትተዋል።

የሕግ የበላይነትንና የፖለቲካ ተጠያቂነትን መሸርሸር፡- በፖለቲካ ገበያ በታነቀ ሥርዓት ውስጥ ሥራዎችና ውጤቶች የሚዳኙት በሕግ አይደለም። ማንነትን መሠረት አድርገው እንጂ። በዚህ ጠንቅ የተነሣ የፖለቲካ ተጠያቂነት ይሸረሸራል። ከሕዝብ ጋር የሚኖረው ግንኙነትም ግለሰባዊ ስለሆነ፣ ሕጋዊና ተቋማዊ በሆነ መንገድ ተጠያቂነትን ለማምጣት ያስቸግራል። የማኅበረሰቡ ተወካይ አድርገው ራሳቸውን የሚቆጥሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ንግግራቸውንም ይሁን ድርጊታቸውን የማንነት ሽፋን ይሰጡታል። ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚደረግ ማንኛውም ጥረት በማንነቱ ላይ እንደተቃጣ ጥቃት ይወሰዳል። በዚህም ተጠያቂነትን አጣብቂኝ ውስጥ ይከታል።

**11.9.** መንግሥትነት ከምርጫ ወደ ሽያጭ

ተቋማዊ ዐቅም ባለመዳበሩ የተነሣ፣ የመንግሥት ሥልጣን ከሐሳብ ይልቅ በጫካ ትግል ይሆናል። በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ለታመሙ አዳጊ ሀገራት፣ የፖለቲካ ገበያ ተቋማዊ ያልሆነ የሥልጣን መወጣጫ መንገድ ይዞ መምጣቱ ሌላ አደጋ ነው። የተቋማት መዳከምና የሐሳብ አልባ ፖለቲካ መስፋፋት፣ መንግሥትነትን በምርጫ የሚገኝ ሳይሆን፤ ይልቁንም በፖለቲካ ገበያ ነጋዴዎች አማካኝነት በድርድር ለሽያጭ የሚቀርብ ያደርገዋል። የሐሳብ አልባ ፖለቲካ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፈተና ሆኖ መጥቷል።

የሀገራችንና የአህጉራችን አዲሱ የመንግሥትነት ፈተና ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ነጋዴዎች የፈጠሩት የፖለቲካ ንግድ ነው። እኛና አህጉራችን በተለያየ የጭቆና ምዕራፍ አልፈናል።

CamScanner

እንደ ሀገርና እንደ አህጉር በእርስ በርስ ጦርነት ተፈትነናል። ተደጋጋሚ መፈንቅለ መንግሥት መትቶናል። ይሄም ዴሞክራሲያዊ የሆነ የሥልጣን ሽግግር ብርቅ እንዲሆንብን አድርጓል። ዐማጽያን ክላሽ አንግበው ወደ ቤተ መንግሥት እንዲገቡ ካስቻሏቸው ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች መካከል ተቋማዊ ዐቅም አለመገንባቱና የውጭ ጣልቃ ገብነት ተጠቃሽ ነው።

ማንነትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች በውስጥ ሲነጭ የውጭ ኃይሎች ጥቅሞቻቸውን ለማስቀጠልና ለማስጠበቅ ሲሉ ጣልቃ ይገባሉ። ይህን ጊዜ አህጉራችን መንግሥታዊ ሥርዓት አልረጋ ይላታል። የሐሳብና የሥርዓት ዐቅም ሲዳከም የጡንቻ ዐቅም ቦታውን ይወስዳል። በዚህ የተነሣ ባለ ክላሹ ሁሉ እየተነሣ መፈንቅለ መንግሥት ይሞክራል። አህጉራችንም ባልረጋ መንግሥታዊ ሥርዓት እንድትወዘወዝ ያደርጋታል። አብዛኞቹ መፈንቅለ መንግሥት የተካሄደባቸው ሀገራት፣ ሕዝቡን ከጭቆና እናወጣለን በማለት የተጀመሩ ነበሩ። አብዛኞቹ ግን ሥልጣን ከያዙ በኋላ ቃላቸውን ዘንግተውት ጨቋኝን ተኩ ጨቋኞች ይሆናሉ። እንዲህ ባለ ቀውስ ተቋማት እየደቀቁ፣ መንግሥታዊ ቅቡልነት ከሕዝብ ሳይሆን ከጠመንጃ እንዲሆን አስገድዷል።

በአፍሪካ እ.አ.አ. ከ950 ወዲህ ባሉት ጊዜያት ውስጥ በርካታ መፈንቅለ መንግሥታት ተደርገዋል። አብዛኞቹ በሕዝቡ ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል ለማስወገድ ያለሙ ነበሩ። ቀሪዎቹ የካፒታሊስት-ሶሻሊስት ሥርዓቶች ፍትጊያ የወለዳቸው ናቸው። በተለይ በ1970ዎቹ መፈንቅለ መንግሥት በአፍሪካ የተለመደ ነበር። እንዲህ ያሉ ልምምዶች መደጋገምና መሳካት የመንግሥትነት መፍጠሪያ መንገድ ጉልበት እንዲሆን አለማምዷል።

ከአንጋችና ፈንቃይ የፖለቲካ ባህል በመውጣት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመትከል በአፍሪካ ብዙ ተሞክሯል። ባለፉት ሁለትና ሦስት ዐሠርት ዓመታት ውስጥ የመንግሥት ሥልጣን ከጠመንጃ ወደ ምርጫ እንዲያመራ እንደ አህጉርና እንደ ሀገር በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል። አንዱ ችግር መልኩን እየቀየረ ሌላ ፈተና እየወለደ ከአዙሪቱ ሳንወጣ፣ በጅምር ያለውን የዴሞክራሲ ልምምድ የሚፈትን የፖለቲካ ገበያ ተወለደ። መፈንቅለ መንግሥት በፖለቲካ ንግድ ተተክቶ ሌላ የሀገረ መንግሥት ፈተና ሆኖ መጥቷል። በአፍሪካ የመንግሥትነት ሥልጣንን በምርጫ ለመያዝ የሚደረግ ልምምድ፣ በፖለቲካ ነጋዴዎች ተጠልፏል። በዚህም የተነሣ ሥልጣን በምርጫ ሳይሆን በሸያጭ እንዲሆን አድርጎታል።

የአሁኑና የቀጣዩ ዘመን የሀገራት ቀውስ በፖለቲካ ገበያ የሚፈጠር እንደሆነ በርካታ ምልክቶች ይታያሉ። የዴሞክራሲ ሥርዓት ልምምድ በፖለቲካ ነጋዴዎች ተጠልፎ ማንነትን መሠረት ያደረገ መከፋፈልና ግጭት ተስፋፍቷል። የዴሞክራሲ ሥርዓት ልምምድ ሥር መሠረት እንዳይዝ በፖለቲካ ነጋዴዎችና በውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ተቋማት ሳይጸኑ እንዲፈርሱ እየተደረገ ነው። ሀገረ መንግሥታት ፈተናውን መቋቋም አዳጋች ሆኖባቸዋል።

ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ገበያው የመንግሥትነት ሥልጣንን ከኮሮጆ ወደ ገበያ ሥርዓት ስቦታል። መንግሥትነትን ከሐሳብ ትግል አውጥቶ በጠመንጃ እሩምታ እንዲተካ አድርጎታል። በኋላም ማንነትን መሠረት ባደረገ ግጭትና ጦርነት መንግሥታዊ ሥርዓትን ማዳከምና መቀራመት፣ ለፖለቲካ ነጋዴዎች የሀብትና የሥልጣን ቅርምት ማሳኪያ ስልት ሆኗል።

ቀደም ብሎ በዐማጽያን፣ በኋላም በመፈንቅለ መንግሥት፣ አሁን ደግሞ በፖለቲካ ነጋዴዎች የሚታመሰው የአፍሪካ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ፣ ለውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነት ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። በመከፋፈልና በግጭቶች መካከል ይገባሉ። ሲሻቸው መሣሪያ ሻጮች፣ ሲሻቸው አስታጣቂዎች፣ ሲሻቸው በሰብአዊ መብት ስም ጯሂዎች፣ ሲሻቸው ደግሞ አስታራቂዎች ይሆናሉ። ከንዑሳን ቡድኖች ጋር በኅቡዕና በግላጭ የሚያብሩ የውጭ ኃይሎች የፖለቲካ ነጋዴዎች ሀገረ መንግሥቱን እንዲቆጣጠሩ ያግዛሉ። አልያም የተዳከመ መንግሥት እንዲኖር አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራሉ። መንግሥታዊ ሥልጣን ከሕዝብ ድምፅ ሳይሆን ከውጭ ኃይሎች ድጋፍ እንዲሆን ልማድ ይተክላሉ።

CS CamScanner

በፖለቲካ ነጋዴዎች የተጠለፈ መንግሥት የሕዝብን ሳይሆን የውጭ ኃይሎችን ፊት አይቶ ያድራል። የተዳከመ ማዕከላዊ መንግሥትና የፈረጠሙ አካባቢያዊ ኃይላትን ይፈጥራል። የመንግሥትነት ተፈጥሯዊ ባሕርይው ኮስሶ የጎረምሶች ቤት ይሆናል። በርግጥ ከዚህ የከፋም አለ። በአንድ ሀገር ከአንድ በላይ እንደ መንግሥት ዕውቅና ያላቸው ኃይሎችን የሚፈጥሩም አሉ። ማዕከላዊ መንግሥት ፈርሶ፣ ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ ኃይሎች በተለያዩ ሀገራት ዕውቅና ተሰጥቷቸው ይኖራሉ። ሀገሪቱን "እንደ ገና ዳቦ" ተከፋፍለው ይዋጋሉ።

### 11.10. በድኾች የከበረው ዓለም አቀፍ የፖለቲካ ንግድ

የፖለቲካ ገበያ አንደኛው ክንፍ የውጭ ጣልቃ ገብነት ነው። የውጭ ጣልቃ ገብነት ውስጥና ከውጭ የተሣሠረ ነው። ስለዚህም ቀጣይነት ባለው ሂደት ውስጥ ይከናወናል። የፖለቲካ ገበያውን በማፋፋም የእሳት አሎሎ ያስጨብጠዋል። የውጭ ኃይሎች የተለያዩ ምክንያቶችን እያነሱ በሉዓላዊ ሀገራት ጣልቃ መግባታቸው የተለመደ ሆኗል። በምክንያትነት የሚያቀርቧቸው ዝርዝሮች እውነተኛ መሻታቸውን የሚሸፍኑ ናቸው። እንደ የሰብአዊ መብት፣ ሽብርተኝነት፣ ብሔራዊ ሥጋትና ለወዳጁ ሀገር ከለላ መስጠት የሚባሉ ናቸው።

እውነተኛ ፍላጎታቸው ከሞላ ጎደል ጂኦፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ በሚሉ ሁለት ምክንያቶች ሊገለጽ ይችላል። ሁለቱን ደግሞ የኃይል ፍላጎት በሚል መጠቅለል ይቻላል። በእነዚህ ምክንያቶችና ፍላጎቶች ላይ የተመሠረተ ትንተና በማድረግ የማስፈጸሚያ ስልቶችን ይነድፋሉ። የስልት ማስፈጸሚያዎቻቸው የሀገራት የሁለትዮሽና ባለ ብዙ ወገን ግንኙነቶች፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የብድር አዙሪት፣ ድንበር ተሻጋሪ ኩባንያዎች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና መገናኛዎች እንዲሁም ሀገራዊ ውስጣዊ ሁኔታዎች ናቸው።

የዓለማችን የኃያልነት ሩጫ "ትንሹን ዓሣ ትልቁ ዓሣ የሚሰለቅጥበት አካሄድ ነው። "የዝሆኖች ትግል ለሣሮች ጠንቅ" እንደሆነው ሁሉ፣ አንድ ብቸኛ ኃይል ለመፍጠር የሚደረገው የኃያላን ፍልሚያና ትግል፣ የአዳጊ ሀገራትን የመልማት መሻት አቀበት አድርጎታል። ለአንዱ ኃያል ደጋፊ መሆን እንጂ ለራስ ኃያል መሆንን የማይፈቅድ ሆኗል። በአንድ አስተሳሰብ መጠቅለልና ማደር ብቸኛ አማራጭ እየሆነ ነው።

"በእኔ በኩል ያልተሰለፈ፣በሌላው በኩል እንደተሰለፈ ይቆጠራል" በሚል አንድምታ የሚመራው ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት፣ ድኾችን የበለጠ ያደኸያል። ባለጠጎችን ደግሞ ከልክ በላይ ያበለጽጋል። በዚህ ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ መድረክ የተያዘው የአዳጊ ሀገሮች ህልውና አደጋ ውስጥ ገብቷል። ከድህነት ለመላቀቅ የሚያደርጉት ጥረት በፖለቲካዊ ስልቶች በየጊዜው ይናጋባቸዋል። ዕድገታቸውን ወደ ተስፋ አስቆራጭ አዙሪት ይቀይርባቸዋል። ጉዟቸውን "አንድ ርምጃ ወደፊት፣ ሁለት ርምጃ ወደ ኋላ አድርጎታል። አዳጊ ሀገራት ከድህነት ለመውጣት የሚያደርጉት ትግል፣ በፖለቲካ ንግዱ ተጠልፎ መንገዱ ተዛብቷል። በዚህም ምክንያት እነዚህ ሀገራት የራሳቸውን ዕድል በራስ የመወሰን ትግል ውስጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል።

CamScanner

# ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

## 12. ለሐሳብ አልባ ፖለቲካ ለም መሬት

### 12.1. የሐሳብ አልባ ፖለቲካ አስቻዮች

ለሐሳብ አልባ ፖለቲካና ፖለቲከኞች አስቻይ ሁኔታን የሚፈጥሩት የሀገራችን የፖለቲካ ስብራቶችና ነባራዊ ገጽታዎች እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታው ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በጥቅም ትሥሥር ሥልጣንና ሀብትን ለመቀራመት ለሚደረገው ፖለቲካ ለም መሬት ናቸው። ከተዘበራረቀ የፖለቲካ ትርክት ጀምሮ፣ የተበላሸ የፖለቲካ ባህል፤ የተበታተነው የመረጃ የበላይነት፣ የውጥረት ፖለቲካና ለዚሁ ማስኬጃ የሚሆነው ያልነጠፈ ንዋይ፣ ዋነኞቹ አስቻዮች ናቸው።

### 12.2. የተዛባና የተራራቀ የፖለቲካ ትርክት

በተለያዩ ክሥተቶች ውስጥ አልፎ የመጣ ማኅበረሰብ ስለ ትናንት የተለያየ ዕይታ ይኖረዋል። በትናንት ዕይታ የሚፈጠር ትርክት የማኅበረሰብን የሕይወት ዘይቤ ይቀርጸዋል።ትርክት በመሠረቱ የማስተባበርም የመበተንም እኩል ኃይል አለው። በዋናነት የኃይል ምንጩ ምስል ከሣችና አስተሣሣሪ መሆኑ ነው። ያልነበርንበትን ትናንት እንዳለን አድርጎ ያሳያል። ከዚህ ባለፈ በአካል ያልተገናኘና ቃላት ያልተለዋወጠን ሕዝብ በአንድ ምናብ ያገናኛል። ይህም ምናባዊ ማኅበረሰብ (imagined communities) ለመፍጠር ያስችላል። ይህ ኃይል ለብልጽግና ወይም ለጥፋት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። የማኅበረሰብ ልዩነቶች እንደተከበሩ አካታች ትርክቶች ላይ በመሥራት፣ ዛሬንና ነገን ውብ ማድረግ ይቻላል።

ትርክት ዓለምን የምንቃኝበት ዓይናችን ነው። በሕይወት ውስጥ የምንሰማቸው መረጃዎች፣ የሚገጥሙን ገጠመኞችና የምንኖርበት አካባቢ አስተሳሰብና ዕይታችንን በመቅረጽ የምንጋራውና የምንለያይበትን ትርክት ይሠራሉ። ይህም በማኅበረሰብ ውስጥ ራሳችንን የምንረዳበትን ሁኔታ ይፈጥራል። ከማኅበረሰብ ጋር ያለንን አንድነትና ልዩነት በዕዝነ ኅሊናችን ላይ ይቀርፃል። ትርክት አቅጣጫን ያመላክታል። የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን በመግባባትና በመረዳዳት ለጋራ ግብ የሚያሰልፍና የሚያሠማራ ገፊ ኃይል ነው። የትርክት ኃይል እንዳጠቃቀማችን ማኅበረሰባዊ ትሥሥርን ለማጠንከር አልያም ለግጭት ይውላል።

አዎንታዊ የትርክት ኃይል ፍጥነትንና ፈጠራን የማኅበረሰብ ዕሴት የማድረግ ዐቅም ፡ እንደዚያው ሁሉ አሉታዊ የትርክት ኃይልም ግጭትን ለመፍጠርና የማንነት ንግድ ክሂሎትን ለማዳበር ይውላል። ቅሬታዎችን እያባባሰ ግጭትን ይፈጥራል። ታሪካዊ ቅሬታን በማነሣሣት፣ አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በዕኩይ መነጽር በማሳየት፣ የፖለቲካ ክሥተቶችን በአሉታ በመተርጎም፣ ተቋማዊ ደካማ አሠራሮችን ሕገጋት አድርጎ በማሳየትና የሀብት ክፍፍልን ሆን ተብሎ እንደተደረገ አድርጎ በማመላከት ቅሬታዎች ወደ ግጭት እንዲያመሩ ይደረጋል።

ለቅራኔዎች ምላሽ መስጠቱ በዘገየ ቁጥር የፖለቲካ ገበያው ንግድ ግጭትን እንደ ገንዘብ መጠቀም ይጀምራል። አሉታዊ ትርክት ቅራኔዎችን በመሥራት፣ በማሳደግና በማስተዳደር ረገድ ያለው ድርሻ ትልቅ ነው። ግጭቶችን አርግቦ በሰላም ለመኖር ሥነ ምግባራዊ ትርክቶቻችንን ብንመለከት፣ የትርክትን ኃያልነት እንረዳለን። እንዲሁ የጥላቻ ትርክት አብሮ የኖረን ማኅበረሰብ ለመክፈል አቀጣጣይ ይሆናል።

የአንድ ዛፍ የታሪኩ መነሻ ሥሩ ቢሆንም ቅርንጫፎቹም በታሪኩ ውስጥ የተለያየ መጠንና ደረጃ አላቸው። በማኅበረሰብ ውስጥ ያለ ትርክትም መነሻው ሰው ነው። አሁን ያለንበት የትርክት ልዩነት እንደ ቅርንጫፎቹ ደረጃና መጠን የተለያየ ይሆናል። የዛፉ ሥር እየራቀና አንዳንዱ እየሞተ ሲሄድ የዛፉን የቀደመ ሥር ማግኘት ቀላል አይሆንም። እንደዚሁ ሁሉ፣ ከትናንት የሚነሣን ትርክት ሳይበረዝ ማግኘት ያዳግታል።

CamScanner

ቅርንጫፎች በተለያየ መጠንና ደረጃ በዛፉ ዋና ግንድ ላይ እንደሚኖሩ ሁሉ፣ የተለያየ ትርክት ያላቸው ማኅበረሰቦች የሚኖሩት በአንድ ሀገር ላይ ነው። የዛፉ ግንድ መታመም ለሁሉም ቅርንጫፎች ሥጋት እንደሚሆን ሁሉ፣ የሀገር ትርክት መታመምም ለንዑሳን ማኅበረሰቦችም አደጋ አለው። የሥሩና የግንዱ ጤና ለትልቁም ለትንሹም ቅርንጫፍ ሰላም ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ፣ አካታች ትርክት ለሀገር ጤና አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተቃራኒ ከግንዱ ተገንጥዬ እበቅላለሁ፣ አድጋለሁ፣ እሰፋለሁ፣ በጊዜም ዛፉን እወርሳለሁ የሚል ቅርንጫፍ መጨረሻው ዛፉን ማጥፋት ነው።

ይሁንና በሐሳብ አልባ ፖለቲካ ከአካታች ይልቅ አቃቃሪው ትርክት ይመረጣል። የፖለቲካ ንግዱ ሕይወት የሚኖረው የልዩነት ትርክቶች በደም ሥሩ መዘዋወር ሲችሉ ነው። የሰው ጠባይ ከአካታች ትርክት ይልቅ ቅራኔዎችን ማግነን ይወዳል። የሰው ልጅ ስላለው ሳይሆን ስለሌለው እንደሚጨነቀው ሁሉ በጋራ ድሉ ከመደሰት ይልቅ፣ በደሉ ያንገበግበዋል። ከሽልማት ይልቅ ነውር እንዲዛመት፣ ከመልካም መዓዛ ይልቅ መጥፎ ሽታ እንዲሰፋ፣ ከሚበላ ዘር አረም እንዲበዛ፤ ከሁሉ አካታች ትርክት አሉታዊ ነጠላ ትርክት ይደምቃል።

የአሉታዊ ትርክት ብዜት ሲጨምር የፖለቲካ ገበያ ይሠምራል፤ ከዚያም ጥቂቶች ለጥቂት ጊዜ የፖለቲካ ገበያውን ይወሩታል።

## 12.3. የተበላሸ የፖለቲካ ባህል

የኢትዮጵያ ፖለቲካ በየዘመኑ በርካታ ስብራቶች እያስተናገደ፣ ስብራቱ ሳይድንና ሳይጠነ እያነከሰ በማዝገም ከዚህ ትውልድ ደርሷል። እያነከሱ መፍጠን፣ እየቆዘሙ መፍጠር አይሆንም። ስብራቱ ተጠግኖና ሸሮ ከማንከስ ወደ ርምጃ፣ ከርምጃችን ወደ ሩጫ፣ ብሎም በፈጠራ ታግዘን ክንፍ አውጥተን ከፍ ብለን መብረር እንዲቻለን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ገበያ ማክተም አለበት።

ከትናንት በተሳበ፣ ዛሬ ላይ በተቃኘ እንጉርጉሮ ኃይላችን ዝሎ፣ ቅስማችን ተሰብሮ፣ እህህ በሚል ዜማ ነጋችንን ተሰርቀናል። ትናንትን ከዛሬ፤ ዛሬን ከትናንትና ከነገ ካላስተርን የጋራ ነገ የለንም። በተሰበረ ድልድይ፣ ባልጸና መሰላል መሻገር አይቻልም። ከፍታም አይገኝም። ከትናንት ጫፍ ተነሥተን በዛሬ ምንጣፍ ተጉዘን፣ ከነገ ሕልማችን ለመድረስ፣ ድልድዩን መዘርጋት ያስፈልጋል።

የዘመናችን የፖለቲካ ንግድ በትናንት ቆምሮ ዛሬንና ነገን መብላት ነው። ይህ የፖለቲካ ገጽታችን ፍጥነትን ገትቶ ፈጠራን አላሽቆ ለጋራ ግባችን ለብልጽግና እንዳንረባረብ ጎታች ኃይል ሆኗል። ፈጠራና ፍጥነት በአንድ ኃይል የሚሰለፍ ዐቅም ይፈልጋሉ። የሐሳብ አልባ ፖለቲካ ተዋንያን የተበጣጠሱና በየአቅጣጫው የሚሳሳቡ በመሆናቸው የኃይል ፍሰታቸው ዜሮ ነው። ዜሮ ላይ ሆኖ ፍጥነት የለም። ያልፈጠነ አይፈጥርም፤ ያልፈጠረም አይፈጥንም። በመጓተት የኃይል ፍሰቱ ዜሮ በሆነበት ክንድ ይዝላል፤ ያለአንዳች ለውጥ ኃይል ይሟጠጣል። መጓተት ሁሉንም ያደክማል። አንዱ ሲለቀው ሁለቱም ይወድቃሉ። አብሮ ከመውደቅ ተደጋግፎ መጓዝ መንገድ ያቀላል፤ ፍጥነትን ይጨምራል።

የሀገራችን አንዱ ፈተና ጽንፈኛ ግለሰቦችና ቡድኖች በፖለቲካ ገበያው ውስጥ መብዛታቸው ነው። ስግብግብና አግላይ ፍላጎቶቻቸውን ለማስፈን በሚጥሩ ኃይላት መካከል የሚደረግ፣ በጥቅም ትሥሥር ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ፣ ለሀገራችን ብልጽግና ሥጋትና ዕንቅፋት ነው።

የመንግሥት አስተዳደራዊ ሥርዓቶች በየሀገሩና በየዘመኑ የተለያየ መልክ እንዲኖራቸው ያደረጉ ምክንያቶች አሉ። የፖለቲካ ሥልጣን፣ ፖለቲካዊ ታማኝነትና አገልግሎት የሚገኝባቸው መንገዶች ዋነኞቹ ናቸው። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ከሕዝብ ይገኛል። የፖለቲካ ታማኝነትና አገልግሎትም ለሕዝብ ነው። ወታደራዊ አምባገነን ሥርዓቶች ሥልጣናቸው ከመሣሪያ ይገኛል። በንጉሣውያን አገዛዝ ደግሞ ሥልጣናቸው " ከዘር ሐረግና ከሃይማኖት ይመነጫል።

CamScanner

ሁሉም ሥርዓቶች የተለያየ መልክና ባሕርይ ያላቸው ቢሆንም፣ ገንዘብ በሁሉም ሥርዓቶች ውስጥ ያለው ተጽዕኖ በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላል።

የዴሞክራሲ መገለጫው በሕዝብ የሚደረግ ምርጫ ነው። ከምርጫው አስቀድሞ ያለው ' ይሆናል። በምርጫ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ውጫዊና ውስጣዊ ሁነቶችን መገምገምና ደት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ አመልካች በመሆኑ፣ ከውጤቱ በበለጠ ሂደቱ ወሳኝ መመርመር ተገቢውን ውጤት እንድናገኝ ያስችለናል። በሂደቱ ውስጥ ተፎካካሪዎች የሚያቀርቡት አማራጭ የፖሊሲ ሐሳብ ዋነኛው ቢሆንም፣ በሂደቱ ላይ ተጽዕኖ ከውስጥም ሆነ ከውጭ ይፈጠራል። በምርጫ ሂደት ያደጉና ያላደጉ ሀገራትን አንድ ከሚያደርጉት አሉታዊ ተጽዕኖዎች መካከል ገንዘብ አንዱ ነው።

ገንዘብ በምርጫ ሂደት ውስጥ ያለው ሚና ጨዋታ ወይም ውጤት ቀያሪ የሚባል ያህል ነው። የገንዘብን ዕቅም በተወዳዳሪዎችና በዴሞክራሲ ተቋማት ላይ ባለው ተጽዕኖ ለያይተን መመለክት ይገባል። በአንድ በኩል ዴሞክራሲን ለማስፈን፣ ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሕግን ለማስከበር፣ ብሎም ተአማኒና እውነተኛ ምርጫን ለማካሄድ ገንዘብ ከፍተኛ ድርሻ አለው። በሌላ በኩል ደግሞ፡ ከተቋማዊ አሠራር በመውጣት ተቋማት በግለሰብና በቡድን በተደራጁ ኃይሎች የተገዙ ጊዜ፣ በገንዘብ ምክንያት ትልቅ ማነቆና ችግር ይፈጠራል። በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት ግልጽና ታማኝ ምርጫ ለማድረግ የዴሞክራሲ ተቋማት ዕቅም ብዙ የሚቀረው በመሆኑ፣ የገንዘብ አሉታዊ ሚና ከፍተኛ ነው።

በተፎካካሪዎች መካከል የላቀ አማራጭ ፖሊሲ በማቅረብ ከመወዳደር በላይ የገንዘብ ዕቅም ጎልቶ ሲወጣ፤ ተፎካካሪዎች በፖለቲካ ገበያው እንዲሳተፉ ያደርጋል። ገንዘብ የሥልጣንና የኢኮኖሚ ፍላጎትን በማዛመድ፣ የሕዝብ ሥልጣን የሚቆናጠጠውንና ባለ ሀብቱን ያስተሣሥራል። በገንዘብ ኃይል የሰፊውን ሕዝብ ድምፅ ጥቂት ሚልየነሮች እየገዙት "ሁሉም ድምፆች እኩል ናቸው" የሚለውን መሠረታዊ የዴሞክራሲ መርሕ ጥያቄ ውስጥ ይከቱታል።

ዴሞክራሲ ዳብሮባቸዋል በሚባሉ ሀገራት ሳይቀር ገንዘብ በፖለቲካ ሥርዓቶች ውስጥ ቀላል የማይባል ተጽዕኖ አለው። ለምርጫ ውድድር የሚዘረገፉ ረብጣ ዶላሮች ዕጩዎች አሸንፈው የመንግሥትን ሥልጣን ሲቆጣጠሩ ለከፋዮቻቸው የፖለቲካ ታማኞች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። በዚህም ሳቢያ ከከፋዮቻቸው አምባገነናዊ ተጽዕኖ ማምለጥ አይችሉም። ሀገሮች ጥራት ያላቸው ተቋማትን መገንባት ስለቻሉ ብቻ ዴሞክራሲን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ አያደርጉም።

በእነዚህ ሀገራት በምርጫ ፖለቲካቸው ውስጥ ገንዘብ በፖለቲካ ታማኝነት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያደርግ የሚታይ ነው። ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውለው ከፍተኛ ገንዘብ ከኢኮኖሚ ልሂቁ የሚገኝ ነው። የኢኮኖሚ ልሂቁ በምትኩ ለንግዱ የሚመች የፖለቲካ ወይም ወደ ሥልጣን ለመውጣት የሚያስፈልጋቸውን ከፍተኛ የቅስቀሳ ወጪ በመሸፈን፣ የፖሊሲ ድጋፍ ከፖለቲከኞች ያገኛል። እጅግ የናጠጡት የግል ኢንቨስተሮች፣ ፖለቲከኞች የተመቸን ሁኔታ ይፈጥራሉ። በመሆኑም ለምርጫ ቅስቀሳ ገንዘብ ማሰባሰብ የተፈቀደ ከፖለቲከኞች ጋር ትብብርን ይመሠርታሉ። በዚህም ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው ቢሆንም፣ በዴሞክራሲና በአጠቃላይ በብዙኃኑ ፍላጎት ላይ፣ እንዲሁም በምርጫ ውጤቶች ላይ ተጽዕኖ ያደርግባቸዋል።

ዴሞክራሲ በሌለባቸው ሀገራት ደግሞ ገንዘብ በፖለቲካ ውስጥ ያለው ኃይል ጠንከር ይላል። ጭራሹንም በአንዳንድ ሀገራት፣ ፖለቲካ በገበያ ላይ በገንዘብ የሚሸጥና የሚገዛ ቁስ ነው። እንደዚህ ዓይነት የፖለቲካ መነገጃ ሥርዓቶችም ፖለቲካዊ ጉልት ይባላሉ። በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ለምርጫ የሚወዳደሩ ሹመኞች ረብጣ ዶላሮችን የመክፈል ግዴታ ውስጥ ይገባሉ። ፖለቲካዊ ሥልጣን፣ ታማኝነትና ግልጋሎት እንደ ሸቀጥ ገበያ ላይ ቀርቦ ዋጋ ወጥቶለት የሚሸጥበት ሥርዓት ከሆነ፣ በእንደዚህ ዓይነት ሥርዓቶች ውስጥ ተቋማትና የሕግ የበላይነት ቦታ የላቸውም። ከዚያ ይልቅ የጥቅም ትሥሥር የጨዋታው ሕግጋት ዋነኛ የፖለቲካ ግንኙነት መሥመር ይሆናል። የፖለቲካ ሥርዓቱ በገንዘብ ከተገዛ፣ ወጥመድ ውስጥ

CS CamScanner

ወደቀ ማለት ነው። ልክ የዘር እህሉን እንደበላ ገበሬ ነው። በጸደይ የሚጠብቀው አዝመራ፤ በበጋ የሚሰበሰበው ፍሬ አይኖረውም።

የሀገራችን የዴሞክራሲ ልምምድ ገና በችግኝ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው ማለት ይቻላል። የምርጫ ሥርዓታችን ደግሞ ወደኋላ የቀረ ነው። ምንም እንኳን ስድስተኛውን ሀገራዊ ምርጫ ነጻና ፍትሐዊ ለማድረግ ረጅም ርቀት የተጓዘ ቢሆንም፣ እንደ አጠቃላይ ሀገራችን መንግሥት የመቀየሪያ ባህሉ በኃይልና በጦርነት ነው። የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ትግል እየተደረገ ቢሆንም፣ የባህል ለውጥ ግን ገና በሚገባው ልክ አልመጣም።

ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ለቀጣዩ ምርጫ የራሱን ዐሻራ አሳርፏል። ሀገራችንም ባደረገችው ስድስተኛው ምርጫ ማንም ቡድን ወይም ግለሰብ ካለ ሕዝብ ምርጫ ወደ ሥልጣን መምጣት እንደማይችል አሳይቷል። ነገር ግን ካለፈው ልምምድና አሁን እየተደረጉ ከሚገኙ ግጭት ቀስቃሽና አባባሽ ሁኔታዎች የተነሣ በአቋራጭና በኃይል ሥልጣን ለማግኘት፣ ካልተቻለ ደግሞ ሀገር ለማፍረስ ከፍተኛ ተጋድሎ እየተደረገ ይገኛል።

እነዚህ ኃይሎች ያዋጣናል ብለው ካሰቡት ጋር ሁሉ ይሠራሉ። ለሥልጣን ከሚቋምጡ የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ጋር እንዲሁም ከውጪና ከውስጥ ከሚገኙ ሰላም ወዳድ ካልሆኑ ሐሳብ አልባ ኃይሎች ጋር ይደራደራሉ፤ አብረውም ይሠራሉ።

በሐሳብ አልባ ፖለቲካ ውስጥ ሙስና መገበያያ ገንዘብ ነው። በሐሳብ አልባ ፖለቲካ ውስጥ ሙስና እንደ ሸረሪት ድር ዕለት ከዕለት እየሰፋ ይሄዳል። የፖለቲካ ንግዱን በሌብነት መሥመር እያገናኙት ገንዘብ ተጠቅመው ያምሱታል። አንቂዎችን በመግዛት መወድስ ያሠራሉ። ለዚህም ሥልጣንና ዝናቸውን የሚገነቡበት የገንዘብ ምንጫቸው ሌብነት ነው። የሰረቁትን ቆንጥረው አካፍለው “ገንዘቡን የከፈለ ቅኝቱን ይወስነዋል” በሚል መርሕ የሚኖሩ፤ “በበሉበት የሚጮሁ" ዜማ ደርዳሪዎችን ያበዛሉ። የፖለቲካ ገበያው በሌብነት ጋዝ እየተንበለበለ በሀገር ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ላይ ዘርፈ ብዙ ጉዳት ያደርሳል። የፖለቲካ ገበያው በሙስና ሲናጥ፣ የሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት እየሰለለ በዜጎች መካከል ያልተመጣጠነ የሀብት ሥርጭትን ይፈጥራል።

**12.4.** የተበታተነ የመረጃ የበላይነት

“የሕዝብ መስክ” ፣ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ሕዝብ በነጻነት መረጃን የሚለዋወጥበትና ተጽዕኖ የሚፈጥርበት ከባቢና መንገድ ነው። በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ግለሰቦች በነጻነት የሚወያዩበት፣ የማኅበረሰብ ችግሮችን የሚለዩበትና በዚህ ውይይት መነሻነት በፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩበት ሐሳባዊ ምኅዳር ነው። ይህንን ከባቢ ለመቆጣጠር ብቸኛው መንገድ የብዙኃን መገናኛ ነው።

የዲጂታል መገናኛ አብዮት ከመምጣቱ አስቀድሞ፣ ከአንድ መነሻ፣ በአንድ ጊዜ ለብዙኃኑ መልእክት የሚተላለፍበት ዘመን ነበረ። በዚህም መንግሥት የመረጃና የመለዋወጫ መንገዱን በበላይነት ይይዛል። በአጀንዳ ቁጥጥር የሕዝብ መስክን ያስተዳድራል። በዚህ ዘመን በነበረው ሥርዓተ መንግሥት ሥር፣ የመንግሥት የመረጃ ግንኙነት መረብ እጅጉን ወደ ማኅበረሰቡ ወርዶ ነበር። ሕዝብም ጎረቤት ከጎረቤት ቡና ተጠራርቶ ማኅበራዊ ሕይወቱን ይጫወታል። “ዐደባባይ መዋል” በሚባለው ብሂል የተነሣ ስለ መንግሥት ሲወራ ቀርቦ የመስማት ዕድል ነበረው። ነገር ግን የዲጂታል መገናኛ አብዮት መምጣቱን ተከትሎ፣ የመገናኛ ብዙኃን የበላይነቱ ያልተማከለ ሆነ። ምንጩም፣ መዳረሻውም፣ ማድረሻውም ብዙ ሆነ። መንግሥት የሕዝብ መስክን ለማስተዳደር አስቸጋሪ ሆኖበታል።

አሁን ባለንበት ዘመን የሞባይል ስልክ ከመንደራችን አልፈን ዓለምን መመልከቻ መር ሆኗል። ተጠቃሚዎች እንደ ምርጫቸዉ ያሻቸውን የሚያዩበትና የሚያዳምጡበት ሁኔታ ብዙ ነው። ኢንተርኔትና ማኅበራዊ መገናኛ ደግሞ በተለይም በከተሞች አካባቢ ሰዎች የራሳቸውን ሐሳብና ይዘት ለተቀረው ማኅበረሰብ የሚያካፍሉበት መስክ ሆኗል።

CamScanner

በዚህም የሕዝብ መስክ በፖለቲካው ወይም በመንግሥታቸው ላይ የሰላ ትችታቸውን ባስ ሲልም ቁጣቸውን በግላጭ የሚያቀርቡበት ምኅዳር ሆኗል። ይሄም ምኅዳር ከዐደባባይ አስተዳደር በቀላሉ ወደ መረጃ መረብ አስተዳደር ቀይሮታል። የዲጂታል መገናኛ ማው ወጥቶ የዲጂታሉ ዓለም ሆኗል። የዲጂታል መገናኛ አብዮት የመንግሥትን መዋቅራዊ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አንገት ለአንገት ተናንቆ እንዲሄድ እያደረገው ነው።

ይህም በተለያየ መልኩ ከትብብር ይልቅ የውድድር አካባቢን ይፈጥራል። ለሀገረ መንግሥት ግንባታ አደጋ እንዲሁም ለፖለቲካ ገበያ አስቻይ ሁኔታን ያመቻቻል። ይሄም የፖለቲካ ገበያ ሀገርን ከመሠረቷ ጀምሮ በአሸዋ ላይ እንደተገነባች ቤት በቀላሉ በማዕበል ተጠርጋ የምትወሰድ ያስመስላታል። የፖለቲካ ነጋዴዎች ግለሰቦችን ጨምሮ ሕዝቡን በቀላሉ የመድረስ ዕድል አግኝተዋል። በዚህም ምክንያት የፖለቲካ አትራፊዎች ሀገርን እንደ ሸቀ ወደ ገበያ በማውጣት በጅምላና በችርቻሮ እንድትሸጥ በር ከፋች ሆነ። ይህም ተቆጣጣሪ ተጠያቂ የሌለበት ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴን ይፈጥራል። አለፍ ሲልም ዐመጽን ጎትቶ ወደ ቤታችን ያስገባል።

ይህንን ያህል የቀረበ የመረጃ ልውውጥ ለፖለቲካ ገበያ አስቻይ ነው። በማስተዋልና በንቃት ከተጠቀምንበት ደግሞ ፈጠራን በማበረታታትና ፍጥነትን በማስቻል ረገድ አዎንታዊ ድርሻ አለው። በተለይ እንደኛ ላሉ አዳጊ ሀገራት፣ ያደጉ ሀገራት የሄዱበትን ዳና ተከትለን እንደግ ብንል ብዙ ማገዶ ይፈጅብናል። በመሆኑም የዲጂታል አብዮት ለዝላይ ስትራቴጂያችን ያለውን ዕድል መጠቀም አለብን። በዲጂታሉ ዓለም የሚናፈሰውን በታኝ ወሬ ለፈጠራና ለፍጥነት እንደማይሆን ተረድተን ከተጠቀምን አትራፊ እንሆናለን።

ይሁን እንጂ የፖለቲካ ገበያተኞች ይህንን ዕድል በማምከን፣ የግልና የቡድን ትርፋቸውን ለማጋበስ የዲጂታል አብዮቱን ለፖለቲካ ገበያቸው አስቻይ ዐቅም አድርገውታል፡ የዲጂታል አብዮቱ መረጃዎችን በተለያየ መንገድና ፍላጎት፣ በመበረዝና በማጋነን ለማድረስ የሚቻልበትን ክፉ ዕድል አስፍቷል።

ከዚህ ቀደም የመረጃ ምንጮች በኢትዮጵያ መንግሥት የተያዙ ነበሩ ። ከመንግሥት መገናኛዎች ውጭ መረጃ ለማግኘት የጀርመንና የአሜሪካ ሬዲዮኖችን ማዳመጥ የግድ ነበር። ከዕለት ኑሯቸው ትይዩ ማኅበራዊም፣ ኢኮኖሚያዊም፣ ከፍ ሲልም ፖለቲካዊ ጉዳዮች መለከተናል፣ ያገባናል ያሉ ዜጎች እጅግ ጥቂት ነበሩ። ዛሬ ከሊቅ እስከ ደቂቅ በየሰከንዱ መረጃን ከማኅበራዊ መገናኛዎች ላይ ሚልዮኖች ያፈላልጋሉ። የሚፈልጉትን ጣቢያና መረጃ ቢፈልጉ በቴሌቪዥናቸው ቢፈልጉ በበይነ መረብ በሁለገብ መረጃ አቅራቢዎች በኩል እልፎች ይኮመኩማሉ።

ትናንት ሳምንትን ጠብቀው ጋዜጣ፣ ወርን ጠብቀው መጽሔት በማንበብ መረጃና ትንተናን የሚያነቡ ጥቂት ሰዎች ነበሩ። ዛሬ ሚሊዮኖች በየሰከንዱ በማኅበራዊ መገናኛ መረጃ ተቀባይ ብቻ ሳይሆን መረጃ ሰጪዎችም ናቸው። ትናንት ጓደኝነትና ወዳጅነት ከጣት ቁጥር አይበልጥም ነበር። ዛሬ በማኅበራዊ መገናኛ ዘመን ጓደኝነትና ወዳጅነት ሺዎችን ሚያካትት ሆኗል። በዚህ ሰፊ መረጃ ማሠራጫና ማንሸራሸሪያ ዐውድ የበዛና ያልጠራ መረጃ በገፍ ይቀርባል። በዚህም ለፖለቲካ ነጋዴው የዕብድ ገበያ ፈጥሮለታል።

ዛሬ ባለንባት ሉላዊ ዓለም ላይ “ስንዴው ከእንክርዳዱ ሳይለይ" ብሎም ከነገለባው ጓዙን ጠቅልሎ ወደ በይነ መረብ ከገባ ዋል አደር ብሏል። የመሬት ላይ እማሬያዊ ሕይወትና መረባዊ(Virtual) ሕይወት መሳ ለመሳ ቆመዋል። መረባዊ ሕይወት የሁሉ ነገር አድራጊ ፈጣሪ በመሆን የዕለት ሕይወታችንን ለመቆጣጠር እየሞከረ ነው። የዕለት ተዕለት ክንውኖቻችን ሁሉ ወደ በይነ መረብ ዓለም እየተጓዙ ናቸው።

መገናኛው፣ ኪነ ጥበቡ፣ ጨዋታው፣ ምግብ ቤቱ፣ ሱቁ፣ በጎ አድራጎቱ፣ ስብሰባው፣ ሃይማኖቱ፣ ንግዱ፣ ቢሮው፣ ዘመቻው፣ ወዘተ... ወደ መረባዊው ዓለም ከነግሳንግሳቸው ጓዛቸውን ጠቅልለው ገብተዋል። በአዎንታዊ ጎኑ ቀልጣፋ የፖለቲካ

CS CamScanner

ኢኮኖሚ ሥርዓት ፈጥሯል። ፈጠራና ፍጥነት የሥርዓት ዕሴት እንዲሆን እያላመደ ይገኛል። በአሉታዊው ጎኑ ደግሞ ለፖለቲካ ነጋዴዎች በቀላል ልፋት ፖለቲካን እንዲሸቅጡ አስችሏቸዋል።

መረባዊ ዓለም - ጊዜና ቦታ የሚባሉ ሁለት ዋና ዋና የህላዌ ዓምዶችን ዋጋ ያሳጣል። ዛሬ ምንም ነገር ለማድረግ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ፣ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ፣ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር መሄድ አያስፈልግም። ጥቂት ፊደላትን በመጻፍ ብቻ የትም ቦታ መገብየት፤ ሲኒማ ማየት፤ ስብሰባ መካፈል፤ ዘመቻ መሳተፍ እናም ሌሎች መሠረታዊ ጉዳዮችን መከወን ይቻላል። መረጃ ማግኘትና ማሠራጨት የእስትንፋስ ፍጥነትን ያ ቀላል ሆኗል። ቀሊልነቱ እንዲሁ ለፖለቲካ ነጋዴው መሳ ለመሳ ዕድል ፈጥሯል።

የአንድ ለአንድ የመረጃ ልውውጥን በአካል፣ በስልክ፣ በፖስታ) እና የአንድ ለብዙ የመረጃ ልውውጥን (በጋዜጣ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቭዥን) እየተካ የመጣው የብዙ የመረጃ ልውውጥ (ማኅበራዊ መገናኛ፣ ሰዎች መረጃዎችን እንዴት አጣርተው መጠቀም እንዳለባቸው ግራ እንዲጋቡ ያደረገ ነው። ሰዎች መረጃን በሚዛን ሳያስቀምጡ በግምታቸው ቅለቱንና ክብደቱን እንዲተነብዩ አድርጓቸዋል። የመረጃ መብዛትን ተከትሎ መረጃን አጥርቶ መጠቀም ዋና ችግር ሆኗል። የጠራ መረጃ ማግኘትንም ፈተና አድርጎታል። በዚህም ምክንያት በፊት ከጥቂት ምንጮች ሞያዊ አካሄድን ተከትለውና ተፈትሸው ለብዙኃኑ የሚሠራጩ መረጃዎች፣ ዛሬ ሁሉም ዜጋ እንደፈለገ አብኵቶና ጋግሮ የሚያከፋፍለው ሆኗል።

የመሬት ላይ ሕይወታችን ወደ ምናባዊ ሕይወታችን ሲቀየር፣ ተሰጥዖና ሞያ ፍለጋችንም ወደዚሁ ዓለም ተቀላቅሏል። ይህ ሁኔታ የጋዜጠኝነት፣ የፖለቲከኝነት፣ የዐዋቂነት፣ ወዘተ. ተሰጥዖ ፍለጋዎች አድራሻቸው በምናባዊው ዓለም እንዲሆን አድርጓል። በተጨማሪም ሰዎች ተሰጥዖ ፍለጋ ለመሄድ ወደ ዕውቀት ቤት ከመጓዝ ይልቅ ወደ በይነ መረብ መጓዝን አማራጭ ጎዳና ካደረጉ ቆየት ብለዋል። ይሄም በለማጆች ደረጃ የሚቀርቡ መረጃዎችና ትንተናዎች የብዙኃኑን አስተሳሰብ እንዲያበላሹና እውነትን እንዲያዛቡ ዕድል ይሰጣል። ዕውቀት፣ ትምህርት፣ ልምድ፣ ሥነ ምግባር የሚባሉ ጉዳዮች ትርጉም አጥተው ፍላጎትና ስሜት ብቻ የጨዋታው ገዥ ሕጎች ይሆናሉ።

ይህ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋትና በተለይም የኢንተርኔትና የማኅበራዊ መገናኛ መምጣት የፈጠረው አዲስ ተለምዶ፣ እውነትንና ምክንያታዊነትን በመያዝ ብቻ የሰውን ሐሳብና ዕይታ መቅረጽ የማይቻልበት ሆኗል። ከሐሳብ ጥራት ይልቅ የሥርጭት ዐቅሙና ስሜት ኮርኳሪነቱ የበለጠ ተጽዕኖ የሚፈጥርበት ዓለም አካል እንድንሆንም አድርጓል። ቦታና ጊዜ የሚባሉ ጉዳዮችን ማጥበቡና ማሳጠሩ ደግሞ የመረጃ ሥርጭቱና የተጽዕኖ አድማሱ እንዲሰፋ አስችሎታል።

ከዚህም አልፎ ሰዎች የዘወትር ጥቃቅን ክሥተቶችን የሚያዩበት አትኳሪ ዕይታ(micro scopic view) እንዲኖራቸው አድርጓል። በፊት በራሱ መንደር ከሚከሠት ነገር ውጭ ሰው መረጃ አይደርሰውም ነበር። አሁን በአራቱም አቅጣጫ፣ በየትኛውም ጠባብ መንደር ውስጥ የሚከሠት ክሥተት፣ በደቂቃዎች ውስጥ ይደርሰዋል።

ይህ የመረጃ ፍጥነት ከሰው አዲስ ነገር የመፈለግ ተፈጥሮ ጋር ሲደመር፣ በደንባራ በቅሎ ቃጭል እንደመጨመር ሆኗል። ትንሿ ነገር ልታገኝ ከሚገባት ትኩረት በላይ ትስባለች። ትንኝ ግመል ታክላለች፤ ብልጭታ ፀሐይ ትመስላለች። ነገሩን በስክነትና በብስለት የሚገመግም ይታጣል። ይሄንን ተንተርሶም ጉዳዩ ተጋንኖ ወደ አልተገባ አቅጣጫ የመሄድ ዝንባሌ ይታያል።

ለምሳሌ ትላልቅ የሕዝብ በዓላት በየቦታው ይካሄዳሉ። ከሺዎች አንዱ ላይ የጸጥታ ችግር ሲፈጠር፣ በአብዛኛው ሰላማዊ የነበረውን ሂደት ትተን፣ ጥቂት ችግር ያለበት ላይ ትኩረታችንን፣ ጊዜያችንንና ሀብታችንን እናባክናለን። በስክነት ካየነው በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች በመልካም ሁኔታ ተከብሯል። ይሄንን ስኬት ከማክበር ይልቅ አንድ ቦታ የሚከሠት ፈተና የጠቅላላው ነገር መገለጫ ሆኖ ይቀርባል።

CS CamScanner

ማኅበራዊ መገናኛ ይሄንን ትንኙን የማተለቅና ግመሉን የማሳነስ ዕይታ ወደ ፖለቲካ ገበያ ያመጣዋል። የፖለቲካ ነጋዴዎችም ይህንኑ ማኅበራዊ መገናኛ በመጠቀም የፖለቲካ ገበያውን ያደሩበታል። ይህ ትንኝ የማተለቅና ግመል የማሳነስ ዕይታ በአሉታዊነት ሲተገበር፣ ከፍጥነታችን የሚገታና የመፍጠር ትኩረታችንን የሚበትን ይሆናል። በምናየው ጥቃቅን ነገር ከተረበሽንና ያገኘነውን ትልቅ ነገር ከዘነጋን፣ "እንዳልተገራ ፈረስ" በትንሽ በትልቁ እንደነብራለን፤ አቅጣጫችንንም እንስታለን። አቅጣጫውን የሳተና ትኩረቱ የተበተነ ኃይል ደግሞ ግቡን አይመታም።

በሌላ በኩል ይህ መረባዊ ዓለም የፈጠረው የሩቅ ዕይታ (Telescopic View) የአዲሱ ዓለም እውነታ ክፍል ነው። ቀድሞ ሰው ሁሉ በአካባቢውና በዙሪያው በሌጣ ዓይኑ የሚያየውን ብቻ፣ ዓለም ነው ብሎ ይቀበል ነበር። ከእርሱ ባሻገር ያለውን ዓለም የሚመለከትበት ዕድሉ ጠባብ ነበረ። መገናኛውንና ተረኩን የሚቆጣጠሩ ኃይላት የሰጡትን ተቀብሎ ይኖር ነበር።

ዛሬ ግን በማኅበራዊ መገናኛና እጁ ላይ ባለው በይነ መረብ አማካኝነት፣ በየትኛውም ዓለም የሚካሄደውንና የተከሠተውን ጉዳይ በፍጥነትና ከተለያዩ ምንጮች የማግኘትና የማገናዘብ አማራጭ አለው። ዝርዝሩ(ማይክሮስኮፒክ) ጉዳይም ሆነ አጠቃላዩ(ቴሌስኮፒክ) ጉዳይ ከቀድሞ ይልቅ በቴክኖሎጂ አማካኝነት እጃችን ይገባል።

በይነ መረብ የፈጠረው አንድ ትልቅ ጉዳይ የሩቅ የሚመስለውን አጀንዳ ከደጃችን አቅርቦ መሣሪያ ማበጀቱን ለእኛ ትቶልናል። መዳፋችን ላይ የገባውን ጥቃቅኑን ነገር አጉልቶ ማምጣቱ ነው። ነገር ግን በዙሪያችን ያለውን መልካምና መጥፎ ጉዳይ የምንለይበት ማጥለያ ማየት፣ የራቀውን እንዲሁም የሚመጣውን መመልከት፣ ለነገሮች መፍትሔ መስጠት፣ ከምናባዊው ዓለም ጋር ራስን አስማምቶ መጓዝ፣ ፈጠራንና ፍጥነትን የሚያስችል ዐቅም ሆኖ መጥቷል።

የፖለቲካ ነጋዴው ሀገረ መንግሥቱን በመጥለፍ፣ የሀገርን የፖለቲካ ሥርዓት ለጥቂት ጥቅመኛ ግለሰቦች ጥቅም የሚያገለግል የንግድ ሥርዓት ሊያደርጉት ይጥራሉ። የግል ጥቅም ጥያቄ እንዲመስል በየማኅበራዊ መገናኛው ያስጮሃሉ። ባስ ሲልም በከተሞች ላይ የሥራ ፍላጎታቸውን በ"የሕዝብ ጥያቄ" ሊሸፍኑት ይሞክራሉ። የራሳቸውን ጥያቄ የማኅበረሰቡ ማቆም አድማ በማድረግ ሰላማዊ ጥያቄውን ወደ ዐመጽ ያሻግራሉ። እነሱ ከግርግሩ ያተርፋሉ። በእነሱ ተመርተው ችግር የሚፈጥሩት ግን ወደ አልተፈለገ እሥርና እንግልት ያመራሉ።

በዘመናዊ የልመና አካሄድ፣ ለማኝና አስለማኝ አሉ። አስለማኞቹ እግራቸው ሆን ተብሎ የቆሰለ ሰዎችን ለልመና ያሠማራሉ። የቁስሉ ዓላማ ገንዘብ ማግኘት ነው። ቅን ሰው ቁስለኛውን እንዲታከም ለማድረግ ቢነሣ ቁስለኛው አይቀበለውም። ምክንያቱም ቁስሉ ገበያ ነው። ሕመም አይደለም። ከቁስሉ ማትረፍ እንጂ ቁስሉን መታከም አይፈልጉም:: ቁስለኛው ቢፈልግ እንኳን ቁስለኛውን ያሠማራው አካል አይፈልግም። የፖለቲካ ገበያ እንደዚህ ነው። ሕጉ፣ ፖሊሲው፣ ልማቱ፣ ውሳኔው ሁሉ ለሕዝብ እንዴት ይጠቅማል ሳይሆን፤ የተዘረጋውን የጥቅመኞች የንግድ ሥርዓት እንዴት ይጠቅማል? ከሚል ብቻ ይቃኛል።

በማኅበረሰብ ዘንድ ነባርና አሁናዊ ችግሮች ይኖራሉ። ማኅበረሰቡ እነዚህን ችግሮች እንዲፈቱለት ሲጠይቅ መሠረት በማያፈርስ መልኩ ነው። ለዚህም ነው በትግርኛ "ምእንታይ ምጎጎ እንጭዋ ትሕልፍ" ፡ ለምጣዱ ሲባል አይጧ ትለፍ፤ በአማርኛ "ቁንጫ አለ ተብሎ ቤት አይቃጠልም" ፤ በኦሮምኛ "Namni mana tokko jjaaru citaa wal hin saamu" "አንድ ቤት የሚከድኑ ሰዎች የቤት መክደኛ ሣር አይሻሙም" የሚሉ አባባሎች ያሉት። ችግሮቹ እንዲፈቱለት ይፈልጋል እንጂ፤ ችግሮቹን እፈታለሁ የሚል አካል ሀገር እንዲያሳጣው አይፈልግም። የፖለቲካ ነጋዴዎች ዓላማ ግን ችግሮቹን እንደ ገንዘብ መጠቀም ነው። ችግሮቹ እንዲፈቱ አይደለም።

CS CamScanner

የለውጡ መንግሥት ከመጀመሪያው ጀምሮ የተከተለው ሁለቱን የመለየት አካሄድ ነው፡ የሕዝቡን ችግሮች መፍታት፣ የፖለቲካ ነጋዴዎችን ችግሮች መርታት። “የወደቀ ሥጋ ባለበት አሞሮች ያንዣብባሉ” ይባላል። ያልተፈቱ የሕዝብ ችግሮች ባሉበት የፖለቲካ በሕዝብ ችግር የሚነግዱትን የፖለቲካ ነጋዴዎች አጀንዳ ያስጥላቸዋል።

የሕዝቡን ችግሮች ለመፍታት የለውጡ መንግሥት የፈጸመው የመጀመሪያው ተግባር ከራሱ ከሕዝቡ አፍ ችግሮቹን መስማት ነው። ለዚህ በመላ ኢትዮጵያ በተደረገው ጉዞ የሕዝብ ወኪሎችን በማግኘት ውይይቶች ተደርገዋል። የአካል ምልከታም ተከናውኗል። ይሄም በብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ፣ በሚኒስትሮች፣ ወዘተ. ደረጃ የተከናወነ ነው።

በመቀጠል የሕዝቡን ችግሮች መለየት ነው። ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን መለየት። በመጨረሻም ወደ መፍትሔ መንገዶች በየደረጃው ተገብቷል። ከችግሮቹ መካከል ወዲያው የሚፈቱትን መፍታት። በዕቅድ መያዝ ያለባቸውን በፌዴራልና በክልሎች ዕቅዶች ውስጥ መያዝ። ሂደታዊ መፍትሔ የሚፈልጉትን ደግሞ ከማኅበረሰቡ ጋር በመግባባት በሂደት እየፈቱ መሄድ።

## 12.5. የውጥረት ፖለቲካ

የዴሞክራሲ ሥርዓት ሽግግር የተቋማት የማስተዳደር ዐቅም መዳበርንና ለፖለቲካ ማኅበረሰቡ አዲስ የባህል ልምምድን የሚጠይቅ ነው። ስለዚህም ወደ ተግባር በሚገባበት ጊዜ በአመዛኙ ውጥረቶች ይፈጠራሉ። አሁን ባለንበት ዘመን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ተደላድሎ ተግባራዊ እንዲሆን፣ በውስጡ የሚይዛቸው ዋና ዋና መርሖች አሉት።

ከእነዚህም ውስጥ በውሳኔ ሰጪነት የዜጎች ተሳትፎ፣ የውክልና ሥርዓት መኖር፣ የሕግ የበላይነት መኖር፣ የምርጫ ሂደት(የብዙኃኑ ሕግ)፣ የዜጎች እኩልነት፣ በዜጎች የሚገኝ ወይም የሚሰጥ ነጻነት እንዲሁም ትምህርት መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ዋና ዋና መርሖች ከላይ ወደታች የሚፈሱ አይደሉም። የጎንዮሽ ውይይትና ክርክር ይፈልጋሉ። አለፍ ሲልም አለመግባባቶች ይስተናገዱባቸዋል። ይሄም የፖለቲካ ሜዳውን ውጥረት እንዲሞላው በር ይከፍታል።

የዴሞክራሲ ስኬት የሚለካው ዜጎች በማኅበረሰቡ ጉዳዮች ላይ በእኩልነትና በመደጋገፍ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለማሥረጽ እጅግ የተዋቀረና ተግባራዊነቱ የማያጠራጥር ተቋም ሠርተው ለጋራ ብልጽግና እውነተኛ አጋርነትን በዙሪያቸው ሲያሰፍኑ ነው። በሌላ አነጋገር ከመብትና ከኃላፊነት ጋር አዋሕዶ መጓዝ ሂደቱን ቀላል ያደርገዋል። የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲኖር ይገባል። እንዲሁም በማኅበረሰቡ ፍቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ ሕጎችና ደንቦችን ሀገራት ከቀድሞ ሥርዓቶቻቸው ወደ ዴሞክራሲ ሥርዓት ሲሸጋገሩ የሚጋፈጡት ውጥረት በተፈጥሮው ኃይል ያልተማከለበት ነው። አንዳንዴም በውጥረት የተሞላ ሥርዓት ነው። ለፖለቲካ ገበያ ምቹ ሁኔታን ለጊዜውም ቢሆን ይፈጥራል።

ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ፤ ነባሩ የጀርመን ንጉሣዊ ሥርዓት ለብዙ ነገር ተወቃሽ ሆነ፤ ንጉሥ ካይሠር ዊልኸለም 2ኛም ከሥልጣኑ ወረደ። ጀርመንም እኢአ በ99 ሪፐብሊክ ሆነች። ኋላ ግን የጀርመን ኢኮኖሚ ድቀትና ማኅበራዊው አለመረጋጋት ሕዝቡን የቀድሞውን ሥርዓት እስከ መናፈቅ አድርሶት ነበር። ዴሞክራሲያዊውን ሥርዓት የመለማመድ ፈተና ነበር። ችግሩን የዴሞክራሲ አድርጎ የመመልከት አዝማሚያም ተከሥቶ ነበር።

በ1930 የተፈጠረው ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውስ ደግሞ ውስጣዊ ችግሩን አባሰው:: ጀርመን በቨርሳይ የሰላም ስምነት መሠረት የተጣለባትን የጦር ዕዳዋን መክፈል አቃታት። ሚልዮን ጀርመናውያን ሥራቸውን አጡ። ፖለቲካው ተቃወሰ። ካቢኔው መሥራት አቃተው። ተደጋጋሚ ምርጫዎች ይካሄዱ ጀመር።

እነዚህ ቀውሶች ሰዎች አንዳች ተአምራዊ ነገር ተስፋ እንዲያደርጉ አደረጓቸው። ሂትለር የተጠቀመው ይሄንን የፖለቲካ ገበያ ነው። ለሀገሪቱ መድኅንና ቤዛ አድርጎ ራሱን አቀረበ። ሕዝቡን በንግግር ደለለው። በደልንና ጭቆናን ያቀነቅን ጀመር።

CamScanner

መጀመሪያ መፈንቅለ መንግሥት ሞከረ። የኢኮኖሚ ቀውሱ ለሂትለርና ለሂትለራውያን ዕድል ሰጣቸው። መንግሥትንና የቨርሳይ ስምምነትን መውቀስ የዘወትር ሥራቸው ሆነ።

ያለፈውን በመውቀስ፣ ዓለም አቀፉን ቀውስ እንደ ሕዝብ ስሜት መቀስቀሻ በመጠቀም ዐቅም እያገኙ መጡ። በመጨረሻም በጃንዋሪ 30፣ 1933 በግፊት ሂትለር ቻንስለር ሆነ። የጀርመን መከራ ያበቃ መስሎ ቢታይም፣ የጀርመን የከፋው መከራ ግን እየጀመረ ነበር። የፖለቲካ ገበያ ሀገርን አሳልፎ ለጽንፈኞች የሚሰጠው በዚህ መንገድ ነው።

ዴሞክራሲያዊ ባልሆኑ ሥርዓቶች ኃይል በአንድ ቦታ ይከማቻል። በአመዛኙ ኮሽታ አይሰማባቸውም። ሁሌም ተመሳሳይ ሐሳብ ይናፈስባቸዋል። አብዛኛው ሰው ተቀራራቢ ሐሳብ የያዘባቸው ይመስላሉ። ዝምታ የነገሠባቸውና በእጅጉ የረጉ ሥርዓቶች ናቸው። ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ ወይም የዴሞክራሲ ልምምድ የሌላቸው ሀገራት፣ ከመሪዎች ጀምሮ እስከታች ማኅበረሰቡ ድረስ በውዴታም ይሁን በግዴታ፣ መሪው የሚያዘውን ያለአንዳች መሸራረፍ ይፈጽማል። ይህ ኢዴሞክራሲያዊ አካሄድ ላይ ላዩን ሰላማዊና አልጋ በአልጋ የሆነ ይመስላል። ዳሩ ግን ውስጡን ስንፈትሸው ከውጥረትም በላይ የዜጎችን መብቶች ጨፍልቆ የያዘ ሆኖ እናገኘዋለን።

በአንጻሩ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የዜጎችን መብት የሚያከብርና ሥልጣን በብዙዎች እጅ የሚወድቅበት ሥርዓት ነው። ፍትጊያ፣ ውጣ ውረድና ውጥረት የሥርዓቱ መለያዎች ናቸው። ፓርቲዎች፣ መገናኛዎች፣ የመብት አቀንቃኞች፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ እንዲሁም ሌሎች ያገባናል የሚሉ እያንዳንዳቸው ያላቸውን መብትና ኃይል ተጠቅመው የተለያዩ ሐሳቦችን ያራምዳሉ። ይህም አለመግባባትና ውጥረት እንዲሰፍን ያደርጋል። ይህንን የዴሞክራሲ ጠባይ ታክከው የግልና

የቡድን ጥቅማቸውን ለማጋበስ ለሚራኮቱ የፖለቲካ ነጋዴዎች፣ ሁኔታው "ሠርግና ምላሽ" ይሆንላቸዋል።

በመንግሥት በኩል ሥልጣን ወደ ሦስቱ የመንግሥት አካላት(ሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ) ይሠራጫል። በፖለቲካ ሥርዓቱ ውስጥ የኃይል ፍሰቱ አንድ አቅጣጫን ብቻ ስለማይከተል ፍትጊያና ውጥረት የተለመደ ነው። በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ፣ በመንግሥት የአስፈጻሚዎች አካሄድ፣ አንዱ ከአንዱ ተናብቦ የሚሠራበት አካሄድ አለ።

አሁን አሁን ግን እነዚህ የመንግሥት አካላት ከዚህ በፊት እንደነበረው አንዱ ያንዱ ታዛዥ መሆኑ እየቀረ ነው። እንዲያውም ለሥራው መሳካት አንዱ አንዱን የሚወቅስበት፣ ብሎም የሚተችበት፣ ባስ ካለም ወደ ፍርድ ተቋማት የሚሄድበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ የዴሞክራሲ ሥርዓቱ የፈጠረው የፖለቲካ ውጥረት፣ ለሐሳብ አልባ ፖለቲካ መጎልመስ አስቻይ ምኅዳር ነው።

የዴሞክራሲ ተቋማት ከአስፈጻሚዎች ጋር፣ አስፈጻሚዎች ከሕግ ተርጓሚዎች ጋር መፋጠጣቸው የተለመደ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ፣ ከዚህ ቀደም የሰብአዊ መብት ኮሚሽንና ዕንባ ጠባቂ ተቋም የሚባሉት የዜጎች መብት አስከባሪ ተቋማት፣ የዴሞክራሲ ተቋማት ቢሆኑም ከስም የዘለለ ተግባር አልነበራቸውም። አሁን ግን መንግሥትን የዜጎችን መብት ጥሰሃል ብለው ፍርድ ቤት እስከማመላለስ ደርሰዋል። ፍርድ ቤቶችም አሁን ላይ ከዚህ ቀደም ከነበረው የበላይ አካል ተግሣጽና ቁጣ ተላቀው፣ የሥራ አስፈጻሚ አካላትን ፍርድ ቤት ያመላልሳሉ። በሥራ አስፈጻሚው ላይ ይፈርዳሉ። በዚህም የገለልተኝነት ጉዟቸውን እያሣለጡ ይገኛሉ።

አስፈጻሚ አካላት እርስ በርሳቸው፣ ሕግ አውጭ አካላት እርስ በርሳቸው፣ ሌሎች ተቋማትም እንዲሁ መታገላቸውና መፋተጋቸው ጤናማና የሰርክ ጉዳይ ነው። "የዘመድ ጥል፣ የሥጋ ትል እንዲሉ። በሀገራችን በአስፈጻሚዎችና በዴሞክራሲ ተቋማት(እንደ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ ምርጫ ቦርድ፣ የዕንባ ጠባቂ ተቋም) መካከል፣ በአስፈጻሚውና በፍርድ ቤት መካከል፣ በተለያዩ አስፈጻሚዎች መካከል፣ ወዘተ. ፍትጊያዎችና ውጥረቶች ታይተዋል።

CS CamScanner

በመገናኛዎች፣ በፖለቲከኞች፣ ማኅበረሰብ አንቂዎች፤ ወዘተ. መካከል የሚፈጠሩ ውጥረቶች የሕዝቡንና የፖለቲከኞችን

ልብ ሲሰቅሉ ታይተዋል። ሐሳብ መወራወር፣ በቶሎ አለመግባባት፣ ክርክር፣ ወዘተ. የአዲሱ ተለምዶ መለያዎች ናቸው። ኃይል በተለያዩ አካላት እጅ የተሠራጨ ነው። ይህ ባመጣው ልማድ በእነዚህ አካላት መካከል የሚኖር ትግልና ፍትጊያ የፖለቲካ ዐውዱን በውጥረትና በመናጥ ይሞላዋል። ሆኖም ይህ መናጥ እንሥራው እስካልተሠበረ ድረስ "ቅቤ ይወጣዋል"

። የዴሞክራሲ ሥርዓት ዋነኛ አመክንዮም ይኼው ነው።

ይሄንን የዴሞክራሲ ጠባይ መነሻ አድርገው ጩኸቶችን፣ አለመግባባቶችንና ፍትጊያዎችን በማጋጋልና በማራገብ፣ ሀገራዊ መታወክ ለመፍጠር የሚራወጡ የፖለቲካ ነጋዴዎች አሉ። ሕዝቡ አልተቀበላቸውም እንጂ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነባር

ጠባይ አለው:: ማናቸውም ነገር ሀገር እንዲያፈርስ አይፈቅድም። ጨቁነውኛል በድለውኛል ያላቸውን መሪዎች እንኳን ከውጭ ጠላት ጋር ሲዋጉ ይደግፋቸዋል። አካባቢያዊችግር የሀገርን ምሰሶ እስከማፍረስ እንዲደርስ አይፈቅድም። ሀገር በችግር ውስጥ መሆንዋን ካወቀ ይታገሣል። "ወንዝ እየተሻገሩ ፈረስ አይቀየርም" ይላል።

የፖለቲካ ነጋዴዎች በዴሞክራሲ ሽግግር ውስጥ የሚፈጠርን ውጥረት በዲጂታል መገናኛው አባዝቶ በማቅረብ፣ ለፖለቲካ ገበያ መድራት ያውሉታል። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ የዴሞክራሲ ሂደትን በመረዳት፣ የሚፈጠሩ ውጥረቶችን አርግቦ፣ ዴሞክራሲውን ተቋማዊ መሠረት ስለማስያዝ አያስብም። ይባስ ብሎ የውጥረት ስስ ብልቶችን ፈልጎ፣ የግልና የቡድን ጥቅሞችን የሚቀራመትበት የፖለቲካ ገበያ እንዲደራ ያደርጋል። በእሳት ላይ ቤንዚን፣ በቁስል ላይ ሆምጣጤ ይጨምራል።

በዴሞክራሲ ሽግግር በሚፈጠር ውጥረት፣ የፖለቲካ ነጋዴዎች የመንግሥት የቁጥጥር ኃይል ተዳክሞ እንዲቆይ ይፈልጋሉ። በእንጻሩ በውጥረቱና በፖለቲካ ነጋዴዎች ግፊት መንግሥት ይፈተናል። ሕዝቡ በፍትጊያው ይሸበራል። በዚህ የተነሣ ወደኋላ የመመለስ ዳርዳርታና ናፍቆት ይታይባቸዋል። ብዙ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጅማሮዎች የተቀለበሱት ይህንን የዴሞክራሲ አዲስ ጠባይ አስቀድመው ባለመገንዘባቸውና ዴሞክራሲ በሚፈጥረው ውጥረት አየር በመረበሻቸው ነው ።

ስለዚህም ውጥረቱን ለማርገብ በአሮጌ ዘዴዎች፣ ማለትም ያልተመጣጠነ የኃይል ርምጃዎች(እሥር፣ እንግልት፣ ግድያ፣

ፍርሃት) መጠቀም ያስፈልጋል የሚሉ ድምጾች በረታሉ። ይሁን እንጂ እንደዚህ ያሉ የአፈና ርምጃዎች ለሐሳብ አልባ ፖለቲካው አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራሉ። ሐሳብ አልባ ፖለቲካን በዴሞክራሲ ምኅዳር መታገል የሚቻለው፣ አንድም ሐሳብ አልባ መሆናቸውን ማኅበረሰቡ እንዲያውቅ ዕድል በመስጠት ነው። አንድም ከመሥመር አልፎ ለሀገር አደጋ በሚሆኑበት ጊዜ የሕግ የበላይነትን በማረጋገጥ ነው።

የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚፈጥረው የፖለቲካ ውጥረት ላይ፤ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስፋፋት ታክሎበታል። የሁለቱ ቅንጅት ደግሞ ለፖለቲካ ገበያ የበለጠ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። በአንድ በኩል የዴሞክራሲ ሥርዓት ያልተማከለ ኃይል የሚጠይቅ ነው። ወይም ኃይል በተለያዩ አካላት እጅ እንዲሠራጭ ይፈልጋል። በሌላ በኩል ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂው ለእነዚህ የተለያዩ አካላት የመገናኛ ዐቅምን ይፈጥርላቸዋል። ይህ ደግሞ በበኩሉ ኃይል እጅጉን ያልተማከለበት ሁኔታን ስለሚፈጥር፣ ለፖለቲካ ገበያው አስቻይ ይሆናል።

ረዘም ላለ ጊዜ የኢትዮጵያ ችግር ሆኖ የዘለቀው ጽንፈኝነት ነው። ጽንፈኝነት ከፖለቲካ ገበያ ጋር ሲገናኝ፣ አሁን ያለውን የኢትዮጵያ ፖለቲካን ፈጥሯል። የፖለቲካ ገበያ ለጽንፈኝነት ለም መሬት ማለት ነው። በቀደመው ጊዜ ጽንፈኝነት በመሣሪያ አገዛዝ ድምጹን አጥፍቶ ይኖር ነበር። አሁን ግን ዴሞክራሲ የፈጠረለትን ምቹ ሁኔታና ማኅበራዊ መገናኛ የሚሰጠውን የመረጃ ጉልበት በመጠቀም፣ የፖለቲካ ገበያውን የማድራት ዕድል አግኝቷል።

## **12.6.** ያልነጠፈ ንዋይ

CS CamScanner

ባለፉት ሁለት ዐሠርት ዓመታት በሀገራችን ከኢኮኖሚ ዕድገት ባላነሰ ያደገው ሌብነት ነው። የተነሣ ሌብነት በደረቱ ከመሳብ ወጥቶ በራሪ ዘንዶ ሆኗል። ዕድገቱ ደረጃ በደረጃ ወደ ቡድናዊ የኢኮኖሚ የበላይነት ለፖለቲካ ኃይል የበላይነት እንደ ዋስትና ተቆጥሯል። ሥርዓትነት ተቀየረ። ተቋማትም ዋና ሥራቸውን ዘነጉ። ፉክክሩ ማን ከማን የበለጠ ሰረቀ መደበቂያ

የቀማኞች ዋሻ ሆኑ። የልማታዊ መንግሥት መርሕ ተገርሥሦ፣ የግሉ ዘርፍና ከማን ጋር ብንሆን የበለጠ እንሰርቃለን? የሚል ሆነ። መንግሥታዊ መዋቅሮች የመንግሥት ሥርዓት በአንድ አግዳሚ ወንበር ተቀመጡ። የፋይናንስ ተቋማት ተሟጠጡ። የተፈጥሮ ሀብቶች በብላሽ ተዛቁ። የጸጥታና የደኅንነት ተቋማት ወደ ኮንትሮባዲስትነት ተቀየሩ።

በዚህ አዲስ ልምምድ የሥርዓት ጠባቂ ባለ ሀብትና በሥርዓቱ ተጠቅሞ የሚዘርፍ ስም ያልወጣለት አዲስ ኃይል ከጥቁሩ መጋረጃ ጀርባ ሆኖ መሥራት ጀመረ። እንታደስ ብለው የጮኹ ጩኸታቸው "የቁራ ጩኸት" ሆኖ ተቆጠረ። የተቃውሞ ድምፆች በድብቅ አፋኞች ተዘጉ። በሌብነት ያበጠው ሥርዓት ሥጋቱ ወደ አምባገነንነት ቀየረው። ሥልጣንና ሀብት መሥመር ተላለፉ። ሀብታምን ከባለ ሥልጣን፤ ባለ ሥልጣንን ከሀብታም መለየት አዳጋች ሆነ። ሥርዓቱ ኦሊጋርኪዎችን ፈጠረ። ሁለቱ የማይነጣጠሉ አንድ አካል ሆነው ሥርዓቱን ይዘውሩት ጀመር።

እነዚህ ኃይሎች ፍርሃታቸው የፈጠረው አፈና ገንፍሎ እንደደራሽ ከመድረኩ አወረዳቸው:: ሥልጣን ቢያጡም ገንዘባቸውን ይዘው ቀጠሉ። የገንዘብ ዐቅማቸውንና የቆየ መረባቸውን ተጠቅመው፣ እነዚህ ኃይሎች የፖለቲካ ገበያውን በተደራጀ ዐቅም አስጀመሩት። በፋይናንስ፣ በስለላና በአጀንዳ ድጋፍ የሚደረግለት ፖለቲካዊ ግርግርና ሁከት ተቀጣጠለ። በዚህም መንገድ የፖለቲካ ገበያውን ለኮሱት።

የተፈጠረው አዲስ ኃይል አንድ መደበኛ የፖለቲካ ኃይል ያለውን ኃይል ያክል በቀጥታና በተዘዋዋሪ መጠቀም ጀመረ። ይህንን ኃይል ተጠቅሞ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ፍላጎቱን ለማሳካት ግድግዳ ይቧጥጣል። ይህ ኃይል በሀገረ መንግሥት ሥርዓት ውስጥ ካለው የቅርብ ትዝታ የሀገሪቱን ዋና ዋና የቅራኔ ምንጮች ያውቃል። እነዚህን ቅራኔዎች በመነካካትና በመፍጠር፣ በሀገሪቱ የፖለቲካ ገበያ ቀንደኛ ተዋናይ ሆኖ ወጥቷል።

እንዲሁ መታገላቸውና መፋተጋቸው ጤናማና የሰርክ ጉዳይ ነው። "የዘመድ ጥል፣ የሥጋ አስፈጻሚ አካላት እርስ በርሳቸው፣ ሕግ አውጭ አካላት እርስ በርሳቸው፣ ሌሎች ተቋማትም ትል" እንዲሉ። በሀገራችን በአስፈጻሚዎችና በዴሞክራሲ ተቋማት(እንደ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ ምርጫ ቦርድ፣ የዕንባ ጠባቂ ተቋም) መካከል፣ በአስፈጻሚውና በፍርድ ቤት መካከል፣ በተለያዩ አስፈጻሚዎች መካከል፣ ወዘተ. ፍትጊያዎችና ውጥረቶች ታይተዋል። በመገናኛዎች፣

CamScanner

በፖለቲከኞች፣ ማኅበረሰብ አንቂዎች፤ ወዘተ. መካከል የሚፈጠሩ ውጥረቶች የሕዝቡንና የፖለቲከኞችን ልብ ሲሰቅሉ

ታይተዋል። ሐሳብ መወራወር፣ በቶሎ አለመግባባት፣ ክርክር፣ ወዘተ. የአዲሱ ተለምዶ መለያዎች ናቸው። ኃይል በተለያዩ አካላት እጅ የተሠራጨ ነው። ይህ ባመጣው ልማድ በእነዚህ አካላት መካከል የሚኖር ትግልና ፍትጊያ የፖለቲካ ዐውዱን በውጥረትና በመናጥ ይሞላዋል። ሆኖም ይህ መናጥ እንሥራው እስካልተሠበረ ድረስ "ቅቤ ይወጣዋል" ። የዴሞክራሲ ሥርዓት ዋነኛ አመክንዮም ይኼው ነው።

።

ይሄንን የዴሞክራሲ ጠባይ መነሻ አድርገው ጩኸቶችን፣ አለመግባባቶችንና ፍትጊያዎችን በማጋጋልና በማራገብ፣ ሀገራዊ መታወክ ለመፍጠር የሚራወጡ የፖለቲካ ነጋዴዎች አሉ። ሕዝቡ አልተቀበላቸውም እንጂ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ነባር ጠባይ አለው። ማናቸውም ነገር ሀገር እንዲያፈርስ አይፈቅድም። ጨቁነውኛል በድለውኛል ያላቸውን መሪዎች እንኳን ከውጭ ጠላት ጋር ሲዋጉ ይደግፋቸዋል። አካባቢያዊችግር የሀገርን ምሰሶ እስከማፍረስ እንዲደርስ አይፈቅድም። ሀገር

በችግር ውስጥ መሆንዋን ካወቀ ይታገሣል። "ወንዝ እየተሻገሩ ፈረስ አይቀየርም" ይላል።

የፖለቲካ ነጋዴዎች በዴሞክራሲ ሽግግር ውስጥ የሚፈጠርን ውጥረት በዲጂታል መገናኛው አባዝቶ በማቅረብ፣ ለፖለቲካ ገበያ መድራት ያውሉታል። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ የዴሞክራሲ ሂደትን በመረዳት፣ የሚፈጠሩ ውጥረቶችን አርግቦ፣ ዴሞክራሲውን ተቋማዊ መሠረት ስለማስያዝ አያስብም። ይባስ ብሎ የውጥረት ስስ ብልቶችን ፈልጎ፣ የግልና የቡድን ጥቅሞችን የሚቀራመትበት የፖለቲካ ገበያ እንዲደራ ያደርጋል። በእሳት ላይ ቤንዚን፣ በቁስል ላይ ሆምጣጤ ይጨምራል።

በዴሞክራሲ ሽግግር በሚፈጠር ውጥረት፣ የፖለቲካ ነጋዴዎች የመንግሥት የቁጥጥር ኃይል ተዳክሞ እንዲቆይ ይፈልጋሉ። በአንጻሩ በውጥረቱና በፖለቲካ ነጋዴዎች ግፊት መንግሥት ይፈተናል። ሕዝቡ በፍትጊያው ይሸበራል። በዚህ የተነሣ ወደኋላ የመመለስ ዳርዳርታና ናፍቆት ይታይባቸዋል። ብዙ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጅማሮዎች የተቀለበሱት ይህንን



ኦሊጋርኪዎች በኃይል፣ በዘር ሐረግ አልያም በሃይማኖት ጠገግ፣ እንዲሁም በአንዳንች አጋጣሚ የመንግሥትን ሥልጣን ይይዙ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የመጡበትን ቡድን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ለመጥቀም ጥረት ያደርጋሉ። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ የሀገሪቱን የመንግሥት ሥርዓት በቡድን በመዝረፍ በሀብት መክበር ይጀምራሉ።

በሥርዓቱ ምክንያት የከበረው የሀብት ምንጫቸው እንዳይደርቅ መሪዎቹም ዘመናቸው እንዳያጥር አፋኝ ሥርዓት ይዘረጋሉ። ኦሊጋርኪዎች ለሥርዓቱ ታማኞች ናቸው። ሥርዓቱም ታማኞቹን ይጠብቃል። ሥርዓቱን በመቆጣጠር የሚገኝ በውድድርና በትብብር ያልተመራ በመሆኑ፣ ለአዲስ ፈጠራና ሥራ ክፍት አይደለም።

ሀብት በፍትፍት መልክ የሚቀርብለት ኦሊጋርኪ፣ መሰብሰብና መዋጥ እንጂ ለአዲስ ሥራና የፈጠራ ትግል ለመነሣት አይዳዳውም። ሠርቶ ካለመብላት የከፋው ደግሞ በሚሠሩ፣ በሚለፉ፣ በሚሮጡና በሚፈጥሩ ለፍቶና አሰላስሎ አደሮች ላይ የሚደረድሩት መሰናክል ነው። የሀገርና የማኅበረሰብን ሀብት በግል መሰብሰብና ሰፊውን ሕዝብ እያራቆቱ ተስፋ ማስቆረጥ መገለጫቸው ነው። በዚህ የተነሣ ማኅበረሰባዊ ቅራኔ ይፈጠራል። ማኅበረሰባዊ ቅራኔ ለውጥ የማዋለድ ኃይል እንዳለው ሁሉ፣ ለፖለቲካ ገበያውም ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

CamScanner

## 12.7. የሐሳብ አልባ ፖለቲካ ምርኩዞች

የፖለቲካ ገበያ ተዋንያን ወደ ፖለቲካ ሜዳው የሚገቡባቸው የተለያዩ ምርኩዞች አሏቸው። እነዚህ ኃይላት በዋናነት ማንነት፣ ገንዘብና ኃይልን በመጠቀም ሀብትና ሥልጣን ለመቀራመት የሚሠሩ ናቸው። ጽንፈኝነት፣ ሕዝበኝነት፣ ዐመጽና የጥቅም ትሥሥሮች መገለጫቸው ናቸው።

### 12.7.1. የጥቅም ትሥሥር

ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ምኅዳርን በተዋንያኑ ማንነት ብንመለከተው ሦስት ኃይሎች በቋሚነት ያቆሙታል። እነዚህም፥ የፖለቲካ ነጋዴዎቹ፣ ባለሀብቱና የፖለቲካ ነጋዴው ሕዝባዊ መሠረቴ የሚላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ናቸው። እንደተገለጸው እነዚህ ሦስት አካላት ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ምኅዳርን ለማቆም በቂ ናቸው። ነገር ግን የእነዚህ ተዋንያን ቅንጅት የሚፈጥረው የፖለቲካ ስልት የተለያዩ ንዑሳን ኃይሎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል።

የእነዚህ ተዋንያን ቅንጅት፣ የታጠቀ ኃይል፡ ሓከት ግርግርና አድማ የሚመራ ኃይል፤ የፕሮፓጋንዳ ኃይል፤ ሠርጎ ገብ ኃይልና የመሳሰሉ ንዑ ሳን ኃይሎችን ይፈጥራሉ። በዚህም ፖለቲካ ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር ይሠራሉ። በእነዚህ ሦስት ኃይሎችና በቅንጅታቸው የሚፈጠሩ ንዑሳን ኃይሎች አሉ። በመሐል ግን የፖለቲካ ገበያውን በመምራት የፖለቲካ ኢኮኖሚውን ጠቅልሎ የሚወስድ አንድ ቡድን ይወጣል።

እነዚህ ኃይሎች የእርስ በእርስ ጦርነት፣ የሃይማኖት ግጭትና ጥቃት፣ ማኅበረሰባዊመድሎና ገለል እየፈጠሩ አገናኝ ድልድዮችን ይሰብራሉ። አስተሣሣሪ ክሮችን ይበጣጥሳሉ። ማኅበረሰቦች በእነርሱ የተነሣ በአንድ ጣሪያ ማደር የማይችሉ "ዓይንና ናጫ ይሆናሉ። በዚህ ሂደት የፖለቲካ ምኅዳሩ በበዳይና ተበዳይ፣ በጎጂና ተጎጂ፣ በተገፋና በታቀፈ፣ ወዘተ. ተቃራኒ ምንታዌዎች ይገፋል። በዚህ ግፊት የተነሣም የፖለቲካ ምኅዳሩ የጡዘት ደረጃ ከፍ ይላል። በሐሳብ አልባ ፖለቲካ ከአንድ ወደ ሁለት የተለወጡ ሀገራት ትናንትን "እኛና እነርሱ" ብለው ከፍለውት ነበር። ዛሬም በራሳቸው መካከል "እኛና እነርሱ" በሚል ሌላ የፖለቲካ ገበያ አዙሪት ውስጥ ገብተዋል።

በአንድ ሀገር የፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ደረጃ ወይም አሁናዊ ሁኔታ ለመበየን፣ አሁን ካለበት እውነታ ባሻገር መነሻ ምንጮቹን መመርመር ያስፈልጋል። ዛሬ የሚሆነው ከትናንት ብቻ የመጣ አይደለም። አልያም ዛሬ ብቻ የወለደው ሊሆን የሚችልበት የተለየ መሥመር የለውም። ይልቁንም ከትናንት ስቦ፣ በዛሬ አቀጣጥሎ በሚፈጠር የፖለቲካ ሤራ የሀገራትና የዜጎች ነገ ይፈተናል።

አንድ ሀገርነት ችግራችን ነው ብለው ወደሁለት የመጡ ሀገራት አሉ። ሁለትነት ግን ከአዙሪቱ አላወጣቸውም። በአንድ ሀገር የነበረው ችግር በሁለት ሀገር ነው የቀጠለው። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ የታሪክ፣ የፖለቲካ፣ የሃይማኖት፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቅሬታዎችን ከትናንት ስቦ ያመጣል። በዘመናዊ መሣሪያዎች ኃይል ደግሞ ዛሬ ላይ ያቀጣጥላቸዋል።

ሐሳብ አልባ ፖለቲካ ትናንትን ከዛሬ በትርክትና በመሣሪያ ያቀናጃል። ፍረጃን ከአሁን ጋር አጣምሮ በማውጣት እኛና እነርሱ በሚል ሁለትና ከሁለት በላይ በሚሆኑ ንዑሳን ቡድኖች መካከል ውጥረት ያነግሣል። ቅራኔዎችን በመሳብ እንደመሻታቸው እየተረጎሙ የፖለቲካ መነገጃ ዲናር ያደርጉታል። ሰውና ዲናርን በአንድ ገጽ አድርገው ለገበያ ያቀርባሉ።

"የእነርሱ" የሚሉትን ሰው ለፖለቲካ ዕብደት በጭዳነት ገብረው ዲናራቸውን ይሰበስባሉ። የእኔ ለሚሉት ሰው ጠባቂ መልአክ ይሆናሉ። በዚህም የመነገጃ ዲናሩን ለበለጠ ትርፍ ያሰባስቡታል።

ሐሳብ አልባ ፖለቲካ የሕዝቡን "በደል" በቁጭትና በእልህ ያፋፍማል። ስለትናንት እያላሰበ ነጋዴው በሚፈልገው ሰዓት ያቀጣጠለውን እሳት ማጥፋት አይቻለውም። በቅራኔ ክብረት ሩጫ ውስጥ መቆም በፈለጉበት ቅጽበት ለመቆም አይቻልም።

CS CamScanner

በፖለቲካ ንግድም የፖለቲካ ነገውን ይነጥቀዋል። በዚህም የፖለቲካ ምኅዳሩን የቁልቁልት ሩጫ ያደርገዋል። በቁልቁለት የተለኮሰ የፖለቲካ ንግድ እየተቀጣጠለ መቆሚያው የት እንደሆነ መሪውም ተከታዩም አያውቁትም። ለትርፍ ያቀጣጠለው እሳት ራሱን ይበላዋል።

ሐሳብ አልባ ፖለቲካ ቅሬታን ከማከም ይልቅ ተያያዥ ቅሬታዎችን ያባዛል። ቅሬታዎቹንምበአንድነት የማይኖሩ ተጠፋፊ ኃይሎች አድርጎ ያፋፍማል። በአንድ ሀገር የፖለቲካ ምኅዳር የተሠመሩ ብዙ ቀይ መሥመሮች እንዲበዙ ያደርጋል። አትድረስብን የሚል ቅሬታ እየጎመራ ቀዩ መሥመር በእሳት ዛንጅር ይታጠራል። መሥመሩን አልፎ ለመጣ በነበልባል እንዲወረስ ይፈረድበታል። በነበልባል ከታጠረው መሥመር የወጣ በአርዮስነት ይፈረጃል። መሥመሩን ያለፈው ሰው፣ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለው ሕይወት ከባሕር እንደ ወጣ ዓሣ ይሆናል። የፖለቲካ ነጋዴዎች ቅሬታን በዚህ መልክ እያቀጣጠሉ፣ ተፋላሚና ተገዳዳሪ ኃይል ማብዛትን የመጀመሪያ ደረጃ ግባቸው አድርገው ይነሣሉ።

በቅሬታ ያበጠ ተቀጣጣይ ኃይል መፈጠሩ ሲታመን፣ በእኛና በእነርሱ መካከል ለማይቀረው ፍልሚያ ለመዘጋጀት ወደ ኃይል ማብዛት ደረጃ ያድጋል። የኃይል ማብዛት ፍላጎት ግቡ ከተገዳዳሪ የበለጠ ኃይል ማግኘት ነው። ተገዳዳሪን ማስከንዳት ነው ስልቱ። በኃይልና በነውጥ የሚመራው ሐሳብ አልባ ፖለቲካ፣ በዚህ ዓይነት ስልት የፖለቲካ ምኅዳሩን ያቀጣጥላል። በኢኮኖሚና በፖለቲካ ውስጥ ከዐቅም በላይ ድርሻ ለመያዝም ይጋጋጣል።

ሐሳብ አልባ ፖለቲካ፣ ከባላንጣዎቹ በልጦ በፖለቲካ ምኅዳሩ የአጥቂ ቦታ ለመያዝ፣ ብሎም በቅሬታ የተሰባሰበውን ኃይል ለማብዛት፣ የውስጥና የውጭ አጋር ይፈልጋል። "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" በሚል መርሕ እየተመራ ከውስጥም ከውጭም ሐሳብ አልባ ኃይል ያሰባስባል። ከውስጥ ቅሬታን አባብሶ ኃይል ለማሰባሰብ አራት መንገዶችን ይጠቀማል፥ በሀገረ መንግሥቱ የተፈጠሩ ፈተናዎችን፤ አንድ ሕዝብ በሌላ ሕዝብ ላይ ፈጥሮታል ብሎ የሚነዛውን በደል፤ በአንድ ሕዝብ መካከል ያሉ ንዑሳን ማንነቶችን በቅሬታ ማነሣሣት፤ እና በአንድ ማኅበረሰብ መካከል ተጠቃሚና ተጎጂ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ፣ ገዥና ተገዥ፣ ዓይነት መደቦችን በመፍጠር። ከዚህ ባለፈ በተስፋና በገንዘብ እየተሳቡ እንዲቀላቀሉ የሚጋበዙ ኃይሎች ይኖራሉ። ከሀገር ውጭ ደግሞ በሦስት መንገዶች አጋር ይገዛል፥ በሀገር ጥቅም ላይ ቆምሮ አጋር በመፈለግ፤ የሎጅስቲክስና የፖለቲካ ሽፋን የሚሰጥ ኃይልን በመሳብና በማብዛት፤ እንዲሁም በባንዳነት ለውጭ ኃይል በማገልገል።

በቅራኔ ተሰባስቦ በአጋር አይዞህ ባይነት የበዛው ኃይል ወደ ቀጣይ ሦስተኛው የዕድገት መረጃ በማደግ፣ በሐሳብ አልባ ፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ አስቻይ ዐቅሞችን ወደ መዘርጋት ይሻገራል። የተቀጣጠለውንና የበዛውን ኃይል በሥርዓት ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ዐቅም ለማጎልበት አስቻይ መደላድሎችን መዘርጋትና ማሣለጥን ግብ አድርጎ ይሠራል። ይህንን ግብ ለማሳካት በዚህ ደረጃ ሁለት መሠረታዊ እንቅስቃሴዎች ይታያሉ። የመጀመሪያው መዋቅራዊ ግልጽና ኅቡዕ መዋቅሮች ናቸው። ሁለተኛው ደግሞ ገንዘብ ነው።

መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው በአንድ ቁልፍ መላ ሥርዓቱን ለማንቀሳቀስ አልሞ ይሠራል።የፖለቲካ ንግዱን ወደ ቀጣይ ደረጃ ለማሳደግ ይገፋል። በቅሬታ የጋመ ኃይል በማብዛት፣ የተቀባበለውን የፖለቲካ ኃይል ወደ ተግባራዊ ድርጊት የሚመራ ደረጃ ለማሳደግ ጥረት ያደርጋል። እነዚህን ደረጃዎች ማለፍ በፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ ጎልተው እንዲወጡ ስለሚያደርጋቸው፣ የብዙዎች የፖለቲካ ነጋዴዎች ሩጫ እዚህ ጋር ጎልቶ ይታያል።

አስቻይ ዐቅም መፈጠሩ ሲረጋገጥ በፖለቲካ ምኅዳሩ ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚያስችል ስልት ይነድፋሉ። ከዚያም በሥርዓቱ ውስጥና በተቃራኒያቸው ንዑስ ቡድን ውስጥ መሥረግ ይጀምራሉ። በዚህ ደረጃ ዐመጽና ረብሻን በተለያዩ ስልቶች ይመራሉ። ከዚያም የኢኮኖሚ ውንብድና፣ ሽብር፣ መሠረተ ልማት ማውደምና የመሳሰሉትን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያውኩ ተግባራትን መፈጸም ይቀጥላሉ። በዚህም በሕዝቡ ላይ ሥነ ልቡናዊ ጫናዎችን መፍጠርን አጠናክረው ይቀጥላሉ።

CamScanner

የተነደፉ ስልቶች ከላይ በተመለከትናቸው አደረጃጀቶች እየተመሩ በማኅበራዊ መገናኛው ይቀጣጠላሉ። በድኅረ እውነት ዘመን መገናኛው የሥርዓትን ኃይል ለሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች ከፍሎ በመስጠት የመንግሥትን ኃይል አጋርቷቸዋል። ይህንን ኃይል በአንጻራዊ ዕድል በመጠቀም ከዐቅማቸው በላይ ገዝፈው ለመታየት ይሞክራሉ። በዚህም በተቃራኒ ኃይል ላይ ሥነ ልቡናዊ ጫና ለማሳደር ይራወጣሉ።

በስልት በተነደፉ እንቅስቃሴዎች እየተመሩ ሥርዓትና ማኅበረሰብን ውዥንብር ውስጥ መክተትን ከአራተኛው ደረጃ ጋር አስታከው ያራምዳሉ። በጸጥታና በደኅንነት ተቋማት፣ በኢኮኖሚ አመንጪ ተቋማት፣ በዴሞክራሲና በሰብአዊ መብት

ተቋማት፣ በተቃራኒ ኃይል(ፓርቲ) ውስጥ ሠርጎ መግባት ዋናው ትኩረታቸው ነው። ሠርጎ ገብነቱ በእስስትነት ተጀምሮ በውስጥ የተለየ ኃይል ሆኖ ለመውጣት ይሞክራል። ከውጭ እየተናበበ ከውስጥ በተገኙ ስንጥቆች ውስጥ ሽብልቅ ያስገባል። ከዚያም የኃይል መሰንጠቅና መከፋፈል ይፈጥራል። በመጨረሻም ሠርጎ የገባው ኃይል ተቋም አፍርሶ አንድ ሌላ ኃይል ሆኖ ይወጣል።

ሠርጎ ገቡ ኃይል በተልዕኮ ፈጻሚ አካላት ውስጥ ገብቶ የተልዕኮ ትኩረት እንዲያጡ ያደርጋቸዋል። ለዚህም የተሳሳተ ዒላማ ይፈጥራል። በየተቋማቱ የሽብር ወሬ ይዛሉ። ከተቋማት መረጃ ያስፈተልካሉ።የመረጃ መሣሪያዎችን ትክክለኛነት ያዛባሉ። በዚህም የጸጥታና የደኅንነት ተቋማትን የማድረግ ዐቅም ያዳክማሉ። የመንግሥትን መርሐ ግብሮች በቢሮክራሲ

ያደናቅፉሉ። ሕዝብ እንዲማረር ካደረጉ በኋላ መልሰው "እኛ ምን እናድርግ፣ ታዝዘን ነው" ይላሉ። ከውጭና ከውስጥ በተነደፈ ስልታዊ ዕቅድና ተግባር የኃይል ሚዛን እስኪዛባላቸው ድረስ በዚህ ሁኔታ ተሠወረው ይቆያሉ።

የኃይል መዛባት መፈጠሩን ሲያረጋግጡ፣ አልያም የመገዳደር ዐቅም አለን : ብለው መጀመሪያ የሆነው ደረጃ ቀጣይነት ያለው ኃይል የታከለበት ዐመጽን ከሰላማዊ መንገድ ጋር በሚያስቡበት ጊዜ፣ የፖለቲካ ንግዱ ወደ ቀጣዩ አምስተኛ ደረጃ ያድጋል። የመጨረሻው እየደበላለቁ የሚመሩበት ነው። እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ከአንድ ማዘዣ ጣቢያ የሚመራ የታቀደ ዐመጽ ይከፍታሉ። ከላይ ባሉት ደረጃዎች ይታይ የነበረው ዐመጽና ጥያቄ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርሱ ይቀየራል።

ቀድሞ የዳቦ ጥያቄ ነበረ። አልያም ከፍ ቢል ፍትሕ ይስፈንልን የሚል ጥያቄ ነበር። አሁን በአምስተኛው ደረጃ ጥያቄው ድንገት ይታጠፍና የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ ይነሣል:: ጊዜያዊ መንግሥት መመሥረት፣ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም፣

የመንግሥትን ሥርዓት የሚነጥቅ ኃይል ማደራጀት፣ እየተሰበሰቡ "መንግሥት የለም" የሚል መግለጫ ማውጣት ይጀምራሉ። ያልታጠቁና የታጠቁ ኃይሎች ተደባልቀው የጸጥታ አካላትን ይፈትናሉ። በወጣቶች፣ በሴቶችና በሕፃናት ተከልለው ተኩሰው ይገድላሉ። እዚያው ገድለው እዚያው ይደበቃሉ።

እንዲህ እየሆነ ዐመጸንና ደም ማፍሰስን ልምድ ያደረገው ኃይል፣ ሥርዓቱን ሙሉ በሙሉ አልያም በከፊል የመያዝና የመጋራት ዕድል በእጁ ከገባ አዲስ የፖለቲካ ገበያ ምዕራፍ ይከፍታል። የሀገሪቱን የፖለቲካ ኢኮኖሚ አውታሮች በመጠቀም፣ የፖለቲካ ገበያ ሌላኛውን ገጽ ያቀጣጥላል።

ወደ ታቀደ ዐመጽ ደረጃ ላይ የደረሰ የፖለቲካ ንግድ፣ ከተቀለበሰ ሁለት ዕጣ ፋንታዎች ይኖሩታል። አንድም ከፖለቲካ ምኅዳሩ ተኖ ይጠፋል። አለያም በዱር በገደል ከትሞ አክራሪ ኃይሎችን ማደራጀትና ማሠልጠን ሥራው ይሆናል። የሐሳብ አልባ ፖለቲካ የመጨረሻ የዕድገት ደረጃ ጽንፈኛ ኃይል በመፍጠር በዐማጺነት መንቀሳቀስ ነው። ዐማጺዎች ምንም ያህል ድጋፍ ቢያገኙ ሥርዓትን የሚገዳደር የጦር ኃይል ማንቀሳቀስ አይችሉም። ስለዚህም ወደ አሸባሪነት ይቀየራሉ። በዐመጽና በሽብር ገፍተው ግባቸውን

CamScanner

እንዳይመቱ ዐቅም እያነሳቸው ይመጣል። ጥለው እንዳይወጡ የደም ዋጋ ያናውዛቸዋል። ተስፋ በመቁረጥ ሁሉን አጥፍቶ መጥፋት መጨረሻቸው ይሆናል።

### 12.7.2. ጽንፈኝነት

ጽንፈኝነት ማለት የማኅበረሰብን መሠረታዊ ዕሴቶችና መርሖች የማይቀበል የፖለቲካ የሚያቀነቅን፣ እና/ ወይም የዴሞክራሲ መሠረታዊ መርሖችንና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ ርዕዮተ ዓለም ነው። በሊበራል ዴሞክራሲ ዕይታ፣ የዘር ወይም የሃይማኖት የበላይነትን መብት ድንጋጌዎችን የማይቀበል አካል ጽንፈኛ ይባላል። የቃሉ ትርጉም፣ የፖለቲካ ተዋንያን ዓላማቸውን ለማሳካት ሲሉ የሌሎችን ሰዎች ሕይወት፣ ነጻነትና ሰብአዊ መብት ዝቅ በማድረግ የሚሄዱበትን አሠራርም ይጨምራል።

ጽንፈኝነት ማለት አክራሪነት ሲጎለምስ የምናገኘው መልክ ነው። ዳር የወጣ ወይም ጽንፍ የያዘ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ተመሳሳይ አቋሞችን መያዝ ወይም ማንጸባረቅ ማለት ነው። በተጨማሪም ጽንፈኝነት ማለት የራስ ብሔር፣ ሃይማኖት ወይም ፖለቲካዊ ርእዮት ላይ ተመሥርቶ፣ ከሌላው የበላይ ሆኖ መታየት፣ ወይም የበላይነት መረጋገጥ አለበት የሚል ጠባብ ፍላጎትና ይህንኑ ለማስፈጸም የኃይል መንገድን መከተል ነው። ጽንፈኝነት ተምረነው እንጂ አብሮን የተፈጠረ አይደለም። ለዚህም ፈርጀ ብዙ መነሻ ምክንያቶችና መገለጫዎች አሉት። በዓለም ዙሪያም ሆነ በሀገራችን በየዘመኑ ሲስተዋሉ የቆዩትን እንደ ምሳሌ ብናነሣ አንድ ጽንፈኛ የሆነ ሰው ወይም ቡድን የሚያንጸባርቃቸው የጽንፈኝነት መገለጫዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ።

በግለሰብ ደረጃ የሚያጋጥም የደኅንነት ሥጋት፡- አንድ ግለሰብ የደኅንነት ሥጋት ካጋጠመው ወይም የማንነት ጥያቄ ካለበት፣ ተመሳሳይ ሥጋትና ጥያቄን የሚጋራ ቡድንን በመቀላቀል ጥያቄውን ለመመለስ ይመኛል። ይህም ምሉዕ የመሆን ስሜትን ያድለዋል። ይህ ግብር በመርሕ ደረጃ ምንም ዓይነት ነውር ወይም ስሕተት የለበትም። በቆይታ ግን ይህ የቡድን ማንነት ወደ ሁለተኛው ደረጃ ያመራል።

ለሌላ ቡድን የሚኖር የጠላትነት ስሜት፡- ግለሰቦች የቡድናቸውን ማንነት ለማጠንከር ሲሉ በሌሎች ቡድኖች ላይ ቁጡና ጠብ ጫሪ የሆነ ባሕርይን ይላበሳሉ። የቡድኑ አባላት ለሌሎች ቡድኖች ያላቸውን ልባዊነት ይቀንሳሉ። ለራሳቸው አባላት ብቻ የተለየና ከፍ ያለ ርኅራኄ ያሳያሉ። በሌሎች ቡድኖች ላይ የጭካኔ አመለካከት ያድርባቸዋል። በሌሎች ቡድኖች የሚገኙ ግለሰቦችን በቡድናቸው ልክ መፈረጅ፤ ማለትም ግለሰቦችን እንደግል ሰብእናቸውና ባሕርያቸው ሳይሆን በሚገኙበት ቡድን ልክ በጭፍን የመፈረጅ አባዜ ውስጥ ይገባሉ።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን የጽንፈኝነት ጅማሮ ደረጃዎች ተከትለው የሚከተሉት የጽንፈኝነት ባሕርያት ይስተዋላሉ። የሌሎችን እውነታ፣ ሁኔታና አመለካከት ወደ ራስ ወስዶ ለመቀበል አለመፈለግ፤ ሁልጊዜ "እኔ ያሰብኩት፣ እኔ የያዝኩትና እኔ ያመንኩት ብቻ ልክ ለመመልከትና ትኩረት ለመስጠት አለመቻል ወይም አለመፍቀድ፤ ሌሎች አማራጮችን ነው"

ብሎ ማመን፤ በጥቅሉ "የእኔ የሆነ ነገር ሁሉ ትክክል ነው" ብሎ ማሰብ፤ ሌሎች ከኛ አስተሳሰብ ውጪ ያሉ ሰዎችን በአንድ ቅርጫት ውስጥ የመክተትና የመፈረጅ ዝን ደረጃ ደግሞ፣ የአመለካከት ወይም የአስተሳሰብ ጽንፍን በቀጥታ ወደ ተግባር መቀየር መኖር። "ከእኔ ጋር ካልሆነ ከጠላቴ ጋር ነው" ብሎ መፈረጅ፣ አደገኛውንና የመጨረሻውን ይሆናል።

ጽንፈኝነት የፖለቲካ ገበያ መመርኮዣ ምርኩዝ ነው። በፖለቲካ ገበያ ውስጥ ቡድኖች የግልና የቡድን ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም መመርኮዣቸው ጽንፈኝነት ነው። ጽንፈኝነት እኛና እነርሱ በሚል መከፋፈል ውስጥ የሚፈጠር የፖለቲካ ገበያ መነገጃ ገንዘብ ነው። ጽንፈኝነት ከፖለቲካ ገበያ አንጻር ግብ ሳይሆን ወደ ጥቅሞች በሚደረግ ጉዞ መዣ ምርኩዝ በመሆን

CamScanner

አገልግሎት ይሰጣል። በመሆኑም ጽንፈኝነት የሚሠራበትና የሚቆምበት ብሎም የሚራመድባቸው ማኅበረሰባዊ ቡድኖች ይፈልጋል።

የሥነ ልቡና ጥናት እንደሚያሳየው፤ ቡድኖች ከግለሰቦች በላይ ጽንፈኝነትን ይፈበርካሉ፣ ያዛምታሉ፣ ያቆያሉ። ምክንያቱም፣ የቡድን ዐውዶች ጽንፈኝነት እንዲበረታታ ያደርጋሉ ግለሰቦች በግል ከሚያስቡት በላይ በቡድን ሲሆኑ የበለጠ ጽንፈኞች ይሆናሉ። በአንድ ቡድን ያሉ ግለሰቦች በተናጠል ከሚኖራቸው የጽንፈኝነት አዝማሚያ ይልቅ ቡድኑ በድምር የያዘው የጽንፈኝነት አዝማሚያ አደገኛ ነው። በቡድን መወሰን በግል ከመወሰን ያነሰ አመክንዮና የባሰ መድሎ አለው።

በአንድ ቡድን የሚሰባሰቡ ሰዎች በመርሕ፣ በአመክንዮና በዴሞክራሲ እስካልተመሩ ድረስ፣ ለራሳቸው ቡድን የተለየ ቦታ መስጠት ይጀምራሉ። ቀጥሎም ቡድናቸው በሌሎች ቡድኖች ሊጠቃ ይችላል ብለው ያምናሉ። ከዚያም ቡድናቸውን ከሌሎች ቡድኖች ጥቃት ወደ መከላከል ያመራሉ። ቡድናቸውን በመርሕ፣ በአመክንዮና በዴሞክራሲ ከመመሥረትና ከማኖር ይልቅ፣ ለሌሎች ቡድኖች ባለ ጥላቻ፣ ተቃርኖና ትግል እየመገቡ ያቆዩታል፡ ግለሰቦች በቡድን ውስጥ ሲሆኑ አነስ ያለ ኃላፊነት የመውሰድ ስሜት ያድርባቸዋል።

“ብዙ ሰው አለ፤ ሐሳቡ የብዙዎች ነው፤ እኔ ብቻዬን አላጠፋሁም፤ ችግር ከመጣ በጋራ እንጠየቃለን” ፤ የሚሉ ስሜቶች ጽንፈኝነት በቡድን ውስጥ እንዲጸና ያደርጋሉ። በቡድን ውስጥ ሰዎች ማበረታቻ ያገኛሉ። ሥልጣን፣ ገንዘብ፣ ክብር፣ ዝና፣ ታዋቂነት፣ መሪነት፣ ተቀባይነት፣ ቁሳዊና ሥነ ልቡናዊ ድጋፍ፣ ወዘተ ያገኛሉ። በዚህ የተነሣም በግል ከሚሆኑት በላይ ለእነዚህ ነገሮች ሲሉ በቡድን ውስጥ የበለጠ ጽንፈኞች ይሆናሉ። ቡድኖች ውስጣዊ ባህል፤ ልማድ፣ ሕግና አሠራር አላቸው። ይሄም በዴሞክራሲያዊ መንገድ ካልተዳደረ በቀር የግለሰቦችን የማሰብና የመወሰን ነጻነት ይነጥቃል። ግለሰቦች

እንደዚህ ባሉ ቡድኖች ውስጥ፣ አሳቢዎች ሳይሆኑ፣ የሐሳብ ማስፈጸሚያ መሣሪያዎች ብቻ ይሆናሉ። የሚነገራቸውን ብቻ ይሰማሉ፤ የተፈቀደላቸውን ብቻ ያምናሉ፤ የታዘዙትን ብቻ ያደርጋሉ። ይሄም ለጽንፈኝነት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።

በሀገራችንም ሆነ ድንበር ተሻግረው ባሉ ሀገራት አክራሪነት መብቀያውና ማደጊያው በአመዛኙ ማንነት፣ ፖለቲካና ሃይማኖት ናቸው። እነዚህ በፖለቲካና በማኅበረሰብ አወቃቀር ውስጥ ያሉ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ መስተጋብሮች የሚፈጠሩባቸው ናቸው።

የፖለቲካ ገበያ ነጋዴዎች ይህንን መስተጋብር በመጠቀም በግንኙነቶች መካከል አክራሪነትን ይዘራሉ። አክራሪነቱ እግር አውጥቶ በጠላትነት እንዲረማመድ በደልን፣ መገፋትን፣ መነጠቅን የመሳሰሉ ብሶት ቀስቃሽና አስቆጪ የማልሚያ ማዳበሪያዎችን ይዘራሉ።በልዩነት ስብከት ስንጥቃቶችን እያሰፉ የመከፋፈል ገደልን ይፈጥራሉ። ከገደል ማዶና ማዶ አቁመው፣ በልዩነት ተረክ እያናወዙ፣ ራሳቸውን የማኅበረሰቡ ተወካይ በማድረግ፣ ግላዊና የንዑስ ቡድን ጥቅሞችን ይነጥቃሉ። በፖለቲካ ገበያ ውስጥ ነጋዴዎቹ አክራሪነትን ተመርኩዘው የልዩነት ዘርን ሲዘሩ ከተጠያቂነት መከለያ ዋሻቸው ማኅበረሰብ ነው።

በመሆኑም በፖለቲካ ገበያ ውስጥ አክራሪነትን የሚያዋልዱ ሃይማኖት፣ ብሔር፣ ዘር፣ ርዕዮተ ዓለም፣ ወዘተ. ናቸው። እነዚህ ዕሴቶች በራሳቸው በጎዎች ቢሆኑም በአሉታዊ ትርክት፣ ሌሎችን በመሥጋትና በመጥላት ከተመረዙ ግን አደገኞች ናቸው። የፖለቲካ ነጋዴዎች እነዚህን ማንነቶች ተጠቅመው ባለጋራን ለመውጋት የሚያዘጋጁት የጦር መሣሪያ ይኖራል። በዚህ የጦር መሣሪያ አይወጉበትም፤ ያስወጉበታል እንጂ። በየትኛውም ማንነት ላይ የቆመ አክራሪነት፤ የሚዋጉለት ቡድኖቹ እንጂ መሪዎቹ አይደሉም። በዚህ እውነት ብዙዎች ቢስማሙም፤ በምክንያት ላይ ያላቸው መረዳት ለየቅል ነው። በመሠረታዊነት

የልዩነታቸው ምክንያት በፖለቲካ ነጋዴዎችና በተከታዮቻቸው መካከል የግብ ልዩነት በመኖሩ ነው።

CamScanner

የፖለቲካ ነጋዴዎች ራሳቸውን በመሲሕነት እየሣሉ ቡድኑን በጭፍራነት በማሰለፍ፣ ጥቅማቸውን ማስጠበቅ ላይ ያተኩራሉ። ተከታይ ቡድኖች በክፋት የተዘራውን ጥላቻ ተገን በማድረግ እየተመሩ ለጥፋትና ለክፋት ከአቦ ሸማኔ ይፈጥናሉ። ስለት ስለትን እንዲያለው ክፋት በክፋት ይበዛል እንጂ አይጠፋም።

አክራሪነት ለመካከለኝነት ቦታ የለውም። አንደኛ በእኛና እነርሱ መካከል የጠላትነት ገደል መካከል ያለው ፖለቲካዊ ዕይታ ነው። የፖለቲካ ነጋዴው ፖለቲካን ነግዶ እንደማትረፍ በመፈጠሩ አገናኝ ድልድይ አይኖርም። ሌላኛው ገጽ በፖለቲካ ነጋዴውና በተከታዮቻቸው ያሳጣቸውን ጠላት እንደማጥፊያ አድርገው ይወስዱታል፡ የፖለቲካ ነጋዴዎች ተከታይ ይመለከተዋል። ጽንፈኝነት ውስጥ ያሉ አባላት ግን አደጋ ያመጣባቸውንና እነርሱን ከማይመስሏቸው ጋር እቻ ትግግዝና ትሥሥር መፍጠር እምነት እንደማጉደልና እንደመሸነፍ ይቆጥሩታል። በሌላ አገላለጽ ከሰይጣን ጋር እንደመሥራት ይቆጥሩታል።

የፖለቲካ ነጋዴው የቡድኖቹ አክራሪነት ጫፍ በነካ ቁጥር ይበልጥ ጥቅሞቹ ይሰፋሉ። አስተማማኝ መከለያም እያበጀ እንደሆነ ይሰማዋል። አክራሪነቱን በገፋ ቁጥር የጥቅም መጠኑ እኩል ማደጉ ከአደጋው ይልቅ ጥቅሙ ጎልቶ እንዲታየው ያደርጋል። በዚህ የተነሣ የፖለቲካ ነጋዴው የቡድኑ አክራሪነት ከእጁ እየወጣ እንደሆነ ለመገንዘብ ያረፍዳል። የቡድ አክራሪነት እንደ እቶን በተንበለበለበት፣ የፖለቲካ ነጋዴው ለመመቻመች የሚያደርገው ሙከራ ቡድኑ በእርሱ ላይ አደጋ እንደሚያስከትልበት ስለሚረዳ፣ ያለው አማራጭ በያዘው ሐሳብ መቀጠል ብቻ ይሆናል። በአጠቃለይ አክራሪነት በፖለቲካ ነጋዴዎች ዘንድ እንደ ስልት ሲቆጠር በተከታይ ቡድኖቻቸው ዘንድ እንደ እምነት ይያዛል።

በሐሳብ አልባ የፖለቲካ ነጋዴዎች በአክራሪነት የሚጦዝ ፖለቲካ፣ የአንድን ሀገር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሕጋዊ ሥርዓትን ይረብሻል። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ የዴሞክራሲ መርሖችን በመፈተን አጣብቂኝ ውስጥ ለመክተት ይሠራል። የዴሞክራሲ ተቋማትን ቅቡልነት ለማሳጣት ይጥራል። መንግሥትን በአምባገነንነት እየከሰሰ አክራሪነትና ዐመጽን ያፋፍማል።

መንግሥት በአንድ በኩል የዴሞክራሲ ምኅዳርን በማስፋት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሕግን - ማስከበር መካከል አጣብቂኝ ውስጥ ይገባል። ለዴሞክራሲ ምኅዳር መስፋት ብሎ ነገሩን ታገሥ፤ ሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች በሀገሪቱ ሕግ የሌሌ እንዲመስል ምኅዳሩን የብጥብጥ መድረክ ያደርጉታል። መንግሥት ሕግ በማያከብሩ አካላት ላይ ሕግ ማስከበር ሲጀምር ድግም የዴሞክራሲ ምኅዳሩ ጠበበ ብለው ይከሱታል። አክራሪዎች በመንግሥት የሚደረጉ ማናቸውንም ዓይነት ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን ባለመቀበል፣ ማጣጣል ይቀናቸዋል። የሚቀርቡ የለውጥ ሐሳቦችና ድርጊቶች በሙሉ
ከወቀሳና ከነቀፌታ አያመልጡም። ሐሳብ አልባ ፖለቲካ ምርኩዙ ሥራን ሁሉ ማጠልሸትና ማኅበረሰባዊ ሰላምን ማወክ ነው።

ጽንፈኝነትን መመርኮዣ ያደረገው የፖለቲካ ገበያ ማደሪያውና ማደጊያው ብሔር፣ ሃይማኖትና ፖለቲካ ናቸው። አክራሪነት የተለያዩ ምክንያቶችን መነሻ በማድረግ ቢነሣም አንድ የሚያደርጋቸው ባሕርይ አለ። በሌላ በኩል ላለው ወገን አንዳች ቦታ ሳይሰጡ፣ የኔ ለሚሉት ፍላጎት፣ እምነት ወይም ቁስ ሁሉንም ዋጋ በመክፈል የሚደረግ ጠርዘኛ እንቅስቃሴ ነው። ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ገበያ እነዚህን ተቋማት ተመርኩዞ ግላዊ ፍላጎቱን በማስፈጸም ለብልጽግና ራዕይ ፈተና የሚሆንበት ምርኩዝ ነው።

የጽንፈኝነት መነሻው አስተሳሰብ ነው። መድረሻው ደግሞ ጽንፈኛ አስተሳሰብን መተግበር ይሆናል። የአግላይነት ፖለቲካ፣ ሥልጣንን እንዲሁም የኢኮኖሚያዊ ጥቅም ተገቢነትን ወይም ተገቢ አለመሆንን በቡድን አባልነት ይፈርጃል። የሆነ ሰው ለሥልጣን ወይም ለሆነ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ተገቢ ነው ተብሎ የሚመዘነው፣ የሆነ ቡድን አባል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ነው። እንደዚሁ አይገባውም ተብሎም የሚከለከለው የሆነ ቡድን አባል ነው ተብሎ ነው። እኔ የዚህ ብሔር ወይም ሃይማኖት

CS CamScanner

አባል ነኝ፤ ይህ ሥልጣንና ሀብት ለእኔ ይገባኛል፤ እገሌ ደግሞ የዚያ ብሔር ወይም ሃይማኖት አባል ስለሆነ አይገባውም የሚል ዕሳቤ ነው። እገሊት ሀገራዊ ብሔርተኛ ወይም የማኅበረሰብ ብሔርተኛ ናት፤ ይህ ሥልጣን ለምን ተሰጣት? ወይም ለምን ተከለከለች? የሚል፣ በፖለቲካ መሥመር በተሠመረ ቡድናዊነት የሚያቅፍ ወይም የሚያገል ፖለቲካ ነው።

በእንደዚህ ዓይነት ምልከታዎች ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ፣ ቡድናዊ ወይም የማንነት ውድድሮች የበዙበት ነው። አለፍ ሲልም በእነዚህ ልዩነቶች ላይ የተመሠረቱ ግጭቶች ይበዙበታል። ስለዚህም ፖለቲከኞች ወይም ልሂቃን ግጭቶችን ለማብረድና መረጋጋትን ለመፍጠር የሥልጣንና የሀብት ቅርምት ድርድር ውስጥ ይገባሉ። የጥቅም ትሥሥሮችን ይፈጥራሉ።

የፖለቲካ ሕይወት ወይም የፖለቲከኞች ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በሥርዓት ሊተዳደር የሚያደርጉት ጥረት እንዲሁም በሥልጣን ላይ የሚፈጽሙት ድርጊት ሁሉ ሥርዓትና ሕግ ይገባል። ድጋፍ ለማሰባሰብ፣ ወደ ሥልጣን ለመውጣት፣ በሥልጣን ለመቆየት ይፈልጋል። በዴሞክራሲ ሥርዓቶች ይህ የፖለቲካ ሕይወት በሥነ ሥርዓቱ የብዙኃኑን ወይም የሕዝብን ጥቅም ማስከበሩን በሚያረጋግጥ መልኩ በሕግና በተቋማት ቁጥጥር ይደረግበታል። በአምባገነናዊ ሥርዓቶች ግን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች የአምባገነኑን ጥቅም በማይቃረን ወይም የአምባገነኑን ሥልጣን በሚያስጠብቅ መልኩ መከወናቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ብቻ ጠንካራ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።

ሕጋዊነትንና ተቋማዊነትን ዐቅም ማሳጣት፡- ጽንፈኝነት፣ ቁጥጥር ያለበትንና በሕግ የተመሠረተን ፖለቲካ ይሸራል። ጽንፈኝነት በሞራላዊ ሕዝበኝነት የተመሠረተ ነው:: ልሂቃን ራሳቸውን የሕዝብ አዳኝ አድርገው በማቅረብ ግለሰባዊ ግንኙነት የሚፈጥሩበት መረብ ነው። በዚህም ለሚፈጽሙት ሕገ ወጥ ድርጊት ሕዝብን ሽፋን አድርገው በማቅረብ ከነበረው ሕጋዊና ተቋማዊ ፖለቲካ በላይ ሆነው ይቆማሉ፡ የፖለቲካ ገበያ የሚፈጠረው ተቋማት የፖለቲካ ሕይወትን ለመቆጣጠር ዐቅም ሲያንሳቸው ነው። ጽንፈኝነት የተቋማትን ዐቅም በማሳነስ (እምነት እንዲያጡ በማድረግ) ወይም ተፈጻሚነታቸው እንዲገደብ በማድረግ፣ ግለሰቦች ከተቋማት በላይ ሆነው እንዲቆሙ ዕድል ይሰጣል። ጽንፈኝነት ፖለቲከኞች ሕግን ጥሰው ለመሸሽግ የሚችሉበት ሰብአዊ ምሽግ ይፈጥርላቸዋል።

ልዩነቶች እንዲከሩ፣ ውድድሮች እንዲለጠጡ፣ ጽንፈኝነት በማኅበረሰብ አካላት ወይም በልሂቃን መካከል የልዩነት መሥመርን(የእኛና የእነርሱን መሥመር) አድምቆ ያሠምራል። በዚህም የከረረ ሽኩቻ ይፈጥራል። ይህ የከረረ ውድድርና ሽኩቻ አንዱ በአንዱ ላይ የበላይ ለመሆን በሚደረግ ጥረት ለፖለቲካ ገበያ መፈጠር አንዱን መደላደል ይፈጥራል።

ለዐመጻ በር መክፈት፡- ጽንፈኝነት በስሜት ኮርኳሪና በሞራሊዝም አግላይ ትርክቶች ላይ የተመሠረተ መሆኑ ይታወቃል። ይህም ለልሂቃን በቀላሉ ድጋፍ ለማሰባሰብ ይረዳቸዋል። ድጋፍ ማሰባሰቡ ችግር ባይሆንም፣ ድጋፉን ወደ ዐመጻ ሊቀይር፣ ከፍ ሲልም ወደ ትጥቅ እንቅስቃሴ ሊያሸጋግር ይችላል። የፖለቲካ ነጋዴዎች ማኅበረሰባዊ መተማመንን ማላላት፣ አክራሪነትን ማጠናከርና ፖለቲካን የኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማጋበሻ ማድረግ ሥራቸው ነው። ጽንፈኝነት የፖለቲካ ወረት ይሰጣቸዋል። ስለዚህም ተጠናክሮ እንዲወጣ የተለያዩ ጉዳዮችን አቀናጅተው ይጠቀማሉ።

ፖለቲካ በተፈጥሮው የሐሳብ ውድድር አለው። የፖለቲካ ንግድ በተንሠራፋበት ሁኔታ ውስጥ ደግሞ የመደራደሪያ መንገድ ሐሳብ ሳይሆን ማንነት፣ ገንዘብ፣ ብጥብጥ፣ ግጭትና መሰል ጉዳዮች ናቸው። በፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ከፍተኛውን ዋጋ የሚያገኘው ከፍተኛ መደራደሪያ ዐቅም ያለው ነው። በእነዚህ የሲቪክ ባህል ባልዳበረባቸው ሀገራት ደግሞ ዋነኛው የመደራደሪያ ዐቅም ማንነት ነው። ይህ ዓይነቱ የፖለቲካ ሁኔታ ዴሞክራሲ በዳበረባቸው ሀገራትም ይታያል። ዴሞክራሲ ባልሰፈነባቸው ሀገራት ግን በዋነኝነት | ፖለቲከኞች የድጋፍ ምንጫቸው ወይም የሥልጣን መሠረታቸው ማንነት ነው።

CamScanner

ወደ ገበያ ይዘውት የሚቀርቡት የፖለቲካዊ ሥልጣን ቅቡል እንዲሆን የሚጥሩት ብሔራቸውን ወይም ሃይማኖታቸውን ጠቅሰው ነው።

የፖለቲከኞች የተወሰነ ሕዝብን ከጎናቸው ለማሰለፍ በሕዝብ ውስጥ የሚፈጠር ፍርሃትን ይጠቀማሉ። ይህ አካሄድ በአንድ በኩል ሕዝብ አደጋ እንደተጋረጠበትና ጠላት እያንዣበበት እንደሆነ የሚገልጽ ትንታኔን ያዘለ ነው። በሌላ በኩል ራስን

የሕዝብ ጠበቃ፣ ከአደጋ ተከላካይና ወዳጅ አድርጎ የሚያቀርብ ነው። "የተፈጠረና እየተፈጠረ ያለ አደጋና ጠላት አለ" ብሎ ሕዝቡን ያሸብራል። ከዚያ ራሱን ሕዝብን ሊያድንና ሊጠብቅ የቆመ ኃይል አድርጎ ያቀርባል። የፖለቲካ ንግድ የቆመው በእንደዚህ ዓይነት የሤራ ትንታኔ ላይ ነው።

በልዩነት ላይ በተመሠረተ ፖለቲካ የሚመራው የፖለቲካ ንግድ ግቡን ለማሳካት በሤራ ትንታኔ ላይ ይንጠለጠላል። በልዩነት ውስጥ የጠላትነት ትርክትን በመፍጠር አንዱን የተጨቆነና አደጋ የተጋረጠበት፣ ሌላውን ደግሞ ጨቋኝና አደጋ ፈጣሪ በማድረግ አግላይ ትርክቶች ይፈጠራሉ። የተጨቆነውና አደጋ የተጋረጠበት ፍርሃት ይፈጠርበታል። በሌላኛው ወገን ላይ ደግሞ ጥላቻ እንዲፈጠርበት ይደረጋል።

### 12.7.3. ሕዝበኝነት

ሕዝበኝነት ወይም ልወደድ ባይነት በፖለቲካ ውስጥ ስላለው ቦታ ብያኔ ለመስጠት እ.አ.አ. ከ990ዎቹ ጀምሮ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን በርካታ ጥናቶችን እያደረጉ ብያኔዎችን እየሰጡ ይገኛሉ። ነገር ግን ብያኔያቸው ጥርት ያለና ሁሉንም በሚያስማማ ደረጃ ላይ አልደረሰም። አንዳንዶች አማካኝ ርዕዮተ ዓለማዊ ባሕርይ አለው በማለት የደቡብ አሜሪካ ሀገራትን የፖለቲካ መሪዎችና መንግሥታትን አጣቅሰው ያስረዳሉ። ከዚህ ሐሳብ በተለየ ሕዝበኝነት የፖለቲካ ፍላጎትን ማስፈጸሚያ ስልት እንደሆነ አድርገው የሚያቀርቡም አሉ። አንዳንዶች እንዲያውም የፖለቲከኞች ወግ አድርገው ያቀርቡታል።

በምሁራን ዘንድ ይሄንን የመሳሰሉ ተያያዥ ጉዳዮች እያነው ውይይትና ሙግት ያደርጉበታል። በምሁራኑ ዘንድ ትኩስ የጥናት መስክ ቢሆንም ሕዝበኝነት ታሪካዊ ዳራው ነው። እኢአ በ890 ገበሬውን ማዕከል ካደረገው የሕዝብ ፓርቲ ንቅናቄ ጋር ተያይዞ ከረም ያለ ነው። የሕዝበኝነት ታሪካዊ መነሻ ከደቡብና ከማዕከላዊ ምዕራብ አሜሪካ ሌኒኒዝም አቀንቃኝ

ቢሆንም፣ በጣት የሚቆጠር ኢንዱስትሪ ለሌላት ቻይና ርዕዮተ እንደመጣ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ። እንዲሁም ማኦ ሴቱንግ የማርክሲዝምና ዓለማዊ ተቃርኖን ያለግጭት ለማለፍ ሲል፣ ገበሬውን ማዕከል ያደረገ ሕዝበኝነትን እንደስልት እንደተጠቀመ ይነገራል።

ሕዝበኝነት በአንድ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም አተያይ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ሕዝበኝነት በቀኙ ክንፍ አክራሪዎች ዘንድ በስፋት የሚታይ ቢሆንም በግራ ክንፍ ፖለቲከኞች ዘንድም አለ። በካፒታሊስቱም ሆነ በሶሻሊስቱ፣ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓትም ሆነ በአምባገን ሥርዓት ውስጥ ሕዝበኝነት ይታያል።

በሀገራችን የሕዝበኝነት ገቢራዊ ባሕርያት እንዳሉ ባያጠራጥርም፣ በምልዐት መረዳት እንደሚጎድለን ከፖለቲካ ሐቲታችን ተነሥተን መደምደም ይቻለናል። ሕዝበኝነትን በምልዐት ለመረዳት በሕዝበኝነት ውስጥ ያሉ ተዋንያንን መለየትና ፖለቲካዊ ሐቲቶች እንዴት እንደሚፈጠሩ መመልከትና መዳሰስ ይገባል።

በመሠረቱ "ሕዝበኛ" በሚለው ጽንሰ ሐሳብ ውስጥ ሕዝብ፣ የፖለቲካ ልሂቃን፣ ምልዐተ ፈቃድና የመሳሰሉ አንኳር ሐሳቦችን ከፋፍሎ መመልከት ጠቃሚነቱ ብዙ ነው። የሕዝበኝነት መገለጫ አልያም ማሳያ ተብለው የሚጠቀሱ አስረጂዎች አሉ። ሕዝብ በአንድ ሀገር ውስጥ ለየትኛውም የፖለቲካ ዓይነት መሠረት መሆኑ ክርክር የሚነሣበት አይደለም። የትኛውም

CamScanner

ፖለቲከኛ ያለ ሕዝብ ቅቡልነት የፖለቲካ ሕይወት አይኖረውም። ሕዝበኞች ከሌሎች ፖለቲከኞች የሚለዩት ሕዝቡን በሚደርሱበትና ሕዝቡን በሚያዩበት መንገድ ነው።

ሕዝበኞች የተደራጀ ሐሳብ ከማቅረብ ይልቅ ለሕዝቡ መሲሐዊ ስብከት ያበዛሉ። ለዚህ ሕዝብ የተሰጡ በረከቶች እንደሆኑና ዕድሉን ሲያገኙ ችግሩን ሁሉ አንዳች በማይታወቅ ኃይል እንደሚያበኑት አብዝተው ይሰብካሉ።

ሕዝበኞች የተሠራን ማጣጣል፣ ተቋማት እንዳይታመኑ ማንቋሸሽ፣ መፍትሔዎችን በማቅለል “እኛ ብንሆን እንዲህ አይሆንም” የሚል “ሾላ በድፍን” ሐሳብ ይሠነዝራሉ። እዝበኞች ይህንን ሐሳባቸውን ለማጋባት የማኅበረሰብን ስስ ብልቶች በመነካካት ስሜት ኮርኳሪና አስቆጪ ዲስኩሮችን ያሰማሉ። አስፈላጊ ሲሆን ሙሾ እየደረደሩ የሕዝብን ቀልብ ለማግኘት ይሠራሉ።

የሕዝበኞች ሌላው ገጽ ራሳቸውን የተበዳዮች ብቸኛ ነጻ አውጪ አድርገው ማቅረባቸው ነው። የሕዝብን በደልና ቁስል እያከኩ በማመርቀዝ “አዛኝ ቅቤ አንጓቾች” ይሆናሉ። የተበዳይ ቁስል የሚሽርበትን አንዳች መውጫ ሳያመላክቱና ሳይሠሩ ትኩረታቸውን በቁስሉ ላይ ብቻ ያደርጋሉ። እነዚህን ሁለት ገጾች አንድ የሚያደርጋቸውና በአንድነት የሚያስጠራቸው ራሳቸውን የሕዝብ ድምፅና ተወካይ አድርገው ማመናቸው ነው። ሕዝበኝነትን ተመርኩዘው በፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ የሚንቀሳቀሱት ሐሳብ አልባ የፖለቲካ ነጋዴዎች፣ ለሕዝብ የሚጨበጥና የሚያሻግር ሐሳብ አያቀርቡም። ከዚያ ይልቅ የሕዝብን ስለ ጎን በመነካካት የግል መሻታቸው የሆነውን ሀብት፣ ሥልጣንና ዝና በማሳደድ ላይ ያተኩራሉ።

ዛሬ ዛሬ በሕዝብ ስም የማይነግድ የለም። በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገራት ከተከሠቱ ሁነቶች ስንነሣ፣ ሕዝበኞችን አንድ ነገር ያመሳስላቸዋል። ይሄውም ራሳቸውንና ሕዝብን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ አድርገው ማስቀመጣቸው ነው።

ሌሎችም እንዲሁ ዲጂታል አብዮት በፈጠረላቸው አስቻይ ዕቅም ነጋ ጠባ “ሕዝባችን እንዲህ ሆነ፣ ሕዝባችን እንዲህ ተደረገ፣ ሕዝባችን ይህንን አይፈልግም” የሚሉ የድፍረት ንግግሮችን ማድረግ የተለመዱ ሆነዋል። ሕዝበኞች ምኞት እንጂ ዕቅድ የላቸውም። ወሬ እንጂ ሥራ አይችሉም። የታሰበውን ያናንቃሉ እንጂ አዲስ ሐሳብ የላቸውም። የሀገራችን ሰው “አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል” የሚላቸው እነርሱን ነው። ጤፉ ቢፈጭና ቢጋገር ነበር የሚጠቅመው። ሕዝበኞች ግን ይቆሉታል።

ሕዝበኞች በሕዝብ ድምፅ ከተመረጡ አስተዳዳሪዎች በበለጠ ራሳቸውን ሐቀኛ የሕዝብ ተወካይ አድርገው ሲያቀርቡ፣ አይደነቃቀፉም። ሕዝበኞች ለራሳቸው ራሳቸው ድምፅ ይሰጣሉ። ከሕዝብ መካከል ለሚነሣባቸው ጥያቄ “እኔ እኮ ሁሉ ሞልቶ የተትረፈረፈልኝ ነኝ፤ ለእናንተ ብዬ ነው እንደሻማ የምቀልጠው" በማለት ሕዝብ ማስፈራራት ይቃጣቸዋል።

በሕዝበኝነት ውስጥ ሌላው ሊታይ የሚገባው የዕይታ መነጽራቸው ነው። ልሂቃኑ ሁሉንም ነገር የሚመለከቱት ለሁለት በመክፈል ነው። ራሳቸውን መነሻ አድርገው ከራሳቸው ውጭ ያለውን በጠላት ወገን ያሰልፋሉ። ሕዝበኛ ልሂቃን አተያያቸው በዚህ እንዲቃኝ ያደረገው ራሳቸውን የሕዝብ ብቸኛ ወኪል አድርገው መመልከታቸው ነው። ከእነርሱ ውጭ ያ ባሻገር ያሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኪነ ጥበባዊም ሆነ መገናኛዊ ነገሮችን ሁሉ በብቸኝነት ማኅበረሰብ ወኪል የለውም። አለሁ የሚል ካለ ታፔላ ለጥፈው ያሳድዱታል። ከፖለቲካ መያዝና መቆጣጠር ይፈልጋሉ። እነዚህ ልሂቃን የሕዝቡ ብቸኛ ተወካይነታቸው በሁሉም መስክ እንዲሆን ከመፈለጋቸው የተነሣ፣ የዕድርና ዕቁብ አደረጃጀቶችን ሳይቀር ከእነርሱ ዕይታ እንዲወጡ አይፈቅዱም። “ሕዝቡ የኔ ብቻ ነው” ከማለታቸው የተነሣ “የፈጠርኩት እኔ ነኝ” ሊሉ ጥቂት ነው የሚቀራቸው።

CamScanner

ከእነርሱ ውጭ የሆኑት በሙሉ የጠላት እንደሆኑ ይፈርጃሉ። ሕዝበኝነት የሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች መመርኮዣ ነው። የማንነትንም ሆነ የሐሳብ ብዝኃነትን የሚያስተናግዱበት ዕውቀትም፣ እውነትም፣ ፍላጎትም የላቸውም። ዓለምን የሚመለከቷት የእኔ በሚሉት አጥር ውስጥ ሆነው ነው። አጥራቸውን ለማስጠበቅ የልዩነት ዘርን ይዘራሉ። የእኛ ብሔር፣ የእኛ ሃይማኖት፣ የእኛ መሬት፣ የእኛ… በሚል ትንታኔ፣ ሕዝብን የራስ ሀብትና ሥልጣን ማስገበሪያ እያደረጉ ሌሎችን ነጣቂ ተኩላ አድርገው ያቀርባሉ።

የሀገራችን ፖለቲካ እንደነዚህ ባሉ ሐሳብ አልባ ፖለቲከኞች የተሞላ ነው። ማንነትን ለፖለቲካ ንግድ የሚያውሉ ሕዝበኞች ከፖለቲካ ገበያ የተለየ ሐሳብ እንደሌላቸው የሚያደርጉት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ይመሰክርባቸዋል። በአጠቃላይ ሕዝበኝነት አንድን ማኅበረሰብ እየከፋፈሉ በልዩነቱ ሀብትን ለማጋበስና ሥልጣንን ለማቆየት የሚተጋ የፖለቲካ ገበያ መመርኮዣ ነው።

በሕዝበኝነት ውስጥ ሌላ የሚታይ ደፋር አቀራረብ አለ። የሕዝብ ምልዐተ ፍቃድ እንደተቸራቸው አድርገው የሚያቀርቡት አቀራረብ። ሕዝበኞች ሕዝብ በእነርሱ ዓይን የሚያይ፣ በእነርሱ ጆሮ የሚሰማ፣ በእነርሱ አእምሮና ልብ የሚረዳ እንጂ የራሱ መረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ፣ ብሎም ማመዛዘኛና መበየኛ ልቡና አለው ብለው አያምኑም። በመሆኑም ሕዝብን እንደፈጠሩት ሮቦት አንድ ዓይነት እንቅስቃሴና ምላሽ የሚሰጥ አድርገው ይቆጥሩታል።

ሕዝበኞች በሚልዮን የሚቆጠር ሕዝብ ምልዐተ ፍቃድ በአንድ ድምፅ ተችሮኛል ብለው ማመናቸው፣ የሰው ልጅን ተፈጥሮ ፍጹም የካደ ነው። ሕዝበኞች እንዲህ ባለው የሐሳብ ውድቀት ውስጥ የጣላቸው ራሳቸውን መሲሕ አድርገው ከማቅረባቸው የተነሣ ነው። ፖለቲካዊ ገጹ ደግሞ ፈላጭ ቆራጭ የመሆን መሻት ነው።

ሕዝበኞች ከዚህ ዕይታቸው በመነሣት የዴሞክራሲ ጠንቅ ናቸው ማለት እንችላለን። ከዚህ በተጨማሪ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሂደትን የሚጣሉ በርካታ ተግባሮች ይፈጽማሉ። በዋናነት ሕዝበኞች የመንግሥት መዋቅሮች እንዲሠሩ አይወዱም። በመሆኑም ስም በማጥፋትና በማጠልሸት ተቋማት በሕዝብ ዘንድ እምነት እንዳይጣልባቸው አበክረው ይሠራሉ። በዚህም የተቋም ግንባታ ሂደት ላይ አፍራሽ ሚና ይጫወታሉ። የተቋም ደካማነት በሕዝበኞች ዘንድ የሚፈለገው በሕግና በሥርዓት ለመሥራት የሚያስችል የፖለቲካ ሐሳብና ባህል ስለሌላቸው ነው። ተከታዮቻቸውን በስሜት ከመጋለብ የሕግ ልጓም ስለሚገታቸው አስቀድመው ተቋማትንና ሥርዓትን ያጠቃሉ።

ሕዝበኝነት ዴሞክራሲን የሚፃረረው ለብዝኃነት ባለው ዕይታ ነው። ሕዝበኝነትና ብዝኃነት ውኃና ዘይት ናቸው። ሕዝበኞች ሁሉን እኩል ማየት፣ ብዝኃ ሐሳብ ማስተናገድና ለሁሉም የሚመች ሥርዓት ማበጀት እንዳይችሉ "የእኔ" የሚሉት አጥር ይገድባቸዋል። በአጠቃላይ የሕዝቡን ድምፅ ከመንጠቅ ባሻገር ለዴሞክራሲ መሠረት የሚሆኑ ተቋማትን አይፈልጉም። ብዝኃነትንም አይቀበሉም። በሀገራችን የዐቅም ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር በቃልና በሐሳብ ይህ ብሔር ምልዐተ ፍቃዱን ሰጥቶኛል የማይል ሕዝበኛ ፈልጎ ለማግኘት ያዳግታል። ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ ነኝ የሚለውም "ኢትዮጵያውያን በሙሉ ፍቃዳቸውን ለእኔ ብቻ ሰጥተውኛል" ይላል። ለኢትዮጵያ ትንሣኤ የተላክሁ መሲሕ ነኝ ብሎ ይቀርባል።

በሐሳብ አልባ የፖለቲካ ገበያ ውስጥ ሕዝበኝነት ሥራውን የሚሠራው መጀመሪያ አንድን ሕዝብ ለሁለትና ከዚያም በላይ በመከፋፈል ነው። ሕዝበኞች ከራሳቸው ንዑስ ቡድን ውጭ ያሉትን ሆነ ሌሎችን ልሂቃን በመፈረጅና በማጥላላት እንጀራቸውን ይጋግራሉ። እንዲሁም ሕዝብ በካርድም ሆነ እጅን አውጥቶ ሳይመርጣቸው፣ የሕዝቡን ምልዐተ ፍቃድ በራሳቸው ሥልጣን በመውሰድ የፖለቲካ ንግዳቸውን ያጧጡፉበታል። የሕዝበኞች ግብ በሕዝብ ስም ንዋይ፣ ሥልጣንና ዝናን የራሳቸው ማድረግ ነው። ይህንን ለማሳካት የሚሄዱበት መንገድ በኅቡዕና በግልጽ የተደራጀ በመሆኑ፣ በፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ቀላል አይደለም።

**12.7.4.** የጠቅላይነት/ አግላይነት ሸኩቻ

CamScanner

“ጠቅላይነት” ማለት ብዝኃነትን ባለመቀበል ሁሉን ዓይነት ልዩ ልዩ ዓይነቶች፣ በአንድ ቋት ብቻ የሚከትና የሚያስብ አመለካከት ነው። አግላይነት ደግሞ የራሱን አመለካከት ወይም ቡድን ብቻ ይዞ ሌላውን በማግለል፣ኅብረትንና አንድነትን የሚፃረር ነው።

አግላይና አክራሪ አመለካከቶች በአንድ በኩል ሀገራዊ ብሔርተኝነትን እንደ ካባ ይጠቀማሉ። ወደ አንድ ዓይነትነት ይጠቀልላሉ እንጂ ብዝኃነትን ለመቀበል አይዘጋጁም። በሌላ በኩል በአካባቢያዊ ብሔርተኝነት ካባ የተሸፈኑት አግላዮች ደግሞ አንድነትን ለመቀበል ይከብዳቸዋል። ይህ የተካረረ የፖለቲካ ሽኩቻ፣ ጎራ እየለየ በማይታረቅ ሕልም ውስጥ

ይከትተናል። ሀገረ መንግሥቱም የቅቡልነት መሳሳት እንዲያጋጥመው ያደርጋል።

ፖለቲከኞች፣ ባለ ሀብቶች፣ የማኅበረሰብ አንቂዎች፣ አክራሪ የኢትዮጵያ ብሔርተኞች፥ አካባቢያዊ ብሔርተኞች፣ እንዲሁም የሃይማኖት አክራሪዎች፣ በፖለቲካ ንግድ በኩል የሕዝብን ድጋፍ በማሰባሰብ፣ ለግላዊ ጥቅማቸው ያውሉታል።

አክራሪነት በውስጡ ጠቅላይነትና አግላይነት ይጠናወቱታል። በእነዚህ ጎራዎች መካከል ፖለቲካዊ ኢኮኖሚውን ለመጠቅለልና ሌላውን ለማግለል ከፍተኛ ውድድሮች ይካሄዳሉ። የአክራሪነትን ፖለቲካ በሕግ ለመግራት ከባድ ስለሆነ፣

ፖለቲከኞች ግባቸውን ለማስፈጸም ማንኛውንም ዓይነት (ሕጋዊም ይሁን ሕገ ወጥ) ፖለቲካዊ እንቅስቃሴና ትብብር ለማድረግ ዕድል ይሰጣቸዋል። በሕዝበኝነት ውስጥ የሚኖር አክራሪነት ግለሰቦች ከሕዝብ ጋር በሚፈጥሩት ግለሰባዊ ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው። ግለሰቦቹ የሕዝብ ታዳጊ፣ ጠበቃ፣ ዋስትናና መሪ ሆነው እንዲታዩ ሕዝበኝነት ዕድል ይሰጣቸዋል። ከሌሎች የተሻሉ ሆነው ለመታየት የሚወዳደሩበት መንገድ፣ ነገሩን የበለጠ በማክረር ነው። በዚህ ያልተገባ ግንኙነት የተነሣ እነዚህ ግለሰቦች ከሕግ በላይ ሆነው ለመውጣት እንዲሞክሩ ዕድል ይሰጣል።

በሀገራችን እነዚህ አክራሪ ኃይላት በሞራላዊ ሕዝበኝነት የሕዝብን ስሜት በመቀስቀስ ድጋፍ የማሰባሰብ ዐቅም አለን ብለው ያስባሉ። ይህንን የጋሸበ ዐቅም፣ ለሚያደርጉት ሕገ ወጥ ድርጊት እንደ መከላከያ ቅርፊት ሲጠቀሙት ቆይተዋል። አንዳንድ

ግለሰቦች ዐመጻ የተሞላበት ማኅበረሰባዊ እንቅስቃሴን (Social Movement) በመፍጠርና እፈጥራለሁ በማለት ያስፈራራሉ። ሌሎች ደግሞ የታጠቀ ኃይል አደራጃለሁ አንቀሳቅሳለሁ በሚል ይዝታሉ።

በዚህ ዓይነት ሕገወጥ መንገድ የፖለቲካ ግብን ለማስፈጸምና ኢኮኖሚያዊ ትርፍን ለማግኘት ሲሠሩ ታይተዋል። የፖለቲካ ገበያ አንዱ መነገጃ ዐመጽን መቀስቀስ ወይም እቀሰቅሳለሁ ብሎ ማስፈራራት ነው። ይህም ለአቀባባይ ልሂቃን ከፍ ያለ ገንዘብ ያስገኝላቸዋል። ሰውጭ ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ ከሚያሰባስቡት ከፍተኛ ገንዘብ በተጨማሪ የፖለቲካ ማንነታቸውን በመሸጥ ከፍተኛ ገንዘብ ይሰበስባሉ።

የመጀመሪያው በሥጋት የተነሣ ነው። እነዚህ የፖለቲካ ነጋዴዎች ስም ያጠፋሉ። በሀብትና ባለ ሀብቶችና ሌሎች ኃይላት በሁለት ምክንያቶች ለፖለቲካ ነጋዴዎች ድጋፍ ያደርጋሉ። በንብረት ላይ አደጋ እንዲደርስ ይቀሰቅሳሉ። ባለቤትንና ቤተሰብን ያስፈራራሉ። ለዚህ ደግሞ ማኅበራዊ መገናኛውንና ሐሜትን ይጠቀማሉ። በዚህ የተነሣ ባለ ሀብቶችና ሌሎች አካላት ገንዘብ በመክፈል ከዚህ ሥጋት ራሳቸውን ለመከላከል ይሞክራሉ ።

በሌላ በኩል ደግሞ ፖለቲካዊ ፍላጎት ኖሯቸው የእነዚህን ሰዎች ፖለቲካዊ ታማኝነት ለመግዛት ብዙ ገንዘብ የሚያወጡም አሉ። ዐመጽን የመቀስቀስ ዐቅም በፖለቲካ ገበያ ውስጥ ተፈላጊ ሸቀጥ ነው። በሀገራችን ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የሚፈልጉ የውጭ ኃይላት በቀላሉ የእነዚህን ኃይላት ታማኝነት እንደ ሸቀጥ በመግዛት ይጠቀሙበታል። ሌላው ቀርቶ በመንግሥትና በፓርቲ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሥልጣንን ለማግኘትና ለማስጠበቅ ከእነዚህ ሰዎች ጋር የጥቅም ትሥሥር ይፈጥራሉ።

CamScanner

ፖለቲከኞች ፖለቲካዊ ግባቸውን ለማሳካትና ኪሳቸውን ለማድለብ፣ ባለሀብቶች ኢኮኖሚያዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በፖለቲካ መሥመሮች (ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ ወይም አካባቢያዊ ብሔርተኛ፣ ወይም ሃይማኖታዊ ወገንተኛ) ላይ የተመሠረተ የጥቅም ትሥሥር ይፈጥራሉ። ፖለቲከኛው ሥልጣን የሚያገኘው፤ ባለ ሀብቱ መሬት፣ ብድር፣ የውጭ ምንዛሪ
የሚያገኘው፣ ፕሮጀክት የሚወስደው በእነዚህ መሥመሮች ላይ ነው።

በአጭሩ የፖለቲካ ገበያ ማለት፣ ማንነት በግልጽ ወደ ፖለቲካ ሸቀጥነት ተለውጦ የሕዝብ ወይም የቡድን ድጋፍ የማሰባሰቢያና የማማለያ ዘዴ ሲሆን ነው። ይህ ገበያ ይበልጥ የሚደራውና የሚጧጧፈው ደግሞ ዓለም አቀፍ ኃይሎች በገበያው የመሳተፍ ፍላጎት ሲኖራቸው ነው። ዓለም አቀፍ ኃይሎች ለእንዲህ ዓይነት ግለሰቦችና ቡድኖች ድጋፍ፣ ከለላና ጥበቃ ስለሚያደርጉላቸው በገበያው ውስጥ ትልቅ ዋጋ ያላቸው ኃይሎች ይሆናሉ።

በዚህ ሂደት ውስጥ ግለሰቦች እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት የራሳቸውን ብራንድ ለመፍጠር ይሞክራሉ። ይህ የማንነት ብራንድ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ እነርሱ የብሔሩና የሃይማኖቱ ወኪል እንዲመስሉ የሚያደርጋቸው ነው። በገበያው ውስጥ የበለጠ አክራሪነትን የያዘ ኃይል እንደ ጥሩ ብራንድ የመቆጠር ዕድል ስላለው፣ ግለሰቦች ጥሩ የብሔር ወይም የሃይማኖት ብራንድ ለመሆን ሰፊ ርብርብ ያደርጋሉ።

በፖለቲካ ገበያው ውስጥ ማንነትን መሠረት ያደረጉ እጅ መንሻዎችን በማቅረብ የሕዝብን ድጋፍና ተቀባይነት ለማግኘት ይጥራሉ። እነዚህ እጅ መንሻዎች መሬት፣ ብድር፣ ገንዘብ፣ ትርክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህን እጅ መንሻዎች በአድልዎ በማድረስና ከሕዝቡ ድጋፍ የፖለቲካ ኃይለ ቃል፣ የሥራ ቅጥር፣ ወይም የዚያን ማኅበረሰብ ቁስል የሚቀሰቅሱ ያስገኝልኛል የሚሏቸውን አጀንዳዎች በማራገብ የፖለቲካ ወረት ይሰበስባሉ። ይህንን የፖለቲካ ወረት በመጠቀምም ወደ ሥልጣን ለመውጣት፣ በሥልጣን ለመቆየት፣ ወይም ሥልጣናቸውን ለማደራጀት ይሞክራሉ።

የፖለቲካ ግብይቱ በማንነት ሸቃጮችና በሕዝብ መካከል ብቻ የሚደረግ አይደለም። ይልቁንም በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ ተቋማዊነትን በሚገድል ሁኔታ የማንነት መረብን ለግል ሥልጣን ማደራጃ የማድረግ ጥረቶች በሰፊው ይታያሉ። በሀገራችን ማንነትን እየጠቀሱና ራስን የብሔርና የሃይማኖት ወኪል በማድረግ፣ የማንነት መረብን በመጠቀምና በማስፋት፣ ፖለቲካዊ ሥልጣንን የማደላደልና ጥቅምን የማጋበስ ዝንባሌዎች እየጎለበቱ መጥተዋል።

በእንዲህ ዓይነት የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ውሳኔዎች የሚወሰኑት የማንነት መረብን በመጠቀም ነው። እንዲሁም ድጋፍና ተቃውሞ የሚደረገው ግለሰቡ የማንነት ብራንዱን ባስተዋወቀበት መጠን ይሆናል። በመሆኑም ሰዎች ብቃታቸውን ከማሻሻልና በጥረታቸው ለውጥ ከማምጣት ይልቅ፣ በአቋራጭ የማንነት ንግዱን ይቀላቀላሉ። በብቃታቸው ሳይሆን በማንነታቸው፣ በልፋታቸው ሳይሆን በገበያው ውስጥ ባላቸው መረብ አማካኝነት ሥልጣናቸውንና ጥቅማቸውን ያደላድላሉ።

ይህ የፖለቲካ ገበያ ሂደት ግለሰቦች ማንነታቸውን እንደ ገንዘብ በመጠቀም የሚፈልጉትን ለማሰባሰብና ውሳኔዎችን ለመወሰን ማንነትን እንደ ከረሜላ ለማባበያነት የመጠቀም ድጋፍና የሥልጣን ኮርቻ የሚያማትሩበት ነው። በፓርቲዎች ውስጥም ድጋፍን ይታያሉ።በመንግሥት ውስጥም የማንነት መረብን በመዘርጋት በማንነት ዝንባሌዎች በሥልጣን እያደጉ ለመሄድ፤ ጠንካራ አዝማሚያዎች ይታያሉ። ድርጊቶችና ውሳኔዎች ምን ስም ድጋፍን ለማሰባሰብ፣ ውሳኔዎችን ለመወሰን፣
ሥልጣንን ለማደላደልና ለማስጠበቅ፣ ውጤት ያስከትላሉ? በሚል ሳይሆን፣ ከገበያው ደንበኞቼ ምን ድጋፍ ያስገኝልኛል? በሚል የሚካሄዱ ይሆናሉ።

በፖለቲካ ገበያ ውስጥ ማንነት እንደ ገንዘብ ብዙ ድጋፍ ለመግዛት ያስችላል እንጂ በራሱ ምንም ትርጉም የለውም። ምክንያቱም የፖለቲካ ነጋዴዎቹ ዋነኛ ዓላማ በማንኛውም አቋራጭ መንገድ ሥልጣንን ማደላደል እንጂ፣ ማንነትን

CamScanner

ለሚያቀነቅኑለት ቡድን መቆም አይደለም። ስለሆነም ትርፋቸውን የሚያስገኝ እስከሆነ ድረስ ከማናቸውም ቡድኖች ድጋፍ ለማሰባሰብ መረብ ይዘረጋሉ። ጠበቃነታቸውን ለብሔር ያስመስሉ እንጂ የጥቅም ሸሪኮቻቸው ድጋፍ ለማግኘት እንዲችሉ ከማንኛውም ባለሥልጣን ሰፊ ፖለቲካዊ የንግድ ግንኙነት አላቸው። በፖለቲካ ገበያው ውስጥ ትርፍ ሊያስገኝላቸው የሚችለውን፣ በሥልጣንና በጥቅም ሊደግፋቸው የሚችለውን ማንኛውንም አካል ይወዳጃሉ።

ከዚህ አካል የሚያገኙት ትርፍ ሲሟጠጥ ወይም ይህ አካል የገበያ ዋጋው የቀነሰ መስሎ ከታያቸው፣ ሌላ የትርፍ መረብ ይፈልጋሉ። የውጭ ኃይሎች ደግሞ የካበተ የፖለቲካ ልምዳቸውንና የፖለቲካ ገበያ ረቂቅ ተሞክሯቸውን ይዘው ይህንን የማንነት ገበያ ከተለያየ ማዕዘን ይቀላቀላሉ። በሀገራችን ውስጥ የማንነት ሸቀጥ እንዳይቆም፣ ብሎም በሕዝቡም ሆነ በመንግሥት ውስጥ ማንነትን መሠረት ያደረገ ተጽዕኖና ትርፍ ለማግኘት፣ ገንዘባቸውንና ዕውቀታቸውን ይረጫሉ።

# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## 13. የሐሳብ ገበያ

አንድ ሰው ተሹሞ በመገናኛ ዜናው ሲሰማ በብዙኃኑ ዘንድ የሚነሱት የመጀመሪያዎቹ ጥያቄዎች ብሔሩ ምንድነው፤ ሃይማኖቱስ፤ ሠፈሩስ እያለ ማንነቱን የሚያጣሩ ናቸው። በአብዛኛው ከነአካቴው የማይነሡ፤ ከተነሡም ከማንነት ማጣራት

ቀጥሎ የሚዘሩ ከዚህ በፊት ምን ሠርቷል፤ ለቦታው ብቁ ነው ወይ? ምን ልምድ አለው የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህ የማንነት ጥያቄዎች ቀድመው የሚመጡበት ምክንያት፤ ልሂቃኑ በሰውዬው ላይ የሚኖራቸው እምነት የሚመነጨው ከማንነቱ በመሆኑ ነው።

የሐሳብ ገበያ ማለት አንድ ሐሳብ ከአቅራቢው ማንነት፣ ሥልጣን ወይም የኋላ ዳራ ተለይቶ በመቅረብ፣ ልክ እንደ ሸቀጦች ሁሉ፣ በሐሳብ ልውውጥ የተሻለ ተቀባይነት የሚያገኝበት መንገድ ነው። መነሻው የነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ሐሳብ ነው። በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ የተለያዩና ብዙ ሸቀጦች ይቀርባሉ። ሰዎች አሳቢዎችና በምክንያት የሚንቀሳቀሱ ስለሆኑ፣ አመዛዝነውና መርጠው የተሻለውን ሐሳብ ይመርጣሉ።

የሐሳብ ገበያ፣ ፖለቲካዊ እምነትና ይሁንታ ከማንነት ሚዛን ሳይሆን፣ ከሐሳብና ከውጤት ሚዛን የሚመነጭበት ፖለቲካ ነው። ፖለቲካና ፖለቲከኞች በውጤትና በውጤታማነት የሚመዘኑበት ነው። ሐሳብ ተመዝኖ፣ ተዋዳድሮ፣ ተግባብቶና ዳብሮ፣ ነጥሮ የሚወጣበት ነው። ይህ ዓይነት ፖለቲካ በተለያዩ አማራጭ የዕይታ ማሕቀፎችና ንድፎች መካከል ውድድርና ትብብር የሚደረግበት ምኅዳር ወይም ሜዳ ነው። የሐሳብ ገበያ ለተለያዩ አማራጭ ሐሳቦችና ዕውቀቶች ክፍት የሆነ የፖለቲካ ምኅዳር አለበት። በእነዚህ አማራጭ ሆነው በቀረቡ ሐሳቦች መካከል በሚደረግ ውድድር አሸናፊው በሕዝብ ይሁንታና ውሳኔ የሚለይበት ነው።

የሐሳብ ገበያ ለውድድር ብቻ ሳይሆን ለትብብርም ክፍት የሆነ ምኅዳር ነው። በሐሳቦች መካከል የሚደረግ አመክንዮአዊና ሰላማዊ ውድድርና ትብብር የማኅበረሰቡን ፍላጎት ለማሳካትና መግባባት ለመፍጠር የሚያስችሉ የጠሩና የጎለበቱ ሐሳቦች እንዲወለዱ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። ሁሉም ሐሳቦች ወደ ገበያው ቀርበው በአመክንዮአዊ ውይይትና የሐሳብ ፍጭት ይሞረዳሉ። በሚያስማሙ ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመሥራት የሚያስችል ምቹ ምኅዳርም ይፈጠራል። በማያስማሙ ጉዳዮች ደግሞ በሐሳብ ውድድር አሸናፊው በሕዝብ ዘንድ ባገኘው ቅቡልነት ይለያል።

ፖለቲከኞች

የሕዝብን ፍላጎት ማዕከሉ ባደረገ ፖለቲካ ውስጥ፣ ሐሳብ የሕዝብ ፍላጎትን ይወክላል። ፖለቲከኞች የሕዝብን ይሁንታ የሚያገኙት የሕዝቡን ፍላጎት ለማሟላት በሚያቀርቧቸው አጀንዳዎች ነው። ሕዝብም ከሚቀርቡት አጀንዳዎች መካከል

CS CamScanner

ፍላጎቴን የተሻለ ያሟላልኛል ለሚለው ድጋፍ ይሰጠዋል። በዚህ ዓይነት የሐሳብ ገበያ ውስጥ፣ ከፖለቲካ ገበያ በተለየ ድጋፍና ይሁንታ፣ ትብብርና ፉክክር እንዲሁም ታማኝነት በሐሳብ ላይ ከሚኖር ስምምነትና እምነት ይመነጫል። የሐሳብ ገበያ ሐሳቦቹ በተግባር ሊያመጡት ከሚችሉትና ያመጣሉ ተብሎ ከሚታመነው ውጤት አንጻር ተመዝነው የሚሸለሙበት ነው።

የሐሳብ ተዋጽዖና መዋጮ አለበት። የተለያዩ ሐሳቦች ተደጋግፈውና ተናብበው ሀገር " የሐሳብ ገበያ በአማራጭ ሐሳቦች መካከል ውድድር የሚደረግበት ፖለቲካ ብቻ አይደለም። የሚመሩበት ነው። ተፎካካሪዎች፣ መገናኛዎች፣ ምሁራንና ሌሎች ተዋንያን በምክንያት ላይ በተመሠረተ ትችትና ድጋፍ በፖሊሲዎች ላይ ተጽዕኖ ያደርጋሉ። በሐሳብ ተዋጽዖ ዳብሮና ነጥሮ በወጣ የተሻለ ሐሳብ ሀገር ይመራሉ። በዋናነትም እንደኛ ዓይነት የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ባልተጠናቀቀባቸውና በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ስምምነት በሌለባቸው ሀገራት፣ የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ለመፍጠር
የተለያዩ ሐሳቦች ውክልናና ተዋጽዖ እጅግ ቁልፍ ነው።

የለውጡ መንግሥት ከመነሻው የፖለቲካ ገበያን ለማዳከምና የሐሳብ ገበያን ለማጎልበት ሊሠራ ነበር። የፖለቲካ ገበያውን ለማምከን ሁለት መንገዶችን እየተከተለ ነው። መሸሸጊያ ማሳጣትና ሚዛንን መጠበቅ ናቸው፡

መሸሸጊያ ማሳጣት፡- የፖለቲካ ገበያ ዋናዎቹ መሸሸጊያዎች የሃይማኖትና የብሔር ካባዎች ናቸው። እነዚህ ሁለት ካባዎች

ከመሸሸጊያነት ነጻ የሚሆኑት በነጻነትና በሕግ ነው። | ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ማንነትን ዕውቅና የመስጠትና የብሔር መለያዎችን የመጠቀም ችግር አሁን የለም። ሕጉም ባህሉም፣ ሥርዓቱም ዳብሯል። በዚህ ረገድ የተሟላ ነጻነት እንዲኖር ተሠርቷል።

ይህ ነጻነት ግን በሕግ የሚመራ ነጻነት መሆን አለበት። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ነጻነትን የማስተዳደር ፈተና ስለሚገጥም። የብሔር ማንነትን የማስከበርና የመጠቀም ነጻነት የሌላውንም ከማክበር ግዴታ ጋር አብሮ ይሄዳል። የሌላውን ለማክበር ደግሞ የሁሉንም ብሔሮች መብት በማዕከል የሚያስከብርና ተመጣጣኝ መድረክ የሚሰጥ ሀገራዊ ማሕቀፍ ያስፈልጋል። ይህ ማሕቀፍ መፈጠር ያለበት በሕግና በተግባር ነው። በሕግ ተደንግጎ ተግባራዊ እንዲደረግ የፖለቲካ ቁርጠኝነትን በማሳየት። ሁለተኛው መፍትሔ የሚመጣው በዚህ ጊዜ ነው። ሀገራዊ ማንነትንና አካባቢያዊ ማንነትን በሚዛን ይዞ የመጓዝ መፍትሔ።

ሚዛን መጠበቅ፡- አካባቢያዊ ማንነቶች ያለ ሚዛን ጎልተው እንዲወጡ ከተደረገ ሁለት አደጋዎች ይከሠታሉ። የመጀመሪያው በተለያዩ ማንነቶች መካከል የሚኖር አላስፈላጊ ይፈጥራል። ለፖለቲካ ገበያተኞችም ምቹ ሁኔታ ያስገኛል። ሁለተኛው አደጋ ሀገራዊ ፉክክር ነው። ከላይ አግላይነት ያልነው ይሄንን ነው። ይሄም የብሔር ሽኩቻንና ግጭትን ማኅበረሰብ የመመሥረት ዕድልን ያጠፋል። ለዚህ መፍትሔው ሀገራዊ ማንነትንና ማንነትን እንዲቀጭጭና እንዲጠፋ ማድረጉ ነው። ይህ ደግሞ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አካባቢያዊ ማንነትን በሚዛን ይዞ መጓዝ ነው።

እንደኛ ባለ ብዝኃ ማንነት ባለበት ሀገር፣ ሀገራዊ ማንነት በራሱ ብቻውን የሚቀነቀን ከሆነ ሁለት አደጋዎች ያመጣል። የመጀመሪያው ሐሳዊነት ነው። የኢትዮጵያ መልክና ጠባይ ብዝኃነት ነው። የቋንቋ፣ የእምነት፣ የባህል፣ የሥልጣኔ፣ የአኗኗር

ዘይቤ፣ ወዘተ. ብዝኃነት ከጥንትም አለ። ይህ ብዝኃነት ዛሬም አለ። የምትገነባው ኢትዮጵያ ይህንን ብዝኃነት የምትመስል መሆን አለባት። ከዚህ ውጭ ለመሆን ካሰበች ሐሳዊነት ይነግሥባታል። የሚወጡት ፖሊሲዎች፣ ሕጎችና አሠራሮች ከዚህ እውነታ ጋር ስለሚጋጩ ሀገርን ከመገንባት ይልቅ የውዝግብ፣ የጭቅጭቅ፣ የመብት ክርክርና ያለመግባባት መነሻዎች ይሆናሉ። ይሄም የአካታችነትንና የፍትሐዊነትን ጥያቄ እያስነሣ፣ የሀገረ መንግሥት መዳከምን ያስከትላል።

CamScanner

ሁለተኛው ጠቅላይነት ነው። ጠቅላይነት ማለት ሁሉንም ጠቅልሎ በአንድ ከረጢት መክተት፣ በአንድ ዓይን መመልከት፣ በአንድ መስክ ማሠማራት ነው። አግላይነት ለብዝኃ ማንነት ቦታ የሌለው ምኅዳር ይፈጥራል። በዚህ ጊዜ እዋጣለሁ፣ ወይም ማንነቴን ላጣ ነው ብሎ የሚሠጋው አካል ወደ ትግል እንዲገባ ያደርገዋል። ይሄም የማኩረፍ፣ የመነጠልና የመገንጠል ሐሳቦችን በማበረታታት፣ ሀገረ መንግሥቱን አደጋ ላይ ይጥለዋል።

እነዚህን ፈተናዎች የመፍቻ ቁልፍ መንገድ አድርጎ የለውጡ መንግሥት እየተጠቀመ ያለው "ሚዛናዊነት" ን ነው። በሀገራዊ

ማንነትና በአካባቢያዊ ማንነት፤ በብሔር ተዋጽዖና በሜሪት፤ ወዘተ. መካከል ሚዛኑን ጠበቆ መጓዝ። ይህንን ሚዛን ደግሞ በሕግ መደንገግና መተግበር ነው።

የፖለቲካ ገበያ የሚጠቀምበት አንዱ ካባ የሃይማኖት ካባ ነው። ይህንን ካባ እንዲያወልቅ ለማድረግ የሃይማኖት ተቋማት በነጻነትና በሕግ እንዲሠሩ እየተደረገ ነው። ቀደም ብሎ መንግሥት በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ገብቶ መሪዎችን ራሱ እስከ መምረጥ ይሄድ ነበር። ሃይማኖታዊ አደረጃጀታቸውን ይወስን ነበር። ይህ በለውጡ ጊዜ ቀርቷል።

የሃይማኖት ተቋማት ዘመናትን ያስቆጠሩ ተቋማት ናቸው ብሎ መንግሥት ያምናል። ሕግን አክብረው፣ በነጻነታቸው ተጠቅመው መንቀሳቀስ አያቅታቸውም የሚል እምነት አለው። መንግሥት በሴኩላሪዝም መርሕ ለሁሉም እምነቶችና

(እምነትም ለሌላቸው) ምቹ ምኅዳርን መርሕን የጠበቀ ትብብር ይኖራል። በሰላም፣ በማኅበራዊ ልማት፣ በሀገር ገጽታ ግንባታ፣ ይፈጥራል እንጂ የትኛውንም እምነት አያራምድም። በሁለቱ መካከል ሕገ መንግሥታዊ በቅርስ ጥበቃ፣ በቱሪዝም ልማት፣ በዕሴትና በሞራል ማስከበር፣ ወዘተ. ተባብረው ይሠራሉ። | በሌሎች ጉዳዮች ደግሞ በየድርሻቸው ሕግ የሚፈቅድላቸውን ያከናውናሉ።

ይህ ግን በረከት ብቻ ሳይሆን ፈተናም አስከትሏል። በረከቱ ነጻነት አግኝቶ በሃይማኖት አስተምህሮ፣ በሕግና በሥርዓት የመመራት ሙሉ መብት በመገኘቱ ነው። ፈተናው ደግሞ ነጻነትን ካለመልመድ የሚመጣው ነጻነትን የማስተዳደር ፈተና ነው። ከለውጡ በፊት የአደረጃጀት ጥያቄ የነበራቸው የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮችና የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ። የሁለቱም ጥያቄ በሕግ ተመልሷል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የነበረባቸውን ለሁለት የመከፈል አደጋ ለመፍታት በተሠራው ሥራ አንድነታቸውን አጠናክረዋል።

ይህንን ዕድል በመጠቀም ረገድ በተፈጠረው ነጻነትን የማስተዳደር ፈተና የተነሣ፣ ሃይማኖታዊ ተግባርን ከፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ጋር አጃምሎ ለመሄድ የተሞከረበት ጊዜ አለ። ይህ የሆነው ሃይማኖቶቹ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴውን ስለሚያስተምሩ ወይም ስለሚፈቅዱ አይደለም። የፖለቲካ ገበያተኞቹ የሃይማኖትን ካባ ለብሰው ስለሚንቀሳቀሱ ነው። በዚህ ጊዜ ወሳኙ መፍትሔ የፖለቲካ ገበያተኞቹን ከሃይማኖተኞች የሚለይ የማስተማርና ሕግን የማስከበር ሥራ መሥራት ነው።

ችግሩን ለመፍታት ከሃይማኖት አባቶችና ከማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገዋል። የሃይማኖት ካባን አጥልቀው የሚሠሩ ፖለቲከኞችን ራሳቸው አማኞቹ ካባቸውን እንዲነጥቋቸው ለአማኞች ዕድል ተሰጥቷል። ከአማኞች ዐቅም በላይ የሆኑትን ደግሞ መንግሥት ሕግን በማስከበር ኃላፊነቱ የግድ ካባቸውን እንዲያወልቁ አድርጓቸዋል።

አሁን ባለችው ኢትዮጵያ የሐሳብ ገበያ ባህል እንዲሆን እየተሠራ ነው። ለዚህ ሦስት መንገዶችን መንግሥት እየተከተለ ይገኛል። ሀገራዊ ምክክር፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክክርና የሕዝብ መድረኮች።

ሀገራዊ ምክክር፡- በሀገራችን የሚደረገው ሀገራዊ ምክክር የተለያዩ ሐሳቦች በአንድ መድረክ ቀርበው፣ በውይይትና በምክክር ጎልብተው፣ አሰባሳቢና አስማሚ ሆነው የሚወጡበት መድረክ ነው። ሁሉም ስለ ሀገር የሚያገባው አካል

CamScanner

በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ አዋጥቶና ተነጋግሮ መግባባት የሚፈጥርበት ምኅዳር ነው። በውይይትና በምክክር ወደ መግባባት የሚደረስበት መንገድ ነው።

በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ከገጠሙን እጥረቶች አንዱ ሀገራዊ ምክክር ነው። በሀገረ መንግሥት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ሕዝብ ተመካክሮ፣ የጋራ መግባባት ላይ ደርሶ፣ የተግባባባቸውን በሕግና በሥርዓት አጽንቶ፣ ያልተግባባባቸውን ደግሞ ለወደፊት ምክክሮች አቆይቶ አልተጓዘም። በዚህ የተነሣ በየጊዜው ቅሬታ፣ ኩርፊያ፣ አብዮት፣ ዐመጽ ይፈጠራል። ነገሮች በተናጠል እየቀረቡ ለፖለቲካ ነጋዴዎች ምቹ ሁኔታ ይመቻቻል። ሁለንተናዊ ዕይታ ይጠፋል። ሀገራዊ ምክክር ይሄን

የዘመናት ስብራት የሚጠግን ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክክር፦ ገዥው ፓርቲ ተፎካካሪ ሐሳቦችን በተመለከተ ሁለት መንገዶችን ይከተላል። የመጀመሪያው ተፎካካሪ ሐሳብ የሚኖራቸውን የተፎካካሪ ፓርቲ አባላትና ሌሎች ግለሰቦች በመንግሥት ሥርዓት ውስጥ ማካተት ነው።በዚህም ሐሳቦቻቸው በፖሊሲዎች፣ በሕጎችና በአሠራሮች ውስጥ ለሐሳብ ገበያ ቀርበው ተጽዕኖ የሚያሳድሩበትን መንገድ አመቻችቷል። ሁለተኛው ደግሞ በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤትና በሌሎች መድረኮች አማካኝነት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ውይይቶችን ማድረግ ነው። በመንግሥት ፖሊሲዎችና አፈጻጸሞች ላይ ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ጋር መንግሥት ተደጋጋሚ ውይይቶችን አካሂዷል። የእነዚህ ውይይቶች ዓላማ የተፎካካሪዎች ሐሳቦች የሀገር ሐሳቦች ሆነው እንዲካተቱ ለማድረግ ነው።

የሕዝብ መድረኮች፦ ምልዐተ ሕዝቡ በሐሳብ ገበያ እንዲሳተፍ ለማድረግ ከፌዴራል እስከ ወረዳ ድረስ በመንግሥት ሐሳቦች፣ ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች ላይ ተደጋጋሚ ውይይቶች ከሕዝቡ ጋር ተደርገዋል። ከውይይቶቹ የተገኙ ሐሳቦች ተለቅመው የፖሊሲ፣ የሕግና የአሠራር ግብአቶች እንዲሆኑ ይደረጋሉ፡ ሕዝብ ለሚያነሣቸው ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ፈጣን ማስተካከያዎችም ይወሰዳሉ።

የሐሳብ ገበያ በመታገያ አጀንዳውና በመታገያ መንገዱ የተለየ ነው። አንደኛ፣ የመታገያ አጀንዳው አማራጭ ሐሳብን በማቅረብ ላይ የተመሠረተ ነው። ማንኛውም ሐሳብ የሚሳተፍበት ክፍትና አሳታፊ ነው። የሐሳብ ገበያተኞች ሕጋዊ

መሥፈርቱን የሚያሟሉና ማኅበረሰቡን የሚጎዱ እስካልሆኑ ድረስ"፣ አለኝ የሚሉትን ሐሳብ ይዘው በገበያው መሳተፍ ይችላሉ። እንደ ገበያው ጥንካሬ፣ በሚቀርቡት ሐሳቦች ጥራትና ውድድር፣ ሕዝብ የተሻሉ አማራጮችን ማግኘት ይችላል።

ሁለተኛው፣ ሰላማዊ ውድድር ነው። የሸቀጥ ነጋዴዎች በዋጋ፣ በጥራትና በሌሎች መንገዶች ተወዳድረው ገበያን ለማግኘት ይሞክራሉ። መርጦ ያዋጣኛል ያለውን ምርት መግዛት የገበያተኛው ውሳኔ ነው። በዋጋ ወይም በጥራት ተበልጦ የገበያ ብልጫ የተወሰደበት ነጋዴ፣ የተወሰደበትን ብልጫ ለማስመለስ ዋጋውና ጥራቱን አሻሽሎ እንዲሁም ማስታወቂያ አሠርቶ ሊመጣ ይችላል። ሌላኛውን ነጋዴ አስፈራርቶና ኃይልን ተጠቅሞ ገበያን ሊያገኝ ግን አይችልም።

በሐሳብ ገበያ ውስጥ ሥልጣን የሚመነጨው ከሕዝብ ይሁንታ ነው። ሥልጣንን ለማግኘት የሚሠሩ የፖለቲካ ኃይሎች ከሌሎች ጋር ተወዳድረው የሕዝቡን ቀልብና ይሁንታን ማግኘት የሚችሉት በያዙት ሐሳብና ያንንም ለሕዝብ በተገቢው መንገድ አድርሰው ተቀባይነት በማግኘት ነው። ከተወዳዳሪዎች መካከል ያዋጣኛል ያለውን መምረጥ የሕዝቡ ውሳኔ ነው። የሕዝቡንይሁንታ ያገኘው የተሰጠውን ይሁንታ ለማስቀጠል ይተጋል። ይሁንታን ያላገኘውም በቀጣይ ተቀባይነትን ለማግኘት እንደገና ይተጋል። ከዚህ ውጭ የሐሳብ ገበያ ሥልጣን ያገኘው ሥልጣኑን አስጠብቆ ለመቆየት፣ ሥልጣን ማግኘት ያልቻለው ደግሞ በሐሳብ ሜዳው የደረሰበትን ሽንፈት ለማካካስ ኃይልን እንደ አማራጭ የሚጠቀሙበት ግንባር አይደለም።

CamScanner

የሐሳብ ገበያ በሐሳብ ተጀምሮ በሐሳብ የበላይነትን ለማግኘት እንጂ ልዩነትን ለማጥፋት የሚደረግ ትግል መሆን የለበትም። የሐሳብ ገበያ በንግግርና በውይይት ወደ ስምምነት የሚደረሱበት ወይም የጋራ የሆነ እውነት የሚፈጠርበት መንገድ ነው። ወደ እዚህ ስምምነት ለመድረስ የሚያስችለው ቁልፍ መንገድ ደግሞ የሐሳብ ልዩነትን በማክበር፣ በመደማመጥና በመነጋገር

መግባባት ሲቻል ነው። "እኔ ያልኩት ካልሆነ" ከሚል ብሂል በመውጣት፣ የሐሳብ ልዩነቶችን በማክበር፣ በመደማመጥና በመነጋገር ሐሳብ እንዲያሸንፍ መፍቀድ ወይም ወደ ጋራ ሐሳብ መድረስ ስንችል ነው።

በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባትና በሐሳብ ላይ የተመሠረተ ፖለቲካን ለማዳበር ዋነኛው ፈተና ያልተለወጠ የትግል ስልትና ያልዳበረ የፖለቲካ ባህል ነው። የዴሞክራሲ ምኅዳርን በማስፋት የተለያዩ ሐሳቦች እንዲደመጡ፣ ዴሞክራሲያዊ ምርጫን በማድረግ ሥልጣን በሕዝብ ድምፅ ብቻ እንዲገኝ ለማድረግ የተደረገው ጥረት፣ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ያለፈ ነው።

በሀገራችን ያለው ፖለቲካዊ እውነታ ሐሳብ እንዲያሸንፍ ሳይሆን ኃይል እንዲያሸንፍ የሚያስችል ነው። ይህ ከነባር ባህልና ከፖለቲካ ባህል ይመነጫል። በነባሩ ባህል ገዳይ  አሸናፊ ነው። ገዳይ ጀግና ነው። የተሻለ የውይይትና የክርክር ባህል የነበራቸው ማኅበረሰቦች እንኳን ይሄንን ባህል ማስጠበቅ አልቻሉም።

ነገሥታቱ ሥልጣን የሚወስዱት እርስ በርስ በመጠፋፋት ነው። የጠመንጃ ባህል · የበላይነቱን ወስዷል። የተሻለው ተንኮለኛና ሤረኛ ነው ዕድል የሚያገኘው። ዘግይቶ የመጣው ዘመናዊ የፖለቲካ ባህልም ፖለቲካውን ጠመንጃ አስታጥቆ ነው የመጣው። መደምሰስን፣ ማስወገድን፣ ማውደምንና በሌላው መቃብር ላይ መቆምን የፖለቲካ ባህል የተማሪዎች ንቅናቄና እርሱን ተከትሎ የተፈጠረው የፓርቲ አደረጃጀት ርምጃ መውሰድን፣ እንዲሆን አድርጓል። ቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር የመጡት ዘመናዊ የፓርቲ ፖለቲካ ተጀምሮ አምስት ዓመት እንኳን ሳይሞላው ነው።

የሐሳብ ልዩነትን በሐሳብ ላይ ከሚደረግ ሰላማዊ ውድድር(ማለትም ልዩነትን አክብሮ ተደማምጦና ተነጋግሮ ከመስማማት ወይም ተቻችሎ ከመውጣት) ይልቅ የሐሳቡን ባለቤት በኃይል በማጥፋት የበላይ ሆኖ ለመውጣት የሚደረገው ጥረት

የግጭት አዙሪት ውስጥ የሚከት ነው። ዘመናዊው የፖለቲካ ባህላችንም በዚህ ሾተላይ የተያዘ ነው። የፖለቲካ ተዋንያን ወደ ስምምነት የሚደርሱት ወይም የሐሳብ የበላይነትን ማረጋገጥ የሚችሉት የኃይል የበላይነትን ፈጥረው አይደለም። በመደማመጥና በመነጋገር ሐሳብን በሐሳብ በማሸነፍ ተቀባይነትን አግኝተው ነው።

ይህ ዓይነቱ የሐሳብ ውድድር ሁለት ቁልፍ ነገሮችን ይሻል። የመጀመሪያው፣ የአብዛኛውን ሕዝብ ቅቡልነት አግኝቶ የመምራት ዕድልን ያገኘው ሐሳብ፣ ሌሎች ሐሳቦችን የሚያከብርና እንዲደመጡ ቦታ የሚሰጥ መሆን አለበት። ሁለተኛው፣ በሐሳብ ተበልጠው የመምራት ዕድልን ያላገኙት ደግሞ ሽንፈትን በጸጋ መቀበል የሚችሉ መሆን አለባቸው። በሐሳብ ገበያ የደረሰውን ሽንፈት በፖለቲካ ገበያ ለማካካስ የሚሠሩ መሆን የለባቸውም።

የዴሞክራሲ ልምምዱ ብዙም ባልገፋባቸው ሀገራት፣ ለዴሞክራሲ መቀልበስና ለሐሳብ ገበያው መቀጨጭ አደጋ ከሆኑ ዋነኛ ምክንያቶች መካከል እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ተጠቃሽ ናቸው። በአብዛኛው ሕዝብ ቅቡልነት ያገኘው ሐሳብ ለሌሎች ሐሳቦች ዝግ መሆን ይጀምራል። እንዲሁም በዚህ ውድድር ውስጥ የብዙኃኑን ተቀባይነት ያላገኙት ቅቡልነትን በኃይል ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ። ሁለቱም የዴሞክራሲ ዕንቅፋት ናቸው።

በሀገራችን የተጀመረው ዴሞክራሲን የመትከልና የማጽናት ሂደት እንዳይቀለበስ፣ እንዲሁም የሐሳብ ውድድሩ ወደ ምንፈልገው ስምምነትና የጋራ እውነት እንዲያመጣን፣

CS CamScanner

የመንግሥት ሆደ ሰፊነት እጅግ ቁልፍ ጉዳይ ነው። በሀገራችን ከተደረጉት ምርጫዎች የተሻለ በነበረውና ለዴሞክራሲ መተከልና መጽናት ትልቅ በር ከፋች ተደርጎ በተወሰደው ምርጫ 2013 ያሸነፈው ሐሳብ መንግሥት ለመመሥረት ችሎ እስካሁን ዘልቋል። ሥር የሰደደ የሀገረ መንግሥት ቅቡልነት ጥያቄ በቀጠለበት ሁኔታ ውስጥ ግን የሚፈለገውን በቂ የጋራ ስምምነት አይፈጥርም።

ለዚህም መንግሥት በምርጫ የተገኘውን ስምምነት ሊያጠናክር በሚችል መልኩ፣ ሌሎች | ሐሳቦች ቦታ ሊያገኙበትና ለሀገር ግንባታው አስተዋጽዖ ሊያደርጉበት የሚችሉበትን በር መክፈት ነበረበት። ከላይ ያነሣናቸውን (የተፎካካሪ ፓርቲ አባላት በመንግሥት ውስጥ ማካተትና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በየጊዜው መነጋገር) እንደ መፍትሔ የተከተልነው ለዚህ ነው። ይህ አካሄድ በተለያዩ ሐሳቦች መካከል አብሮ የመሥራት ባህልን ያዳብራል። ተፎካካሪ ፓርቲዎችም በመንግሥት ውሳኔዎች ላይ ሐሳባቸውን እንዲያዋጡ አድርጓል።

ከዚህም በላይ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ለመፍጠር የሚያስችል ብሔራዊ ምክክር ማድረጉ አስተዋጽዖው የጎላ ነው። በሚያግባቡን ለመሥራት፣ በሚያለያዩን ጉዳዮች ላይ ደግሞ በመነጋገር የጋራ ስምምነት ለመፍጠር ያስችላል።

በሐሳብ የደረሰ ሽንፈትን በሐሳብ ለመቀልበስ መሞከር በሐሳብ ገበያ ውስጥ ለፖለቲካ ዕድገት አስተዋጽዖ የሚያደርግ እጅግ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ከአንድ ምርጫ በኋላ ድምፅ ስላላገኙ የሚከስሙ ሳይሆን፣ በየምርጫው ሐሳባቸው ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚጥሩ ዘመናትን የሚሻገሩ የፖለቲካ ኃይሎች ያስፈልጋሉ፡እነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች ሥልጣን ማግኘትን ብቻ የሞት ሽረት ጉዳይ አድርገው የሚመለከቱ አይደሉም። በየጊዜው በምክንያት ላይ ተመሥርተው ለመንግሥት ፖሊሲዎች ትችትና ድጋፍን በማቅረብ፣ የተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲኖር አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ናቸው።

የፖለቲካ ኃይሎች በዚህ ዓይነት መንገድ ሲንቀሳቀሱ፣ የመንግሥት ሥልጣንን ያዙም አልያዙም ጠንካራ ሀገር ለመገንባት አዎንታዊ ሚና ይጫወታሉ። ነገር ግን የፖለቲካ ኃይሎች በሐሳብ የደረሰ ሽንፈትን በኃይል ለመቀልበስ ጥረት የሚያደርጉ ከሆነ፣ የሐሳብ ውድድር ልምምድን ያቀጭጫሉ፤ ሀገርንም አደጋ ላይ ይጥላሉ።

በኃይል ፍላጎትን የማስፈጸም አካሄድ እስካልተለወጠ ድረስ በፖለቲካችን ውስጥ ሐቀኛ | ለውጥ ለማምጣት አይቻልም። ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት ዋነኛው ደንቃራ | በኃይል ሥልጣንን ለማስጠበቅና ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት ነው። ሥልጣን ሕጋዊና | ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚገኝበትን መንገድ ካላጠናከርን በስተቀር፣ ፖለቲካችን ከአዙሪቱ ሊላቀቅ አይችልም። ፖለቲካችን የተበየነው በማሸነፍና በመሸነፍ ነው። ለመጣጣል እንኳ ተጋግዞ ለመቆም ቦታ የለውም። ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት ምኅዳር፣ ሁሉም ሊደመጥና ሐሳብ ሊያዋጣ የሚችልበት የፖለቲካ ምኅዳር ነው።

### 13.1. የሐሳብ ፖለቲካ ልምምዳችን

ለአሜሪካ ጠንካራ ሀገርነት ትልቁን አስተዋጽዖ ያደረገው ሀገሪቷ የተመሠረተችበት ጥንስስ ነው። በሀገሪቱ ምሥረታ ወቅት ሲደረጉ የነበሩ የሐሳብ ፍጭቶችና ውይይቶች ከዚያ ቀጥላ ለተፈጠረችው ልዕለ ኃያል ሀገር መሠረት የጣሉ ናቸው። ሌሎች ሀገራት በእንደዚህ ዓይነት መልኩ የመመሥረት ሂደት ባይገጥማቸውም፣ በኋላ ላይ በእንደዚህ ዓይነት የውይይት፣ የክርክርና የሐሳብ ልውውጥ ሂደት ራሳቸውን እያጠናከሩ መጥተዋል። የተረጋጋና ጠንካራ ሥርዓትም ፈጥረዋል። በየጊዜው አዳዲስ ሐሳቦችን በማምጣት፣ በዚያ ሐሳብ ላይ በመወያየትና በመከራከር ስምምነትን ፈጥረው፣ በሐሳብ በመወዳደር ሀገራቸውን ማጠናከር ችለዋል።

CamScanner

በፖለቲካችን ውስጥ እንደዚህ ዓይነት የሐሳብ ፍጭት መታየት የጀመረውና እያደገ የመጣው በቅርቡ ነው። ይሄውም የትምህርት መስፋፋት፣ የጋዜጦች መታተምና ሥርጭት እያደገ መምጣትን ተከትሎ ነው። የተለያዩ የፖለቲካ ሐሳቦች በጋዜጦችና በተለያዩ መድረኮች ክርክር ይደረግባቸው ነበር። ሐሳቦቹን ተከትሎ ሐሳቦቹን የሚወክሉ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ስብስቦች ሊመሠረቱ ችለዋል። የነበረው የሐሳብ ክርክርና ውይይት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ያመጣው አዎንታዊ ተጽዕኖ ቀላል የማይባል ቢሆንም፣ ልምምዱ ግን የተለያዩ መሠረታዊ ክፍተቶች ነበሩበት።

የመጀመሪያው የታጠቁ ሐሳቦች መሆናቸው ነው። ቀደም ብለን እንዳየነው ሐሳቦቹ በሐሳብ ገበያ በሐሳብነት ብቻ አልቀረቡም። ሐሳቦቹ ጠመንጃ ታጥቀዋል። የዘመኑ ኮሙኒስታዊ ዕሳቤም ጠላትና ወዳጅ የሚለይ ነው፡ ስለዚህ ጠላትህን በሐሳብ ብቻ ሳይሆን በጠመንጃም ማስወገድን የግድ ይላል። ይህም የሐሳብ ገበያውን የደም ገበያ አድርጎት ሄዷል።

ሁለተኛው ሳያላምጡ መዋጥ ነው። ሐሳቦች የሕዝብን ፍላጎትና ችግሮች ከመወከል ቢሆንም የዚያ ዘመን ክርክሮችና ውይይቶች በሰፊ ንባብ መሠረት ላይ የቆሙ ነበሩ። ይልቅ ከሌላ ቦታና በሌላ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ የበቀሉ ሐሳቦች እንዳለ

የተቀዱበት ነበር። ' ዓይነት በዕውቀት ላይ የተመሠረቱ ውይይቶች ለሐሳብ መዳበርና ለሐሳብ ለውጥ አስተዋጽዋቸው የጎላ ነበር። ነገር ግን ውይይቶቹ ከሀገራዊ ነባራዊ ሐቅ ጋር የተዛመዱ ባለመሆናቸው ተገቢውን ውጤት ሊያመጡ አልቻሉም። ከዚያ በኋላ የሚደረጉ የፖለቲካ ውይይቶችና ክርክሮች ግን ከቀደመው የንባብ ባህልን አልወረሱም ማለት ይቻላል። አሁን አሁን በድኅረ እውነት ፖለቲካ ውስጥ የሚደረጉ ውይይቶች ደግሞ ከንባብና ከዕውቀት የተፋቱ ናቸው።

ሦስተኛው የሐሳብ ልምምዳችን ከሚያቀራርቡንና ልንሠራባቸው ከምንችላቸው ብዙ ጉዳዮች ይልቅ ለልዩነት ቦታ የሚሰጥ መሆኑ ነው። በዘመኑ የነበሩት ሁሉም ኃይሎች የሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለም ተከታይ ነበሩ ማለት ይቻላል። የመረጡት መንገድ ግን ከሚያስማሟቸው እልፍ አእላፍ ጉዳዮች ይልቅ አነስተኛ ልዩነቶችን አጉልቶ የሚያሳይ ነበር። የሀገራችን የፖለቲካ ባህልም ከዚህ ከሁለተኛው የሐሳብ ልምምዳችን ባሕርይ ጋር የተዛመደ ነው። ለጥቃቅን ልዩነቶች ቦታ የሚሰጥና የሐሳብ ልዩነቶችን በሐሳብ የማስታረቅ ክፍተት ያለበት ነው።

ሐሳብ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ውስጥ የሚሰጠው ቦታ ተፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት እጅግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ሐሳብ የማንኛውም ውጤትና ምርት ጥንስስ ወይም መጀመሪያ ነውና። ውጤት የጠራ ሐሳብ ፍሬ ነው። ሐሳብ ደግሞ ተፋጭቶ፣ ጠርቶና ነጥሮ ሊወጣ የሚችለው አዲስ ሐሳብን ለመቀበልና ለማመንጨት ዝግጁ የሆነና ለሐሳብ በቂ ቦታና ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ ማኅበረሰብ ሲኖር ነው።

በፖለቲካችን ውስጥ ሐሳብ ተፋጭቶ ጠርቶና ነጥሮ የሚወጣበት ምኅዳር ደካማ በመሆኑ ፖለቲካችን በሐሳብ ድርቀት ይፈተናል። በአንድ በኩል ተቀባይነትን ለማግኘት በፖለቲካችን ውስጥ ከሐሳብ ይልቅ ማንነትና የተለያየ ብሔርተኝነት ትኩረት የሚስብ ነው። በዚህም ከሐሳቡ ይልቅ የሰውየው ማንነት ትኩረትን ያገኛል። በሌላ በኩል ለሐሳብ ልዩነትና የሐሳብ ልዩነትን ለማስተናገድ የሚመረጠው መንገድና ዘዴ ሐሳብ ነጥሮ እንዲወጣ የሚያስችል አይደለም። ሐሳቦች የተራራቁና አክራሪነት የተጣባቸው ሲሆኑ፤ ገር የሐሳብ የበላይነትን ለማረጋገጥ የሚደረገው ጥረት የኃይል የበላይነትን ምርጫው ያደረገ ነው። ይህም በመሆኑ የተለያዩ ሐሳቦች የመደመጥና ሐሳብ በሐሳብ ተፋጭቶና ጠርቶ፣ የተሻለው ሐሳብ የሚወጣበትን ዕድል አምክኖታል።

ፖለቲካችን በዋናነት ስሜትን በሚቀሰቅሱ ትንታኔዎች የተመሠረተ ሆኗል። አዲስ ሐሳብን የማምጣትና በሐሳብ የመሸናነፍ ክፍተት ገጥሞታል። ዘመኑን የሚመጥን አዲስ ሐሳብ ክርክሮች ትኩረታቸው ችግሮችን እንዴት እንሻገር ከሚለው ይልቅ ትናንት ላይ የተጠመዱ ከማመንጨት ይልቅ ትናንትን በማወደስና በመተቸት ላይ የተመሠረተ ነው። የፖለቲካ ናቸው። ድጋፎችም ይሁኑ ትችቶች፣ ትብብሮችም ይሁኑ ውድድሮች በማንነትና በትናንት፣ በአክራሪ ብሔርተኝነት ጥላ ሥር የሚወድቁ ናቸው።

CS CamScanner

ከዚህ ዓይነት ፖለቲካ በመላቀቅ ሐሳብን ቦታ የሚሰጥ ፖለቲካና ማኅበረሰባዊ ባህል ትብብርና ውድድር፣ ለአንድ የፖለቲካ ሥርዓት ዕድገትና መረጋጋት እጅግ ቁልፍ ነው። ማዳበር ያስፈልጋል። ሐሳብን ተመሥርቶ የሚኖር ምክንያታዊ ድጋፍና ትችት እንዲሁም ይህ ዓይነት ፖለቲካ ከአብሮነትና ከውጤት አንጻር አስተዋጽዖው የላቀ ነው። አንደኛ፣ ሐሳብ የሚያቀራርቡ ዕሴቶችን ይፈጥራል። የሐሳብ ፖለቲካ ማንነትን የተሻገሩ አብሮነትንና ትብብርን በመፍጠር፣ በተለያዩ ማንነቶች ዙሪያ መቀራረብና አንድነት እንዲጠነክር ያደርጋል።

ሁለተኛ፣ የሐሳብ ገበያ የተለያዩ ሐሳቦች በሐሳብ ፍጭት ተፋጭተው የጠራና የዳበረ ሀገር የሚያሻግር ሐሳብ እንዲወጣ ያደረጋል። ጠንካራ ተቋማትና ሥርዓት የሚገነባው በተለያዩ ሐሳቦች ፍጭት ነጥረው በሚወጡ ሐሳቦች ላይ ነው። ሦስተኛ፣ የሐሳብ ገበያ ለውጤታማነትና ለቅልጥፍና ቦታ ይሰጣል። ማኅበረሰቡ ሐሳቡን ስላነገበው ሰው ማንነት አይጨነቅም።

ጉዳዩ ሐሳቡ ያሻግራል ወይ? መሬት ላይ ወርዶ ፍሬ ያፈራል ወይ? በሚለው ላይ ነው። ይህም ፖለቲከኞች ከማንነታቸው በላይ ለውጤት ትጋት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ውክልና ሲነሣ "የኔ ማንነት" ከሚለው በዘለለ "የኔ ሐሳብ" ወደሚለው ያደላል። ነገሩንም ምን ውጤት ይዞልኝ መጣ? እና ምን ይዞልኝ ሊመጣ ይችላል? በሚለው ይመዝነዋል።

### 13.2. እውነትና ዕውቀት

ለሐሳብ ገበያ መሞቻው ሐሰትና ስሜት ሲሆን፣ መዳኛው እውነትና ዕውቀት ነው። በሐሳብ ለመወዳደር የሚያስችል ክፍት ምኅዳርን የሚያቀጭጨው ሐሰትና ስሜት ነው። በድኅረ ለውጥ ዓመታት የተዘጉ መገናኛዎች ተከፍተው፣ ፖለቲከኞች

ከእሥር ተፈተውና ከያሉበት ወደ ሀገር ገብተው ተወዳድረው(በምርጫ) እና ተባብረው(በሀገራዊ ምክክር) ለሀገር ግንባታ አስተዋጽዖ የሚያደርጉበት ክፍት ምኅዳር እንደተፈጠረ የሚታወቅ ነው። ነገር ግን ይህ በሐሳብ ለመወዳደር የተፈጠረው ክፍት ምኅዳር፣ ከታሰበለት አዎንታዊ ዓላማ በተቃራኒ የሚጎትቱት አሉ።

የሐሳብ ገበያ የታለመለትን ዓላማ ሊያሳካ የሚችለው፣ እውነትና ዕውቀትን መሠረት ያደረገ በምክንያት የሚደረግ ውይይትና ንግግር ሲኖር ነው። ከዚህ በታቃራኒ ለእውነትና ሙግባባትን አይፈጥርም። ከዚያ ይልቅ ለልዩነትና ለግጭት በር ይከፍታል። ፖለቲከኞች፣ ለዕውቀት የተከፈተው ምኅዳር፣ የሐሰትና የስሜት መፈን ሲሆን ቅቡልነትንና መገናኛዎች፣ ምሁራንና ሌሎች ተዋንያን በኃላፊነት ስሜት እንዲሁም በእውነትና በዕውቀት ላይ ተመሥርተው የማይንቀሳቀሱ ከሆነ አደጋቸው የከፋ ነው። የሐሳብ ፖለቲካ ልምምዱ ባልዳበረባት ሀገራችንም ይሁን፣ ጠንካራ የዴሞክራሲን ባህል ገንብተዋል በሚባልላቸው ሀገራት፣ ለሐሳብ ገበያና ለዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ፈተና የሆኑት ኃላፊነት የጎደላቸው፣ መርሕን የሳቱ፣ ሕዝብን በስሜት የሚጋልቡ፣ የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭቶች ናቸው።

ሐሳብን ለመግለጽ የተፈጠሩ ክፍት የፖለቲካ ምኅዳሮችንና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የፈጠረውን መረጃ የማሠራጨት ዐቅም አላግባብ በመጠቀም የሚሠራጩ የሐሰትና የሐሜት መረጃዎች፣ ለፖለቲካ ዕድገት መሠረት የሆኑ በእውነትና በምክንያት ላይ ተሠመሩ ውይይቶችን አቀጭጨዋል። ለዘመናት የተገነቡ ዕሴቶችንና መርሖችን በመናድና ለአለመግባባት ምክንያት በመሆን፣ የተከፋፈለ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር አድርገዋል።

በሐሳብ ገበያ ውስጥ ሐሳቦች ነጥረውና ጎልብተው የሚወጡት አመክንዮአዊ በሆኑ ውይይቶችና ንግግሮች ነው። በአንድ በኩል ልሂቃን በኃላፊነት ስሜት በእውነትና በዕውቀት ላይ ተመሥርተው መሥራት አለባቸው። በሌላ በኩል ሕዝቡ ነገሩን መዝኖና መርምሮ የሚቀበል መሆን አለበት። የሕዝብ የፖለቲካ ንቃተ ኅሊና ለፖለቲካ ዕድገቱ አስተዋጽዖው የላቀ ነው። የመረጃ ልዩነት በገበያ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚፈጥረው ሁሉ የሕዝብ የንቃተ ኅሊና ልዩነት በሐሳብ ገበያ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። ሕዝብ የገበያው መረጃ ከሌለው ሻጩ የመረጃ የበላይነቱን ተጠቅሞ ከልክ በላይ ጥቅም እንደሚያጋብስበት ሁሉ፣ ሕዝቡ አመዛዝኖና በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ የሚወስን ካልሆነ፣ ለፖለቲካ ኃይሎች ተጽዕኖ ተጋላጭ ይሆናል።

CS CamScanner

ነገርን ከሥሩ፤ የድኅረ ዘመናዊነት ፖለቲካ፦ በሐሳብ ገበያ ውስጥ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትና የሐሳብ ውድድር ወደ እውነታው ይመራናል። ተያይዞም ሀገርን የሚያሻግሩ ጠንካራ ሐሳቦች ይወጣሉ። ነገር ግን በዚህ በድኅረ እውነት ፖለቲካ ውስጥ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት አደጋን በሚደቅን መልኩ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። ወደ እውነቱ፣ ወደ ተሻሉ ሐሳቦችና ወደ መቀራረብ ሳይሆን፣ ወደ ልዩነትና ወደ አለመረጋጋት አደጋ እየወሰዱን ነው።

"የአሉ" ድኅረ እውነት ፖለቲካ፦ የፖለቲካችን መሠረታዊ ችግር ነገርን በቅጡና ከሥሩ አለመረዳት ነው። አሉባልታ ለማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገታችን ትልቅ ዕንቅፋት ነው። ብዙ ሀገር ሊለውጡ የሚችሉ ዕሳቤዎችና ሰዎች የደረቁት በአሉባልታ ነው። አንድ ወሬ ከየት መጣ? እንዴት ተነሣ እና ምክንያቱ ምንድነው? ሳይባል በመንጋ ይፈረጃል። በማኅበር

ይጠላል። በማኅበር ይደነቃል። በጋራ ይወደዳል። "በአሉ" ብቻ ፍርድ ይሰጣል። ሰው ይቀጣል። ብዙ ነገሮች ይደረጋሉ።

"በአሉ" ብቻ ብዙ ጥፋት ደርሷል።

ፖለቲካችን አንዱ የሚያስፈልገው ትልቅ ለውጥ ነገርን ከሥሩ መመልከት ነው። ወቅቱ ደግሞ ከምንም በላይ በጥልቀት መመልከትና ከሥሩ መመርመር የሚፈለግበት ነው። ይህም ከመረጃና ከማኅበራዊ መገናኛ አብዮት ጋር በተያያዙ ሁለት ምክንያቶች የሚያስፈልግ ነው።

አንደኛው የመረጃ ምንጭና የማሠራጫው መንገድ እየሰፋና ተጽዕኖው ከፍ እያለ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ነው።የመረጃ ቴክኖሎጂ ማንም የመሰለውንና ደስ ያለውን በዐደባባይ እንዲናገር ዕቅም በመሆኑ፣ የፖለቲካ ዐውዱን በእጅጉ ለውጦታል።

ዓለም ከመረጃ አብዮት ጋር በተያያዘ ካስተናገደቻቸው ለውጦች ቀዳሚው ፖለቲካና የእውነት ምልከታ ነው፡ማንኛውም ሰው በአንድ ነጠላ የፌስቡክ ልጥፍ እውነትን ጥያቄ ውስጥ የመክተትና የማዛባት ዕቅም አለው። እውነትን ከአመክንዮአዊ ፍለጋ አውጥቶ በተከታይ ብዛት እንድትመዘን አድርጓታል። የማኅበራዊ መገናኛ አብዮት ድሮ በጓዳ የሚወራውን ዐደባባይ

ይዞት ወጥቷል። አንድ "በመሰለኝ" የተወራ ጉዳይ ማስረጃ አምጣ ሳይባል ብዙ ተከታይ ያለው እውነት ሆኖ ቁጭ ይላል። ነገሮችን በጥልቀት መመልከት ከምንም ጊዜ በላይ ዛሬ አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛው መረጃ ዋነኛ መሣሪያ መሆኑ ነው። ሆን ተብሎ ውሳኔዎችን ለማስቀየርና አቅጣጫን ለማሳት መረጃን በሚፈልጉት አቅጣጫ የመቀየርና የማቀናበር ሥራ ይሠራል። ዛሬ የሞራል ድንበርን ጥሶ፣ እየገደለ ቪድዮ በመቅረጽ ከፍ ያለ አለመረጋጋትን ለመፍጠር ይሠራል። በአንድ ተንቀሳቃሽ ምስል ሀገር እንዳትረጋጋ ለማድረግ ይሠራል። ይህ የመረጃ አብዮት የጠላት የጥቃት ማዕዘንና ዒላማንም ቀይሮታል። ዒላማው ከሕንጻና ከከተማ ወደ አእምሮና ሥነ ልቡና ዞሯል። የማጥቂያ መሣሪያውም ከሚተኮሱ ጥይቶች ወደ ሚሠራጩ መረጃዎች ተቀይሯል።

ጦርነት አካላዊ ውድመት ከመፍጠር ፖለቲካዊ ውድመት ወደመፍጠር ተለውጧል። የመረጃ አብዮት የግራጫ ጦርነትን ፈጥሯል። መረጃን የማዛባት፣ አመለካከትንናአስተሳሰብን የማደናገርና ውሳኔን የማስቀየር ጦርነት የዘመናችን መገለጫ ነው። ሚሳኤል ሳይተኩሱና ጥይት ሳያነሡ ሕንጻ ሳያፈርሱና አካላዊ ጥቃትን ሳይፈጽሙ፣ ሀገርን የመናጥና ሀገርን የማፍረስ ዘመን ነው። ፖለቲካዊ ጦርነት ያለ ሚሳኤልና ታንክ ሀገርን የመማረኪያ መንገድ ሆኗል።

የፖለቲካ ጦርነት ፖለቲካዊ መንገዶችን በመጠቀም ተገዳዳሪ የእኛን ፍላጎት እንዲያስፈጽም ማስገደድ ነው። የሆነ ኃይል ሌላኛውን ዒላማ የሆነ ኃይል ተጽዕኖ ውስጥ ለመክተት የሚያደርገው የተሰላ ግንኙነት ነው። በመንግሥታት፣ በተለያዩ ቡድኖችና በኃይላት ዘንድ ሌሎች መንግሥታትን፣ ሕዝቦችንና አካላትን ለማጥቃት የሚውል መሣሪያ ነው። በዋናነትም የተወሰነ ሐሳብን፣ ድርጊትንና ውሳኔን ተጽዕኖ ውስጥ ለመክተት ወይም ለማስለወጥ የሚደረግ ነው።

CamScanner

ይሄንንም በማድረግ የራስን ግብ ለማሳካት ሲባል፣ ምቹ ምኅዳር መፍጠርና ተገዳዳሪ ኃይል አቅጣጫውን ስቶ በሌሎች ፍላጎትና መንገድ እንዲመራ የሚያደርግ ነው። የተገዳዳሪን ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ሕዝባዊ ፍላጎትና ተነሣሽነት በማዳከምና በማውደም ለራስ ምቹ የሆነ ፖለቲካዊ ሁኔታ እንዲከወንና እንዲፈጠር ያደርጋል።

አመክንዮአዊ ኀሠሣ፡- "እሉ" ከጓዳ ወጥቶ ዐደባባይ በዋለበትና መረጃ ሆን ተብሎ በሚምታታበት ዘመን፣ ፖለቲከኞች ከቀደመው በላቀ ነገሮችን በአንክሮ የሚመለከቱ መሆን አለባቸው። እንደ ጎርፍ ደራሽ የሆነ መረጃ አጥፊ ነው። ዘመናችን ደራሽ መረጃ የበዛበት ነው። የሆነ መረጃ ከሆነ ቦታ ይነሣል፤ ያገኘውን ሁሉ አጥለቅልቆ ይወስዳል። ውሳኔን ያስቀይራል፤ አቅጣጫን ያስታል፤ በማዕበል ውስጥ መወዛወዝን ይፈጥራል። በእንደዚህ ዓይነት ዓለም አቀፍ ሁኔታ ውስጥ ነገርን ከሥሩ አለመረዳት ለፍጥነት ዕንቅፋት ነው። ጉዟችንን መለስ ቀለስ የሚል መዋለል ውስጥ ይከተዋል። በዓላማ መጓዝ ትተን
መረጃ በሚያወዛውዘን መንገድ እንጓዛለን። ከዚያም ወደ መዳረሻችን ሳይሆን ወደ ጥፋት እናመራለን።

በእያንዳንዱ ዕለትና አጋጣሚ የእኛን ውሳኔ ከሚፈልጉ ጉዳዮች ጋር እንፋጠጣለን። መሪዎች ስንሆን ደግሞ የእኛ ውሳኔ ከእኛ አልፎ በብዙዎች ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል። የመረጃና የማኅበራዊ መገናኛ አብዮት ደግሞ በየዕለቱ በውሳኔያችንና በምልከታችን ላይ ተጽዕኖ ከሚያደርጉ የበዙ መረጃዎች ጋር እንድንጋፈጥ ያደርጋል።

ዘመኑ፣ በየደቂቃውና በየሰከንዱ አስተያየቶችና መረጃዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ውሳኔያችንንና አካሄዳችንን ለማስቀየር የሚተሙበት ዘመን ነው። በዚህ የተነሣ ወጀቡን ተቋቁሞ ትክክለኛውን ውሳኔ ማስተላለፍ ከባድና የተለየ ትኩረት የሚጠይቅ ነው። በድኅረ እውነት ዓለም ውስጥ እውነትን ማግኘትና በእውነት ላይ ተመሥርቶ ውሳኔን ማስተላለፍ የተለይ ትኩረት ማድረግ ይፈልጋል።

እውነትን ለማግኘት አመክንዮአዊ ኀሠሣ ወሳኝ ነገር ነው። ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡልንን መረጃዎች፣ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ያለምንም ማገላበጥ የምንቀበል ከሆነ፣ ካለምነው መዳረሻ ሳይሆን ካላሰብነው አጣብቂኝ ውስጥ ይከቱናል። ምክንያቱም ወገን ፍላጎት የሚገልጹ ሲሆን፣ እነርሱን ተከትለን ስንጓዝ መዳረሻችንም የዚያው ወገን በዚህ የፖለቲካ ጦርነት ዘመን ውስጥ የሚሠራጩ መረጃዎች የእኛን ሳይሆን ያሠራጨውን ይሆናሉ።

በመሆኑም እያንዳንዱን የሚቀርብልንን መረጃ በስሜት መከተል ሳይሆን በምክንያት መመርመር ያስፈልጋል። ነገርን ከሥሩ ማጤንና መመልከት ያስፈልጋል። ለሚከሠቱ ነገሮች ቅርንጫፉን ብቻ በማየት ከመወሰን ይልቅ ከሥሩ መጀመር መቻል አለብን። ችግሮችን ከመነሻው ወይም ከምንጩ ማጤንና የሚሠራጩ መረጃዎችን በጥልቀት መነጽር እያንዳንዷን ነገር ሰባብሮ መመልከት ያስፈልጋል።

ባለንበት ወቅት እጅግ ለቁጥር የሚያዳግቱ አስተያየቶችና መረጃዎች ይሠራጫሉ። የሤራ ትንታኔዎች እዚህም እዚያም ይነሣሉ። ክሥተቶችን ተከትሎ ተረኮች፣ አስተያየቶችና የሤራ ትንታኔዎችይበተናሉ። የእነዚህ አሉባልታዎችና ወሬዎች አደገኛነት ሕዝብን ማሸበራቸውና ማናጋታቸው ብቻ አይደለም። አመራሩን በቀላሉ ቀልቡን መግዛታቸውና አቅጣጫውን ማሳታቸው ጭምር ነው። መሪ ሳያላምጥ አይውጥም። በመጣ በሄደው አይወሰድም። ዙሪያ ገባውን መመልከት አለበት። ከማኅበራዊ መገናኛውና ከሕዝቡ ስሜት ጋር አብሮ ሞቅ በረድ የሚል መሆን የለበትም። ረግቶ ሌላውን የሚያረጋጋ መሆን አለበት። የፖለቲካ ገበያና የድኅረ እውነት ዘመን ይህንን ዓይነት መሪ ማግኘትን እንደ ዲዮጋን መብራት በርቶ በቀን የሚፈለግ አድርገውታል።

መሪ ነገሮችን በጥልቁ የሚመለከትና ከምንጩ የሚያጤን መሆን አለበት። ጉዳዮችን በመረጃ፣ በማስረጃ፣ በተጠየቅና በአመክንዮ የሚረዳ፤ ከሚናፈሰው ጋር የማይነፍስ መሆን አለበት። እንደ ወንዙ ወራጅ ሳይሆን እንደ ዐለቱ ጽኑ ሆኖ ወንዙን የሚያሳልፍ መሆን አለበት። እንደዚህ ስናደርግ በተሳሳተ ውሳኔ ምክንያት የሚመጣውን ጥፋት መከላከል እንችላለን።

CamScanner

አንበሳ ታመመ ተብሎ ተወራ። እንስሳው ሁሉ "አንበሳ ታሟልና መጠየቅ አለብን ብሎ በጅምላ መንጎድ ጀመረ። ይሄዳል፤ በአንበሳ ተደቁሶ ይቀራል። ጥንቸል ብቻ ቀረች። እንደ ሌሎች ብትሆኚ አይሻልም ወይ? " የሚለው ጉትጎታ መቆሚያ መቀመጫ አሳጣት። "ከመንጋው ለምን ትለያለሽ? አንቺ ከማን በልጠሽ ነው በኋላ አንበሳ ሲድን አይለቅሽም፤ እርሷ ደግሞ የምታሰባስበውን መረጃ ስትመዝነው አንበሳ ታሟል ብላ ማመን አልቻለችም። በኋላ ጓደኞቿ አስገድደው ወሰዷት። መንገዱን ስታየው የሄደ እንጂ የተመለሰ የእንስሳት ኮቴ አይታይም። ለምን? አለች። ጓደኞቿን ብትጠይቃቸው መልስ የላቸውም። "አንቺ ምን አስጨነቀሽ፤ ለምን አርፈሽ አትሄድም አሏት። ፈላስፋ፣ ነገረኛ፣ ተጠራጣሪ፣ ተብላ ተተቸች።

ጥንቸል ሄደች። ወደ ዋሻው በበሩ በኩል መግባት ትታ በመስኮቱ በኩል መመልከት ጀመረች። "እኔ ሳውቀው አንበሳ ሲታመም አፉን ከፍቶ ይተኛል እንጂ አፉን ገጥሞ አይተኛም" አለች ድምፅዋን ከፍ አድርጋ። አንበሳው ነቃ። "ቆይ የታመምኩ ልምሰላት" ብሎ አፉን ቀስ አድርጎ ከፈተ። አሁን ጥርጣሬዋን አረጋገጠች። አንበሳ ለስልቱ እንጂ አልታመመም። እሷ ተመለሰች፤ አልመራመር ያሉትም ተበሉ።

ማኅበረሰባችን እንደዚህ ነው። ቅቤ እንጂ እውነት አያነጥርም። በቅቤ ውስጥ ቅቤውና አንጉላው ይቀላቀላል። ስሙ ግን ቅቤ ነው። ቅቤው ሁሉ ቅቤ አለመሆኑ የሚታወቀው ሲነጠር ነው። እውነት ሁሉ እውነት አለመሆኑ የሚታወቀውም ሲነጠር ነው። አመራር በመንጋ የሚመራ ሳይሆን እውነትን የሚያነጥር መሆን አለበት። በጫጫታ፣ በበለው በለው፣ በጅምላ አይመራም። ጊዜ የወለደው፣ ዘመን የወደደው ስለሆነ ብቻ አይቀበልም። ያነጥራል።

በፖለቲካ ውስጥ "ለምን? " የሚለው ጥያቄ ሐሳቦች ነጥረው እንዲወጡ ቁልፍ ነው። የፖለቲካ ሐሳቦችን፣ ንግግሮችን፣ ጠባይና ድርጊቶችን ትክክለኛነታቸውን ለማሳየት ወይም ስሕተት መሆናቸው ለማሳወቅ ምክንያታዊነት ወሳኝ ነው። ሐሳቦቹን፣ ንግግሮቹንና ድርጊቶቹን በምክንያታዊነት መዝኖ መረዳትና መገንዘብ ያስፈልጋል። "ለምን?" የሐሳቦች ትክክለኛነትና ስሕተት ማንጠሪያ እሳት ነው።

ምክንያት የፖለቲካ ሂደትና ዕድገት ማቀጣጠያ ነው። መንግሥት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎች ምክንያታዊ መነሻ ሊኖራቸው ግድ ነው። እንዲሁም ለመንግሥትም ይሁን ለፖለቲካ ኃይሎች የሚኖር ድጋፍ በምክንያት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። መንግሥት ወይም ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች የሚያመጧቸው ሐሳቦች የጠራ ግብን ያነገቡና ለሕዝብ ካለው ጥቅምና ጉዳት አንጻር የተሰሉ መሆን አለባቸው። በሌላ በኩል ሕዝብ የቀረቡለትን ሐሳቦች አመዛዝኖ፣ ጥቅምና ጉዳታቸውን አስልቶ፣ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የሚተችና የሚደግፍ መሆን ይገባዋል።

የሚቀርቡ የሐሳብ አማራጮች ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘቡ፣ ችግሮችን በቅጡ የተገነዘቡና ሊሠሩ የሚችሉ መሆን አለባቸው። ሐሳቦችን የሚተችና የሚደግፍ አካል ሐሳቦቹ ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበና ሊሳኩ የሚችሉ መሆናቸውን አለመሆናቸውን ማገናዘብ ይኖርበታል። ድጋፎቹ የሐሳቦቹን ጥንካሬና ውጤታማነት የሚያሳዩ፤ ትችቶቹም የሐሳቦቹን ክፍተትና ደካማ ጎን የሚያመለክቱ መሆናቸው ሊሠመርባቸው ይገባል። ፖለቲካ ውስጥ በጭፍን መውደድም ይሁን በጭፍን መጥላት ላልተገባ ኪሳራ ይዳርጋል። ከዚያ ይልቅ መሬት ላይ ያለውን እውነታ በመገንዘበ በምክንያትና በውጤት መተቸትና መደገፍ ፖለቲካዊ ዕድገትን ያረጋግጣል።

### 13.3. ተቋማዊ አሠራር፣ መርሕና ሕጋዊ ሂደት

CS CamScanner

ተቋማዊና ሕጋዊ አሠራሮችና ሂደቶች፣ የሕዝብ ፍላጎት መፈጸሙን ያረጋግጣሉ። ሰላማዊ የሕዝብና የመንግሥት ግንኙነትን ያሣልጣሉ። እንዲሁም በሕዝብ መካከል መልካም ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋሉ። የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ሊያደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ ይቀንሳሉ።

በጋራ ፍላጎትና በግለሰቦች ፍላጎት መካከል የሚኖር ተቃርኖና መጣረስ አይቀሬ ነው። ውሳኔ ሰጪዎችና ሌሎች ፖለቲካዊ ተጽዕኖ ያላቸው አካላት የሚያስተላልፉት ውሳኔና የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የጋራ ፍላጎትን አደጋ ላይ በመጣል ግላዊ ፍላጎትን የሚያስጠብቅ እንዳይሆን መጠንቀቅ ተገቢ ነው። ለዚህ ደግሞ እነዚህ ውሳኔዎችንና እንቅስቃሴዎችን የሚገዛ ተቋማዊ አሠራርና ሕጋዊ ሂደት እጅግ አስፈላጊ ነው። ተቋማዊ አሠራሮችና ሕጋዊ ሂደቶች ለግላዊ ፍላጎቶች ልጓም በማበጀት የማኅበረሰቡን ደኅንነት ያስጠብቃሉ።

የሐሳብ ገበያ የታለመለትን ዓላማ እንዲመታ ሐሳብ ለመግለጽ የተከፈተው ነጻነት የኃላፊነት ልጓም ሊኖረው ይገባል። ሐሳብ የሚንሸራሸርበት ምቹ የመጨዋቻ ሜዳ ሊኖር ያስፈልጋል። እነዚህ የመጨዋቻ ሜዳዎች የሕዝቡን የፖለቲካ ልምምድ፣ ባህሉን፣ ወጉንና ሥነ ልቡናውን ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል። አሳሪም፣ ልቅም መሆን የለባቸውም።

የሐሳብ ውድድር እንዲዳብርና የሐሳብ ገበያው እንዲጠናከር ሐሳብን በነጻነት መግለጽ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ሐሳብን በነጻነት መግለጽ የተለያዩ አማራጭ ሐሳቦች ወደ መድረክ እንዲመጡና የተለያዩ ድምጾች እንዲሰሙ ያደርጋል። ሰዎች ያለማንም ጣልቃ ገብነትና ፍርሃት ሐሳባቸውን መግለጻቸው፣ የተለያዩ ሐሳቦች ወደ መድረኩ መጥተው የተሻለው ሐሳብ ነጥሮ እንዲወጣ ያደርጋል።

ብዝኃ ማንነቶች ባሉበት፣ ሰፊ ልዩነት ባለበት፣ የዴሞክራሲ ባህል ባልዳበረበትና ያልተጠናቀቀ ሀገረ መንግሥት ባለበት ሀገር፣ ሐሳብን ያለምንም ገደብ በነጻነት የመግለጽ መብት ጥንቃቄን የሚሻ ነው። ምክንያቱም ከተገቢው ውጤት በተቃረነ መልኩ ለግጭት ምክንያት በመሆን ሀገራዊ አንድነትን ሥጋት ውስጥ ሊጥል ይችላል። የሰው ልጅ ነጻነትን ከግዴታ ጋር ካላስተሣሠረ፣ ነጻነት ልቅነት ተደርጎ ይወሰዳል። ነጻነትና ልቅነት ሲደባለቁ ደግሞ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ ጉዳይ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል።

ነጻነትና ኃላፊነት የአንድ ርግብ ሁለት ክንፎች ናቸው። በአንዱ ክንፍ ብቻ ለመብረር አይቻልም። ሁለቱ ክንፎች ሚዛን ጠብቀው መጓዝ አለባቸው። ኃላፊነት ወደ ጽንፍ ሲሄድ ባርነትን ያመጣል። ነጻነት ወደ ጽንፍ ሲሄድ ደግሞ ሥርዓት አልበኝነትን ያስከትላል። ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ከሕጋዊና ከሥነ ምግባራዊ ኃላፊነት ጋር የሚመጣ ነው። ልምምዱ እንዲዳብርና ተገቢው ውጤት እንዲመጣ ሐሳባችን ሕጋዊና ሥነ ምግባራዊ ኃላፊነቶችን የተወጣ መሆን አለበት።

ነጻነታችን የሌላውን መብት ያከበረ፣ ሌላውን በጥላቻ የማይዘልፍ፣ ማኅበራዊ ትሥሥርን፣ ሀገራዊ አንድነትንና ብሔራዊ ጥቅምን የማይጎዳ፣ ሉዓላዊነትን የማይሸረሽር፣ ቁልፍ ማኅበረሰባዊና ሥልጣኔያዊ ዕሴቶችን የሚያከብር መሆን አለበት።

በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ በእውነትና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ክርክርና ውይይት እምብዛም የሚታይ ጉዳይ አይደለም። ባልዳበረው የፖለቲካ ባህላችን የድኅረ እውነት ፖለቲካ ሲጨመርበት በደንባራ በቅሎ ቃጭል እንደመጨመር ሆኗል። በእውነትና በውጤት ላይ የሚደረጉ ውይይቶችና ክርክሮች ቀርተው በመሰለኝና በደሳለኝ የሚደረጉ ክርክሮች ለፖለቲካ ዕድገት ፈተና ሆነዋል። የሤራ ትንታኔ፣ ሐሰተኛ መረጃና ጥላቻ የፖለቲካ አጀንዳችን ዋነኛ መገለጫዎች ናቸው።

የፖለቲካ ሰዎችን በምክንያትና በውጤት የመመዘን ክፍተት አለብን። ድጋፍና ትችት በሰዎቹ ማንነት ላይ ይመሠረታል። የሀገራችን ፖለቲካ በአንድ በኩል አማራጭ ሐሳቦችን የማቅረብ ፈተና አለበት። በሐሳብ ድርቅ ተመትቷል። በሌላ በኩል የጋራ አጀንዳንና የመታገያ አጀንዳን መፍጠር አልቻለም።

በሐሳብ ገበያ ውስጥ ፖለቲካ በራሱ ግብ ሳይሆን፣ ማኅበረሰባዊ ዓላማን የማስፈጸሚያ መንገድ ነው። ፖለቲካችን ይህንን ማኅበረሰባዊ ዓላማና ግብ እንዲያስፈጽም የምናደርገው በሕግና በመርሕ ነው። ሕግና መርሕ የሰዎችን ጠባይና ድርጊት

CS CamScanner

በመግራት እንዲሁም ፖለቲካውን ቅርጽ በማስያዝ ማኅበረሰባዊ ግብ እንዲረጋገጥ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ። ሰዎች በጋራ እንዲኖሩና የጋራ ግብን እንዲያረጋግጡ የሚያስችሉ ማሕቀፎች ናቸው።

ሕግና መርሕ ዋነኛ ዓላማቸው ግጭቶችን በመፍታት፣ መብቶችን በመጠበቅ፣ ማኅበረሰብን ከጉዳት በመጠበቅ፣ እንዲሁም ሥርዓትን በመቅረጽ ጤናማና ሰላማዊ ማኅበረሰባዊ የሚገቡ ግዴታዎችና ሊከተላቸው የሚገቡ ሥርዓቶች አሉ። ሕግና መርሕ እነዚህ ለመፍጠር፣ ሁሉም የማኅበረሰብ አባል፣ እንደ አባልነቱና እንደ ሞያው ሊወጣቸው መስተጋብርን መፍጠር ነው። ይሄንን ጤነኛና ሰላማዊ ማኅበረሰባዊ መስተጋብር ግዴታዎችንና ሥርዓቶችን ያቀፉ ናቸው። ትክክል የሆነውን ትክክል ካልሆነው፣ ሠናዩን ከእኩዩ የምንለይባቸው ማሕቀፎች ናቸው።

ሕግ መደበኛ የሆነ የተጻፈ/ያልተጻፈ፣ አንድ ማኅበረሰብ በመከተሉ/በመጣሱ ሕጋዊ የሆነ ቅጣትን/ነጻ መሆንን የሚያስከትል ነገር ነው። ዕሴቶችና መርሖች ግን መደበኛ ያልሆኑ ግብረ ገባዊና ማኅበረሰባዊ ግዳጆች ናቸው። ኅሊናዊ ደስታ፣ ማኅበረሰባዊ ርካታና ተጠያቂነት ያላቸው ናቸው። አሣሪ ግን አይደሉም። ነገር ግን እነዚህ ዕሴቶችና መርሖች በማኅበረሰቡ ወግና ልማድ ውስጥ የተደባለቁ ሲሆን፤ መደበኛው ሕግንም ይሁን የሰዎችን ባሕርይ በመቅረጽ ረገድ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ናቸው። ለዚህም ነው የትኛውንም ዓይነት ሥርዓት ለመገንባት እነዚህ ዕሴቶች ቁልፍ የሚሆኑት።

እነዚህ መርሖችና ዕሴቶች የፖለቲካ ውሳኔንና ድርጊትን የሚመሩ ገዥ ማሕቀፎች ናቸው። ትክክል ያልሆነውን ትክክል ከሆነው የሚለዩ ናቸው። በፖለቲካችን ውስጥ የትኛው ልክና የትኛው ስሕተት እንደሆነ ተደበላልቋል። የተለያዩ ማንነቶች ላይ ተመሥርቶ ጽንፍ የያዘው ፖለቲካ፣ ትክክለኛነትን የሚመዝነው በመርሕ ሳይሆን፣ በማንነት ነው። አንድ ዓይነትና

ተመሳሳይ የሆኑ ጉዳዮችን "የራስ" የሚባለው ወገን ሲያደርገው ትክክል፣ "የሌላ" የሚባለው ወገን ሲያደርገው ስሕተት ይሆናል። ጉዳይን በድርጊቱ ሳይሆን በአድራጊው ማንነት የሚፈርጀው የፖለቲካችን ባህል መቀየር የዚህ ዘመን አንዱ የሠለጠነ የፖለቲካ ባህል ግንባታ ዒላማችን ነው፡ ጉዳይን በጉዳይነቱ ለመመዘን የሚያስችል መርሕ በፖለቲካችን ውስጥ ማዳበር አለብን።

ድርጊቶችንና ውሳኔዎችን ትክክልና ትክክል ያልሆነ ብለን የምንበይንበት መነጽር እስካልተስተካከለ ድረስ የተቃናና የተስተካከለ የፖለቲካ ሁኔታ መፍጠር አዳጋች ነው። የምንሸልመውና የምንቀጣው በመርሕ እስካልሆነ ድረስ ትክክለኛውን ውጤት ልናመጣ አንችልም። እኩይ ድርጊቶችን በመርሕ ማውገዝና መልካም ምግባሮችን በመርሕ ማወደስ ካልተቻለ በስተቀር፣ ዘላቂ የሆነ ለውጥ ማምጣት የዳገት ሩጫ ይሆናል።

የፖለቲካ ገበያ አዝማሚያዎችን ለማረምም ይሁን ለሐሳብ ገበያ መሠረት ለመጣል ዕሴቶቻችን ቁልፍ ሚና አላቸው። ሌብነትን ማረም የምንችለው በሕግ ብቻ ሳይሆን በሥነ ምግባር የታነጸ ትውልድ በመፍጠር ጭምር ነው። አንድነትን ለማጠናከር የወንድማማችነት ዕሴት ቁልፍ ነው። በመርሕ ላይ ስንቆም ፖለቲካችን ከስሜት የራቀ ይሆናል። ከስሜትና ከደመ ነፍስ በመራቅ በጠራ መንገድ ተመርተን ወደ ታለመ መዳረሻ ማምራት እንችላለን።

ወደ ጠራ መዳረሻና ግብ ልናመራ የምንችለው፣ የምናደርገውን ለምን እንደምናደርግ የምንመራበት መርሕ፣ ክፉውን ከደጉ የምንለይበት የጠራ ገዥ ማሕቀፍ ሲኖረን ነው። መልካም ዕሴቶች መልካም ድርጊትንና ጠባይን ይወልዳሉ። በዚህም አዎንታዊ ውጤትን በመፍጠር ወደ ተሻለ መዳረሻ ይመሩናል። በዚያው ልክ እኩይ ዕሴቶች በተቃራኒው ይወስዱናል።

ያልተረጋጋ ፖለቲካ የሚፈጠረው አብሮ ለመኖር የሚያስችሉ ዕሴቶች እየላሉ ሲመጡ ነው። የፖለቲካ ገበያ በማንኛውም አጋጣሚ ግጭትን፣ ሞትንና የሰው ልጆችን ኀዘን ጭምር እንደ መሣሪያ ይጠቀማል። የሰው ልጅን ጉዳት ግለሰቦች ኪሳቸውን

ለማደለብ፣ ሥልጣንን ለማግኘትና ለማስጠበቅ ይገለገሉበታል። ከዚህ በላይ የሥነ ምግባር ዝቅጠት ማሳያ ምን አለ?

CamScanner

ብልጽግናን ለማረጋገጥ ከዚህ ውል አልባ መንገድ መራቅ የግድ ነው። ግብና መዳረሻው የግለሰቦችን ኪስ ማድለብ ከሆነ አስተሳሰብ መውጣት ለነገ የማይባልበት ነው። በዚያው መጠን፣ ግብና መዳረሻው የሚታወቅ፣ በሕግና ልዕልና ላይ የቆመ፣ በመርሕ የሚመራ የፖለቲካ ሽግግርን ማምጣት አለብን። የፖለቲካ መረጋጋት የሚፈጠረው፣ ፖሊሲዎች ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉት፣ ጠንካራ ተቋማትን ለመገንባት የሚቻለው፣ በአንድ በኩል ሰዎች ለሕግ ተገዢ መሆን ሲችሉ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ያነገቧቸው ለሠለጠኑ ዕሴቶች ግንባታ ቁልፍ አስተዋጽዖን ካበረከቱ ነው።

ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚቻለው አብሮነትን፣ ትሥሥርን፣ መደማመጥን፣ መከባበርን፣ በልዩነት መኖርንና መቻቻልን በሚያጠነክሩና ሥርዓትን በሚፈጥሩ ዕሴቶች መሠረት ላይ ነው። በዓለም ላይ የተፈጠሩት ሥልጣኔዎች የዕድገታቸው መነሻ እንደዚህ ዓይነት ዕሴቶች መኖር ነው። ለውድቀታቸው ምክንያትም የእነዚህ ዕሴቶች መዝቀጥ ነው። በዘመናዊው ዓለም ረጅም ዘመናትን የተሻገሩ የተረጋጉ ሥርዓቶች የተፈጠሩት በእንደዚህ ዓይነት የዕሴት ለውጦች ነው።

የዘመናዊነት ዕሴቶች በምዕራቡ ዓለም የተረጋጉ ሀገራትንና ሰላምን በመፍጠር ረገድ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርገዋል። በምሥራቁ እስያ የሥራ ባህል መስፋፋቱ፣ ሌብነትን የሚጸየፍ ማኅበረሰብ መገንባቱ፣ የሥራ የዕዝ ሠንሠለትን ጠብቆ የመሥራት ልማድ በመኖሩና ሌሎች ጉዳዮች ለዕድገታቸው መሠረት ሆነዋቸዋል።

ተቻችሎ፣ ተቀራርቦና ተባብሮለመኖርና የጋራ ግብን ለማሳካት አዎንታዊ ዕሴቶች ቁልፍ ሚና አላቸው። በፖለቲካችን ውስጥ የግለሰቦችን ጠባይ የሚገዙ ሕጋዊና ተቋማዊ ቁጥጥሮችን ሊፈጠር የሚችለው የሰው ልጅን ጠባይ ሊገሩ የሚችሉ መርሖችና ዕሴቶች በአንድ መገንባት አለብን። ሥነ ምግባራዊ መርሖችንና ዕሴቶችን ማዳበር ያስፈልገናል። ሥልጣኔ ማኅበረሰብ ውስጥ ሲዳብሩ ነው። በሀገራችን ለሌብነት፣ ለፖለቲካ ውጥንቅጥና ለሌሎች ቀውሶች መነሻቸው የሰዎችን ጠባይ የሚገሩ ዕሴቶችና መርሖች እየላሉ መምጣታቸው ነው።

ሕጋዊና ተቋማዊ የሆነ ፖለቲካ እንዲዳብር እንደዚህ ዓይነት ዕሴቶች ቁልፍ ናቸው:: በተቋም ውስጥ በጎ ባህልና የአሠራር ሥርዓት በመፍጠር ለውጤታማነት ቁልፍ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።ጠንካራ ሥርዓት የሚፈጠረው በእነዚህ ባህሎች ላይ ነው።

በለውጡ ዘመን ፈተናዎችን እየተቋቋምን ዴሞክራሲን ለመገንባት ጥረት ያደረግነው ለሠለጠነ ሲቪክ ባህል ግንባታ ወሳኝ በመሆኑ ነው። አፋኝ ሕጎችን አሻሽለናል። መብት ገዳቢ አሠራሮችን ለቀቅ አድርገናል። የመገናኛ ምኅዳሩን በቁጥርም በተደራሽነትም አስፋፍተናል። በሐሳብና በመገናኛ ነጻነት ስም መንግሥትን ለአደጋ የሚዳርጉ እንቅስቃሴዎችን እየተመለከትን እንኳን በትዕግሥት አልፈናል።

የመንግሥት ኃላፊዎችና ደጋፊዎች መንግሥት ጨከን ያለ ርምጃ እንዲወስድ ይወተውቱ ነበር። መንግሥት ግን ሆደ ሰፊነትን መረጠ። አንዳንዶቹ ወዳጆቻችን የወተወቱንን ለማድረግ ሕጉ ይፈቅድ ነበር። ነገር ግን ለዴሞክራሲ ባህል ግንባታ ሲባል መንግሥት እየተጎዳም ቢሆን ታግሦ ነበር። የመንግሥትን ትዕግሥትና ሆደ ሰፊነት ግን አንዳንዶች እንደ መንግሥት ድክመት ቆጠሩት።ራሳቸውንም ከመንግሥት ጋር እንዲያፎካክሩ የልብ ልብ ሰጣቸው።

ይህ የሆነው ለዴሞክራሲ ሥርዓት ማበብ ምቹ የሆኑ የፖለቲካ ዕሴቶች ባለመኖራቸው ነው። የመቻቻል፣ የሐሳብ የበላይነት፣ ልዩነትን የማክበር፣ የነጻነት፣ የእኩልነት እና የወንድማማችነት/እህትማማችነት እሴቶች አልዳበሩም። በዚህ የተነሳ፤ ዴሞክራሲ የሚፈጥረው የነጻነት አካባቢና የሰፋ ምኅዳር ለአለመረጋጋት በር ሲከፍት ተስተውሏል።

የለውጡ መንግሥት ይህንን ፈተና እየፈታው ያለው በሦስት መንገዶች ነው። የመጀመሪያው _ ከላይ እንደገለጥነው አሁንም ሆደ ሰፊ በመሆን ነው። የፖለቲካ ባህላችን ኃይል መጠቀምን ያበረታታል። "ሌባ ተይዞ ዱላ ይጠየቃል ወይ" የሚለው

CamScanner

ባህል አጥፊ በተባለው ላይ ሁሉ የሕግ ሳይሆን የኃይል ርምጃ መውሰድን ይፈቅዳል። “ፖሊስ ሁለት ጊዜ በጥፊ ሲልህ እውነቱን ታወጣለህ” የሚለው ማኅበራዊ ብሂል ለሕግ አስከባሪው ጉልበትን የመጠቀም ሙሉ መብት የሚሰጥ ነው። መንግሥት የሠለጠነውን ሲቪክ ባህል ለመገንባት ሲል ትዕግሥቱን ያበዛው ለዚህ ነው።

እስካሁን በፖለቲካ ባህላችን ያልተገነቡት ዋናዎቹ ዕሴቶች መቻቻልና የሐሳብ ልዕልና ናቸው። የሐሳብ ልዕልና በምኅዳር ስፋትና በሐሳብ ገበያ ባህል ግንባታ የሚመጣ ነው። መቻቻል ደግሞ መንግሥት እየቻለ አርአያ በመሆን የሚፈጥረው ሲቪክ ባህል ነው።

ሁለተኛው፥ ምኅዳሩን በሕግ መምራት ነው። የሀገር ሕግና የሞያ ማኅበራት ሕግ ለዚህ መፍትሔ እንዲሆኑ ይታሰባል። የሀገር ሕግ የሚባለው ነጻነትን ለማስተዳደር እንዲቻል የሚወጡት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ሕግጋት ናቸው። እነዚህ ሕግጋት ነጻነትን ገዳቢም፣ ልቅ አድራጊም እንዳይሆኑ ተደርገው የሚወጡበትን መርሕ እንከተላለን። የሞያ ማኅበራት ሕግጋት ደግሞ ልዩ ልዩ ሞያ ያላቸውና በሲቪክ ምኅዳሩ የሚሳተፉ አካላት እርስ በርሳቸው የሚገማገሙባቸውንና የምኅዳራቸውን መብትና ግዴታ የሚያስጠብቁባቸው የውስጥ ደንቦች ናቸው።

ሦስተኛው ማኅበረሰባዊ ጫና ነው። ከሕዝብ ዕሴቶች ያፈነገጡ፣ ሀገርንና ማኅበረሰብን ለአደጋ የሚዳርጉ፣ ጥላቻና ግጭት የሚቀሰቅሱ፣ የወጣቶችን ተስፋ የሚያጨልሙ፣ ብሔራዊ ጥቅምን አሳልፈው የሚሰጡ፣ ወዘተ. ተግባራትን ፈጻሚዎችን፣ ሕዝቡ እንዲያወግዝና በማኅበረሰባዊ ባህሉ እንዲቀጣ ማድረግ ነው።

### 13.4. አማራጭ ዕይታ፤ የጋራ ትርክት

የፖለቲካችን አንዱና ዋነኛው ክፍተት ከመታገያ አጀንዳችን ጋር የተያያዘ ነው። የጋራ አጀንዳን በመፍጠር አጠቃላይ ሕዝቡን አስተባብሮ በመምራት ረገድ ክፍተት አለበት። ማንነት ላይ የሚያተኩር፣ ከትልቅ አሰባሳቢ ጉዳይ ይልቅ ለልዩነት ቦታን የሚሰጥና አለመግባባት የሰፈነበት ነው። በዚህ የተነሣ ለግጭትና ለፖለቲካ አለመረጋጋት ምክንያት ነው። በሁለት ጽንፍ ማንነቶችና በአክራሪ ብሔርተኝነት የተወጠረው ፖለቲካችን አቀራራቢ ጉዳዮችን ከፖለቲካ ሜዳው ያሸሸ ነው።

በመጠፋፋት ላይ የተመሠረተው የሁለቱ ጫፍ ፖለቲካ፣ በሐሳብ ገበያው እኩ ዝርያ የመወዳደር ፍላጎት አይታይበትም። ከዚህም በላይ ይህ በማንነት ላይ የተመሠረተው ከአለመረጋጋት ወጥቶ ብልጽግናን ለማረጋገጥ የሚያስችል እንዲሆን፣ አግላይ ከሆነ ፖለቲካ፣ ሌላ ተጨማሪ አማራጭን ይዞ በመምጣት ረገድ ክፍተት አለበት። ፖለቲካን የማንነት ፖለቲካ መውጣት ይገባዋል። አሰባሳቢ በሆኑ የጋራ አጀንዳዎችና ዕሴቶች ላይ መመሥረት አለበት። ፖለቲካችን የአማራጭ ሐሳቦች እጥረት አለበት ብለናል ። ይህም ብቻ ሳይሆን፣ ዋልታ ረገጥ ማንነት ላይ የተመሠረተም ነው።

ፖለቲካችን ሁሉን ሊያቀራርብ በሚችል አማራጭ ትርክት እጥረት በሁለቱ ዋልታ ረ ትርክቶች ሽኩቻ ይናጥ ነበረ። ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን ለማረጋገጥና የጋራ ግብን አንግበን በጋራ ጥረት ወደ ብልጽግና ለማምራት፣ በጽንፍና ጽንፍ ያሉ ትርክቶችን ሊያስታርቅ የሚችል ሦስተኛ አማራጭ ትርክት ያስፈልጋል።

ሐሳብ በፖለቲካ ውስጥ የፍላጎት መግለጫና እነዚህን ፍላጎቶች ማሳካት የሚቻልበትን መንገድ የሚተነትን ነው። መደመር ከአክራሪ ማንነቶች በመውጣት በሐሳብ ላይ የቆመ ፖለቲካን ይከተላል። መደመር የሰው ልጆችን ፍላጎቶች ማለትም የሀብት፣ የክብርና የነጻነት ፍላጎቶችን መሠረት ያደረገ ነው። እነዚህን ለማሟላት ደግሞ የራሱን አማራጭ ይዞ ቀርቧል። ብልጽግና የእነዚህ ሰብአዊ ፍላጎቶች መሟላት ውጤት ነው።

CS CamScanner

የብሔራዊነት ትርክት በነጻነት፣ በእኩልነትና በወንድማማችነት/ እኅትማማችነት ላይ የተመሠረተ ነው። አቀራራቢ በሆነ ታሪክ ላይ ይገነባል። የትናንትን ብቻ ሳይሆን የዛሬ አብሮነትንና የነገ የጋራ ዕጣ ፈንታችንን የሚያመለክት ነው።

ወደ ሐሳብ ገበያ በምናደርገው ጉዞ ለፖለቲካ ገበያ በር የሚከፍቱ ያለፉ ስብራቶቻችንን ለመጠገንና መሻገር ያስፈልገናል። ለሐሳብ ገበያ መሠረትን ለመጣልና ስብራቶችን ለመጠገን የሚያስችል ብሔራዊ መግባባትን የሚያመጣ ምክክር አስፈላጊ ነው።

ኅብረ ብሔራዊ አንድነትና የተረጋጋ ፖለቲካ ብልጽግናን ለማረጋገጥ መደላድል ነው። ልዩነትን በአግባቡ አለማቻቻልና መከፋፈል ብልጽግናን ለማምጣት ደንቃራ ነው። ምክንያቱም በትብብርና በውድድር መካከል ሚዛን ከመጠበቅ ይልቅ

ያልተገባ ሽኩቻን ይፈጥራል። ምክንያቱም ሕዝብን በአንድ ላይ አስተባብሮ ወደ አንድ የብልጽግና ዓላማ [ ለመምራት አዳጋች ይሆንበታል። የፖለቲካ ኃይሎች፣ የተለያዩ ማንነቶች እንዲሁም በአጠቃላይ ማኅበረሰቡ ለአንድ ከፍ ላለ ዓላማ ከመቆም ይልቅ፣ ለአነስተኛና ለአንጻራዊ ጥቅም ፉክክር ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ኃይል ይበትናል።

በተጨማሪም፣ ልዩነትን የሚፈጥረው ሽኩቻ ትብብርን ከማጥፋት ባሻገር ያልተረጋጋ ፖለቲካዊ ሁኔታና የሰላም መደፍረስ ይፈጥራል። በመሆኑም የመንግሥት ትኩረት፣ ዐቅምና ሀብት እንዲበታተን በማድረግና ፍጥነትን በመቀነስ፣ ብልጽግና ሊረጋገጥ የሚችልበት ጊዜ እንዲራዘም ያደርጋል።

ብሔራዊ መግባባት የሀገራችን ለውጥ ማነቆዎች የሆኑ ጉዳዮችን የምንፈታበት መንገድ ነው። የረጅም ጊዜ ችግሮቻችንንና ስብራቶቻችንን በመጠገን በአንድ ላይ ወደፊት የምንሻገርበት መንገድ ነው። በፖለቲካ ወደፊት ሳይሻገሩ በኢኮኖሚ ሙሉ ለሙሉ ወደፊት መሻገር የማይታሰብ ነው።

ሀገራዊ ምክክር፣ በአንድ በኩል አንድነትና ኅብረትን በማጠናከር፣ ልሂቃንና ሕዝብ ለአንድ ከፍ ላለ ዓላማ በአንድ ላይ እንዲቆሙ ያደርጋል። በዚህም ጥረቶች ሁሉ በአንድ አቅጣጫ እንዲፈሱ ያደርጋል። በሌላ በኩል ፖለቲካዊ መረጋጋትና ሰላምን በመፍጠር የመንግሥት ትኩረት፣ ሀብትና ጊዜ ሳይበታተን ብልጽግናን ለማረጋገጥ ብቻ እንዲውል ያደርጋል።

ማጠቃለያ

የመጀመሪያው የምንሄድበትን መንገድ ማጥራት ነው። ያ ምን ማለት እንደሆነ በቀደሙት ከላይ በቀረቡት ክፍሎችና ምዕራፎች የመደመር አስተሳሰብ ጸጋዎች ተቀንብበው ቀርበዋለ። የመደመር ሥራዎች በዝርዝር ተገልጿል። በዚህ መጽሐፍ የመደመርን አስተሳሰብ በመጠቀም ብልጽግናን ለማምጣት የመደመር መንግሥት አስፈላጊ መሆኑን አይተናል። መንገድ መጓዝ ብቻውን አያደርስም። በትክክለኛው መንገድና በፍጥነት መጓዝ ያለውን የመደመር መንግሥት ባሕርያትም ተገልጠዋል። ወደ አንድ ቦታ ለመድረስ በትክክለኛው አስፈላጊነት ለማሳየት ተሞክሯል። መዘግየት ብዙ ዓይነት ዋጋዎች አስከፍሎናልና።

አንድ የለውጥ ጉዞ የሚጓዝበት ፍጥነትና ለውጡ የሚበስልበት ጊዜ ወሳኝ ነው። ምክንያቱም ለውጥ የሚደረግበት አካባቢ በአንድ በኩል የተከፈቱ ዕድሎች አሉበት። እነዚህን በወቅቱ መጠቀም ይጠይቃል። በሌላ በኩል ለውጥን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ተገዳዳሪ ነገሮች አሉ። ለውጥ የሚካሄደው በእነዚህ ሁለት ነገሮች መካከል ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለውጥ

በራሱ ተለዋዋጭና ኢተገማች በሆነው ዓለም አቀፍ ከባቢ ተጽዕኖ ይደረግበታል:: በመሆኑም በዓለም አቀፍ ከባቢ ውስጥ የሚኖረው ቦታ በፍጥነቱ ልክ የሚወሰን ነው::

ብልጽግናን ለማረጋገጥ የምናደርገው ጉዞ ከጊዜ ጋር እሽቅድድም አለው። ከጊዜ ጋር እሽቅድድም እንድንገባ ያደረጉን አንደኛ የገጠመን ዕድል ሲሆን፣ ሁለተኛ ያሉብን ፈተናዎች ናቸው። በፍጥነት መጓዝ ካልቻልን ዕድሎቻችን ይመክናሉ፤ ችግሮቻችን ደግሞ ጠልፈው ይጥሉናል። ብልጽግናን ለማረጋገጥ የምናደርገው ጉዞ በአቅጣጫ ሲለካ፣ በትክክለኛው መንገድ ላይ ነን።

CamScanner

በውጤትም ሲለካ መልካም የሆኑ ጅምሮችን ማምጣት ችለናል። ነገር ግን የለውጥ ጉዞ በአቅጣጫው፣ በስፋቱና በጥልቀቱ ብቻ ሳይሆን በፍጥነቱም ሊመዘን ይገባል። የብልጽግና አስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን አንገብጋቢነትም ከፍተኛ ትኩረት ይሻል።

ብልጽግናን ማረጋገጥ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ጉዞና ጥረትን የሚጠይቅ ነው። ለውጡ የነበረውን ሁኔታ በመለወጥ ብልጽግናን ለማረጋገጥ በሚያስችል መደላድል ወይም ምኅዋር ውስጥ እንድንገባ አድርጓል። ይህ ጉዟችን ነገሮች ጠርተው ለመውጣትና የብልጽግና መሠረትን ለመጣል የሚደረግ ጥረት በመሆኑ፣ መለስ ቀለስ የበዛውና ወደኋላ ጎታች ነገሮችም የገጠሙት ነበር። ቀጣዩ ጉዟችን በለውጥ የተጣለውን መሠረት ተጠቅሞ፣ የጉዞውን ፍጥነትና ቀጣይነት የምንጨምርበት ነው።

ፍጥነት በቶሎ በመማርና በመሻሻል ነገሮችን ከግብ ማድረስ ነው። በለውጡ ያሳካናቸው ስኬቶች እንዲሁም የተፈጠሩ ስሕተቶች አሉ። ስኬቶቹን በፍጥነት ማስፋፋትና ማስቀጠል፣ ስሕተቶቹንም በፍጥነት ማረምና ማቃናት አለብን። ብልጽግናን ለማረጋገጥ ፍጥነትን መጨመር ያስፈልገናል።

የብልጽግና መነሻችን ወለል ዝቅተኛም አነስተኛም ነው። በመንገዱም ከኋላ ቀርተናል። ስለዚህም ውድድር በበዛበት ዓለም ከጊዜ ጋር ለመራመድና ሌሎች ከደረሱበት ደረጃ ለመድረስ መፍጠን አለብን። ከኋላ በመቅረታችን ከሚደርስብን ጫና ለመላቀቅ ከሌሎቹ ጋር እኩል በምንታይበት ደረጃ መድረስ አለብን። ከመነሻ እስከ መዳረሻችን ያለው ጉዞ ሩቅ ነው። ስለዚህ ፍጥነት መጨመር ያስፈልጋል።

መፍጠን ነገሮችን በቶሎ ለማጠናቀቅና ሌሎች ሥራዎችን ቶሎ ለመጀመር ጊዜ ይሰጣል። አንዳንድ ፕሮጀክቶችን በቶሎ ማጠናቀቃችን፣ ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን እንድንሠራ የጊዜና የዋጋ ነጻነት ሰጥቶናል። በመሆኑም የፍጥነትን ዋጋ ተገንዝበን ለመፍጠን የሚያስፈልገውን ሥርዓታዊ ጥንካሬ ማምጣት ይኖርብናል።

መንገዳችንን ስለለየን፣ በፍጥነት መጓዝ እንዳለብን ስለወሰንን፣ የሚያፈጥኑንን ሁኔታዎች ስላስቀመጥን፣ ጉልበቱም ስላለን፣ መንገዱ አልጋ በአልጋ አይሆንም። ምክንያቱም በቀናው መንገዳችን ውስጥ ደንቃራ አለ። ደንቃራው - የፖለቲካ ገበያ አስተሳሰብ ነው። የፖለቲካ ነጋዴዎች የድካማችን ፍሬን ከመቀራመታቸውም በላይ በፍጥነት እንዳንጓዝ በመንገዳችን ላይ የተቀመጡ የዕንቅፋት ድንጋዮች ናቸው። ስለሆነም ጉዟችን የፖለቲካ ነጋዴዎች የደነቀሩትን ዕንቅፋት እያስወገድን ሊሆን ግድ ነው። ሀገራችንንና ሕዝባችንን ለማበልጸግ በምናደርገው ሩጫ የሚያበረታቱን እንዳሉ ሁሉ፣ ሊያሰናክሉን የሚፈልጉም ብዙ ናቸው። ይሄንን ተገንዝበን በሐሳብ ገበያ ብልጽግናን ለማረጋገጥ እንዘጋጅ!!

CamScanner

CS CamScanner